የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዩት የሕግ መፅሔት

AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE JUSTICE PROFESSIONALS' TRAINING AND LEGAL RESEARCH INSTITUTE JOURNAL OF LAW

ቅጽ ፮	ISSN 2663-1210	ነሀሴ ፳፻፲፩ ዓ.ም
Vol. 6	ISSN 2663-1210	AUGUST 2019 G.C

በዚህ እትም፡-

- ✓ የምርምር ፅሁፎች
- ✓ የፍርድ ትችት

IN THIS ISSUE:

ARTICLES
CASE COMMENT

በአብክመ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዩት በአመት አንድ ጊዜ የሚታተም
ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ
Published Once Annually By ANRS Justice Professionals' Training and Legal Research Institute
Since, 2014 G.C

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዩት የሕግ መፅሔት

AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE JUSTICE PROFESSIONALS' TRAINING AND LEGAL RESEARCH INSTITUTE JOURNAL OF LAW

ቅጽ ፮	ISSN 2663-1210	ነሀሴ ፳፻፲፩ ዓ.ም
Vol. 6	ISSN 2663-1210	AUGUST 2019 G.C

በዚህ እትም፡-

- ✓ የምርምር ፅሁፎች
- ✓ የፍርድ ትችት

IN THIS ISSUE:

ARTICLES
CASE COMMENT

በአብክመ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዩት በአመት አንድ ጊዜ የሚታተም
ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ
Published Once Annually By ANRS Justice Professionals' Training and Legal Research Institute
Since, 2014 G.C

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዩት ከሕግ ጥናትና ምርምር ስራዎች አኳያ፡-

- ✓ **በስራ ላይ ያሉ ሕግጋትን ለማሻሻል የሚያስችሉ የሕግ ጥናትና ምርምሮችን ማከናወን፤**
- ✓ **የክልሉን የፍትህ ስርዓት የተሟላ ለማድረግ የሚያስችሉ አዳዲስ ሀሳቦችን ማመንጨት እንዲሁም**
- ✓ **የፍትህ ስርዓቱን ዋና ዋና ችግሮች ከነመንስዔዎቻቸው በማጥናትና በምርምር የተደገፉ የመፍትሔ ሀሳቦችን ማቅረብን የሚመለከቱ ስልጣንና ተግባራት ተሰጥተውታል።**

<u>አድራሻዎቻችን፡-</u>

+251 582260319 (+251 582260122)

www.amharajusticetraining.gov.et

abuworkneh@gmail.com

ፖ.ሳ.ቁጥር 3514

ባህር ዳር-ኢትዮጵያ

በአብክመ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዩት በአመት አንድ ጊዜ የሚታተም ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ

Published Once Annually By ANRS Justice Professionals' Training and Legal Research Institute Since, 2014 G.C

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዩት የሕግ መፅሔት

AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE JUSTICE PROFESSIONALS' TRAINING AND LEGAL RESEARCH INSTITUTE JOURNAL OF LAW

ቅጽ ፮	ISSN 2663-1210	ነሀሴ ፳፻፲፩ ዓ.ም
Vol. 6	ISSN 2663-1210	AUGUST 2019 G.C

ዋና አዘጋጅ

አበበ ካሴ (LLB, LLM

የህግ ጥናትና ምርምር ዋና የስራ ሂደት መሪ)

የአርትዖት (ኢዲቶሪያል) ኮሚቴ አባላት

ሳባ አበረ (LLB, LLM የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር)

ተገኘ ዘርጋው (LLB, LLM በባህር ዳር ዩንቨርስቲ የህግ ት/ቤት ዲን)

ፀጋዬ ወርቅአየሁ (LLB, LLM በአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰ/ሰ/ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ)

ደሴ ስዩም (LLB, LLM በአብክመ ጠቅላይ ዐ/ህግ መ/ያ ቤት የህግ ምክር፣

ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር)

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዩት የሕግ መፅሔት

ይህ የሕግ መፅሔት የክልሉ ፍትህ ስርዓት ከፍተኛ ሙያዊ ብቃት፣ መልካም ሥነ-ምግባር፣ ህዝባዊ አመኔታና ለህገ መንግስታዊ ስርዓቱ መከበር በጽናት በሚቆሙ ሙያተኞች የተገነባ እንዲሆን ለማስቻል፣ አይነተኛ ችግሮቹን በመለየት ከምንጫቸው ለማድረቅ የሚረዱ ተግባራትን በማከናወን የፍትህ ሥርዓቱን ተደራሽነት፣ ቀልጣፋነትና ውጤታማነት ለማሻሻል እንዲሁም የክልሉ ነዋሪ ህዝብ ከሚጠቀምባቸው አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ውስጥ የተሻሉትንና ከህገ መንግስቱ ጋር የሚጣጣሙትን በጥናትና በምርምር በመለየት ሕግና ስርዓት ተቀርያላቸው በጥቅም ላይ እንዲውሉ ምቹ ሁኔታ መፍጠርን ዋና አላማ አድርጎ በተቋቋመው እና ከሕግ ጥናትና ምርምር ስራዎች አንጻር ደግሞ፡-

1. በስራ ላይ ያሉ ሕግጋትን ለማሻሻል የሚያስችሉ የሕግ ጥናትና ምርምሮችን ለማከናወን፣
2. የክልሉን የፍትህ ስርዓት የተሟላ ለማድረግ የሚያስችሉ አዳዲስ ሀሳቦችን ለማመንጨት እንዲሁም
3. የፍትህ ስርዓቱን ዋና ዋና ችግሮች ከነመንስዔዎቻቸው በማጥናትና በምርምር የተደገፉ የመፍትሔ ሀሳቦችን ለማቅረብ ከፍተኛ ሀላፊነት በተሰጠው የአብክመ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የሕግ ምርምር ኢንስቲትዩት አማካኝነት የሚዘጋጅ ነው።

በመሆኑም ውድ (የሕግ ባለሙያዎች) አንባቢያን፡-

- ✓ በዚህም ሆነ ከዚህ ቀደም በታተሙት የኢንስቲትዩቱ የሕግ መፅሔቶች ላይ የሚኖራችሁን ማንኛውንም አይነት ገንቢ አስተያየት ብታደርሱን እንዲሁም
- ✓ **በተለይም ከላይ የተገለጸውን የኢንስቲትዩቱን አላማ እና የሕግ ጥናትና ምርምር ስራዎች የትኩረት አቅጣጫዎችን መሰረት አድርገው በተጨባጭ ለክልሉ ብሎም ለአገሪቱ የፍትህ ስርዓት መዳበር የበኩላቸውን ድርሻ የሚያበረክቱ የሕግ ምርምር ስራዎችን፣ አጫጭር ፅሁፎችን እንዲሁም በተመረጡ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ላይ የተዘጋጁ ትችቶችን በመላክ በመጽሔታችን ላይ እንዲታተሙ ብታደርጉ በደስታ የምንቀበል መሆኑን ከልብ እየጋበዝን በዚህ የጥናትና ምርምር መጽሔት ለተካተቱት ስራዎች መሳካት የተለያዩ መረጃዎችን (ግብዓቶችን) በመስጠት የተባበራችሁትን አካላት እና ግለሰቦች በሙሉ በእጅጉ በማመስገን መልካም ንባብ እንዲሆንላችሁ እንመኛለን።**

<u>አድራሻዎቻችን፡-</u>

+251 582260319 (+251 582260122)

www.amharajusticetraining.gov.et

abuworkneh@gmail.com

<u>ፖ.ሳ.ቁጥር 3514</u>

<u>ባህር ዳር-ኢትዮጵያ</u>

ማውጫ **ገጽ**

1. በምርመራ ወቅት ለፖ/ሊስ የተሰጠ የእምት ቃል በማስረጃነት ስለሚወሰድበት አግባብ ሰለሞን ተገኘወርቅ 1
2. በአማራ ክልል የገጠር መሬት ይዞታና የመጠቀም መብት ላይ የሚነሱ ክርክሮችን የሚወስኑ አካላት ሁሉን አቀፍ መሆናቸው እና ተቃርኗቸው ሰሎሞን ጐራው አዳነ 25
3. የሕግ አስከባሪ አካላት ኃይል አጠቃቀም ስልጣን እና የተጠያቂነት ስርዓት፡- ሕጉና አተገባበሩ በአማራ ክልል ታፈሰች ወልዴ 78
4. ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክርክር ሂደት በዓለም አቀፍ እና በኢትዮጵያ ህግ አራጌ ዘለቀ 103
5. የቋሚ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣንና አተገባበር ዳሰሳ በምዕራብ አማራ ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አበበ ካሴ 132
6. ትርጓሜያዊ የማግለል ጽንሰ-ሃሳብ በኢትዮጵያ የአሠሪ እና ሠራተኛ ሕግ ወርቁ ካሳው ጸጋዬ 178
7. ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ስርዓት፡- (Standard of proof under Ethiopian criminal justice system) የአማራ ክልል ተግባራዊ አፈጻጸም ይማም ሰይድ ሀሰን 196
8. ሀሠተኛ ምስክርነት በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ይበልጣል ይመር 225
9. የፍትሐብሄር እና የወንጀል ክርክር የነገር ጭብጥ አመሰራረትና የማስረጃ አግባብነት ግንኙነት፤ የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች ተሞክሮ ዮሐንስ ቢሻው 258
10. የመንግስት የግንባታ ውሎች እና አጠቃላይ የዉል ሁኔታዎች ከግንባታ አፈጻጸም ጋር ያላቸዉ ግንኙነት ምልከታ ጋሻዬ ቢያድግ 281

በምርመራ ወቅት ለፖሊስ የተሰጠ የእምት ቃል በማስረጃነት ስለሚወሰድበት አግባብ

በሰለሞን ተገኘወርቅ*

አጽርኦተ-ይዘት

*በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ስርዓት ውስጥ የተጠርጣሪ የእምነት ቃል እንደ ሌሎች ማስረጃዎች አግባብነትና ተቀባይነት ያለው ማስረጃ ነው። በእርግጥ ማስረጃው ተቀባይነት የሚኖረው ተጠርጣሪው በራሱ ፍላጎት ያለምንም ተጽዕኖ የሰጠው የእምነት ቃል ሲሆን ነው። በተጨማሪም የእምነት ቃሉ የተገኘው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉና በህገ መንግስቱ ለተጠርጣሪ የተደረጉ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች ተፈጻሚ ሆነው የሰጠው ቃል ሲሆን ነው። እነዚህ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች ዓላማ ተደርገው የተቀመጡበት ዋናው ምክንያት ተጠርጣሪው አላስፈላጊ ጫና ውስጥ እንዳይገባ ለመከላከል ያግዛሉ በሚል እምነት ነው። ይሁን እንጂ በተግባር መርማሪ ፖሊሶች ቃል በሚቀበሉበት ወቅት እነዚህን ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች የማያከብሩበት ጊዜ ያጋጥማል። ታዲያ ተጠርጣሪው በፍርድ ቤት በሚከራከርበት ወቅት በህጉ የተቀመጡት ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች (መብቶቹ) ሳይነገሩኝ የሰጠሁት የእምነት ቃል ስለሆነ በማስረጃ ሊያገለግለኝ አይገባም የሚል ክርክር ቢያቀርብ ፍርድ ቤቶች ምን መወሰን አለባቸው የሚለው አከራካሪ ሲሆን ይታያል። ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉም ሆነ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ.ፌ.ዲ.ሪ) ህገ መንግስት የተጠርጣሪው መብቶች ሳይገለጹ የሰጠው የእምነት ቃል ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መልስ ሰላልሰጡ ነው። ህጉ በፈጠረው ክፍተት ምክንያት በባለሙያዎች ዘንድ ሁለት ዓይነት አረዳድና አሰራር እንዲኖር ምክንያት ሆኗል። አንዳንድ ባለሙያዎች እንደሚሉት ተጠርጣሪው ቃሉን ከመስጠቱ **በፊት ዝም የማለት ያለመናገር መብት ያለው መሆኑና የተናገረው ነገር እንደ ማስረጃ በፍርድ ቤት እንደሚወሰድ ሳይነገረው የሰጠው የእምነት ቃል በፍርድ ቤት ውድቅ ሊደረግ ይገባል** በማለት ይከራከራሉ። በሌላ በኩል ይህንን ሀሳብ የሚቃወሙ ባለሙያዎች እንደሚሉት ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች ለተጠርጣሪው መገለጽ እንዳለባቸው በግልጽ ተቀምጧል። ነገር ግን ይህ ሳይፈጸም የተሰጠ የእምነት ቃል ቢኖር የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ ውጤቱ ምን መሆን እንዳለበት ያስቀመጠው ነገር **ስለሌለ ማስረጃውን ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል የህግ መሰረት ስለሌለ ማስረጃውን መቀበል ይገባል በሚል በዚሁ አግባብ ሲሰሩ ይታያል**። እንደጸሀፊው እምነት ከሆነ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች የተቀመጡበትና በወንጀል ፍትህ ስርዓት ውስጥ ያላቸው ታሪካዊ እድገትም ሲታይ ተጠርጣሪው የሚሰጠው የእምነት ቃል ያለምንም ተጽዕኖ በነጻ ፈቃዱ እንዲሰጥ ለማስቻል በመሆኑ ይህ መብት ሳይከበር የተሰጠ የእምነት ቃል በፍርድ ቤት ተቀባይት ሊኖረው አይገባም።*

---

* (LLB, LLM በአብክመ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መስሪያ ቤት የአዲስ አበባ ቋሚ ምድብ ዐቃቤ ህግ (ከዚህ በፊት በኢንስቲትዩቱ አሰልጣኝና ተመራማሪ የነበረ))።

1. ስለእምነት ቃል አንዳንድ ነጥቦች

የአንድ ሀገር የወንጀል ፍትህ ስርዓት ዋና ግብ ተደርጎ የሚወሰደው በሀገርና በህበረተሰብ ላይ ወንጀል እንዳይፈጸም አስቀድሞ መከላከል ሲሆን መከላከሉን አልፎ ወንጀል በተፈጸመ ጊዜ ጠንካራ የምርመራና የማስረጃ አሰባሰብ ስርዓት በመዘርጋት ወንጀለኞችን ጥፋተኛ ለማስባል የሚያስችል ማስረጃ በማቅረብ አጥፊዎች ተገቢ የሆነ ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ ነው።[1] የወንጀል ጉዳይን ለማስረዳት የተለያዩ የማስረጃ ዓይነቶች እንዳሉ ከተለያዩ የማስረጃ ህግ አስተምህሮቶች ማየት ይቻላል።[2] ከእነዚህም ውስጥ የሰው ምስክርነት፣ የሰነድ ማስረጃ፣ የኤግዚቪት ማስረጃ፣ የቴክኒክ ማስረጃ፣ የተጠርጣሪው /የተከሳሽ/ የእምነት ቃልና ሌሎችም ሊጠቀሱ ይችላሉ።[3] የተጠርጣሪ የእምነት ቃል በሀገራችንና በሌሎች ሀገራት የማስረጃ ህግ ወይም የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ ውስጥ አግባብነትና ተቀባይነት ካላቸው ማስረጃዎች አንዱ በመሆኑ በወንጀል ምርመራ ወቅት የተጠርጣሪን ቃል የመቀበል ስራ ቀዳሚ ተግባር ነው።[4] በወንጀል ምርመራ ሂደት የተጠርጣሪን የእምነት ክህደት ቃል መቀበል የሚያስፈልግበት አንዱ ምክንያት ተጠርጣሪው የተጠረጠረበትን ወንጀል ስለመፈጸሙ ያለምንም ተጽዕኖ በራሱ ፍላጎት ወንጀል በመፈጸሙ ምክንያት በመጸጸት በአንደበቱ ስለወንጀል አፈጻጸሙ በዝርዝር የእምነት ቃሉን ሊሰጥ ስለሚችልና የሚሰጠውም የእምነት ቃል ወንጀሉን ለማስረዳት ከፍተኛ ጠቀሜታ ስላለው ነው።[5] በሌላ በኩል ተጠርጣሪው በሚሰጠው የእምነት ቃል መነሻነት ሌሎች ግዙፍና ግዙፍነት የሌላቸውን ማስረጃዎች ለማሰባሰብ መርማሪ ፖሊሶች በእጅጉ ስለሚጠቀሙበት ነው። ለምሳሌ ተጠርጣሪው በእምነት ቃሉ ወንጀሉን ለመፈጸም ያነሳሳው ምክንያት ምን እንደነበረ?፣ ወንጀሉን መቼ እንደፈጸመው?፣ ወንጀሉን እንዴት እንደፈጸመው?፣ ወንጀሉ የት እንደተፈጸመ?፣ ወንጀሉን በምን ዓይነት መሳሪያ እንደፈጸመው?፣ ወንጀሉን ሲፈጽም ግብረ አበሮች ከነበሩት ግብረ አበሮቹ እነማን እንደሆኑና አድራሻቸው የት እንደሆነ ሊጠቁም ይችላል።[6] ከእዚህም ሌላ ወንጀሉን ከፈጸመ በኋላ ወንጀል የተፈጸመው በንብረት ወይም በእንስሳ ላይ ከሆነ ንብረቱ /እንስሳው/ የት እንደሚገኝ፣ ወንጀል የፈጸመበት መሳሪያ የት

---

[1] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ (1996 ዓ.ም) የወንጀል ህጉ ዓላማ በሚለው ስር የተቀመጠው እና የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ፣ (2003 ዓ.ም)

[2] John Henry, Evidence in trials at common law, 3rd ed. V. 3, Boston Little brown and Company, 1940, ገጽ 248-250

[3] ዝኒ ከማሁ

[4] በኢትዮጵያ፣ በእንግሊዝ፣ በአሜሪካ፣ በህንድና በሌሎች አገሮች የማስረጃና የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ ውስጥ ተጠርጣሪ ለመርማሪ ፖሊስ የሚሰጠው የእምነት ቃል እንደ ማስረጃ የሚወሰድ መሆኑን በየሀገራቱ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህጎናችና የማስረጃ ህጎች ተካቶ ይገኛል።

[5] 'Confessions', American Jurisprudence, 2nd ed., V. 29, (1967) ገጽ 276

[6] ዝኒ ከማሁ

እንደሚገኝ፣ የወንጀሉ ሰለባ የሆነው የተፈጥሮ ሰው ከሆነ ተጎጂው ወይም የተጎጂው አስከሬን የት እንደሚገኝ፣ ተጎጂው በወቅቱ ለብሶት የነበረው ልብስ ወይም ሌላ በእጁ የነበረ ማናቸውም ነገር የት እንደሚገኝ በዝርዝር የሚገልጽበት አጋጣሚ ስለሚኖር የተጠርጣሪውን ቃል በመጠቀም ለተጨማሪ ምርመራ በር ከፋች ስለሚሆን ነው።[7] የተጠርጣሪን የእምነት ቃል የመቀበል ዓላማ እነዚህና ሌሎች ሊጠቀሱ የሚችሉ ሲሆን አንድ ተጠርጣሪ የሚሰጠው የእምነት ቃል እንደ ማስረጃ ተቀባይነት እንዲያገኝና እንደ ማስረጃ ተወስዶ ከማስረጃ ምዘና ውስጥ እንዲገባ ማስረጃው የተገኘው ከማናቸውም ዓይነት ተጽዕኖ ነጻ በሆነ መንገድ የተሰጠና ተጠርጣሪው ቃሉን የሰጠው በሙሉ ፍላጎቱና ነጻ ፈቃዱ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል።[8] የቃል መቀበል ሂደት በባህሪው መርማሪ ፖሊስ ተጠርጣሪው ስለተጠረጠረበት ወንጀል የእምነት ቃሉን እንዲሰጥ የሚፈልግበት ተግባር ነው። በዚህም ምክንያት መርማሪ ፖሊስ በተጠርጣሪው ሰብዓዊ መብት ላይ ጥሰት ሊፈጽም የሚችልበት እድል ይኖራል። ይህ እንዳይፈጸም ለማድረግ የሚያግዙ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች (procedural safeguards /protection methods) በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት እና በሌሎችም ሰነዶች ላይ ተገልጸ ይገኛል።[9] እነዚህ ጥበቃዎች ምንድን ናቸው ብለን ብንጠይቅ ተጠርጣሪው ቃሉን በሚሰጥበት ወቅት ዝም የማለት ያለመናገር መብት ያለው መሆኑ፣ የሚሰጠው ማናቸውም ቃል በፍርድ ቤት እንደ ማስረጃ ሆኖ የሚቀርብበት መሆኑ ሊነገረው የሚገባ መሆኑ፣ ጠበቃ የማማከር መብት ያለው መሆኑ፣ የሰጠው ቃል ሁሉ መመዝገብ የሚገባው ስለመሆኑና ቃሉን ከሰጠ በኋላ በሰጠው ቃል ላይ ከመፈረሙ በፊት የሰጠውን ቃል እንዲያነብ እንዲደረግ ወይም እንዲነበብለት መደረግ ያለበት መሆኑን የሚገልጹ መብቶች ተደንግገው ይገኛሉ።[10]

ከላይ እንደተመለከትነው ተጠርጣሪው የሚሰጠው የእምነት ቃል በወንጀል ፍትህ ስርዓቱ ውስጥ ትልቅ ጠቀሜታ የሚኖረው ተጠርጣሪው ቃሉን የሰጠው **በራሱ ነጻ ፍላጎትና በሙሉ ፈቃደኝነት መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ** ነው።[11] ምክንያቱም የእምነት ቃሉ የተገኘው በነጻ

---

[7] ዝኒ ከማሁ

[8] Richard A. እና Leo Richard J. Consequences of False Confessions: Deprivations of Liberty and Miscarriages of Justice in the Age of Psychological Interrogation, **Journal of Criminal Law and Criminology** Volume 88, በ www.campbellcollaboration.org ላይ ይገኛል፣ ገጽ 431-432፣ ሚያዚያ 26/2011 ዓ.ም የተወሰደ እንዲሁም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት (1987 ዓ.ም) አንቀጽ 19(5) ስር እንደተገለጸው በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት እንደሌለው ተደንግጓል።

[9] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት (1987 ዓ.ም) አንቀጽ 19(2)፣ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ (1967) አንቀጽ 27(2)

[10] ዝኒ ከማሁ

[11] Saul M. Kassin Æ Steven A. Drizin Æ Thomas Grisso, Police-Induced confessions, risk factors and recommendations, በ www.campbellcollaboration.org, የሚገኝ ገጽ 3፣ ሚያዚያ 25/2011 ዓ.ም ተወሰደ

ፍላጎትና ህጉ ያስቀመጠውን ስርዓት ተከትሎ ባልሆነ ጊዜ ማህበረሰቡ በፍትህ ስርዓቱ ላይ እምነት ያጣል፤ የተጠርጣሪውን ሰብዓዊና መሰረታዊ መብቶች ይጥሳል።[12] ለምሳሌ ያክል የተወሰኑ ጉዳዮችን ወስደን ብንመለከት በፖሊስ የሚወሰዱ የተጠርጣሪ የእምነት ቃሎች ከተጠርጣሪው ነጻ ፍላጎት ውጭ በሆነ መንገድ የተሰጠ የእምነት ቃል ሀሰት ሊሆን ስለሚችል በሀሰተኛ ማስረጃ መሰረት ንጹሀን ያለጥፋታቸው አላግባብ ሊፈረድባቸው ይችላል፤ ትክክለኛ ወንጀል ፈጻሚዎችም ከፍትህ ተጠያቂነት ሊያመልጡ ይችላሉ፤ በዚህም ምክንያት ማህበረሰቡ በወንጀል ፍትህ ስርዓት አስተዳደሩ ላይ ያለው እምነት ሊሸረሸር ይችላል።[13] በሌላ በኩል አንድ ተጠርጣሪ ባልፈጸመው ወንጀል የእምነት ቃሉን በተለያዬ አላማ (motive) ሊሰጥ የሚችልበት እድል ይኖራል።[14] ይሄውም አንድም የእምነት ቃሉ የተሰጠው በመርማሪው በኩል በሚደረጉ የማስገደድ፣ የማባበል ወይም ከሌሎች የአካልና የስነ-ልቦና ጫናዎች ለመላቀቅ ሲባል ሊያምን ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ ተጠርጣሪው ከራሱ ወይም ከቅርብ ቤተሰቡ ከሚመነጭ ግፊት ቤተሰቡ ወይም የሚወደው ሰው እንዳይታሰርበት ለማድረግ በማሰብ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ደም መላሽ ወይም ጀብደኛ ሆኖ ለመታየት በመፈለግ፣ በገንዘብ በመገዛት እና በሌሎችም ምክንያቶች ሌላ ሰው የፈጸመውን ወንጀል ተጠርጣሪው እራሱ እንደፈጸመው አድርጎ የእምነት ቃሉን ሊሰጥ ይችላል።[15] ይህ ሁኔታ የሚያሳየው የእምነት ቃል ለወንጀል ፍትህ ስርዓት አስተዳደሩ ጠቀሜታ እንዳለው ሁሉ በጥንቃቄ የማይመራ ከሆነ መርማሪ ፖሊሶች ተጠርጣሪው አምኗል በሚል ምክንያት ሌሎች ተጨማሪ ማስረጃዎችን እንዳያሰባስቡ በማዘናጋት ትክክለኛ ወንጀል የፈጸሙ ወንጀለኞች በቁጥጥር ስር ባለመዋላቸው ማስረጃ ሊያጠፉና ከፍትህ ስርዓቱ ሊያመልጡ የሚችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል።[16] ስለሆነም መርማሪ ፖሊሶች በጥንቃቄ ሊሰሩት የሚገባው ጉዳይ የእምነት ቃል ከተጠርጣሪ በሚቀበሉበት ወቅት አንድም ተጠርጣሪው ቃሉን በራሱ ነጻ ፍላጎትና ፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ እንዲሰጥ ማድረግ ሁለትም ማስረጃ በሚሰበስቡበት ወቅት ተጠርጣሪው የተጠረጠረበትን ወንጀል ስለመፈጸሙ በዝርዝር ማመኑን እንደ ስኬት በመቁጠር ቀጣይ ማስረጃዎችን ከማሰባሰብ መታቀብ ሳይሆን ከእምነት ቃሉ በመነሳት ሌሎች አሉ የሚባሉ ግዙፍነት ያላቸውንና ግዙፍነት የሌላቸውን ማስረጃዎች ሁሉ ማሰባሰብ ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም መርማሪዎች ተጠርጣሪው ወንጀሉን ስለመፈጸሙ በዝርዝር አምኗል በማለት ሌሎች ማስረጃዎችን ከመሰብሰብ የሚቆጠቡ ከሆነ በክስ መመስረትና በክርክር ወቅት ዐቃቤ ህግ ወይም ፍርድ ቤት ማስረጃው ተዓማኒና አሳማኝ አይደለም

[12] ዝኒ ከማሁ
[13] ዝኒ ከማሁ
[14] ዝኒ ከማሁ
[15] ዝኒ ከማሁ
[16] ዝኒ ከማሁ

በማለት ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ሊያዙ ይችላሉ ወይም ተጠርጣሪው የእምነት ቃሉን የሰጠው በውስጣዊና ውጫዊ ጫና ምክንያት በራሱ ነጻ ፍላጎት ስላልሆነ ማስረጃው ተቀባይነት የለውም በማለት ክርክር በማንሳት ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል።[17]

2. መርማሪ ፖሊስ የተጠርጣሪ ቃል ሲቀበል ሊከተለው የሚገባ የቃል አቀባበል ስርዓት

በመርማሪ ፖሊስ የሚደረግ የተጠርጣሪ ቃል መቀበል ስራ ለወንጀል ፍትህ አስተዳደር ስራው ወሳኝ ምዕራፍ ከሚባሉት ውስጥ አንዱ እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል። በእርግጥ የእምነት ቃል በወንጀል ፍትህ ስርዓት አስተዳደሩ ውስጥ አስተዋጽዖ የሚኖረው የተገኘው የእምነት ቃል ተጠርጣሪው በራሱ ነጻ ፍላጎትና ከማናቸውም ተጽዕኖ ነጻ በሆነ መንገድ የሰጠው የእምነት ቃል ሲሆን ነው። ከዚህም በላይ የእምነት ቃሉ የተገኘው ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ተጠርጣሪው ቃሉን ከመስጠቱ በፊትና በሚሰጥበት ወቅት የተደረጉለት ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች (procedural safeguards) በአግባቡ ተፈጻሚ ሆነው የተገኘ የእምነት ቃል ሲሆን ነው። በቃል መቀበል ወቅት የተጠርጣሪው ዝም የማለት ያለመናገር መብት እንደ አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ህንድና በሌሎች ሀገሮች ስነ-ስርዓት ህግ ውስጥም ተካቶ የሚገኝ ነው።[18]

የተጠርጣሪ የቃል አቀባበል ስርዓትን አሁን ካለንበት ዘመን ወደኋላ መለስ ብለን ስንመለከት በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ሀገራት የተለያዩ ሂደቶችንና ስርዓቶችን እንዳለፈ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ለምሳሌ ቀደም ባለው ጊዜ (በ1920ዎቹ እና 1930ዎቹ) አንድ ተጠርጣሪ የተጠረጠረበትን ወንጀል መፈጸሙን እንዲያምን ለማድረግ መርማሪ ፖሊሶች በስፋት የሚጠቀሙበት የቃል አቀባበል ስርዓት በማስገደድ ወይም ሀይል በመጠቀም (third degree method) በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ የአካል እና የስነ-ልቦና ጉዳት በማድረስ የእምነት ቃል ለማግኘት የሚደረግ ጥረት እንደነበር የሚያመለክቱ ጽሁፎች አሉ።[19] ይህ ጊዜ በወንጀል ፍትህ ስርዓቱ ውስጥ አስቸጋሪ ዘመን የነበረበት ወቅት እንደነበር መገመት ይቻላል። ምክንያቱም በመደብደብ፣ በማሰቃየት፣ በማስገደድ፣ በማባበል /በመደለል/ በአጠቃላይ አላስፈላጊ የሆነ የአካልና የስነ-ልቦና ጉዳት በማድረስ የሚገኙ የእምነት ቃሎች በአንድ በኩል የእምነት ቃሉ በነጻ ፍላጎት ላይ ያልተመሰረተ በመሆኑ የእምነት ቃልን መሰረት በማድረግ

---

[17] የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ (1967 ዓ.ም) አንቀጽ 134 እና የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት (1987 ዓ.ም) አንቀጽ 19(5) በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ውድቅ እንደሚሆን ያስቀምጣል።

[18] Zelman Cowen and P.B Carter, Essays on the evidence, (Oxford University, the claderon press, 1956), ገጽ 62

[19] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11

የጥፋተኝነት ውሳኔ ሲሰጥ ንጹሀንንም ያለአግባብ ጥፋተኛ የሚያደርግበት አሰራር የሚኖርበት አጋጣሚ ሰፊ ነው። በሌላ በኩል መንግስት ወንጀልን የማስረዳት ሀላፊነቱንና ግዴታውን እንዳልተወጣ የሚያሳይ ሲሆን በማስገደድ የተገኘ የእምነት ቃል በፍርድ ቤት ተቀባይነት የሚኖረው ከሆነ ለመርማሪ ፖሊሶች ተግባሩ ማበረታቻ (bad incentive) በመሆን በቀጣይም በተመሳሳይ ስራ እንዲሳተፉ ከማድረጉም በላይ አንድ ሰው ራሱን ያለመወንጀል ህገ መንግስታዊ መብት ("the right not to incriminat one self") የሚጥስ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።[20] ይህ ተግባር በተለይም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በብዙ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችና የህግ ምሁራን እንዲሁም በፍርድ ቤቶች ጭምር ትችት እየገጠመው እንደመጣ በዘርፉ የተጻፉ ጽሁፎች ያስገነዝባሉ።[21] ይህንንም ተከትሎ በወንጀል ፍትህ ስርዓታቸው ከፍተኛ እድገት ያሳዩ እንደ አሜሪካ ባሉ ሀገራት ውስጥ የእምነት ቃል በተጠርጣሪው ነጻ ፍላጎት የተገኘ ለመሆኑ ማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት እየተዘረጋ መምጣት ጀመረ።[22] ለምሳሌ የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በ1950ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ ያስቀመጠው አሰራር ፍርድ ቤቶች የእምነት ቃልን እንደ ማስረጃ ከመውሰዳቸው በፊት ማስረጃው የተገኘው በፈቃደኝነት መሆን አለመሆኑን (voluntariness test) በሚባል አሰራር ፍርድ ቤቶች እንዲያጣሩ የሚያስችል ስርዓት እንዲዘረጋ እንዳደረገ በዚሁ ዙሪያ የተጻፉ ጽሁፎች ያመለክታሉ።[23] ይህ ዘዴም በተጠርጣሪ የተሰጠ የእምነት ቃል ተጠርጣሪው ሳይገደድ በራሱ ነጻ ፍላጎትና በሙሉ ፈቃዱ የሰጠው ነው አይደለም የሚለውን ለማጣራት ጥረት ይደረግ ስለነበር በተወሰነ መልኩም ቢሆን በተጠርጣሪዎች ላይ የሚደረገውን ጫና እንዲቀንስ ምክንያት እንደሆነ ይገለጻል።[24] ይህ አሰራር እየዳበረ መምጣቱ ተጠርጣሪውን ካላስፈላጊ መገደድ ለመጠበቅ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የራሱ አስተዋጽዖ ነበረው ለማለት ይቻላል። የዚህ ስርዓት መዘርጋት ተጠርጣሪው ላይ የሚደርሰውን ስቃይና ጫና ከመቀነሱም በላይ በነጻ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ያልተሰጠ የእምነት ቃል ተዓማኒ ያልሆነ ነው በሚል ከማስረጃ ውድቅ መደረጉ ለተጠርጣው ከፍተኛ ድል ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል። ምክንያቱም በብዙ ሀገራት ሲሰራበት የነበረው የቃል አቀባበል ሂደት ዋና እና ማዕከላዊ ችግሩ በቃል መቀበል ወቅት መርማሪ ፖሊሶች የሚፈጽሙትን የማስገደድ ወይም የማባበል ተግባር እንዴት ሊቆም ይችላል? ተጠርጣሪው ጥያቄ ከመጠየቁ በፊት ምን ምን ስርዓት ሊሟላ ይገባል? ተጠርጣሪውን

---

[20] ዝኒ ከማሁ

[21] Jason K. Jensen, The Dilemma and Debate Over Confession and Evidence Strategies, ከ www.campbellcollaboration.org, ገጽ 13፣ ሚያዚያ 25/2011 ዓ.ም ተወሰደ

[22] ዝኒ ከማሁ

[23] ዝኒ ከማሁ

[24] ዝኒ ከማሁ

በመጠየቅ ሂደት ውስጥ ጥያቄዎቹ እንዴት መመራት አለባቸው? ቃሉ እንዴት ተቀባይነት ይኑረው? በሂደትም የእምነት ቃሉ ተቀባይነት እንዲኖረው የእምነት ቃሉ በፈቃደኝነት፣ በፍትሀዊነት፣ በነጻ ፍላጎት እና በህግ አግባብ የተሰጠ ከሆነ ነው የሚሉት ነጥቦች እየዳበሩ እንዲመጡና የተጠርጣሪ ቃል አቀባበል ሂደት አሁን ለደረሰበት ደረጃ መድረስ የራሱን አሻራ ጥሎ ያለፈ በመሆኑ ነው።[25] አንድ ተጠርጣሪ የእምነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ቃሉን የሰጠው በነጻነትና በራሱ ፍላጎት ላይ በመመስረት እንዲሆን ለማስቻል የሚረዱ ስርዓቶች (The due process test) ዘዴዎች እንዲዘረጉ ተደርጓል።[26] ይህ ስርዓትም የእምነት ቃል አሰጣጥን በተመለከተ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ እንዲመጣና አዳዲስ ስርዓቶችና በይበልጥ የተጠርጣሪውን መብት ሊያስጠብቁ የሚችሉ ስርዓቶች እንዲመጡ በማድረግ የራሱ የሆነ አስተዋጽዖ አበርክቷል።

የተጠርጣሪ ቃል አቀባበል ስርዓት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ በመምጣቱ አሁን ስራ ላይ ያለው የቃል አቀባበል ስርዓት ምን ምን ሁኔታዎችን ማሟላት እንደሚገባው የሚያሳዩ መሰረታዊ መርሆዎች በብዙ ሀገራት የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግጋትና የወንጀል ፍትህ ፖሊሲዎች ውስጥ ተካተው ይገኛሉ።[27] አሁን በብዙ አገራት ላይ ለተዘረጋው የተጠርጣሪ የቃል አቀባበል ስርዓት እንደ ትልቅ መነሻ ተደርጎ የሚወሰደውና በብዙ ሀገራት የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግጋት ውስጥ ተካቶ የሚገኘው በ1960 ዎቹ በአሜሪካን ሀገር ሚራንዳ በተባለ ግለሰብና በአሪዞና ግዛት መካከል የነበረውን የወንጀል ክርክር መነሻ በማድረግ የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያስተላለፈው ውሳኔ ነው። ይህ ውሳኔ በተለይ አንድ ተጠርጣሪ የእምነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት፡-

> *"ሀ. ያለመገደድ መብት ያለው ስለመሆኑ፤*
>
> *ለ. ዝም የማለት ያለመናገር መብት ያለው ስለመሆኑ፤*
>
> *ሐ. የሚሰጠው ማናቸውም ቃል በፍርድ ቤት እንደማስረጃ እንደሚቀርብበት ሊነገረው እንደሚገባ እና*
>
> *መ. ጠበቃ የማማከር መብት ያለው መሆኑ ሊነገረው እንደሚገባ በግልጽ አስቀምጧል::[28]"*

---

[25] John Sankey, Basic rules of law enforcement on Miranda warning and anti-torture warning www.campbellcollaboration.org, ገጽ 23፣ ሚያዚያ 24/2011 ዓ.ም ተወሰደ

[26] ዝኒ ከማሁ

[27] የኢትዮጵያ፣ የአንግሊዝ፣ የአሜሪካ፣ የህንድና የሌሎች አገራት የወንጀል ስነ-ስርዓት ህጎች ውስጥ ተካቶ ይገኛል።

[28] ዝኒ ከማሁ

በዚህ ውሳኔ መሰረት አንድ ተጠርጣሪ ለመርማሪ ፖሊስ የእምነት ክህደት ቃሉን እንዲሰጥ ከመደረጉ በፊት በፖሊስ ሊገለጽለት የሚገቡ መብቶች ተብለው የተቀመጡ ሲሆን እነዚህ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎችም ተጠርጣሪው ለፖሊስ ቃሉን በሚሰጥበት ወቅት አላግባብ በተጽዕኖ ስር እንዳይወድቅ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች (procedural safeguards) ናቸው። እነዚህ መርሆዎችም በተለምዶ የሚራንዳ ማስጠንቀቂያዎች (Miranda warnings) ተብለው ይታወቃሉ።[29] ይህ ውሳኔ ከተወሰነ በኋላ ለፖሊስ የሚሰጥ የእምነት ቃል ምን መስፈርትን መከተል አለበት በሚለው ዙሪያ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደረገ እንደነበርና ከውሳኔው በኋላ ብዙ አገራት በወንጀል ስነ-ስርዓት ህጎቻቸው ውስጥ አካተውት አንደሚገኝ ይገለጻል።[30] እነዚህን ለተጠርጣሪው የተደረጉ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች (መብቶችን) መርማሪ ፖሊስ ለተጠርጣሪው መግለጹ ብቻ በቂ አይደለም ይልቁንም ተጠርጣሪው መብቶቹን በአግባቡ መረዳቱን ማስገንዘብ ይጠበቅበታል።[31] ስለሆነም ፍርድ ቤቶች አንድን የተጠርጣሪ የእምነት ቃል እንደ ማስረጃ ከመቀበላቸው በፊት የእምነት ቃሉ የተገኘው የሚራንዳ መርሆዎች (miranda warnings) ተሟልተውና የተጠርጣሪው መብት በፖሊስ የተነገረው መሆኑን ፖሊስ እንዲያረጋግጥ በማድረግ መሆን ይገባዋል ማለት ነው።[32] በተጨማሪም ፖሊስ ተጠርጣሪው የእምነት ቃሉን የሰጠው በህግ የተቀመጡትን መብቶቹን ለማለፍ በሙሉ ግንዛቤና እውቀት (knowingly and intelligently) እንደሆነ እንዲሁም በፈቃደኝነት (voluntarily) መሆኑን ለፍርድ ቤቱ ማረጋገጥ ይገባዋል።[33]

የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እነዚህን የሚራንዳ ማስጠንቀቂያዎች ሲወስን መነሻ ያደረገው በአሜሪካ ህገ መንግስት እንዲሁም ሰብዓዊ መብትን ለመደንገግ በተለያዩ የዓለም ዓቀፍ ሰነዶች ላይ የተቀመጡ የተጠርጣሪ መብቶችን የሚደነግጉ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ ነው።[34] ለዚህ ውሳኔ መነሻ ከሆኑ የተጠርጣሪ መብቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ማንኛውም ተጠርጣሪ እራሱን ያለመወንጀል መብት (privilege against self-incrimination) መብት ያለው መሆኑን የሚደነግገው የተጠርጣሪዎች ህገ መንግስታዊና በተለያዩ ዓለም ዓቀፍ ሰነዶች ላይ የተደነገገው መብት ነው።[35] ይህ መብት የሚያረጋግጠው ማንኛውም ተጠርጣሪ እራሱን ያለመወንጀል መብት ያለው መሆኑን ሲሆን በሌላ በኩል ወንጀልን የማስረዳት ሀላፊነት በመንግስት ጫንቃ ላይ ያረፈ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። ስለሆነም ይህ መብት

[29] ዝኒ ከማሁ ገጽ 30
[30] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 26
[31] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 24
[32] ዝኒ ከማሁ ገጽ 31
[33] ዝኒ ከማሁ ገጽ 35
[34] ዝኒ ከማሁ
[35] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 12

ተፈጻሚ መሆን የሚገባው በፖሊስ ከቅድመ ቃል መቀበል ጀምሮ እስከ ፍርድ ሂደቱ መጨረሻ ድረስ ነው በሚል እምነት ነው። አንድ ተጠርጣሪ ለጥያቄዎች መልስ ሲሰጥ ራሱን ሊያስወነጅል የሚችል ነገር ካለ ዝም በማለት ራሱን የሚያስወነጅለውን ጉዳይ ከመግለጽ ሊቆጠብ ይችላል። በእርግጥ ይህ ማንኛውም ሰው ራስን ያለመወንጀል መብት ያለው መብት የሚመነጨው እንደ ንጹህ ሆኖ ከመቆጠር መብት ነው።[36] ምክንያቱም ራስን ያለመወንጀል መብት የሚከበረው በዋናነት ማንኛውም ሰው ከፍርድ በፊት እንደ ንጹህ ሆኖ የመቆጠር መብት አለው ከሚለው በመነሳት ነው።[37] ይህ ማለት ራስን ያለመወንጀል መብት ሊረጋገጥ የሚችለው ዝም የማለት መብት ሲረጋገጥ ነው ከሚል አመክንዮት በመነሳት ነው። በዚህም መሰረት እራስን ያለመወንጀል መብት ሲረጋገጥ ማንኛውም ተጠርጣሪ /ተከሳሽ/ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ከመባሉ በፊት እንደ ንጹህ ሆኖ የመቆጠር መብትን ያረጋግጣል በሚል ይገለጻል።[38] በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ስርዓት ውስጥ በግልጽ ራስን ያለመወንጀል መብት የተደነገገው ለምስክሮች ሲሆን እንደ ንጹህ ሆኖ የመቆጠር መብት ግን ለተከሳሽ የተሰጠ መብት ነው። በእርግጥ አንዳንድ ባለሙያዎች እንደሚሉት በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት **ዝም የማለት መብት ለተከሳሹ** የሚያገለግል ሲሆን **ራስን ያለመወንጀል መብት ግን ለምስክሮችም** ያገለግላል በማለት ያስቀምጣሉ።[39] ሁለቱም የሚመነጩት ለተጠርጣሪና ለምስክሮች ከሚደረግ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃ መሆኑን መገንዘብ ይገባል። ሌላው የሚራንዳ መርሆዎችን ለመወሰን መነሻ የሆነው አንድ ተጠርጣሪ ቃሉን ሲሰጥ ቃሉ የተገኘበትን መንገድ የሚያረጋግጠው ስርዓት የተገኘበት ሂደት በፈቃደኝነት ነውን በሚል የሚለካበት ሂደት (The due process voluntariness test) ነው።[40] ከዚህም ሌላ የወንጀል ጉዳዮችን የማስረዳት ሀላፊነት የመንግስት እንደ መሆኑ መጠን ተጠርጣሪው ቃሉን በሚሰጥበት ወቅት ከየትኛውም ተጽዕኖ ነጻ በሆነ መንገድ ቃሉን የሰጠ ለመሆኑ ማስረዳት ያለበት ቃል የተቀበለው መርማሪ ነው ከሚል መርህ በመነሳት ነው። ከላይ ከተቀመጡት ምክንያቶች በተጨማሪ የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት የሆነው ሌላው ጉዳይ ማንኛውም ተጠርጣሪ ጠበቃ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን የሚደነግገው የህገ መንግስቱ ድንጋጌ ነው።[41] አንድ ተጠርጣሪ ጠበቃ የማማከር መብት

---

[36] ዝኒ ከማሁ ገጽ 134
[37] ዝኒ ከማሁ
[38] ዝኒ ከማሁ
[39] Aderajew Teklu and Kedir Mohammed, teaching materials (unpublished), March, 2009, Addis Ababa ገጽ 5
[40] ዝኒ ከማሁ ገጽ 138
[41] RICHARD A. LEO" AND RICHARD J., THE CONSEQUENCES OF FALSE CONFESSIONS: DEPRIVATIONS OF LIBERTY AND MISCARRIAGES OF JUSTICE IN THE AGE OF PSYCHOLOGICAL INTERROGATION, ገጽ 145፣ ከ www.wcjsc.org/ ድህረ ገጽ የተወሰደ ሚያዚያ 26/2011 ዓ.ም

መከበር ያለበት ከቃል መቀበል ወቅት ጀምሮ መሆን ይገባዋል ከሚለው ግንዛቤ በመነሳት ነው።[42] ምክንያቱም የጠበቃው መኖር መርማሪ ፖሊስ የሚያደርሳቸው ተጽዕኖዎች አይኖሩም ተብሎ ይታመናል። ስለዚህ ተጠርጣሪው ከላይ የተቀመጡትን መብቶቹን በግልጽ ካልተዋቸው በስተቀር ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ሊፈጸምለት ይገባል ማለት ነው።

በአጠቃላይ ሚራንዳ በተባለ ግለሰብና በአሪዞና ግዛት መካከል የተደረገው ክርክርና የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በተለይ መንግስት በአንድ በኩል ወንጀልን የመቆጣጠር ሀላፊነት ያለው መሆኑንና በሌላ በኩል አንድ ተጠርጣሪ እንደ ንጹህ ሆኖ የመቆጠር መበቱ እንዳይሸረሸር፣ ያለመገደድ መብት ያለው መሆኑን፣ ለተጠርጣሪው በህግ የተደረገለትን ጥበቃ የሚያሳይና ፖሊስ የተጠርጣሪውን የእምነት ቃል በፍርድ ቤትና በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው እንዲሆን የማድረግ ሀላፊነት ያለበት መሆኑን ያረጋገጠ እንደነበር መገመት ይቻላል። አሁን በብዙ ሀገራት የወንጀል ፍትህ ስርዓት ውስጥ ስራ ላይ የዋለው የእምነት ቃል አወሳሰድ ስርዓትም አንድ ተጠርጣሪ የሚሰጠው የእምነት ቃል እንደ አንድ ማስረጃ ተቀባይነት ያለው በማድረግ ፍርድ ቤቱ የቃል አቀባበል ስርዓት የተሰጠው የእምነት ቃል ፍትሀዊ እና በነጻ ፍላጎት የተሰጠ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው። እነዚህን ጥበቃዎች ለማድረግ ጥረት የሚደረግበት ምክንያት ተጠርጣሪው ተገዶ የእምነት ቃል እንዳይሰጥ ለመከላከል ነው።. ስለሆነም ፍርድ ቤቱ የተገኘውን የእምነት ቃል ከማስረጃ ምዘና ውስጥ እንዲያስገባው ከተፈለገ የእምነት ቃሉ የተሰጠው በተጠርጣሪው ነጻ ፍላጎት፣ ያለምንም ተጽዕኖና ለተጠርጣሪው የተደረጉ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎችን መሰረት አድርጎ የተገኘ መሆን እንደሚገባው ማየት ተገቢ ይሆናል።

3. የተጠርጣሪ ቃል አቀባበል ስርዓት በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት

መነሻቸውን ከአውሮፓ ያደረጉት "የሲቭልና የኮመን" ሎው የህግ ስርዓቶች ለኢትዮጵያ የዘመናዊ የህግ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዳበረከቱ ይታመናል።[43] ኢትዮጵያ በዋናነት ዘመናዊ ህጎቿን ስትቀርጽ እነዚህን ሁለት የህግ ስርዓቶች በተለይም "የሲቭል ሎው" የህግ ስርዓትን እንደ ዋነኛ ምንጭ በመውሰድ የተለያዩ ህጎችን በማጽደቅ ሀገሪቱ የዳበረ የህግ ስርዓት እንዲኖራት በማድረግ ረገድ ትልቅ እርምጃ እንደተወሰደ ይታመናል።[44] ከምዕራባውያን የህግ ስርዓት ("ከሲቪልና ኮመን ሎው") የህግ ስርዓቶች ተቀድተው ስራ ላይ

[42] የግርጌ ማስታወሻ 30

[43] "የሲቪልና የኮመን ሎው" የህግ ስርዓቶች በብዙ ሀገራት ኢትዮጵያን ጨምሮ ለህግ ስርዓት መዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ መሆኑ በተለያዩ ጽሁፎች የሚያመለክቱ ጽሁፎች የተገለጸ ሲሆን ከዚህም አልፎ ብዙ የሀገራችን ህግ መምህራን ይህን ሲገልጹ ይሰማል።

[44]Stanely Z. Fisher, Ethiopian criminal procedure, A source Book, (Adiss Ababa, Faculity of law, HSIU, 1966), ገጽ 8

ከዋሉት ህጎቻችን ውስጥ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ ተጠቃሽ ነው። በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጋችን ውስጥ ምርመራ እንዴት ይከናወናል፤ በወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎች እንዴት በቁጥጥር ስር ሊውሉ ይችላሉ፤ የተጠርጣሪ ቃል አቀባበል ስርዓት ምን መርህ መከተል አለበት፤ የተከሰሱ ሰዎች ጉዳይ ክርክር በፍርድ ቤት እንዴት እንደሚመራና ሌሎችንም ዝርዝር ድንጋጌዎችን በመያዝ በወንጀል ጉዳዮች ላይ በአንድ በኩል አጥፊዎች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚችሉበትን ስርዓት ለመዘርጋት በሌላ በኩል ተጠርጣሪዎች በምርመራ ጊዜና በክርክር ወቅት አላስፈላጊ ጫና ውስጥ እንዳይገቡ ሊከላከሉ የሚችሉ ስርዓቶችንና የተጠርጣሪ መብቶችን የያዙ ዝርዝር ድንጋጌዎች ተካተውበት ይገኛል።[45] እነዚህ የተጠርጣሪና የተከሳሽ መብቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በዋናነት ዓላማ አድርገው የተቀረጹት በወንጀል መከላከልና ወንጀለኞችን ለፍትህ ለማቅረብ በሚደረገው ሂደት ውስጥ የዜጎች ሰብዓዊ መብቶች እንዳይጣሱ በመንግስት (በህግ አስፈጻሚው) ስልጣን ላይ ገደብ በማስቀመጥ በወንጀል ምርመራና ክስ ሂደት ያለውን ስራ ሚዛናዊ አድርጎ ለማስኬድ በማሰብ ነው። ይህንንም እውን ለማድረግ በወንጀል ስነ-ስርዓት ህጉ ውስጥ አንድ ተጠርጣሪ መቼና እንዴት በቁጥጥር ስር ሊውል ይገባል፣ ተጠርጣሪው የእምነት ክህደት ቃሉን ሲሰጥ ምን ምን ሁኔታዎች ሲሟሉና በምን ሁኔታ እንደሚሰጥ፣ ምርመራው እንዴት እንደሚከናወንና ከምርመራ በኋላም ክርክሩ እንዴት እንደሚመራ የሚያመለክቱ ዝርዝር ድንጋጌዎች ተቀምጠው ይገኛሉ።[46]

በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጋችን በግልጽ እንደተመለከተው አንድ ተጠርጣሪ ወንጀል ለመፈጸሙ በቂ ጥርጣሬ የሚፈጥር ምክንያት (reasonable suspition) በተገኘ ጊዜ ፖሊስ ምርመራ ለማከናወን እንዲያስችለው ተጠርጣሪው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ በአንቀጽ 25 መሰረት እንዲቀርብ መጥሪያ ሊልክለት ይችላል ወይም በዚሁ ስነ-ስርዓት ህግ በአንቀጽ 26፣ 50 እና 51 መሰረት እንደነገሩ ሁኔታ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር ሊያውለው ይችላል። በወንጀል ተጠርጥሮ በቁጥጥር ስር የዋለ ተጠርጣሪ ስለተጠረጠረበት ወንጀል የእምነት ክህደት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ተጠርጣሪው ስሙን፣ አድራሻውንና ግላዊ ሁኔታውን የሚገልጹ ጉዳዮቹን ሊገልጽ እንደሚገባ ተመልክቷል።[47] ተጠርጣሪው ስሙንና አድራሻውን ከገለጸ በኋላ ስለተጠረጠረበት ወንጀል የእምነት ክህደት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት የቃል አቀባበል ስርዓቱ የተለያዩ መርሆዎችን መከተል እንዳለበት በዚሁ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ ተደንግጎ

[45] የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ (1967)፣ አንቀጽ 25፣ 27(2)፣ 29፣ 35፣ 46፣ 54 እና ሌሎች ድንጋጌዎች ያመለክታሉ።
[46] ዝኒ ከማሁ
[47] የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ (1967) አንቀጽ 27(1)

ይገኛል።[48] እነዚህ የእምነት ቃል አቀባበል ስርዓቶች ከወንጀል ስነ-ስርዓት ህጉ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ.ፌ.ዲ.ሪ) ህገ መንግስት በአንቀጽ 19(2) ስር ተደንግገዋል። ይህም የሚያሳየው የተጠርጣሪ ቃል አቀባበልን የሚመለከቱ ስርዓቶችና የተጠርጣሪ መብቶች በህገ መንግስት ጭምር ዋስትና ያገኙ መብቶች እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል። በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ በአንቀጽ 27(2) ስር በግልጽ እንደተመለከተው አንድ ተጠርጣሪ የእምነት ክህደት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ቃል ተቀባዩ ፖሊስ ለተጠርጣሪው ሊገልጽለት ይገባል ተብለው የተቀመጡት የተጠርጣሪው መብቶችና መርሆዎች በሚከተለው መልኩ ተገልጸው ይገኛሉ።

ሀ. "ተጠርጣሪው ምላሽ እንዲሰጥ ለማስገደድ አይቻልም፤ ነገር ግን ምላሽ ለመስጠት ነጻ እንደሆነና ፈቅዶ የሚሰጠው ማናቸውም ቃል በማስረጃነት የሚቀርብ መሆኑን ጠያቂው ፖሊስ ለተጠርጣሪው መንገር ይገባዋል"።

ለ. "ማንኛውም የተሰጠ ቃል መመዝገብ አለበት"።

ከላይ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ የተመለከቱት በቃል መስጠት ጊዜ ሊከበሩ የሚገቡ የተጠርጣሪ መብቶች በተመሳሳይ ሁኔታ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በአንቀጽ 19(2) ስር እንደሚከተለው ተቀምጠዋል። ***"የተያዙ ሰዎች ላለመናገር መብት አላቸው፤ የሚሰጡት ማናቸውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብባቸው እንደሚችል መረዳት በሚችሉት ቋንቋ እንደተያዙ ወዲያውኑ ሊነገራቸው ይገባል"*** በሚል ተቀምጦ ይገኛል።

እነዚህ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በግልጽ የተመለከቱት የተጠርጣሪ መብቶች የተቀመጡበት ምክንያት ምንድን ነው ብለን ብንጠይቅ በወንጀል ምርመራ ወቅት የመንግስትና የተጠርጣሪዎች አቅም በእጅጉ የተራራቀ በመሆኑ ተጠርጣሪዎች አላስፈላጊ ጫና ውስጥ እንዳይገቡ የቃል አቀባበል ስርዓት በመዘርጋት ለተጠርጣሪዎች ጥበቃ ለማድረግ በማሰብ የተደነገጉ ናቸው። በወንጀል ጉዳዮች ላይ ተጠርጣሪው ወንጀል የፈጸመ ለመሆኑ የማስረዳት ተፈጥሯዊ ሀላፊነት /inherent responciblity/ ያለበት መንግስት ሲሆን የሚሰበሰቡት ማስረጃዎችም ተቀባይነትና አግባብነት ያላቸው መሆን ይገባቸዋል። ምክንያቱም የወንጀል ምርመራ ስራ የሚደረገው ሁለት ፈጽሞ የማይነጻጸር ጉልበት ባላቸው አካላት መካከል ነው። ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱት መብቶች የተደነገጉበት ዋናው ምክንያት መርማሪ ፖሊስ ወይም ስልጣን የተሰጠው አካል ተጠርጣሪውን በመደለል፣ በማባበል፣ የተስፋ ቃል በመስጠት፣ በማስፈራራት፣ የሀይል ስራ ወይም ሌሎች ከህግ ውጭ የሆኑ ዘዴዎችን በመጠቀም

[48] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 27(2)

ከተጠርጣሪው የእምነት ቃል ለማግኘት በሚደረግ ጥረት ውስጥ የተጠርጣሪው ሰብዓዊና መሰረታዊ መብቶች እንዳይጣሱ ለማድረግ የተቀመጡ መርሆዎች ናቸው። ተጠርጣሪው ከተጠረጠረበት ወንጀል ጋር በተያያዘ ምንም ነገር ለመናገር ካልፈለገ ዝም ማለት እንዲችል መብት የተሰጠውም ከላይ በተጠቀሱት ዘዴዎች ከተጠርጣሪው ፍላጎት ውጭ የእምነት ቃል እንዳይገኝ ለማድረግ ነው። ቃል ተቀባዩ ፖሊስም ቃል ከመቀበሉ በፊት ተጠርጣሪው ዝም የማለት መብት ያለው መሆኑን እንዲገልጽ በህጉ ላይ ግዴታ ተጥሎበታል። ይህ ሲሆን ተጠርጣሪው ምን ምን መብት እንዳለው ይገነዘባል እንዲሁም የሚሰጠው የእምነት ቃል በፍርድ ቤት የሚሰጠው ዋጋ (credibility /weghit/) ከፍ ይላል። አንድ ተጠርጣሪ ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ያሉት መብቶች ሲነገሩት በምርመራ ወቅት ዝም ማለቱ ወንጀሉን እንዳመነ ተደርጎ እንዳይወሰድበት ያለውን ስጋት ይቀንሳል፤ ተጠርጣሪው ዝም በማለቱ በፍርድ ቤቶች ዘንድ ወንጀሉን እንዳመነ ተደርጎ እንደማይቆጠርበትም ይረዳል። መብቶቹ እንዲነገሩት የሚደረግበት ዋናው ምክንያትም እነዚህ መብቶች ለተጠርጣሪው ሲነገሩት ተጠርጣሪው አስቦ የሚጠቅመውን በመምረጥ መናገር አለብኝ ወይስ የለብኝም የሚለውን በማሰብ የሚጠቅመውን ለመወሰን እንዲችል ለማድረግ ነው።[49] በተጨማሪም ተጠርጣሪው የሚናገረው በራሱ ነጻ ፍላጎትና ፈቃደኝነት ብቻ እንደሆነ እንዲረዳ ለማስቻል ነው። ሆኖም ተጠርጣሪው መብቶቹ በመርማሪው ፖሊስ ከተገለጹለት በኋላ መብቶቹን ላይጠቀምባቸው ይችላል። ለምሳሌ ዝም የማለት ያለመናገር መብቱን አልፎ ቃሉን ሊሰጥ ይችላል ወይም አለመናገርን ሊመርጥ ይችላል። የሚናገር ከሆነም የተናገረው ነገር ሁሉ እንደ ማስረጃ ሆኖ እንደሚቀርብበት በሙሉ ግንዛቤ አውቆ ይወስናል፤ መናገሩ የሚያስከትለውን ውጤትም ይቀበላል ማለት ነው።

አንድ ተጠርጣሪ ዝም የማለት መብቱን በመተው በምርመራ ወቅትም ሆነ ጉዳዩ በፍርድ ቤት በክርክር ላይ እያለ ዝም የማለት መብቱን በመተው የእምነት ቃሉን ሊሰጥ ይችላል። ተጠርጣሪው ዝም የማለት መብቱን በማለፍ ለመርማሪ ፖሊስ ቃሉን በሚሰጥበት ወቅት ቃሉ ሳይቀነስና ሳይጨመር ተጽፎ እንዲቀመጥ ይደረጋል። የተናገረው ቃል እንዲነበብለት እና አንብቦ እንዲፈርም መደረግ እንዳለበትም በህጉ ላይ በግልጽ ተቀምጧል። ክርክሩ በሚታይበት ወቅት በፍርድ ቤትም ተጠርጣሪው መናገር ከፈለገ ቃሉን ከውሳኔ በፊት በማንኛውም ጊዜ ስለወንጀል አፈጻጸሙ በማመን በዝርዝር ለመናገር መብት አለው።

[49] Christian A. Meissner, Allison D. Redlich, interview and interrogation methods and their effects on true and false confessions, ገጽ 87 በ www.http://ilab.utep.edu ላይ ይገኛል ሚያዚያ 23/20011 ዓ.ም የተወሰደ

አንድ ተጠርጣሪ ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ዝም የማለት መብት ከመጎናጸፉም በላይ እንደ እንግሊዝ፣ አሜሪካ፣ ህንድና ሌሎች አገራት በወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ መሰረት **አንድ ተጠርጣሪ** በቅድመ ክስ ሂደት ወቅት ጠበቃ እንዲያገኝ የሚያስችል የህግ ስርዓት አላቸው።[50] በእንግሊዝ የህግ ስርዓት ዝም የማለት መብቱን በማለፍ በጠበቃው ፊት የሚሰጠው ቃል ያለተጨማሪ ማስረጃ ፍርድ ቤቶች ማስረጃውን በመቀበል ከማስረጃ ምዘና ውስጥ በማካተት ውሳኔ እንደሚሰጡበት ጽሁፎች ያሳያሉ።[51] ምክንያቱም ጠበቃው በሚሰጠው ምክር መሰረት ያለመናገር መብቱን በመተው በተጠርጣሪው ነጻ ፍላጎት ቃሉን እንደሰጠ ከመገመቱም በላይ ከማናቸውም ተጽዕኖ ነጻ በሆነ መልኩ ቃሉን እንደሰጠ ስለሚታመን ነው። ምክንያቱም ቃሉን በሚሰጥበት ወቅት ጠበቃው ፊት ለፊቱ ስለሆነ የትኛውም ዓይነት ጫናና ማስገደድ ይኖራል ተብሎ ስለማይታመን ነው። በሌላ በኩል በህንድ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ መሰረት አንድ ተጠርጣሪ የእምነት ክህደት ቃሉን የሚሰጠው የቅድመ ክስ የወንጀል ጉዳዮችን ማለትም የዋስትና፣ የጊዜ ቀጠሮና የምርመራ ጉዳዮችን ለማከናወን ስልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት ፊት በመሆኑና ይህ ፍርድ ቤትም ገለልተኛ አካል በመሆኑ በዚህ አግባብ የተሰጠ የእምነት ቃል ጉዳዩን በሚያየው ፍርድ ቤት እንደ ማስረጃ ይወሰዳል።[52]

ከላይ እንደተመለከትነው በሌሎች አገሮች ጠበቃ የማማከር መብት በቃል መቀበል ወቅት /at the time of interrogation/ እንደሚጀምር ተመልክተናል። በተመሳሳይ በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ስርዓት ውስጥ ጠበቃ የማማከር መብት በምርመራ ወቅት እንደሚጀምር የሚያመለክቱ ድንጋጌዎች በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ውስጥ ተደንግጎ ይገኛል። በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ በአንቀጽ 61 ስር ለምርመራ በማረፊያ ቤት የሚገኝ ተጠርጣሪ ጠበቃውን የማማከር መብት እንዳለው ተመልክቷል። እንዲሁም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በአንቀጽ 21(2) ስር ማንኛውም ተጠርጣሪ በጠበቃውና በቤተሰቡ የመጎብኘት መብት እንዳለው ተቀምጧል። ከላይ እንደተመለከትነው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉና በህገ መንግስቱ ላይ እንደተገለጸው አንድ ተጠርጣሪ ጠበቃ የማግኘት መብቱ የሚጀምረው በቃል መቀበል ወቅት ወይም ተጠርጣሪው በፖሊስ ቁጥጥር ስር ከዋለበት ቅጽበት ጀምሮ እንደሆነ ተመልክቷል። ከላይ በተጠቀሱት የህግ ክፍሎች ውስጥ ጠበቃ የማማከር መብት የሚጀምረው አንድ ተጠርጣሪ በቁጥጥር ስር ከዋለበት ቅጽበት ጀምሮ በምርመራ ወቅት ጭምር እንደሆነ የሚያመለክት ነው። ይሁን

[50] ዝኒ ከማሁ
[51] ዝኒ ከማሁ
[52] ዝኒ ከማሁ

እንጂ በምርመራ ወቅት ጠበቃ ከማማከር ጋር በተገናኘ በእኛ አገር ነባራዊ ሁኔታ በቃል መቀበልና የምርመራ ስራ በሚከናወንበት ጊዜ ጠበቃው የቃል መቀበሉ ስራ በሚከናወንበት ቦታ ተገኝቶ ሂደቱን እንዲከታተል የሚፈቅድ አሰራር የለም።[53] በእርግጥ ከላይ የተመለከትናቸው ድንጋጌዎች የአንድ ተጠርጣሪ ጠበቃ ተጠርጣሪው ቃሉን በሚሰጥበት ወቅት ሂደቱን ልከታተል በማለት አቤቱታ ቢያቀርብ ህጉ የሚከለክል አይደለም። በተግባር በስፋት ያለው አሰራር የሚያመለክተው ግን የቃል መቀበል ስራ የሚከናወነው ጠበቃ ባለበት ይቅርና ሌሎች ሰዎች በሌሉበት በጠባብ ክፍል ውስጥ ነው።[54] ይህም በመሆኑ ምክንያት ተጠርጣሪዎች ፍርድ ቤት ከቀረቡ በኋላ የሰጠነው የእምነት ቃል በሀይልና በተጽዕኖ እንዲሁም መብታችን ሳይነገረን ስለሆነ ማስረጃው ሊያዝብን አይገባም የሚል አቤቱታ በተደጋጋሚ ሲያቀርቡ ይታያል።[55] ይህንን ተቃውሞ ለመከላከል በሚል እምነት መርማሪ ፖሊስ የተጠርጣሪውን ቃል በሚቀበልበት ወቅት ቃሉን በራሱ ነጻ ፍላጎትና ሳይገደድ መሆኑን ለማስረዳት የደረጃ ምስክር ባለበት የቃል መቀበል ሂደት እንደሚከናወን ይገለጻል።[56] በእርግጥ የደረጃ ምስክር በመሆን የቃል መቀበል ሂደቱን የሚከታተሉት ብዙ ጊዜ የምርመራ ስራ በሚከናወንበት ፖሊስ ጣቢያ የሚሰሩ የፖሊስ ባልደረቦች ናቸው።[57] ሌላው ጠበቃ ከማግኘት መብት ጋር በተገናኘ ሊነሳ የሚችለው ጉዳይ ከክስ በፊት በምርመራ ወቅት ጠበቃ ለማማከር የሚችሉት በግል ጠበቃ የመቅጠር አቅም ያላቸው ተጠርጣሪዎች ብቻ እንደሆኑ እንረዳለን። ምክንያቱም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በአንቀጽ 20(5) ስር እንደተገለጸው አንድ ተጠርጣሪ ጠበቃ በራሱ ማቆም ካልቻለ በመንግስት ወጭ ጠበቃ ሊቆምለት የሚችለው ክስ ከቀረበበት በኋላ ጉዳዩ በክርክር ላይ ባለበት ወቅት ፍርድ ቤቱ ፍትህ ይዛባል የሚል እምነት ሲኖረው ለተከሳሹ ተከላካይ ጠበቃ እንዲቆም ትዕዛዝ ሲሰጥ ነው። ይህ ደግሞ በምርመራ ወቅት በመንግስት ወጭ ተከላካይ ጠበቃ የማግኘት መብት የሌለ መሆኑን ያሳያል። በሌላ በኩል ክስ ከቀረበ በኋላ በክርክር ወቅትም ቢሆን በመንግስት ወጭ ጠበቃ እንዲቆም የሚደረገው እንደ ሰው መግደል፣ ከባድ ውንብድናና ሌሎች ከባድ ወንጀሎች በመሆናቸው ፍርድ ቤቱ ጠበቃ ባለመቆሙ ምክንያት ፍትህ ይዛባል የሚል እምነት ሲኖረው ተከላካይ ጠበቃ እንዲቆም ሲወስን የሚፈጸም ስለሆነ ወጥ የሆነ አሰራር

[53] የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ በተለያዩ ወቅቶች በተለይም በ2007 ዓ.ም በአማራ ክልል በሁሉም ዞኖች ለሚገኙ መርማሪ ፖሊሶች ስልጠና በሰጠሁበት ወቅት የቃል መቀበል ስራ በሚከናወንበት ወቅት ጠበቃም ሆነ ሌሎች ሰዎች በሌሉበት እንደሚከናወን ከመርማሪዎቹ ጋር ከተደረገ ውይይት ለመገንዘብ ችሏል።

[54] ዝኒ ከማሁ

[55] ዝኒ ከማሁ

[56] ዝኒ ከማሁ፣ እንዲሁም የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ በስራ አጋጣሚ ተጠርጣሪው የእምነት ቃሉን በራሱ ፍላጎት የሰተ ለመሆኑ ያረጋግጣሉ በሚል የደረጃ ምስክር የቀረቡባቸውን የተለያዩ መዝገቦች ለማየት ችያለሁ።

[57] ዝኒ ከማሁ

የለም።[58] ስለሆነም በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት አንድ ተጠርጣሪ በጠበቃው ፊት ቃሉን የሚሰጥበት ወቅት ካለመኖሩም በላይ በመንግስት ወጭ ተከላካይ ጠበቃ እንዲቆም የሚደረገው ጉዳዩ በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ባለበት ወቅት ለከባድ ወንጀሎችና ፍርድ ቤቱ ለተከሳሹ ተከላካይ ጠበቃ ካልቆመ ፍትህ ይዛባል የሚል እምነት ሲኖረው ነው።

3.1 ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃል በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥ የሚደረግበት አሰራር

አንድ ተጠርጣሪ ስለተጠረጠረበት ወንጀል የእምነት ቃሉን በቃል መቀበል ወቅት ለመርማሪ ፖሊስ ሊሰጥ ይችላል ወይም ጉዳዩ በክርክር ላይ ባለበት ወቅት ለፍርድ ቤት የእምነት ቃሉን ሊሰጥ ይችላል። ይህ ማለት የእምነት ቃል ከፍርድ ቤት ውጭ ወይም በፍርድ ቤት ሊሰጥ ይችላል ማለት ነው። በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት ሁለቱም ዓይነት የእምነት ቃል አሰጣጦች በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ ውስጥ ተካተዋል። ለፖሊስ የሚሰጠው ቃል በወ.መ.ስ.ስ.ህ.ቁ. በአንቀጽ 27(1 እና 2) ስር የተመለከተ ሲሆን ለፍርድ ቤት የሚሰጥ የእምነት ቃል ደግሞ በዚሁ ህግ በአንቀጽ 35፣ 85 እና 134 መሰረት የሚሰጥበት ሁኔታ ነው። በዚሁ ህግ በአንቀጽ 85 መሰረት የሚሰጠው ቃል ጉዳዩ በቀዳሚ ምርመራ በሚታይበት ጊዜ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ከተሰሙ በኋላ ተከሳሹ የሚሰጠው ቃል ካለና ቃሉን ለመስጠት በራሱ ነጻ ፍላጎት ከወሰነ ቃሉን ይሰጥና ተመዝግቦ ጉዳዩን ለሚያየው ፍርድ ቤት ይላካል። በሌላ በኩል በአንቀጽ 134 ስር የሚሰጠው የእምነት ቃል ተከሳሹ በክሱ ላይ የተጠቀሰውን ወንጀል ስለመፈጸሙና ጥፋተኛ መሆኑንም በማረጋገጥ ስለድርጊት አፈጻጸሙ በዝርዝር ጉዳዩን ለሚያየው ፍርድ ቤት የሚያስረዳበት ስርዓት ነው። በዚሁ የእምነት ቃል መሰረትም ፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሊሰጥ እንደሚችል ህጉ ያስቀምጣል። ይሁን እንጂ ፍርድ ቤቱ የእምነት ቃሉን መሰረት አድርጎ ውሳኔ መስጠት ተገቢ አይደለም የሚል እምነት ካለው የእምነት ቃሉን በማለፍ ሌሎች ማስረጃዎች እንዲሰሙ /እንዲቀርቡ/ ሊያደርግ የሚችልበት ስልጣንም ተሰጥቶታል።

በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ መሰረት ተጠርጣሪ የእምነት ቃሉን እንዲሰጥ ከሚደረግበት አግባብ አንዱ በዚሁ ስነ-ስርዓት ህግ በአንቀጽ 35 ስር የተመለከተው ነው። በዚህ ድንጋጌ መሰረት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 27(2) ስር ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃል ህጉ በሚፈቅደው አግባብ ከተሰጠ ራሱን ችሎ እንደ ማስረጃ የሚወሰድና ተቀባይነት አግኝቶ ከማስረጃ ምዘና ውስጥ ሊገባ እንደሚችል ተመልክተናል። በሌላ በኩል በወ.መ.ስ.ስ.ህ.ቁ 35 በተገለጸው መሰረት ተጠርጣሪ ቃሉን በራሱ ነጻ ፍላጎት

[58] በአብክመ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መስሪያ ቤት በደብረ ብርሀን ቋሚ ምድብ ከሚሰሩ ዐቃቢያነ ህግ ጋር ግንቦት 11/2011 ዓ.ም የተደረገ ቃለ ምልልስ

ለመስጠት የወሰነ እንደሆነ ተጠርጣሪው የሚሰጠውን ቃል ፍርድ ቤቱ ለመቀበል እንደሚችል ተመልክቷል። ተጠርጣሪው የሚሰጠው ማናቸውም ቃል ሳይጓደል በመመዝገብ የተሰጠውን የእምነት ቃልም ለዐቃቤ ህግ እና ዋናውን ጉዳይ የሚመለከተው ሌላ ፍርድ ቤት በሆነ ጊዜ ይሄው ማስረጃ ጉዳዩን ለሚያየው ፍርድ ቤት እንደሚላክ ተደንግጓል።[59] በተግባር ያለውን አሰራርም ስንመለከት መርማሪ ፖሊስ የተጠርጣሪውን ቃል ከተቀበለ በኋላ ተጠርጣሪው ወንጀሉን ስለመፈጸሙ አምኗል የሚል ግምት ሲኖረው በግዛት ስልጣኑ ወደሚገኝ ፍርድ ቤት በመውሰድ የተሰጠው የእምነት ቃል በፍርድ ቤት ይረጋገጥልኝ የሚል አቤቱታ በማቅረብ ፍርድ ቤቶችም በስነ-ስርዓት ህጉ በአንቀጽ 35 በተቀመጠው አግባብ የእምነት ቃል ሲያረጋግጡ ይስተዋላል። የቃል አቀባበል ስርዓቱ የሚፈጸመውም በወ.መ.ስ.ስ.ህ.ቁ 35 መሰረት በተገለጸው መንገድ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ተጠርጣሪው ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ቀደም ሲል ለፖሊስ ቃሉን ሲሰጥ መደረግ ያለበት ስርዓት ተጠብቆና የስነ-ስርዓት ህጉ ጥበቃዎች (የሚራንዳ ማስጠንቀቂያዎች) ተነግረውት መሆን እንዳለበት ያስገነዝባል። ታዲያ ከዚህ ስነ-ስርዓታዊ ድንጋጌና በተግባር ከሚሰራው ጋር በተያዘ የሚነሳው ጥያቄ በወ.መ.ስ.ስ.ህ. አንቀጽ 27(2) መሰረት ስነ-ስርዓት ህጉ በሚያዘው አግባብ የተሰጠ የእምነት ቃል ተቀባይነት ያለውና ከማስረጃ ምዘና ውስጥ የሚገባ ከሆነ በዚሁ ህግ በስነ-ስርዓት ህጉ አንቀጽ 35 የተቀመጠው ድንጋጌ አላማው ምንድን ነው? ከስነ-ስርዓት ህጉ አንቀጽ 27(2) ጋር ሲታይ ድግግሞሽ አይሆንምን? የሚል ሀሳብ በባለሙያዎች ዘንድ ሲነሳ ይታያል። በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ በአንቀጽ 35 ስር የተቀመጠውን በሚመለከት ሁለት ዋና ዋና ሀሳቦች በባለሙዎች ዘንድ ሲነሱ ይታያል። የመጀመሪያውን ክርክር የሚያቀርቡ ባለሙያዎች እንደሚሉት በስነ-ስርዓት ህጉ በአንቀጽ 27(2) እና በአንቀጽ 35 ስር ያሉት ድንጋጌዎች ራሳቸውን ችለው የቆሙ ሳይሆን ተደጋጋፊ ናቸው።[60] ምክንያቱም በአንቀጽ 27(2) መሰረት ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃል በአንቀጽ 35 መሰረት በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥ የሚደረግበት ዋናው ምክንያት ዳኞች ከክርክሩ የመጨረሻ ውጤት (out come of the case) የሚያገኙት ምንም ጥቅም ስለሌለ ገለልተኛ በሆነ መንገድ የተጠርጣሪውን ቃል መቀበል ስለሚችሉ ህግ አውጭው ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃል በአንቀጽ 35 መሰረት በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥ ሲደረግ ተዓማኒ መሆኑን በማሰብ የተቀመጠ ድንጋጌ ነው ሲሉ ያስቀምጣሉ።[61] በተጨማሪም ፍርድ ቤቶች ችሎት የሚያስችሉት በግልጽ ችሎት በመሆኑ ምናልባትም የትኛውም ሰው ሊመለከት በሚችል ደረጃ ስለሆነ ተጠርጣሪው

[59] የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ (1967) አንቀጽ 35
[60] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 58
[61] ዝኒ ከማሁ

በነጻነትና በሙሉ ፍላጎት ቃሉን ለመስጠት የሚችልበት እድል አለው በሚል ነው።[62] በሌላ በኩል ፖሊስ ቃል የሚቀበለው ምናልባትም ሰው በማይኖርበት ቦታ፣ በጠባብ ክፍል ውስጥ፣ የቦታው ሁኔታ በራሱ ፍርሀትና ጭንቀት የሚፈጥር፣ መርማሪ ፖሊሱ የተጠርጣሪውን የእምነት ቃል ለማግኘት ከፍተኛ ፍላጎትና ጥረት የሚያደርግበት ሁኔታ ስላለ በየትኛውም ሁኔታ ተጠርጣሪው ነጻ ሆኖ ሊሰጥ የሚችልበት እድል ስለሌለ በወ.መ.ስ.ስ.ህ አንቀጽ 27(2) ስር ለፖሊስ የሚሰጥ ቃል ብቻውን ተዓማኒ ሊሆን አይችልም የሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ።[63] በሌላ በኩል ከላይ የተቀመጠውን ሀሳብ የሚቃወሙ ባለሙያዎች እንደሚሉት በወ.መ.ስ.ስ.ህ. በአንቀጽ 27(2) ስር ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃል ራሱን ችሎ የቆመና በራሱ እንደ ማስረጃ እንደሚወሰድ ህጉ በግልጽ ያስቀመጠው ስለሆነ በአንቀጽ 35 መሰረት በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥ የሚደረግበት አሰራር በልምድ የመጣ እንጂ የስነ-ስርዓት ህጉን ዓላማ የተከተለ አይደለም የሚል ክርክር ያነሳሉ።[64] እነዚህ ባለሙያዎች ጨምረው የሚያነሱት ጉዳይ ምናልባት ተጠርጣሪው በ27(2) መሰረት ካመነ በኋላ በፍርድ ቤት ወንጀሉን መፈጸሙን ቢክድ ለፖሊስ የሰጠውን የእምነት ቃል ውድቅ ለማድረግ ወይም ማስረጃው ተዓማኒ አይደለም በማለት ማስረጃውን ውድቅ ለማድረግ ወይም ክብደቱን ዝቅ ለማድረግ የሚያስችል የህግ መሰረት የለም የሚል ክርክር ያነሳሉ።[65] እነዚሁ ባለሙያዎች እንደሚሉት ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃል በፍርድ ቤት መረጋገጥ አለበት የሚል ክርክር የሚያነሱ ባለሙያዎች ዓላማቸው ለፖሊስ የተሰጠው ቃል በፍርድ ቤት ሳይረጋገጥ የእምነት ቃሉ ተዓማኒ ሊሆን አይችልም የሚል ከሆነ ተጠርጠሪው ቃሉን በፍርድ ቤት ከሰጠ በኋላ ተመልሶ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ስለሚሄድ ቀድሞ ከተናገረው ቃል ውጭ ቢናገር ሊገጥመው የሚችለውን የሀይልም ሆነ የስነ-ልቦና ጉዳት እያሰበ አልፎ አልፎም ቃልህን የምትቀይር ከሆነ በሚል በመርማሪ ፖሊስ ዛቻ እየተዛተበት ወደ ፍርድ ቤት ስለሚሄድ ለፖሊስ ከሰጠው ቃል የተለየ ነገር ይናገራል ተብሎ አይጠበቀም የሚል ክርክር ያቀርባሉ።[66] ይህንን ነጥብ በሚመለከት የጸሀፊው እምነት በወ.መ.ስ.ስ.ህ. አንቀጽ 35 ስር የተቀመጠው ድንጋጌ ዓላማ ለፖሊስ የሚሰጥ የእምነት ቃል በነጻ ፍላጎት የተሰጠ ስለማይሆን የማስረጃው ተዓማኒነት ዝቅተኛ ስለሚሆን በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥ የተደረገበት አግባብ ከገለልተኝነትና ከማስረጃ ተዓማኒነት ጋር የተያዘ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በህንድ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ የተገለጸውን ስንመለከት የቃል መቀበል ስራ

[62] ዝኒ ከማሁ
[63] ዝኒ ከማሁ
[64] አባዬ ዳኜው፣ በፌደራልና በአማራ ክልል ከጠበቃና የህግ አማካሪ ጋር ግንቦት 11/2011 ዓ.ም የተደረገ ቃለ ምልልስ፣ እንዲሁም ተስፋ አባተ፣ በአብክመ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የአዲስ አበባ ቋሚ ምድብ አቃቤ ህግ ጋር ሚያዚያ 21/211 ዓ.ም የተደረገ ቃለ ምልልስ
[65] ዝኒ ከማሁ
[66] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 58

የሚከናወነው የቅድመ ክስ የወንጀል ጉዳዮችን ለማየት ማለትም የጊዜ ቀጠሮ፣ የዋስትናና የምርመራ ስራን ለመምራት የሚመራው ስልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት ስለሆነ የኢትዮጵያ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ የህንድ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግን እንደ ምንጭ የወሰደ በመሆኑ የኢትዮጵያ የወንጀልኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግም ተመሳሳይ አቋም በመያዝ የተቀረጸ ነው፡፡ ምክንያቱም ለፖሊስ የተሰጠው የእምነት ቃል በአንቀጽ 35 መሰረት በፍርድ ቤት እንዲረጋገጥ ካልተደረገ የተገኘው ማስረጃ ገለልተኛና ተዓማኒ አይሆንም ከሚል እምነት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያን የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ ያረቀቁት ባለሙያዎች አንቀጽ 35 ስር ያለውን ሲያስቀምጡ የህንድን የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ አቀራረጽ የተከተለ ሊሆን እንደሚችል የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ያምናል፡፡ ምክንያቱም በህንድ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ መሰረት በቃል መቀበል ወቅት በፍርድ ቤት የተሰጠው የእምነት ቃል ነው እንደ ማስረጃ የሚወሰደው፡፡ በፍርድ ቤቱ ፊት ያልተሰጠ እንደ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም፡፡ በተመሳሳይ በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግም በአንቀጽ 35 መሰረት በፍርድ ቤት ካልተረጋገጠ ተቀባይነት እንዳይኖረው በማሰብ አንቀጽ 35 የተቀረጸው በዚህ አመክንዮት እንደሆነ ይታመናል፡፡ በተግባር ያለውን አሰራር ስንመለከትም በወ.መ.ስ.ስ.ህ. አንቀጽ 27(2) መሰረት የተሰጠ የእምነት ቃል በዚሁ ህግ በአንቀጽ 35 መሰረት ያልተረጋገጠ ከሆነ የእምነት ቃሉን ፍርድ ቤቶች እንደ ማስረጃ ቢቀበሉትም ለማስረጃው የሚሰጡት ክብደት ዝቅተኛ ነው፡፡[67] ለዚህም የሚቀርበው ምክንያት ማስረጃው በነጻነትና በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የተሰጠ ነው ተብሎ ስለማይገመት ማስረጃው ገለልተኛ እና ያለምንም ጫና ያልተሰጠ ማስረጃ ነው የሚል እምነት እንደሌላቸው በመገንዘብ ለማስረጃው የሚሰጠው ክብደትና ተዓማኒነት ዝቅተኛ ነው፡፡[68]

3.2 የተጠርጣሪ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች ሳይፈጸሙ የተገኘ የእምነት ቃል በፍርድ ቤት ያለው ተቀባይነት

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ አላማ መርማሪ ፖሊሶች ማስረጃ በሚያሰባስቡበት ወቅት የተጠርጣሪውን የእምነት ቃል ሲቀበሉ ማናቸውንም የሀይልና የማባባያ ዘዴዎች ከመጠቀም መታቀብን ጨምሮ የስነ-ስርዓት ህጉ ለተጠርጣሪው ያስቀመጣቸውን ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች መሰረት አድርጎ ቃሉን እንዲሰጥ ማድረግ እንደሆነ አይተናል፡፡ በተለይም አሁን ባለንበት ዘመን ሀይል በመጠቀም ማስረጃ ለመሰብሰብ የሚደረገው ተግባር በማህበረሰቡም ሆነ በፍትህ አካሉ ዘንድ በእጅጉ የሚወገዝ ተግባር

[67] ዝኒ ከማሁ
[68] ዝኒ ከማሁ

እንደሆነ ልብ ማለት ይገባል። ምንም እንኳን የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጋችን ስራ ላይ ከዋለ ከግማሽ ምእተ ዓመት በላይ እድሜ ያስቆጠረ ቢሆንም በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ በፍርድ ቤት ያለው እጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይገባል የሚለው አከራካሪ ጉዳይ ላይ መልስ የለውም። በዚህም ምክንያት በባለሙያዎች ዘንድ የተለያዬ ግንዛቤና በተግባርም የተለያዬ አሰራር እንደነበር ይታወሳል። አንዳንድ ባለሙያዎች እንደሚሉትና በተግባርም ሲሰሩ የነበረው ተጠርጣሪው የእምነት ቃሉን የሰጠው በማስገደድና በሌሎች ተጽዕኖዎች የተገኘ ቢሆንም ማስረጃው ጉዳዩን ለማስረዳት ተጨባጭ እስከሆነ ድረስ ማስረጃውን በመቀበል መርማሪ ፖሊስ ለፈጸመው ተግባር በህግ እንዲጠየቅ ማድረግ ይገባል በሚል ክርክር ማስረጃውን በመቀበል ውሳኔ ሲሰጡ እንደነበር ይታወቃል።[69] በሌላ በኩል ያሉ ባለሙያዎች እንደሚሉትና በተግባርም ሲሰሩ የነበረው በማስገደድና በሌሎች ዘዴዎች የተገኘን ማስረጃ ልንቀበል አይገባም፤ ማስረጃው የቱንም ያክል ለጉዳዩ ጠቃሚ ቢሆንም የውሸት የእምነት ቃሎች አንድም በማስገደድ የተገኙ ሊሆኑ ይችላሉ ወይም ተስፋ በመቁረጥ ወይም ከጭንቀት በመነጨ ምክንያት የተሰጡ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ተጠርጣሪዎቹ ከሚደርስባቸው ጫና ለመላቀቅ ሲሉ የሚሰጡት ቃል ሊሆን ይችላል።[70] ምክንያቱም የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጋችን ክፍተት ቢኖርበትም ከአጠቃላይ ከማስረጃ ህግ አስተምህሮትና ልምድ በመነሳት በሀይል የተገኙ ማስረጃዎች እንዲሁም ከእምነት ቃሉ በመነሳት የተገኙ ሌሎች ማስረጃዎችም ውድቅ ሊደረጉ ይገባል ከሚል በመነሳት ነው።[71] ምክንያቱም የህገ-ወጥ ተግባር ፍሬ ነው ልክ የመርዛማ ዛፍ ፍሬዎች (Fruit of Poisonous Tree Doctrine) እንደሚባለው ዓይነት ስለሆነ ማስረጃዎችን ባለመቀበል በግልጽ ባይሆንም እንኳን ማስረጃውን ያለመቀበል አሰራር (The exclusionary rule) መርህን ተፈጻሚ የሚያደርጉበት እንደነበር እንረዳለን።[72] ይህንን በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጋችን ይታይ የነበረውን ክፍተት የቀየረው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት ስራ ላይ መዋል ነው። ምክንያቱም በዚሁ ህገ መንግስት በአንቀጽ 19(5) ስር **"የተያዙ ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጡ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያምኑ አይገደዱም። በማስገደድ የተገኘ የእምነት ቃል ተቀባይነት አይኖረውም"** በማለት ያስቀምጣል። ከዚህ ድንጋጌ ስር በግልጽ እንደተመለከተው በማናቸውም ሁኔታ በማስገደድ የተገኘ የእምነት ቃል ተቀባይነት እንደሌለው መገንዘብ ይቻላል።

---

[69] የወንጀል መዝገብ ቁጥር 236/59 በ Stanley Z. Fisher እንደተጠቀሰው፣ Ethiopian criminal procedure: A source Book, (Faculty of Law, HSIU, Addis Ababa, 1969) ገጽ 73 እንደተጠቀሰው

[70] ዝኒ ከማሁ

[71] የወንጀል መዝገብ ቁጥር 62/75 በንጋቱ ተስፋዬ እንደተጠቀሰው፣ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ ማስተማሪያ (ያልታተመ) አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ህግ ትምህርት ቤት፣ 1990፣ ገጽ 193

[72] ዝኒ ከማሁ

ሌላው ከእምነት ቃል ጋር ተያይዞ የሚነሳውና በህጎቻችን በግልጽ ምላሽ ያልተቀመጠለት ጉዳይ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጋችን በአንቀጽ 27(2) ስር እና በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በአንቀጽ 19(2) ስር ዝም የማለት መብት እንዳለ ያስቀምጥና ይህን መብት በመተላለፍ የተገኘ ማስረጃ ውጤቱ ምን ሊሆን ይችላል የሚለው በግልጽ ተቀምጦ አለመገኘቱ ነው። እነዚህ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች **"ዝም የማለት ያለመናገር መብትና የተናገረው ማንኛውም ቃል በፍርድ ቤት እንደ ማስረጃ ተደርጎ ሊቀርብ እንደሚችል"** የተገለጸው ነው። ይህ የሚደረግበት ሁኔታ ተጠርጣሪው ያለመናገር መብት ያለው መሆኑን እንዲያውቅና የሚናገር ከሆነም መናገሩ ውጤት እንዳለው በቂ እውቀት እንዲኖረው በማድረግ የሚጠቅመውን አስቦ እንዲወስን ለማድረግ ነው። እነዚህ መብቶች በግልጽና በሚገባው ቋንቋ ሊነገሩት እንደሚገባ ያመለክታል። እነዚህ መብቶች እንዳሉት ካወቀ በኋላ በማወቅና በመገንዘብ ቃሉን ለመስጠት ወይም ላለመስጠት ይወስናል ማለት ነው። ለተጠርጣሪው የተደረገው ጥበቃ ከዚህ ዓላማ የመነጨ ነው። ስለሆነም ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃል ተጠርጣሪው እነዚህ መብቶች ሳይነገሩት የእምነት ቃሉን የሰጠ ቢሆንና ዐቃቤ ህግም በማስረጃ ዝርዝር ውስጥ በማካተት በፍርድ ቤት ቢያቀርበው ተጠርጣሪው በበኩሉ ለፍርድ ቤቱ እነዚህ መብቶች ያሉኝ መሆኑ ሳይነገረኝ የሰጠሁት ቃል ስለሆነ ማስረጃው ሊያዝብኝ አይገባም የሚል አቤቱታ ቢያቀርብ ፍርድ ቤቱ በማስረጃው ተቀባይነት ላይ ምን ሊወስን ይችላል የሚለው አከራካሪ ነው። ይህን ጉዳይ በሚመለከት በባለሙያዎች ዘንድም የተለያዩ ግንዛቤ እንዳለና በተግባርም የተለያዩ ውሳኔ ሲሰጥ ይስተዋላል። አንዳንድ ባለሙያዎች እንደሚሉት ተጠርጣሪው በስነ-ስርዓት ህጉ የተቀመጡት መብቶቹ በዝርዝርና በሚገባው አኳኋን ሳይነገረው ቃሉን እንዲሰጥ ተደርጎ ከሆነና የእምነት ቃሉን ከሰጠ መብቶቹ ሳይነገሩት የተሰጠ ቃል ስለሆነ ውጤቱ ምን መሆን አለበት የሚለው በግልጽ ስላልተመለከተ ማስረጃውን ውድቅ ማድረግ አይቻልም በሚል ይከራከራሉ።[73] በሌላ በኩል ያሉ ባለሙያዎች እንደሚሉት ተጠርጣሪው በህጉ የተደረጉለት ጥበቃዎች ሳይነገሩት የእምነት ቃል ሰጥቶ ከሆነና ይሄው ከተረጋገጠ ማስረጃው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በሚል ክርክር ያቀርባሉ። ለክርክራቸው ማጠናከሪያ የሚያደርጉት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 9 ስር የተመለከተውን መነሻ በማድረግ ነው። *ይሄውም በዚህ ድንጋጌ በንኡስ ቁጥር 1 ስር* ህገ መንገስቱ የሀገሪቱ የበላይ ህግ እንደሆነ ያስቀምጥና ማንኛውም ህግ፣ ልማዳዊ አሰራር፣ የየትኛውም ባለስልጣን ውሳኔ ይህን ህገ መንግስት የሚቃረን ከሆነ ውጤት

[73] በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሚሰሩ ዳኞች ጋር በ2010 ዓ.ም የተደረገ የጋራ ውይይት

እንደሌለው ያስቀምጣል። ይህ ማለት መርማሪ ፖሊስ የመንግስት አካል እንደመሆኑ መጠን አንድ ተጠርጣሪ የእምነት ቃል ከመስጠቱ በፊት በህገ መንግስቱ ለተጠርጣሪ የተደረጉ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎችን ተግባራዊ ሳያደርግ የተቀበለው የእምነት ቃል ህገ መንግስቱ ላይ የተቀመጠውን የሚቃረን ስለሆነ የተገኘው ማስረጃ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ከሚል መነሻ ነው። ከላይ የተቀመጠውን የህገ መንግስት ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ፍርድ ቤቶች የተጠርጣሪው መብቶች ሳይገለጹ የተገኘ ማስረጃ ውቅድ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው።[74] እንደ ጸሀፊው እምነት ከሆነ በአንቀጽ 27(2) ስር ተጠርጣሪው የሚሰጠው ማንኛውም ቃል እንደ ማስረጃ ሊወሰድ የሚችል መሆኑ ሊነገረው ይገባል በማለት ያስቀምጣል። ይህን መብት መግለጹ ዋናው ምክንያት ተጠርጣሪው በመብቱ ላይ ለሚወሰደው እርምጃ ሙሉ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ ነው። ማለትም ቃል በመስጠቱና ባለመስጠቱ መካከል ሊኖር የሚችለውን ጉዳትና ጥቅም አገናዝቦ እንዲሰጥ ያደርገዋል በሚል ነው። ስለሆነም እዚህ ላይ መገንዘብ የሚቻለው መብቱን ለተጠርጣሪው መግለጽ የሚጠቅመው ለሚሰጠው ማስረጃ ተቀባይነት ወይም ተዓማኒነት መሰረታዊ መሆኑ ነው። ምክንያቱም እነዚህ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች የተዘረጉት የእምነት ቃል በነጻ ፍላጎትና በሙሉ ፍላጎት እንዲሰጥ ለማስቻል ነው። ይህ ካልተደረገ ግን አንድ ተጠርጣሪ ራሱን ያለመወንጀል መብቱን ከመጣሱም በላይ ተጠርጣሪው ያሉትን ህገ መንግስታዊ መብቶች በተለይም እንደ ንጹህ ሆኖ የመቆጠር መብት ይጋፋል። ፍርድ ቤቶች እነዚህን ማስረጃዎች ውድቅ የማያደርጉ ከሆነ መርማሪ ፖሊሶች ሌላ ማስረጃ በተመሳሳይ መንገድ ለመሰብሰብ መንገዱን እንዲጠቀሙ ይገፋፋቸዋል፤ በሌላ አገላለጽ አሉታዊ/መጥፎ ማበረታቻ (bad incentive) በመሆን ሊያገለግል ይችላል።

ሌላው ከእምነት ቃል ጋር በተያያዘ የሚነሳው ክርክር የተጠርጣሪው መብቶች ተነግረውት ነው የእምነት ቃሉን የሰጠው አይደለም የሚል ክርክር ቢነሳ ጉዳዩን ማስረዳት ያለበት ማነው ነው የሚለው ነው። ይህንን በተመለከተ ሁለት ዓይነት ሀሳቦች ይቀርባሉ። አንዳንዶች እንደሚሉት የተሰጠው የእምነት ቃል ህጉ ያስቀመጠውን ስርዓት ተከትሎ መሆን አለመሆኑን ተጠርጣሪው እንዲያስረዳ ቢደረግ ተጠርጣሪው ቃሉን የሚሰጠው በጠባብ ክፍል ውስጥ እና ሰው በሌለበት ሁኔታ ስለሆነ ተጠርጣሪውን አስረዳ ማለት ምክንያታዊና አመክንዮታዊ ስላልሆነ ተጠርጣሪው የእምነት ቃሉን የሰጠው መብቶቹ ተነግረውት መሆኑን መርማሪ ፖሊስ ሊያስረዳ ይገባል የሚል ክርክር የሚያቀርቡ አሉ።[75] እነዚሁ ባለሙያዎች ተጠርጣሪው በፍርሀትና ብዙ ጫናዎች ሊደርሱበት በሚችል ሁኔታና

[74] ዝኒ ከማሁ
[75] ዝኒ ከማሁ

ቦታ ውስጥ ሆኖ ቃሉን የሰጠ በመሆኑ መብቶቹ ሳይነገሩኝ ነው የሚለውን እንዲያስረዳ ቢደረግ ፍትሀዊ አይደለም በማለት ክርክራቸውን ያጠናክራሉ።[76] ይህንን ክርክር ለመመለስ በማሰብ አሁን አሁን በመርማሪ ፖሊሶች በኩል እየተለመደ የመጣው አሰራር ተጠርጣሪው በራሱ ፍላጎት ቃሉን የሰጠ ለመሆኑ ምስክሮች ናቸው በማለት የደረጃ ምስክር ሲቀርብ ይታያል። በእርግጥ የደረጃ ምስክር በህጉ ላይ የተቀመጠ ባይሆንም ዓላማው ተጠርጣሪው በነጻ ፍላጎቱና መብቶቹ ተነግረውት ቃሉን የሰጠ ለመሆኑ ለማረጋገጥ እስከሆነ ድረስ አሰራሩ ብዙ ላይነቀፍ ይችላል። ይሁን እንጂ የደረጃ ምስክር በመሆን የሚቀርቡት ሰዎች ምርመራው በሚከናወንበት ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ የሚገኙ/የሚሰሩ/ የፖሊስ አባላት ስለሆኑ ገለልተኛና ነጻ ሆነው ስለነበረው ነገር በአግባቡ ያስረዳሉን የሚለው ሌላ አከራካሪ ጉዳይ ነው። በእርግጥ ፍርድ ቤቶች አንድን ለፖሊስ የተሰጠ የእምነት ቃልን ምን ያክል በነጻ ፍላጎት የተሰጠ ነው የሚለውን ለመለካት ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ ቃል መቀበሉ የተከናወነበት ጊዜ፣ ቃል ለመቀበል የወሰደው የጊዜ ርዝማኔ፣ ቃል የመቀበል ስራው የተካሄደበት ቦታ፣ የተጠርጣሪው እድሜ እና ሌሎች መመዘኛዎችን ማየት ይገባቸዋል። ለምሳሌ በቃል መቀበያ ክፍል ውስጥ ሰው በሌለበት ሁኔታ ቃላቸውን እንዲሰጡ የሚደረጉ ተጠርጣሪዎች በሀሰት የእምነት ቃል ሊሰጡ ይችላሉ። በሌላ በኩል የእምነት ቃል በምን ሀሳብና ዓላማ ተሰጠ የሚለውም መታየት ይገባዋል። ይሄውም የተገኘው የእምነት ቃል ሀሰተኛ የእምነት ቃል እንዳይሆን ከሚፈጥሩ ስጋቶች ነጻ መሆን ይገባዋል። *አሰገዳጅ በሆነ አካባቢ (ጠባብ ክፍል እና ሰው በሌለበት) የሚደረግ ቃል መቀበል በተፈጥሮው የተጠርጣሪውን እራስን ያለመወንጀል ነጻነት የሚጋፋ ወይም የሚጫን ነው።* የቃል መቀበሉ ጊዜ መርዘም፣ ቃል የተሰጠበት ቦታ እና ሌሎች ሁኔታዎች የማስገደድን ውጤት ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ፍርድ ቤቶች እነዚህን አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ማየት ይኖርባቸዋል። እንዲሁም የተጠርጣሪን የእምነት ቃል በሚመለከት የተጠርጣሪው የትምህርት ደረጃ፣ እድሜ እና ሌሎች ዙሪያ መለስ የሆኑ ጉዳዮችን ማየት ይገባል።

[76] ዝኒ ከማሁ

ማጠቃለያ

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ስርዓት ውስጥ ለፖሊስ የሚሰጥ የእምነት ቃል በፍርድ ቤት ተቀባይነት ያለው ማስረጃ በመሆን ከማስረጃ ሚዛን ውስጥ እንዲገባ ከተፈለገ ማስረጃው የተገኘበት አግባብ ህጋዊ መሆን ይገባዋል፡፡ ይሄውም የመጀመሪያው ነጥብ ተጠርጣሪው ቃሉን የሰጠው በራሱ ነጻ ፍላጎትና ያለምንም ተጽዕኖ መሆኑን መርማሪ ፖሊስ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በሌላ በኩል ተጠርጣሪው የእምነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ለተጠርጣሪው ይጠቅማሉ በሚል በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉና በህገ መንግስቱ የተቀመጡ ስነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎች ማለትም ዝም የማለት ያለመናገር መብት ያለው መሆኑ፣ የሚናገረው ማናቸውም ቃል እንደ ማስረጃ በፍርድ ቤት ሊወሰድ የሚችል መሆኑ ለተጠርጣሪው በሚገባው ቋንቋና በግልጽ ተነግሮት የሰጠው ቃል መሆኑን ፖሊስ እንዲያረጋግጥ ማድረግ ይገባል፡፡ እነዚህ ከላይ የተቀመጡት መሰረታዊ ጉዳዮች ሳይከበሩ የተሰጠ የእምነት ቃል በፍርድ ቤት ማስረጃ ሆኖ ከቀረበ ፍርድ ቤቶች ማስረጃውን ውድቅ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

በአማራ ክልል የገጠር መሬት ይዞታና የመጠቀም መብት ላይ የሚነሱ ክርክሮችን የሚወስኑ አካላት ሁሉን አቀፍ መሆናቸው እና ተቃርኗቸው

ሰሎሞን ጐራው አዳነ♣

አህፅሮተ ፅሁፍ

በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 40 ላይ የገጠር መሬት ይዞታ በመሰረታዊ መብትነት ተካቷል። በሀገራችን ዘመናዊ የሕግ ሥርዓት ከወጣበት ጀምሮ ያለውን ከአንድ ክፍለ ዘመን የማይበልጥ የጊዜ ዑደት ብቻ ስንመለከት የመሬት ክርክር አንዳንድ ጊዜ በፍርድ ቤት ሲታይ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከፍርድ ቤት ውጭ በሆኑ አካላት ሲስተናገድ ቆይቷል። የመሬት ክርክርንም መወሰን መቻል ከመብቱ አጠባበቅ ዋስትና እና ፖለቲካዊ አንድምታው በመነሳት የተለያዩ አካላት የመሬት ክርክርን ለመዳኘት መሸቀዳደም ታይቷል፤ አሁንም ይስተዋላል። ይህ ሕገ መንግስታዊ ወሳኝ የብዙሐኑ ሕብረተሰብ መብት ላይ ክርክር በተነሳ ጊዜ በየትኛው የክርክር መፍቻ አካል ይስተናገዳል የሚለው ግልፅ አቋም የተያዘበት ሆኖ አናገኘውም። ይልቁንም የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት የመሬት ክርክሮችን ለመፍታት እንደሌሎች ጉዳዮች በአንቀፅ 37 ፍትህ ከማግኘት መብት አንፃር ሊስተናገዱ የሚችሉ መሆኑን ያስገነዝባል። በተጨማሪም በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 79 መሰረት ሥነ-ሥርዓትን የማይከተል አካል የፍርድ ቤትን ዳኝነት ሊወስድ እንደማይችል ያሳያል። ከዚህ መሰረተ ሀሳብ ስንነሳ የሕግ አውጪው የሚደነግጋቸው የመሬት ሙግት መፍቻ አካላት ሕጋዊነታቸው የሚፈተሽ ይሆናል። የፌደራል መንግሥቱ ሕግ አውጪ በአዋጅ ቁጥር 456/97 አንቀፅ 12 መሰረት የመሬት ክርክርን በስምምነት መፍታትን በአመላካችነት በማስቀመጥ ቀሪውን የክርክር አፈታት ጉዳይ ክልሎች በሕግ እንዲደነግጉ እድሉን በሚሰጥ ሁኔታ የተቀረፀ ነው። በመሆኑም ለክልሎች ሰፊ ፅድል የመስጠቱ ሕጋዊነት እና ክልሎች የመሬት ክርክር ወሳኝ አካላትን ሲመርጡ ያለባቸውን የሕግ ገደብ መለየት ወሳኝነት አለው። የአማራ ክልል የገጠር መሬት ይዞታና መጠቀም መብት አለመግባባት በሚመለከት ውሳኔ የሚሰጡ አካላት ስንመለከታቸው በአዋጅ ቁጥር 252/2009 እና ደንብ ቁጥር 159/2010 መሰረት ሲታይ ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ በባለጉዳዮች ስምምነት፣ በአስተዳዳር አካላት እና በፍርድ ቤት ውሳኔ እልባት የሚያገኙበት አግባብ ያለ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ሆኖም የእነዚህ የክርክር መፍቻ አካላት በሕግ የተሰጣቸው የሥልጣን ወሰንና አሰራራቸው ከጠቅላላው ሕገ ሣይንስ ጋር ያለው ጥምርታ ተቃርኖ ይታይበታል። በመሆኑም በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የእነዚህ ተቃርኖዎች መነሻና ምንአልባትም የመፍትሔ ሀሳቦችን ለመጠቆም ታሳቢ ያደረገ ነው።

♣ ሰሎሞን ጐራው አዳነ፣ (LLB- ከሐረማያ ዩኒቨርስቲ) እና (LLM - ከባህር ዳር ዩኒቨርስቲ)፣ ከ2000 - 2002 ዓ.ም አጋማሽ ድረስ የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ከ2002-2010 ዓ.ም የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ የሰራ እና አሁን ላይ በወሎ ዩኒቨርስቲ የሕግ መምህር ሆኖ በመስራት ላይ ይገኛል። ለዚህ ፅሑፍ እውን መሆን ረዳት ፕሮፌሰር ግዛቸው ስለሽና የማላውቃቸው የፅሁፉ ተችዎች የሰጡኝ ጥልቅ ሀሳብ ሥራየን በዚህ ደረጃ እንዳደረስ አስችሎኛል በመሆኑም በአንባቢዎች ስም ሁሉንም ላመሰግናቸውም እወዳለሁ።

1. መግቢያ

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አዳጊ ሀገሮች መሬት ዋነኛ የኢኮኖሚ መሰረት ነው።[1] በሀገራችን የመሬት አስተዳደር ሥርዓት የፖለቲካ መረጋጋትን እና የፍትህ አስተዳደሩ ታዓማኒነት መኖር ላይ አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው መቻሉ የማይቀር ነው።[2] የመሬት ይዞታ መብትንም ተግባራዊ በማድረግ ረገድ የመሬት ሙግት አፈታት የሚኖረው ሚና ቀላል አይሆንም። በመሆኑም የመሬት ክርክር አፈታት መዋቅርን ለመገንዘብ የሕግ አውጭውን የሕግ ማዕቀፍ፣ የመሬት አስተዳደር አካላት አፈፃፀም እና የዳኝነት አካላት የውሳኔ አሰጣጥ ጥምረትን መመርመር ለሚስተዋሉ አንዳንድ ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት አስፈላጊነት ይኖረዋል።[3]

በመሬት ሙግት አፈታት ዙሪያ ያለው የህግ ማዕቀፍ ሲታይም በፌዴራል እና በክልል ሕግ አውጪ አካላት በተዋረድ የሚታወጁ ሕጎችን ያካተተ ነው። በፌዴራሉ መንግሥት በኩል በቀዳሚነት የመሬት ሕግ ማውጣት ሥልጣኑን መሰረት በማድረግ በአሁኑ ጊዜ ተፈጻሚነት ያለውን አዋጅ ቁጥር 456/97 ሕግ አውጿል።[4] ይህ የፌዴራል አዋጅም ለክልሎች የትኛውን የክርክር አፈታትን መተግበር ይገባል የሚለውን በተመለከተ ፈቃጅ በሆነ መልኩ የተቀመጠ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። በመቀጠልም የመሬት ጉዳይን በፍርድ ቤት አከራክሮ መወሰን የመቻሉ ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 456/97 በግልፅ ባይጠቀስም ቢያንስ ክልከላ የሌለበት መሆኑን መረዳት ይቻላል።[5]

---

[1] Duncan Green, From Poverty to Power, (London, Oxfam International, 2008), ገፅ 119-145

[2] *የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የገጠርና ግብርና ፖሊሲዎቻችን፣* 1994፣ ማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ አዲስ አበባ፣ ገፅ 72። (ከዚህ በኋላ *የገጠርና የግብርና ፖሊሲ* እየተባለ የሚጠራ)። ዳንኤል ወ/ገብርኤል፣ *የኢትዮጵያ የከተማ መሬት ሕግ፣ ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች የተዘጋጀ የስልጠና ጽሑፍ* (ባህር ዳር ዩንቨርሲቲ መሬት አስተዳደር ኢንስቲትዩት፣ መስከረም 2006 ዓ.ም) (ያልታተመ)

[3] Gizachew Sileshi and Solomom Goraw, *Rural Land Litigation and Prevailing Dilemmas in Amhara National Regional State (ANRS): Inventory of Legislative, Administrative and Judicial Hurdles (*Bahir Dar University, available at Bahir Dar University Library) 2015 (Unpublished) (ከዚህ በኋላ ግዛቸውና ሰለሞን፣ *የመሬት ሙግት መፍቻ መንገዶች* እየተባለ የሚጠራ) የሚለው በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ስፖንሰር አድራጊነት በእንግሊዘኛ ቋንቋ የጻፉትን ለበለጠ መረጃ ዝርዝር መረጃዎች ያሉት በመሆኑ መመልከት ይቻላል።

[4] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት፣ 1987፣ አዋጅ ቁጥር 1፣ 1ኛ ዓመት፣ ቁጥር 1፣ አንቀፅ 55(5) (ከዚህ በኋላ *የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት* እየተባለ የሚጠራ)

[5] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ፣ 1996፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 456፣ 11ኛ ዓመት፣ ቁጥር 44፣ አንቀጽ 12 (ከዚህ በኋላ *አዋጅ ቁጥር 456/97* እየተባለ የሚጠራ)

የአማራ ክልል ሕግ አውጭም በፌደራሉ የመሬት አዋጅ በተሰጠው ፍቅድ ስልጣን መሰረት የገጠር መሬት ሙግት መፍቻ መንገዶችን በሕግ እንዲካተቱ አድርጓል።[6] በክልሉ ሥራ ላይ ባለው የመሬት ሕግ ሥርዓት ላይ እንደተመለከተው የመሬት ግጭትን በመፍታት ረገድ በአማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴነት ስምምነትና ሽማግሌዎች፣ የመሬት አስተዳደር አካላት[7] እንዲሁም ፍርድ ቤቶች[8] ድርሻ እንዳላቸው ተመልክቷል። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ክርክሩ የፌዴራል ጉዳይ ቢሆንም እንኳ የአማራ ክልል ወረዳ ፍርድ ቤቶች የመሬት ጉዳይን የማከራከር ብቸኛ ሥልጣን ያላቸው ስለመሆኑ በአስገዳጅነት ወስኗል።[9] በአሁኑ ወቅትም ከዚህ ውሳኔ ጋር በሚጣጣም ሁኔታ በአማራ ክልል የመሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 52(2) መሰረት የወረዳ ፍርድ ቤት በስምምነት ያላለቀን ጉዳይ አከራክሮ የመወሰን የመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን ያለው መሆኑን በግልፅ አካቶ ደንግጓል። ከዚህ ጎን ለጎን የመሬት አስተዳደር አካላት በመሬት ላይ አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጡበት አሰራርም ተዘርግቷል። የመሬት አስተዳደር አካላትም በሚሰጡት ውሳኔ በፍርድ ቤትም ለማስተካከል የሚያስችል ሥርዓት ተካቷል።[10] በጥቅሉ ሲታይ የክልሉ የመሬት ሕግ ማዕቀፍ ሁሉን አቀፍ (Comprehensive) የግጭት አፈታት ሥርዓትን መዘርጋቱን ያመለክታል። ሆኖም እነዚህ ተቋማት ካካተቱት የመሬት ግጭት አፈታት ሥርዓት ውስጥ የጉዳዮች አይነትና የሥልጣናቸውን ወሰን በግልፅ ያለመለየት ሁኔታ ይስተዋላል። የመሬት ግጭት አፈታት ሲተገበርም ከሌላው የሕግ ማዕቀፍ ጋር እንዴት ተሳስሮ እንደሚቀጥል ግልፅ አለመሆን

---

[6] የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ፣ 2009፣ 252፣ *ዝክረ ሕግ ጋዜጣ፣* 22ኛ ዓመት፣ ቁጥር 14 (ከዚህ በኋላ *አዋጅ ቁጥር 252/09* እየተባለ የሚጠራ) የተሻሻለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም *ሥርዓት* ማስፈፀሚያ ደንብ፣ 2010፣ 159፣ *ዝክረ ሕግ ጋዜጣ፣* 23ኛ ዓመት፣ ቁጥር 4 (ከዚህ በኋላ *አዋጅ ቁጥር 159/10* እየተባለ የሚጠራ) በአዲስ መልክ ተፈፃሚ ሲሆኑ የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ፣ 1998፣ ዝክረ ሕግ ጋዜጣ፣ 133፣ 11ኛ ዓመት ቁጥር 18፣ (ከዚህ በኋላ *አዋጅ ቁጥር 133/98* እየተባለ የሚጠራ) እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓትን ማስፈፀሚያ የወጣ የክልል መስተዳደር ደንብ፣ 1999፣ ዝክረ ሕግ ጋዜጣ፣ ደንብ ቁጥር 51፣ 12ኛ ዓመት፣ ቁጥር 44፣ (ከዚህ በኋላ *ደንብ ቁጥር 51/99* እየተባለ የሚጠራ) የተሻሩ ሕግጋት ናቸው። ከዚህ ላይ አንባቢዎች እንዲረዱት የሚፈለገው ጥናቱ በአብዛኛው የተደረገው አዋጅ ቁጥር 133/98 በሥራ ላይ በነበረት ጊዜ ተጠናቆ የነበረ በመሆኑና ለማጣቀሻነት የተጠቀምንባቸው መዝገቦች በዚሁ አዋጅ መሰረት ውሳኔ ያገኙ ናቸው። በመሆኑም ከአዲሱ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር ልዩነት ያላቸው ሀሳቦች ቢኖሩ በዚሁ አግባብ መረዳት ይጠይቃል።

[7] አዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀፅ 52(6) ላይ በግልፅ አስተዳደራዊ ውሳኔ እንደሚሰጥና የይግባኝ ሥርዓቱንም ከፍርድ ቤት ጋር በማስተሳሰር አካቷል። ይህ ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 133/98 በግልጽ አልተካተተም ነበር።

[8] *አዋጅ ቁጥር 133/98፣ አንቀጽ 29* እና *ደንብ ቁጥር 51/99፣* አንቀጽ 35 እና 36

[9] *ወ/ሮ አርክሽ (አዛለች) ኪዳኔ* እና *ሀፃን ፌቨን ፍፁምሰው ምግዚት ፍፁምሰው ኪዳኔ፣* 2007፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ የሰበር መዝገብ ቁጥር 106560 (ከዚህ በኋላ *እነአርክሽ (አዛለች ኪዳኔ ጉዳይ* እየተባለ የሚጠራ)

[10] አዋጅ ቁጥር 252/09፣ አንቀፅ 52(6)

ይታይበታል።[11] እነዚህ የመሬት ግጭት አፈታት ተቃርኖዎች በሕግ አቀራረጽም ሆነ በተግባር ከሚስተዋለው የአሰራር ጉድለት የሚከሰቱ መሆናቸውን አመላካች ሁኔታዎች አሉ።[12]

በዚህ ጽሑፍም በአማራ ክልል የገጠር መሬትን አስመልክቶ የሚነሱ አለመግባባቶችን በስራ ላይ ባሉት የሙግት መፍቻ ተቋማት እልባት የሚሰጡበት ሁኔታ የሚመረመር ይሆናል።[13] በዋናነት የመሬት ክርክር ፈች አካላትም ያላቸውን ተቋማዊ አደረጃጀትና በሕግ ከተሰጣቸው ኃላፊነት አንፃር በተግባርም እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን ማዕከል በሚያደርግ መልኩ የተጠና ነው። ጥናቱም የገጠር መሬት ክርክር አፈታት ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ ነው። የጥናቱ ውጤትም የመሬት ሕጉን በቀጥታ ለሚያስፈፅሙ ባለድርሻ አካላት እና ለሕግ ባለሙያዎች ሕጉ ያለበትን የተዛቡ የትርጉም አጋጣሚዎችንና የአፈፃፀም ተቃርኖዎችን በቀጣይ በሚደረግ ውይይት ለማስተካከል ይረዳል የሚለውን ታሳቢ ያደረገ ነው።

2. በኢትዮጵያ የገጠር መሬት ክርክር መፍቻ ዓይነቶችና ሕጋዊነታቸው

2.1 በኢትዮጵያ የገጠር መሬት ክርክር መፍቻ መነሻ ሀሳብ

በኢትዮጵያ ዘመናዊ የሕግ ሥርዓት መተግበር ከጀመረ በኋላ በነበረው የመንግስት መዋቅር መለዋወጥ ውስጥ የመሬት ሙግት አፈታት አንዳንድ ጊዜ በፍርድ ቤት እና ሌላ ጊዜ ደግሞ ከፍርድ ቤት ውጭ ወጥ ባልሆነ ሁኔታ ሲታይ መቆየቱን መገንዘብ ይቻላል።

በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ተፈፃሚ የነበረው የፍትሐብሔር ሕጉ ስለነበርና መሬትም የግል ሐብት እንደመሆኑ መጠን የመሬት ነክ ክርክር በፍርድ ቤት እንደማንኛውም የንብረት ክርክር ሲታይ የነበረ መሆኑን መረዳት ይቻላል።[14] በሌላ ጊዜ ደግሞ የመሬት ክርክር ወደ

---

[11] ይበልጣል ይመር፣ *በአማራ ክልል የገጠር ይዞታ መሬት ክርክሮች መበራከት መንስኤዎችና የመፍትሔ ሀሳቦች*፣ አርታኢ ዶክተር ዳንኤል ወ/ገብርኤል፣ የአማራ ክልል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የህግ ምርምር ኢንስቲትዩት የህግ ጥናትና ምርምር መፅሔት፣ ቁጥር 1፣ ባህር ዳር፣ ሰኔ 2006 ዓ.ም፣ ገፅ 66-155።

[12] የግርጌ ማስታወሻ 3፣ በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ በተደረገው ጥናት የመሬት ሕጉ በተለይም በሙግት አፈታቱ ላይ ችግር ያለ መሆኑን ያሳያል። ፀሐፊው ቀደም ሲል በፍርድ ቤት ሲሰራ በፍርድ ቤት መዝገቦች ላይ የሚነሱ ክርክሮችና በመሬት ሕግ ላይ በሚደረጉ የተለያዩ ውይይቶች ላይ ካደረጋቸው ተሳትፎዎች የተገነዘበው ነው።

[13] የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ፣ 2004፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 721፣ 11ኛ ዓመት፣ ቁጥር 4 (ከአሁን በኋላ *አዋጅ ቁጥር 721/04* ተብሎ የሚጠራ) እና የተሻሻለው የከተማ ቦታ በሊዝ ይዞታ ማስተዳደሪያ የክልል ምክር ቤት ደንብ፣ 2004፣ ዝክረ ሕግ፣ ደንብ ቁጥር 103፣ 17ኛ ዓመት፣ ቁጥር 23 (ከአሁን በኋላ *ደንብ ቁጥር 103/04* ተብሎ የሚጠራ) የከተማ መሬት አስተዳደር ራሱን የቻለና በፌደራል አዋጅ ቁጥር 721/2004 እና በክልሉ ደንብ ቁጥር 103/204 መሰረት የሚተዳደር ነው።

[14] የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት የፍትሐብሔር ሕግ፣ 1952፣ አዋጅ ቁጥር 165፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 19ኛ ዓመት፣ ቁጥር 15 (ከዚህ በኋላ *የፍ/ብ/ሕግ* ተብሎ የሚጠራ)፣ መሬት አንደኛው የግል ንብረት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1206 እና ሌሎች ተከታይ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ።

አስተዳደር አካል ውሳኔ ሰጪነት መሸጋገሩን በወቅቱ የነበሩ ሕግጋት ያስረዳሉ፡፡ ለዚህም በደርግ ዘመነ መንግሥት በሀገሪቱ በአዋጅ ቁጥር 31/67 እና በአዋጅ ቁጥር 223/74 መሰረት መሰረታዊ የመሬት ፖሊሲ ለውጥ ሲደረግ የመሬት ዳኝነት ስልጣን "በፍርድ ሸንጎ" እንዲታይ ተደርጓል፡፡[15] ይህም በወቅቱ መሬት የነበረውን የኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ማጠንጠኛ ስለነበር ወደ መደበኛ ፍርድ ቤቶች መስጠት ያልተፈለገ መሆኑን ከአዋጆች አወቃቀርና የአዜው ሥርዓት ከተወገደበት "መሬት ለአራሹ" ከሚለው መሪ መፈክር መረዳት ይቻላል፡፡ የመሬት ዳኝነትም ፍርድ ቤቶች መነጠቃቸው የመሳፍንቱ አገልጋይ ናቸው የሚለውን ታሳቢ የሚያደርግ ይመስላል፡፡[16]

እንዲሁም አሁን በሥልጣን ላይ ያለው የኢፌዲሪ መንግሥት ወደ ሥልጣን ሲመጣ የትኛውን የገጠር መሬት የሙግት አፈታት እንደመረጠ ግልጽ አቋም አልያዘም፤ አሁን በሀገር ደረጃ ወጥ አቋም የለም፡፡ አንድ ግልፅ የሆነው ነገር መንግስት ወደ ስልጣን ሲመጣ የፍርድ ሸንጎዎች ስልጣናቸው እንዲያከትም ማድረጉ ላይ ብቻ ነው፡፡[17] ልዩ ሕግ ከሌለም ተፈፃሚ ወደሆኑት ሕግ ሲታይ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው አዋጅ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 18 መሰረት መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ ነው በመባሉ የመሬት ክርክር በገንዘብ እንደማይገመት ማንኛውም ንብረት ታይቶ በመደበኛ ፍርድ ቤት ሲታይ የነበረ መሆኑ ግምት የሚወሰድበት ነው፡፡ ለዚህም ማሳያዎቹ በ1989 ዓ.ም የመሬት ሕጎች በፌደራልም ሆነ በክልል ሲወጡ ግልጽ የመሬት ጉዳይን የሚዳኝ አካል ይዘው ያለመውጣታቸው ጉዳይ ነው፡፡ ይልቁንም በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ከሁለቱም ሥርዓቶች ጋር የፖሊሲ ተቃርኖ ይዞ የመጣ በመሆኑ መደናገር ይታይበት ነበር ለማለት ይቻላል፡፡[18]

---

[15] የገጠር መሬትን የሕዝብ ሀብት ለማድረግ የወጣ አዋጅ፣ 1967፣ አዋጅ ቁጥር 31/1967 (ከዚህ በኋላ *አዋጅ ቁጥር 31/1967* እየተባለ የሚጠራ) እና የገበሬ ማሕበራትን ለማጠናከር የወጣ አዋጅ፣ 1974፣ አዋጅ ቁጥር 223 (ከዚህ በኋላ *አዋጅ ቁጥር 223/1974* እየተባለ የሚጠራ) የሆኑትን ሕጎች ይመልከቱ፡፡ መሬትን አስመልክቶ በአገር አቀፍ ደረጃ ከ1900 ዓ.ም ጀምሮ በህግ መገዛት የጀመረ ሲሆን በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት የመሬት ክርክር እንደሌሎች የንብረት ክርክሮች በመደበኛ ፍርድ ቤት ይዳኝ የነበረ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በደርግ ዘመነ መንግስት በማንኛውም ሁኔታ የገጠር መሬት ክርክር ለመደበኛ ፍርድ ቤት እንዳይቀርብ መደረጉን ከአዋጅ ቁጥር 223/1974 አንቀጽ 36-40 እና ከአንቀጽ 53-60 በሚሰጠን ጣምራ ንባብ የምንረዳው ነው፡፡ አሁን ላይም የፌደራል መንግሥቱ የመሬት ጉዳይን በግልፅ ሁኔታ በፍርድ ቤት እንዲታይ ሕግ አለ ለማለት የሚቻል አለመሆኑን ማሰቡም ጠቃሚ ነው፡፡

[16] ለዚህም በአዋጅ ቁጥር 31/67 አንቀጽ 28(1) እና (2) ላይ አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ "*በመደበኛ ፍርድ ቤት*" የሚገኙ የገጠር መሬት ክርክሮች በሙሉ የተሰረዙ መሆኑን መደንገጉ የሚያመለክተው ቀደም ሲል ፍርድ ቤቶች የመሬት ጉዳይን የሚዳኙ አካላት እንደነበሩ የሚያሳይ ድንጋጌ ነው፡፡

[17] የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር፣ 1983፣ *ነጋሪት ጋዜጣ*፣ 50ኛ ዓመት፣ ቁጥር 1 "ን" ይመልከቱ፡፡

[18] ለዚህም ማስረጃው በሕገ መንግስቱ መሪ ድንጋጌ የነበረው ቢሆንም በመሬት ሕጉ እስከ 1997 ዓ.ም አዋጅ ቁጥር 456/97 እስከሚታወቅ ድረስ የመሬት ግጭት አፈታትን አቋም ሳይወስድ መቆየቱ ነው፡፡

ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ የሆነው የፌደራሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 79(1) የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች መሆኑ አቋም የተያዘበት ነው። ይልቁንም በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ አንቀፅ 4 መሰረት ከፍርድ ቤት ሥልጣን መወሰድ የማይገባ እና የመዳኘት ሥልጣን የሚሰጠው አካል ቢኖር እንኳ የዳኝነት ሥርዓትን የማይከተል ልዩ ፍርድ ቤትም ሆነ ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም የሚል ክልከላ ይዞ የመጣበት ሁኔታ ተስተውሏል። በመሆኑም በመርህ ደረጃ የመሬትም ክርክር በፍርድ ቤት በቀዳሚነት ዳኝነት ያገኛል የሚለውን የትርጉም ድምዳሜ ላይ መድረስ ይቻላል። ይህ ትርጓሜም እንደተጠበቀ ሆኖ ከሕገ መንግስቱ መውጣት በኋላም ቢሆን የተለያዩ ክልሎች ከፍርድ ቤት ይልቅ በአስተዳደር አካላት የመሬት ክርክር በቀዳሚነትና በመጀመሪያ ደረጃ እንዲፈታ የሚያደርጉበት ሁኔታ እየተከሰተ ነው።[19] ለዚህ ወጥነት መጥፋትም የመሬት አዋጅ ቁጥር 456/97 ለክልሎች የመወሰን ስልጣን አስፍቶ መስጠቱ በመሆኑ ከተወቃሽነት እንዳያመልጥ ያደርገዋል።

በአጠቃላይ የመሬት ሙግት አፈታት ሥርዓትን መወሰን መሬትን የፖለቲካ መሳሪያ የማድረግ ዕድል ያለውና የመሬት ይዞታ መብት መቆጣጠሪያ መሳሪያ ሊሆን እንደሚችል ከቀድሞ የመንግሥታት ፖሊሲዎች ያስተዋልነው ሀቅ ነው።[20] የሙግት አፈታት ወጥነት መጥፋትም የመሬት ስሪቱ መብት አጠባበቅ ላይ አሉታዊ ጫና ያመጣል። በመሆኑም የገጠር መሬት ሕግ አወጣጥ በተለይም የመሬት ክርክር ሙግት ፈች አካላት ሕግን የተከተለ ቁጥጥር የማይደረግባቸው እንዲሁም ምሁራንም የሕግ ክፍተቶቹን የማይተቹ ከሆነ ችግሩ ዛሬም ሆነ ለወደፊቱ እንደማይደገም ዋስትና የለም።

[19] ለምሳሌም በተሻሻለው የኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ፣ 1999፣ አዋጅ ቁጥር 130 የተሻሻሉ አዋጆች ቁጥሮች 56/2002፣ 70/2003 እና 103/2005፤ የተሻሻለዉ የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም እንደገና ለመወሰን የወጣ አዋጅ፣ 2000፣ *የትግራይ ነጋሪት ጋዜጣ*፣ አዋጅ ቁጥር 136፣ 16ኛ ዓመት፣ ቁጥር 1 እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም፣ 2000፣ *ደቡብ ነጋሪት ጋዜጣ*፣ አዋጅ ቁጥር 110፣ 13ኛ ዓመትን የወጡትን ሕግጋት ይመልከቱ። በተለይም የትግራይ ክልል እና የደቡብ ክልል የመሬት አዋጆች የመጀመሪያ ደረጃ ክርክርን የሚፈታው በፍርድ ቤት ሳይሆን በመሬት አስተዳደር በቀጥታ እንዲታይ ሥልጣን በመስጠት የአስተዳደር ፍርድ ቤት መሰል አሰራርን የተጠቀመ ይመስላል።

[20] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 3፣ ግዛቸውና ሰሎሞን፣ የመሬት ሙግት መፍቻ መንገዶች፣ በምዕራብ አማራ ክልል የመሬት ቢሮክራት የተባሉ የደርግ ባለስልጣናት አራት ቃዳ መሬት ወይም አንድ ሄክታር መሬት ብቻ እንዲሰጡና ሌላውን ግን እንደተነጠቁ መደረጉን ማስታወስ ይቻላል።

2.2 በኢትዮጵያ በሥራ ላይ ያለው የገጠር መሬት ክርክር አፈታት የሕግ ማዕቀፍና ሕጋዊነቱ

አሁን ላይ ባለው የመንግስት መዋቅር ውስጥ በፌደራልና በክልሎች ያለውን የመሬት ግጭት አፈታት ለመረዳት የመሬት ፖሊሲን እንዲሁም በፌደራልና በክልል መንግስታት የሚወጡ ሕግጋት ይዘታቸውንና የሕጋዊነት ጥምረት መቃኘት ተገቢ ነው።

በኢትዮጵያ የመሬት ፖሊሲን በተመለከተ ራሱን ችሎ የተቀረፀ ባይሆንም በግብርና ፖሊሲው ውስጥ የመሬት ጉዳይም አብሮ የተዳሰሰ መሆኑን መረዳት ይቻላል።[21] ነገር ግን በፖሊሲ ደረጃ በሚያሰኝ መልኩ መሬት የህዝብና የመንግስት ስለመሆኑ በፌደራሉ ሕገ መንግስት አንቀፅ 40 ላይ አቋም ተወስዶበታል። ይህ የመሬት ፖሊሲም በሕገ መንግስት የመካተቱ ጉዳይ እንደአስፈላጊነቱ ማሻሻያ ለማድረግ ከባድ በሆነ መልኩ የተቀረፀ መሆኑን የሚያሳይ ነው ለማለት ይቻላል።[22] ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ ሥር ለገጠር አርሶ አደሮችና ለአርብቶ አደሮች መሬትን በነፃ እስከማግኘት ሰፊ መብት ያላቸው ስለመሆኑ መደንገጉን ሰነዱ ያስቀምጣል።[23] በሕገ መንግሥቱ ላይ የመሬት ይዞታና የመጠቀም መብት ቋት ሰፋ ባለ መልኩ የመረጋገጡን ያክል የሙግት አፈታቱ የሚመራበት ሕገ መንግስታዊ ቅርፅ በመሬት መብት ጥበቃ ላይ ጉልህ ተፅዕኖ ማሳደሩ የማይቀር ነው። ይህም የመሬት መብት ዋስትናን ከማረጋገጥ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ይኖረዋል።

በሕገ መንግሥቱ የመሬት ግጭት አፈታትን በሚመለከት፣ ቀጥተኛ ድንጋጌ ባናገኝም እንኳ፣ በሰነዱ ውስጥ ጉዳዩ ፍትህ ከማግኘት መብት ጋር መያያዙ የማይቀር ነው። በሕገ መንግሥቱም አንቀጽ 37 ላይ በግልጽ እንደተደነገገው ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል አቅርቦ ፍርድ የማግኘት መብቱ ተረጋግጦለታል።[24] በድንጋጌው ውስጥ "በፍርድ ሊወሰን..." የሚለው ሀረግም ከመሬት ክርክር ጋር የተያያዘ ጉዳይንም ጭምር ለፍርድ ቤት ወይም በሕግ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጠውን አካል ማቅረብን የሚያካትት እንደሆነ መረዳት ይገባል። የመሬት ግጭት

---

[21] የግርጌ ማስተወሻ ቁጥር 2፣ የገጠርና ግብርና ፖሊሲውን ይመልከቱ።

[22] የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ 104 እና 105። ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘት እንደምንገነዘበው ስለመሬት መብት የሚመለከተው የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 በሰብአዊ መብቶች በክፍል ሶስት ስር ስለሚገኝ ይህንን የሕገ መንግስት የመሬት ፖሊሲ ለመለወጥ ውስብስብና ከባድ ሒደትን ማለፍ የሚጠይቅ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

[23] የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት፣ አንቀፅ 40(3) እና (4)

[24] የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ፣ *ዝክረ ሕግ ጋዜጣ*፣ 1994፣ አዋጅ ቁጥር 59፣ (ከዚህ በኋላ *የአብክመ ሕገ መንግሥት* እየተባለ የሚጠራ) እና የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ 37 እና 79

ፈቺ አካላትም ከፍርድ ቤት ውጭ ያሉ አካላት በሕግ የዳኝነት ሥልጣን እስከተሰጠ ድረስ የመሬት ክርክርን ሊዳኙ ይችላሉ የሚለውን ግን ማለፍ አንችልም። አሁን ባለው የኢትዮጵያ የመሬት ሕግ ማዕቀፍ ውስጥ የመሬት አስተዳደር አካላት የመሬት ይዞታ መብትን እስከማሳጣት ውሳኔ ሲሰጡ መደበኛ ሥነ-ሥርዓትን የሚከተሉ ስለመሆኑ ግልፅ አይደለም።[25] በመሆኑም በአንቀፅ 37 "በሕግ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጠው አካል" የሚለው የድንጋጌው ጽንሰ ሀሳብ ወሰኑ የአስፈፃሚ አካላት የአስፈፃሚነት ሥራቸውን በሚከናወኑበት ጊዜ የሚሰጡት አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ስለመጨመሩም አከራካሪ ነው።

የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደርን ሕግ በተመለከተ ሕግ የማውጣት ስልጣን፣ በሕገ መንግሥቱ እንደተመለከተው፣ በቀዳሚነትና በበላይነት ለፌደራል መንግሥት[26] የተሰጠ ነው። ለክልል መንግሥታትም ሥልጣን ተሰጥቷል።[27] ከሕግ አወጣጡ ላይ በተለይም የመሬት ግጭት መፍቻ ዓይነቶችን ከመወሰን አንጻር ካለው ሕገ መንግስታዊነት ጥያቄ ሁለት ዓይነት መከራከሪያዎችን ማቅረብ ይቻላል።[28]

በመጀመሪያ የክልሎች የመሬት ክርክር ማን መፍታት አለበት የሚለው ሥልጣን በውክልና ብቻ መገደብ አለበት የሚለውን መከራከሪያ የሚከተሉ የህግ ባለሙያዎች ይበዛሉ። ለዚህ ክርክር መነሻ የሚሆነው ሀሳብ የፌደራሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 51 የፌደራሉ መንግስትን ሥልጣንና ተግባር ሲዘረዝር በንዑስ አንቀፅ 5 ላይ "የመሬት አጠቃቀምና ጥበቃን በተመለከተ" ህግ የማውጣት ሥልጣኑን ለፌደራል መንግስቱ መስጠቱ ነው።[29] ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት በአዋጅ ቁጥር 456/97 አንቀጽ 17(1) መሰረት እያንዳንዱ *የክልል ምክር ቤት* የፌደራሉን የመሬት ሕግ ለማስፈጸም "የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ" ያወጣል የሚለው ተካቷል። የፌደራል መንግስቱ አማራጭ የሙግት መፍቻን እንዳካተተው ጉዳዩ በፍርድ ቤት ብቻ እንዲዳኝ የመወሰን ሙሉ ስልጣን ይኖረዋል በሚል መከራከር ይቻላል። ስለሆነም የመሬት ግጭት መፍቻ ተቋማትን የመወሰን ሥልጣኑ የፌደራል መንግስቱ ነው የሚል ድምዳሜ ነው።

ሁለተኛው የክርክር መስመር ክልሎች የመሬት ግጭት አፈታትን በራሳቸው የመምረጥ ሥልጣን አላቸው የሚል ነው። ለዚህም ክልሎች የየራሳቸውን የገጠር መሬት በፌደራሉ ሕግ

[25] በአዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀፅ 21 እና 26 የአማራ ክልል የመሬት ሕግ ውስጥ መሬትን የክፍሉ ወረዳ መሬት አስተዳደር በአስተዳደራዊ ውሳኔ እስከመንጠቅ የሚያስችል ሥልጣን በሕግ ተሰጥቷል።
[26] የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ 51(5)
[27] የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ 50(9)
[28] የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ 52(2)(መ)
[29] ድንጋጌውም "የመሬት አስተዳደር" የሚለውን ሀረግ አለመጠቀሙን ለመረዳት ይቻላል።

መሰረት “የማስተዳደር” ስልጣን የተሰጣቸው ስለመሆኑ ከራሱ ከፌደራሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 52(2)(መ) የምንረዳው ጉዳይ ነው። በተጨማሪም የዚሁ አዋጅ ቁጥር 456/96 አንቀፅ 2 መሰረት መሬት ማስተዳደር የሚለው የመሬት ግጭቶችን መፍታትንም ያካተተ በመሆኑ ለክልሎች የተሰጠው የሥልጣን ወሰን ሰፊ ስለመሆኑ መከራከር ይቻላል።

በፀሐፊው በኩል ተቀባይነት ያለው ሁለተኛው የክርክር መስመር ነው። ከላይ የተመለከትነው የፌደራሉ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 52(2)(መ) መሬትን ማስተዳደር ለክልሎች መስጠቱና የገጠር መሬት አስተዳደር ትርጉም የመሬት ግጭት አፈታት ሥርዓትን የሚያካትት ስለመሆኑ አስረጅ ነው። እንዲሁም የፌደራል አዋጅ ቁጥር 456/97 አንቀፅ 2 “የገጠር መሬት አስተዳደር” የሚለውን ሲተረጉም፡-

> *“የገጠር መሬት አስተዳደር” ማለት በገጠር መሬት ይዞታ ላይ ዋስትና የሚሰጥበት፣ የገጠር መሬት አጠቃቀም ፅቅድ የሚተገበርበት፣ በገጠር መሬት ተጠቃሚዎች መካከል <u>የሚነሱት ግጭቶች የሚፈቱበትና</u> ማንኛዉም የገጠር መሬት ተጠቃሚ መብትና ግደታዎች የሚተገበሩበት እንዲሁም የባለይዞታወች ማሳወችን የግጦሽ መሬትን መረጃ በመሰብሰብና በመተንተን ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ የሚደረግበት ሂደት ነው።* (ሰረዝ የተጨመረ) በሚል ያስቀምጠዋል።

ከዚህ ትርጉም የምንረዳውም ክልሎች መሬትን የማስተዳደር ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣን ያላቸው በመሆኑ የክርክር አማራጮችን የመወሰን ነፃነት አላቸው ማለት ነው። በተጨማሪም የዚሁ አዋጅ ቁጥር 456/96 አንቀፅ 12 መሬትን አስመልክቶ የሚነሳ ክርክርን “... በክልሎቹ በሚወጣ ህግ መሰረት እንዲፈታ ጥረት ይደረጋል” በሚል የመሬት ግጭት ፈች አካላትን ክልሎች እንዲወስኑ ዕድል መስጠቱ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 52(2)(መ) ጋር የሚጣጣም ነው። በመሆኑም ክልሎችም የገጠር መሬት ማስተዳደርን በጠቅላላው፣ የግጭት መፍቻ መንገዶችን መምረጥና መወሰን በልዩ ሁኔታ ከውክልና ባለፈ ሁኔታ ሕገ መንግሥታዊ በሆነ አግባብ የመወሰን ሥልጣንና ነፃነት አላቸው በሚል መደምደም ይቻላል። በዚህ አዋጅ ቁጥር 456/97 አንቀፅ 17 መሰረት የፌደራሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፌደራሊዝም ሥርዓት አወቃቀር አንጻር በየሥልጣን ወሰናቸው አቻ የሆነውን የክልል ምክር ቤትን የመወከሉ ጉዳይ

ለየት ያለ ሁኔታ ነው።[30] ከክልል ምክር ቤት ሉዓላዊነትና ከአቻ ሕግጋት ውክልና አሰጣጥ ረገድ ውስንነት ያለበት መሆኑን መረዳት አያዳግትም።

የክልል ምክር ቤቶች የመሬትን ሕግ ሲያወጡ የመሬት ግጭት አፈታትን ከመደበኛ ፍርድ ቤት ውጭ ማድረግ የሚያስችላቸውን ዕድል በሚሰጥ መልኩ የመቀረፁ ሁኔታ ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል።[31] ሆኖም ክልሎች ሁልጊዜ ሥልጣናቸውን በማስፋት ከመወሰናቸው በፊት በሌሎች ሕጎች ያሉባቸውን የሕግ አወጣጥ መርሆችን ማጤን ይኖርባቸዋል። በዚሁ መሰረትም የክልል ምክር ቤቶች በሚያወጡት የመሬት ህግ በፌደራሉ ሕገ መንግሥት የዳኝነት ስልጣን የሥነ-ሥርዓት ሕግን ለሚከተል አካል የተሰጠ ስለመሆኑ የተደነገገውን ገዥ መርህ በማይቃረን መልኩ የመሬት ክርክር ውሳኔ ሰጭ አካላትን ማቋቋም ይኖርባቸዋል።[32] ይህም ሲባል ተገቢውን ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ (procedural due process of law) የሚያስጠብቅ አሰራር ያላቸውን የመሬት ዳኝነት ሰጪ አካላትን ማቋቋምን መሰረት ያደረገ ሕግ ማውጣት ሕገ መንግስታዊ ግዴታቸው ይሆናል ማለት ነው።

በመጨረሻም መሬት ዋነኛውና የአብዛኛው ሕብረተሰብ የኑሮ መሰረት እስከሆነ ድረስ መሬትንና ከመሬት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ግብይቶች (transactions) አስመልክቶ ለሚከሰቱ አለመግባባቶች ከተደራሽነት፣ ከተግባራዊነቱ እና ከውጤታማነቱ አኳያ መዝኖ ተገቢውን ዓይነት የግጭት መፍቻ መንገድ መምረጥና የአፈፃፀም ሥርዓቱን መዘርጋት ያስፈልጋል። ክልሎችም የሚያወጡት ሕግ ከፌደራሉ አስገዳጅ ድንጋጌዎች ማፈንገጥ ባይገባቸውም ፈቃጅ በሆኑት ጉዳዮች ላይ እንደየክልሎች ተጨባጭ ሁኔታ የየራሳቸውን የመሬት ሕግ ማውጣት መቻላቸው የሕጉን ጥቅል አሳሪ ያለመሆኑንና ተራማጅ እሳቤ የተላበሰ መሆኑን የሚያመለክት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። በዚሁ ጽነሰ-ሀሳብ መነሻነት የአማራ ክልል ያካተታቸውን የመሬት ግጭት መፍቻ ተቋማት የተዋቀሩበትን የሕግ ማዕቀፍና አሰራራቸውን ዘርዘር ባለመልኩ እንደሚከተለው ይመረመራሉ።

---

[30] በሌሎች መሰል ሕጎችም በንፅፅር ሲታይ ለምሳሌ የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 33(2) መሰረት ለክልሎችና ለከተማ አስተዳደሮች በተዋረድ ሥልጣን ሲሰጥ ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈፀምም የሚያስፈልጉ ደንቦችና መመሪያዎችን ያወጣሉ" በሚል የተደነገገውን መመልከት ይቻላል። የውክልናው ደረጃ በክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ከማውጣት አዋጅ እንዲወጣ መደረጉ ለጉዳዩ ትኩረትና ክብደት በመስጠት በቂ ውይይት እንዲደረግበትና የዳበረ ሕግ እንዲኖር መፈልግ ከሆነ መልካም ነው።

[31] በተለይም የትግራይ ክልል እና የደቡብ ክልል የመሬት አዋጆች የመጀመሪያ ደረጃ ክርክርን የሚፈታው በፍርድ ቤት ሳይሆን በመሬት አስተዳደር በቀጥታ እንዲታይ ሥልጣን የሰጡ ስለመሆኑ ሕጉ ያመለክታል።

[32] የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት፣ አንቀፅ 37 እና 79

3. የአማራ ክልል የገጠር መሬት ክርክር መፍቻ ተቋማት እና ተግባራቸው

በአማራ ክልል የመሬት ክርክር አፈታትን ለመወሰን በመጀመሪያ በፌደራሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 79 በፌደራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች መሆኑን ማክበር የሕጋዊነት መርህ የሚጠይቀው ጉዳይ ነው። የአማራ ክልል ሕገ መንግሥትም ከዚሁ ጋር በተጣጣመ አግባብ የተቀረፀ ነው።[33] ሁለተኛው የአማራ ክልልም የፌደራል መንግስት አባል ክልል እንደመሆኑ መጠን በፌደራሉ አዋጅ ቁጥር 456/97 መሬትን አስመልክቶ የሚነሳ ክርክር በስምምነት ሊፈታ ካልቻለ በሽምግልና ወይም በክልሎቹ በሚወጣ ሕግ መሰረት እንዲፈታ ጥረት ይደረጋል[34] በማለት አማራጮችን ማስቀመጡን ያመለክታል። ሶስተኛው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የክልሉን የመሬት ሕጎች ከፌደራሉ አዋጅ ጋር ያላቸው ግንኙነት መሰረት በማድረግ የሕግ ትርጉም የሰጠባቸውን ጉዳዮች መኖራቸውም ይታወቃል።[35] አራተኛው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የፌደሬሽን ምክር ቤት በግለሰቦች መካከል የሚነሳ የመሬት ጉዳይ ላይ በርካታ ውሳኔዎች ማሳለፍ መጀመሩ ይስተዋላል።[36]

የአማራ ክልል መንግሥትም ከላይ የተጠቀሱትን የቁጥጥር መሰላሎችን ባገናዘበ ሁኔታ የመሬት ሙግት መፍቻ ሁሉን አቀፍ ለማድረግ ጥረት ስለመደረጉ ይስተዋላል። ሆኖም ሁሉን አቀፍ የገጠር መሬት ክርክር መፍቻዎች ሲመረጡ እርስ በእርሳቸው የሚቀናጁበት እና ከሌሎች ሕጎች ጋር ያለውን ውህደት ማጤን የሚያስፈልግ ነው። ቀጥለንም በመሬት ሙግት አፈታት ሥርዓቶች መካከል የሚስተዋሉ ተቃርኖዎች ስለመኖር ወይም አለመኖራቸው ዘርዘር ባለ መልኩ ይመረመራል።

---

[33] የአብክመ ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ 66

[34] የአዋጅ ቁጥር 456/1997፣ አንቀጽ 12

[35] በፋና ብሮድካስቲንግ ቴሌቪዥን፣ ነሐሴ 09 ቀን 2011 ዓ.ም የተላለፈ፣ የፌደሬሽን ምክር ቤት ባስጠናው ጥናት መሰረት ክልሎች መሬትን በሚመለከት ከተሰጣቸው ሥልጣን በላይ ሕግ እያወጡ መሆኑን እና ለሕገ መንግስቱ ከቀረቡለት 2,200 መዝገቦች ውስጥ 500 የሚሆኑት መሬትን የሚመለከቱ መሆኑን ጠቅሷል።

[36] ይህ እንኳ የፌደሬሽን ምክር ቤት በክልሎች መካከል ያለውን የድንበር ወሰን ደም ለማፋሰስ ተቃርቦ እያለና ስንት ሕገ መንግስቱን የሚጥሱ አዋጆች እያሉ ሳይወስን የፍርድ ቤት ክርክሮች ላይ ጣልቃ መግባቱ አሳማኝ አይደለም። "የራሷ እያረረም..." ይመስላል። ለዚህ ሁነኛ ማሳያም በቅርቡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቷ እንደአጣሪ ጉባኤ ሰብሳቢነታቸው የፌደሬሽን ምክር ቤት አቅጣጫ መሠጠቱን በኢቲቪ የካቲት ወር 2011 ዓ.ም ላይ በተናገሩት ተላልፏል።

3.1 የገጠር መሬት ክርክር በውይይት ወይም በሽምግልና የሚፈታበት አግባብ

ከፌደራሉ ሕገ መንግስት ቀጥሎ የገጠር መሬትን መሪ ድንጋጌዎችን ይዞ የወጣው የፌደራል አዋጅ ቁጥር 456/1997 ነው። የመሬት ሙግትን በሚመለከት ቀጥተኛ ድንጋጌ የሆነው የአዋጁ አንቀጽ 12፡-

> *የገጠር መሬት ይዞታ መብትን በተመለከተ ክርክር ሲነሳ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ተከራካሪዎች በውይይትና ስምምነት እንዲፈታ ጥረት ይደረጋል። በስምምነት ሊፈታ ካልቻለ በተከራካሪ ወገኖች በተመረጡ [ሽማግሌዎች] ወይንም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ህግ በተደነገገው መሰረት ይወሰናል።*[37] በሚል የተደነገገ ነው።

የዚህን ድንጋጌ ይዘት ስንመረምረውም በውይይትና በስምምነት ክርክርን መፍታት ቀዳሚ የመሬት ክርክር መፍቻ መንገድ መደረጉን ነው። ሁለተኛው አማራጭ የመሬት ግጭትን በስምምነት መፍታት ካልተቻለ ብቻ በተከራካሪ ወገኖች በተመረጡ ሽማግሌዎች እንዲወሰን መምረጡን ያሳያል። ሶስተኛው አማራጭ በክልል የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ በሚደነግገው መሰረት አለመግባበትን መፍታት መቻል ነው። ሶስተኛው አማራጭም በሽማግሌዎች ከመፍታት ጋር በአማራጭ መቀመጡን "ወይም" በሚል ቃል መያያዙን ያሳያል። ከዚህ የድንጋጌው አወቃቀር አንፃር የፌደራሉ የመሬት አዋጅ ከሙግት መፍቻ መንገዶች ውስጥ በአስገዳጅነት ያስቀመጠው ስምምነትን ነው። ስምምነትም በባለጉዳዮች በራሳቸው ወይም በባለጉዳዮች የተመረጡ ሽማግሌዎች አደራዳሪነት ሊደረስ ይቻላል። በዚህ የመሬት ክርክር መፍቻ አማራጭም የመሬት አለመግባባትን ለምፍታት ጥረት ማድረግ በክልል ሕጎችም እንደማይታለፍ የሚያመለክት ነው። በዚህ ድንጋጌ የመጀመሪያ ዓረፍተነገር መጨረሻ ላይ "...ጥረት ይደረጋል" የሚለው አገላለጽ የሚያሳየው ከተከራካሪዎች መብት አንፃር የተቀመጠ ነው። ይህም አገላለፅም በውይይትና በሥምምነት ክርክርን መፍታት ለተከራካሪዎች ዕድልን መስጠቱ መብት ሲሆን ነገር ግን መብቱን በመሬት ሕግ ውስጥ መደንገግ የክልሎች ግዴታ መሆኑን የሚያስቀር አይደለም። ነገር ግን በሽምግልና የመሬት ክርክርን መፍታት በክልል ሕግ ውስጥ ሊለወጥ ስለመቻሉ ድንጋጌው ያስገነዝባል።

ከዚህ በመነሳትም ክልሎችም የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ ሲያወጡ በውይይት መጨረስ የመጀመሪያው የሙግት መፍቻ ተቋም በሚያደርግ አግባብ እያካተቱ አውጥተዋል። ቀደም ሲል

[37] አዋጅ ቁጥር 456/97፣ አንቀፅ 12 የእንግሊዘኛውን ቅጅ ይመልከቱ።

የአማራ ክልል በአዋጅ ቁጥር 133/98[38] እና ደንብ ቁጥር 51/99[39] መሰረት ስምምነትና ሽምግልናን በሙግት መፍቻነት በማካተት ሲሰራበት ቆይቷል። እነዚህን ሕጎች በመሻር አሁን ላይ ተፈፃሚነት ያለው የክልሉ መሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 ክፍል ስምንት አንቀፅ 52 "በገጠር መሬት ይዞታና የመጠቀም መብት ላይ የሚነሱ ክርክሮችን ስለመወሰን" በሚለው ክፍል ላይ የሽማግሌዎች አስታራቂነት አንደኛው የገጠር መሬት ክርክር መፍቻ አማራጭ ሆኖ ተካቷል። የአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 52 ሲነበብ ይዘቱ፡-

1. *የገጠር መሬት ይዞታንና የመጠቀም መብትን በሚመለከት የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና የሚነሱ ክርክሮች በመጀመሪያ ደረጃ፡-*

   ሀ) በራሳቸው በባለጉዳዮች መካካል በሚካሄድ ውይይትና በሚደረግ ስምምነት እንዲፈቱ ይደረጋል፤

   ለ) ተከራካሪ ወገኖች በስምምነት ሊፈቷቸው ካልቻሉ ራሳቸው በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አስታራቂነት ጉዳያቸው እልባት እንዲያገኝ ይደረጋል።

2. *በዚህ ንዑስ አንቀፅ (1) ስር በተደነገገው መሰረት አለመግባባቱ ያልተፈታ እንደሆነ ይኸው ከታወቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ጉዳዩ ለአቅራቢያው ወረዳ ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል።*

የእነዚህን ሁለት ንዑስ ድንጋጌዎች አወቃቀርን ስንመለከት በአዋጅ ቁጥር 133/98 ከነበረው አቻ ድንጋጌ መጠነኛ ልዩነት የሚታይባቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል። የመጀመሪያው ልዩነት የአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀፅ 52 ድንጋጌ ይዘት ሲታይ የፌደራል አዋጅ ቁጥር 456/97 በተዋቀረበት አግባብ በሚቀራረብ ሁኔታ አማራጭ የሙግት መፍቻ የሆኑትን ውይይትና ስምምነት እንዲሁም በሽምግልና መፍታት በአንድ ንዑስ አንቀጽ ሥር በማካተት መደንገጉ ነው። ሁለተኛው የፌደራሉ አዋጅ በሰጠው ሥልጣን መሰረትም በአማራጭ የክርክር መፍቻ አግባብ ያልተፈታ ጉዳይ በግልፅ የወረዳ ፍርድ ቤት ቀርቦ እልባት ሊያገኝ ስለመቻሉ ተደንግጓል። ይህም ድንጋጌ በቀድሞው አዋጅ ቁጥር 133/98 ላይ "መደበኛ ፍርድ ቤት" የሚለውን በማስቀረት "የወረዳ ፍርድ ቤት"[40] በሚል መተካቱ ከሕግ አወጣጥ መርህ አኳያ በግልፅ ተቀምጧል። ሶስተኛው ደንብ ቁጥር 51/99 በተለየ መልኩ የአዋጅ ቁጥር 252/09

[38] በስምምነት ወይም የሽማግሌዎች አንደኛው የሙግት መፍቻ ተቋም ያደረገበት ሁኔታ ከድንጋጌው አወቃቀር ለማነፃፀር አዋጅ ቁጥር 133/98፣ አንቀጽ 29

[39] እንዲሁም በአሁኑ ደንብ ቁጥር 159/2010 ላይ ተነፃፃሪ ድንጋጌ ባይኖርም የተሻረው ደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 35"ን" ይመልከቱ።

[40] ችግሩን ለመፍታት የክልሉ መንግሥት አዋጅ ቁጥር 148/99 የሆነውን ለማውጣት ተገዶ የነበረ መሆኑ የሚታወስ ነው።

ማስፈፀሚያ ደንብ ቁጥር 159/2010 ስለመሬት ክርክር አፈታት ጉዳይ በዝምታ አልፏል። የደንቡ ዝምታም አላስፈላጊ ድግግሞሽንና ምንአልባትም አወዛጋቢ ግጭቶች እንዳይነሱ ከወዲሁ የሚያስቀር በመሆኑ ተመራጭ የሕግ አወጣጥ ዘዴ ነው ማለት ይቻላል። ይህ ለውጥ መደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ አንዳንድ ተቃርኖዎች ያሉት ስለመሆኑ ቀጥለን እንመለከታለን።

ከመሬት የሕግ ማዕቀፎች በመነሳት ተፈፃሚነት እንዲኖረው የታሰበውን አማራጭ የክርክር መፍቻ ዘዴ ምንነት፣ አሰራር፣ ስልጣን እንዲሁም የሚደረስበት እልባት ስለሚኖረው ውጤት አከራካሪ ነጥቦች አሉ። በመጀመሪያ እንደሚታወቀው አለመግባባትን ከፍርድ ቤት ውጭ ለመፍታት ያሉትን አማራጮች በሶስት ዋና ዋና መንገዶች ማለትም በውይይት/ድርድር (negotiation)፣[41] በሽምግልና/በማስማማት ወይም በእርቅ (mediation or conciliation)[42] እና በግልግል ዳኝነት (በዘመድ ዳኛ) (arbitration)[43] መጨረስ በሚሉት ተከፍለው የሚታዩ ናቸው። በፌደራሉም ሆነ በክልል የመሬት ሕጎች የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ስንመለከት የአማርኛው እና ከእንግሊዝኛው ቅጅ ጋር የማይጣጣም እንዲሁም በአንደኛው ድንጋጌ እና በሌላኛው ድንጋጌ የተለያየ ቃላትን ስለሚጠቀሙ ከሶስቱ አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች መካከል የትኛውን(ኞችን) እንዳካተቱ ለመለየት አስቸጋሪ ያደርገዋል።[44] ከዚህ ሁሉ የምንረዳው የመሬት ሕጉ የግጭት መፍቻ ዓይነቶችን በመምረጥ ረገድ ለትርጉም ስለሚጋለጥ ተቃርኖ የሚታይበት መሆኑን ነው።

በፌደራሉ አዋጅ 456/97 እና በክልሉ አዋጅ 252/09 ላይ እንደተጠቀሰው ስምምነት እና ሽምግልና የሙግት መፍቻ አማራጮች ተካተው ይገኛሉ።[45] በእነዚህ የመሬት ሕግጋት ላይ በአማርኛው "ሽማግሌዎች" የሚለውን ሲጠቀሙ በእንግሊዝኛዉ ቅጅ ደግሞ "Arbitrators" የሚለውን ቃል ይጠቀማሉ።[46] የአማርኛውና የእግሊዘኛው ቃላት አጠቃቀም በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ የተለያዩ ናቸው። በተለመደው አመዳደብ ሲታይ የእንግሊዝኛው ቅጅ በግልግል ዳኝነት መጨረስ

---

[41] የፍ/ብ/ሕ/ቁጥሮች 3307-3317

[42] የፍ/ሕ/ቁ/ 33018-3324

[43] የፍ/ሕ/ቁ/ 3325-3347

[44] ዝኒ ከማሁ፣ ሽምግልና ባለጉዳዮችን ውጤት ላይ እንዲደርሱ የሚያግዝ ገለልተኛ የሆነ ሶስተኛ ወገን ያለበትና የሶስተኛ ወገን አስተዋጽዖም ባለጉዳዮች እንዲስማሙ መልካም ውጤት ላይ እንዲደርሱ መገፋፋት ነው። በዕርቅ ጊዜ የሶስተኛው ወገን ሰው ሚና መነሻ አስታራቂ ሀሳብ እስከማቅረብ የሚደርስ ሲሆን በሽምግልና ጊዜ አሸማጋዩ እንዲስማሙ መገፋፋት እንጂ ሀሳብ የማቅረብ መብት ሊኖረው አይችልም በሚል የተቀመጠ ነው።

[45] አዋጅ ቁጥር 456/1997፣ አንቀጽ 12 ምንም እንኳ የእንግሊዝኛዉ ቅጅ በሽምግልና (mediation/reconcilation) ፈንታ የግልግል ዳኝነት (arbitration) የሚል ቢመስልም አስገዳጅ የሆነዉ ከአማርኛው ቅጅ ግን ለማለት የተፈለገው ሽምግልና እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ከዚህ ላይ የሚጠቀማቸው እኩያ ቃላት "discussion and agreement" to refer to "ውይይትና ስምምነት" እናም "arbitral body" የሚለውን "ሽምግልና" በማለት ይተረጉመዋል።

[46] በፌደራል አዋጁም ልዩነት በተመሳሳይ ይታያል።

የሚለውን እንድምታ ይፈጥራል። ሆኖም ግን የአማርኛውን ቅጅ በመከተል የተፈለገው ግብ ሶስተኛ ወገኖች አስገዳጅ ውሳኔ እንዲሰጡ ሳይሆን ለባለጉዳዮች ስምምነት የተፈለገው አማራጭ ሽምግልና እንደሆነ መገንዘብ ይገባል።[47] በመሬት ክርክር አማራጭ የክርክር መፍቻ ዘዴን በተለይም በራሳቸው ተነሳሽነትም ሆነ በሶስተኛ ወገን እገዛ በባለጉዳዮች ስምምነት መጨረስ ሕጉ ልዩ ትኩረት በመስጠት ሰፋ ያለ የህግ ማዕቀፍ አስቀምጧል የሚለውን መደምደም ይቻላል።[48]

ከእነዚህ የፌደራልና የክልሉ ሕጎች ጥቅል ጽንሰ ሀሳብ ስንነሳ የገጠር መሬት ክርክርን በስምምነት ለመጨረስ ከድርድር/ከውይይት በተጨማሪ ሽምግልናን የሚመለከቱ ስለመሆናቸው የተረዳን ሲሆን ከመሬት ጋር የተያያዘ ግጭት በዘመድ ዳኛ መጨረስ (arbitration) የመታየት ጉዳይ አከራካሪ ነው። ቀደም ባለው የአማራ ክልል የመሬት ሕግ መዋቅር ላይ ይህን የሚከለክል ህግ ካለመኖሩም በላይ የፍትሐብሔር ህጉ አለመግባባት የፈጠሩ ሰዎች ክርክራቸውን በመረጡት የዘመድ ዳኛ (arbitrator) መጨረስ እንደሚችሉ ያመለክታል።[49] እንዳውም የአዋጅ ቁጥር 456/97 አንቀፅ 12 የእንግሊዘኛው ትርጉም “arbital bodies” የሚለውን አገላለፅ መጠቀሙ የግልግል ዳኝነትን የሚቀበል ይመስላል። ሆኖም በአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀፅ 52(6) ላይ ከፍርድ ቤት እና ከአስተዳደር አካላት ውጪ ሌላ አካል የመሬት ክርክርን ሊወስን አይችልም በሚል መቀመጡ የግልግል ዳኞች ሶስተኛ ወገን ሆነው አስገዳጅ ውሳኔ የሚሰጡ አካላት በመሆናቸው በመሬት ጉዳይ ላይ አከራክረው እንዳይወስኑ ክልከላ የተደረገባቸው መሆኑን የሚያመለክት ድንጋጌ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ የምንዳስሰው ጥያቄ በሽማግሌዎች መስማማት እንደ አንድ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴ የተቀመጠ በመሆኑ የዚህ ተቋም አወቃቀር ምን ይመስላል? የሚለውን ማየቱ ጠቃሚ ነው። በመሰረቱ ሽምግልና በጽንሰ ሀሳብ ደረጃም ሆነ በኢትዮጵያ ባህላዊ የግጭት

---

[47] በቀድሞው አዋጅ ቁጥር 133/98 እና ደንብ ቁጥር 51/99 መሰረት የዚህ ዓይነት ችግር ነበረ። በተለይም የክልሉ ደንብ ቁጥር 51/99 በእንግሊዘኛዉ ቅጅ ላይ ስምምነት (agreement) እና በዘመድ ዳኛ መጨረስ (arbitration) የሚል መልዕክት የያዙ ናቸው።

[48] በቀድሞው የመሬት ሕግ ላይ በየቀበሌው የሽማግሌዎች ሸንጎ የሚባል ተቋም አቋቁሞ የነበረ መሆኑ ከደንቡ ማስፈፀሚያ መመሪያ ላይ የምንረዳው ነው።

[49] የፍ/ብ/ሕ/ቁጥሮች 3325-3346 ይመልከቱ። የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ፣ 1958፣ ድንጋጌ ቁጥር 52፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 25ኛ ዓመት፣ ቁጥር 3 (ከዚህ በኋላ *የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/* እየተባለ የሚጠራ) በዘመድ ዳኛ የመጨረስ ስምምነት የማይደረግባቸውን አለመግባባቶችን የሚያመላክተው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 315 እንኳ የአስተዳደር መስሪያ ቤት ውሎችን ብቻ ይጠቅሳል እንጅ የመሬት ክርክሮችን አስመልክቶ ግለጽ ክልከላ የለም። እነዚህ አካላት ግን የሚሰጡት ውሳኔ የመሬት ፖሊሲውን ዓላማ ያልሳተ መሆን አለበት። በእርግጥ ይህን ችግር ለመቅረፍም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 352 ድንጋጌ እንዲህ ዓይነት ስህተት ቢከሰት በከፍተኛው ፍርድ ቤት በይግባኝ ማረም መቻሉን ማስቀመጥ ይቻላል።

አፈታት ልማድ እራሱን ችሎ በቋሚነት የማሸማገል ስራ የሚሰራ ተቋም የለውም። እንዳውም ከአማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ውስጥ አልፎ አልፎ በግልግል ዳኝነት የመጨረስ ስራን በቋሚነት የሚሰሩ አንዳንድ ተቋማት ከመኖራቸው በስተቀር በመርህ ደረጃ ሁለቱም የአንድን ክርክር መከሰት መሰረት አድርጎ በጊዜያዊ መልኩ (*ad hoc*) በተከራካሪ ወገኖች በሚመረጡ ሶስተኛ ወገኞች የሚካሔዱ ናቸው።[50] በአዲሱ አዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀፅ 52(1)(ለ) ተከራካሪ ወገኖች በስምምነት ሊፈቷቸው ካልቻሉ "ራሳቸው በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አስታራቂነት" እልባት ሊያገኙ ስለመቻላቸው ተደንግጓል። ይህም የፌደራል አዋጅ ቁጥር 456/97 አንቀጽ 12 ከሚለው ጋር የሚጣጣምና በቀደመው የመሬት አስተዳደር ሕጎች መሰረት የሽማግሌዎች ሸንጎ በማሕበረሰብ ምርጫ ይቋቋማል የሚለውን አስቸጋሪ መስፈርት ቀሪ ያደረገ ድንጋጌ ነው።[51] በዋናነትም የሽማግሌዎች ምርጫ በተከራካሪ ወገን ፍላጎት ላይ እንዲመሰረት ማድረግ የሽምግልናውን ተቀባይነት እና ውጤታማነቱን ማሳደጉ አይቀርም። ይህ አይነቱ ድርድር ከሽማግሌዎች አመራረጥ በመለስ በፍትሐብሔር ሕጉ ላይ ስለ እርቅ ከተደነገገው ጋር በእጅጉ ስለሚመሳሰል በመሬት ህጉ ላይ ክፍተት ባጋጠመ ጊዜ እነዚህን ድንጋጌዎች መመልከት የላቀ ጠቀሜታ ይኖረዋል።[52]

በሶስተኛ ደረጃ ከሽምግልና ጋር ተያይዞ መልስ የሚያስፈልገው ጉዳይ በተደጋጋሚ በአሰራር ረገድ ከሚፈጠረው ብዥታ አንጻር አንድ ጉዳይ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ምን ጊዜም በሽምግልና ቅድሚያ መታየት ግዴታ ነው ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው። አልፎ አልፎ በፍርድ ቤቶች አሰራር በሽምግልና ያልታየ አለመግባባት ፍርድ ቤት መቅረብ እንደማይችል እና የሽምግልናውን አማራጭ ማናቸውም ተከራካሪ መሞከር እንዳለበት በመቀበል ክሳሾችን የሚመልሱበት ጊዜ ይስተዋላል።

በዚህ ዙሪያ የሕጉን ይዘት ስንመረምረው የፌደራል አዋጁ "...ክርክር ሲነሳ [ከመሬት ጋር ተያይዞ] ጉዳዩ በሚመለከታቸው ተከራካሪዎች በውይይትና ስምምነት እን[ዲ]ፈታ ጥረት ይደረጋል"[53] የሚል ነው። ይህ ጽንሰ ሃሳብም በአዲሱ የመሬት አዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀፅ

[50] ለምሳሌ ያክል የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤትን መጥቀስ ይቻላል።

[51] የፌደራል እና የክልሉ አዋጆች ሽማግሌዎቹ በተከራካሪ ወገኖች የሚመረጡ መሆናቸውን ቢያመለክቱም የክልሉ ደንብ ቁጥር 51/99 ግን በአንቀጽ 35(1) ላይ "...አለመግባባቶችን በስምምነት የመፍታቱን አሠራር ተግባራዊ ለማድረግ የቀበሌው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ከየንዑስ ቀበሌው የተውጣጡ አባላት የሚገኙበት የአካባቢ ሽማግሌዎች ሸንጐ በየሚመለከታቸው ማህበረሰቦች ምርጫ ያቋቁማል" ይል ነበር።

[52] የተሻረው አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 35 "አለመግባባት <u>ቅድሚያ</u> በሽምግልና ታይቶ በእርቅ እንዲፈታ ጥረት መደረግ <u>አለበት</u>" የሚል ይዘት ያለው መሆኑን በንዕዕር መመልከት ይቻላል።

[53] አዋጅ ቁጥር 456/97፣ አንቀፅ 12

52(1) ላይም ተደግሞ ከመሬት ጋር የሚያያዙ አለመግባባቶች "*በመጀመሪያ ደረጃ*" በስምምነት ወይም ራሳቸው በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች እልባት እንዲያገኙ (እንዲፈቱ) ይደረጋል በሚል ተደንግጓል። በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 2 ላይ በስምምነት ወይም በእርቅ አለመግባባቱ ያልተፈታ እንደሆነ ይኸው ከታወቀበት ጀምሮ በ30 ቀን ውስጥ ወደ ፍርድ ቤት ሊቀርብ ስለመቻሉ ተደንግጓል።[54] ከእነዚህ ሕጎች ይዘት ላይ "...ጥረት ይደረጋል" እና "በመጀመሪያ ደረጃ ... እንዲፈቱ ይደረጋል" የሚሉት አማራጭ የሙግት መፍቻ ተቋማትን የመጠቀም ግዴታን ዓይነት የሚያሳዩን ወሳኝ ሐረጎች ናቸው። እነዚህ ሀረጎችም የሙግት መፍቻ አማራጮችን መጠቀምን አዛዥ በሆነ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያበረታቱ ናቸው። ከዚህ ባለፈ ግን ከህግ አቀራረጽ አንፃር አስገዳጅ ሆነው መቀመጣቸውን የሚያሳዩ ተደርጎ መወሰድ የለበትም።[55]

ከላይ በሕግጋቱ ውስጥ የግዴታውን ዓይነት ይጠቁማሉ ካልናቸው ሀረጎች አንፃር ግዴታው የተጣለው በጋራ በተከራካሪ ወገኖች እና በፍርድ ቤት ላይ መሆኑን ያስገነዝባል። ተከራካሪ ወገኖች በሽምግልና ለመፍታት ጥረት ሳያደርጉ ወደ ፍርድ ቤት የሄዱ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በቀጥታ ክሱን ውድቅ በማድረግ ፋንታ ክሱን ተቀብሎ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በሽምግልና ለመፍታት የሚችሉበትን ሁኔታ በራሱ ማመቻቸት ይችላል። ነገር ግን አንድ ተከራካሪ ወገንን በማስገደድ ጉዳዩ በሽምግልና እንዲታይ ቢደረግ ለውጥ የማያመጣ መሆኑን በችሎት በአሳማኝ ሁኔታ ሊያስረዳ ይችላል። በተለይም ሽምግልናውን የሚያከናውኑት ሰዎች ብቃትና ልምድ ማነስ ወይም ከሌላኛዉ ወገን ጋር ባላቸዉ ዝምድና ወይም ቀረቤታ በሽምግልናው ሂደትና ውጤት ላይ እምነት ሊታጣበት ይችላል። እንዲሁም ተከራካሪዎች ራሳቸው በመረጡት ሽማግሌ የእርቅ ሙከራ አድርገው ሳይሳካ ቀርቶ ወደ ፍርድ ቤት የመጣ ጉዳይ ሊሆን ይችላል። ይህ በሆነበት ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት ውስጥ አልገባም በሚል መነሻ ብቻ ሥርዓቱ እንዲሟላ የሚያስገድድ ቢሆን ለደንቡ ያክል ተሞክሮ አልተሳካም ከማለት በስተቀር የሚያመጣው ሁነኛ ለውጥ አይኖርም። ለዚህም መሰረቱ አማራጭ የክርክር መፍቻ ዘዴዎች በባህሪያቸው በተደራዳሪዎች ፈቃድ ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው ነው። በአንዳንድ ጉዳዩች ላይ በሕግ ተለይቶ በተቀመጠ ጊዜ

[54] አዋጅ ቁጥር 133/98፣ አንቀጽ 29 እና ማስፈጸሚያ ደንብ ቁጥር 51/1999፣ አንቀጽ 35ን ይመልከቱ።

[55] አንዳንድ የሕግ ባለሙያዎች እንደሚሉት ድንጋጌው በራሱ አስገዳጅ አድርጎ ያስቀመጠዉ ይመስላል። ለዚህ መሰረቱም ህጉ በስምምነት ወይም በእርቅ አለመግባባቱ ያልተፈታ እንደሆነ ይኸው ከታወቀበት ጀምሮ በ30 ቀን ውስጥ ወደ ፍርድ ቤት ይቀርባል ማለቱ ይህንን የሚያጠናክር ነው የሚሉ አሉ።

በመጀመሪያ በግልግል ዳኝነት እንዲያልቅ ሕግ የሚያስገድድበት ሁኔታ ቢኖርም[56] በሽምግልና ሂደት እንዲህ አይነት ነገር የተለመደ አይደለም። በመሆኑም በሽምግልናም ቢሆን አስገዳጅ ውሳኔ የሚሰጥበት ባለመሆኑ ተከራካሪዎች (አንደኛው ብቻም ቢሆን) ፈቃደኛ ባልሆኑበት ጊዜ ማስገደዱ ምክንያታዊ አይሆንም።

ከሥነ-ሥርዓት ሕግ አኳያም[57] ሌሎች የፍትሐብሔር ክርክሮች በሚመሩበት አግባብ ክስ ሲመሰረት መዝገቡን ከፍቶ እና ተከራካሪዎችን ጠርቶ በሽማግሌዎች እንዲጨርሱ ለማግባባት ጥረት ማድረግ እና መመለስ እንዲሁም ይህ የማይሳካ በመሰለው ጊዜ ክርክሩን ማስቀጠል ተገቢነት ይኖረዋል። ፍርድ ቤቱ ተከራካሪዎች በመረጧቸው ሽማግሌዎች እንዲፈቱ በሚመልስበት ጊዜ የፍርድ ቤቱን መዝገብ ሳይዘጋ የሽምግልናውን ውጤት መጠበቅ ያለበት መሆኑን የሚጠቁም ነው። አለበለዚያ በፍርድ ቤት ሬጅስትራር በኩል ከሽማግሌዎች ለመታረቅ የሞከርክበትን ደብዳቤ አላያያዝክም በሚል ክሱን ውድቅ የሚያደርግ ከሆነ ወይም ዳኛውም ቢሆን ከፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 231 መሰረት የክሱን ብቃት ሲመረምር እርቅ አልተሞከረም በሚል ክሱን መዝጋት አይጠበቅበትም። የመሬት ጉዳይ ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ ሰዎች በሌላ ጉዳይ ክስ ከሚቀርቡ ሰዎች መድሎ መደረጉን የሚያመጣ ይሆናል።[58] ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 አንፃርም በሕግ አግባብ ሥነ-ሥርዓትን ተከትሎ የሚሰራና አስቀድሞ የተቋቋመ ፍትህ ሰጪ አካል ሳይኖር ፍርድ ቤት እንዳይቀርብ መከልከል ሕጋዊነት የለውም። ውይይትም ሆነ ሽምግልና የሚለውን ቃል ለመናገር ቀላል ሲሆን በተግባር ሲታይ በአለመግባባት ጊዜ የሚጠቅም ስምምነት ላይ ለመድረስ የመደራደር ብቃት ከፍተኛ መሆንን የሚጠይቅ ነው። ይህን ከባድ መስፈርትም በቅድመ-ሁኔታነት እንዲያሟላ ማስገደድም ለምልልስና ለወጪ የሚዳርግ አሰራር ስለሚሆን አቅመ-ደካማ አርሶ-አደር የማህበረሰብ ክፍሎችን እንዳይጎዳ የፍትህ አካላት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል።

የመሬት አዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀፅ 52(1) አለመግባባቱ በስምምነትም ሆነ በሽምግልና ሊፈታ ያልቻለ እንደሆነ በስምምነት የመፍታቱ ጥረት ከተቋረጠበት ቀን ቀጥሎ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው ወረዳ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይቻላል የሚል ድንጋጌ

---

[56] ለምሳሌ ያክል የፍ/ሕ/ቁ/ 461(1)(ለ) በዘመድ ዳኛ ለመጨረስ የሚያስገድድ ሕግ ሊኖር እንደሚችል ይጠቁማል።

[57] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 276 እና ተከታይ ድንጋጌዎች በፍርድ ቤትና ከፍርድ ቤት ውጭ ውሉ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ እስካልሆነ ድረስ በስምምነት መጨረስ ይቻላል የሚለውን ማጤን ይገባል።

[58] የኢፌዲሪ ሕገ መንግስቱ አንቀፅ 25 የእኩልነት መብት መጠበቅ አለበት። መብት ለማስፋት በሚል የሚወጣ ሕግ መብቱን በሚያጣብብ አግባብ መተርጎምም አይገባም።

አስቀምጧል።[59] 30 ቀናት የተቀመጠው ምንን ለማመልከት ነው? እንዲሁም ይህን የጊዜ ገደብ አለማክበር ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። ከላይ የተጠቀሰው ሕግ በራሱ ያስቀመጠው ውጤት የለም። ስለሆነም ከፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ እና ሌሎች ሕጎች[60] በመነሳት አመክንዮ ባለው መልኩ ምላሽ መስጠት ይገባል። ከፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ አንፃር ስንመለከተው ለዚህ ጉዳይ ቀረቤታ ያለው ሀሳብ ክስ ከመቅረቡ በፊት ያለውን ሂደት የሚመለከት በመሆኑ 30 ቀን የሚለው መነሻወር ያለበት ከይርጋ ሕግ ወይም ከይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ከሚለው ጽንሰ ሀሳብ ጋር ነው። ይህ ሀሳብም በአዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀጽ 55 መሰረት በወረራና በሕገ-ወጥ መንገድ መሬትን መያዝ ይርጋ የለውም የሚለውን ጽነሰ ሀሳብ ውጤት በሚያሳጣ እና እጅግ ባጠረ ጊዜ ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብን ለመገደብ መሞከር የሕግ ፍልስፍና ድጋፍ የለውም። በስምምነት ለመጨረሰ ካልሞከረው ይልቅ በሞከረው ተከራካሪ ላይ ግዴታን የሚያከብድ የሕግ ገደብም ማስቀመጥ የአሰራሩን ተመራጭነት የሚቀንሰው ይሆናል። እንዲሁም ግልፅነት የሚጎድለው አሰራርም ይፈጥራል። ይግባኝም ቢሆን ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሁለት ወይም በሶስት ወር ማቅረብ እንደተጠበቀ ሆኖ በሽምግልና የተሞከረ በመሆኑ ብቻ የይግባኝ ጊዜውን ማሳጠርም አይገባም።[61] በግልግል ዳኝነት መጨረስም በመሬት ክርክር የተፈቀደ ባለመሆኑ በስምምነትና እርቅ ይግባኝም የለም።[62] በመሆኑም የ30 ቀን መስፈርቱ ሲታይ የድንጋው ይዘት ፈቃጅ በመሆኑ ክርክር ካለ በፍጥነት መፍትሔ ማግኘት የህጉ ፍላጎት በመሆኑ ግፊት ያደርጋል የሚለውን ብቻ መረዳት ይገባል። በሌላ አግባብ ደግሞ የ30 ቀን ጊዜ ገደብ መቀመጥ አንድ ጊዜ ቢያንስ በእርቅ ለመጨረስ የተሞከረን ጉዳይ ከተሞከረ በኋላ 30 ቀን ካለፈው ድጋሜ በሽምግልና ለመጨረስ የግድ ይሞከር የሚለውም ተቀባይነት የሌለው ትርጉም ይሆናል።

---

[59] ደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 35 ይመልከቱ። ይህ ጉዳይ የመጨረሻ መሆኑ በአዲሱ አዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀጽ 52(3) ላይም በድጋሜ በአዋጅ ደረጃ እውቅና ያገኘ ፅንሰ ሃሳብ ነው።

[60] ለምሳሌ ያክል ከላይ የተጠቀሰዉን የቤተሰብ ሕግ ንጽጽር ብንወስድ የመፋታት ሀሳባቸዉን እንዲተዉ የማሰላሰያ ጊዜ የተሰጣቸዉ ባልና ሚስት በመፋታት ሀሳባቸዉ የጸኑ ከሆነ የማሰላሰያ ጊዜዉ ካለቀበት ቀን ጀምሮ በሚቀጥሉት ስድስት ወራት ዉስጥ የመጀመሪያዉን መዝገብ ማንቀሳቀስ ሲችሉ ከዚያ በኋላ ግን አዲስ የፍች ጥያቄ ካልሆነ በስተቀር በመጀመሪያው መዝገብ መቀጠል አይችልም። ይህ ንጽጽር የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ላይ ተመስርተን ለደረስንበት መደምደሚያ ማሳያ ነው።

[61] እንደ አጋጣሚ ሆኖ ከዚሁ ጋር የሚጣጣም ለመሬት ክርክር ከወረዳ ፍርድ ቤት ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረቢያው 30 ቀን መሆኑን እናገኛለን።

[62] በግልግል ዳኝነት የሚሰጥ ውሳኔ በይግባኝ ሊታይ ስለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 350 ያመለክታል። በመሬት ላይ በገላጋይ ዳኛ አስገዳጅ ውሳኔ ቢሰጥ በዚህ አግባብ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት በማቅረብ ማሳረም እንደሚቻል ሕጉ ያሳየናል። ለዚህም የመሬት ጉዳይን የወረዳ ፍርድ ቤት በብቸኝት ስለሚመለከት ጉዳዩ አንድ እርከን ከፍ በሚል እንዲታይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 352 ስለሚያስገነዝብ ለወረዳ ፍርድ ቤት ይቀርባል የሚለውም ተቃርኖ የሚታይበት ነው።

በአራተኛ ደረጃ ከሽምግልና ጋር በተያያዘ የምንመለከተው ጉዳይ ሽምግልናው ተካሂዶ የተሳካ ቢሆን የሚያስከትለው ውጤት ምን መሆን አለበት የሚለው ነው። የመሬት ጉዳይ በግልግል ዳኝነት መወሰን የማይቻል መሆኑን ቀደም ሲል ተመልክተናል። ሌላው ግን በሕጉ የተፈቀደው ሽምግልና ከተሳካ ለአለመግባባቱ የመጨረሻ እልባት የሚሰጥ ነው። ሽማግሌዎች አስገዳጅ ውሳኔ የሚሰጡ ሳይሆን ተከራካሪ ወገኖች ስምምነት ላይ እንዲደርሱ የሚያደራድሩ ናቸው። የመጨረሻው ሕጋዊ ተግባር ተከራካሪዎች የሚደርሱበት የስምምነት ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1729-30 ባለው የአጻጻፍ ሥርዓት (ፎርም) አግባብ ሲስማሙበት ነው። ይህ ስምምነትም በተዋዋይ ወገኖች በዚሁ ሕግ ቁጥር 1731 በተዋዋይ ወገኖች መካከል ሕግ ነውና ማስገደዱ ተገቢነት አለው። በባለጉዳዮች ስምምነት ላይ ተመስርቶ ሽማግሌዎች በፈቱት አለመግባባት ላይ አዲስ የፍትሐብሔር ክስም ሆነ ይግባኝ ሊቀርብበት እንደማይችል ሕገ ሳይንሱ የሚነግረንም ለዚሁ ነው።[63]

ከዚህ ላይ ሳይነሳ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ የመሬት ክርክር በባለጉዳዮች ፍላጎት እንዲያልቅ በመፈለግ ወይም ወደ ፍርድ ቤት እንዳይመጣ በመፍራት የመሬት ህጉን ዓላማ ሊያዛባ ከሚችል ሁኔታ ላይ እንዳይወድቅ ለማድረግ በቂ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ተከራካሪ ወገኖች በመሬት ሕጉ ላይ ያሉ አስገዳጅ ድንጋጌዎችን ሁሉ በሚጥስ መልኩ በተለይም መሬትን በሕገ-ወጥ መልኩ የማስተላለፍ ውጤት ያለው ስምምነት ቢያደርጉ መቀበል አይገባም። ይልቁንም እንዲህ ዓይነት ሕገ-ወጥ ተግባር እንዳይከናወንና አርሶ አደሮች ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብታቸውን ለመጠበቅ ሲባል የፍትሐብሔር ሕግ ማዕቀፍ ውስጥ የውል ይፍረስልኝም ሆነ ውል ይፈፅምልኝ የሚለውን የውል ሕግ ዕነሰ-ሀሳብ ተፈፃሚ ማድረግ ይገባል።[64] በተጨማሪም በውል ሕግ መሰረት የውል አደራረጉ የፈቃድ ጉድለት ካለበት በባለጉዳዮች አቅራቢነት አይፈርስም ወይም የተደረገበት አግባብ ሕግና ሞራልን የሚቃረን ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1808 መሰረት በፍርድ ቤት እንዲፈርስ ማድረግ አይገባም ማለት አይሆንም። አለበለዚያ የተከራካሪ ወገኖች ሙግትን ለመፍታት በሚል ምክንያት ብቻ ስምምነታቸው

[63] የፍ/ብ/ቁ/ 3312 እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 244 የሆነውን ድንጋጌ በጣምራ ንባብ ይመልከቱ።

[64] ለምሳሌ በሥጦታ ወይም በኑዛዜ የገጠር መሬት የሚተላለፍበት ሁኔታ የሕግ ገደብ አለው። ሆኖም ሁለት ግልሰቦች ክርክር አለን በሚል ቁጭ ብለው በበቂ ደመወዝ በመንግስት ሥራ የተቀጠረ ሰው መሬቱን እንዲጠቀም ቢስማማ ምንም ዓይነት ክርክር አይቀርብበትም በሚል መቀበል ሕገ ወጥ ውል ባልታሰበ ሁኔታ ሕጋዊ ሽፋን መስጠት ስለሚሆን ለወደፊት በመሬት ሕጎች ውስጥ መፍትሔ ማሰላሰሉ ተገቢነት ይኖረዋል። ይልቁንም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 277 መሰረት ውሎች በፍርድ ቤት ሲፀድቁ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆናቸው በሚመረመርበት አግባብ ህጋዊነቱ የሚታይበትን ዕድል መፍጠር ተገቢ ነው። ከዚህ ባለፈ ስምምነቶችስ በመሬት አስተዳደር ማዕደቅና ምዝገባ ሳይከናወን ተፈጻሚነታቸው እንዴት ይታያል የሚለውም ገና ያልተፈተሸ ጉዳይ በመሆኑ አብሮ መዳሰሱ ተገቢ ነው።

በፍትሐብሔርም ሆነ በወንጀል አያስጠይቅም ከተባለ የመሬት መብት የሚተላለፍባቸውን ቅድመ-ሁኔታዎች በሕግ ማስቀመጥን በተዘዋዋሪ መንገድ ዋጋ የሚያሳጣ አሰራር ይሆናል።

በመጨረሻም በሽምግልና የተፈታ የመሬት ክርክር በወረዳ ፍርድ ቤት ቀርቦ በቀጥታ እንደፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፈፀም ስለመቻሉ ማየት ያስፈልጋል። ውል እንደ ፍርድ ቤት ውሳኔ ያለቀለት ጉዳይ አይደለም። በሽምግልናም ሆነ በውይይት የሚደረገው ስምምነት በመጨረሻ የሚይዘው የውል ቅርፅ ነው፤ ውጤቱም የውል ከሆነ እንደ ውሉ አልተፈፀመልኝም የሚል ሰው የውል አለመፈፀም ውጤቶች የሆኑትን አስገድዶ ማስፈፀም፣ ውልን መሰረዝ እና ለደረሰበት ጉዳት ካሳ መጠየቅ የሚቀሩ አይሆንም።[65] ስለሆነም የመሬት ሕጉ በስምምነት መጨረስ ያለቀለት ነው በሚል ሙሉዕ መስሎ መቅረቡ አሁንም ተቃርኖ የሚታይበት ነው ማለት ይቻላል።[66]

በአጠቃላይ በሽምግልና የተገኘው የእርቅ ውጤት ከመሬት ሕጉ በተጨማሪና በተሟላ መልኩ በፍትሐብሔር ሕጉ[67] እና በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ[68] ላይ ስለ ግልግል (compromise) በጠቅላላው በተደነገጉት ሕጎች የሚመራ ነው ለማለት ይቻላል። በመሆኑም ማሕረሰባዊ ግጭትን ለመቀነስ ሲባል ይህን በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የክርክር አፈታት ሥርዓት አርሶ አደሮች በቀላል ሁኔታና ሕግን ሳይቃረኑ ተገንዝበውት እንዲጠቀሙበት ማብቃትና የሕግ ጥበቃም ማድረግ ጠቃሚ ነው።

3.2 በአማራ ክልል የገጠር መሬት ሙግት በመሬት አስተዳደር አካላት የሚፈታበት አግባብ

በአሁኑ ሰዓት አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በአስተዳደር አካላት እንዲታዩ ማድረግ ከጥያቄ የማይገባ ጉዳይ እየሆነ የመጣ ይመስላል። ይልቁንም እነዚህ አካላት ተቋማዊ አደረጃጀታቸው ምን መሆን አለበት? በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ መለስተኛ የዳኝነት ስልጣን ሊሰጣቸው ይገባል? በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚከተሉት ሥነ-ሥርዓት ምን መምሰል አለበት? በአስተዳደር አካል የተሰጠ ውሳኔን በመደበኛ ፍርድ ቤት እንዴት ሊታረም ይችላል? በሚሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ይደረጋል።

---

[65] የፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1677 እና 1771-1805

[66] በመሬት ጉዳይ የግልግል ዳኝነት ያልተፈቀደ በመሆኑ የግልግል ዳኝነትን ይግባኝ ሥርዓት መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም።

[67] የፍ/ሕ/ቁ 3307-3317 ያሉትን ይመልከቱ።

[68] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 274-280 ያሉትን ይመልከቱ።

3.2.1 የአስተዳደር አካላት ውሳኔ ምንነት መነሻ ጽንሰ-ሃሳብ

አስተዳደር አካላት የሚለው አነጋገር ከሦስቱ የመንግስት አካላት የስራ አስፈጻሚ አካላትን በጥቅሉ የሚወክል ነው።[69] የአስተዳደር አካላት አስተዳደራዊ ሥራዎችን ሲያከናውኑ መመሪያ የማውጣት ሥልጣን (rule making) እና ከአስተዳደራዊ ሥራ ጋር በተያያዘ መለስተኛ ዳኝነት ስልጣን (quasi-judicial /administrative adjudication) ይኖራቸዋል።[70] በዚሁ መሰረት የአስተዳደር አካላት መለስተኛ የዳኝነት ሥራ ካለቸው ከማስፈፀም መደበኛ ሥራቸው የሚለይበትን መስፈርት ማስቀመጥ ይገባል። የመጀመሪያው አስተዳደራዊ ውሳኔው የአንድ ሰው ወይም ቡድን መብት እና ግዴታን የሚመለከት ውሳኔ መሆን አለበት።[71] ለምሳሌ ያክል በእንግሊዝ ህግ መሰረት የህዝባዊ ተቋማት ውሳኔ (public authorities decision) ማለት በዋናነት አንድን ሰው ወይም ቡድን በቀጥታ የሚመለከት ጉዳይ ሲሆን ነው ይለዋል።[72] በዚህ አተረጓጎም መሰረት አንድ የአስተዳደር አካል የሚያወጣቸው ፖሊሲዎች እና እስትራቴጅዎች፣ ሪፖርቶች እና የሚሰጣቸው አስተያየቶች አንድን ሰው ወይም ቡድን በቀጥታ ስለማይመለከቱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ቢሆኑም እንኳ አስተዳደራዊ ውሳኔ አይባሉም ማለት ነው። ሁለተኛው አስተዳደራዊ ውሳኔው ላይ ለመድረስ መደበኛ ወይም ኢ-መደበኛ ሥነ-ሥርዓትን መከተልን የሚጠይቅ መሆኑ ነው። ብዙውን ጊዜ የአስተዳደር አካላት ከአንድ ውሳኔ ለመድረስ ይብዛም ይነስም ማስረጃን ተቀብሎ መስማትን (hearing) እና ፍሬ ነገርን ከህግ አንፃር መመዘን ይጠበቅባቸዋል። ሶስተኛው የአስተዳደር አካሉ ከውሳኔው ለመድረስ አስቀድሞ የነበረን ቢያንስ የአስተዳደር አካሉን ማቋቋሚያ ሕግ የአሰራር ሥርዓት እንደ መስፈርት መጠቀምና መተርጎም መቻሉ ነው። እነዚህ ሶስት መስፈርቶች በጣምራ ተሟልተው ከተገኙ በአስተዳደር

---

[69] Mohamed Abdo, Administrative law (2010) teaching text prepared under the auspice of NUFFIC PROJECT, ገፅ 5 (ከዚህ በኋላ *መሀመድ አብዶ፣ የአስተዳደር ሕግ* ተብሎ የሚጠራ)

[70] See Types of Administrative Agency Action: Rulemaking, Adjudication, Investigation- See more at:http://administrativelaw.uslegal.com/three-types-of-administrative-agency-action-rulemaking-adjudication-investigation/ (accessed on 26/02/2014) በዚህ ፅሑፍ ውስጥ ከሰፈረው ሀሳብ ላይ የአስተዳደር አካላት ዝርዝር ደንቦችን ሕግ አወጣጥ ሥርዓት መሰረት ያወጣሉ። ይህም ሳይንሳዊ ሙያ የሚጠይቅ፣ ዝርዝር ቁጥጥር ለማድረግ እና የኢንዱስትራላይዜሽን ልዩ ሙያዊ ችሎታዎችን ለማሳደግ ነው። እነዚህ የአስተዳደር አካላት ሕግ ሲያወጡም ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ያገናዘበ ሊሆን ይገባል። ፅሁፉም እንደሚለው አስተዳደራዊ ሥልጣን በሕግ አውጪውም ሆነ በዳኝነት ተቋሙ የማይታይን ቅሪት የመወሰን ሥልጣን (residual power) አላቸው ለማለት ይቻላል።

[71] አስተዳደራዊ ውሳኔ አንድ የአስተዳደር አካል ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜ የውሳኔ ቅርፅ ሳይዝም ጭምር የሚወሰንበት አግባብ ሊወሰን መቻሉን የሚነግረን ፅሑፍ The Free Dictionary, Administrative Agency, http://legaldictionary.thefreedictionary.com/Administrative+Agency, accessed on 26/02/2014.

[72] የግርጌ ማስታወሻ 69፣ ገፅ 144

አካሉ የተሰጠው ውሳኔ በመለስተኛ የዳኝነት ሥራው አስተዳደራዊ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን አለው ለማለት ይቻላል።[73]

በመሬት ባለይዞታዎች መካከል ከሚነሱት አለመግባባቶች ውስጥ ቀላል የማይባሉት የአስተዳደር አካላት በዕለት ከዕለት የስራ እንቅስቃሴያቸው የሚወስዷቸዉ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ጋር የተያያዙ ናቸው። የአስተዳደራዊ ውሳኔዎች በባህሪያቸው ልዩ እውቀት፣ ችሎታን እና የማጣራት ዘዴን መሰረት ባደረገ መልኩ የሚወሰዱ እርምጃዎች በመሆናቸው አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በመደበኛ ፍርድ ቤት ውጤታማ ላያደረጋቸው ይችላል።[74] እንዲሁም መደበኛ ፍርድ ቤቶች ሙግት ሲመሩ ጥብቅ የሆነ ሥነ-ሥርዓትን ስለሚከተሉ ለመሬት ክርክር በተፈለገው ፍጥነት እልባት ለመስጠት ስለማያስችል የአስተዳደር አካላትን ስራ እንደሚያስተጓጉል ብዙዎች ይስማሙበታል።[75] በመሆኑም የመሬት ክርክርን እልባት ለመስጠት ሲባል የአስተዳደር አካላትን ሚና ማስወገድ ከባድ ያደርገዋል።

በሌላ መልኩ ደግሞ የአስተዳደር አካላት መለስተኛ የዳኝነት ሥልጣን አላቸው ሲባል ሁሉንም ጉዳይ ይመለከታሉ ማለት አይሆንም። ይልቁንም የአስተዳደር አካላት የሚሰጡበት ውሳኔ ከማስፈፀም ስራቸው ጋር የተገናኘ እንዲሆን ገደብ መኖሩን የሚያሳዩን ምክንያቶች አሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ውሳኔ (እልባት) የሚያስፈልገው አለመግባባት ውስጥ ካሉት ወገኖች ቢያንስ አንደኛው የአስተዳደር አካል መሆን አለበት። በሁለተኛ ደረጃ አለመግባባቱ የተከሰተበት ጉዳይ የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ በሕግ ከተጣለበት የማስፈፀም ኃላፊነት ጋር የተያያዘ መሆን አለበት።[76] ከዚህ ውጭ አንድ የአስተዳደር አካል በውል ወይም ከውል ውጭ በሚመጣበት ሀላፊነት እንዲሁም በግለሰቦች መካከል በሚነሳ አለመግባባትን ሁሉ የአስተዳደራዊ ዳኝነት ስልጣን (adjudication power) አይኖረውም።

በአስተዳደር አካላት የሚሰጥ አስተዳደራዊ ውሳኔ የመጨረሻ እልባት ሊሆን ይችላል ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው። የአስተዳደር አካል ውሳኔ ሲሰጥ እንደ ፍርድ ቤት ነፃና ገለልተኛ በሆነ አግባብ ፍትህ የመስጠት አቅማቸው ጥያቄ የሚያስነሳ በመሆኑ በብዙ ሀገሮች የተወሰደው አማራጭ በአስተዳደር አካላት የሚሰጡት ውሳኔ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች በመጨረሻ

---

[73] Peter Cane, An Introduction to Administrative Law, Clarendon Press, Oxford, 3rd ed.,1996፣ ገፅ 18 ላይ እንደተመለከተው የፍርድ ቤት ውሳኔ የሚባለው አንድ ፍሬ ነገርንም ሆነ የሕግ ክርክርን የሚቋጭ ሌላ የሚያዕድቅ አካልን ሳይጠብቅ ያለቀለትና አስገዳጅ የሆነ ውሳኔ ሲሆን ነው።

[74] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 103

[75] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 102

[76] የግርጌ ማስታወሻ 69፣ ገጽ 142

የሚታይበትን እድል መፍጠር በብዛት ይስተዋላል።[77] ይሁን እንጅ በመጀመሪያ አንዳንድ እንደ ፈረንሳይ አይነት ሀገሮች የአስተዳደር አካል የሚሰጡት ዳኝነት መደበኛ ፍርድ ቤት መቅረብ ሳያስፈልገዉ የመጨረሻ እንዲሆን የሚያደርጉ አሉ።[78] ሌሎች ደግሞ የጉዳዩን አይነት መሰረት በማድረግ እንደሁኔታው በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ብቻ የመጨረሻ እልባት የመስጠት ስልጣን ሲኖራቸው በሌሎች ጉዳዮች ደግሞ በመደበኛ ፍርድ ቤት የመጨረሻ እልባት እንዲያገኙ ያደርጋሉ።[79] ሶስተኛ አማራጭም በክርክሩ ውስጥ የፍራ-ነገር እና የሕግ ትርጓሜ የሚያስፈልገውን ጭበጥ በመለየት በመጀመሪያው ጉዳይ ላይ የአስተዳደር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የመጨረሻ እልባት ሲሆን በሁለተኛው ጭብጥ ላይ ብቻ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ዳኝነት እንዲያገኝ የሚደረግበትን አሰራር የሚከተሉበት ሁኔታ መኖሩን መገንዘብ ይቻላል።[80] ይህን ፅነሰ ሀሳብ ታሳቢ ባደረገ መልኩ በመቀጠልም የአማራ ክልል መሬት አስተዳደር አካላት በመሬት ላይ የሚከተለውን የውሳኔ አሰጣጥ ሁኔታ እንመለከታለን።

3.2.2 የአማራ ክልል መሬት አስተዳደር የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓትና የውሳኔው ወሰን

በአዋጅ ቁጥር 252/09 መሰረት የአማራ ክልል መሬት አስተዳደር ተቋም ተግባራት እንደ አብዛኛው የአስተዳደር አካላት በሶስት የሚከፈል ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 60 ህግ የማውጣት ስልጣን፣ በአንቀጽ 21 የማስፈጸም ስልጣን እንዲሁም በአንቀጽ 52(6) የዳኝነት ስልጣን መሰጠቱን ያሳያል። በክልሉም መሬትን በበላይነት የሚያስተዳድረው የአማራ ብሔራዊ ክልል የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ ነው።[81] በሥሩም በየደረጃው የዞን መሬት አስተዳደር፣[82] የወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት፣[83] የቀበሌ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ፅ/ቤት[84] እና የንዑስ ቀበሌ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ የሚባሉ አካላት በሥልጣን

---

[77] ዝኒ ከማሁ፣ ገፆች 140-143.

[78] Peter Leyland and Terry Woods, Text Book on Administrative Law, Oxford University Press, 4th ed, 2002, ገፅ 233

[79] ዝኒ ከማሁ

[80] የግርጌ ማስታወሻ 73፣ ገፆች 111-128። በኢትዮጵያም እንዲህ ዓይነት አዝማሚያ የሚያሳዩ አዋጆች አሉ። በአማራ ብሔራዊ ክልል የተሻሻለው መንግስት ሰራተኞች አዋጅ፣ 2010፣ አዋጅ ቁጥር 253፣ ዝክረ ሕግ ጋዜጣ፣ 22ኛ ዓመት፣ ቁጥር 14፣ ከአንቀፅ 78 ጀምሮ እንደተደነገገው የአስተዳደር ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ በሕግ ጉዳይ ላይ ብቻ በሰበር እንዲታረም ለፍርድ ቤት ሥልጣን ይሰጣል።

[81] አሁን ላይም አዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀፅ 46 የገጠር መሬት አስተዳደር ቢሮ መሬትን በማስተዳደር በኩል እውቅና ተሰጥቶታል። በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 47 ላይ የዞን መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መምሪያም ድርሻ አለው።

[82] አዋጅ ቁጥር 252/09፣ አንቀፅ 47

[83] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 48

[84] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 49

ተዋረድ ተዋቅረዋል።[85] እንዲሁም በደንብ ቁጥር 159/2010 አንቀፅ 17 እና 18 መሰረት የቀበሌ ገጠር መሬት አስተዳደር አጠቃቀም ግብረ-ኃይል እና የቴክኒክ ኮሚቴ ተዋቅረዋል። ከዚህ በተጨማሪም የወረዳ መሬት አስተዳደር ፅ/ቤት፣[86] የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤቶች[87] እና ሌሎችም መስሪያ ቤቶች[88] ለመሬት ሕግ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ ተጥሎባቸዋል። እነዚህ በርካታ የአስተዳደር አካላት የተሰጣቸው ኃላፊነት ወጥ በሆነ መልኩ መፈፀም መቻላቸው ለመልካም አስተዳደር መስፈንና ደረጃውን ጠብቆ አስተዳደራዊ ማስተካከያ ለማድረግ የራሱ የሆነ አስተዋፅዖ ይኖረዋል። እንደየተግባራቸው መዋቀራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የተቋማቱ መብዛት ለቁጥጥርና ስህተት ቢኖር ለመተራረም የሚያስችግር ሊሆን መቻሉን ግን መገመት አያዳግትም።

በኢትዮጵያ የአስተዳደር ፍርድ ቤቶች ለማቋቋምና ወይም አስተዳደራዊ ውሳኔ ለመስጠት ሕገ መንግሥታዊ የሕግ ማዕቀፍ አለ ለማለት ይቻላል።[89] በዚህ መሰረትም በሀገራችንም ከግብር፣ ከሥራ ቅጥር እና በመሳሰሉት ውሱን ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ራሳቸውን የቻሉ የአስተዳደር ፍርድ ቤቶች የተቋቋሙ ቢሆንም በስፋት እና በተጠናከረ መልኩ እነዚህ ተቋማት አሉ ለማለት አይቻልም።[90] የአስተዳደር አካላትን የሚያቋቁሙ ሕጎችም የሕግ ክርክር ከተነሳ በፍርድ ቤት በይግባኝና በሰበር ቀርበው እንዲታረሙ የሚያስችል አሰራር ይዘረጋሉ።[91] ምንአልባት የአስተዳደር ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ነክን ጉዳይ በመጨረሻ የመወሰን ስልጣን ቢሰጣቸው እንኳ የሰጡት ውሳኔ የሕግ ስህተት ካለበት በክልልና በፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎቶች መታየትን የሚያስቀር መሆን የለበትም።[92]

በአማራ ክልል መሬትን በሚመለከት በርካታ ተቋማት የመዋቀራቸውን ያክል ራሱን ችሎ የተቋቋመ ልዩ የመሬት አስተዳደር ፍርድ ቤት ቅርፅ የያዘ ተቋም የለም። ነገር ግን በውስን ጉዳዮች ላይ ብቻ የተቋቋሙ ኮሚቴዎች አሉ። ለምሳሌ መሬትን ለህዝብ ጥቅም ከማስለቀቅ እና ካሳ (expropriation compensation) ጋር በተያያዘ እንደሁኔታው የሚቋቋም የካሳ ቅሬታ

[85] አዋጅ ቁጥር 252/09፣ አንቀፅ 50(2)
[86] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 26(3)
[87] ደንብ ቁጥር 159/2010፣ አንቀፅ 31
[88] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 36
[89] የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት፣ አንቀፅ 79
[90] የግርጌ ማስታወሻ 69፣ ገፅ 104
[91] አዋጅ ቁጥር 253/2010፣ አንቀፅ 80(5)
[92] በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት፣ አንቀፅ 79(1) ላይ "በፌደራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው" በሚል ተደንግጓል። በዚሁ ሰነድ ላይ አንቀፅ 80 የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌደራል ጉዳዮች ላይና የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ በክልል ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻ ስልጣን ያላቸው መሆኑ ተደንግጓል።

አጣሪ ጉባኤ እንደሚኖር ይደነግጋል።[93] በዚህ የካሳ ቅሬታ አጣሪ ጉባኤ ቅር የተሰኘ ሰው ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል በሚል ተደንግጓል። በክልሉ መሬትን በመለካት እና በመመዝገብ ሂደት ባለይዞታዎች በአዋሳኝ ያልተስማሙ እንደሆነ የቀበሌዉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ማስረጃ በመሰብሰብ ውሳኔ እንደሚሰጥ ይደነግጋል።[94] በመሆኑም ከመሬት ጋር በተያያዘ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ብቻ የአስተዳደር ፍርድ ቤት መሰል ተቋም አለ ለማለት ይቻላል።

በሌሎች ጉዳዮች ላይ የመሬት አስተዳደር አካላት አስተደደራዊ ውሳኔ የሚሰጡ መሆኑን ግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው። ሆኖም በአዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀፅ 52(8) መሰረት የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ ሰጪነት ከፍርድ ቤት ውሳኔ ሰጪነት ጋር በእኩል ሚዛን ላይ ማስቀመጡ ምን ዓይነት ውሳኔዎችን ነው የሚለው ግልፅ አይደለም።[95] እንዲሁም በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 6 መሰረት በአስተዳደር አካል የመሬት ክርክር እልባት መስጠት ስለመቻሉም ተደንግጓል። በመሆኑም የአብክመ መሬት አስተዳደር አካላት የሚሰጡት ውሳኔ የግለሰብ ወይም የቡድን መብቶችን የሚነካ ከሆነ፣ ከውሳኔ ለመድረስ ሥነ-ሥርዓትን የሚከተሉ ከሆነና ለውሳኔ አሰጣጡ ቀድሞ የተቀመጠ ሕግን መሰረት አድርገው የሚሰሩ ከሆነ ከላይ በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ በተመለከተው መሰረት መለስተኛ የዳኝነት ሥልጣን እንዳላቸው ግምት መውሰድ ይቻላል። በክርክሩ ውስጥም አንደኛው ተከራካሪ ራሱ መስሪያ ቤቱ ስለሚሆን ለመስፈርቱ ቅርበት አላቸው። በመሆኑም ከላይ ለአስተዳደራዊ የዳኝነት ስልጣን በተሰጠው ትርጓሜ መሰረትም የአብክመ መሬት አስተዳደር ተቋማት ሰፊ አስተዳደራዊ የዳኝነት ስልጣን መኖሩን ከዝርዝር የክልሉ የመሬት ሕግ ማዕቀፍ መረዳት ይቻላል።

የአማራ ክልል የመሬት አስተዳደር አካላት የአስተዳደራዊ የዳኝነት ስልጣን ወሰን (scope of adjudicatory power) ስንመለከት በየደረጃዉ የሚገኙ የአስተዳደር ተቋማት መዋቅሮች የራሳቸው ድርሻ ያላቸው ሲሆን በጥቅሉ ሲታይ ግን በአብዛኛው መሬትን ማስተዳደር በሚል የተገለጹ ናቸው። በአዋጅ ቁጥር 252/09 በአንቀጽ 2(44) መሰረት "አስተዳደራዊ ውሳኔ" ለሚለው ትርጉም ሲሰጥ፡-

[93] አዋጅ ቁጥር 252/09፣ አንቀጽ 26

[94] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 38 መሰረት የተዋሳኝ መሬቶች ድንበር በተቻለ መጠን በአዋሳኝ ባለይዞታዎች የጋራ ስምምነት መወሰን ይኖርበታል።

[95] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 52(6) በግልጽ በአዋጅ ደረጃ እውቅና ተሰጥቶታል።

"አስተዳደራዊ ውሳኔ" ማለት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ባለጉዳዮች፣ በይዞታ መብትና መጠቀም ጥያቄ ሲያቀርቡ ወይም በተቃራኒው ግዴታቸውን ሳይወጡ ሲቀሩ አግባብነት ያላቸውን የመረጃ ምንጮች በመጠቀምና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በሕዝብ በማስተቸት ጉዳዩ በሚመለከተው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አካል ከተጣራ በኋላ በጽሁፍ የሚሰጥ ማናቸውም ውሳኔ ሲሆን ከገጠር መሬት ልኬታ፣ ምዝገባ፣ ከይዞታ ደብተር አሰጣጥ፣ ከመሬት አጠቃቀም እቅድ፣ ከይዞታ መታጣትና ሌሎች ተዛማጅ እርምጃዎች ጋር በተገናኘ የሚተላለፉ ትዕዛዞችን ያጠቃልላል። **የሚል ነው።**

ከዚህ ትርጉም ጋር በሚጣጣም መልኩም የመሬት አስተዳደር አካላት በመሬት ሕግ ማዕቀፉ ውስጥ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ውስጥ የመሬት እደላ ማካሄድ፣ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ማዘጋጀትና መስጠት፣ በይዞታ መሬት ላይ የሚከናወኑ እንደ ኪራይ ያሉ የመብት ማስተላለፍን (ግብይቶችን) መመዝገብ፣ የመሬት ስጦታ እና ውርስ ማስተላለፍና መመዝገብ፣ የመሬት ባለይዞታዎችና ተጠቃሚዎች በሕግ የተጣለባቸውን ግዴታ እየተወጡ ስለመሆናቸው መከታተልና ግዴታቸውን ባልተወጡት ላይ ደግሞ ይዞታን እስከ መንጠቅ የሚደርስ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን መውሰድ፣ የመሬት ይዞታ ከግል ወደ መንግስት ይዞታ የሚዞርባቸው ሁኔታዎችን ተከታትሎ ማስፈጸም እና የመሳሰሉትን ጉዳዮችን መወሰን ተጠቃሾች ናቸው።[96]

የመሬት አስተዳደር አካላት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚከተሉት ሥነ-ሥርዓት ከላይ ከተመለከትነው የአዋጁ "የአስተዳደራዊ ውሳኔ" ትርጉም ፍንጭ ይሰጣል።[97] **የመሬት አስተዳደር አካላት አስተዳደራዊ ውሳኔ ሲሰጡ ምን አይነት ሥነ-ሥርዓት መከተል አለባቸው የሚለውን ጥቅል በሆነ አግባብ ማስቀመጡን ያሳያል። በተለይም የአስተዳደር አካላት ውሳኔ ሲሰጡ ማስረጃ ማሰባሰብ ያለባቸው እና ውሳኔውንም በፅሁፍ ማሳወቅ እንደሚገባቸው ሲታይ የአስተዳደር አካላት መለስተኛ የዳኝነት አካላት እንደሆኑ የሚያመለክት ነው።**

የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን ለመደንገግ የወጣው የሕግ ማዕቀፍ ከላይ ከተሰጠው ትርጉም በተጨማሪ የአስተዳደር አካላትን ሲያቋቁም የአስተዳደር አካላት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ሊከተሏቸዉ የሚገቡትን ሥነ-ሥርዓቶች በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ

[96] አዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀጾች 17፣ 24፣ 33(5)፣ 35(8)፣ 38፣ 42፣ 43፣ 47፣ 48 እና 50(1)"ን" ይመልከቱ።

[97] የግርጌ ማስታወሻ 69፣ ገፅ 32። በኢትዮጵያ ከ1950ዎቹ ጀምሮ የአስተዳደር አካላት ውሳኔ አሰጣጥ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ለማውጣት የሕጉ ረቂቅ (draft) ተዘጋጅቶ የነበረ ቢሆንም እስካሁን ድረስ አልጸደቀም።

በዝርዝር ሕጉ ውስጥ አስቀምጧል።[98] ከእነዚህም ውስጥ፡- መሬት የሚታጣባቸው ሁኔታዎች፣[99] የድንበር ወሰንን የመለየት ሂደት፣[100] መሬትን ለህዝብ አገልግሎት ስለማስለቀቅ፣[101] መሬትን የመንከባከብ ግዴታን ካለመወጣት ጋር በተያያዘ ይዞታን ስለማጣት[102] እና ያለ ፈቃድ መሬትን መጠቀም ይዞታን ስለማጣት[103] የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል።[104] እነዚህ የአስተዳደራዊ ውሳኔዎች የሚሰጡበት ዓይነት፡- የአንድ ፍሬ-ነገር መኖር ያለመኖርን ማረጋገጥ፣ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር በመከተል የቃል ማስጠንቀቂያ መስጠት፣ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣ የመሬት አጠቃቀምን ለጊዜው ማገድ፣ ለሌላ ሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት እና በመጨረሻም መሬቱን ከእነ አካቴው ማሳጣት የሚሉ አማራጮችን መያዙን ከሕጉ የምንገነዘበው ነው።[105] የመሬት አስተዳደር አካላትም እነዚህን በሕግ የተደነገጉ ሥነ-ሥርዓቶችን በማክበር አስተዳደራዊ ሥራቸውን ማከናወን ይጠበቅባቸዋል።[106] በአስተዳደር ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ሥነ-ሥርዓቶችን መደንገግ ያስፈለገበት ምክንያት የዜጎችን የመደመጥና የቀረበባቸውን ክስ የመከላከል መብት በማስጠበቅ (procedural due process of law) ፍትሀዊ ውሳኔ ለመስጠት ለማስቻል ነው። ይህ አይነቱ ጥበቃ በፌደራሉ ሕገ መንግስት ጭምር እውቅና ያገኘ ጉዳይ ነው።[107] በመሆኑም አንድ ወጥ ማስፈጸሚያ ሕጎች ባይኖሩንም

---

[98] አዋጅ ቁጥር 252/09፣ አንቀጽ 43 እና 28

[99] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 21

[100] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 33

[101] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 26

[102] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 27

[103] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 21፣ 26 እና አንቀጽ 9

[104] ለዚህ ማሳያም *አሰናቀኝ እጅጉ እና ደሴ ሰጦታው*፣ የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ.ም፣ የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የሰበር መ/ቁ/ 41994 (ያልታተመ)። በዚህ መዝገብ የይግባኝ ባይን መሬት ሰኔ 03 ቀን 2004 ዓ.ም በቃለ ጉባዔ ሲያስተላልፍ በምን አግባብ መሬቱ እንደተላለፈ በውሳኔው ላይ አልተገለፀም። ይህን መሰረት በማድረግም የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሬቱ ለመልስ ሰጭ ተሰጥቷል በሚል ወስኗል። በሁለተኛ ይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲቀርብ በአዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀፅ 12 መሰረት መሬቱ አልተነሳበትም በማለት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ወስኗል። ለውሳኔውም መሰረት ያደረገው የአዋጅ ቁጥር 133/98 እና ደንብ ቁጥር 51/99 የመሬት መመሪያው መሰረትም አቤቱታ ሲቀርብ መከተል ያለበትን መስፈርት አላሟላም በሚል ነው።

[105] ለምሳሌ በአዋጅ ቁጥር 252/09፣ አንቀፅ 21 መሰረት መሬት ከሚታጠበት ሁኔታ ውስጥ ከ5 ዓመት በላይ ከአካባቢው የሌለ ሰው መሆኑን ማስረዳት ይጠይቃል።

[106] ይህን ግዴታ ባለማክበርም የመሬት አስተዳደር አካላት በግለሰቦች መካከል የቀረበን ክርክር መወሰናቸውን ከሚያሳዩን ውስጥ ለምሳሌ፡- *ፈለቀ አለማየሁ እና እኑየሽ ተሰማ*፣ ሰኔ 2006 ዓ.ም፣ የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የሰበር መ.ቁ. 37432 (ያልታተመ)፤ *እኑ-ወርቅነሽ ክበደ እና ሰዋየሁ ፈንታሁን*፣ ሰኔ 2005 ዓ.ም፣ የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የሰበር መ.ቁ. 17936 (ያልታተመ) እና *እንዳንው ጫኔ እና ጌጡ ተድላ*፣ መስከረም 2004 ዓ.ም፣ የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የሰበር መ.ቁ.13203 (ያልታተመ) መመልከት ይቻላል።

[107] የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት፣ አንቀፅ 15፣ 17፣ 40 እና 37። ይህን ግዴታ ባለማክበርም የመሬት አስተዳደር አካላት በግለሰቦች መካከል የቀረበን ክርክር ሲወስኑ ይስተዋላል።

ከአጠቃላይ የህግ ፍልስፍና በመነሳት የአስተዳደር አካላት ውሳኔ ሲሰጡ የሚያስፈልገውን ዝቅተኛ የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓቶችን መከተል ይጠበቅባቸዋል።[108]

3.2.3 በመሬት ጉዳይ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በፍርድ ቤት የሚታዩበት አግባብ

አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በመደበኛ ፍርድ ቤቶች መታየት አለባቸው ወይስ የለባቸውም? የሚለው ጉዳይ የተለያየ አስተያየትን የሚጋብዝ ሲሆን ሁለት ዓይነት የክርክር መስመሮችም ይነሳሉ። አንደኛው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች (administrative decisions) ወይም የአስተዳደር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ (decisions of administrative tribunals) በመደበኛ ፍርድ ቤቶች መታየት (judicial review) በማንኛውም ጊዜ የሚጠየቅ ሳይሆን ግልጽ የሆነ የህግ ማዕቀፍ ያስፈለገዋል የሚሉ አሉ። በተቃራኒው ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ፍትህ የማግኘት መብት ያለው በመሆኑ በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ግልጽ የህግ ማዕቀፍ እንዲቀመጥ መጠበቅ ሣያስፈልግ ወደ ፍርድ ቤት መውሰድ ይቻላል የሚሉ አሉ።

የሀሳብ ልዩነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የመሬት ክርክርን ከፍርድ ቤት ጋር ማስተሳሰሩ ሁለቱም አካላት በየራሳቸው የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ እድል የሚሰጥ አሰራር ነው። ሆኖም በፍርድ ቤቶች ከአስተዳደር አካላት የሚነሱ ውሳኔዎችን በይግባኝና ብሎም በሰበር የሚዳኙበት ሁኔታ ግልፅ ያለመሆን ችግር ይታያል። በመሆኑም መደበኛ ፍርድ ቤቶች በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ፣ መቼ እና መደበኛ ፍርድ ቤቶች ምንን መሰረት አድርገው የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ ስህተት ሊያርሙ ይገባል የሚሉት ጥያቄዎች መልስ ያስፈልጋቸዋል።

በመሰረቱ በአማራ ክልል የመሬት አስተዳደር ከመሬት ይዞታ ጉዳይ ጋር ተያይዞ የሚነሱ አለመግባባቶች ላይ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች በይግባኝ የሚታረሙበትን ሥርዓት ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋወቀው፣ የፌደራሉ እና የክልሉ መሬት አዋጆች ሳይሆኑ፣ በደንብ ቁጥር 51/99 አንቀፅ 36 ስለመሆኑ ልብ ማለት ይገባል።[109] ነገር ግን አዋጅ ቁጥር 252/09 በአንቀፅ 38፣ 52 እና በሌሎች ድንጋጌዎች ሥር የአስተዳደር አካላት ውሳኔ ሲሰጡ የሚከተሉትን ቅድመ-ሁኔታና የይግባኝ ሥርዓት (በክስ መቅረብ) በክልሉ ሕግ አውጪ እውቅና እንዲያገኝ

[108] በአዋጅ ቁጥር 252/09፣ አንቀጽ 2(44) ከተሰጠው ትርጉም በተጨማሪ ሕገ መንግስቱን፣ የአስተዳደር አካላትን የሚያቋቁሙ ሕጎች እንዲሁም አጠቃላይ የሕግ ፍልስፍናን በማገናዘብ የአስተዳደር አካላት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ሊከተሏቸው የሚገቡትን መሰረታዊ የሥነ-ሥርዓት መርሆችን ማስቀመጥ ይቻላል።

[109] ይህም ከቀበሌ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ የሚነሳን አስተዳደራዊ ውሳኔ በወረዳ ፍርድ ቤት በመቀበል በይግባኝ ወይም በሰበር ለከፍተኛው ፍርድ ቤት የሚቀርብ መሆኑን ያሳያል። በሕጉ ላይ "ሰበር" የሚለው አገላለፅ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት መሰጠቱ የህግ ስህተትን ለማረም የሚል ካልሆነ በስተቀር የሰበር ሰሚ ችሎት አደረጃጀትን የተከተለ ነው ወይ የሚለው ጥያቄ የሚያስነሳ ነው።

አድርጎታል። በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 52(6) መሰረትም እስከ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ተፈቅዷል።[110] የድንጋጌው ይዘት፡-

> *የገጠር መሬትን ከመለካት፣ ከማስተዳደርና ከሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት በሚሰጡት አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘው ወገን ውሳኔ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ክሱን ለወረዳ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል። የወረዳው ፍ/ቤት የጽ/ቤቱን ውሳኔ ያፀናው እንደሆነ ይግባኙን ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል። ይግባኙ የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የሥር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ያፀናው እንደሆነ ውሳኔው የመጨረሻ ይሆናል።*

የዚህ ድንጋጌ ይዘት ቀደም ሲል ከነበረው ደንብ ቁጥር 51/99 አንቀፅ 36 ይዘት የሚለይባቸው መሰረታዊ ነጥቦች መኖራቸውን የሚጠቁሙን ነጥቦች አሉ። የመጀመሪያው "... ክሱን ለወረዳ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል" የሚለውን ሀረግ መጠቀሙን በግልጽ ማየት ይቻላል። ይህም የቀድሞው ሕግ "ይግባኙን" ሲል የአሁኑ ደግሞ "ክሱን" በሚል መለወጡ ግልፅ ነው። ይግባኙን ለማለት ተፈልጎ ነው እንዳይባል በፍርድ ቤቶች መካከል ያለውን ግንኙነት በይግባኝ የሚታረም መሆኑን በግልፅ በተመሳሳይ ንዑስ አንቀፅ ውስጥ ክስና ይግባኝ የሚሉትን ቃላት ሕግ አውጪው ተጠቅሟል። በሥነ-ሥርዓት ሕግ ፍልስፍና ውስጥ ክስና ይግባኝ በጽንሰ-ሀሳብ ደረጃ የተለያዩ ናቸው። "ክስ" በመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ክርክር ተደርጎና ማስረጃ ቀርቦ የሚወሰንበት ሂደት ሲሆን "ይግባኝ" ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ በተደረገው ክርክር የተፈጠሩ ስህተቶች የሚታረሙበት ሥርዓት ነው።[111] በመሆኑም አዋጁ "ክስ" የሚለው ቃል መጠቀሙ የይግባኝ ሥርዓት ለመዘርጋት አለመፈለጉን የሚያሳይ ሆኖ ሊወሰድ ይችላል። በድንጋጌው "ይግባኝ" ከሚባል ይልቅ "ክስ" መባሉ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ለዚህ መነሻውም አስተዳደራዊ ውሳኔ ሙሉ ክርክር የማይደረግበት እና መደበኛ የፍርድ ቤት ሥነ-ሥርዓትን በመከተል የማይወሰን በመሆኑ ልክ እንደ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተቆጥሮ ተጨማሪ ክርክር ሳይደረግ ስህተትን ማረም ያስቸግራል። በመሆኑም አንድ ግለሰብ በአስተዳደራዊ ውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው የመሬት አስተዳደር ፅ/ቤቱን በተከሳሽነት አስጠርቶ በወረዳው ፍርድ ቤት ሙሉ ክርክር ማድረጉ ከሳሽ ያለውን ሙሉ ክርክርና ማስረጃ በዝርዝር የማስረዳት ዕድል እንዲኖረው

---

[110] ይህ አተረጓጎም በምን አግባብ መሆን እንዳለበት በዚሁ ጽሁፍ ክፍል ውስጥ ስለተብራራ መድገሙ አስፈላጊ አልሆነም።

[111] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥሮች 222 እና 338

የሚያስችል ነው።[112] በዚህ መካከልም የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ አስተዳደራዊ ውሳኔ መስጠቱ ባለጉዳዮችን አስቀድሞ ሊያረካና ወደ ፍርድ ቤት እንዳይመጡ ሊያደርጋቸው በመቻሉ የፍርድ ቤት ጉዳይ ፍሰትን እንዲቀንስ ያስችላል። አዋጁም በአንቀጽ 52(6) መሰረት የአስተዳደር አካላት አንድ ውሳኔ ሰጭ ናቸው በሚል ማስቀመጡ ይህን ጽነሰ-ሀሳብ ታሳቢ በማድረግ ነው ለማለት ያስችላል።

ከዚህ ጋር አብሮ የሚነሳው ጉዳይ በወረዳ ፍርድ ቤት የሚቀርበው "ይግባኝ" ሳይሆን "ክስ" ነው ከተባለ በ30 ቀናት ውስጥ ለወረዳ ፍርድ ቤት ይቅረብ መባሉ ከላይ በዚሁ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር 3 ላይ የመሬት ክርክርን በውይይት መፍታት በሚለው ቀዳሚ ክፍል ያነሳነውን ጽንሰ-ሀሳብ መልሶ እንዲመጣ የሚያደርግ ነው። ምንአልባት በዚህ የሕጉ ክፍል ለየት የሚለው የመሬት አስተዳደር አካላት የመሬት ውሳኔ ሰጭ አካላት በመሆናቸው የሚሰጡትን ውሳኔ ከፍርድ ቤት ጋር በይግባኝ ሥርዓት የሚያያዝ ስለሚመስል የይግባኝ ጊዜ አድርጎ መውሰድ የሚገባ ይመስላል። የ30 ቀን ጊዜ ካለፈም የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ማቅረብ ይቻላል የሚለውን መውሰድ ይገባል።[113] አለበለዚያ በአስተዳደር አካል ውሳኔ እንደተስማማ በመቁጠር በዚሁ አግባብ ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ የሕጉ ፍላጎት መሆኑን መረዳት ይቻላል።

በአስተዳደር አካላት ውሳኔ ያገኘ የመሬት ክርክርን ከወረዳ ፍርድ ቤት ወደ ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በይግባኝ የሚቀርብበትም ሂደት ችግር ያለበት ነው።[114] በአዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀፅ 52(6) ላይ እንደተመለከተው ለወረዳው ፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ የፍሬ-ነገር ክርክርን ጭምር ማሳረም እንደሚቻል መብት ሰጥቷል። በአዋጁ አንቀጽ 56(6) ላይ የወረዳው ፍርድ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ሊቀርብ ይችላል በሚል ተደንግጓል። ይህም ቀደም ሲል በደንብ ቁጥር 51/99 አንቀፅ 36 መሰረት በወረዳው ፍርድ ቤት አስተዳደራዊ ውሳኔው ከፀና ለከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የመቻሉን ጉዳይ ማስቀረቱን የሚያስገነዝበን ነው። ስለሆነም በአዲሱ አዋጅ ድንጋጌ መሰረት የከፍተኛው

---

[112] እንዲህ በሆነ ጊዜ የወረዳው ፍርድ ቤት አስተዳደራዊ ውሳኔ በሰጠ ጊዜ ሁሉ ተጠርቶ ይችላል ወይ? የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል። ከዚህ ጋር በሚመሳሰል በአማራ ክልል የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 253/2010 ላይ እንደተደነገገው የአስተዳደር ፍርድ ቤት የተመሰረተ ሲሆን አስቀድሞ ውሳኔ የሰጠው መስሪያ ቤት በተጠሪነት እየመጣ እንዲከራከርና በሠራተኛው ላይ የሰጠውን ውሳኔ ሕጋዊነት የማስረዳት ግዴታ ተጥሎበታል።

[113] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 326

[114] ይህን አካሄድ ከግብ ለማድረስ የመሬት አስተዳደር አካሉ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች ለፍርድ ቤት የሚቀርቡበት ሳይገደብ ነገር ግን ፍርድ ቤቱ ሥልጣን ያለው ስለመሆን አለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 229 እና 231 ከመዝገብ አከፋፈት ጀምሮ የሥረ-ነገር ስልጣንን በዳኞች ቢመረመር አግባብነት ያለው ነው።

ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ በወረዳ ፍርድ ቤት የፀና ቢሆንም እንኳ በፍሬ-ነገር ጭምር መወሰን ያስችለዋል፡፡

እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 52(6) መሰረት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ከአስተዳደር አካላት የተነሳን ጉዳይ የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ያፀናው እንደሆነ "የመጨረሻ" ይሆናል ካለ በኋላ ከተሻረ ምን ይሆናል የሚለው ከድንጋጌው ንዑስ አንቀፅ 5 አቀራረፅ ጋር ሲነፃፀር ልዩነት አለው፡፡ ይህ ጽነሰ-ሀሳብም በፍርድ ቤቶች ትርጉም ለመስጠት ክፍት ሲሆን በሁለት መስመር ክርክር ሊቀርብ ይችላል፡፡ የመጀመሪው አዋጁ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ሲያፀና የመጨረሻ ይሆናል በሚል ከገለፀ በኋላ ሲሻር ምን ይሆናል የሚለውን በግልፅ የሚለው ነገር የለም፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ እንደደንብ ቁጥር 51/99 አንቀፅ 36 የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ በየትኛውም አግባብ የመጨረሻ ነው ከመባሉ ጋር ስለሚጣጣም በዚሁ አግባብ መረዳት ይገባል የሚለውን አቋም መያዝ ይቻላል፡፡ ይህም ሕጉ የአስተዳዳራዊ ውሳኔ ይግባኝን በልዩ ሁኔታ ማስተናገዱን የሚያሳይ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ሁለተኛው የክርክር መስመር በንዑስ ድንጋጌው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ የመጨረሻ የሚሆነው ውሳኔው ሲፀና መሆኑን ማመልከቱ፤ ውሳኔው ሲሻር ወይም ሲሻሻል የይግባኝ መብት በንዑስ አንቀጽ 5 በተጠቀሰው አግባብ ተፈጻሚ ይሆናል በሚል መከራከር ይቻላል፡፡ በዚህ ክርክር በከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ሲሻር ወይም ሲሻሻል ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት መሰጠቱን መረዳት ይቻላል፡፡

ሁለቱ የክርክር መስመሮች ለትርጉም አሻሚ ቢሆኑም የይግባኝ ባይን መብት በሚያሰፋ መልኩ መተርጎም ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ በተለይም በወረዳ ፍርድ ቤት ክስ ይቀርባል ከተባለ ከመደበኛው የመሬት ይግባኝ ሥርዓት መለየት የለበትም፡፡ በመሆኑም ከአስተዳደር ፍርድ ቤት የተነሳ ጉዳይ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ከተለወጠ ወይም ከተሻሻለ በይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ መፍቀድ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ ይህ አተረጓጎም ተቀባይነት ካለው ለጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜውንም በልዩ ሕጉ በግልፅ ካልተመለከተ በመደበኛው ሥነ-ሥርዓት ያለውን የሁለት ወር ጊዜ መጠቀሙ አሳማኝነት ይኖረዋል፡፡[115]

ማንኛውንም ከመሬት ጋር የተያያዘ አስተዳደራዊ ውሳኔ ለፍርድ ቤት ያለ ቅድመ-ሁኔታ ሊቀርብ የመቻሉን ጉዳይ ማጤን ተገቢ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 252/2009 መሰረት አስተዳደራዊ

[115] አዋጅ ቁጥር 223/07፤ አንቀጽ 16 እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 320 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን ይመልከቱ ።

ውሳኔ የሚሰጥባቸውን ጉዳዮች በዋናው ክፍል ውስጥ መዘርዘሩ እንዲሁም በትርጉም ክፍሉ ላይ ጭምር መገለፁ አስተዳደራዊ ውሳኔ አንደኛው የመሬት ክርክር መፍቻ ተቋም መሆኑን የሚያሳይ ነው። ከዚህ አንፃር በወረዳ ፍርድ ቤት አንድ የመሬት ክርክር በክስም ቢሆን ለመቅረብ አስተዳደራዊ ውሳኔ ማግኘት ቅድመ-ሁኔታ መሆን አለበት ለማለት ይቻላል።[116]

የሕጉን ዓላማ ለማሳካት አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲያገኙ የተባሉ ጉዳዮችን በወረዳ ፍርድ ቤት ለማስተናገድ ቅድመ-ሁኔታ መሟላቱን ማረጋገጥ ይገባል። በመጀመሪያ ደረጃ አንድ ጉዳይ ለወረዳ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በሕግ ተለይቶ የተቀመጠን አስተዳደራዊ መፍትሔን ሳይጨርስ የሚቀርብ ከሆነ አማራጮችን አሟጦ መጠቀም እና የበሰለ ሂደት (exhaustion of local remedies and ripeness)[117] አላሟላም በሚል ውድቅ ማድረግ ስለመቻሉ መረዳት ያስፈልጋል።[118] ይህም ከወረዳ መሬት አስተዳደር ወደ ዞን ወይም ወደ ክልል የመሬት አስተዳደር አካላት በየደረጃው አስተዳደራዊ ቅሬታ የማቅረብ ግዴታን ስለሚያስቀር ለባለጉዳዮች ውጣ ውረድ የሚቀንስላቸው ይሆናል።[119] ከዚህ ላይ የአስተዳደር አካላት ውሳኔዎችን በተገቢው ጊዜ ያለመወሰን እና ያላግባብ ውሳኔን ማዘግየት ከተፈጠረ ቅር የተሰኘው ሰው አማራጮችን አሟጦ እንደተጠቀመ እና ጉዳዩም የበሰለ ሆኖ ሊቆጠር እንደሚገባው መገንዘብ ይገባል።[120] ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ነጥብ የወረዳው መሬት አስተዳደር የሰጠውን ውሳኔ ለዞንና ለክልል መሬት አስተዳደሮች ማቅረብ አይቻልም ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው። አንዳንድ ድንጋጌዎች ለምሳሌ በአዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀፅ 43 ወደ ዞን ገጠር መሬት አስተዳደር

---

[116] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 73፣ ገፅ 233 ላይ እንደተመለከተው በአንዳንድ ሀገሮች እንዲህ አይነቱን ችግር ለመቀነስ ቅር ተሰኝቻለሁ የሚል ሰው በመጀመሪያ ቅሬታው ምክንያታዊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚከፍለው ገንዘብ አስይዞ የቅሬታው መነሻም በግልጽ ተጽፎ ወደ ፍርድ ቤት እንዲሄድ የሚደረግበት አግባብ አለ።

[117] መሀመድ፣ የግርጌ ማስታወሻ 69

[118] በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 5 እና 244 በፍርድ ያለቀ ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ ተቃውሞ ቢቀርብ መቃወሚያ ሊሆን ስለመቻሉ ማነፃፀር ይችላል። በቀድሞው ደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 36 መሰረት በአቀራረፁ ትንሽ ለየት በሚል አግባብ ቅሬታው ከመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች ውሣኔ ላይ ከሆነ ለወረዳው መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ማቅረብ የሚጠበቅበት መሆኑን ያስቀመጠ ነበር። አሁን ግን የወረዳው መሬት አስተዳደር መወሰኑን እንጅ ከታች ያለውን ይግባኝ ብዙም ግምት ውስጥ አላስገባም።

[119] በግልፅ ለዞን መሬት አስተዳዳር ሊዝን አስመለክቶ ውል እንዲዋዋሉ ስልጣን የሰጠ መሆኑን መመልክት ይቻላል፡ የክልሉ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም የሚሰጣቸው ውሳኔዎች ግን ወደ ይግባኝ ስርዓቱ የሚገቡ ናቸው ለማለት የሚቻል አይደለም። ይህም በቀጥታ በህግ የተሰጣቸው ሲሆን ነው። አለበለዚያ የቀበሌና ወረዳ መሬት አስተዳዳርን በሕግ የተሰጣቸውን ሥራ በመተካት ሥራ ከሰሩ የይግባኝ ስርዓቱን የሚያፋልስና የባለጉዳዩን በፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት የሚያጣብብ ይሆናል።

[120] በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በመንግሥታዊ የመንግሥት ሠራተኞች ዲስፕሊን አፈፃፀምና የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት መወሰኛ የክልል መስተዳደር ደንብ፣ 2003፣ ዝክረ ሕግ ጋዜጣ፣ ደንብ ቁጥር 75፣ 16ኛ ዓመት፣ ቁጥር 3 (ከዚህ በኋላ *ደንብ ቁጥር 75/2003* እየተባለ የሚጠራ) አንቀፅ 32(3) መሰረት የመስሪያ ቤቱ ኃላፊ በውስን ጊዜ ውስጥ ምላሽ የማይሰጥ ከሆነ እንደተከለከለ በመቁጠር በ1 ዓመት ጊዜ ውስጥ ይግባኝ የሚባል መሆኑን እንደጠቃሚ ልምድ መውሰድ ይቻላል።

አቤቱታ ማቅረብ ስለመቻሉና ለወረዳ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብን በግልፅ አማራጭ መሆኑ ተደንግጓል። ይህም በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 52(6) ይዘት ግልፅ መሆኑ ላይ ችግር ያመጣል። ሁለቱንም አማራጮች በመብትነት መያዙ ለተገልጋዮች ጠቃሚ ሲሆን ነገር ግን ለዞን መሬት አስተዳደር አቤቱታ ማቅረብ ግዴታ አለመሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

እንዲሁም አንዳንድ ከመሬት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ከዚህ በተለየ መልኩ የይግባኝ ሥርዓት የተደነገገላቸው መሆኑን መገንዘብ ይገባል። ለምሳሌ በአዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀጽ 28 የካሳ ተመንና አከፋፈል አቤቱታን አስመልክቶ ቅሬታ አቅራቢው በሕግ ለተቋቋመው የካሳ ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ የሚያቀርብና በዚህ ውሳኔ ላይ ሁለተኛ ቅሬታ ካለውም ውሳኔው ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ይግባኙ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብ መሆኑ ተደንግጓል። ይህ ድንጋጌም አጣሪ ጉባኤም ባይኖር እንኳ ይግባኙ በምትክ ለወረዳ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ በቀጥታ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይቀርባል የሚለው ምክንያቱ ግልፅ አይደለም። ነገር ግን ሕጉን መተግበር ያስፈልጋል።

ከዚሁ ጋር አብሮ የሚነሳው ጉዳይ የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ በቅሬታ ሰሚነት የሚመለከተው አካል የመሬት ጉዳዮችን ለማስተናገድ የመቻሉ ጉዳይ ነው። ለዚህ ልምድ መኖር መነሻውም ቀደም ሲል የአዋጅ ቁጥር 133/1998 እና ደንብ ቁጥር 51/1999 ማስፈፀሚያ በመመሪያ ቁጥር 6(4) ላይ በአስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ በአማራጭነት ለቅሬታ ሰሚ ጽ/ቤት[121] አቤቱታ ማቅረብ ስለመቻሉ ይደነግግ ስለነበር ነው። ሆኖም በአዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀፅ 52(8) መሰረት ከመሬት አስተዳደር ውጭ ሌላ የአስተዳደር አካል ውሳኔ መስጠት የማይገባው መሆኑን ግልፅ ክልከላ ማድረጉ ቀደም ሲል ከዚህ አንፃር የተፈጠረውን ችግር የሚፈታ ነው። እንዲሁም ለአስተዳደራዊ ቅሬታ ሰሚ መቋቋም መነሻ የሆነው የደንብ ቁጥር 55/2000 በራሱ ምላሽ የሰጠ ስለመሆኑ በአንቀፅ 9(1) በቅሬታ ሰሚ አካላት የማይታዩ ጉዳዮችን በተመለከተ ሲደነግግ "በመደበኛ ፍርድ ቤቶችና በህግ የመዳኘት ሥልጣን በተሰጣቸው መሰል ተቋማት ዘንድ ቀርበው በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮችና የተሰጡ ውሳኔዎች ወይም ትዕዛዞች" በቅሬታ ሰሚ አይታዩም በማለት ደንግጓል።

[121]በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በመንግሥታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ረገድ የሚነሱ ቅሬታዎች አቀራረብ፣ ምርመራና አወሳሰን ሥነ-ሥርዓት መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ፣ 2000፣ ገዝረ ሕግ ጋዜጣ፣ ደንብ ቁጥር 55፣ 13ኛ ዓመት፣ ቁጥር 4 (ከዚህ በኋላ *ደንብ ቁጥር 55/2000* እየተባለ የሚጠራ) በሆነው ላይ የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት ያለ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል።

በሁለተኛ ደረጃ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ለማረም (ለማጽደቅ ወይም ለመሻር) መነሻ ምክንያታቸው (grounds for judicial review) ምንን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት የሚለውን ጉዳይ መመለስ የሚገባ ይሆናል። አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን በመደበኛ ፍርድ ቤቶች እንዲታረሙ ለማድረግ መሰረቱ የህግ የበላይነትን ከማስፈን (rule of law) ጋር የተያያዘ ነው። ይህ የህግ የበላይነትን የማስከበር ስራ ደግሞ የፍርድ ቤቶች ሚና መሆኑ ይታወቃል። የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት በግልጽ እንዳስቀመጠው በየደረጃው ያሉ የፌደራል እና የክልል ህግ አውጭ፣ ህግ አስፈፃሚ እና ህግ ተርጓሚ አካላት መሰረታዊ መብቶችን እና ነጻነቶችን የማክበር እና የማስከበር ሕገ መንግስታዊ ሀላፊነት ተጥሎባቸዋል።[122] በመሆኑም ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር አካላት ውሳኔን የሚያርሙት የሕጋዊነትን መርህ መሰረት በማድረግ ነው።

ከሚዳሰሱት ህጎች ክፍፍል በመነሳት የመሰረታዊ እና የሥነ-ሥርዓት ህጎችን የውሳኔ ሕጋዊነትን (substantive legality and procedural legality of administrative decisions) ከማረም አንጻር በማለት በሁለት መክፈል ይቻላል።[123] አስተዳደራዊ ውሳኔዎች መሰረታዊ ህጋዊነትን ስለመጣሳቸው ጸሀፍት የተለያዩ መነሻዎችን ይጠቅሳሉ።[124] ከእነዚህም ውስጥ የአስተዳደር አካል ከተሰጠው ስልጣን ውጭ መስራት (ultra virus)፣ በህግ የተጣለበትን ግዴታ አለመወጣት (failure to perform legal duties)፣ የህግ ስህተት መፈፀሙ (error of law) እና ለውሳኔው በቂ ምክንያት/ማስረጃ አለመኖር (no sufficient evidence /reason to justify the making of the decision) ከሚሉት አንጻር ከመሬት ሕግ ማዕቀፎች በመፈተሽ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ለማረም ወይም ለማጽናት መቻሉን መረዳት ይቻላል።[125] የሥነ-ሥርዓት ጉዳይን በሚመለከት የመሬት አስተዳደር አካላት አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ሲሰጡ በሕግ የተቀመጠውን ቅደም-ተከተል በማክበር መወሰን ያለባቸው በመሆኑና አሰራሩንም ከተላለፉ ውሳኔው በፍርድ ቤት ሊስተካከል ይችላል።[126]

---

[122] የኢፌዲሪ ህገ መንግስት፣ አንቀጽ 13

[123] Nguyen Van Quang, Grounds for Judicial Review of Administrative Action: An Analysis of Vietnamese Administrative Law, CALE Discussion Paper No.3, January, 2010, P.11.

[124] ዝኒ ከማሁ

[125] ዝኒ ከማሁ፣ ገጾች 30-33

[126] ለምሳሌ በአዋጅ ቁጥር 252/09፣ አንቀፅ 28 መሰረት ያለውን የአስተዳደራዊ እርምጃ ቅደም ተከተል መዛባት ካለ የአስተዳደር ውሳኔው ሊሻር ይችላል። እንዲህ በሆነ ጊዜ የአስተዳደር አካሉ ድጋሜ አከራክሮ እንዲወስን ይመለስለታል ወይስ ፍርድ ቤቱ ሙሉ ክርክሩን ጨርሶ ለጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል የሚለው ግር ያሰኛል። እንደፀሀፊው ግን ሁለተኛው አማራጭ የአስተዳደር አካሉን ውሳኔ የማይጋፋ እስካልሆነ ድረስ የሚሻል ይመስላል።

ይህን አሰራር ተከትሎ የሚነሳው ጥያቄ በአስተዳደር አካል መሬትን አስመልክቶ የሚሰጥ ውሳኔ በፍርድ ያለቀ ነው ሊባል የመቻሉ ጉዳይ ነው። አስቀድሞ የአስተዳደር አካሉ በፊታው ጉዳይ ላይ አዲስ ለአስተዳደራዊ ውሳኔ እንደገና አዲስ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ መወሰንን መከልከል ምክንያታዊነት የለውም። ነገር ግን ያለምክንያት በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ውሳኔን መቀያየር የአስተዳደር አካሉን የውሳኔ ሰጭነት ሚናና ብቃት (integrity) የሚያሳንስ ይሆናል። የአስተዳደር አካሉ የሰጠው ውሳኔም ወደ ፍርድ ቤት ቀርቦ የመሬት አስተዳደሩ ጋር ተከራክረው ከተወሰነ አስገዳጅነቱ የማይቀር ነው።[127] ሆኖም ከአስገዳጅነት አንጻር የአስተዳደር አካላትን ውሳኔ ሁሉ እንደ ፍርድ ቤት ውሳኔ እኩል ደረጃ መስጠት የሕጉን ዓላማ የሚያሳካ አይሆንም።

ለማጠቃለል በመሬት ይዞታ የአስተዳደር አካላት ውሳኔ አሰጣጥን አስመልክቶ ራሱን ችሎ የተሟላ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ባይኖርም በመሰረታዊነት የሚታወቁ መርሆች፡- የመሰማት፣ የእኩልነት እና የፍትሐዊነትን መብትን በማክበር ረገድ የራሱ ጉድለት ሊኖርበት ስለሚችል በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ሰፋ ባለ ሁኔታ በይግባኝ ጭምር እንዲስተካከሉ እድል መሰጠቱ አሳማኝ ነው። ይሁን እንጅ ከዚህ ላይ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ለፍርድ ቤት በቀጥታ የሚቀርቡትን እና ከአስተዳደር ፍርድ ቤት ተጀምረው የሚቀርቡት ጉዳዮች ላይ የሚኖራቸውን ሚና በመለየት መወሰን ለሕጉ መዳበር ወሳኝነት ይኖረዋል።

3.3 የገጠር መሬት ክርክር በፍርድ ቤቶች የሚዳኝበት አግባብ

ፍርድ ቤቶች የመሬት ግጭቶችን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ ከማከራከር እስከ ይግባኝ ሰሚነት ሥልጣን ያላቸው መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም የመሬት ተመልካች ፍርድ ቤት ማንነት፣ የወረዳ ፍርድ ቤት ከሌሎች ፍርድ ቤቶች ጋር ያለውን ግንኙነትና ከመሬት ክርክር ጋር በተገናኘ የማስረጃ አሰባሰብን በቀጣይ ንዑስ ክፍሎች በቅደም-ተከተል እንመለከታለን።

3.3.1 የፍርድ ቤቶች የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣንና ወሰኑ

በመሰረቱ ፍርድ ቤቶች ክርክርን በመምራት ረገድ የመጀመሪያ ደረጃ እና የይግባኝ ሥልጣን መኖሩ በመደበኛው የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መገዛት ያለበት ቢሆንም አሁን አሁን

[127] የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሀ/ቁ/ 5ን ይመልከቱ።

ላይ መሰረታዊ ሕጎችም ተጨማሪ ሥነ-ሥርዓታዊ ድንጋጌዎችን ይጠቅሳሉ።[128] ይህ አይነት ባህሪን ከሚያንፀባርቁት ሕጎች ውስጥ የመሬት ሕግ ማዕቀፍ አንደኛው ነው። ከላይ እንዳየነውም የመሬት ክርክር በስምምነት ሳያልቅ ሲቀርና በአስተዳደር አካል ቢፈታም አከራካሪ ጉዳይ ካለው በፍርድ ቤት ቀርቦ የሚታይ ስለመሆኑ በዚህ ክፍል በቀደሙት ሁለት ተከታታይ ንዑስ ክፍሎች በዝርዝር ተመልክተናል። እንዲሁም የመሬት ክርክር ከታሪክ አንፃር በፍርድ ቤት ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ በአስተዳደር አካላት የታየበት ጊዜ የነበረ መሆኑን ከተለያዩ ሕጎች መረዳት ስለመቻሉ በዚህ ፅሁፍ ክፍል 2 ላይ ተዳሷል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የገጠር መሬት ክርክርን በመጀመሪያ ደረጃ ለመዳኘት የሥረ-ነገር ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ማን ነው? የሚለው ፅነሰ-ሀሳብ ምላሽ የሚፈልግ ነው። በአዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀፅ 52(2) መሰረት የመሬት ክርክር ለወረዳ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ማቅረብ መቻሉን ደንግጓል። ይህ አገላለጽ አሁንም ችግሮች ሊኖርበት መቻሉን ቀደም ሲል በአማራ ክልል ተፈፃሚ የነበሩ ሕግጋት ይዘት እና በተግባርም ከሌሎች የሕግ ማዕቀፎች ጋር ያጋጠሙ የሕግ ግጭቶች በጥናት ስለተለዩ በንዕዕር መመልከቱ ጠቃሚ ነው።

በኢፌዲሪ ሕግ አውጪ መሬትን በተመለከተ በመጀመሪያ የወጣው አዋጅ ቁጥር 89/89 ሲሆን በልዩ ሁኔታ የመሬት ሙግት አፈታትን አስመልክቶ የሚለው ነገር አልነበረም። የአማራ ክልልም በወቅቱ ውክልናን መሰረት ሳያደርግ በ1989 ዓ.ም የመሬት ሕግ ማውጣት ሲጀምር የመሬት ክፍፍሉን አስመልክቶ ሁለት አዋጆች በተከታታይ አውጥቷል።[129] እነዚህ የመሬት ሕግጋት ስለመሬት ዳኝነት ጉዳይ ላይ ፍንጭ የሚሰጥ ድንጋጌ የነበራቸው መሆኑን ለመረዳት ይቻላል። ከእነዚህ አዋጆች አወቃቀር የምንገነዘበው መሬት የመደበኛው ፍርድ ቤት ስልጣን የነበረ መሆኑን ነው። ድልድሉን ለማከናወን ዓላማ ሲባል በልዩ ሁኔታና ለጊዜው ብቻ የፍርድ ቤት ውሳኔ ታግዶ የቆየ መሆኑን ጠቋሚ ድንጋጌ አለ። ይህም የአዋጁ ተፈፃሚነት ወሰን በ1989 ዓ.ም ድልድሉ በተደረገባቸው አካባቢዎች በመሆኑና ቀደም ሲል ድልድል በተደረገባቸው አካባቢዎች "መደበኛ ፍርድ ቤት" የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው ስለመሆኑ አስረጂ

[128] አዋጅ ቁጥር 252/09፣ አንቀጽ 52 እና የአዋጅ ቁጥር 133/1998፣ አንቀጽ 29። አዋጆች ሲወጡ ራሳቸውን ችለው የሥነ-ሥርዓት ሕጎችንና የወንጀል ጉዳዮችን ሁሉ በማካተት እየወጡ ያለበትን ሁኔታ መመልከት ይቻላል።
[129] የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ፣ 1989፣ ዝክረ ሕግ ጋዜጣ፣ 16፣ 1ኛ ዓመት፣ ቁጥር 16 (ከዚህ በኋላ የአማራ ክልል አዋጅ ቁጥር 16/1989 እየተባለ የሚጠራ) እና የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ፣ 1989፤ ዝክረ ሕግ ጋዜጣ፣ 16፣ 1ኛ ዓመት፣ ቁጥር 17 (ከዚህ በኋላ የአማራ ክልል አዋጅ ቁጥር 17/1989 እየተባለ የሚጠራ) ታውጀዋል። እነዚህ ህጎችም ዝርዝር ሕግ መሬት ስለሚተላለፍባቸውና ስለግጭት አፈታቱ ግልፅ ስላልነበሩ ክርክሮች ቆይተውም ቢሆን ሲነሱ ለመዳኘት አስቸጋሪ እየሆነ ስለመምጣቱ መረዳት ይቻላል።

ድንጋጌ ነው ለማለት ይቻላል።[130] ይህም በአማራ ክልል በተጨባጭ በደርግ ዘመነ መንግሥት የመሬት ጉዳይን አከራክሮ መወሰንን ለአስተዳደራዊ ፍርድ ቤት መሆኑን የቀየረ መሰረታዊ ለውጥ እንደሆነ መውሰድ ይቻላል።[131]

ብዙም ሳይቆይ በታወጀው በክልሉ የማሕበራዊ ፍርድ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 20/89 መሰረት የመሬትን ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ የመወሰን የሥረ-ነገር ሥልጣንን ለማሕበራዊ ፍርድ ቤት በግልፅ የሚሰጥ ሕግ ወጥቷል።[132] ይህም ለአሥር ዓመታት ያክል በተግባር ላይ ቆይቷል። ከዚህ ላይ መሬትን ያክል ጉዳይ ማሕበራዊ ፍርድ ቤት እንዲወስን ሲደረግ ለተገልጋዩ ሕብረተሰብ ከሚኖርበት አካባቢ ከሚኖረው ቅርበት አኳያ በበጎ ጎኑ የሚታይ ቢሆንም የዳኞች የትምህርት ዝግጅትና የክርክር አመራርን በህግ አግባብ የማድረግ ሂደት ችግር የነበረበት መሆኑን ግን መገንዘብ የሚያስቸግር አይሆንም። የፍርድ ቤት መዛግብት አያያዝም ሥርዓት አልነበረውም። አሁን ላይ በፍርድ ቤት ክርክር ሲደረግ አስቀድሞ በማህበራዊ ፍርድ ቤት አልቋል የሚል ክርክር ሲቀርብ የዳኞች ውሳኔ የማይገኝበትና ውሳኔው መኖሩም ሲያከራክር አልፎ አልፎም በወቅቱ የነበሩ የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ቀርበው እንዲመሰክሩ የሚደረግበት አግባብ ያለ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል።[133]

ዘርዘር ያለ የመሬት ሕግ በ1992 ዓ.ም ሲወጣም መደበኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ያለው መሆኑን የሚያሳይ አልነበረም።[134] ይልቁንም የአማራ ክልል ምክር ቤትም የተሰጠውን በውክልና ሕግ የማውጣት ሥልጣን መሰረት በማድረግ በመሬት አዋጁ ውስጥ የመሬት ጉዳይ

---

[130] በምስራቅ አማራና ጎንደር አካባቢ በ1983 ዓ.ም የመሬት ድልድል መከናወኑን መረዳት ይቻላል። ለምሳሌ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 3 ላይ ግዛቸውና ሰለሞን፣ *የመሬት ግጭት መፍቻ መንገዶች* በሚለው ላይ በክልሉ የሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች ላይ ድልድል የተደረገበት ጊዜ ወጥ አለመሆኑን በጥናት ተረጋግጧል።

[131] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 17፣ ከሽግግሩ ጀምሮ የገበሬዎች ማሕበር ፍርድ ሸንጎ መስራቱን የተቋረጠ መሆኑን እንረዳለን።

[132] በሂደት ግን በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተሻሻለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ፣ 1999፣ ዝክረ ሕግ ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 148፣ 16ኛ ዓመት፣ ቁጥር 26 (ከዚህ በኋላ አዋጅ ቁጥር 148/1999 እየተባለ የሚጠራ) መሰረት ተሸሮ በመደበኛ ፍርድ ቤት እንዲታይ ሆኗል።

[133] ፀሀፊው በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች እስከ ሰበር ችሎት ድረስ ሲሰራ በተለያየ ጊዜ የተገነዘበው ነው። ዳኞችም በአብዛኛው መደበኛውን የሕግ ትምህርት የወሰዱም አይደሉም።

[134] የፌደራላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ፣ 1989፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 89፣ 3ኛ ዓመት፣ ቁጥር 54 (ከዚህ በኋላ አዋጅ ቁጥር 89/89 እየተባለ የሚጠራ) የሆነው የፌደራል አዋጅ ወጥቶ ክልሎች ሕግ እንዲያወጡ ያደረገ ሲሆን የክልል መንግስት አዋጅ እንዲያወጣ የተወከለበትን አግባብ እንመለከታለን። ይህ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት፣ አንቀጽ 50(9) ላይ የተፈቀደ አሰራር ነው። አዋጅ ቁጥር 721/2004 የሆነውን ብንመለከት ለክልል መንግስት የተሰጠው ስልጣን በመስተዳደር ምክር ቤቱ የሚወጣ ደንብ እንጅ የክልል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አዋጅ እንዲያወጣ በሚጠይቅ አግባብ የተቀረፀ አይደለም። ይህ ከሆነ ታድያ በአዋጅ መልክ ሕግ እንድያወጣ ስልጣን የተሰጠበት አግባብ ሕጉን ቀጥታ የሕዝብ ውክልና ያለው ምክር ቤት የሚደነግገው ስለሆነ በክልል ደረጃ የሚወጡ ሕጎች የሚኖራቸው ክብደት ከደንብ በላይ ነው የሚያሰኝ ነው።

ሙግት አፈታት በመደበኛ ፍርድ ቤት መዳኘት መብት መሆኑን ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ በመርህ ደረጃ ደንግጓል።[135] አዋጅ ቁጥር 133/98 ላይ የመሬት ግጭት መፍቻው "መደበኛ ፍርድ ቤት" ነው የሚል ቢሆንም ፍርድ ቤቶች ቀደም ሲል በአዋጅ ቁጥር 20/89 በሆነው ላይ ለማህበራዊ ፍርድ ቤት መሰጠቱን በትርጉም መስጠት ስልጣናቸው መለወጥ ባለመቻላቸው በአዋጅ ቁጥር 148/99 በግልፅ የመሬት ጉዳይ "በወረዳ ፍርድ ቤት" መታየት እንዳለበት የሕግ አውጪን ጣልቃ ገብነት ጠብቋል።[136] በክልሉ ሕገ መንግሥት በአንቀፅ 67(1) መሰረት "የወረዳ ፍርድ ቤት የክልሉ የበታችና የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት አካል ነው" በሚል ተደንግጓል።[137] ምንም እንኳ የማህበራዊ ፍርድ ቤት በአማራ ክልል ሕገ መንግስት ውስጥ የቀበሌ የዳኝነት አካል ተደርጎ እውቅና ቢሰጠውም ባህላዊ ፍርድ ቤት በሚለው ሊወሰድ ይገባል እንጅ መደበኛ ፍርድ ቤት በሚለው ይካተታል ለማለት አያስደፍርም።[138] ሲጠቃለልም የመደበኛ ፍርድ ቤት ማለት በሕገ መንግሥቱ የተሰጠው ትርጉምና የመሬት ሕጉ ከፌደራሉ የመሬት አዋጅ ቁጥር 456/1997 መሰረት የተደነገገውን ልዩ ሕግ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት የክልል አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀፅ 29 መደበኛ ፍርድ ቤት የሚለው አገላለፅ ለወረዳ ፍርድ ቤት እንደሆነ እውቅና መስጠት ይገባ ነበር። በሂደት አዋጅ ቁጥር 148/99 መሰረት የማሕበራዊ ፍርድ ቤት ሥራ-ነገር ሥልጣን ተነስቶ ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት እስከሚመራ ድረስ መጠበቅ አልበረበትም ማለት ይቻላል። የሕግጋቱን ጣምራ ንባብ የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት ሳያውቅ በመዝገብ ቁጥር 106560 ላይ ሲወስን ይህ ከላይ የተጠቀሰው ሁኔታ ይቻል እንደነበር መረዳት ይቻላል። የውሳኔውም ይዘት፡-

> *በአዋጅ ቁጥር 456/97 አንቀፅ 12 እና 17፣ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀፅ 29 እና ደንብ ቁጥር 51/99 አንቀፅ 35(4) መሰረት ጉዳዩን [የመሬት ክርክር] የማየት የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን ያለው የወረዳ ፍርድ ቤት ነው፤ ከተከራካሪ ወገኖች መካከል አንዱ የሌላ ክልል ነዋሪ መሆኑ ጉዳዩን የፌደራል የሚያደርግ አይደለም ብለናል።*[139] የሚል ሀተታ ሰጥቷል።

---

[135] አዋጅ ቁጥር 252/2009፣ አንቀፅ 52

[136] በፌደራሉ ሕገ መንግስት አንቀፅ 78(3) ላይ የክልል ጠቅላይ፣ ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ተቋቁመዋል በሚል ተደንግጓል። በዚህ ድንጋጌ ላይ "የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት" የሚለው በክልል "የወረዳ ፍርድ ቤት" ለማለት እንደሆነ ግምት ይወሰዳል።

[137] ምንም እንኳ ማህበራዊ ፍርድ ቤቱም በሕገ መንግስቱ እውቅና የተሰጠው ቢሆንም ማሕበራዊ ፍርድ ቤት መደበኛ ፍርድ ቤት ሳይሆን ባህላዊ የአካባቢ ባህልን መሰረት አድርጎ የሚሰራ ፍርድ ቤት ነው ማለት ይቻላል።

[138] የአብክመ ሕገ መንግስት፣ አንቀፅ 65 እና 107

[139] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9፣ የእነ አርክሽ (አዛለች) ኪዳኔ ጉዳይን ይመልከቱ።

ይህ የሰበሩ ውሳኔ የሚያሳየን ቁም ነገር፣ በአዋጅ ቁጥር 148/99 መሰረት የመሬት ጉዳይን አከራክሮ መወሰን ለወረዳ ፍርድ ቤት ከማሕበራዊ ፍርድ ቤት ተነስቶ መሰጠቱን መመልከት ሳያስፈልግ፣ የአዋጅ ቁጥር 133/98 እና ደንብ ቁጥር 51/99 ጥምር ንባብ "*መደበኛ ፍርድ ቤት*" የሚለው አገላለፅን ብቻ በመውሰድ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣኑ የወረዳ ፍርድ ቤት የተሰጠ ነው ማለት የሚቻል የነበረ መሆኑን ነው።[140] ነገር ግን ከላይ ከተጠቀሰው የሰበር ውሳኔ በፊት የአማራ ክልል ምክር ቤት የአዋጅ ቁጥር 133/98 ማሻሻያ በሆነው አዋጅ ቁጥር 148/99 በግለፅ ከማሕበራዊ ፍርድ ቤት ወደ መደበኛው ወረዳ ፍርድ ቤት ሲያዛውር የሕግ ግጭት የነበረ መሆኑን አመልክቷል። የሕግ ግጭቱም የነበረው በመሬት አዋጁና[141] በማህበራዊ ፍርድ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 20/89 መካከል የነበረ መሆኑን የሚያመለክት ነው። ይህ ከሆነ የመሬት ሕጉ የመሬት ጉዳይን በሚመለከት ልዩ ሕግ ሲሆን እንዲሁም በቅርቡ የታወጀ ሕግ በመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 20/89 በቅድሚያ ተፈፃሚነት ይኖረዋል የሚል አውዳዊ ትርጓሜ መስጠት ይቻል ነበር።[142] ይህን የትርጉም ችግር ለማስወገድና ከቀደሙት ችግሮች በመገንዘብ በሚመስል ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀጽ 52(2) መሰረት የወረዳ ፍርድ ቤት የመሬት ክርክርን በመጀመሪያ ደረጃ የሚመለከት መሆኑን ግልጽ ድንጋጌ መካተቱ ተገቢ እርምጃ ነው።[143]

---

[140] በዚህ ውሳኔ ላይ ሌላው የታየው ጉዳይ መሬትን በተመለከተ በልዩ ሁኔታ ለክልል የወረዳ ፍርድ ቤት የተሰጠው በክልል ሕግ አወጪ ቢሆንም ውክልናው የተገኘው በፌደራል የመሬት አዋጅ ቁጥር 456/1997 መሰረት አዋጅ ቁጥር 25/1988 (የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ፣ 1988፣ አዋጅ ቁጥር 25፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 2ኛ ዓመት፣ ቁጥር 15) የመሬት ሕግ ልዩ ህግ በመሆኑ ጉዳዩ የፌደራልም ቢሆን የሚቀርበው ለክልል ወረዳ ፍርድ ቤት ነው በሚል አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቷል። ይህም በውክልና የወጣ የክልል ሕግ ከውክልና በላይ ነው የሚል ጥያቄ ያስነሳል። በመሰረቱ በዚህም አዋጅ ላይ ለሕጉ መሻሻል መሰረት ሕግ አውጪው ሲያስቀምጥ፡- *በሥራ ላይ ያለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ በተግባር ላይ ሲውል ከገጠር መሬት ይዞታና አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩትን አለመግባባቶች በመፍታትና ፍትሐብሔር ነክ ክርክሮችን በመዳኘት ረገድ ከሌሎች ህጐች ጋር ባጋጠመው ቅራኔ ምክንያት አንዳንድ ድንጋጌዎቹን መርምሮ ማሻሻል በማስፈለጉ* ነው በማለት በአዋጁ መግቢያ ላይ በግልፅ አስቀምጦታል።

[141] አዋጅ ቁጥር 456/97፣ አንቀፅ 12 እና 17፣ አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀፅ 29 እና ደንብ ቁጥር 51/99 አንቀፅ 35(4)

[142] አሁን ግን ይህ አዋጅ ራሱም ተሽሮ የመሬት ጉዳይን በግልፅ የሰጠው ድንጋጌም አብሮ ተሽሯል። ይህ ድንጋጌ ቢኖርም አልፎ አልፎ የመሬት አስተዳደር አካላት የፍርድ ቤት ውሳኔን ዋጋ በሚያሳጣ መልኩ ሲወስኑ ይታያል። ለምሳሌ *አሚናት እንድሪስ እና ዘይነብ እሸቱ*፣ ሰኔ 2007 ዓ.ም፣ የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደሴ ተዘዋዋሪ ችሎት፣ የሰበር መ/ቁ/ 03-10222 (ያልታተመ) በሆነው ላይ በተሳሳተ ማስረጃ ላይ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ስለሰጠ መሬቱን በፍርድ ከያዘው ሰው የባቲ ወረዳ መሬት አስተዳደር በመንጠቅ ወደ መሬት ባንክ አስገብቶታል። በሌላ መዝገብም በሆነው *የሰከላ ወረዳ አካባቢ ጥ/መ/አስ/አጠ/ጽ/ቤት እና ታደሰ*፣ 2006 ዓ.ም፣ የአብክመ ሰከላ ወረዳ ፍርድ ቤት፣ የፍ/መ/ቁ/ 9013 (ያልታተመ) በተመሳሳይ ተከሳሺ ወ/ሮ ወርቅነሽ ምትኩ መሬቷን አላግባብ በፍርድ ቤት ውሳኔ ተቀምታለች መባሉን በመጥቀስ ክስ አቅርቧል። ይህም የሕግ የበላይነትን የሚጥስ ስለሚሆን በጥንቃቄ መታየት ያለበት ነው።

[143] አዋጅ ቁጥር 252/09፣ መግቢያው 7ኛው ፓራግራፍ ላይ የተመለከተው መሰረተ ሀሳብ ከመሬት ጋራ የተያያዙ የሚነሱ ግጭቶችን ለመቀነስ ሕጉ እንደታወጀ ያመለክታል።

አሁን ላይ የወጣው አዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀጽ 52(2) ላይ የወረዳ ፍርድ ቤት ከመሬት ጋር የተያያዙና መሬት ነክ ክርክርን ተጣምረው ሲመጡ የማየት ብቸኛ ሥልጣን የመኖር አለመኖር ችግር መሆኑን አሁንም መቀጠሉ ግልፅ ነው። ለምሳሌ አላባን በሚመለከት የገንዘብ ግምት ተቀምጦለት ክስ ሲቀርብ ከወረዳ ፍርድ ቤት በላይ ቢሆን ውጤቱ ምን ሊሆን ይችላል የሚለው ምላሽ የሚያስፈልገው ነው።[144] ለዚህም ቀደም ሲል ከወጡ ሕግጋት ይዘት የሕግ አውጪውን ሀሳብ ለመረዳት በአዋጅ ቁጥር 148/99 መሰረት የመሬት ጉዳይ ለወረዳ ፍርድ ቤት ሲሰጥ አዲስ የገባው ድንጋጌ በእንጥልጥል ላይ ስላሉ ጉዳዮች እንደሚከተለው ገልፆታል።

> *ይህ አዋጅ በፀናበት ወቅት የገጠር መሬት ይዞታና አጠቃቀምን የሚመለከቱ ሆነው በገጠር ቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች ስልጣን ስር በምርመራ ላይ ያሉ ፍትሐብሔር ነክ ጉዳዮች በአዋጁ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት በባለጉዳዩቹ ስምምነት የማይፈቱ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ <u>አግባብ ወዳላቸው መደበኛ ፍ/ቤቶች</u> ተዛውረው በመታየት የመጨረሻ ውሳኔ ያገኛሉ።* (ሰረዝ የተጨመረ)

በዚህ ድንጋጌ የገጠር መሬት ይዞታና አጠቃቀምን የሚመለከቱ ፍትሐብሔር ነክ ጉዳዮች አግባብነት "ወዳላቸው መደበኛ ፍ/ቤቶች ይዛወራሉ" የሚለው አገላለጽ መሬት ነክ ክርክሮች ሁልጊዜ ወደ ወረዳ ፍርድ ቤት ብቻ የሚዛወሩ አለመሆኑን የሚያስረዳ ነው። ለምሳሌ ከመሬቱ ላይ የአላባ ዳኝነት ግምት ከ300,000 ብር በላይ ቢሆን መሬቱ በወረዳ ፍርድ ቤት የሚቀርብ ሲሆን የአላባው ጥያቄ ደግሞ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢቀርብ ክርክሩን በመምራት ረገድ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ባህሪያት የሆኑት የውጤታማነትና ወጪ ቆጣቢነቱ ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ ይገባል። በሌላ መልኩ ሁሉም ክርክሮች እንደ መሬት ይዞታ መብት ክርክር መታየት አለባቸው የሚባል ቢሆን በገጠር ክልል የሚገኙ ክርክሮች በአመዛኙ ከመሬት ጋር የተገናኙ ስለሚሆን ክርክሮች በአብዛኛው የሚቀርቡት በወረዳ ፍርድ ቤት መሆን አለበት ሊያሰኝ ሁሉ ይችላል። ሆኖም ክርክሩ የመሬት ክርክር የሌለበት ከሆነና ከመሬቱ የተነጠለን ንብረት ክርክር የሚመለከት ከሆነ ድንጋጌው ላይገዛው መቻሉ አሳማኝ ሀሳብ ነው። ከዚሁ ጋር በሚስማማ ሁኔታ የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በቅርቡ በሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ ላይ የመሬት ይዞታ

[144] አዋጅ ቁጥር 223/2007፣ አንቀፅ 8 መሰረት ከ500,000 ብር በላይ የሆነ የገንዘብ ክርክር የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥረ-ነገር ስልጣን መሆኑን ይደነግጋል።

ክርክር እና ሌሎች ንብረቶች ተነጣጥለው ይቀርባሉ ማለቱ ንብረቱ እንደ ግምቱ መጠን ታይቶ ሥልጣን ለሚኖረው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይገባል የሚለውን ያመላክታል።[145]

በመሆኑም የመሬት ይዞታ ክርክር በወረዳ ፍርድ ቤት መቅረቡ እንደተጠበቀ ሆኖ ችግሩ ከመሬት ይዞታው ጋር የሚቀርበው የንብረት ግምትን በተመለከተ ብቻ በመሆኑ አማራጭ መፈለግ የሚገባው በዚሁ ነጥብ ላይ ብቻ ይሆናል። ለዚህም የመጀመሪያው አማራጭ የንብረት ክርክሩ ከመሬት ጋር እስከቀረበ ድረስ ግምቱ ሳይታይ እንደባልና ሚስት ክርክር በወረዳ ፍርድ ቤት መወሰን አንደኛው አማራጭ ነው። ሁለተኛው ደግሞ የመሬት ክርክሩን በወረዳ ፍርድ ቤት አቅርቦ የመሬት ክርክርና የአላባ ክርክርን መነጣጠል ስለተፈቀደ ከመሬት ጋር የተያያዘውን የገንዘብ ክርክር ራሱን ችሎ ሥልጣን ለሚኖረው ፍርድ ቤት ማቅረብ ነው።

እንደፀሐፊው ግንዛቤ ተቀባይነት የሚኖረው የመጀመሪያው አማራጭ ሁሉንም ክርክሮች የመሬት ይዞታ ክርክር እስካለበት ድረስ በወረዳ ፍርድ ቤት አጠቃሎ ማቅረብ ይገባል የሚለው ነው። በእርግጥ ይህ ሀሳብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 17 መሰረት አንደኛው ጉዳይ ከወረዳው ፍርድ ቤት ከፍ የሚል ከሆነ ከፍተኛው ግምት በሚቀርብበት ከፍተኛው ፍርድ ቤት አጠቃሎ ማቅረብ የሚገባ ከመሆኑ ጋር ተቃርኖ የሚታይበት ነው። ሆኖም በፍርድ ቤት የሚደረጉ ክርክሮችን መነጣጠል ውጤታማነትን የሚያሳጣ ነው። እንዲሁም ከመሬት ይዞታ መብቱ ከፍ ያለ ንብረት ግምት ቀረበ በሚል ምክንያት ክርክሩን መነጣጠሉ ከመሬት ይዞታ መብት የሚበልጥ ክብደት አለው ማለት አመክንዮ ይጎድለዋል። በተጨማሪም ሁለቱ ክርክሮች በተለያየ ፍርድ ቤት ይቅረቡ የሚባል ቢሆን የጭብጥ አያያዝ እና የውሳኔ መጣረስን ሊያስከትል ይችላል። ለምሳሌ ለከሰሰ ሰው ሰብል ይገባዋል በሚል በከፍተኛው ፍርድ ቤት ቢወሰን እና በወረዳው ፍርድ ቤት ለተከሳሹ የመሬቱ ባለይዞታ ነው የሚባል ቢሆን የውሳኔ አፈፃፀም ችግር ማጋጠሙ የማይቀር ነው። ይልቁንም ከዚሁ ጋር የሚመሳሰል የባልና ሚስት ክርክር በአዋጅ ቁጥር 79/95 መሰረት የንብረቱ ግምት የቱንም ያክል ይብዛ ከጋብቻው መፍረስ ጋር አብሮ በውጤት ደረጃ በወረዳ ፍርድ ቤት የሚታይ መሆኑ የተለመደ አሰራር በመኖሩ በዚሁ አግባብ የመሬት ይዞታና ተያያዥ ክርክርን መምራት ጠቀሜታ ይኖረዋል።[146]

የወረዳ ፍርድ ቤት የመሬት ክርክርን ከመመርመርና መወሰን አንፃር ከሌሎች ፍርድ ቤቶችም ጋር የጎንዮሽ ሽሚያ (horizontal competition) ውስጥ የሚገባበት ሁኔታ መኖሩንም መገንዘብ

[145] የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ የሰበር መዝገብ ቁጥር 120087፣ ቅጽ 21"ን" ይመልከቱ።
[146] የአማራ ክልል የቤተሰብ ሕግ፣ አዋጅ ቁጥር 79፣ ገዝረ ሕግ፣ 1995 ዓ.ም፣ 8ኛ ዓመት ቁጥር 3

ያስፈልጋል። ይህም ቀደም ሲል በራሱ የወረዳ ፍርድ ቤት ከሌሎች የክልል መደበኛ ፍርድ ቤቶች ጋር ካለው የሥልጣን ብዥታ (vertical competition) የተለየ ፅንሰ ሀሳብ ነው። በቀጣይ የክልል ወረዳ ፍርድ ቤት ከፌደራል ፍርድ ቤት፣ ከማሕበራዊ ፍርድ ቤት፣ ከከተማ ነክ ፍርድ ቤት እና ከሸሪዓ ፍርድ ቤት ጋር ያለውን ግንኙነትን መመርመር ነው። እነዚህ የተጠቀሱት ፍርድ ቤቶች በሕግ የተሰጣቸውን ጉዳይ ሲያስተናግዱ በሂደት የመሬት ጉዳይን አጣምረው የሚመለከቱበት አጋጣሚ መኖሩ የሕግ ጥያቄ ያስነሳል።

ከዚህ ውስጥ የመጀመሪያው የክልል ወረዳ ፍርድ ቤት ከፌደራል ፍርድ ቤቶች ጋር ያለውን ግንኙነት በሚመለከት የፌደራል ሰበር ሰሚው ችሎት *በእነአርክሽ (አዛለች) ሲዳኔ ጉዳይ* በሰጠው ውሳኔ ላይ "...በተከራካሪ ወገኖች መካከል አንዱ የሌላ ክልል ነዋሪ መሆኑ ጉዳዩ የፌደራል የሚያደርግ አይደለም ብለናል" የሚለው አገላለፅ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80 መሰረት ያለውን የውክልና ግንኙነትም የቀየረ ውሳኔ ነው። ይህም ከመሬት ጋር የተያያዘው ጉዳይ የፌደራል ጉዳይ ቢሆንም እንኳ በክልል ወረዳ ፍርድ ቤት መታየት እንዳለበት በአስገዳጅነት ወስኗል። በእርግጥ ቀጥታ ግጭቱ ያለው በፌደራሉ አዋጅ ቁጥር 25/88 እንደተሻሻለና በክልል መሬት ህግጋት መካከል ነው። ነገር ግን የሰበር ችሎቱ የያዘው ግንዛቤ የፌደራሉ መንግስት በአዋጅ ቁጥር 456/97 በሰጠው ውክልና መሰረት የወጣ የክልል ሕግ በመሆኑ በዚሁ የቅርብ ጊዜ ሕግ ደረጃ መቆጠሩን ያመለክታል። ከሁለቱ የፌደራል አዋጆች በቅርብ ጊዜ መውጣትና ልዩ ሕግ በመሆን ረገድ 456/97 የሆነው በትርጉም አሰጣጥ በቀዳሚነት ተፈጻሚ ይሆናል። ይህንን ጽነሰ-ሀሳብ በሚያንፀባርቅ ሁኔታ በሰበር ችሎት የክልል ወረዳ ፍርድ ቤት የመሬት ክርክርን ለመመልከት ብቸኛ የሥረ-ነገር ሥልጣን (exclusive jurisdiction) ያለው መሆኑ ተወስኗል።[147] ይህም የመሬት ይዞታ ክርክር የፌደራል ጉዳይ ቢሆን እንኳ በክልል ወረዳ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የሚያስገድድ ነው።[148]

ሁለተኛው ከወረዳ ፍርድ ቤት የመሬት ክርክርን በተደራቢነት የመመለከት ጉዳይ የሚነሳው በማሕበራዊ ፍርድ ቤት ነው። በአማራ ክልል የማሕበራዊ ፍርድ ቤቶች በመሬት ጋር የተያያዙ

[147] ይህም በእርግጥ ልዩ ሕጉ የትኛው ነው የሚለውን የሚመለከት ነው። የሰበር ችሎቱ በሰጠው ውሳኔ ላይ የክልል ሕጎችን በቀጥታ ውክልና የወጡ ስለሆነ የፌደራሉን ሕግ ያህል ክብደት ሰጥቷቸዋል። ይህ ከሆነ በሌሎች የክልል ሕግ አውጪ አካላት የሚወጡ ሕጎችን በተመለከተ በቀዳሚነት ተፈፃሚነት ያለው የትኛው ነው የሚለውን የሚያስነሳ ነው።

[148] ከዚህ ላይ በተመሳሳይ ፅንሰ-ሀሳብ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 138 መሰረት በወረዳ ፍርድ ቤት ይታያል የሚለውን የፌደራል ጉዳይም ቢሆን በተመሳሳይ በፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት መወሰኑ የሚታወስ ነው።

ክርክሮችን በሙሉ አከራክሮ የመወሰን የሥረ-ነገር ሥልጣን፣ በህግ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ከመተላለፉ በፊት የነበራቸው ስለመሆኑ የሚታወስ ነው። ሆኖም አሁንም ቢሆን አልፎ አልፎ ለማሕበራዊ ፍርድ ቤት ከተሰጡ የሥረ-ነገር ስልጣናቸው ጋር በማጣመር ውስን ጉዳዮችን በማቀላቀል የሚታይበት አጋጣሚ መኖሩ አልቀረም። ለዚህም ማሳያዎች በመጀመሪያ ደረጃ በአዋጅ ቁጥር 246/09 አንቀፅ 19(2) ላይ የማሕበራዊ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ዳኝነት የሥረ-ነገርን ስልጣን ሲደነግግ "... በአካባቢ ደረጃ የሚነሱና በገንዘብ የማይተመኑ አለመግባባቶችን እና ከዚህ በታች የተመለከቱትን የፍትሐብሔር ነክ ክርክሮችና አለመግባባቶችን የመመርመርና የመዳኘት ሥልጣን ይኖራቸዋል" በሚል ተደንግጓል።[149] በአዋጅ ቁጥር 246/09 አንቀፅ 19(2) ከዚህ በታች የተጠቀሱት የተባሉት እንደመተላለፍ መብት፣ የውሃ ቦይ መተላለፊያ፣ በእጅ ያለ መሬት፣ ከወደታች የሚገኝ መሬት እና ሌሎች ክርክሮች ከመሬት ይዞታ አጠቃቀም ጋር በቀጥታ ስለሚገናኙ በማህበራዊ ፍርድ ቤት ክርክር እንዲታይ ሥልጣን መሰጠቱ ከመሬት አዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀፅ 52(2) እና (8) ጋር የሚጣረስ በመሆኑ ሕጋዊነት ሊኖረው አይገባም።[150] በሁለተኛ ደረጃ ከመሬት ጋር በማህበራዊ ፍርድ ቤት የገንዘብ መጠን ያለው ንብረት ተጠቅሶ ቢቀርብ ከላይ በፍርድ ቤቶች እርከን መካከል ያየነውን ብዥታ መፍጠሩ አይቀርም። ሆኖም ከመሬቱ ላይ የተነጠሉ እንደሰብል፣ ሳር፣ ዛፍ የመሳሰሉት በማህበራዊ ፍርድ ቤት እንዲታይ ያለው የገንዘብ ግምት ድረስ ዳኝነት ቢቀርብ የማሕበራዊ ፍርድ ቤት የሥረ-ነገር ዳኝነት ሊሆን ይችላል። ሆኖም በክርክሩ ላይ ለምሳሌ ተከሳሽ በመልሱ ላይ የመሬቱ ባለይዞታ መብትን የሚመለከት ክርክር ቢያቀርብ የማሕበራዊ ፍርድ ቤት የሥረ-ነገር ሥልጣን መኖሩ ሊያከራክር ይችላል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በተከሰተ ጊዜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 17 መሰረት ሁለቱንም ክርክሮች ወደ ወረዳ ፍርድ ቤት መላክ ተገቢነት ይኖረዋል። ከማሕበራዊ ፍርድ ቤት የመሬት ክርክር የሥረ-ነገር ሥልጣን የተነሳው ዳኞቹ የመሬት ክርክር ያለውን ውስብስብነት ተገንዝበው በመዳኘት ረገድ ጉድለት የሚኖርባቸው መሆኑን እንዲሁም በቀላሉ ለሙስናና ለብልሹ አሰራር የሚጋለጡበት ሁኔታ

---

[149] አሁን ላይ ተፈፃሚነት ያለውና የተሻሻለው የማሕበራዊ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 246/09 አንቀጽ 19(2) የመሬት መብትን የሚነኩ ጉዳዮች መነሳታቸውን በተመለከተ ብዙም የተለየ አይደለም። በዚህ ድንጋጌ በገንዘብ የማይተመኑ ጉዳዮች የሚለው በአዋጅ ቁጥር 223/2007 አንቀጽ 14(2) መሰረት አስቀድሞ ለወረዳ ፍርድ ቤት የተሰጠ በመሆኑ የዚህ ድንጋጌ ክፍል ተፈፃሚነት የሚኖረው አይሆንም።

[150] እንዲህ ዓይነት መብቶች ቀደም ሲል በአዋጅ ቁጥር 20/89 መሰረት ለማሕበራዊ ፍርድ ቤት በግልፅ ተሰጥተው የነበረ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል። ለምሳሌ *አህመድ ይመር እና ጋሻው ዘሩ*፣ 2006 ዓ.ም፣ የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደሴ ተዘዋዋሪ ችሎት፣ የሰበር መ/ቁ/ 03-10256 (ያልታተመ) በሆነው ላይ የባህር ዛፍ ክርክር በተነሳበት ላይ የመሬት ክርክር ተነስቶ እያለ የባህር ዛፉ ግምት ላይ ብቻ በማተኮር ተወስኗል።

መኖሩን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው።[151] ስለሆነም አሁን ባለው አሰራር የማህበራዊ ፍርድ ቤት የመሬት ጉዳይን በውጤት ረገድ አከራክሮ የመወሰን ሁኔታ ሲያጋጥም የሥልጣን ወሰናቸው በጠባቡ መተርጎም ይኖርበታል።

ሶስተኛው የወረዳ ፍርድ ቤት ሥልጣን ብዙውን ጊዜ የሚነሳው ችግር ከከተሞች መስፋፋት ጋር ተያይዞ ወደ ከተማ የሚከለሉ የገጠር የእርሻ መሬትን አስመልክቶ የመሬት ጉዳይን የትኛው ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን አለው የሚለው ነጥብ ነው።[152] ይህም በከተማ ነክ ፍርድ ቤት፣ በከተማ አስተዳደር መደበኛ ወረዳ ፍርድ ቤት እና የአካባቢ ገጠር መደበኛ ወረዳ ፍርድ ቤት ሚና መለየትን ይጠይቃል። የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶችን የሥረ-ነገር ሥልጣን ስንመለከት ለረጅም ጊዜ ተፈጻሚ የነበረው በአዋጅ ቁጥር 91/96 መሰረት የተቋቋሙና በአዋጁ ማስፈፀሚያ ደንቦች ስልጣናቸው ሲወሰን የቆየ ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል።[153] በቀድሞ ሕግጋት ላይ የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች በገጠር መሬት ክርክር ላይ የዳኝነት ሥልጣን ስለመኖር አለመኖሩ በተለያዩ መድረኮች ክርክር ሲደረግ የነበረ መሆኑ ይታወሳል። የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተከታታይና ተቀራራቢ ውሳኔ በመስጠት በሁለቱ ፍርድ ቤቶች መካከል የነበረውን ውዝግብ ለመቀነስ ጥረት ያደረገ መሆኑን የሚያመለክቱ መዝገቦች አሉ።[154] ሆኖም በሂደት የሥረ-ነገር ስልጣናቸው በደንብ ሲደነገግ የተፈጠረውን ብኽርታ ለማስወገድ አዋጅ ቁጥር 91/96 የሆነውን በማሻሻል አዋጅ ቁጥር 226/07 የሆነው ታውጇል።[155] አሁንም ይህን ችግር ለማስቀረት በወጣው ሕግ ላይም ተመሳሳይ ብኽርታዎች እንዳልተወገዱ መመልከት ይቻላል።

በአዲሱ አዋጅ ቁጥር 226/07 የተተካው አንቀፅ 57(1)(ሀ) ለከተማ ነክ ፍርድ ቤት የስረ-ነገር ስልጣን ሲሰጥ "የመሬት ይዞታ ባለመብትነት" የሚለው ከሌሎች ጉዳዮች ጋር ተካቷል። ሆኖም

---

[151] ቀደም ሲል በአዋጅ ቁጥር 31/67 መሰረት የመሬት ጉዳይን ይመለከት ከነበረው የገበሬ ማህበር ፍርድ ሸንጎ ለከፍተኛ ብልሹ አሰራር የተጋለጠ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ።

[152] *አለሙ ካሴ እና ጤናየ ጋሻው፣* 2004 ዓ.ም፣ የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የሰበር መዝገብ ቁጥር 09499 (ያልታተመ) እና ሌሎች የክልሉ ሰበር መዝገቦችን 17806፣ 14880፣ 16858፣ 14420 እና 14459ን መመልከት ይቻላል።

[153] በሶስቱ የሜትሮፖሊታን ከተሞች ማለትም ደሴ፣ ጎንደርና ባሕር ዳር እንዲህ ዓይነት ፍርድ ቤቶችን በማቋቋም ሲሰሩ የቆዩ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

[154] ሰኔ ወር 2005 ዓ.ም የፍትህ አካላት በቀድሞው የክልሉ ምክር ቤት አዳራሽ ከክልሉ ከፍተኛ አመራሮች ጋር በተደረገ ውይይት የከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የሥረ-ነገር ሥልጣን ተገፋ በሚል አቶ መርሀዕድቅ መኮንን የርዕስ መስተዳደሩ አማካሪ የሆኑት የሕግ ባለሙያ ሲከራከሩ ነበር።

[155] የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ከተሞችን ለማቋቋም፣ ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራትን ለመወሰን እንደገና ማሻሻያ አዋጅ፣ 2007፣ ዝክረ ሕግ ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 226፣ 20ኛ ዓመት፣ ቁጥር 149 (ከዚህ በኋላ አዋጅ ቁጥር 226/2007 እየተባለ የሚጠራ) ይህ አዋጅም በድጋሜ በአዋጅ ቁጥር 247/2009 መሰረት በድጋሜ የተሻሻለ ሲሆን በፍርድ ቤት ሥረ-ነገር ስልጣን መለወጥ ዓላማ የወጣ ባለመሆኑ በቀድሞው አዋጅ የሚሰጠው ሀሳብ ብዙም ማዛባት አላመጣም።

ይህ ማለት ወደ ከተማ የተከለሉ የገጠር መሬት ይዞታና አጠቃቀም ክርክር ማለት ስለመሆኑ ምላሽ የሚጠይቅ ነው።[156] በድንጋጌው በራሱ ወደ መጨረሻው ክፍል "... ሕግጋት፣ ደንቦችና መመሪያዎች የሚመለከቱ ጉዳዮች" የሚለው ሲታይ በግለሰቦች መካከል የሚደረግ የመሬት ይዞታ ክርክርን ሳይሆን የመሬት ሕጎችን የሚመለከት በሚመስል አግባብ የተቀረፀ መሆኑን ያሳያል። ይህን የበለጠ ግልፅ የሚያደርገው የአዋጁ የእንግሊዘኛው ቅጅ "land administration and use laws" በሚል የተገለፀው በከተማ ነክ ፍርድ ቤት የሚመለከተው ሕጉን ብቻ መሆኑን ያስረዳል። ስለሆነም ከዚህ ትርጉም በመነሳትም የመሬት ይዞታ በግልፅ በዚህ ድንጋጌ ሥር ለከተማ ነክ ፍርድ ቤት ከተሰጡት የሥራ-ነገር ሥልጣን ጋር በቀጥታ ካልተያያዘ በስተቀር የመሬት ይዞታ ክርክር በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚታይ ነው የሚለውን ድምዳሜ መያዝ ይቻላል።

ለዚህ ጥያቄ ቀጥታ ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችለን ወደ ከተማ አስተዳደር የሚከለሉ የገጠር መሬቶችን በተመለከተ ሥልጣን ከሚኖረው ፍርድ ቤት የበለጠ ትኩረት የሚጠይቀው ተፈፃሚነት ያለውን መሰረታዊ የመሬት ሕግ መለየት ላይ ነው። በመርህ ደረጃ የትኛውም መሬት ወደ ከተማ ከተከለለ በኋላ የሚተዳደረው በሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 መሰረት ስለሚሆን የፍርድ ቤቶች ስልጣን ውስን ነው።[157] ይህን ውስብስብ ችግርም የክልሉ መሬት አዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀጽ 2(1) በሰጠው ትርጉም የገጠር መሬት ማለት ወደ ከተማ የተከለለ የገጠር መሬትንም የሚያጠቃልል ነው በሚል ትርጉም ሰጥቷል። በመሆኑም ወደ ከተማ የተከለለ የገጠር መሬት ከባቢያዊ ሥልጣኑ የከተማ አስተዳደር ወረዳ ፍርድ ቤት ቢሆንም ተፈፃሚነት ያለው የገጠር መሬት እንደሆነ መገንዘብ ተገቢነት ያለው ነው። መሬቱ ይገኝበት የነበረው የወረዳ ፍርድ ቤቱም ወደ ከተማ የተከለለን የገጠር መሬት ለመዳኘነት

---

[156] የአዋጅ ቁጥር 226/2007 ንዑስ አንቀፁ ይዘትም "የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አጠባበቅ፣ የመሬት ይዞታ ባለመብትነት፣ የሕንፃ ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፣ የቦታ አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግጋት፣ ደንቦችና መመሪያዎች የሚመለከቱ ጉዳዮች" በሚል የተቀመጠ ነው።

[157] የሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004ም ሆነ አዋጅ ቁጥር 133/98 የገጠር መሬት ማለት አግባብ ያለው አካል የከተማ ክልል ብሎ ከሚጠራው ውጭ ያው ሲሆን የመሬት ሕጉ ተፈፃሚነቱ በገጠር መሬት ላይም ነው። በዚህ ላይ የሚፈጠረው መምታታት ለፍርድ ቤቶችም ሆነ ለአስተዳደር አከላት ችግር ሲሆን ይታያል። ሆኖም ከዚህ ላይ አብሮ መታየት ያለበት አንድ የገጠር መሬት ወደ ከተማ ሲከለል አስቀድሞ ካሳ ከፍሎ ከተማው እንዲያዝበት ካልተደረገ በስተቀር አርሶ አደሩ ወደ ከተማ በመጠጋቱ ብቻ በከተማ ክልል እየተከለለ ከመሬቱ አላግባብ ሲፈናቀል ያለመፍትሔ የሚቀርበት ሁኔታ መፍጠሩ የማይቀር ነው። በሊዝ ደንብ ቁጥር 103/2004 ላይም የሊዝ ሕጉን የተፈፃሚነት ወሰን ለመለየት ጥረት የተደረገ ስለመሆኑ ለመረዳት ይቻላል። ይልቁንም አዋጅ ቁጥር 230/2008 ቢሮዎች ሲቋቋሙ የገጠር መሬትን ማስተዳደር ለመሬት አስተዳደር ስልጣን መሰጠቱ የገጠር መሬት በባሕሪያቸው የከተማ መሬት ሁኔታ አለመሆኑንና የገጠር እርሻ መሬትነቱን እንደያዘ መቀጠሉን የሚጠቁም ነው። ከዚህ ላይ ፍርድ ቤቶች ስልጣን የማይኖራቸው ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ መሬቱ ሲወሰድ ብቻ ስለመሆኑ ከሊዝ አዋጁም ሆነ ከገጠር መሬቶች ይዘት መረዳት ይቻላል።

ከባቢያዊ ሥልጣን በአስተዳደራዊ ወሰኑ መለወጥ ምክንያት የሚያጣ ይሆናል። ይህ የአዲሱ መሬት አዋጅ ትልቅ ለውጥና የአርሶ አደሮችን ተጠቃሚነት የሚያሳድግ ነው። በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 52(2) መሰረት የወረዳ ፍርድ ቤት ብቸኛ የሥረ-ነገር ሥልጣን ያለው መሆኑን የደነገገ በመሆኑ ቀደም ሲል ከከተማ ነክ ፍርድ ቤት ጋር ያለውን የሽሚያ ዝንባሌ በዚሁ የሚቋጭ መሆን አለበት።

አራተኛው የሽሪዓ ፍርድ ቤት የመሬት ጉዳይን በባልና ሚስት ክርክር ውስጥ በማካተት አከራክሮ መወሰን መቻሉ የሕግ ክርክር ያስነሳል። አዋጅ ቁጥር 132/98 አንቀጽ 4 ላይ እነደተደነገገው በፈቃድ ላይ በተመሰረተ አግባብ የጋብቻ፣ የፍችና የንብረት ክፍፍል እንዲሁም የውርስ፣ ኑዛዜና ስጦታንና የመሳሰሉትን የፍትሐብሔር ክርክሮች አስመልክቶ በእስልምና ሕግ መሰረት በሽሪዓ ፍርድ ቤት ሊዳኙ የሚችሉ ስለመሆኑ ተደንግጓል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ የመሬት ጉዳይ አብሮ እንደ ጋብቻ ንብረት ተቆጥሮ በሽሪዓ ፍርድ ቤት ሊስተናገድ የመቻሉ ጉዳይ ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። ይህን አስመልክቶ ሁለት ክርክሮች ሊቀርቡ ይችላሉ። የመጀመሪያው የሽሪዓ ፍርድ ቤት የጋብቻ ክርክርን ሲመለከት መሬትም እንደ ጋብቻ ሀብት ተቆጥሮ በእስልምና ሕግ መሰረት ውሳኔ ሊያገኝ ይገባል እንጅ መሬት ብቻውን ተነጥሎ ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ይሂድ ሊባል አይችልም የሚል ሀሳብ ይነሳል። በአዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀፅ 52 መሰረት የመሬት አለመግባባትን ተከራካሪ ወገኖች በስምምነት ጉዳያቸውን መጨረስ የሚችሉ ከሆነ እንዲሁም በአስታራቂም መስማማት ይችላሉ ከተባሉ በተመሳሳይ ደረጃ ስምምነትን መሰረት አድርጎ ወደ የሽሪዓ ፍርድ ቤት ባለጉዳዮች ከሄዱ የሽሪዓ ፍርድ ቤቱ ሥልጣን አለው ማለት ይቻላል። ለዚህ ክርክርም መነሻ የሽሪዓ ፍርድ ቤት ሥልጣን መሰረቱ ስምምነት በመሆኑ ነው። ሁለተኛው ክርክር ደግሞ የመሬት ጉዳይ እንደ ማንኛውም ንብረት ያልሆነና የፖሊሲ ጉዳይን የሚመለከት በመሆኑ በግልፅ ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ በመሬት ሕጎች መሰረት መዳኘት አለባቸው የሚሉ አሉ። ለዚህም አዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀፅ 52(8) ከመሬት አስተዳደር አካሉና ከመደበኛው ፍርድ ቤት ውጭ ሌላ አካል መወሰን አይችልም በሚል ክልከላ ማድረጉም ለዚህ ክርክር ደጋፊ ነው። እንደ ፀሐፊው ሀሳብ ሁለተኛው መከራከሪያ ከሕጉ አቀራረፅ አንፃር ተቀባይነት ያለው ይመስላል። ለዚህ ደግሞ ከላይ ያየናቸው የመሬት ሕግ ማዕቀፍና የሰበር ችሎት ውሳኔ መደበኛው የወረዳ ፍርድ ቤት ብቸኛ ሥልጣን አለው በሚል ስለተተረጎመ የመሬት ጉዳይን የሽሪዓ ፍርድ ቤት ሊመለከት አይችልም

የሚያሰኝ ነው።[158] ሆኖም በዚህ አካሄድ ክስ ተነጣጥሎ መታየት እና በአዋጁ ላይ የመደበኛ ፍርድ ቤትና የሸሪዓ ፍርድ ቤት አንዱ በአንዱ ጣልቃ አይገቡም ከሚለው መርህ ጋር አብሮ የሚሄድበት አግባብ በሂደት የፍርድ ቤቶችን ተግበራዊ አሰራር በተለይም የፌደራል ሰበር ችሎትን አስገዳጅ የሕግ ትርጉምን የሚጠይቅ ነው። በመሆኑም የመሬት ይዞታና አጠቃቀምን አስመልክቶ በመጀመሪያ ደረጃ በየትኛው ፍርድ ቤት ይታይ የሚለው በቀላሉ የሚታለፍ አለመሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሕጉን መቃኘት የሚገባና በፍርድ ቤቶች የዳበረ አሰራር እንዲኖር ይጠበቃል።

በመጨረሻም ፍርድ ቤቶች በሕግ የተዘረጋውን የይግባኝና የሰበር ሥርዓት በመጠቀም ስህተቶችን የሚያርሙ ሲሆን የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልገዋል ከተባለ የፌደሬሽን ምክር ቤት በመሬት ክርክር ውሳኔ አሠጣጥ ላይ የራሱ ሚና ያለው መሆኑን ማጤን ይገባል። በቅርቡ የመሬት ጉዳይን አስመልክቶ የፌደሬሽን ምክር ቤቱ በብዛት ውሳኔ መስጠቱን የሚያሳዩ ውሳኔዎች እየወጡ ነው።[159] በዚህ ውሳኔ ላይም የፌደሬሽን ምክር ቤት ከሥልጣኑ በላይ በማለፍ ውሳኔ የሰጠ መሆኑን የውሳኔው ይዘት ይጠቁማል። የዚህ አይነት አካሄድ የሚጠቁመን ሁሉም የመንግሥት አካላት ለመሬት መብት መከበር ድርሻቸውን ለመወጣት ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ሲሆን በተጨማሪም የገጠር መሬት መብት መከበር ትኩረት እያገኘ መምጣቱን ነው። ሆኖም ከላይ ከተመለከትናቸው የመሬት ክርክር ውሳኔ ሰጭ አካላት መበራከት የገጠር መሬት ክርክር አፈታትን ውስብስብ እንዳያደረገውና አልፎ አልፎ ባለመናበብ በሚፈጠር ችግር የይዞታ መብትን የሚያሳጣ አሰራር እንዳይፈጠር ጥንቃቄ የሚያስፈልግ መሆኑን ለባለድርሻ አካላት ጠቋሚ ነው።

3.3.2 በፍርድ ቤት የመሬት ክርክር አመራር የማስረጃ ተቀባይነትና አሰባሰብ ችግሮች

የወረዳ ፍርድ ቤት የሥረ-ነገር ሥልጣን አለው ከሚለው ፅንሰ-ሀሳብ አወዛጋቢነት ባልተናነሰ በመሬት ክርክር ሂደት ውስጥ የማስረጃ አቀባበልና አግባብነት ጉዳይም አከራካሪ ነው።[160]

---

[158] የእነአርክሽ (አዛለች) ኪዳኔን ጉዳይ ይመልከቱ

[159] ወ/ሮ ቀልቤ ተስፋ እና አቶ አየልኝ ደርበው፣ የኢፌዴሪ የፌደሬሽን ምክር ቤት 4ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ፣ ሰኔ 18 ቀን 2007 ዓ.ም (ያልታተመ)። መሬትን በመያዣ ስለተሰጠ ሕገ መንግስቱን ይጥሳል የሚለውን መደምደሚያ ዝርዝር የክርክሩን ይዘት ከተመለከተ በኋላ ምክር ቤቱ የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር መወሰኑን ያሳያል።

[160] አቻምየለህ ጋሹ፣ የመሬት አስተዳደር ፅነሰ-ሃሳብ፣ ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች የተዘጋጀ የስልጠና ጽሑፍ፣ ባህርዳር ዩንቨርሲቲ መሬት አስተዳደር ኢንስቲትዩት፣ (መስከረም/ 2006 ዓ.ም) ያልታተመ

የወረዳ ፍርድ ቤት የመሬት ክርክርን በመምራትና ቅርፅ በማስያዝ ረገድ ሰፊ ስልጣን አለው። ነገር ግን ፍርድ ቤት በሕግ እንዲወስነው የተሰጠውን የመሬት ጉዳይ ወደ ሌሎች አካላት በውጤት ደረጃ እንዲወስኑት ማስተላለፍ የዳኝነት ስልጣንን አሳልፎ መስጠት ከመሆኑም በላይ ዜጎች አሉን በሚሏቸውና በህግ ክልከላ ባልተደረገባቸው ማስረጃዎች በፍርድ ቤት ተሟግቶ ፍትህ የማግኘት መብትን የሚገታ አሰራር ነው።

አሁን በተግባር እየተሰራ ያለው የመሬት ባለሙያው የሚልከው ማጣሪያ እንደ መጨረሻና የማይስተባበል ማስረጃ አድርጎ የመውሰዱ አዝማሚያ ፍትህን የሚያዛባ መሆኑ የማይቀር ነው።[161] ነገር ግን እውነታው ሲመረመር በተለያዩ የፍርድ መዝገቦች ላይ አንድ የመሬት ባለሙያ የሚልካቸው ማሥረጃዎች ወጥነት የጎደላቸውና አንዳንድ ጊዜም እርስ በእርሳቸው የሚጣረሱ ናቸው።[162] የመሬት ባለስልጣኑ አስቀድሞ ተጽፎና ተመዝግቦ ያልተያዘ ፍሬ ነገርን፣ ለምሳሌ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ይዞታን (ከባህር መዝገቡ ላይ የሚሰጥ ማስረጃ) ሳይሆን በመስክ ላይ ውስን ሰዎችን በመጠየቅ ብቻ የሚሰበሰብ ፍሬ ነገርን፣ ለውሳኔ መጠቀሙ የቀረበው ማስረጃ ለሙስና የሚጋለጥና ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህንም ላያሰፍን ይችላል። ይህ ማስረጃ በፍርድ ቤት ቀርቦ ከሚሰጠው የምስክርነት ቃልም የሚለይ አይሆንም። እንዳውም ፍርድ ቤት ቀርቦ የሚሰጥ ቃል ቃለ-መሀላ ተፈጽሞ የሚሰጥና መስቀለኛ ጥያቄም የሚጠየቅበት ስለሚሆን የበለጠ ክብደት ሊሰጠው ይችላል። ይልቁንም ፍርድ ቤቶች ከክርክሩ በመነሳት ተገቢውን ጭብጥ እንኳን በአግባቡ ሳይያዝ በቀጥታ ለክፍሉ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት መሬቱ የማን እንደሆነ ተጣርቶ እንዲቀርብ በማዘዝና በመጣው ማስረጃ ላይ ብቻ በመመስረት መወሰን ይታያል።[163]

---

[161] እነአዱኛ አበራ እና መኪ አያሌው፣ የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ 2005፣ የሰበር መ/ቁ/ 24594 (ያልታተመ)። በዚህ መዝገብ ላይ ጉዳዩ መጀመሪያ ከጫሚት ንዑስ ወረዳ ፍርድ ቤት የጀመረ ሲሆን የተጠሪው ክስ 6 ሜትር የሆነ መሬት ገፉን በማለት በአዋሳኝ የተቀነሰ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ግን ጭብጥ በአግባቡ ሳይዝ በውሳኔው ላይ ጠቅላላ መሬቱን እንደጠየቀ በማድረግ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ የካቲት 11 ቀን 2005 ዓ.ም ከሰበር ችሎቱ እንደገና አከራክሮ እንዲወስን ተመልሶለታል።

[162] ፀሐፊው ዳኛ ሆኖ በችሎት ሲሰራ ብዙ ጊዜ ከበርካታ መዝገቦች የተገነዘበው ነው።

[163] ወርቁ ያዜ ወዳጀ፣ በገጠር መሬት የይዞታ ክርክር ሂደት ትኩረት የሚያሻቸው የማስረጃ ሕግ ጉዳዮች፣ በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ መሬት አስተዳደር ኢንስቲትዩት እና የስዊድን የልማት ተራድኦ ድርጅት ድጋፍ ለወረዳ ፍ/ቤት ዳኞች ስልጠና የተዘጋጀ (መስከረም 2006 ዓ.ም) ያልታተመ። በዋናነትም የመሬት ሕግ ከሥነ-ሥርዓት ህግ ጋር ያለው ግንኙነት የጠበቀ ነው። ዳኞች የመሬት ክርክርን ሲመሩ ተከራካሪ ወገኖችን በጥሞና ከማዳመጥ ባለፈ የታመነው ወዲያውኑ መወሰን እና በተካደው ላይ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ጭብጥ በመመስረት በተገቢ ማረጋገጫ አጣርቶ መወሰን ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው የሚለውን ጽነሰ ሀሳብ ከተግባሩ ጋር በማገናዘብ መረዳት ይገባል የሚለውን የሚያንጸባርቅ ዕሁፍ ነው።

የመሬት ባለሙያ ከቦታው ድረስ በመሄድ ማስረጃ የሚቀርብበት ሁኔታ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136 እና ተከታይ ድንጋጌዎች በፍርድ ቤት የሚላክ ምትክ ዳኝን በሚመስል መልኩ ከሆነ ያለውን የአስረጅነት ሚዛን በመጠበቅ መወሰን ስህተት አይሆንም፡፡ ሆኖም የሚታለፈው ጉዳይ በመሬት ጉዳይ የሚጣራው ፍሬ-ነገር በሰው ምስክርም የሚጣራ መሆኑ መዘንጋቱ ነው፡፡ የመሬት ክርክር ሁልጊዜ ሙያዊ እውቀት የሚጠይቅ ነው ማለትም የሚቻል አይደለም፡፡ መሬትን አስመልክቶ የሚደረግ ክርክር የመሬት ባለሙያው በራሱ አግባብ ያጣራውን ፍሬ ነገር በመውሰድ ፍርድ ቤት የሚወስን ከሆነ ቀድሞውንም ፍርድ ቤት ክርክር ማቅረብ ሳያስፈልግ ለመሬት አስተዳደር ሙሉ ሥልጣን መስጠት በተገባ ነበር፡፡ በሕግ አውጪው የመወሰን ሥልጣን ተለይቶ ቢሰጠውና ኃላፊነቱን ሳይወጣ ሲቀር ተጠያቂነትንም የሚያስከትል አሰራር ለመፍጠርም ያስችል ነበር፡፡ አለበለዚያ በሕግ በፍርድ ቤት እንዲወሰን የተሰጠን ኃላፊነት አሳልፎ ከሰጡ በኋላ መወጋገዝ ከምክንያታዊነት የራቀ ነው፡፡

በተጨማሪም በመሬት ማስረጃ አቀባበል ውስጥ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ያለውን ሚና በተመለከተም የግንዛቤ ችግሮች አሉ፡፡ የመጀመሪያው የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ማስተባበያ የማይቀርብበት አድርጎ የመውሰዱ ነገር በራሱ የችግር ምንጭ እየሆነ መጥቷል፡፡ በመሰረቱ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የተሰጠበት አግባብ እንከን የሌለው ቢሆን ኖሮ ፍርድ ቤቶች በመሬት ጉዳይ መዛግብት እንዳይጨናነቁ የሚያደርግ ይሆን ነበር፡፡[164] ለባለጉዳዮችም ቢሆን የፍርድ ቤት ክርክርን ቢያንስ የሚቀንስላቸው ይሆናል፡፡ ሆኖም በክርክር ሂደት ውስጥ የሚታየው ከዚህ የተለየ ሁኔታ ነው፡፡ የመሬት ይዞታ ደብተር በአስተዳደራዊ ውሳኔም የሚሰረዝ ሰነድ እንጅ አይነኬ ሰነድ ለማስመሰል መሞከር ተገቢነት የለውም፡፡[165] በመሆኑም ከይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በተጨማሪ ያሉ ማስረጃዎችን በመመልከት መወሰን የፍርድ ቤት ተግባር መሆኑን ማስቀረት የሕገ መንግሥቱን አንቀፅ 37 ፍትህ የማግኘት መብትን የሚጥስና ዳኞችንም ያለማመን ሁኔታ ነው፡፡[166]

---

[164] ወ/ሮ ዘውዳ ገ/ስሊሴ እና ወ/ሮ ህይወት ባህታ፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ (ቅፅ 9) መ.ቁ 36320፣ ጥቅምት 21 ቀን 2001 ዓ.ም፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይም የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለንብረትንት ካርታ በማቅረብ ብቻ ሊወሰን የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1195 ተጠቅሶ ተወስኗል፡፡

[165] ለምሳሌ ያክል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 6ን መመልከት ይገባል፡፡

[166] በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 1196 እና ተከታይ ድንጋጌዎችም ይህን አስመልክቶ ፍርድ ቤቶች የከተማ ቤት ይዞታ ማረጋገጫ እያለም ቢሆን ውሳኔ የሚሰጥባቸው ምክንያቶች ያሉ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎትም በቅርብ በወጡት ቅፆች ላይ ይህን በሚያጠናክር መልኩ የሰጣቸው ውሳኔዎች ያሉ ስለመሆኑ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በሚቃረን አግባብ በአዲሱ የመሬት አዋጅ ቁጥር 252/09 አንቀፅ 35 ላይ የዳኞችን ስም ጠርቶ የይዞታ ደብተር እንዲቀበሉ ያዛል፡፡ ወረድ ብሎ ደግሞ ጠንከራ የዕሁፍ ማስረጃ ከቀረበ ደብተሩ ሊስተባበል ይችላል

አንዳንድ የሕግ እና የመሬት ባለሙያዎች ፍርድ ቤቶች ከይዞታ ማረጋጫ ደብተር በመለስ ያሉትን ማስረጃዎች የሚቀበሉበትን አግባብ ከሥልጣናቸው ውጭ የመሬት አስተዳደር አካላትን ሥልጣን በመጋፋት የሚከናወን መሆኑን የሚገልፁበት ሁኔታ ይታያል።[167] በፀሀፊው ግንዛቤ ይህ አገላለፅ ብዙም ተቀባይነት ያለው አይመስልም። የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎትም የሰጠው ውሳኔ የሚያሳየው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አስገዳጅና የማይስተባበል አለመሆኑንና የሰው ምስክርም በመስማት ጭምር ሊስተባበል ስለመቻሉ ወስኗል።[168] የሰበሩ ውሳኔ ይዘት የሚያሳየን የመሬት ክርክር ያላቸው ወገኖች አሉን የሚሉትን ማስረጃ ሁሉ በፍርድ አደባባይ አቅርበውና ተመዝኖ መብታቸውን የሚያስከብሩበት እድልን ስለሚፈጥር ፍትሐዊ ነው ለማለት ያስችላል። የደብተሩ አሰጣጥ ችግር ያለበት መሆኑ በመሬት አስተዳደር ባለሙያዎችም ጭምር የሚታመን ነው። በመሆኑም በአማራ ክልል አብዛኛው አርሶ አደር የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አውጥቷል የሚባል ከሆነና ደብተሩም አይስተባበልም ከተባለ ይህ ሁሉ አርሶ አደር ወደ ፍርድ ቤት የመሬት ይዞታ መብት ክርክር የማቅረብ መብት የለውም እንደማለት ይሆናል።

በመሬት ማስረጃ አሰባሰብ ሂደትም በሕዝብ ተሳትፎ ተጣርቶ የሚቀርብበትን አግባብም መመልከት ተገቢ ነው። በሕዝብ ችችት የሚቀርብ ማስረጃን በተመለከተ በሕዝብ ተሳትፎ በብዛት ግልጽና ፍትሐዊ ማስረጃ ይቀርባል የሚል መነሻ ቢኖረውም ሁልጊዜ የሚሰራ ግምት ነው ለማለት ያስቸግራል። ይህ አሰራር እጅግ ለፍትህ አሰጣጥ ሲባል ቢደረግ ችግር ላይኖረው ይችላል። ነገር ግን በግለሰቦች መካከል የመሬት ክርክር በተነሳ ጊዜ ሁሉ የቀበሌው ሕዝብ ለመተቸት ይሰብሰብ የሚለው ተገቢነት ያለው አይመስልም። የመጀመሪያው ነገር ለአንድ ክርክር ከጎጡ ሰው ምን ያህል ሰውና በምን አግባብ መሳተፍ አለበት የሚለው ከወጪና ከጊዜ አንጻር አዋጭነት የለውም። ከፍትሐዊነት አንፃርም ግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች በማጣራት ሂደቱ ላይ በእኩልነት መሳተፉ ላይ ችግር አለው፤ የውሳኔ ሰጪው ሕዝብ ተጠያቂነትም መርህ የለውም። በዚህ ሂደትም አቅመ ደካሞች፣ ሴቶች ወይም ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች

የሚለው ለመሬት አስተዳደር አካላት የበላይነት እና እምነት የሰጠ ነው። ነገር ግን ለዜጎች የተሰጠውን ፍትህ የማግኘት መብት የሚያጣብብና በመንግሥት መዋቅር ውስጥ የፍርድ ቤትን አስፈላጊነት ዋጋ ያሳጣ ነው።

[167] ፀሐፊው ዳንግላ ከተማ በ2005 ዓ.ም በመሬት ርዕሰ ጉዳይ ስብሰባ በነበረበት ወቅት በተሳታፊዎች ሲቀርብ ከነበረው ሀሳብ ተገንዝቧል። ስብሰባውም የተዘጋጀው የግብርና ሚኒስቴር፣ ለአማራ ክልል ወረዳ ዳኞች፣ ዐቃቢያነ ሕጎች እና የመሬት አስተዳደር ባለሙያዎች ከክልሉ መሬት አስተዳደር ቢሮ ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ስልጠና፣ ዳንግላ፣ ታህሳስ 23-26፣ 2006 ዓ.ም ነው።

[168] *ጥላሁን ጎበዜ እና እነ መክተ ኃይሉ (2 ሰዎች)፣* የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ ቅጽ 13፣ መ/ቁ 69821፣ ታህሳስ 17/2004 ዓ/ም

ላይ አላግባብ ተፅዕኖ የሚደርስባቸው መሆኑን መረዳት አያዳግትም። የመሬት ክርክር ህዝባዊ ውሳኔ (community justice) መወሰን በቀደመው ጊዜ አውጫጪኝ የሚባለው የፍርድ ሂደት የሚመስል ሲሆን ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ስለሚያመዝን በመሬት ክርክር ውሳኔ አሰጣጥ ላይ አለመጠቀሙ ይመረጣል።[169]

በመሆኑም የመሬት ይዞታ ክርክር ሲመራ የማስረጃ ጉዳይን አስመልክቶ በሀገራችን ራሱን ችሎ የማስረጃ ሕግ ባለመኖሩ ምክንያት የመሬት ሕጉን ድንጋጌዎች ከሌሎች ማስረጃን የሚመለከቱ ሕግጋትና አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ጋር እንደአግባብነቱ በማጣመር ውሳኔ መስጠት ተገቢ ይሆናል።[170] የመሬት ሕግን ብቻውን በመጠቀም በመሬት አስተዳደር ፍትህ ማስፈን ይቻላል ማለት ከሕገ-ሃይንሱ ጋር አለመጣጣም ነው።

4. ማጠቃለያ

የመሬት መብት በኢትዮጵያ በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 40 መሰረት በፖሊሲ ደረጃ እውቅና የተሰጠው ነው። የመብቱ ቋት ሰፋ ባለ መልኩ የመረጋገጡን ያክል የሙግት አፈታቱ አነዳደፍ ሁኔታ የመብቱን አጠባበቅ ውጤታማነትን ያመለክታል። የመሬት ክርክር አፈታትን በተመለከተ በልዩ ሁኔታ በፖሊሲ ደረጃ የህግ ማዕቀፍ የለም። ሆኖም በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 37 መሰረት ሌሎች ጉዳዮች በሚስተናገዱበት አግባብ የመሬት ክርክር በፍርድ ሊያልቅ የሚችል ጉዳይ ተብሎ ሊወሰድ የሚችል ነው። የመሬት አለመግባባት መፍቻ ተቋማቱም በሕግ አውጪው ተለይተው ሲቋቋሙ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 37 እና 79 ጣምራ ንባብ ሕገ መንግስታዊ የህጋዊነት መሰረት የሚኖራቸው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

በመሬት ጉዳይ ላይ ሕግን የማውጣት በቀዳሚነትና በበላይነት ስልጣን የፌደራል መንግሥቱ ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 456/1997 አስገዳጅና ፈቃጅ ድንጋጌዎችን ማዕከል በማድረግ በውክልና ክልሎችም በገጠር መሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር ተሳትፎ እንዲኖራቸው ተደርጓል። በአዋጁ አንቀፅ 12 መሰረትም ለክልሎች ሲወክል ከስምምነት ውጪ ያለው የግጭት መፍቻ መንገዶችን መወሰን የክልሎች ሥልጣን መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ክልሎችም እንደራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ የመሬት ግጭት መፍቻን የመምረጥ እድል የሚሰጥ መሆኑ ሕጉ ተራማጅ እሳቤ ያለው

[169] ደሴ ስዩም፣ የገጠር መሬት ህግጋትና እያጋጠሙ ያሉ ችግሮች፣ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች የተዘጋጀ የስልጠና ጽሑፍ፣ ባህር ዳር ዩንቨርሲቲ መሬት አስተዳደር ኢንስቲቱት፣ (መስከረም 2006 ዓ/ም)፣ ገፅ 44-53 ያቀረበውን ምሳሌ መመለከት ይቻላል።

[170] የፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2000 ጀምሮ ያሉትን ይመልከቱ።

መሆኑን ያሳያል። ነገር ግን ክልሎች ይህ ሰፊ ስልጣን ሲሰጣቸው የመሬት ይዞታና አጠቃቀም ላይ ለሚነሱ አለመግባባቶች ውሳኔ ሰጪ አካላት ሲያቋቁሙ የዳኝነት ባህሪ ያላቸው እንዲሆኑ ማስቻል ይኖርባቸዋል። ቢያንስ የሚሰጠው ውሳኔ በፍርድ ቤት በይግባኝም ቢሆን የሚከለስበትን ዕድል ማለፍ አይገባም።

በአማራ ክልል አሁን ተፈፃሚነት ባለቸው አዋጅ ቁጥር 252/2009፣ ደንብ ቁጥር 159/2010 እና መመሪያዎች መሰረት አማራጭ የግጭት መፍቻ መንገድ፣ የአስተዳደር አካል እና ፍርድ ቤት በመሬት ክርክር ላይ የውሳኔ ሰጭነት ሚና ተሰጥቷቸዋል። ከሙግት መፍቻ መንገዶች ውስጥ በስምምነትና በሽምግልና የመሬት ክርክርን መፍታት በፌደራል አዋጅ ቁጥር 456/1997 አንቀፅ 12 ላይ ቅድሚያ የተሰጠውና በአማራ ክልልም እውቅና የተሰጠው ነው። የመሬት ክርክር ወደ ፍርድ ቤት ሲቀርብ የወረዳ ፍርድ ቤት ብቸኛና በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን የተሰጠው ሲሆን ከመሬት አስተዳደር የሚሰጥ አስተዳደራዊ ውሳኔንም የማረም ሥልጣን ተሰጥቷል። ይህም የመሬት ሙግት መፍቻ መንገዶች ባለሶስት ገጽታ (three-dimentional) እና ሁሉን አቀፍ (comprehensive) እንዲሆን መደረጉን መረዳት ይቻላል።

በመሆኑም ባለጉዳዮች ራሳቸው ሲስማሙ፣ የመሬት አስተዳደር ባለሙያዎች ሕግን ሲያስፈጽሙና ዳኞች ሕግን ሲተረጉሙ በመሬት አስተዳደር ሥርዓቱ ላይ የየራሳቸው ሚና ይኖራቸዋል። የመሬት ክርክር አፈታቱ ሊሳለጥ የሚችለውም ሕጉ በአግባቡ ሲተረጎም፣ አስቀድሞ በሚታወቅ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ የጉዳይ አቀራረብና አፈታት እንዲሁም በእነዚህ ሶስት አካላት መካከል በህግ አግባብ ጤናማ ተግባቦት ሲኖር መሆኑ ግልፅ ነው። እነዚህ አካላትም የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በጥናት እየመለሱ የመሬት መብት ልውውጥን እንዲፋጠን ማድረግ አሁን ሀገሪቱ የግል ሀብት እንዲለማ በምትከተለው ካፒታሊዝም ዘመንም ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ሚና ይኖረዋል። የመሬት ይዞታ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሚዛኑን ጠብቀው ማህበረሰባዊ ግንኙነትና የመሬት መብት ጥበቃን በማጣጣም እስከተከናወነ ድረስ የመሬት ሕግ ፍልስፍናና ተግባራዊ ቁርኝቱ በክልላችን ብሎም በሀገራችን እያደገ መሄዱ የማይቀር ነው።

የሕግ አስከባሪ አካላት ኃይል አጠቃቀም ስልጣን እና የተጠያቂነት ስርዓት፡- ሕጉና አተገባበሩ በአማራ ክልል

ታፈሰች ወልዴ*

አጽርዖተ-ይዘት

የህግ አስከባሪ አካላት ስራቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ካላቸው ሃይል የመጠቀም ሰፊ ስልጣን አንጻር ዜጎችን የማስቆም፣ የማሰር፣ የመጠየቅ ከዚህም ባለፈ ገዳይ የሆነ የጦር መሳሪያ በመጠቀም በህይወት እና በአካል ላይ ጉዳት ለማድረስ ይችላሉ። ይህም የሃይል አጠቃቀም ስልጣን በህግ ሊገደብ እና ሊለካ በሚችል ስርዓት ሊታገዝ ይገባል። በአገራችን ያለው የሃይል አጠቃቀም የህግ ማዕቀፍ በዜጎች ላይ ኢፍትሃዊ እና ምክንያታዊነት የሌለው የሃይል አጠቃቀም ስርዓት እንዲይዳብር ለማድረግ በቂ አይደለም። በመሆኑም አሁን ያለው የተጠያቂነት ስርዓት አጥጋቢ እንዳይሆን አድርጎታል።

የዚህ ጥናት አላማም የሃይል አጠቃቀም ፅንሰ ሃሳብን መሰረት በማድረግ አሁን በተግባር ያሉ የህግ እና የአሰራር ስርዓቶችን በመፈተሽ ችግሮቹን ነቅሶ በማውጣት ማሳየት ነው። የጥናቱም ዘዴ አይነታዊ ሲሆን በጥናቱ ሆን ተብለው በተመረጡ የፍርድ ቤት መዝገቦች፣ ከወረዳ እስከ ክልል የሚገኙ የክልሉ ፖሊስ ተቋማት የዲሲፕሊን ጉዳዮችን በመመልከት፣ ከባለሙያዎች ጋር ቃለ-መጠይቅ በማድረግ እንዲሁም ህጎችን በመዳሰስ በመረጃ መሰብሰቢያ ስልትነት ተጠቅሟል። ጥናቱም በሃይልና በመሳሪያ አጠቃቀም ዙሪያ ያሉ ሰፊ የህግ ክፍተቶችን ከማሳየቱም ባሻገር የሃይል አጠቃቀም ስርዓትን እና የተሻለ የተጠያቂነት ስርዓት ነጻና ገለልተኛ በሆነ አካል የሚፈተሽ ያለመሆኑን ያሳያል። በተጨማሪም የህግ ክፍተቶችን የሚሞሉ መመሪያዎችን ከማመላከት ባለፈ የተሻለ የተጠያቂነት ስርዓት እንዲዳብር የሚያስችል የሃይል አጠቃቀም ስርዓት ሊያግዙ የሚያስችሉ ስልቶችን ያመላክታል።

ቁልፍ ቃላት፡- የህግ አስከባሪ አካላት፣ የሃይል አጠቃቀም፣ ተመጣጣኝ ሃይል፣ ከልክ ያለፈ ሃይል፣ ተጠያቂነት።

---

* LLM,LLB, በአብክመ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የህግ ምርምር ኢንስቲትዩት አሰልጣኝና ተመራማሪ። ለጥናቱ ግብዐት በመስጠት ለተባበራችሁኝ ሰዎች በሙሉ ከልብ አመሰግናለሁ።

1. መግቢያ

ለአንድ አገር ሰላምና ደህንነት መረጋጥ ከፍተኛ አስተዎፅዖ ከሚያበረክቱት የመንግስት አደረጃጀቶች ውስጥ ዋነኞቹ የህግ አስከባሪ አካላት ናቸው። የህግ አስከባሪ አባላት ስራቸውን ሲተገብሩ የሚጠቀሙት ሃይል ህጋዊና ተመጣጣኝ ሊሆን ይግባል። ይህ ካልሆነ ግን በሰዎች ሰብአዊ መብቶች ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ ነው። ሆኖም በአገራችን የሃይል አጠቃቀምን በተመለከተ በቂና የዳበረ ህግ ካለመኖሩ ባሻገር የሃይል አጠቃቀም ተመጣጣኝነትን ለመመዘን የሚያስችል የህግ ስርዓት አልተዘረጋም። ይህ በመሆኑ ምክንያት የህግ አስከባሪ አባላት የሃይል አጠቃቀም ላይ ያላቸው ተግባራዊ አፈጻጸም አጥጋቢ የሚባል አይደለም።[1] የተባበሩት መንግስታት የሰዎች ሰብአዊ መብቶችን ለማስጠበቅ በየግዜው የተለያዩ መመሪያዎችን ይደነግጋል። ከእነዚህ ውስጥም አንዱ መንግስታት የህግ አስከባሪ አካላቶቻቸው ሰብአዊ መብትን ያማከለ የሀይል እና የመሳሪያ አጠቃቀም እንዲከተሉ ግዴታ የሚጥል መመሪያ ነው። በአገራችን ይህን መመሪያ መሰረት ያደረገ ህግ በበቂ ሁኔታ አልተደነገገም። በመሆኑም በተግባር የህግ አስከባሪዎችን የሃይል አጠቃቀምን ሊወስን የሚችል ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል በቂ ህግ አልዳበረም።[2] ከዚሁ ጋር ተያይዞ ጥቅም ላይ የዋለን የሃይል አጠቃቀም ለመመዘን የሚያስችል ስልት ባለመዘርጋቱ ርትዕ ላይ መሰረት ያደረገ ሲሆን ይህም ወጥ የሆነ ስርዓት ለመዘርጋት አመቺ ሁኔታን አልፈጠረም። የህግ አስከባሪ አካላትም ተጠያቂ የሚሆኑበት ስርዓት ነጻና ገለልተኛ በሆነ አካል ያልተዋቀረ በመሆኑ በተጠያቂነት ዙሪያ የሚታይ ክፍተት ነው።

---

[1] Human right watch, Ethiopia - World Report 2018: https://www.hrw.org/world-report/2018/country-chapters/ethiopia እንዲሁም
Amenesty international https://www.amnesty.org/en/countries/africa/ethiopia/report-ethiopia and also Release of the 2017 Human Rights Report for Ethiopia, https://et.usembassy.gov/release-of-the-2017-human-rights-report-for-ethiopia/ የህግ አስከባሪ አካላትም በዜጎች ላይ የሚያደርሱትን የሰብአዊ መብት ጥሰት በተመለከተ የአሜሪካ መንግስት እ.አ.አ. በ2016 ኢትዮጵያን አስመልክቶ ባወጣው ሪፖርት የህግ አስከባሪ አካላት ከልክ ያለፈ ሃይልን በመጠቀም በግለሰቦች ላይ ጉዳት ያደረሱ መሆኑን በመጥቀስ በተለይም የህግ አስከባሪ አካላት ከሚያደርሱት የመብት ጥሰቶች ውስጥ ዜጎችን ያለ መያዣ መያዝ፣ ኢሰብአዊ ለሆነ አያያዝ መዳረግ እንዲሁም ህጋዊ ያልሆነ ብርበራ ማድረግ መሆኑን በሪፖርቱ አስታውቋል:: በተመሳሳይም የሰብአዊ መብት ታዛቢ (ሂውማን ራይትዎች) 2016 ባወጣው ሪፖርት መሰረት ከልክ ያለፈ ሃይል መጠቀም፣ በዜጎች ላይ ገዳይ የሆነ መሳሪያ መጠቀም፣ በዘፈቀደ መያዝ በሪፖርቱ ከተካተቱት የመብት ጥሰቶች ጥቂቶቹ ናቸው።

[2] የኢፌዲሪ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ... በፖሊስና ማረሚያ ቤት አባላት የሀይል አጠቃቀም እና የተጠያቂነት ስርዓት የህግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ መሆኑን ባሳወቀበት ወቅት ገደብ አልባ የሆነውን የሃይል አጠቃቀም ስርአት ማሻሻል እንደሚገባ ጠቅሷል። https://hi-in.facebook.com/.../posts/...-/1318423651585049/
accssesed at: 8/9/2019 9:40

2. **የህግ አስከባሪ አካላት**

የህግ አስከባሪ አካላት ተጠርጣሪን ይዞ የማሰር፣ የመፈተሽ፣ እንዲሁም በሚታሰሩበት ግዜ ጥበቃ ማድረግ እና በስራቸው ወቅትም የሚገጥሟቸውን ተቃውሞ ለመመለስ ሀይል እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው አካላት ናቸው፡፡ በአገራችን የህግ አስከባሪ አካላት እነማን ናቸው የሚለውን በግልጽ የሚያስቀምጥልን ህግ የለም፡፡ ሆኖም በ2009 ዓ.ም የወጣው የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ "የሕግ አስከባሪ አካል" ማለት የአገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የክልል ፖሊስ እና ሌሎች የፀጥታ አካላት ናቸው በማለት ለዚህ አዋጅ አላማ ሲል ትርጉም ይሰጣል፡፡[3] በተመሳሳይም የሃይል አጠቃቀም ስርዓትን በተመለከተ የፌደራል ዐቃቤ ህግ ባዘጋጀው ረቂቅ ህግ ላይ ፖሊስ፣ የማረሚያ ቤት ፖሊስ አባላት፣ በፖሊሳዊ ስራ ላይ የተሰማራ የአገር መከላከያ ሰራዊት የሚያካትት ይዘት አለው፡፡[4] ከዚህ በተጨማሪም በተባበሩት መንግስታት የሃይል አጠቃቀም መመሪያ መሰረት

The term "law enforcement officials", includes all officers of the law, whether appointed or elected, who exercise police powers, especially the powers of arrest or detention.[5] **ይህም በግርድፉ ወደ አማረኛ ሲመለስ ‹‹ማንኛውም የተሾመም ይሁኑ የተመረጡ የህግ አካላት በተለይም የማሰር እና የማቆየት ስልጣን ያላቸው አካላትን ይጨምራል›› በሚል ያስቀምጠዋል፡፡**

ከላይ ካየናቸው ጠቅላላ ትርጉሞች በመነሳት በተለይም ፖሊስ የማሰር ብሎም በጣቢያ የማቆየት ስልጣን ያለው በመሆኑ እንዲሁም የማረሚያ ቤት ፖሊስ አባላት በእስር ላይ ያሉ ታራሚዎችን የመጠበቅ ሃላፊነት ያላቸው መሆኑን መነሻ በማድረግ የህግ አስከባሪ አካላት ናቸው በማለት ልንወስዳቸው እንችላለን፡፡

---

[3] የሕዝብን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ የወጣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣ 2009 ዓ.ም፣ ቁጥር 1/2009፣ አንቀጽ 2(3) ትርጉም ክፍል ላይ እንደተመለከተው፡፡ acessed at፡ https://www.abyssinialaw.com/quick-links/item/1794-1-2009 8/15/2019 at፡ 9፡13

[4] የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ የሰብአዊ መብት ድርጊት መርሃ-ግብር ጽህፈት ቤት አስተባባሪነት የህግ አስከባሪ አካላት የሃይል አጠቃቀም ረቂቅ ሰነድ አስመልክቶ ያወጣው መግለጫ accessed at:- 8/11/2019, 11፡54 https://news.et/2019/02/12/%E1%8B%A8%E1%88%95%E1%8C%8D%E1%8A%A0%E1%88%B5%E1%8A%A8%E1%89%A3%E1%88%AA%E1%8A%A0%E1%89%A3%E1%88%8B%E1%89%B5%E1%8B%A8%E1%8A%83%E1%8B%AD%E1%88%8D%E1%8A%A0%E1%8C%A0%E1%89%83%E1%89%80%E1%88%9D/

[5] Basic principle on the use of force and firiarems by law enforcement officials adopted by the eight eight united nation congeress on the prevention of crime and treatement of ofeenders Havana, Cuba, 1990.https://www.ohchr.org/en/professionalinterest/pages/useofforceandfirearms.aspx accessed at 6/6/2019. 3፡38

3. የኃይል አጠቃቀም ምንነት

የህግ አስከባሪ አካላት የእለት ተእለት ስራቸውን ሲተገብሩ የሚያጋጥሟቸው የተለያዩ የሃይል ተቃውሞዎች አሉ፡፡ እነዚህን ተቃውሞዎች እያንዳንዳቸው የተለያዩ ከመሆናቸው አንጻር ሁሉንም የሚወክል ወጥ እና ገዢ የሆነ የሃይል ትርጉም ማስቀመጥ አይቻልም፡፡ ሆኖም ሃይል ምንድን ነው የሚለውን በተለያዩ አካላት ትርጉም ለመስጠት የተሞከረ ሲሆን ከእነዚህ መካከል በምሳሌነት የሚከተለውን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የስኮትላንድ ፖሊስ መመሪያ ሃይልን በሚከተለው መንገድ ትርጓሜ ሰጥቶታል፡፡

“Use of force is strength, power, energy, and includes influence and anything that tends to produce an effect on the mind or will.”[6] ይህም በግርድፉ ሲተረጎም “ሃይል ስንል ህግን ለማስከበር ሲባል ግለሰብን አካላዊ በሆነ መንገድ ትዕዛዝን እንዲፈጽም ማድረግ ሲሆን ይህም በሰፊው ሲቀመጥ አንድን ግለሰብ በመንካት፣ ግለሰቡ እንዳይንቀሳቀስ በማድረግ፣ አንዳንዴም እስከ ገዳይ የሆነ መሳሪያ መጠቀምን ይጨምራል”፡፡

የሃይል ትርጉምን ካስቀመጥን በኋላ አብሮ የሚነሳው ሌላው ጽንሰ ሃሳብ ተመጣጣኝ ሃይል ምንድን ነው የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ተመጣጣኝ ሃይልን ለመተርጎም የሚያስችለን ወጥ የሆነ ትርጉም ባይኖርም አንድን የሃይል ጥቃት ለመመለስ የተወሰደ የሃይል እርምጃ ከስራው ሁኔታ፣ በኑሮ ልማድ እንዲሁም ከሁኔታው በመነሳት ተመጣጣኝ መሆን አለበት የሚል መርህ ነው፡፡ የተባበሩት መንግስታት ሃይልን በተመለከተ በመመሪያው ላይ ሲያስቀምጥ፡-

Action taken must be proportionate to the threat in all circumstances.[7] ይህም ወደ አማረኛ ሲመለስ ‹‹የተወሰደ የሃይል እርምጃ ከተቃጣው የሃይል እርምጃ ጋር በማንኛውም ሁኔታ ተመጣጣኝ መሆን አለበት›› የሚል መርህ ነው፡፡ የተመጣጣኝነትን ትርጉም አለምአቀፍ የፖሊስ አዛዦች ትርጓሜውን ሲያስቀምጡ “amount of effort required by police to compel compliance from an unwilling subject.”[8] ይህም በግርድፉ ሲተረጎም ‹‹ፖሊስ ተባባሪ አልሆንም ያለን ተጠርጣሪን ተባባሪ ለማድረግ የሚያወጣው ጥረት መጠን ነው›› በማለት ተርጉመውታል፡፡ ይህንም ትርጉም ተከትሎ የሚመጣው ሌላው የሃይል ዕንሰ ሃሳብ ገጽታ ከልክ በላይ ሃይል መጠቀም የሚለው ነው፡፡ አንድ የህግ አስከባሪ ስራውን ለማከናወን

---

[6] Scotland police use of force manual https://www.amnesty.org.uk/files/201704/Module%201%20Use%20of%20Force.pdf?NKD_BwolbDBK5PcXl1SIG_YIQk7_UPI1= accesed at: 19/5/2019, 11፡42

[7] የግርጌ ማስታወሻ 5፣ ገጽ 1

[8] Police use of force in America, The International Association of Chiefs of Police, 2011 https://www.theiacp.org/sites/default/files/2018-08/2001useofforce acceseed at:- 6/5/2019, 4:20

የሚያስፈልገው በቂ ሃይል ይህ ነው ብሎ ከወዲሁ ለመወሰን አይቻልም፡፡ ሆኖም ከልክ በላይ ሃይል ተጠቅሟል ለማለት አስፈላጊ ወይም ምክንያታዊ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው የሚሉትን በመለየት የሃይሉን አጠቃቀም በመመዘን ከልክ በላይ መሆኑን ማሳየት ይቻላል፡፡ ይህም ሆኖ ሁሉን የሚያስማማ አንድ ወጥ ትርጉም ማስቀመጥ ባይቻልም ለአብይነት የሚከተለውን ትርጓሜ መጥቀስ ይቻላል፡፡ እንደ አለም አቀፍ የፖሊስ አዛገቦች ማህበር ትርጓሜም፡-

"The application of an amount and/or frequency of force greater than that required to compel compliance from a willing or unwilling subject."[9] ይህም በግርድፉ ሲተረጎም ‹‹ከልክ በላይ ሃይል ማለት የሃይል መጠን አጠቃቀሙ ብዛት እና/ወይም ተደጋጋሚነት ተባባሪ የሆነ ተጠርጣሪን ወይም ተባባሪ ያልሆነን ተጠርጣሪ ለማስገደድ ልንጠቀምበት ከሚገባ የሃይል መጠን ልክ በልጦ ሲገኝ ነው›› በማለት ተርጉመውታል፡፡

ይህም አንድ ሃይል ተመጣጣኝ ነው ወይም ከልክ በላይ ነው ለማለት የሚያስችለን መመዘኛ ምንድን ነው ወደሚለው ጥያቄ ያሸጋግረናል፡፡

3.1. የኃይል አጠቃቀም እንዴት ይለካል

የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ ድንጋጌዎች ስር ፖሊሰ ከተጠርጣሪው የሚገጥመውን ሃይል ለመመለስ ተመጣጣኝ የሆነ ሃይል እንዲጠቀም ድንጋጌው ያስቀምጣል፡፡[10] ሆኖም ይህ ሃይል ተመጣጣኝ ወይም ከልክ ያለፈ የሃይል አጠቃቀም ነው ለማለት የሚያስችለን መለኪያ ስልት የስነ-ስርዓት ህጋችን አካቶ አልያዘም፡፡ በሌሎች አገራት የሃይል አጠቃቀም ሊመዘንበት የሚችልበት የህግ ስርዓት በፍርድ ቤት ውሳኔዎች (ፕሪስደንስ)፣ በህጎች፣ በፖሊሲዎች በማካተት ሃይል ሊለካ የሚችልበትን መንገዶች በየግዜው እያዳበሩ መጥተዋል፡፡ ለአብነት፡-

---

[9] ዝኒ ከማሁ ገጽ 14 እንዲሁም Albert J. Reiss፣ The Police and the Public, 1971, Case Western Reserve Law Review, Volume 24 I Issue, እ.አ.አ.1968 አልበረት ሪስ የተባለ የታወቀ ክሪሚኖሎጂስት ስለ ከመጠን ያለፈ ሃይል ትርጉም ሲያስቀምጥ ከልክ በላይ የሆነ ሃይልን ለመረዳት ከምንጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ ሁኔታዎችን በመለካት ሀይል መጠቀም አላስፈላጊ የሚሆንበትን ሁኔታዎች በመለየት ነው በማለት ያስቀምጣል፡፡ ለምሳሌ አንድ የህግ አስከባሪ ተጠርጣሪው ላይ ሃይል ተጠቅሞ በቁጥጥር ስር ያላዋለው ከሆነ (ሃይል መጠቀሙ ፋይዳው ምንድን ነው)፣ ተጠርጣሪው በቃላትም ይሁን በጉልበት ምንም አይነት ተቃውሞ ሳያደርግ ሃይል የተጠቀምን እንደሆነ እንዲሁም የህግ አስከባሪው ግለሰቡን በቁጥጥር ስር ካዋለም በኋላ ሃይል መጠቀም የቀጠለ እንደሆነ ከልክ ያለፈ ሃይል መጠቀሙን ማቋቋም ይቻላል በማለት ያስቀምጣል፡፡

[10] የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 1/1954 ዓ.ም፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዲስ አበባ፣ 1954 ዓ.ም አንቀፅ 56(4) (ከዚህ በኋላ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ወይም የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

እ.አ.አ. 1989 የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት[11] በቀረበለት ክርክር ላይ የተሰጠው የሃይል መጠን መለኪያ ለሌሎች ፍርድ ቤቶች ፕሪስደንስ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል። በዚህ ውሳኔ ላይ የፖሊስ የሃይል አጠቃቀም መለካት ያለበት ምክንያታዊ ከሆነ ዓላማ "objective reasonableness" በመነሳት ነው በሚል ፍርድ ቤቱ ሃይል የሚለከባትን ሁኔታ አስቀምጧል። ፍርድ ቤቱ በሃተታው ላይ ምክንያታዊ ዓላማ "objective reasonableness" መታየት ያለበት አንድ ምክንያታዊ ከሆነ እና በቦታው ከነበረ የፖሊስ አባል አንጻር እና ፖሊሶች በስራ ላይ በሚሆኑበት ግዜ በሰከንዶች ሽርፍራፊ ውሳኔ እንዲወስኑ የሚገደዱበትን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ መሆን አለበት ከሚል መነሻ ነው። በመሆኑም በዚህ ውሳኔ መሰረት የሃይል አጠቃቀም ሊለካ የሚገባው በወቅቱ በጉዳዩ ተሳታፊ ከሆነ አባል እና ወዲያውኑ ውሳኔ እዛው ላይ ሊሰጥበት ያስገደደውን ሁኔታን ከመመዘን አንጻር ነው።

ሌላው የሃይል አጠቃቀምን ለመለካት እንደመነሻ አድርገን የምንመለከተው የስኮትላንድ ፖሊስ ሃይል አጠቃቀምን ለመለካት የሚጠቀምባቸውን መለኪያዎች ነው።[12] ይህ የሃይል አጠቃቀም የመለኪያ መንገድ ዝርዝር የሆነ እና ከሃይል ይልቅ ሌሎች መንገዶችን እንድንጠቀም የሚያበረታታ በመሆኑ በዚህ ጥናት ላይ እንደ ጥሩ ተሞክሮ ተወስዷል።

የስኮትላንድ ፖሊስ የሃይል አጠቃቀምን ለመለካት 7 የሚሆኑ መለኪያዎች አሉት። እነዚህም፡-

1. **ተመጣጣኝነት** /Proportionality/

የተወሰደው እርምጃ ሊደርስ ከነበረው ስጋት ጋር በሁሉም ሁኔታዎች ተመጣጣኝ መሆን አለበት የሚል መርህ ነው። ከተወሰደው እርምጃም ይልቅ ሌላ ያነሰ አማራጭ ሃይል በመጠቀም ተመሳሳይ ውጤት ማስገኘት ይቻል ከነበረ የተወሰደው እርምጃ ተመጣጣኝ አልነበረም ማለት ነው። በመሆኑም ተመጣጣኝ ነው ለማለት የተወሰደው እርምጃ ሊደርስ ከነበረው ስጋት ጋር ተመጣጣኝ መሆን ይኖርበታል የሚል መርህ ነው።

2. **ህጋዊነት** /Legality/

ሃይልን ለመጠቀም ሁልግዜም ህጋዊ መሰረት መኖር አለበት የሚል መርህ ነው። ይህም ሃይልን ለመጠቀም የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት ያስፈልገዋል ማለት ነው።

---

[11] Graham v. Connor, Supereme court of united state, 490 U.S. 386, 396-97 (1989)

[12] Scotland police, Standard Use of Force Operating Procedure, accesed at: 6/5/2019, 4:20 https://www.google.com/search?safe=strict&client=firefox-b&biw=800&bih=486&ei=KprjXLGXLY_SkwWdjpXwAg&q=scotland+police++use+of+force+manual++pdf&oq=scotland+police++use+of+force+manual++pdf&gs_l=psy-ab.3...1969.22491..25163...0.0..1.769.9490.0j35j7j5-1j2.....0....1..gws-wiz.....0i71j35i304i39j0i67j0i7i30j0i8i7i30j33i10.q94i2NFPqfI

3. **ምክንያታዊነት** /Justification

የህግ አስከባሪው አካል በግለሰቡ ላይ የተጠቀመው ሃይል ግለሰቡ ህግ አስከባሪው እንዳይዘው በተከላከለበት መንግድ ልክ ሊሆን ይገባል። ይህም በምሳሌ ስናስደግፈው የህግ አስከባሪው ተጠርጣሪውን ሊይዘው ሲል የተኮሰ እንደሆን መልሶ መተኮስ መቻል ነው። አንድ የህግ አስከባሪ ለወሰደው እርምጃ ምክንያታዊ የሆነ መነሻ ሊኖረው ይገባል።

4. **አስወጋጅ** /Preclusion/

የህግ አስከባሪ አካላት ሃይልን ከመጠቀማቸው በፊት ሌሎች መንገዶችን ለመጠቀም መሞከር ወይም ሞክረው መክሸፍ ወይም ለመጠቀም ቢታሰቡ እንኳን ከተፈጠረው ሁኔታ አንጻር ተገቢነት ያልነበራቸው መሆኑን ማሳየት አለባቸው።

5. **አስፈላጊነት** /Necessity/

በህግ አስከባሪው የተወሰደው እርምጃ ህጋዊ የሆነ ስራቸውን ለማከናወን አስፈላጊ የሆነ ሃይል መሆን አለበት።

6. **ስነ-ምግባር** /Ethical/

የህግ አስከባሪ አባል ስራውን በሚያከናውንበት ግዜ አንድ ህግ አስከባሪ ሊከተላቸው የሚገቡ ስነ-ምግባራዊ መርሆችን ተከትሎ ስራውን ማከናወን አለበት። ይህም ሃይልን አላግባብ እንዳይጠቀም የሚረዳ ነው።

7. **ተጠያቂነት** /Accountablity/

የህግ አስከባሪ አካላት የወሰዱትን እርምጃ ለምን እንደወሰዱ፣ እርምጃውን ለመውሰድ የተገደዱበትን ሁኔታ ሊያስረዱ ይገባል። ይህም በሚወስዱት እርምጃ ልክ ተጠያቂ እንዲሆኑ ያስችላል።

3.2 አለም አቀፍ መሠረታዊ የኃይል እና የጦር መሳሪያ አጠቃቀም መርሆዎች

የተባበሩት መንግስታት ሰብአዊ መብቶችን ለማስጠበቅ በየግዜው ውሳኔዎችን ያሳልፋል። በመሆኑም የአገራት ህግ አስከባሪ አካላት በሰዎች ሰብአዊ መብት ላይ ሊያደርሱ የሚችሉትን ሰብአዊ መብት ጥሰት ለመወሰን ብሎም ለማስቀረት እንዲያስችል የህግ አስከባሪ አካላት ስራቸውን ሲተገብሩ ሊከተሉ የሚገባቸውን የሃይል እና የመሳሪያ አጠቃቀም መመሪያ አዘጋጅቷል።[13] በዚህ መመሪያ ላይ በዋነኝነት የሰፈሩ አጠቃላይ መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው።

[13] የግርጌ ማስታወሻ 5፣

3.2.1 የህጋዊነት መርህ

አገራት የህግ አስከባሪ አካላት በሰዎች ላይ የሚኖራቸውን የሃይል እና የመሳሪያ አጠቃቀም በተመለከተ የሚገዛ ህግና ደንብ አውጥተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል። ይህም የህግ አስከባሪ አካላት ሃይል የተጠቀሙበትን ምክንያት እና ዓላማ የሕግ መሰረት እንዲኖረው ያደርጋል። በመሆኑም ማንኛውም የሃይል ድርጊት ህጋዊ የሆነ መሰረት ሊኖረው ይገባል።[14]

3.2.2 የአስፈላጊነት መርህ

የአስፈላጊነት መርህ የህግ አስከባሪ አካላት ሃይል መጠቀማቸው አስፈላጊ ነው ወይ? አስፈላጊስ ከሆነ በምን ያህል መጠን መሆን አለበት? የሚለውን ለመመለስ የሚጠቅመን ነው። በዚህ መርህ ስር ሶስት አለዎት (elements) አሉ። የመጀመሪያው ሃይል ያስፈልጋል ወይ? ወይም ሃይል መጠቀም ሳያስፈልግ የታለመውን ዓላማ ማሳካት ይቻላል ወይ? በሁለተኝነት ደግሞ ምን ያህል ሃይል መጠቀም አላማውን ስኬታማ ሊያደርገው ይችላል? ሶስተኛው እና የመጨረሻው ዓላማው ከተሳካ በኋላ የሃይል ጥቅም ተቋርጧል ወይ? የሚሉ ናቸው። እነዚህ አለዎት የሃይል አጠቃቀሙን አስፈላጊት ለመወሰን የሚረዱን ናቸው።[15]

3.2.3 የተመጣጣኝነት መርህ

የተመጣጣኝነት መርህ ስንል የተወሰደው የሃይል እርምጃ ከተከሰተው ወይም ሊከሰት ከነበረው ጉዳት ጋር ሲመዘን በልጦ መገኘት የለበትም የሚል መርህ ነው። ይህም ሲባል ሃይል በመጠቀም የተገኘው ጥቅም ከደረሰው ጉዳት መብለጥ አለበት። ይህ ካልሆነ የተመጣጣኝነትን መርህ ተላሯል የሚል ነው። በተመጣጣኝነት መርህ ስር ሁል ግዜ ከተጠቀምነው ሃይል ውጭ ሌላ ያነሰ የሃይል አማራጭ በመጠቀም የታሰበውን አላማ ማሳካት የሚያስችል አማራጭ ካለ ድርጊታችን የተመጣጣኝነትን መርህ ተጻሯል። ምክንያቱም የተወሰደው እርምጃ ሊደርስ ከነበረው ስጋት ጋር በሁሉም ሁኔታዎች ተመጣጣኝ ነው ሊባል የሚችል መሆን አለበት።[16]

4. የሰብአዊ መብቶች እና የሃይል አጠቃቀም

ሰብአዊ መብቶች ማንኛውም ሰው በሰውነቱ ያለምንም መድልኦ የተጎናፀፋቸው መብቶች ናቸው። የህግ አስከባሪ አካላት የሰዎችን ሰብአዊ መብት ሊያከብሩ እንዲሁም ሊጠብቁ

---

[14] ዝኒ ከማሁ ገፅ 1፣ መርህ አንድ ላይ ‹‹አገራት እና የህግ አስከባሪ አካላት የሃይል አጠቃቀምን በተመለከተ ህግ ማውጣትን መተግበር አለባቸው የሚለውን መርህ ያስቀምጣል››።

[15] ዝኒ ከማሁ ገጽ 2፣ የህግ አስከባሪ አካላት ሃይል ሲጠቀሙ ሃይል የተጠቀሙበት ሃይል ከመጠቀም ውጭ ሌላ አማራጭ የሌለ ሲሆን ነው በሚል በመርህ አራት ላይ አስቀምቶታል።

[16] ዝኒ ከማሁ ገጽ 2፣ መርህ አምስት ላይ በህግ አስከባሪ አካላት የሚወሰዱ እርምጃዎች ተመጣጣኝ ሊሆኑ እንደሚገባ በመርሁ ላይ አስቀምጧል።

ይገባቸዋል።[17] በመሆኑም የህግ አስከባሪ አካላት የሰዎችን መብቶች ከመጠበቅ እና ከማክበር አንጻር ያላቸውን ግዴታ ከመብቶቹ ጋር አያይዘን እንመለከታለን።

4.1. የመጠበቅ ግዴታ

መንግስት የሰብአዊ መብቶችን የመጠበቅ እና የማክበር ሃላፊነት አለበት። ይህንንም ስንል በህግ አስከባሪ አካላትም ይሁን በሌሎች አካላት የሚደርሰውን የወንጀል ድርጊት አስቀድሞ በመከላከልም ሆነ ከደረሰም በኋላ ተጠያቂ ሊያስደርጉ የሚችሉ የተፋጠኑ የምርመራ ስልቶችን በመጠቀም ተጠያቂ የሚሆኑበትን ስርዓት ሊፈጥር ይገባል። በተለይም የህግ አስከባሪ አካላት በመሰረታዊነት የሰዎችን ሰብአዊ መብት የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው። ለምሳሌ፦

ሀ. በህይወት የመኖር መብት

የህግ አስከባሪ አካላት በዋነኝነት ሊጠብቁ ከሚገባቸው የሰዎች ሰብአዊ መብቶች ውስጥ ዋነኛው በህይወት የመኖር መብት ነው። የሰብአዊ መብቶች መግለጫ በአንቀጽ 3 ላይ አንዳስቀመጠው ማንኛውም ሰው የህይወት፣ የአካል ነጻነት እና ደህንነት መብት አለው።[18] በህይወት የመኖር መብት በህግ መጠበቅ ያለበት የሰብአዊ መብት ነው። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ስር በተመሳሳይ ማንኛውም ሰው ካለ ፍርድ ውሳኔ በቀር ህይወቱን ሊያጣ አይገባውም በሚል ተደንግጓል።[19] በመሆኑም ለዚህ የሰብአዊ መብት መጠበቅ የህግ አስከባሪ አካላት ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የሰዎችን የሰብአዊ መብቶች በማይጥስ መልኩ እንዲፈጽሙ የሚያስችል አሰራር ሊያዳብሩ ይገባል። ለዚህም የህግ አስከባሪው አካላት ከሃይል ይልቅ በሌሎች መንገዶች ግጭቶችን ለመፍታት የሚጥሩ ሊሆኑ ይገባቸዋል።[20] ይህም ሀገራት የህግ አስከባሪ አካላት የሚወስዱት እርምጃ የሚያደርሱት ጉዳቶችን ለመቀነስ ሲባል ቀድመው ሊታቀዱ እና የጥንቃቄ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል።[21] ይህ ሲሆን የሃይል እርምጃ ከመውሰድ በመቆጠብ ለህይወት ደህንነት ቅድሚያ በመስጠት ህይወት ሊያሳጡ የሚችሉ ሁኔታዎችን ውስን በማድረግ በህይወት የመኖር መብትን መጠበቅ ይችላል።

---

[17] ዝኒ ከማሁ እንዲሁም police use of force; an examination of modern police practicing, U.S. commission on civil rights, 2018 accesed at:- https://www.usccr.gov/pubs/2018/11-15-Police-Force 6/5/2019, 11፡55

[18] የተባበሩት መንግስታት አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ ሰነድ፣ አንቀጽ 3 acessed at፡- https://www.un.org/en/udhrbook/pdf/udhr_booklet_en_web 6/5/2019 11:58

[19] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 1/1987፣ አዲስ አበባ። ከዚህ በኋላ ህገ መንግስት ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል። አንቀጽ 15 ላይ እንደተመለከተው።

[20] Use of Force in Law Enforcement and the Right to Life: The Role of the Human Rights Council, Geneva Academy of International Humanitarian Law and Human Rights, brief no. 6, Geneva, November 2016. ገጽ 7

[21] ዝኒ ከማሁ

ለ. የአካል ደህንነት እና ነጻነት መብት

ሌላው የህግ አስከባሪ አካላት ሊያስከብሩት ከሚጠበቅባቸው የአካል ደህንነት ጥበቃዎች ውስጥ ገና ከጅምሩ በጥርጣሬ በሚያዙበት ወቅት በትዕግስት እና በሰከነ መንፈስ በህግ የተቀመጡትን የስነ-ስርዓት መርሆችን መሰረት በማድረግ የሰዎችን የአካል ደህንነታቸውን መጠበቅ ይገባል። ከአካል ደህንነት መብት ጋር ከሚነሱ ጉዳዮች መካከል አንዱ ተጠርጣሪዎችን መያዝ ወይም በቁጥጥር ስር ማዋልን ይመለከታል። በዚህ ግዜ የህግ አስከባሪ አካላት የተጠርጣሪዎችን የአካል ደህንነት በጠበቀ መልኩ ስራቸውን ሊያከናውኑ ይገባል። ሆኖም በአገራችን ተጠርጣሪዎች የሚያዙበት አግባብ በስነ-ስርዓቱ መሠረት በመያዣ ወይም ያለ መያዣ መሆኑን መፈተሽ የሚያስችል አሰራር የለም። በመሆኑም አንድ ህግ አስከባሪ የሰዎችን የአካል ደህንነት እና ነጻነት ለማሳጣት በመጀመሪያ ህጋዊ የሆነ ዓላማ እንዳለው የእያንዳንዱ የመያዝ አላማም በቅርብ አለቃው ምክንያታዊነቱ ሊፈተሽ የሚችልበት ስርዓትን በመዘርጋት ሰዎች በዘፈቀደ፣ ኢ-ፍትሃዊ እና ምክንያታዊነት በሌለው መነሻ ነጻነታቸውን እንዳያጡ ለመጠበቅ ያስችላል። ሌላኛው በእስር ወቅት በሚቆዩበት ግዜ ሊደረግላቸው የሚገባ ጥበቃን የሚመለከት ሲሆን በዚህ ወቅት የተጠርጣሪዎች ማንኛውም ኢሰብአዊ የሆነ አያያዝ የተከለከለ ነው።[22] ይህም በጊዜ ቀጠሮም ይሁን በፍርድ ያሉ ሰዎችን የአካል ደህንነት መብት ለመጠበቅ የሚያስችል አንዱ መንገድ ነው። በህገ መንግስቱም[23] ላይ እንደተመለከተው የተያዙ ሰዎች ሰብአዊ መብታቸውን ክብር በማይጥስ መልኩ መጠበቅ አለባቸው በሚል ያስቀምጣል። የክልሉ የማረሚያ ቤት አባላት ማቋቋሚያ ደንብም[24] ቢሆን በእጅባም ሆነ በጥበቃ ወቅት የሚጠቀመው ሃይል በህግ የተደገፈና ህጋዊ ስልጣንን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት በማለት ያስቀምጣል። በመሆኑም መንግስትም የህግ አስከባሪ አካላት ስራቸውን በሚተገብሩበት ወቅት የአካል ደህንነት እና ነጻነት ላይ ጥሰት እንዳያደርሱ የሃይል መጠን አጠቃቀማቸውን የሚቆጣጠርበትን ስልት በመዘርጋት የሰዎችን አካላዊ ደህንነት መጠበቅ ይኖርበታል።

4.2. የማክበር ግዴታ

የህግ አስከባሪ አካላት የሰዎችን መብት በማክበር ረገድ የሚያበረክቱት አስተዋጽዖ ጉልህ ነው። የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 13 ላይ እንደተደነገገው እያንዳንዱ የመንግስት አካል

---

[22] የፌደራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ፣ 1995፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ 365/95፣ 9ኛ አመት ቁጥር 90፣ አንቀጽ 22(1) እና 37።

[23] የግርጌ ማስታወሻ 19፣ አንቀፅ 21።

[24] በአማራ ክልላዊ መንግስት የማረሚያ ቤቶችን የፖሊስ አባላት ለማስተዳደር የወጣ፣ 1996፣ ዝክረ ህግ፣ ደንብ ቁጥር 22/1996፣ አንቀጽ 60(1)።

ሰብአዊ መብቶችን ማክበር እና የማስከበር ሃላፊነት እና ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል።[25] በአገራችን ያሉ የፌደራልና የክልል የህግ አስከባሪ ተቋማት ይህ ሃላፊነት ከተጣለባቸው ተቋማት ውስጥ ዋነኞቹ ናቸው። ስለዚህም ሃላፊነታቸውን በሚወጡበት ወቅት የሚጠቀሙት የሃይል ድርጊት የሰዎችን ሰብአዊ መብት ባከበረ ሁኔታ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው። ከእነዚህም የመብት ማክበር ግዴታዎች ውስጥ በጥርጣሪ ከመያዝ ጀምሮ እስከ ምርመራ ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ተጠርጣሪዎች፣ የወንጀል ሰለባዎችም ሆነ የባለጉዳዮችን መብት ማክበር ይጠበቅባቸዋል። የሃይል አጠቃቀምን አስመልክቶ የሕግ አስከባሪ አካላት የሰዎችን መብት እንዲያከብሩ ለማስቻል መንግስት እና የህግ አስከባሪ ተቋማት ለህግ አስከባሪዎች የተለያዩ ትጥቆችን ሊያሟሉ እንደሚገባ በተባበሩት መንግስታት መመሪያ ላይ ተደንግጓል። በተለይም ገዳይ ያልሆኑና የሚገጥሟቸውን የሃይል ተቃውሞ በቀላሉ ለመመከት የሚያስችል መሳሪያዎች በማሟላት የሃይል አጠቃቀምን በመወሰን የሰብአዊ መብቶችን በተሻለ ሁኔታ እንዲከበሩ ማድረግ ይቻላል። ለምሳሌ እንደ ጋሻ (shields)፣ የጭንቅላት መከላከያ ቆብ (helmets) ጥይት መላሽ መከላከያ (bullet-proof vests) እንዲሁም ጥይት መመከት የሚችሉ መኪናዎች (bullet-proof means of transportation) መኖራቸው ሃይልን ለመጠቀም የምንገደድባቸውን አማራጮች በመቀነስ በኩል አስተዋፆአቸው ከፍተኛ ነው።[26] በክልሉ በአሁኑ ሰአት ያለውን የህግ አስከባሪ አካላት ትጥቅ ሁኔታ ስራን በበቂ ሁኔታ ለማከናወን በቂ ነው ወይ በሚል ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ም/ኮማንደር አየልኝ ታክሎ ተከታዩን መልስ ሰጥተውኛል። *‹‹ፖሊስ ስራውን በሚገባ እንዲያከናውን ሙሉ ትጥቅ የለውም። ለምሳሌ ሁሉም ፖሊስ ካፊና የለውም ይህ ያለመኖሩ ብዙ ግዜ ተጠርጣሪን ወደ ጣቢያ ለማምጣት ፍቃደኛ ያልሆነን ሰው በየመንገዱ ግብ ግብ የሚያደርግ በመሆኑ ካፊና ቢኖር እጁን በማሰር ግብግቡን መቀነስ ይቻላል። በሌላ በኩል ሁሉም የፖሊስ አባል የጦር መሳሪያ የለውም። የሰውን ህይወት እና ደህንነት ለማስጠበቅ ስራ ላይ የተሰማራ ፖሊስ ራሱንም ሆነ ሌላውን ከጥቃት የሚከላከልበት የጦር መሳሪያ ለሁሉም አባላት አልተሟላም ይህም ከአቅም ማነስ የተነሳ ነው። ስለዚህ የትጥቅ ያለመሟላት እራሱ የሰላም ማስከበር ስርዓቱ ላይ የራሱ አሉታዊ ገጽታ አለው››* በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተውኛል።[27]

[25] የግርጌ ማስታወሻ 19 አንቀጽ 13።
[26] የግርጌ ማስታወሻ 5 አንቀጽ 2።
[27] ም/ኮማንደር አየልኝ ታክሎ፣ የባህር ዳር ከተማ የወንጀል ምርመራ ክፍል ሃላፊ፣ የህግ አስከባሪ አካላት ሃይል አጠቃቀምን በተመለከተ የተደረገ ቃለ-መጠይቅ፣ ግንቦት 7/2011 ዓ.ም።

አሁን አሁን እየዳበሩ ያሉም አተያዮች የሰዎችን መብት የማክበር ሃላፊነት ከህግ አስከባሪ አባላት ደህንነት አንጻር ሊመዘኑ ይገባቸዋል የሚሉ ናቸው።[28] ስለዚህ የህግ አስከባሪ አካላት የሰዎችን መብት ለማክበር እንዲያስችላቸው በመጀመሪያ ስራቸውን ሲያከናውኑ ደህንነታቸውን ሊያረጋግጡላቸው የሚገቡ ትጥቆች ሊሟሉላቸው ይገባል። የአለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች በአንቀጽ 2 ስር እንዳስቀመጠው አገራት ከግለሰብ፣ ከቡድን እንዲሁም ከተቋማት የሚደርስ የሰብአዊ መብት ጥሰት እንዳይኖር አስፈላጊውን የሆነ ዝግጅት ማድረግ አለባቸው በማለት ይደነግጋል።[29] በተለይም በህግ ማስከበር ስራ ላይ የተሰማሩ ተቋማት ወንጀልን ከመከላከል ጀምሮ የሰዎችን ደህንነት የማክበር ሃላፊነት አለባቸው።

5. ኃይል አጠቃቀምን በተመለከተ የሚታዩ ችግሮች በአማራ ክልል

5.1. የሃይል አጠቃቀምን በተመለከተ በቂ ህግ ያለመኖር

የህግ አስከባሪ አካላት አጠቃላይ አደረጃጀትን በተመለከተ በኢ.ፌ.ድ.ሪ. ህገ መንግስት ውስጥ ተመላክቶ አልፏል።[30] የእነዚህ የፀጥታ አካላትን የሃይል አጠቃቀም ስርዓትን የሚደነግጉ ድንጋጌዎች በተለያዩ ህጎች ላይ ተሰባጥረው ይገኛሉ። ለምሳሌ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 56(4) ላይ ተጠርጣሪን በቁጥጥር ስር ለማዋል ተመጣጣኝ ሃይል መጠቀም ፖሊስ እንደሚችል ይደነግጋል።[31] እንዲሁም የፌደራል ፖሊስ ደንብ በአንቀጽ 45 ስር ፖሊስ ሃላፊነቱን በሚወጣበት ግዜ ግልጽ ተቃውሞ ከገጠመውና ሌሎች አማራጮች ሲያጣ ተመጣጣኝ የሆነ ሃይል መጠቀም እንደሚችል ያስቀምጥልናል።[32] በተመሳሳይ የአማራ ክልል

---

[28] Emerging Use Of Force Issues Balancing Public And Officer Safety. Report from the International Association of Chiefs of Police, Use of Force Symposium, May 4, 2011, p. 27. acesessed at፡ 19/5/2019 at፡ 11:42 https://www.theiacp.org/sites/default/files/201808/emerginguseofforceissues041612.pdf

[29] International covenant on civil and political right, 16,12,1966, united nation, resolution 2000 A (XXI). acessed at፡- 18/8/2019 at 3:13 www.ohchr.org

[30] የግርጌ ማስታወሻ አንቀጽ 19 አንቀፅ 51(6) የፌደራል መንግስትን ስልጣንና ተግባር ሲወስን የሃገርና የሕዝብ መከላከያ፣ የደህንነትን እና የፖሊስ አደረጃጀትን የመወሰን ስልጣን እንዳለው ሲያስቀምጥ በተመሳሳይም ክልሎች በበኩላቸው በዚሁ ህገ መንግስት አንቀጽ 52(2)(ሰ) መሰረት የክልሉን የፖሊስ ሃይል ያደራጃል፤ ይመራል። የክልሉን ሰላምና ጸጥታ ያስጠብቃል በሚል የፖሊስ ተቋማት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ይደነግጋል። በእነዚህ ድንጋጌዎች የተቋቋሙት የፌደራል እና የክልል የፖሊስ ተቋማት ሃይል አጠቃቀምን የሚገዙ ድንጋጌዎች በተለያዩ ህጎች እና ደንቦች ላይ ሰፍረዋል።

[31] የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ፣ 1961፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 185/1961፣ አንቀጽ 56

[32] የፌደራል ፖሊስ አባላት መተዳደሪያ ደንብ 2005፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ ደንብ ቁጥር 268/2005፣ 19ኛ አመት፣ አንቀጽ 45(1)

የፖሊስ ደንብ[33] አንቀጽ 38 ላይ እንደሚደነግገው በፖሊስ የሚወሰድ የሃይል አጠቃቀምም ተመጣጣኝ፣ ህጋዊ ስልጣንን መሰረት ያደረገ፣ በህግ የተደገፈ መሆን አለበት በማለት ያስቀምጣል። እንዲሁም የሃይል አጠቃቀምን በተመለከተ በመከላከያነት ሊቀርቡ የሚችሉ ሁኔታዎች በተሻሻለው የወንጀል ህግ ላይ የተቀመጡ ሲሆን በአንቀፅ 78[34] ህጋዊ መከላከል በሚል እንዲሁም በአንቀጽ 69 ላይ እንደተመላከተው የሙያ ስራ ግዴታን በሚተገብሩበት ወቅት የተፈጸሙ ድርጊቶች ከሙያው ደንብና አሰራር ልማድ ውጭ ካልሆኑና ከባድ የሙያ ጥፋት ካልፈፀሙ በቀር የማያስቀጣ መሆኑን ይደነግጋሉ። ሆኖም እነዚህ ህጎች በአንድ መልኩ የተደራጁ እና ያልዳበሩ ከመሆናቸው ባሻገር የህግ አስከባሪ አካላት ሃይል አጠቃቀምን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዝርዝር ህጎች አይደሉም። በመሆኑም በአገራችን ብሎም በክልላችን ራሱን የቻለ የህግ አስከባሪ አካላትን የሚገዛ የሃይል አጠቃቀም ስርዓትን ለመዘርጋት እና ለመወሰን የሚያስችል በቂ የሆነ ህግ አስፈላጊ ነው።

ሌላው ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሰው ዋና ነጥብ ሃይል የሚለካበት ስርዓት በህጉ ውስጥ ያለመካተቱ ነው። በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 56 ስለ ተጠርጣሪ አያያዝ ሁኔታ እንደሚከተለው አስቀምጧል።

በመጀመሪያ ደረጃ የሚያዘው ሰው በቃል ወይም እጁን በመስጠት እንዲያዝ ያልተስማማ እንደሆነ ፖሊሱ ሰውየውን በመንካት ወይም በመጨበጥ ለመያዝ ይችላል።[35] ሆኖም ግን የሚያዘው ሰው አልያዝም ብሎ በሃይል የተከላከለ ወይም ለማምለጥ የሞከረ እንደሆነ ሁኔታው በሚፈቅደው ተመጣጣኝ ዘዴ ፖሊሱ ሰውየውን ለመያዝ ይችላል በማለት ያስቀምጣል። በተመሳሳይ የፌደራል ፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ ላይ የፖሊስ አባል ሃላፊነቱን በሚወጣበት ወቅት በግልጽ ተቃውሞ ካጋጠመውና ሌሎች አማራጮች ሲያጣ ተመጣጣኝ ሃይል ሊጠቀም ይችላል በሚል ይደነግጋል።[36] በተጨማሪም በአማራ ክልል ፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ ስር የሃይል አጠቃቀም ተመጣጣኝ የሆነ፣ በህግ የተደገፈና ህጋዊ ስልጣንን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት በማለት ያስቀምጥ[37] እንጂ እነዚህ መነሻዎች የድርጊቱን ተመጣጣኝነት ልንለካበት የምንችልባቸውን ሁኔታዎችን በማመላከት በጥቅል የተቀመጡ ናቸው። ይህንንም ስንል ይህ

[33] በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአማራ ክልል ፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ፣ 1995 ዓ.ም፣ ዝክረ ህግ፣ ደንብ ቁጥር 6/1995፣ 8ኛ አመት ቁጥር 9 አንቀፅ 38

[34] የኢፌድሪ የወንጀል ህግ 1996 ዓ.ም፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 414፣ አዲስ አበባ አንቀጽ 78 እና 69 ላይ እንደተመለከተው።

[35] የግርጌ ማስታወሻ 31፣ አንቀጽ 56(3) እና (4)

[36] የግርጌ ማስታወሻ 32፣ አንቀጽ 45(1)

[37] የግርጌ ማስታወሻ 31፣

መመሪያ ተመጣጣኝ ሃይል ስንል ምን ማለታችን ነው? እንዴትስ ተመጣጣኝነቱን ልንለካው እንችላለን? የሚለውን ካለማመላከቱ ባሻገር ህጋዊነትን በተመለከተ ህጋዊ ስልጣንን መነሻ ቢያደርግም የህግ ወሰንን መተላለፍ የሚያስከትልባቸው ሁኔታዎች እንዴት ሊለዩ ይችላሉ? የሚሉትን መሰል ጥያቄዎች በአጥጋቢ ሁኔታ አይመልስልንም። ከዚህም ባሻገር የተባበሩት መንግስታት ያስቀመጠውን መመሪያ በሚመለከት መልኩ የተቃኘ የሃይል አጠቃቀም ስርዓት በህግ ማዕቀፍ ውስጥ አለመካተቱም እንደ አንድ ችግር ሊጠቀስ ይችላል። አገራችን አለም አቀፍ የፖለቲካና የማህበራዊ መብቶች የቃል ኪዳን ሰነድን ከተቀበሉት አባል አገራት አንዷ እንደመሆኗ ስለ አገራት የቃል ኪዳን ሰነዱ ትግበራ ኮሚቴው (treaty body) ሊስተካከሉ ይገባቸዋል ብሎ ካቀረባቸው ዋና ዋና ሁኔታዎች ውስጥ የተባበሩት መንግስታት የሃይል አጠቃቀም መመሪያዎችን ከአገር ውስጥ ህጎች ጋር በማቆራኘት ህግ ማውጣት እንደሚገባ አስገንዝቧል።[38]

5.2. የተሟላ የስነ-ምግባር መተዳደሪያ ደንብ ያለመኖር

በፌደራልም ሆነ በክልል ፖሊስ ማቋቋሚያ ደንቦች[39] እና በሌሎች በተሰበጣጠሩ ህጎች የህግ አስከባሪ አካላት ሊከተሏቸው የሚገቧቸው የስነ-ምግባር መርሆዎች በጠቅላላው ቢቀመጡም በክልላችን ግን ራሱን የቻለ የህግ አስከባሪ አካላት ሊከተሏቸው የሚገቡ የስነ-ምግባር መርሆዎች ተደንግገው አይገኙም። ይህም የህግ አስከባሪ አካላት ሊከተሏቸው የሚገቡትን የስነ-ምግባር መርሆዎች አውቀው እንዲተገብሯቸው እድል የሚሰጥ ከመሆኑም አንጻር ተጠያቂነታቸውን ለማረጋገጥ አመቺ ይሆናል። ውጤታማ የሆነ የፖሊስ ተጠያቂነት እንዲኖር የተከሰተውን ጥፋት በመለየት አጥፊው ተጠያቂ የሚሆንበትን መንገድ ማረጋገጥ ብቻም ሳይሆን የፖሊስ አባላት ሊከተሏቸው የሚገቡ የስነ-ምግባር መርሆች እና ደንቦችን በመደንገግ ማሳወቅ ተገቢ ነው።

[38] United Nations, International Covenant on Civil and Political Rights, Human Rights Committee, Consideration of reports submitted by States parties under article 40 of the Covenant, 102nd session Geneva, 11-29 July 2011.

[39] የግርጌ ማስታወሻ 33፣ በአንቀፅ 39 እና ተከታዮቹ ስር የተጠቀሰውን እንዲሁም የፌደራል ፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ (የግርጌ ማስታወሻ 32) አንቀጽ 44 እና ተከታዮቹ ላይ የተጠቀሰው እንዲሁም የደቡብ ክልል ብሄር ብሄረሰቦች የፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ፣ 2007፣ የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 121/2007፣ 21ኛ ዓመት፣ ቁጥር 9፣ አንቀጽ 48 ላይ

5.3. በቂ የወንጀል የምርመራ ማንዋል ያለመኖር

በተለያዩ አገራት የወንጀል ፍትህ ስርዓታቸውን ለማሻሻል ከሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች አንዱ ለህግ አስከባሪ አካላት ምርመራ የሚያደርጉበትን ስልት በማንዋል መልክ አዘጋጅቶ እና ዋና ዋና የምርመራ መርሆችን አካቶ በስራ ላይ ማዋል ነው። ሆኖም በአገራችን የወንጀል ስነ-ስርዓት ላይ ያሉት የምርመራ ስልቶችም ሆነ በፖሊስ አካዳሚ የሚሰጡ ስልጠናዎችን ለማሻሻል የሚያስችል የዳበረ የወንጀል ምርመራ ማንዋል የለም።[40] ይህም ከጅምር የምርመራ ሂደት፣ በብርበራ ወቅት ጭምር መከተል ስለሚገባቸው የምርመራ ስልቶች አመላካች መንገዶችን ያስቀምጣል። የወንጀል ምርመራ ማንዋል መኖር ለህግ አስከባሪ አካላት እንደ የስራ መመሪያ (directive) በመሆን የሚያገለግል በመሆኑ ጠቀሜታው ላቅ ያለ ነው።[41] ስለዚህ የህግ አስከባሪ አካላት ለስራ እንቅስቃሴያቸው አጋዥ እንዲሆን የወንጀል ምርመራ መመሪያ ማንዋሎች ያስፈልጋቸዋል። በተለይም አዲስና የተሻሻሉትን የምርመራ ስልቶችን በማካተት ተግባራዊ ቢሆን የማስረጃ ግኝትን ጠንካራና የሚተማመኑበት ለማድረግ ያስችላል። ስለሆነም የምርመራ ማንዋል መዳበሩ የህግ አስከባሪ አካላት ከጥርጣሬ ጀምሮ ግለሰቦችን ሲይዙ ሰብአዊ መብቶችን እንዲጠብቁ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስልትን የሚዘረጋ በመሆኑ የሚያበረክተው አስተዋጽዖ የላቀ ነው።

5.4. የጦር መሳሪያ አጠቃቀምን የሚወስን መመሪያ ያለመኖር

የህግ አስከባሪ አባላት ሃይልን ተግባራዊ ከሚያደርጉበት መንገድ አንዱ የጦር መሳሪያ መገልገል ነው። በእርግጥ የህግ አስከባሪ አባላት ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የትኛውን የሃይል መንገድ መጠቀም እንዳለባቸው ከወዲሁ ማስቀመጥ ባይቻልም የጦር መሳሪያ መጠቀም የሚፈቀድባቸውን ሁኔታዎች ግን ከወዲሁ በህግ መገደብ ይችላሉ። አገራት የጦር መሳሪያ በምን አይነት ሁኔታዎች የህግ አስከባሪ አካላት መጠቀም እንዳለባቸው በህግ ሊደነግጉ እንደሚገባ በተባበሩት መንግስታት የሃይል እና የጦር መሳሪያ አጠቃቀም መመሪያ[42] ላይ ተቀምጧል። በዚህ መመሪያ ላይ የጦር መሳሪያን የመጠቀም ስልጣን ማቋቋም እና መቆጣጠር

---

[40] በፕሪቭዝን ፌሎው ሽፕ እና በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የተዘጋጀ ረቂቅ የወንጀል ምርመራ ማንዋል ሰነድ (ይህ ሰንድ የሃገሪቱ ፖሊስ አካላትን የምርመራ ዘዴ ለማሻሻል በማሰብ አዲስ በረቂቅ ደረጃ ያለ ማንዋል ዝግጅት እያደረገ ያለ መሆኑን ያሳያል)

[41] Hand book on police accountability, over sight and integrity, United Nations, July 2011. https://www.unodc.org/.../Handbook_on_police_Accountability_Oversight_and_Integ... Accessed at:- 6/5/2019, 8:30 በገጽ 38

[42] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ 5 ላይ የተጠቀሰው።

እንዲሁም በምን ሁኔታዎች እና ለምን ዓላማ መሳሪያ መጠቀም እንደሚቻል ከወዲሁ የሚያስቀምጡ ህጎችን አገራት እንዲያወጡ ይህ መመሪያ ያመላክታል።[43]

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ገዳይ የሆኑ መሳሪያዎችን ለመጠቀም የህግ አስከባሪ አካላት የሚገደዱባቸው ሁኔታዎች ከጅምሩ መዘርዘር ያለበት መሆኑን እንዲሁም ህይወት የመጠበቅ መርህ በህግ ውስጥ ሊመላከት ይገባል። ገዳይ የሆኑ መሳሪያዎች ጥቅም ላይ የሚውሉ በተወሰኑ እና ውስን ሁኔታዎች መሆን እንደሚገባቸው ያስቀምጣል።[44] ስለዚህም ሞትን ሊያስከትሉ የሚችሉ መሳሪያዎችን በውስን እና በጥብቅ ጉዳዮች ብቻ መጠቀም ያለባቸው መሆኑን በህግ ሊደነገግ ይገባል። እንዲሁም የህግ አስከባሪ አካላት ገዳይ ያልሆኑ ሌሎች መሳሪያዎችን በህግ ማስከበር ሂደት ላይ መጠቀም ተቀዳሚ ምርጫቸው እንዲሆኑ መመሪያው ያስገነዝባል።

የጦር መሳሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ ልዩ በሆኑ ድንጋጌዎች የተቀመጠ እና በጣም ለከባድ ጉዳዮች ብቻ የህግ አስከባሪ አካላት እርምጃ ሊወስዱባቸው የሚችሉባቸው መሆን እንዳለባቸው መገንዘብ አለባቸው። በተለይም የሕግ አስከባሪ አካላት የጦር መሳሪያ ሲጠቀሙ የሰዎችን ህይወት በማያጠፋ መልኩ መሆን አለበት።

ሆኖም በአገራችን የጦር መሳሪያ በህግ አስከባሪ አካላት ጥቅም ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ በበቂ ሁኔታ አልተደነገገም። የህግ አስከባሪ የመሳሪያ አጠቃቀምን በተመለከተም የፌደራል ፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ[45] ላይ በጥቂቱ ያነሳ ሲሆን ይህም የፖሊስ አባላት መሳሪያ ሊጠቀም የሚችለው፡- (ሀ) በራሱ ወይም በሌላ ሰው ላይ ሞት ወይም ከፍተኛ የአካል ጉዳት የሚያደርስ ጥቃት ለመከላከል ወይም በማምለጥ ላይ ያለ አደገኛ የወንጀል ተጠርጠሪ በህግ ቁጥጥር ስር ለማዋል ወይም ከእስር ለማምለጥ ያለን ተጠርጣሪ ወይም ፍርደኛ ለማስቆም ከጦር መሳሪያ ውጭ ያሉ ሌሎች እርምጃዎች በቂ ሆነው ሳይገኙ ሲቀሩ ብቻ ነው በሚል ያስቀምጣል። የጦር መሳሪያ አያያዝን አስመልክቶ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 55 መሰረት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህግ የማውጣት ስልጣን ያለው መሆኑን ይደነግጋል።[46] ሆኖም ይህ የመሳሪያ አጠቃቀም በተለይም በተቃውሞ ሰብሰባዎች፣ ሰላማዊ ሰልፍ፣ በረብሻ ጊዜ ሊወስዱት የሚገባ የጦር

[43] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 4።
[44] ዝኒ ከማሁ
[45] የግርጌ ማስታወሻ 32 አንቀጽ 44 እና ተከታዮቹ። በተጨማሪም የደቡብ ክልል ብሄር ብሄረሰቦች የፖሊስ መተዳደሪያ ደንብ፣ 2007፣ የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ነጋሪት ጋዜጣ፣ ደንብ ቁጥር 121/2007፣ 21 ዓመት፣ ቁጥር 9፣ አንቀጽ 49(2) ላይ በተመሳሳይነት የጦር መሳሪያ አጠቃቀም ተደንግጓል።
[46] የግርጌ ማስታወሻ 19፣ አንቀጽ 55 ስር እንደተገለጸው።

መሳሪያ አጠቃቀም የጥንቃቄ እርምጃዎች እና ተጠያቂነትን በውስጡ በበቂ ሁኔታ አካቶ አይገኝም። ለምሳሌ በአገራችን የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ በታወጀበት ወቅትም በወጣው አዋጅ በአንቀጽ 11 ላይ እንደሚከተለው ሰፍሮ ይገኛል።[47] ‹‹በዚህ አዋጅ የተመለከቱ የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎችን ለማስፈፀም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ሀይል ለመጠቀም ይችላል›› በሚል በጥቅል ሊወሰድ ስለሚቻለው የሃይል እርምጃ አስቀምጧል። ሆኖም የመሳሪያ አጠቃቀምን በሚወስን መልኩ ያስቀመጠው ድንጋጌ የለም። ሌላው የጦር መሳሪያ አያያዝና አስተዳደርን በተመለከተ በረቂቅነት በተዘጋጀው ህግ አንቀጽ 26[48] ላይ የህግ አስከባሪ አባላት የጦር መሳሪያ አያያዝ፣ አይነት እና ብዛት በተመለከተ በሌላ ደንብ እንደሚወሰን አመላክቶ አልፏል። የክልሉ የፖሊስ መተዳደሪያ ጦር መሳሪያ መቼና እንዴት ጥቅም ላይ ሊውል ይገባል በሚል በደንቡ ያላስቀመጠ ሲሆን በክልሉ የተዘጋጀው ደንብ ቁጥር 44/2000[49] የጦር መሳሪያ ቁጥጥር ላይ ያተኮረ ሲሆን የህግ አስከባሪ አባላት የጦር መሳሪያን ጥቅም ላይ ሊያውሉ ስለሚገባቸው ሁኔታዎች እና መወሰድ ስላለባቸው የጥንቃቄ እርምጃዎች በሚያሳውቅ መልኩ አልተቀመጡም። ስለዚህ የጦር መሳሪያ መጠቀም የህግ አስከባሪ አካላት የሚገደዱባቸውን ሁኔታዎች በማመላከትና በውስን ሁኔታዎች ብቻ የጦር መሳሪያ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ የሚያስችል ህግ ሊኖር ይገባል። ይህም ሲሆን የጦር መሳሪያ በጥብቅ ሁኔታዎች ብቻ እንዲጠቀሙ የህግ አስከባሪ አካላት ላይ ሃላፊነት ይጥላል።

6. በተጠያቂነት ስርዓት ዙሪያ በክልላችን የሚታዩ ችግሮች

በአገራችን ብሎም በክልላችን የህግ አስከባሪዎች በሰዎች ላይ ለሚያደርሱት ሰብአዊ መብት ጥሰት ተጠያቂ የሚሆኑበት ስርዓት ተበጅቷል። ከእነዚህ የተጠያቂነት ስርዓት ውስጥ በዋነኝነት **የዲሲፕሊን ተጠያቂነት እንዲሁም የወንጀል ተጠያቂነት ናቸው።** የሰዎችን ሰብአዊ መብት ሊያስጠብቅ የሚችል ጠንካራ የሆነ የተጠያቂነት ስርአት በክልሉ ተዘርግቷል ወይ? ሃይል የመጠቀም ስልጣንን ከሚያስከትለው ተጠያቂነት ከመለየት አንጻር እንዴት እየተሰራ ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን።

---

[47] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ 3፣ በአንቀጽ 11 ላይ እንደተደነገገው።

[48] የጦር መሳሪያን ለመቆጣጠር እና ለማስተዳደር የወጣ አዋጅ ቁጥር፣ ---/2011 ዓ.ም፣ አንቀጽ 26 (ረቂቅ ህግ) Acessed at: 15/8/2019 4:59 https://chilot.me/.../fdre-firearms-control-and-administration-draft-p...

[49] በአ.ብ.ክ.መ. የተሻሻለው የቀላልና አነስተኛ የጦር መሳሪያ አያያዝና አስተዳደር መመሪያ፣ 2001 ዓ.ም፣ ዝክረ ህግ፣ መመሪያ ቁጥር 44/2001፣ (ይህ መመሪያ የጦር መሳሪያ ቁጥጥር እና አስተዳደር ላይ ያተኮረ መመሪያ ሲሆን የህግ አስከባሪ አካላት የጦር መሳሪያ አጠቃቀምን በምን ሁኔታ ነው የሚለውን አይሸፍንም።)

6.1. የዲሲፕሊን ተጠያቂነት[50]

የህግ አስከባሪ አካላት የዜጎችን መብት የመጠበቅ እና የማክበር ሃላፊነት ያለባቸው ሲሆኑ በስራቸው ላይ የመብት ጥሰቶች ሲያደርሱ በዲሲፕሊን ስርዓት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡ ይህም ተቋማት በውስጥ ደንብ ወይም መመሪያ አባሎቻቸው ላይ እርምጃ የሚወስዱበት አካሄድ ነው፡፡ የአማራ ክልል ፖሊስ የዲሲፕሊን መመሪያ 4/2002 መሰረት ከባድ የዲሲፒሊን ግድፈት ተብለው ከተዘረዘሩት ጉዳዩች ውስጥ አንዱ በህገ መንግስት ውስጥ የተመለከቱትን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች መጣስ ሲሆን የሚያስከትለው ቅጣትም በመነሻነት ከ11% የደሞዝ ቅጣት እስከ ሶስት ወር የደሞዝ ቅጣት፣ ከስራ መደብ፣ ከማዕረግ ደረጃ እና ከደሞዝ ዝቅ ማለት እንዲሁም ከስራ መሰናበትን ጨምሮ የሚያስከትል ነው፡፡[51] በመሆኑም የመብት ጥሰት ደርሶብኛል በሚል በዜጎች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን እንዲሁም በህግ አስከባሪ አባሎቻቸው ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል በቂ አሰራር አለ ወይ በሚል ለኮማንደር አንተነህ ቴዎድሮስ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ የሚከተለውን መልስ ሰጥተውኛል፡-

የፖሊስ አባላት ሰብአዊ መብቶችን በማክበር ረገድ ስልጠና በየግዜው ያገኛሉ፡፡ ሆኖም በስራ ላይ የሚፈጠሩ ግጭቶች ስለሚኖሩ አቤቱታ በሚቀርብበት ወቅት ጉዳዩን ይዘን በማጣራት ጥፋተኛ መሆናቸው ከተረጋገጠ እርምጃ የሚወሰድበት የዲሲፕሊን አሰራር አለ፡፡ አባሎቻችንን እንቀጣለን እናርማለን፡፡ ነገር ግን አንዳንዴ አቤቱታ ቀርቦ የመደራደር እና ክሱን መጨረሻ አለማድረስ ችግር ቢታይም በህብረተሰቡ ያለንን ከበሬታ እና አመኔታ የሚያሳጡን አባላት ላይ ከባድ የሆነ የዲሲፕሊን እርምጃ እንወስዳለን፡፡ ሆኖም ጉዳያቸውን በምናይበት ወቅት ስለ ሃይል መጠን አጠቃቀም ግንዛቤ ቢኖረንም የሃይል መጠን ማሳለፍ ወይም ተመጣጣኝ አለመሆን የሚል መርህን መሰረት በማድረግ ሳይሆን አባላት ላይ እርምጃ የምንወስደው የጣሱትን መብት መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በአብዛኛውም ድብደባ፣ አካል ማጉደል፣ የመግደል ሙከራ እያልን ወይም በጠቅላላው በሰብአዊ መብት ጥሰት በሚል የሚቀርብ የዲሲፕሊን ክስ ነው፡፡[52]

በተመሳሳይ የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን የሰው ሃይል አስተዳደር ሃላፊ በክልሉ ያለው የህግ አስከባሪ አካላት የሃይል አጠቃቀም ምን ይመስላል በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ‹‹በአባላት የሚፈጸሙ

---

[50] የዲሲፕሊን ጉዳዮች ላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች አገልግሎት እየሰጡ ያሉ አባላትን የሚጨምር በመሆኑ ሚስጥራዊነትን ለመጠበቅ ስንል ስማቸው በጥናቱ ላይ አልተገለጸም፡፡

[51] በአብክመ ፖሊስ ኮሚሽን የፖሊስ አባላት የዲሲፕሊን መመሪያ፣ 2002፣ መመሪያ ቁጥር 4/20002፣ አንቀጽ 7፣ ገጽ 3

[52] ኮማንደር አንተነህ ቴዎድሮስ፣ የማዕከላዊ ጎንደር ዞን ፖሊስ መምሪያ የሰው ሃይል አስተዳደር ሃላፊ፣ የሃይል አጠቃቀም እና ዲሲፕሊን ተጠያቂነት ላይ የተደረገ ቃለ-መጠይቅ፣ ጥር 5/2011 ዓ.ም

የመብት ጥሰት በአብዛኛው በወረዳው በዚያው የሚታዩ ሲሆን በይግባኝ በዞን እንዲሁም በውስን ጉዳዮች በክልሉ የሚታዩ ጉዳዮች ያሉ ቢሆኑም የህግ አስከባሪ አካላት የሚያደርሱት የመብት ጥሰት በምን ደረጃ ላይ ይገኛል የሚለው በጥናት የተደገፈ ባለመሆኑ ይህን በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም። ሆኖም የመብት ጥሰቶች ሲደርሱ የሚጠየቁበት ስርዓት በመዘርጋቱ አቤቱታ ሲቀርብ ተጣርቶ ተጠያቂ የሚሆኑበት ስርዓት ተበጅቷል››[53] በሚል ምላሻቸውን ሰጥተውኛል።

በመሆኑም የዲሲፕሊን ተጠያቂነት እንዴት እየተተገበረ ነው የሚለውን ለማሳየት የሚከተሉትን የዲሲፕሊን ጉዳዮች እንመልከት፡-

ተከሳሽ ያለበቂ ምክንያት ተጠርጣሪውን በቀበሌ ጊዜዊ ማቆያ ውስጥ አስሮ በማቆየት የድብደባ ወንጀል ፈጽሞበታል በሚል የቀረበ ሲሆን በወረዳው የፖሊስ ጽ/ቤት በመመሪያ ቁጥር 4/2002 ክፍል 7 "ለ" መሰረት ለምናገለግለው ህዝብ በፖሊስ ተቋም ላይ አመኔታ የሚያሳጣ እና የሰብአዊ መብት ጥሰት የፈፀመ በመሆኑ ከስራ ሊሰናበት ይገባል በሚል የተወሰነ ሲሆን ሆኖም በይግባኝ ይህ በመታረም ከሚሰራበት ወረዳ ወደ ሌላ ወረዳ ተዛውሮ እና ከደረጃ ዝቅ እንዲል በማድረግ የ1ወር ደሞዙን እንዲቀጣ ውሳኔውን በማሻሻል ተወስኗል።[54] በሌላ ጉዳይም ተከሳሽ ሮንድ በሚያደርግበት ወቅት የግል ተበዳይን ሰብአዊ የሆነ መብቱን በመጣስ ደብድቦታል በሚል ክስ ቀርቦበት ይህም በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ ከተጣራ የአንድ ወር ደሞዙ 25% እንዲቀጣ ተወስኖበታል። ሆኖም ይግባኙን ለዞኑ መምሪያ አቅርቦ የስር ውሳኔውን በማሻሻል ወደ 15% እንዲቀጣ ተወስኖበታል።

እነዚህ የዲሲፕሊን ጉዳዮች መነሻ ምክንያቶች ስራን መሰረት ያደረጉ በመሆኑ ተጠያቂ ሲደረጉም ስራቸውን ማዕከል ባደረገ መልኩ ሊሆን ይገባል። ለምሳሌ በስራ ላይ እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው ተጠርጣሪን የመያዝ ስልጣን ተመጣጣኝ ሃይል እንዲጠቀሙ የሚፈቅድ ሲሆን

---

[53] ኮማንደር ጋሻዬ መልካሙ፣ የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን የሰው ሃይል አስተዳደር ሃላፊ፣ የሃይል አጠቃቀም እና የዲሲፕሊን ተጠያቂነት ላይ የተደረገ ቃለ መጠይቅ፣ በቀን 19/9/2011 ዓ.ም ከቀኑ 9፡00

[54] በተጨማሪ ለማሳያነት ተከሳሽ በሞባይል ስርቆት በመጠርጠር የያዘውን ግለሰብ ከሳሹን ማግኘት አልቻልኩም በማለት ለ7 ቀናት ያህል በጣቢያ በማቆየቱ እና ለፍርድ ቤት ባለማቅረቡ ከባድ የዲሲፕሊን ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛነቱ በመረጋገጡ በ11% እንዲቀጣ ተወስኖበታል። በሌላ ጉዳይ ተከሳሽ የጥበቃና የአቀራረብ ኦፊሰር ሆኖ በሚሰራበት ወቅት በሰዎች ላይ ድብደባ (የሰብአዊ መብት ጥሰት) በማድረሱ እንዲሁም ሌሎች ከስራው ጋር የተያያዙ ተደራራቢ ክሶች ቀርበውበት የወረዳው ሃላፊ ከስራ እንዲባረር ሲወስን በይግባኝ ለዞን ፖሊስ መምሪያ ጉዳዩ ቀርቦ የመጀመሪያው ጥፋት ከመሆኑ አንጻር የተጣራ የ1ወር ደሞዙን እንዲቀጣ ተወስኖበታል።
በሌላ ጉዳይ ተከሳሽ የግል ተበዳይን በመደብደቡ የተጣራ የ1ወር ደሞዙን እንዲቀጣ ተወስኗል። እዚህ ውሳኔ ላይ ለመደረስም ከዚህ በፊት ትራፊክ ፖሊስ ሆኖ በሚሰራበት ወቅት ከሹፌር ጋር በመደባደቡ በወረዳው 11% ተቀጥቶ በዞኑ 5% የተሻሻለበት ሪከርድ ቀርቦበታል። (የትራፊክ ፖሊስ በፖሊስ አደረጃጀት ስር ያለ በመሆኑ ጉዳዩ የማየት ስልጣን ያለው በየደረጃው ያለው የክልሉ ፖሊስ ነው)

በዚህ ጊዜም የተጠቀሙት ሃይል ያደረሰውን ጉዳት ከመለካት ይልቅ የህግ አስከባሪው ተከሳሽን ለመያዝ በቂ ምክንያት ነበር ወይ ከነበረስ የተጠቀመው ሃይል ተመጣጣኝ ወይም ከልክ በላይ ነበር ወይ የሚለውን በሚመዝን መልኩ አይደለም። በክልሉ የፖሊስ አካላት መተዳደሪያ ደንብ ስር አንድ የፖሊስ አባል ተግባራዊ ሊያደርጋቸው የሚገቡ መርሆች በሚል በጥቂቱ የተጠቀሱትን መርሆዎች በመስፈርትነት በዲሲፕሊን መመሪያው ስር እንደ መመዘኛ አድርጎም አላካተተም። በመሆኑም ውጤታማ የሆነ የተጠያቂነት ስርአትን ለማምጣት ቅድመ-መከላከል እና በበቂ ሁኔታ ማረም የሚያስችል የዲሲፕሊን ተጠያቂነት መመዘኛ ስርዓት ሊዳብር ይገባል።

6.2 የወንጀል ተጠያቂነት

የህግ አስከባሪ አካላት በሰዎች ላይ በሚያደርሱት ጥሰትን በተመለከተ ተጠያቂ የሚሆኑበት አግባብ በህግ ተቀምጧል። የሃይል እርምጃ አወሳሰድ ከሚያስከትሏቸው ተጠያቂነቶቹ ውስጥ የወንጀል ተጠያቂነት አንዱ ነው። እነዚህም ድንጋጌዎች በወንጀል ህግ ውስጥ በተሰባጠረ ሁኔታ ተደንግገው የሚገኙ ሲሆኑ በተለይ በወንጀል ህግ አንቀጽ 424 እና 407[55] ላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች በአብዛኛው ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው።

በተግባር አሁን ያለው አሰራር ፖሊስ ተመጣጣኝ ሃይልን በማሳለፍ ድብደባ ፈጸመ በሚል መልኩ ክሶች የማይቀርቡና ግለሰቦችም የሃይል መጠንን በማሳለፍ ፖሊስ ደበደበኝ ሳይሆን በፖሊስ ተደብድበናል የሚሉ በደፈናው የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ነው የሚያነሱት በማለት ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ ባደረኩላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸውልኛል።[56] በተጨማሪም ብዙ ግዜ ፖሊስ ደበደበኝ ተብሎ አቤቱታ የሚቀርብ ሲሆን ነገር ግን ማስረጃ በማጣት ምክንያት ውጤታማ የማይሆን መሆኑን ገልጸዋል። አቤቱታዎቹ ሲቀርቡ ፖሊስ የሃይል መጠንን በመተላለፍ የሰብአዊ መብት ጥሰት ፈጽሞብኛል በሚል ሳይሆን ተደብድቢያለሁ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች ናቸው።[57] የህግ አስከባሪ አካላት የሃይል አጠቃቀምን በተመለከተ ተመጣጣኝ ሃይል ምንድን ነው? እንዴትስ ይመዘናል? ለመመዘንስ ምን እንጠቀማለን የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ በህግ ውስጥ በበቂ ሁኔታ ባለመካተቱ በማስረጃ ምዘና ወቅት አብሮ ይህንን

[55] የግርጌ ማስታወሻ 34፣ አንቀጽ 424 እና 407

[56] አቶ ተስፋዬ ከበደ እና አቶ ጌትነት ዋጋህ (በጋራ)፣ የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ የሃይል አጠቃቀም ጽንሰ-ሃሳብ እና አተገባበሩ በሚል የተደረገ ቃለ-መጠይቅ፣ በቀን 19/07/2011 ዓ.ም።

[57] አቶ ቻላቸው አሞኘ፣ በአብክመ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ቢሮ የማዕከላዊ ጎንደር ዞን ዐቃቤ ህግ፣ የሃይል አጠቃቀምን በተመለከተ የተደረገ ቃለ-መጠይቅ፣ 7/5/2019

ለማካተት አስቸጋሪ በመሆኑ ይህንንም በሚወስኑበት ወቅት በርትዕ ከጉዳይ ጉዳይ በማየት እንደሁኔታው የሚወስኑ መሆኑን ገልፀዋል።[58] በተመሳሳይም የማዕከላዊ ጎንደር ዓቃቤ ህግ ‹‹አንድ ሃይል ተመጣጣኝ ነው ለማለት አንድ ምክንያታዊ የሆነ ግለሰብ በወቅቱ ሊወስደው ከሚገባው ሁኔታ በመነሳት መመዘን አለበት። በተጨማሪም እንደመለኪያነት ሰብአዊ መብቶችን ከመጠበቅ አንፃር ሊታይ ይገባዋል።››[59] በማለት ተመጣጣኝነት ሊተረጎም የሚችልበትን አግባብ ገልፀዋል። እንዲሁም አቶ ጦይብ እንድሪስ በስነ-ስርዓት ህጉ ተመጣጣኝ ሃይል መጠቀም ተብሎ የተቀመጠው በደፈናው በመሆኑ ተመጣጣኝ ነው ለማለት የሚያስችል በመለኪያነት ልንከተለው የምንችላቸውን መነሻዎች በህጉ ተመላክተው ቢቀመጡ የተሻለ አሰራር እንደሚፈጥሩ ገልጸዋል።[60]

አሁን ባለው የወንጀል ተጠያቂነት ስርዓት ስር አንድ ተጠርጣሪ ያለው የስልጣን ሃላፊነት ማለትም በስራው ምክንያት ያደረሰው ጉዳት ከግምት ውስጥ ሲገባ በስራው ላይ ግን በህግ የተሰጠው የሃይል መጠቀም መብትን ከተላለፈው መብት ጋር በሚመዝን ስልት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የመለኪያ ስልት የለም። ይህንንም ለማሳየት የሚከተሉትን መዝገቦች እንመልከት፡-

ተከሳሽ የፖሊስ ባልደረባ ሆኖ በሚሰራበት ወቅት የግል ተበዳይን "ና" ለጥያቄ ትፈለጋለህ በማለት በጥፊና በቦክስ የግራ አይኑን ደጋግሞ የመታው እና ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ በስልጣን ያላግባብ መገልገል ወንጀል ክስ ቀርቦበት ተወስኖበታል።[61] ፍርድ ቤቱ በፍርድ ሀተታው ላይ፡-

ተከሳሽ በአዴት ፖሊስ ጣቢያ አባል ሆኖ በሚሰራበት ወቅት በተሰጠው የስልጣን ሃላፊነት የሰዎችን መብት ማክበር ማስከበር ግዴታ እያለበት በህገ መንግስቱ የተቀመጠውን የአካል ደህንነት መብት እንዳለው ከህግ ስርዓት ውጭም ሊያዝና ሊታሰር የማይችል መሆኑን እያወቀ የፖሊስ መለዮ ልብሱን እንደለበሰ የግል ተበዳይን ፈልገዋለሁ በማለት በጥፊና በቦክስ የመታው በመሆኑ በስልጣን ያላግባብ መገልገል ወንጀል ጥፋተኛ ነው በማለት ወስኗል። ከውሳኔውም የምንመለከተው በተጠርጣሪው ላይ ያደረሰው የሰብአዊና አካላዊ የመብት ጥሰት እንጂ ተከሳሽ (ፖሊሱ) ተጠርጣሪን ለመያዝ በቂ ምክንያት ነበረው ወይ? የሃይል እርምጃ ሊያስወስድ

[58] በአ.ብ.ክ.መ. የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች ከሆኑት አቶ ተስፋዬ ከበደ እና አቶ ጌትነት ዋጋነህ ጋር በጋራ የተደረገ ቃለ-መጠይቅ 19/07/2011 ዓ.ም

[59] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 48 ላይ እንደተመለከተው

[60] ጦይብ እንድሪስ፣ በአብክመ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ቢሮ የማዕከላዊ ጎንደር ዞን ዐቃቤ ህግ፣ የሃይል አጠቃቀም መመዘኛን አስመልክቶ የተደረገ ቃለ-መጠይቅ፣ በቀን 7/5/2019.

[61]የትዋለ ሙሉነህ ጸጋ እና ዐቃቤ ህግ፣ የወ/መ/ቁ/ 011554፣ ባህር ዳር ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ በቀን 15/5/2011 ዓ.ም ውሳኔ ተሰጠ

የሚያስችል አስገዳጅ ነገር ነበር ወይ? የተጠቀመውስ ሃይል ተመጣጣኝ ነበር ወይ? የሚሉት ጥያቄዎች በውሳኔው አልተቃኙም። ይህ ውሳኔ የፖሊስ አባሉ ስልጣኑን አላግባብ መገልገል ትኩረት በመስጠት የተሰጠ ውሳኔ ነው። ሆኖም ሃይል ለመጠቀም ስልጣንን መነሻ የሚያደርጉ ምክንያቶች በመኖራቸው የተፈጸመው ድርጊት መከሰት ብቻ ተጠያቂነት ከመፍጠሩ ይልቅ የህግ አስከባሪው ስራው ላይ የወሰደው እና ሊወስደው የሚገባ የሃይልን መጠን በማየት ውሳኔ መስጠት ለውሳኔው ሚዛናዊነት የሚያበረክተው አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነው። ይህንንም ሃሳብ በምሳሌ ለማሳየት ተከሳሽ እስረኛ አጅቦ ጥር 23/2008 ዓ.ም አብዱራፊ ከተማ ቀበሌ 01 በሚሄድበት ወቅት እስረኛው ለማምለጥ ጥረት በማድረጉ አንድ ጥይት በመተኮስ ከመቀመጫው ከፍ ብሎ በመምታት የገደለው በመሆኑ የአስገዳጅ ሁኔታ ወሰንን በመተላለፍ ጥፋተኛ ተብሏል። ነገር ግን በዚህ መዝገብ ላይ የአስገዳጅ ሁኔታን አልፏል በማለት የተጠቀመበት መለኪያ በርትዕ ላይ የተመረኮዘ ከመሆኑ ባሻገር በውሳኔውም ዝርዝር ውስጥ ለርትዕ የተጠቀመበት መነሻ መመዘኛ አልተብራራም።[62] በተመሳሳይም ተከሳሽ (ፖሊስ) የግል ተበዳይን በያዘው ዱላ አንድ ግዜ ከመታው በኋላ በድጋሜ የግራ እጁን ክንድ በመምታት እጁን የሰበረ በመሆኑ በፈጸመው ስልጣን ያላግባብ መገልገል ወንጀል ክስ ቀርቦበት በቀረቡት ምስክሮች ተመስክሮበት ጥፋተኛ ተብሏል።[63] በዚህ መዝገብ ውስጥ ተከሳሽ ህግን ለማስከበር መነሻ ቢኖረውም ከልክ በላይ ሃይል መጠቀሙን የቀረቡት ምስክሮች ያሳያሉ ሆኖም በመዝገቡ ውስጥ ተከሳሽ በባለጉዳዩ ላይ ያደረሰውን ጉዳት ከተከሳሹ ስልጣን ጋር አብሮ በማያያዝ የሚደረግበት ስልት ሙያዊ ግዴታን የሚወጡ አካላትን በአግባቡ ለመመዘን የሚያመች ስርዓት አይፈጥርም። በህጉም የተቀመጡትን የመከላከያ ዘዴዎች በሚከተለው ምሳሌ ብንመለከት፡- ተከሳሽ የወንጀል ህግ አንቀጽ 540ን በመተላለፍ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል በሚል ክስ ያቀረበ ሲሆን ተከሳሹ ሟች በመጀመሪያ ተኩሶ ጭኔ ላይ የመታኝ እና በአልሞት ባይ ተጋዳይነት ስተኩስ ህይወቱ ያለፈ ስለሆነ ጥፋተኛ ልባል አይገባም በማለት መብቱን ጠብቆ ተከራክሯል። ፍርድ ቤቱም የቀረቡትን ምስክሮች ከሰማ በኋላ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 113 መሰረት በማሻሻል ህጋዊ መከላከል በማሳለፍ በሚል ጥፋተኛ ነው በማለት ወስኗል።[64] ነገር ግን በፍርድ ቤቱ የውሳኔ ሀተታ ላይ ህጋዊ መጠን ተላልፏል ለማለት

[62] ከሳሽ ዐቃቤ ህግ እና ረ/ሳጅን ህንፃ ሃጎስ፣ የመ/ቁጥር 02-21993፣ በሰሜን ጎንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ በቀን 29/11/2008 ውሳኔ የተሰጠ

[63] በዐቃቤ ህግ እና ኮንስታብል ትእዛዙ ነበረ፣ የመዝገብ ቁጥር 04-04715፣ ባህር ዳር እና አካባቢያዊ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2008 ዓ.ም።

[64] በዐቃቤ ህግ እና ኮንስታብል መሃመድ ዓሊ አመዴ፣ የመ/ቁጥር 16950፣ በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመ/ቁጥር 16950 28/6/2011 ዓም ውሳኔ ተሰጠ

የተጠቀመበት መለኪያ ያልተገለጸ በመሆኑ በመለኪያነት የተጠቀመባቸውን መስፈርቶች ለማወቅ አስቸጋሪ ያደርገዋል። አሁን ያለው የሃይል አጠቃቀም ተመጣጣኝነት መለኪያ ከጉዳይ ጉዳይ በማየት የሚወሰንና በርትዕ ላይ የተመረኮዘ ነው። ይህም የርትዕ መስፈርት ሰፊ የሆነ በመሆኑ ወጥ የሆነ አሰራር እና ተቀራራቢ የሆነ የተጠያቂነት ስርዓትን በህግ አስከባሪ አካላት ላይ ለማስፈን አመቺ አይደለም።

6.3 ነጻና ገለልተኛ የተጠያቂነት ስርዓት ያለመኖር

የህግ አስከባሪ አካላት የመንግስት አሰራር ከሚያንጸባርቁ አካላት ውስጥ ጎልቶ የሚወጡ ከመሆናቸው አንጻር ማህበረሰቡ በህግ አስከባሪ ተቋማት ላይ አመኔታ እንዲኖረው እይታው ላይ በርትቶ ሊሰራ ይገባዋል።[65] ዋነኛው የህግ አስከባሪ አካላት ተልዕኮ ሰላምና ደህንነትን ማረጋገጥ ሲሆን በዚህም ተግባር ውስጥ የግለሰቦችን ዋነኛ መብቶችን እና ነጻነቶችን ማክበር ይጠበቅባቸዋል። ይህም ሊሆን የሚችለው የህግ አስከባሪ አካላት ተጠያቂ ሊያደርግ የሚያስችል ነጻና ገለልተኛ የሆነ የተጠያቂነት ስርዓት ሲኖር ነው።[66] ሆኖም በአገራችን ብሎም በክልላችን ያሉት የዲሲፕሊን መዋቅሮች የውስጥ አሰራርን የያዙ እና ሌሎች አካላትን በውስጣቸው የሚያካትቱ አይደሉም። የህግ አስከባሪ አካላት የሚያደርሱት የሰብአዊ መብት ጥሰት ላይ የተወካዮች ምክር ቤት የማጣራት ስራ የሚሰራ ቢሆንም እንደኛ ባለ በዲሞክራሲ ያልጠነከረ አገር ላይ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ ማጣራት ስራ ማድረግ አዳጋች ይሆናል። ሌሎች ተቋማት እንደ ሰብአዊ መብት እና እንባ ጠባቂም ያሉ ተቋማት የመብት ጥሰቶችን ከማሳወቅ እና ሪፖርት ከማቅረብ ያለፈ ተጠያቂነትን ሊያረጋግጥ የሚያስችል ወሳኝ ስልጣን የሌላቸው በመሆኑ ተጠያቂነትን ለማስፈን አዳጋች ያደርገዋል። በተለይም አሁን ያለው የህግ አስከባሪ ተቋማት በአባላቶቻቸው ላይ በቂ እና ተመጣጣኝ እርምጃ እየወሰዱ የሚገኙ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ አካል የለም።[67] በመሆኑም የህግ አስከባሪ ተቋማት ተቋማዊ አደረጃጀታቸውን በማሻሻል ነጻና ገለልተኛ የሚሆኑበትን መዋቅር ሊፈጥሩ ይገባል።

---

[65] Hand book on police accountability, over sight and integrity, United Nations, July 2011. ገጽ 19 https://www.unodc.org/.../Handbook_on_police_Accountability_Oversight_and_Integ... Accessed at:- 6/5/2019, 8:30

[66] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 2፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የህግ አስከባሪ አካላት በመፍጠር የተጠያቂነትን ስርዓት የሚያጠናክር ስርዓት አስፈላጊ መሆኑን የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ የሰጠው መግለጫ።

[67] The AUSTRALIAN goverement country report, dfat country information report on ethiopia, 28 september 2017, https://dfat.gov.au/about-us/publications/.../country-information-report-ethiopia.pdf Accessed at: 6/5/2019, 8:30 እና ዝኒ ከማሁ

7. መደምደሚያ

በአገራችን የህግ አስከባሪ አካላት የሃይል አጠቃቀምን በተመለከተ ያላቸውን ስልጣን ለመገደብ እና የሃይል አጠቃቀማቸውን ለመመዘን የሚያስችል መነሻ በተለያዩ ህጎች እና ደንቦች ላይ ተጠቅሰው ይገኛሉ። ሆኖም በተግባር ላይ ያሉ ህጎች የህግ አስከባሪዎች ያላቸውን ሰፊ ስልጣን ለመቆጣጠር እና ለመመዘን በሚያስችል መልኩ በበቂ ሁኔታ ተደንግገው አይገኙም። በመሆኑም በሰዎች ላይ የህይወት እና የአካል ደህንነት መብቶች ሲጣሱ ይስተዋላል። ይህን ለመከላከል እንዲቻል በተለያዩ ህጎች ተሰበጣጥረው የሚገኙትን ህጎችን በማዳበር እስካሁን ምንም አይነት እርምጃ አልተወሰደም።

ስለሆነም የህግ አስከባሪዎች ያላቸውን ስልጣን ያላግባብ እንዳይገለገሉ ለመወሰን ያሉትን ህጎች ማዳበር አስፈላጊ ነው። እንዲሁም በተግባር ያለው የተጠያቂነት ስርዓቱ በነጻና ገለልተኛ አካላት የጎለበተ ባለመሆኑ የሰዎችን ሰብአዊ መብቶች ለመጠበቅ የህግ አስከባሪ አባላት የተቀመጡላቸውን የስልጣን ገደቦች ተላልፈው በሚገኙበት ግዜ ነጻ እና ገለልተኛ በሆነ አካል ተጠያቂ የሚሆኑበትን ስርዓት መዘርጋት አለበት። ከዚህም ባሻገር የሰብአዊ መብቶችን ጥበቃ ለማጠናከር እና አሁን ያለውን የሃይል እና የጦር መሳሪያ አጠቃቀምን ለማሻሻል የህግ አስከባሪ አካላት ያላቸውን ስነ-ምግባር ማጎልበትና የተቋማቱንም አቅም ማሳደግ ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ የህግ አስከባሪ አካላት ሃይልን ለመጠቀም የሚያስችል ሰፊ ስልጣን ያላቸው ከመሆኑ አንጻር የሰዎችን ሰብአዊ መብቶችን ጥበቃ ለማሰጠት የሃይል አጠቃቀም ስልጣንን ሊገድብ እና ሊለካ የሚችልበት ህግ ሊጠናከር እንዲሁም ተጠያቂነቱ ነጻና ገለልተኛ አካል እንደገና ሊዋቀር ይገባል።

ምክረ-ሃሳብ

በአገራችን ብሎም በክልላችን የህግ አስከባሪ አካላት የሃይል አጠቃቀም ላይ ያሉት የህግ እና ተግባራዊ ችግሮች በዚህ ጥናት ተዳሰዋል። በመሆኑም አሁን በተግባር ላይ ያለውን የህግ አስከባሪ አባላት የሃይል አጠቃቀም ለማሻሻል በመጀመሪያ የህግ ማዕቀፉን ማዳበር እና የህግ አስከባሪ አካላት የሃይል አጠቃቀምን በመለካት ተጠያቂ የሚሆኑበትን የተሻለ አሰራር መፍጠር ይገባል። ለዚህም በተባበሩት መንግስታት የወጡትን አለም አቀፍ የሆኑ የሃይል አጠቃቀም መርሆች ተግባራዊ እንዲያደርጉ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ሊዳብር ይገባል። ይህም የህግ

አስከባሪ አካላት ስራቸውን ሲተገብሩ ሊደርሱ በሚችሉ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ተጠያቂ እንዲሆኑ የሚያስችል ግልጽ የሆነ ስርዓትን ይፈጥራል።

በተለይም በህግ አስከባሪ አካላት ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች በገለልተኛ አካል እንዲጣሩ የሚያስችል ስርዓት መፍጠር የተቋሙን የውስጥ አሰራር ነጻና ገለልተኛ በሆነ አካል በማዋቀር በንቃት መፈተሽ ይገባል። ይህም ሲሆን የህግ አስከባሪ አካላት ያላቸውን ተቋማዊ ተአማኒነት ለማሳደግ ያግዛቸዋል። በዲሲፕሊን ተጠያቂነት ስር የሃይል አጠቃቀምን በመለካት የህግ አስከባሪ አካላት ሊያስተምር እና ሊያርም እንዲሁም ሌሎችንም ሊከለክል የሚያስችል የተጠያቂነት መመዘኛ በማዘጋጀት ሊዳብር ይገባል። የህግ አስከባሪ አካላት መርህ አድርገው ሊንቀሳቀሱ የሚችሉባቸውን የስነ-ምግባር መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊነቱ የላቀ ነው። የህግ አስከባሪ አካሉ አካላዊ ብቃት እና ጥንካሬ ላይ ከማተኮር ይልቅ በሞራል እና ስነ-ምግባር የተገነባ የሕግ አስከባሪ አካል ማፍራት ውጤታማነቱ የላቀ ነው። በመሆኑም የህግ አስከባሪ አባላት የስነ-ምግባር መርሆች ላይ ተከታታይነት ያለው ስልጠና እና ምዘና ሊያገኙ የሚችሉባቸው ስርዓቶች ሊመቻቹ ይገባል።

በተለይም ሃይል ጥቅም ላይ ከሚውልባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ የጦር መሳሪያ መጠቀም እንደመሆኑ መጠን የጦር መሳሪያ አጠቃቀም ላይ በበቂ ሁኔታ የዳበሩ የጦር መሳሪያ አጠቃቀምን ለመገደብ የተደነገጉ ህጎች ሊኖሩ ይገባል። ይህም የህግ አስከባሪ አካላት የሰዎችን ሰብአዊ መብት ከመጠበቅ አንጻር ሊወስዱ የሚገባቸውን የቅድመ-ጥንቃቄ መርህ የሚጥል በመሆኑ አስፈላጊነቱ የማይካድ ነው። ይህም ሲሆን ገዳይ የሆኑ መሳሪያዎች ጥቅም ላይ የሚውልባቸውን ሁኔታ በህግ የሚገደብበትን አሰራር ይፈጥራል። በመሆኑም የህግ አስከባሪ አካላት መሳሪያ ሊጠቀሙበት የሚገባቸውን ሁኔታዎችን በመገደብ በህግ ማስቀመጥና ገዳይ ያልሆኑ መሳሪያዎች በህግ አስከባሪዎች ዘንድ በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ለሰዎች የህይወት እና የአካል ደህንነት ጥበቃ መፍጠር ይገባል።

በአገራችን ያለው የወንጀል ምርመራ ዘዴ ኋላ ቀር በመሆኑ የምርመራ ማንዋል በማዘጋጀት የወንጀል ጉዳዮች እንደ ወንጀል ይዘታቸው ሊከተሉት የሚገባ የምርመራ ዘዴን እና የማስረጃ ይዘት በማካተት እና አዳዲስ እና ነባር ዘዴዎችን በማዳበር የተሻለ አሰራር ሊፈጠር ይገባል። ይህም የተጠርጣሪዎችን የህይወት እና የአካል ደህንነት የተሻለ ጥበቃ ሊሰጥ ይገባል።

በአጠቃላይ የሃይል አጠቃቀምን በተመለከተ ያለው የህግ ማዕቀፍ ሊዳብር እና አተገባበሩ ላይ ሊወሰዱ የሚገባቸው የመቆጣጠሪያ መንገዶች ሊሻሻሉ ይገባል።

ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክርክር ሂደት በዓለምአቀፍ እና በኢትዮጵያ ህግ

አራጌ ዘለቀ*

አፅርዖተ-ፅሁፍ

ተከሳሽ በሌለበት በተደረገ የወንጀል ክርክር እና ይህን ተከትሎ በሚሰጥ ፍርድ ላይ የሚነሱ የፍ/ቤት ክርክሮችን መመልከት የጀመርኩት ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በደ/ንንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በወንጀል ችሎት በዳኝነት ስሰራ በነበረበት ወቅት በተለይ በግድያ ወንጀል ተከሰዉ ከመኖሪያ አካባቢያቸዉ ባለመገኘታቸዉ ጉዳያቸዉ በሌሉበት ታይቶባቸዉ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ቀርበዉ መከሰሴን አላወኩም (መጥሪያ አልደረሰኝም) ነበር በሚል ክርክሩ እንደገና ባሉበት እንዲታይላቸዉ (re-trial) የሚያቀርቡትን የተከሳሾች ክርክር ስሰማ ነበር። በቅርቡ ደግሞ እነ አቶ በረከት ሰምኦን በተከሰሱበት የሙስና ወንጀል ጉዳያቸንን ችሎት ሳንቀርብ እንከታተል የሚል ጥያቄ አቀረቡ መባሉን እንዲሁም አቶ ጌታቸዉ አሰፋ እና ሌሎች የደህንነት ሰዎች በሌሉበት[1] በተከሰሱበት የሰብዓዊ መብት ጥሰት ወንጀል የነበረዉን የፍ/ቤት የመጥሪያ ሂደት እና የሚሰጡ አስተያየቶችን ስመለከት ይህን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ ትንሽ ዳሰሳ ማድረግ አስፈለገ ሆኖ አገኘሁት።

ስለሆነም ይህ ፁሑፍ በወንጀል የተከሰሰ ሰዉ ክርክሩ በሌለበት የሚታየዉ በምን ሁኔታ ነዉ? ተከሳሽ በክርክሩ እንዲገኝ ማድረግ መብት ወይስ ግዴታ? ክርክሩ በሌለበት ቢታይ በጠበቃ የመወከል መብትስ አለዉ ወይ? ፍርድ ከተሰጠ በኋላስ ክርክሩ እንደገና ባለበት የሚታየዉ በምን ምክንያት ነዉ? ከፍ/ቤት ሳልቀርብ ከእስር ቤት ወይም ከቤቱ ሆኜ ክርክሩን ልከታተል ማለትስ ይችላልን? የሚሉ ነጥቦች ላይ የተከሰሱ ሰዎች ያላቸዉን ህጋዊ መብቶች መነሻ በማድረግ የሀገራችንን ህግጋት ከአለም አቀፍ ህግጋት እና ልምድ ጋር በማነፃፀር ቀርቧል። ከዚህ አኳያ ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል የክርክር ሂደት የተፈቀደዉ በልዩ ሁኔታ እንደመሆኑ የህግ ማዕቀፋችን እና አሰራራችን ከአለም አቀፍ ህግጋትና ተሞክሮ እንዲሁም ከፍትሃዊ የክርክር መብት ጋር የተጣጣመ ስለመሆኑ መርምሯል።

ስለሆነም በረዥም ጊዜ የዳኝነት ስራ ቆይታዬ በጉዳዩ ላይ ያለኝን ተሞክሮ እንዲሁም የፍ/ቤት ዉሳኔዎችን በተለይም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዚሁ ጉዳይ በተለያዩ ክርክሮች የሰጣቸዉን ዉሳኔዎች ዋቢ በማድረግ ተጠቅሜያለሁ። በማጠቃለያም ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክርክር በልዩ ሁኔታ ሊተገበር የሚገባ በመሆኑ በህግ ማዕቀፍ እና በአሰራር የተከሳሽን መሰረታዊ መብት መሰረት ተደርጎ ሊሰራበት የሚገባ ስለመሆኑ፤ ተከሳሽ በችሎት ተገኝቶ ክርክሩን መስማት እና መከላከል መብት ያለዉ ቢሆንም የክርክሩ ሂደት የተጎጅዎችና የማህበረሰቡ መብትና ጥቅም ያለበት በመሆኑ ክርክሩን ተከሳሽ ባለበት ማየት የመብት-ግዴታ መሆኑንም ጭምር ያስገነዝባል። ክርክሩ ተከሳሽ በሌለበት በታዬ ጊዜ ደግሞ የተከሳሽ መሰረታዊ መብቶች የሆኑት በጠበቃ የመወከል መብት፣ የይግባኝ መብት፣ የመሰማት መብት፣ ንፁህ ሆኖ የመገመት መብት እንዲሁም በእኩል ሚዛን የመዳኘት (የመዳኘት) መብት ተከብረዉ ተከሳሽ በቀረበ ጊዜ ክርክሩን እንደገና የማሰማት (re-trial) መብት ያለዉ መሆኑን ያስገነዝባል።

---

*(LLM)፣ የጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኛ፣ አብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት፣ ባህር ዳር <e-mail: aragezeleke2007@gmail.com>

[1] እነዚህ ጉዳዮች በክርክር ሂደት ላይ በመሆናቸዉ የጉዳዮችን ሂደት አንስተን የምንወያይባቸዉ አይሆንም። ነገር ግን ጉዳዮችን የሚመለከቱ የህግ ማዕቀፎችንና ልምዶችን መሰረት በማድረግ የምንመለከት ይሆናል።

1. ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክርክር ሂደት (trial in absentia)፡- እንደ መግቢያ

“In absentia” የሚለዉ ቃል የላቲን ቃል ሲሆን በሌለበት in the absence of (someone); in (someone’s) absence <tried in absentia> የሚለዉን ትርጓሜ የያዘ ነዉ።[2] ተከሳሽ በሌለበት የሚደረግ ክርክር በተግባር ሀገራት እንደሚከተሉት የህግ ስርዓት የሚለያይ ሲሆን መመዘኛዉም ቢሆን የቀረበዉን ጉዳይ በአለም አቀፍ ተቋማት እና በሀገራቱ ፍ/ቤቶች ካለዉ እይታ አኳያ ይሆናል።[3] የወንጀል ክርክር ስርዓት ሁሉንም የክርክር ሂደቶች ማለትም ከወንጀል ምርምራ እስከ ቅጣት ያለዉን ሂደት ስለሚመለከት ተከሳሽ በሌለበት ክርክር የሚለዉ አገላለፅ በክርክሩ በሁሉም ሂደት አለመገኘት (total in absentia) እና በመሃል አቋረጦ የቀረ (partial in absentia) ተብሎ ሊከፈል ይችላል።[4] በክርክር ሂደት የተከሳሽ የመገኘት መብት አስፈላጊነት ዕንሰ ሃሳብ የተጀመረዉ በኮመን ሎዉ የህግ ስርዓት ተከታይ ሀገራት ሲሆን የፍ/ቤቶች ስልጣን የሚወሰነዉም ተከሳሹ ቀርቦ ክርክሩን መስማት ሲችል ነዉ በሚል ሀሳብ ነዉ።[5] ስለዚህ ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክርክር ሂደት በክርክሩ ተከሳሽ መገኘት አለበት ከሚለዉ መርህ በተለዩ በልዩ ሁኔታ የሚፈፀም ሂደት መሆኑን ያሳያል። በሀገራችንም ተከሳሽ በሌለበት ክርክር የሚሰማዉ በልዩ ሁኔታ በህግ በተለዩ ወንጀሎች ስለመሆኑ የወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 161(2) ያስገነዝባል።

በእርግጥ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተፃፈ ማጣቀሻ ዉሑፍ እጥረት በመኖሩ አላካተትኩም። በዉጭ ሀገራት የተፃፉትም ቁጥራቸዉ ዝቅተኛ ከመሆናቸዉ በተጨማሪ በሰብዓዊ መብት ጥሰት ምክንያት በአለምአቀፍ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ተቋማት በግለሰብ የይግባኝ ቅሬታ (individual compliant) በቀረቡ ጉዳዮች መነሻነት የተወሰዱ የህግ ትርጉሞችን እንዲሁም የጦር ወንጀለኞችን የተመለከቱ አለም አቀፍ ወንጀሎች መነሻ ተደርገዉ ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክርክር ሂደትን አስመልክቶ የተሰጡ ማብራሪያዎችን የተመለከቱ ሲሆን እነዚህን በማጣቀስ የምንመለከት ቢሆንም በሀገር አቀፍ ደረጃ (at domestic law level) የማጣቀሻ እጥረት በመኖሩ ይህ ዉሑፍ የሀገራትን ተሞክሮ

---

[2] Black’s Law Dictionary, 8th edition, Bryan A. Garner, THOMSON WEST Business,(1999)

[3] Global Rights Compliance (GRC), trials in absentia, ገፅ 2; available at: https://www.globalrightscompliance.com; accessed on: August 9/2019; see also Timothy T. Tucker, what are the criteria for trials in absentia in civil law systems?, Yugoslavia war crimes project, presented to professor Michael Scharf, ገፅ 2

[4] Mohammad Hadi Zakerhossein and Anne-Marie De Brouwer, Diverse Approaches to Total and Partial in Absentia Trials by International Criminal Tribunals, Criminal Law Forum (2015), ገፅ 183, available: http://creativecommons.org/licenses/by/4.0, accessed፡ August 9/2019

[5] Elizabeta Ivicevic Karas, Reopening of Proceedings in Cases of Trial *in absentia*: European Legal Standards and Croatian Law, EU And Comparative Law Issues and Challenges Series (ECLIC), Vol 2 (2018), ገፅ 292; available: https://hrcak.srce.hr/eclic/article/view, accessed: August 9/2019

በዝርዝር የሚመለከት አይሆንም። ቢሆንም በመርህ ደረጃ የተወሰዱ መመዘኛዎችን ከሀገራችን የህግ ማዕቀፍና ልምድ ጋር በማገናዘብ ተመርምሯል። የፁሁፉን ይዘት ለመመጠን ሲባልም የአለም አቀፍ እና አህጉራት ተሞክሮ በአንድ ክፍል እንዲዋቀር ተደርጓል።

ስለሆነም ፁሑፉ ሁለት ዋና ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያዉ አለም አቀፍ ህግጋት እና ተሞክሮዎችን ይዳስሳል፤ ሁለተኛዉ ክፍል የሀገራችን ህግጋትን (National laws) ይተነትናል። በመጀመሪያዉ ክፍል አለም አቀፍ ህግጋት እና በዓለም አቀፉ የወንጀለኞች ፍ/ቤት፣ በሰብዓዊ መብት ኮሚቴ፣ በአዉሮፓ ሰብዓዊ መብት ፍ/ቤት እና በአፍሪካ ሰብዓዊ መብት ፍ/ቤት ያለዉን ልምድ የሚዘረዝር ሲሆን በሁለተኛዉ ክፍል ዉስጥ ደግሞ በኢትዮጵያ ህግጋት ክርክሩ በሌለበት የሚታይበትን ሁኔታ፣ የሚታዩ የወንጀል ዓይነቶችን፣ በሌለበት የተሰጠ ፍርድ ስለሚነሳበት እና ዉድቅ ስለሚደረግበት ምክንያት የይግባኝ መብትን ጨምሮ የሚያብራራ ሲሆን በመጨረሻም የማጠቃለያ ሃሳብ በማቅረብ ይቋጫል።

2. ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክርክር ሂደት በአለም አቀፍ ህግጋት እና የአለም አቀፍ ተቋማት ተሞክሮ

2.1 ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክርክር በአለም አቀፍ ህግጋት እና የህግ ስርዓት

ፍትሀዊ በሆነ የክርክር ሂደት የመዳኘት መብት በአለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ህግጋት ህግ (norm) ሆኖ ተደንግጎ ይገኛል።[6] በወንጀል የክርክር ሂደት የተከሳሽ የክርክር ፍትሀዊነት መብት በአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች በግልፅ ጥበቃ ተደርጎለት የሚገኝ መብት ነዉ። በአለም አቀፍ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ስምምነት (ICCPR)[7] አንቀፅ 14፣ በአዉሮፓ የነፃነትና ሰብዓዊ መብት ጥበቃ ስምምነት (ECPHR)[8] አንቀፅ 6 እና በአፍሪካ ቻርተር (ACPHR)[9] አንቀፅ 7 የተደነገጉትን ማየት ይቻላል። በአለም አቀፍ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀፅ 14(c & d) እንደተገለፀዉ የተከሳሽ በክርክር የመገኘት

[6] Lawyers Committee for Human Rights, What Is A Fair Trial?, A Basic Guide to Legal Standards and Practice, New York, March 2000, ገፅ 29, available at: www.lchr.org, accessed on August 26/2017 for instance ICCPR, African Charter, American Convention, European Convention, Torture Convention can be mentioned.

[7] International Covenant on Civil and Political Rights, 16 December 1966, entered in to force on (1976).

[8] European Convention for the Protection of Human Rights and Fundamental Freedoms (1950), entered in to force on sept. 1953.

[9] African Charter on Human and Peoples' Rights, adopted 27 June 1981, entered into force 21 October 1986.

መብት በግልፅ ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በመርህ ደረጃ ተከሳሽ በሌለበት ክርክር እንደማይደረግ ይገልፃል።[10]

ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክርክር የተለመደዉ በአብዛኛዉ በሲቪል ሎዉ ስርዓት ተከታይ ሀገራት ሆኖ የኢንኩዚቶሪያል የሙግት ስርዓት በሚከተሉት ሀገራት ነዉ።[11] ይህ ማለት ግን ሁሉም የሲቪል ሎዉ ተከታይ ሀገራት ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክርክርን ፈቃጅ ናቸዉ ማለት አይደለም።[12] በአብዛኛዉ ሀገራት ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክርክርን ለመፍቀድ በሀገራቱ ብሔራዊ ህግጋት ላይ የተመሰረተ ሆኖ እንደወንጀሉ ዓይነት የሚለያይ ይሆናል።[13] ለምሳሌ የፈረንሳይን ልምድ ስንመለከት ለከባድ ወንጀሎች (felony crimes) ክርክሩ ተከሳሽ በሌለበት የሚታይ መሆኑን የወንጀለኛ መቅጫ ህጉ የሚፈቅድ ሲሆን ተከሳሽ በተያዘ ጊዜ ግን ክርክሩ እንደገና የማሰማት መብት አለዉ።[14] በሌላ በኩል በጀርመን፣ በኦስትሪያ እና በስፔን ተከሳሽ በሌለበት ማንኛዉም ከባድ ወንጀል ክርክር እንዲታይ የተፈቀደ አይደለም።[15]

ከዚህ በተለዬ በኮመን ሎዉ የህግ ስርዓት ተከታይ ሀገራት ተከሳሽ በሌለበት ክርክርን ማየት የህግ ስርዓታቸዉ አካል ሆኖ አይስተዋልም።[16] በእርግጥ በእነዚህ የህግ ስርዓት ተከታይ ሀገራትም በብሔራዊ ህግጋታቸዉ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ በየሀገራቱ ልዩነት አለ።[17] የእንግሊዝን ስርዓት ስንመለከት ክርክሩ በከባድ ወንጀል በሆነ ጊዜ ተከሳሽ በሌለበት

---

[10] Alexander Schwarz 'The legacy of the *Kenyatta* case: Trials *in absentia* at the International Criminal Court and their compatibility with human rights' (2016) 16, *African Human Rights Law Journal* 99-116, ገፅ 102-03, available at: http://dx.doi.org/10.17159/1996_2096/2016/v16n1a5, accessed on፡ August 8/2017

[11] ዝኒ ከማሁ፣ በአብዛኛዉ የኢንኩዚቶሪያል ሙግት ስርዓት ተከታይ ሀገራት ተከሳሽ በሌለበት ክርክሩን መፍቀዳቸዉ በእነዚህ ሀገራት ዳኞች በክርክሩ ያላቸዉ ተሳትፎ ከፍተኛ (active participants) ስለሆነ እዉነታን በመፈለግ ረገድ ጥረት ስለሚያደርጉ የተከሳሽ የመከላከል መብት አይጎዳም የሚል እሳቤ በመያዝ ይመስላል።

[12] Anne Klerks, Trials in absentia in international (criminal) law Tilburg University, LLM International and European Public Law Master Thesis -June 2008-ANR: 908200, ገፅ 10, https://arno.uvt.nl/show; accessed: August 9/2019

[13] ዝኒ ከማሁ

[14] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 10

[15] Jean Pardel, Droit Penal Compare, Dalloz, Paris 1995, ገፅ 525 & 526 in Council of Europe, European Committee on Crime Problems, Committee of Experts on the Operation of European Convention in the Penal Field, Judgmente in Absentia, directorate of legal affairs, Strasbourg, 3 March 1998, pc-oc(98)7 እንዲሁም ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 3፣ በጀርመን ተከሳሽ በሌለበት የሚታየዉ የእስራት ቅጣት በማያስከትሉ ወንጀሎች ሲሆን በተከሳሹ ፈቃድ (waiver to present) ክርክሩ በሌለበት የሚታየዉ ቅጣታቸዉ ከስድስት ወራት እስራት በታች በሆኑ ወንጀሎች ብቻ ነዉ (section 231 & 233 German criminal procedure) (1987); በኦስትሪያ ደግሞ ተከሳሽ በሌለበት በታዬ ክርክር የሚወሰነዉ ከፍተኛ ቅጣት እስከ ሦስት ዓመት ብቻ ነዉ (section 427 of the Austria criminal procedure).

[16] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 12፣ ገፅ 10

[17] ዝኒ ከማሁ

እንዲታይ አይፈቅድም።[18] በአሜሪካ የፌደራል ፍ/ቤቶችን ስንመለከት ደግሞ በተመሳሳይ የተከሳሽን በክርክር መገኘት ግዴታ የሚጥል ሲሆን በፌደራል ወንጀል ስነ-ስርዓት ደንብ ቁጥር 43 የወንጀል ክርክሩ ከተጀመረ በኋላ ከሆነ ግን በተከሳሹ ፈቃድ በክርክሩ የመገኘት መብቱን በመተዉ (waive) በማድረግ ከሆነ ይፈቅዳል።[19]

በእርግጥ የተከሳሽ በክርክር የመገኘት መብት እና በክርክር የመገኘት ግዴታ ተለያይተዉ መታየት ያለባቸዉ ጉዳዮች ሲሆኑ የመገኘት ግዴታ ፍ/ቤቶች እዉነታን በመፈለግ ረገድ አላማቸዉን እንዲያሳኩ የሚጠቀሙበትን ሂደት የሚመለከት ነዉ።[20] ተከሳሽ በክርክሩ ሂደት መገኘት መብት አለዉ ሲባል የመገኘት መብቱ ተቃራኒ የሚመስል ነገር ግን ለተከሳሹ መብት መከበር አስፈላጊ የሆነዉን ተደራቢ ቅድመ-ሁኔታ "የመገኘት ግዴታ" የያዘ ነዉ።[21] ከዚህ አኳያ መብት ስንልም በባለመብቱ ነፃ ፍላጎት ላይ ብቻ ተመስርቶ የሚፈፀም በመሆኑ በወንጀል የተከሰሰ ሰዉ ይህን መብቱን በመጠቀም ፍ/ቤት መቅረብ አልፈልግም በማለት ብቻ እንደፈለገ ከክርክሩ ዉጭ መሆን የማይችል ሲሆን በክርክር የመገኘት መብት የተከሳሽን የመቅረብ ግዴታ ጨምሮ የያዘ በመሆኑ ይህን ግዴታ ካልተወጣ ክርክሩ በሌለበት እንዲታይ ተደርጎ ቅጣት የሚወሰንበት ይሆናል።[22] የአሜሪካ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የአዉሮፓ ሰብዓዊ መብት ፍ/ቤት በተመሳሳይ ሁኔታ የተከሳሽ በፍትሃዊ የክርክር ሂደት የመዳኘት መብት የሚከበረዉ ተከሳሽ ራሱ በቀረበ ጊዜ ሆኖ በምስክሮች መሰማት ሂደትም የተከሳሽን መ·ግት ጭምር በአካል በመስማት ይሆናል ብለዉ ያምናሉ።[23]

ስለዚህ የተከሳሽ በክርክር የመገኘት ግዴታ እዉነታን ከመፈለግ በተጨማሪ ሀገራት ፍትህን ከማጓደል (obstruction of justice) ይከላከላል ብለዉ ያምናሉ።[24] ምክንያቱም በተከሳሽ አለመቅረብ የክስ ሂደቱ ከዘገየ የማስረጃ መጥፋት፣ የክስ ይርጋ ጊዜ ማለፍ እና በዘገዬ የክርክር ሂደት ምክንያት የፍትህ መጓደልን ያስከትላል ተብሎ ስለሚታመን ነዉ።[25] የወንጀል ክርክር ሂደት መዘግየት በሲቪል ሎዉ ሀገራት የበለጠ ትኩረት የሚሰጠዉ ሲሆን

---

[18] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 3፣ በደ/አፍሪካ ተከሳሽ በሌለበት ክርክር የሚታይበት ብቸኛዉ ሁኔታ በተከሳሹ የሥነ-ምግባር ችግር ችሎት እንዳይቀርብ ከተከለከለና በጠበቃ የመወከል መብቱ የተከበረ ከሆነ ብቻ ነዉ (የህገ መንግስቱ አንቀፅ 37)።

[19] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 12፣ ገፅ 10

[20] Maggie Gardner, Reconsidering Trials In Absentia At The Special Tribunal For Lebanon: An Application Of The Tribunal's Early Jurisprudence, The Geo. Wash. Int'l L. Rev., (Vol. 43 2011), ገፅ 100

[21] Wheeler, Caleb H. (2017), Right or duty? Is presence at trial a right or a duty in international criminal law? Criminal Law Forum, 28 (1), pp. 99-127. ISSN 1046-8374, Middlesex University Research Repository, available at: http://eprints.mdx.ac.uk/23560/, accessed: August 9/2019

[22] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 20

[23] ዝኒ ከማሁ

[24] ዝኒ ከማሁ

[25] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 101

ምክንያቱ ደግሞ የወንጀል ክርክር ከፍተኛ የማህበረሰብ መሳሪያ ሆኖ ለህዝብ መረጋጋት (public order) የሚያስጠብቅ ነዉ ተብሎ ስለሚታመን መሆኑ ይገለፃል።[26]

እስካሁን ባለዉ ልምድ ተከሳሽ የመገኘት መብቱን ቢተወዉ በክርክር ሂደት ባለመገኘት በፍ/ቤቶችም ሆነ በህግ አዉጭዎች የሚጣል ቅጣት የተለመደ ባይሆንም በአሜሪካ ፍ/ቤቶች ለጠፉ ተከሳሽ ህጋዊ መብቱን መከልከል (fugitive disenfranchisement) ይገባል የሚል ፍልስፍና ያላቸዉ ሲሆን ይህም ተከሳሹ በክርክር ሂደት ከጠፉ እና በቁጥጥር ስር ካልዋለ ፍ/ቤቶች የተከሳሹን ይግባኝ እስከ መሰረዝ ስልጣን የሚሰጥ አሰራር ነዉ።[27] ይህ ፍልስፍና (Doctrine) የተከሳሽን መጥፋትና የፍትህን መጓደል ለመከላከል አላማ ሲባል ምክንያታዊ የሆነ ቅጣት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነዉ።[28]

እንዲሁም አንዳንድ ሀገራት ሙሉ የክርክር ሂደቱን ተከሳሽ በሌለበት ማየት ከክርክር ለመሸሽ የሚጠፉ ተከሳሽን ለመከላከል (deterance) ህጋዊ መሳሪያ አድርገዉ ይጠቀሙበታል።[29] በአንዳንድ የሲቪል ሎዉ ሀገራትም ተከሳሽ በሌለበት ክርክር "*proces par contumace*" (trial in the absent) የሚተገበረዉ በክርክሩ ለሚቀሩ ተከሳሾች የመብት ገደብ በመጣል ለምሳሌ በጠበቃ የመወከል መብቱን በመንፈግ እና ከተቀጣም ማህበራዊ መብቱን (civil rights) የማሳጣት ዉሳኔ በመወሰን ሲሆን ይህም እንደ መቀጣጫ ያገለግላል ተብሎ የሚታሰብ ነዉ።[30]

ይሁን እንጅ ካለፉት 25 ዓመታት ጀምሮ የአዉሮፓ ሰብዓዊ መብት ፍ/ቤት በአባል ሀገራት ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክርክርን በተመለከተ የአሰራር መርሁን በመለወጥ እንደ ቅጣት መሰረት ካደረገ ፅንሰ-ሀሳብ (paradigm) ወደ መብትን መሰረት ወደ አደረግ እይታ (approach) ለዉጧል።[31] በዚህ ምክንያት "*Proces par contumace"* የሚለዉ አስተሳሰብ ወደ "*process par defaut"* (trial in absentia by accused default) የተተካ ሲሆን ይህም የተከሳሽን መብት በመቀጣጫነት አያጣብብም ተብሎ ይታሰባል።[32] የዚህ ፅንሰ ሀሳብ ይዘትም የሚጠፉ ተከሳሾች የፍርድ ሂደቱን እንዳይጎዱት ለመከላከል ሲባል ክርክርን ተከሳሽ በሌለበት ማየት የተፈቀደ ቢሆንም የዚህ አይነት የመብት ገደብ ተመጣጣኝና የተከሳሹን

[26] ዝኒ ከማሁ
[27] ዝኒ ከማሁ
[28] ዝኒ ከማሁ
[29] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 102
[30] ዝኒ ከማሁ
[31] ዝኒ ከማሁ፣ as Maggie noted "France, for example, amended its code of criminal procedure in 2004 to end its use of 'proces par contumace', following repeated criticisms by the European Court of Human Rights (ECHR)."
[32] ዝኒ ከማሁ

መሰረታዊ መብት በማይጥስ ደረጃ ሊተገበር ይገባዋል የሚል ነዉ።[33] ይህም ክርክሩን በሌለበት ከማየት ባለፈ በጠበቃ የመወከል መብትንም ሆነ ሌላ የመብት ገደብን ለምሳሌ የይግባኝ መብትን በመከልከል ገደብ መጣል ተገቢ አለመሆኑን የሚያስገነዝብ ነዉ።[34]

ሲጠቃለልም ተከሳሽ ባለበት የክርክር ሂደት ለተከሳሽ እንደ መብት እና ግዴታ በመሆን (over-laping) የሚያገለግል ፅንሰ-ሀሳብ ሲሆን አንዳንድ ሀገራትም ምንም ቀርቦ በማያዉቅ ተከሳሽም ቢሆን ክርክሩን በሌለበት ያስቀጥላሉ።[35] ይህ ዓይነት ተከሳሽ በሌለበት የክርክር ሂደት በአለምአቀፍ ህግ ተቀባይነት ያለዉ ስርዓት ቢሆንም መሰረታዊ የሆኑ የስነ-ስርዓት ገደቦችን ግን ያስቀምጣሉ።[36] እነዚህን በአለም አቀፍ ህግጋትና ተሞክሮ ደንብ የሆኑ አንድን የወንጀል ክርክር ተከሳሽ በሌለበት ለማየት ሊሟሉ የሚገባቸዉን ቅድመ-ሁኔታዎች ቀጥሎ እንመለከታለን።

2.2 ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክርክር የአለም አቀፍ ተቋማት ተሞክሮ (case law)

2.2.1 የአለም አቀፍ ወንጀለኞች ፍ/ቤት ተሞክሮ

ተከሳሽ በሌለበት ክርክሩ የሚታየዉ በማናቸዉም ጊዜ በክርክሩ ካልተገኘ እና ይህ የሆነዉም ተከሳሹ በመጥፋቱ (fugitive) ከሆነ ወይም በመታሰሩ እና ተላልፎ ባለመሰጠቱ ከሆነ ሲሆን እነዚህ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ተከሳሽ በመጀመሪያዉ ሂደት ተገኝቶ በኋላ ግን አቋርጦ በጠፋ ጊዜም የሚፈፀሙ ናቸዉ።[37] ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክርክር በአለም አቀፉ የወንጀለኞች ፍ/ቤት (International Criminal Court)[38] ደንብ (statutes) ወጥ የሆነ አቋም የለም።[39] በአለም አቀፍ የወንጀለኞች ፍ/ቤት በኑሪምበርግ በተደረገዉ ተከሳሽ በሌለበት ክርክር በተሰጠ የሞት ፍርድ መነሻነት ከዚህ በኋላ በነበሩ የአለም አቀፍ ወንጀለኞች ፍ/ቤት (ለምሳሌ የዩጎዝላቢያ፣ ሩዋንዳ፣ ሴራሊዮን) ተከሳሽ በሌለበት የሚደረግ ክርክር የተከሰሱ ሰዎች ካላቸዉ ፍትሃዊ የክርክር መብት (fair trial rights) ጋር የማይጣጣም ነዉ በሚል

---

[33] ዝኒ ከማሁ

[34] Stefan Trechsel, Human Rights in Criminal Proceedings, Oxford University Press, 2005, ገፅ 255፣ ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5 እንደተገለፀዉ

[35] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 20

[36] ዝኒ ከማሁ

[37] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 10፣ ገፅ 102

[38] The Rome Statute of the International Criminal Court (Rome Statute), U.N. Doc. A/CONF.183/9, July 17, 1998, entered into force July 1, 2002. Art. 5 (1) provides that the jurisdiction of the Court shall be limited to the most serious crimes of concern to the international community as a whole. The Court has jurisdiction with respect to the crimes of genocide, Crimes against humanity, War crimes and crime of aggression.

[39] ከላይ ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 10፣ ገፅ 103

ሳይፈቀድ የቆዬ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሊባኖስ በተቋቋመዉ ፍ/ቤት ተከሳሾች ክፍትህ እንዳያመልጡ ለመከላከል በሚል ምክንያት ክርክሩ ተከሳሽ በሌለበት እንዲታይ ፈቅዷል።[40]

ይህ የሊባኖስ አለም አቀፍ የወንጀለኞች ፍ/ቤት በዚህ አቋሙ ሰፊ ትችት ቀርቦበታል።[41] በልዩ ፍ/ቤቱ ደንብ ተከሳሽ በሌለበት የሚታየዉ ተከሳሹ ፈቅዶ በፁሁፍ መብቱን ሲተዉ እና ተላልፎ ሳይሰጥ ሲቀር ብቻ ሳይሆን በመጥፋቱ ወይም በሌላ ማንኛዉም ምክንያት ሳይገኝ ሲቀር ሆኖ ፍ/ቤቱ እንዲቀርብ የሚቻለዉን ጥረት አድርጎ እና መከሰሱን እንዲያዉቀዉ ተደርጎ ካልቀረበ ነዉ።[42] በሊባኖስ ልዩ ፍ/ቤት ደንብ አንቀፅ 22(3) እንደተገለፀዉ በሌለበት የጥፋተኝነት ፍርድ ከተሰጠ ተከሳሹ በቀረበ ጊዜ ክርክሩ እንዲታይለት የማድረግ መብት ያለዉ መሆኑን ይደነግጋል።[43]

በአለም አቀፍ ወንጀለኞች ፍ/ቤት ተከሳሽ በሌለበት ክርክር ሊታይ እንደማይገባ የሚከለከል ሲሆን በሌለበት ሊታይ የሚችለዉ በልዩ ሁኔታ ክርክሩን ተከሳሽ ባለበት ለማስቀጠል የማያስችል ምክንያት ከገጠመ ብቻ መሆኑን የአዋጁ አንቀፅ 63 (Article 63 of the Rome Statute for the ICC) ይደነግጋል።[44] ድንጋጌዉ ተከታዩን ያስነብባል።

> "Article 63፡ Trial in the presence of the accused
>
> (1) The accused shall be present during the trial.
>
> (2) If the accused, being present before the Court, continues to disrupt the trial, the Trial Chamber may remove the accused and shall make provision for him or her to observe the trial and instruct counsel from outside the courtroom, through the use of communications technology, if required. Such measures shall be taken only in exceptional circumstances after other reasonable alternatives have proved inadequate, and only for such duration as is strictly required."

---

[40] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 4፣ ገፅ 182

[41] P Gaeta, to be present or not tobe present: trial in absentia before the special tribunal of Lebanon (STL) (2007)5 Journal of International Criminal Justice, ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 10 እንደተገለፀዉ፣ ገፅ 10

[42] ICC, in art 22(1.c) of the statuate of the special tribunal for Lebanon, 30 May 2007, un-dc s/res/1757/ (2007)

[43] ዝኒ ከማሁ

[44] Rome Statute of the International Criminal Court (Rome Statute), U.N. Doc. A/CONF.183/9, July 17, 1998, entered into force July 1, 2002; see also Human rights wacth, letter Camdbodia-HRW-ECCC Rules on areas of trials in absentia, the independent of defense offece and the victims unit, and the public nature of the proceedings, Nov. 17/2006, www.hrw.org, accessed on፡ July 10/2017.

ስለሆነም ከዚህ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለዉ በተከሳሹ አዋኪ ባህሪ (በስነ-ምግባር ችግር) ክርክሩን ለመምራት የማይቻል ከሆነ ፍ/ቤቱ ተከሳሹን በጠበቃዉ አማካኝነት በዉጭ ሆኖ እንዲከታተል ሊያደርግ እንደሚችል እና ይህም የመጨረሻ አማራጭ ሆኖ ከተገኘ ብቻ እንጅ ተከሳሽ በክርክሩ የመገኘት ግዴታ ያለበት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡

ስለዚህ በዚህ ፍ/ቤት ተከሳሹ ክርክሩን ትቸዋለሁ (waive) በማለቱ ከክርክሩ ዉጭ በማድረግ የክርክሩን ሂደት በሌለበት ማየት የማይገባ መሆኑን ያስረዳል፡፡

2.2.2 የአለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ኮሚቴ ተሞክሮ

በሰብዓዊ መብት ኮሚቴ (Human Rights Committee)[45] ትርጉም እንደተሰጠበት ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክርክር የሚፈቀደዉ በህጋዊ ምክንያት (justified reasons) በልዩ ሁኔታ (exceptionally) ሆኖ አስቀድሞ የተከሳሽ በጠበቃ የመወከል መብት ሲከበር ነዉ፡፡[46] ኮሚቴዉ በዉሳኔዉ ተከሳሽ በሌለበት ክርክር እንዲታይ የተፈቀደ ቢሆንም ይህ የሚሆነዉ በልዩ ሁኔታ ብቻ ነዉ በማለት አብራርቷል፡፡[47] እንደ ኮሚቴዉ ማብራሪያ ተከሳሽ በሌለበት ማየት የሚቻለዉ ለፍትህ ጥቅም ሲባል ቢሆንም ተከሳሹ ስለ ክሱ እና ክርክሩ ሂደት እዉቅና እንዲኖረዉ ለማድረግ ፍ/ቤቱ ሁሉንም የማሳወቂያ ሂደቶች በመጠቀም የማሳወቅ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ተከሳሽ በክርክሩ የመገኘት መብቱን በግልፅ የተወ ሆኖ ሲገኝ ግን በራሱ ክርክሩን በመተዉ (waive) ምክንያት በሌለበት ሊታይ ይችላል ብሏል፡፡[48] ይህ የመተዉ መብት ኮሚቴዉ በማለኪ እና ጣሊያን[49] በነበረዉ ክርክር እንደተረጎመዉ ተገቢ የሚሆነዉ ፍ/ቤት የራሱን ግዴታ በተለይ ተከሳሹ መከሰሱን እንዲያዉቀዉ ጥሪ አድርጎ እና መጥሪያዉ የደረሰዉ መሆኑ የተረጋገጠ በሆነ ጊዜ ብቻ እንደሆነ ነዉ፡፡

ሀገራት ተከሳሽ በሌለበት ክርክሩን ሊመለከቱ የሚችሉ ቢሆንም ይህ የሚቻለዉ በቅድሚያ ለተከሳሽ በቂ ጊዜ በመስጠት በአግባቡ መጥሪያ ተሰጥቶት ለክርክሩ እንዲቀርብ የችሎቱ ጊዜና ቦታ ተገልፆ የተጠራ መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡[50] እንደ ኮሚቴዉ አቋም ይህ ስነ-ስርዓት ሳይከናወን መቅረት የአንድን ተከሳሽ በክርክር ተገኝቶ የመሰማት መብት ሆኖ በአለም አቀፍ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀፅ 14 የተገለፀዉን የሚጥስ እና ስለክሱ

---

[45] The human rights committee (HRC) is an independent body that moniters compliance on state parties with obligations under ICCPR.

[46] HRC, general comment no.13, art 14, 13 April 1984, UN-DOC HRI/GEN/1/Rev1 (1984) para.11

[47] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9፣ ገፅ 105

[48] HRC, Mbenge v. Zaire, communication no. 16/1977, U.N. Doc. CCPR/C/OP/2 (Mar. 25/ 1983), available: www.worldcourts.com/eng/decisions, accessed: August19/2019.

[49] HRC, Maleki v. Italy, communication no. 699/1996, 27 July 1999, UN-Doc.CCPR/C/66/D/699/1996, available: www.worldcourts.com/eng/decisions, accessed: August 19/2019.

[50] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 20፣ ገፅ 103

የሚያስረዳ የተከሳሽ ጠበቃ ቢኖር እንኳን ይህን የመሰማት መብቱን ሊክስለት የማይችል መሆኑን ነዉ::[51]

ተከሳሽ በሌለበት ክርክሩ የቀጠለዉ ተከሳሹ የመገኘት መብቱን በመተዉ (waive) ምክንያት በሆነ ጊዜ ግን በክርክር የመገኘት መብት ሊታይ የሚገባዉ ከተከሳሽ የመሰማት መብት አንፃር ብቻ ሳይሆን ከተጎጅዎችና ከምስክሮች እንዲሁም ከጠቅላላዉ ማህበረሰብ ጥቅምና ፍላጎት አኳያ ጭምር ሆኖ ወንጀለኞችን ከማስተማር፣ ከማረም፣ ለይቶ ከማስቀመጥ እንዲሁም ተከታታይነት ያላቸዉን ወንጀሎች ከማስቀረት (ከመከላከል) አኳያ ተከሳሽን ባለበት ማከራከር ቅድመ-ሁኔታ ሆኖ ይህን የማህበረሰቡን የጋራ ቀዉስ ማስወገድ በሚቻልበት አግባብ መሆን አለበት::[52]

የወንጀል ክስ ጉዳይ ዐ/ህግንና ተከሳሽን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን የወንጀል ሰለባዎችንም የሚመለከት ሆኖ እዉነትን በመፈለግ ፍትህን የማረጋገጥ ጉዳይ ጭምር በመሆኑ ከዚህ አኳያም ማየት ይገባል::[53] ይህ ህጋዊ የማህበረሰብ ጥቅም በዋናነት የሚገለፀዉና የሚረጋገጠዉ ደግሞ የተከሰሰ ሰዉ በወንጀል ክርክር ሂደት በፍ/ቤት እየቀረበ ሲከታተል በመሆኑ የራሱን የተከሳሹን መብት፣ የተጎጅዎችን እና የምስክሮችንም ፍላጎት እንዲሁም ጥቅም የሚያስጠብቅ ይሆናል ተብሎ ይታመናል::[54] ስለሆነም በልዩ ሁኔታ ተከሳሽ በሌለበት የሚታየዉ ክርክር የተከሳሽ መቅረብ የማይቻል ሲሆን በጠባቡ የሚፈፀም መሆኑን ያመለክታል::

2.2.3 የአዉሮፓ የሰብዓዊ መብት ፍ/ቤት ተሞክሮ

የአዉሮፓ የሰብዓዊ መብት ኮንቬንሽን ተከሳሽ በክርክር መገኘት ያለበት መሆኑን የሚገልፅ ድንጋጌ ባይኖረዉም የአዉሮፓ ሰብዓዊ መብት ፍ/ቤት የተከሳሽ በክርክር ሂደት መገኘት የፍትህዊ ክርክር ሂደት አንዱ መመዘኛ መሆኑን ይገልፃል::[55] ስለሆነም ፍ/ቤቱ በኮሎዛ እና ጣሊያን[56] በቀረበለት ጉዳይ የኮንቬንሽኑ አንቀፅ 6(3 c) ራስን የመከላከል መብት እንዲሁም በአንቀፅ 6(3 d) ምስክሮችን የመጠየቅ መብት ተፈፃሚ የሚሆኑት ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት

---

[51] HRC, General Comment no. 32, art 14, 23 August 2007, UN-Doc CCPR/C/GC/32, para. 36

[52] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 10፣ ገፅ 114

[53] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 115

[54] ዝኒ ከማሁ

[55] ECHR, the convention under art 6(3) provides constitutive elements of a fair trial principle in art 6(1).

[56] ECHR, *Colozza v. Italy* 9024/80 12 February 1985፤ ኮሎዛ በተከሰሰበት የማታለል ወንጀል መኖሪያ አድራሻዉን ቀይሯል በሚል ምክንያት ከፍትህ ለመሸሽ ነዉ ተብሎ በሌለበት 6 ዓመት ተፈርዶበት ተከሳሹ ከፍርድ በኋላ ከቤቱ ተይዞ በእስር ላይ እንዳለ ህይወቱ አልፏል፤ ይህን ተከትሎ ሚስቱ በበኩሏ የጉዳት ካሳ የሚገባት ተጎጅ መሆኗን ፍ/ቤቱ ወስኖ በሌለበት የተፈረደዉ ፍርድ መከሰሱን ስለማወቁ የማያረጋግጥ እንዲሁም በሌለበት ለማየት በሚያበቃ ምክንያት ስለመታየቱ ስለማያስረዳ የኮንቬንሽኑን አንቀፅ 6(1) የጣሰ ነዉ በሚል ስድስት ሚሊዮን ሊሬ መንግስት እንዲከፍላት ወስኗል::

ፍ/ቤት ቀርቦ ከተከራከረ ነዉ በሚል ትርጉም ሰጥቷል።[57] ይህ ቢሆንም ተከሳሽ በሌለበት ክርክሩን መምራት በኮንቬንሽኑ ያልተከለከለ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የተከሰሱ ሰዎችን መሰረታዊ መብት ለማክበር ሲባል ተከሳሽ በሌለበት ክርክሩን ለመምራት ሊሟሉ የሚገባቸዉን መመዘኛዎች የደነገገ ሲሆን በዚህ ዉሳኔ የተዘረዘሩ መመዘኛዎች የሚከተሉት ናቸዉ።[58]

- ተከሳሹ ክስ የቀረበበት ስለመሆኑ እና ክርክር ስለመኖሩ ሙሉ እዉቅና ተፈጥሮለት ከሆነ (በኮሎዛ እና ጣሊያን እንደወሰነዉ)፤
- ተከሳሹ በግልፅና በማያሻማ ሁኔታ (expressly and in unequivocal manner) በክርክሩ የመገኘት መብቱን የተወ ከሆነ፤[59]
- በህግ ባለሙያ የመወከል መብቱ በሌለበትም ቢሆን መብቱ የተከበረለት ከሆነ፤[60]
- የተከሳሹ በክርክር የመገኘት መብት በቀረበ በማንኛዉም ጊዜ ቢሆን ወደ ክርክሩ እንዲገባ መብት ሊሰጠዉና ምንም ዓይነት ገደብ ወይም መቀጫ ሊጣልበት የማይገባ ከሆነ ነዉ የሚል ነዉ።[61]

ስለሆነም የአዉሮፓ ፍ/ቤት በኢክባታኒ እና ስዊዲን[62] በቀረበለት ጉዳይ እነዚህን የማይነጣጠሉ ቅድመ-ሁኔታዎች በመጣስ በሌለበት ክርክሩ የታየበት ተከሳሽ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ ቢቀርብ ክርክሩ እንደገና ባለበት ሊታይለት የሚገባ መሆኑን የወሰነ ሲሆን ይህ ካልሆነ በሌለበት የተደረገዉ ክርክር ኮንቬንሽኑን የሚጥስ ነዉ ብሏል።[63]

---

[57] ዝኒ ከማሁ

[58] ECHR, *Colozza v. Italy* 9024/80 12 February 1985፤ also in Sanader v. Croatia, 66408/12, 12 February 2015, para.76-93.

[59] ECHR, Sejdovic v. Italy, App. No. 56581/00, 42 Eur. H.R. Rep. 17, para.14 (2004), available: https://hudoc.echr.coe.int, accessed on August 19/2019፤ ሴጆቪች በሮም አሲዜ ፍ/ቤት በቀረበበት የሰዉ መግደል ወንጀል ክስ ሚችን መግደሉን ምስክሮች አረጋግጠዋል እንዲሁም ተፈልጎ ሊገኝ ያልቻለዉ ከፍትህ ለማምለጥ ነዉ ተብሎ በሌለበት በተከላካይ ጠበቃ ፍ/ቤቱ እንዲወከል አድርጎ ጥፋተኛ በማድርግ በ21 ዓመት ከ8ወር እስራት እንዲቀጣ የተወሰነበት ሲሆን ተከሳሹ በጀርመን ሀምበርግ ከተማ ይገኛል በማለት የጣሊያን ዐ/ህግ ተላልፎ እንዲሰጠዉ የጠየቀ ሲሆን የጀርመን መንግስትም የጣሊያን ሀገር ህግ ተከሳሽ በሌለበት በተሰጠ ፍርድ ተነስቶለት እንደገና ባለበት እንዲከራከር ፈቃጅ ስለመሆኑ (የሚፈቀድለት ስለመሆኑ ማረጋገጫ የለኝም በሚል) አሳልፌ አልሰጥም በማለት ከታሰረበት እንዲፈታ አድርጓል፤ ይህን ጉዳይ ተከትሎ ተከሳሹ ባቀረበዉ አቤቱታ የቀረበለት የአዉሮፓ ሰብዓዊ መብት ፍ/ቤትም ተከሳሹ መከሰሱን ያወቅ ነበር በማለት የጣሊያን ፍ/ቤት ክርክሩ እንደገና ይታይልኝ የሚለዉን የተከሳሹን ጥያቄ ዉድቅ ያደረገዉ ስለመከሰሱ ማወቁን በበቂ ሁኔታ ስለማያረጋግጥ የኮንቬንሽኑን አንቀፅ 6 ይጥሳል ብሏል።

[60] ECHR, VanGeyseghem v. Belgium, 26/03/95, 21 Jan 1999፤ ዝኒ ከማሁ

[61] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 10፣ ገፅ 108

[62] ECHR, Ekbatani v. Sweden, communication no. 10563/83, 16 May 1988, para. 31, available: https://hudoc.echr.coe.int, accessed on August 19/2019

[63] ዝኒ ከማሁ

ተከሳሽ በሌለበት ክርክሩ ከታየ ግን ክርክሩ በሌለበት በመታየቱ ምክንያት በጠበቃ የመወከል መብትን የማያስቀር መሆኑን የአውሮፓ ሰብዓዊ መብት ፍ/ቤት ትርጉም ያስረዳል።[64] ከዚህ ተከታይ በሆነዉ ክፍል የአፍሪካ ሰብዓዊ መብት ፍ/ቤት ተሞክሮን እንቃኛለን።

2.2.4 የአፍሪካ ሰብዓዊ መብት ፍ/ቤት ተሞክሮ

በአፍሪካ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ መሰረት የሆነዉ የአፍሪካ ቻርተር ሲሆን በአንቀፅ 7 የተከሰሰን ሰዉ የመሰማት መብትና በጠበቃ የመወከል መብትን የሚደነግግ ቢሆንም በክርክር ሂደት የመገኘት መብትን በተመለከተ የሚናገረዉ የለም። ይሁን እንጅ ቻርተሩ በአንቀፅ 60 እንደገለፀዉ የአፍሪካ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የቻርተሩን አንቀፅ 7 ሲተረጉም ሌሎች አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነዶችን ዋቢ በማድረግ ሊሆን እንደሚገባ ይደነግጋል። ተከሳሽ በሌለበት የክርክር ሂደትን በተመለከተ የአፍሪካ ኮሚሽን የዳበረ ተሞክሮ አለዉ ማለት ባይቻልም በጠበቃ ጃን ፍሮንቴ እና ብሩንዲ በነበረ ክርክር የተከሳሽ የመከላከል መብት የተከሳሽን በየክርክሩ ሂደት የመገኘት እና የመከታተል መብትን የሚጠይቅ ስለመሆኑ ወስኗል።[65] በእርግጥ በዚህ ዉሳኔ ላይ ክርክሩ በሌለበት ቢታይ የሚወሰደዉ የማስተካከያ እርምጃ ምን እንደሚሆን አይገልፅም።[66] ቢሆንም ግን በአፍሪካ ቻርተር እና በሰብዓዊ መብት ኮሚቴ ዉሳኔ ያለዉን ክፍተት ለመሙላት የአፍሪካ ኮሚሽን በአፍሪካ ፍትሀዊ የሙግት ሂደት እና የህግ ድጋፍ መብት መርሆና የአሰራር መመሪያ (principles and guidelines) ዝርዝር ደንቦችን አዉጥቷል። እነዚህም፡-[67]

- ተከሳሽ በተከሰሰበት ጉዳይ የመቅረብ መብት ያለዉ ስለመሆኑ፤
- ተከሳሽ በሌለበት ሊታይ የማይገባ መሆኑን፤ በሌለበት ቢታይ መጥሪያ በአግባቡ ያልተሰጠዉ መሆኑን በማሳየት ክርክሩ እንደገና እንዲታይ የመጠየቅ መብት ያለዉ መሆኑን፤ መጥሪያዉ ለተከሳሽ ለራሱ ያልተሰጠዉ መሆኑን ወይም መቅረብ ያልቻለዉ ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን በማሳየት ክርክሩ ባለበት እንዲታይለት የማድረግ መብት ያለዉ መሆኑን፤
- ተከሳሽ በራሱ ፈቃድ በክርክሩ የመቅረብ መብቱን መተዉ የሚችል ሲሆን ይህ የመተዉ መብት በግልፅ እና በዉሁፍ ሆኖ ሊቀርብ እንደሚገባ ይገልፃል።

---

[64] ECHR, Krombach v. France, App. No. 29731/96 (2001), para. 73 and 89, as cited in Human Rigths Wacth, www.hrw.org, (November 17, 2006), para.6-7

[65] ECHR, Avocates Sans Frontieres (on behalf of Bwampamye) v Burundi (2000) AHRLR 48(ACHPR2000) para.27-29

[66] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 10፣ ገፅ 106

[67] Principles and Guidelines on the Right to a Fair Trial and Legal Assistance in Africa, Part N(6)(c),http://www.achpr.org/files/instruments/principlesguidelines-right-fair trial/achpr33_guide_fair_trial_legal_assistance_2003_eng, accessed: August9/2017

ይህ የአፍሪካ ኮሚሽን የፍትሀዊ የሙግት ሂደት መርሆ እና የአሰራር መመሪያ በክርክር የተከሳሽ የመገኘት መብትን በተመለከተ የተሻለ አስተዋፅዖ ባለዉ ደረጃ የገለፀ ሲሆን ከICCPR እና ECHR ሰነዶች ከተገለፀዉ ከፍ ባለ ሁኔታ ጥበቃ ማድረጉን ያሳያል።[68]

በሌላ በኩል የአፍሪካ ሰብዓዊ መብት ፍ/ቤት አስገዳጅ ዉሳኔ የሰጠ ሲሆን ህዳር 20/2015 በቶማስ እና ታንዛኒያ[69] በቀረበለት ክርክር የተከሳሽ የመገኘት መብት ተጥሶበታል ሲል ወስኗል። ፍ/ቤቱ በዉሳኔዉ እንደገለፀዉ ታንዛኒያ በቻርተሩ አንቀፅ 7(1 c) እና ICCPR አንቀፅ 14(3 d) የተደነገገዉን በህግ ስርዓት የመዳኘት መብት (due process) በመጣስ በሌለበት ታይቷል። ቶማስ ክርክሩ በይግባኝ እየታየ ባለበት ጊዜ በጠና ታሞ ሆስፒታል ገብቷል፤ የቀረበትን ምክንያት እንዲያስረዳ ሳይደረግ ቀርቷል፤ ፍ/ቤቱ የቻርተሩን አንቀፅ 7 ከICCPR አንቀፅ 14(3 d) ጋር በማጣመር ተመልክቶ በአንቀፅ 7(1 c) ተከሳሹ ክሱን እንዲከላከል የመገኘት መብት አለዉ፤ የወንጀሉ ከባድነትም ታይቶ የስር ፍ/ቤት በጤናዉ ሁኔታ የዋስትና መብት የሰጠዉ መሆኑ ሲታይ እና በጠበቃ ያልተወከለ መሆኑን በመገንዘብ ይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት ክሱን እንዲከላከል እድል በመስጠት ክርክሩን ሊሰማ ይገባዉ የነበረ በመሆኑ ከቻርተሩ አንቀፅ 7(1 c) አኳያ በጠበቃ የመወከል መብት ተጥሶበታል ብሎ ወስኗል።[70]

ስለሆነም ከዚህ ዉሳኔ የምንረዳዉ ተከሳሹ በክርክሩ ሂደት ባለመገኘቱ በሌለበት ቢታይ በጠበቃ የመወከል መብቱን ሊያጣ እንደማይገባ ነዉ። በቀጣዩ ክፍል በሀገራችን ህግጋት እና አሰራሮች ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክርክር የሚተገበርበት ሁኔታ ይቀርብበታል።

3. ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክርክር ሂደት የብሄራዊ ህጎች (National laws) ዳሰሳ

ተከሳሽ በሌለበት ክርክሮችን ለመምራት በቅድሚያ የተከሰሱ ሰዎች መብቶችን ማየት ያስፈልጋል። ይህ መብት በዚህ ዉሑፍ እንደተመለከትነዉ በተለያዩ አለም አቀፍ ስምምነቶችና ሰነዶች ተደንግጎ እናገኘዋለን። እንዲሁም በህገ መንግስታችን[71] በአንቀጽ 20 ተደንግጎ ይገኛል። የተከሰሱ ሰዎችን መብት በተመለከተ ህገ መንግስቱ በአንቀፅ 20(1) በመደበኛ ፍ/ቤት በግልፅ ችሎት የመሰማት መብት እንዳላቸዉ ይደነግጋል። የተከሰሱ ሰዎች የቀረበባቸዉን ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረበባቸዉን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸዉን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸዉ ቀርበዉ እንዲሰመላቸዉ የመጠየቅ መብት እንዳላቸዉ በአንቀፅ 20(4) ተደንግጓል። ይህን

[68] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 10፣ ገፅ 107
[69] AHRC, *Thomas v Tanzania* 005/2013, 20 November 2015
[70] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 10፣ ገፅ 107-108
[71] ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 1/1987፣ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አዋጅ፣ አንደኛ ዓመት ቁጥር 1፣ ነሃሴ 15/1987፣ አዲስ አበባ

ህገመንግስታዊ መብት ለመተግበር የተከሳሽን በፍ/ቤት ፊት መቅረብ (presence) የሚጠይቅ ሲሆን ፍ/ቤቶች እንዲቀርብ የማድረግ ሀላፊነት እንዳለባቸዉ ያስገነዝባል። ይህም ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸዉ አለምአቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀፅ 14(3 d) ጋር የተጣጣመ እንደሆነ ያመላክታል።

በእርግጥ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 9(4) መሰረት ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸዉ አለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ የህግ አካል ሲሆኑ መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶችን በተመለከተም በተግባራዊ አፈፃፀማቸዉም ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸዉ አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ህግጋት፣ አለምአቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነትና አለምአቀፍ ሰነዶች መርህዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ሊተረጎሙ እንደሚገባ አንቀፅ 13(1 እና 2) ይደነግጋል። ከዚህ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ የምንረዳዉ አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ህግጋትና አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች መርሆዎችን ከሀገራችን ህግጋት ጋር አጣጥሞ ትርጉም መስጠት ህገ መንግስታዊ ተግባር መሆኑን ነዉ። የአለም አቀፉ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ስምምነትን ኢትዮጵያ "[signed on 11 June 1993]" ተቀብላ ያፀደቀች መሆኑ ይታወቃል።

ይሁን እንጅ በዚሁ ኮንቬንሽን ማስፈፀሚያ ስነ-ስርዓት (protocol) በተደነገገዉ መሰረት የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ስምምነቱን በሚጥስ ደረጃ በደል ደርሶብኛል የሚል ግለሰብ (የግል ተበዳይ) (individual compliant) ለኮሚቴዉ አቤቱታ ለማቅረብ ሀገራቱ ከኮንቬንሽኑ በተጨማሪ ፕሮቶኮሉን በመቀበል (በማፅደቅ) አባል ስለመሆናቸዉ ቅድመ-ሁኔታ ይጠይቃል።[72] በመሆኑም ሀገራችን ኢትዮጵያ ይህን ፕሮቶኮል ያልተቀበለች (ያልፈረመች) በመሆኑ የኢትዮጵያ ዜጎች ለሰብዓዊ መብት ኮሚቴ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተፈፅሞብኛል ብለዉ አቤቱታ ማቅረብ እንደማይችሉ መገንዘብ ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል የህገ መንግስቱ አንቀፅ 13(1 እና 2) ድንጋጌ መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶችን በሚመለከት ኢትዮጵያ ካፀደቀቻቸዉ አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች (ስምምነቶች) በተጨማሪ አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነዶችንና መርሆዎችን አጣጥሞ ትርጉም መስጠት እንደሚገባ ያዛል።

ስለሆነም የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ኮሚቴ በተለያዩ ጉዳዮች የሚሰጣቸዉን ሰብዓዊ መብትን የሚመለከቱ ትርጓሜዎችን እና መርሆዎችን ከህጋችን ጋር በማጣጣም መተርጎም ህገ መንግስታዊ ኃላፊነት መሆኑን ማየት ይገባል።

---

[72] Article 1 of the protocol, Optional Protocol to the International Covenant on Civil and Political Rights; "…No communication shall be received by the Committee if it concerns a State Party to the Covenant which is not a party to the present Protocol."

በወንጀል የክርክር ሂደት ክርክሩ የሚመራበት መሰረታዊ ህጋችን የወ.መ.ሥ.ሥ.ህግ[73] ሲሆን በቁጥር 123 እንደተደነገገዉ ክሱ ለፍ/ቤት ሲቀርብ ፍ/ቤቱ ነገሩ የሚሰማበትን ቀን ወስኖ በተወሰነዉ ቀጠሮ ቀን እና ሰዓት ተከሳሽ እና ዐ/ህግ እንዲቀርቡ መጥሪያ ይሰጣል፡፡ ይህንን በማጠናከር የወንጀል ፍትህ ፖ/ሊሲዉም በወንጀል ጉዳይ ላይ የሚሰጡ አላስፈላጊ ቀጠሮዎችን ለመቀነስና የፍርድ ሂደቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ዐ/ህግ እና መርማሪ ፖ/ሶች በፍ/ቤት መጥሪያ መሰረት ተከሳሽና ምስክሮችን በችሎት እንዲቀርቡ የማድረግ ኃላፊነት የጣለ ሲሆን ፍ/ቤትም መገኘታቸውን ማረጋገጥ እንዳለበትና የህግ ማዕቀፎችም በዚሁ ይዘት መሻሻል እንዳለባቸዉ ይደነግጋል፡፡[74] ተከሳሹ ማረፊያ ቤት የሚገኝ ከሆነም እንዲቀርብ አስፈላጊዉን ማድረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በተቀጠረበት ቀን ተከሳሽ ካልቀረበ ወይም በቂ ምክንያት የሚሰጥለት እንደራሴ ያልቀረበ እንደሆነ ተከሳሽ እንዲያዝ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ እንደሚሰጥ የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ. 160(2) ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ 125 ተከሳሽ መጥሪያ ደርሶት ካልቀረበ በፖ/ሊስ ተይዞ እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ የመያዝ ትዕዛዝ መስጠት እንዳለበት ያዛል፡፡ የተከሳሽን የመያዝ ትዕዛዝ መፈፀም ካልተቻለ ነገሩ ተከሳሽ በሌለበት ስለሚሰማበት ሁኔታ ፍ/ቤቱ ያስብበታል በማለት የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ. 160(3) ይገልፃል፡፡

ይህም ክርክሩ በሌለበት እንዲታይ ከመደረጉ አስቀድሞ ተከሳሹ እንዲቀርብ ለማድረግ በፖ/ሊስ ተይዞ እንዲቀርብ የማሰሪያ ትዕዛዝ በመስጠት ጭምር ወደ ፍ/ቤት የማስቀረብ ጠንካራ ሂደት መኖሩን ያስገነዝባል፡፡ ስለዚህ የህጉ አላማ ተከሳሽ በክርክር እንዲገኝ ማድረግ በግዴታ መልክ መታየት ያለበት መሆኑን የሚያስገነዝብ ይዘት የያዘ ነዉ፡፡

ተከሳሽ በሌለበት ክሱ የሚሰማዉ በወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ. 161 በተገለፀዉ አግባብ ነዉ፡፡ ተከሳሽ ያለበቂ ምክንያት ነገሩ ሊሰማ በተቀጠረብት ቀን ሳይቀርብ ከቀረ ፍ/ቤቱ አለመቅረቡን በመዝገቡ በመፃፍ በሌለበት እንዲሰማ እንደሚያዝ የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ 161(1) ይገልፃል፡፡ ፍ/ቤቱ ተከሳሹ በሌለበት ነገሩ እንዲሰማ የሚያዘዉ በቀጠሮዉ ያለበቂ ምክንያት ከቀረ መሆኑን ይህ ድንጋጌ በግልፅ ያስረዳል፡፡ ነገር ግን ያለበቂ ምክንያት የቀረ ነዉ የሚባለዉ በምን ምክንያት እንደሆነ የተገለፀ ማሳያ ባለመኖሩ ግልፅነት የጎደለዉ አገላለፅ ነዉ፡፡ አንድ ተከሳሽ ያለበቂ ምክንያት ቀረ የምንለዉ የፍ/ቤቱ መጥሪያ በአግባቡ የደረሰዉ መሆኑ ተረጋግጦ ነገር ግን በቀጠሮዉ የቀረበት ምክንያት ሳይታወቅና ለፍ/ቤትም ችግሩን

[73] የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት፣ የ1954 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ፣ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 1/1954 በተለይ የወጣ፣ አዲስ አበባ፣ ጥቅምት 23 ቀን 1954 ዓ.ም

[74] የኢፌዲሪ የወንጀል ፍትህ ፖ/ሊሲ፣ ፍትህ ሚኒስቴር፣ የካቲት 25/2003 ዓ.ም፣ ክፍል 4.3.2፣ ገፅ 32፣ available at: http://ethcriminalawnetwork.com.

የሚያስረዳለት እንደራሴ ሳይልክ በቀረበት ሁኔታ ነዉ ሊባል ይችላል። ይህም ተከሳሹ ያለበት ሁኔታ በመጥሪያ አድራሹ አካል ምን ያህል ፍለጋና ጥረት ተደርጓል የሚለዉንም ሁኔታ ማረጋገጥ የሚጠይቅ ነዉ።

ፍ/ቤቱ ነገሩ ተከሳሽ በሌለበት እንዲሰማ ትዕዛዝ የሰጠ እንደሆነ ይህ ትዕዛዝ ተከሳሽ ከተከሰሰበት የወንጀል ዝርዝር ጋር ነገሩ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀን ተከሳሹ ባይቀርብ በሌለበት የሚፈረድ መሆኑን የሚገልፅ የመጥሪያ ማስታወቂያ በጋዜጣ እንዲወጣ ፍ/ቤቱ እንደሚያዝ የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ. 162(ሀ) ይደነግጋል። ለተከሳሽ የሚደርስ መስሎ ከታየዉ ፍ/ቤቱ መጥሪያዉ የሚደርስበትን ሌላ መንገድ ሊያዝ እንደሚችል የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ 162(ለ) ይደነግጋል። በንዑስ ቁጥር "ለ" የተደነገገዉ አማራጭ የመጥሪያ ስርዓት በእንግሊዘኛዉ ቅጅ የሌለ ተጨማሪ ድንጋጌ ሲሆን የአማርኛዉ ቅጅ በተግባራዊ አፈፃፀም የተሻለ ተደራሽነትን ሊፈጥር የሚችል ስለሚሆን የተሻለ ነዉ የሚል እምነት አለኝ። ይህም የጋዜጣ መጥራት አስገዳጅ ሳይሆን ተደራሽነቱንና የመጥሪያ አደራረሱን ቀላልነት በመገንዘብ የሚፈፀም እንዲሆን ያደርገዋል። ለምሳሌ አንድን ያልተማረ ተከሳሽ በሀገሪቱ በሚታተም ጋዜጣ እንዲጠራ ከማድረግ ይልቅ በቀበሌ ማስታወቂያ ዘመዶቹና የአካባቢዉ ማህበረሰብ በሚያዉቀዉ መንገድ መጥራቱ ተመራጭ ሊያደርገዉ ይችላል። በእርግጥ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህጉ ተከሳሽ እንዲቀርብ መጥራት አስፈላጊ መሆኑን ብቻ ይገልፃል እንጅ በምን ስርዓት (the means of the summons) እንደሚጠራ አይገልፅም።

ስለዚህ በወንጀል ክርክር መጥሪያ ደረሰ ሊባል የሚችለዉ ተከሳሹ መከሰሱን እንዲያዉቀዉ በማድረግ ፍ/ቤቱ የጠራዉ መሆኑ ከተረጋገጠ ነዉ ማለት ያስችላል። መጥሪያዉ በቀጥታ ለተከሳሽ ያልተሰጠ ከሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የሚሰጥ የመጥሪያ አደራረስ ለተከሳሹ ደርሶታል ለማለት በቂ ላይሆን ይችላል። በእርግጥ ይህ ሁኔታ በሌለሁበት የተሰጠዉ ፍርድ ይነሳልኝ የሚለዉ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ የሚታይ ሲሆን በአንቀፅ 199(ሀ) መሰረት "መጥሪያ ያልደረሰዉ ከሆነ" የሚለዉ የሚያስረዳዉ ፍ/ቤቱ ፍርዱን ዉድቅ ለማድረግ የሚወስደዉ መመዘኛ ክርክሩን በሌለበት ለማየት ከሚወስደዉ መመዘኛ የሚለይ እና ለመጀመሪያዉ መመዘኛ መጥሪያዉ ለተከሳሽ በቀጥታ ስለመድረሱ ማረጋገጥን የሚጠይቅ መሆኑን የድንጋጌዉ ንባብ ያስገነዝባል።

ለተከሳሽ መጥሪያ ተልኮለት ያልቀረበ እንደሆነ ክሱ እንደማንኛዉም ክስ ይቀጥላል በማለት የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ. 163(2 እና 3) ይደነግጋል። የዐ/ህግ ምስክርም ተሰምቶ ዐ/ህጉ የመጨረሻ ንግግሩን አድርጎ ፍ/ቤቱ እንደማንኛዉም ደንበኛ ክስ ፍርድ እንደሚሰጥ ድንጋጌዉ ይገልፃል። ተከሳሽ ካልቀረበ ክሱ በሌለበት እንደሚታይ ያስገነዝባል። በእርግጥ

በመርህ ደረጃ ተከሳሽ ባለበት ክሱ እንደሚሰማ እስካሁን ያየናቸዉ ድንጋጌዎች አስረጅ ናቸዉ።

ተከሳሽ በሌለበት ክርክር ሲደረግ በጠበቃ የመከራከር መብት እንዴት ሊፈፀም ይችላል የሚለዉ መታየት ይኖርበታል። የተፈጥሮ ሰዎችን በተመለከተ በወንጀል ክርክር ተከሳሽ በሌለበት ጠበቃ ብቻዉን ሊቀርብ እንደማይችል በመግለፅ በአንድ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቀረበ ክርክር ዐ/ህግ መከራከሪያ አቅርቦ ነበር።[75] በህገ መንግስቱ አንቀፅ 20(5) መሰረት የተከሰሱ ሰዎች በመረጡት የህግ ጠበቃ የመወከል መብት ያላቸዉ ሲሆን ጠበቃ የመወከል አቅም የሌላቸዉ በሆኑ ጊዜ ፍትህ ሊያጓድል የሚችል በሆነ ጊዜ ከመንግስት ጠበቃ የማግኘት መብት አላቸዉ።

ተከሳሽ በሌለበት የሚሰማ ክርክር ፍትህ የመጓደል ዕድሉ ሰፊ ስለሚሆን በጠበቃ የመወከል መብት ሊከበር ይገባል ማለት ይቻላል። ይህም የተከሰሱ ሰዎች ህገ መንግስታዊ መብት በመሆኑ በጠበቃ የመወከል መብት መርህ ክርክሩ በሌለበት ለሚታይ ተከሳሽም ያለ ልዩነት ተፈፃሚ ሊሆን ይገባዋል። ይህ ካልሆነ የህጉን እኩል ተፈፃሚነት መርህ የሚጥስ ያደርገዋል። ተከሳሽ ባልቀረበ ጊዜ ክርክሩ በሌለበት የሚታይ ቢሆንም የተከሰሰ ሰዉ መሰረታዊ መብት የሚባሉት የመሰማት መብት እና ንፁህ ሆኖ የመገመት መብት በሌለበትም ቢሆን ሊዘነጉ አይገባም። ፍ/ቤት እንዲቀርቡ ተፈልገዉ ያልተገኙ የተከሰሱ ሰዎች ሁሉ ከፍትህ ሸሽተዉ ነዉ የሚል ግምት መዉሰድ ትክክል አይሆንም። በጠበቃ የመወከል መብት መከበሩ የተከሰሱ ሰዎች ይህን ተማምነዉ ከፍትህ ለማምለጥ ያመቻቻሉ ለማለት በቂ ምክንያት አይሆንም። በጠበቃ መወከል አለባቸዉ ሲባል መከሰሳቸዉን ሳያዉቁ ክርክራቸዉ የሚታይባቸዉን ንፁሃንን መብት ለመጠበቅ ሲባል ተደርጎ መወሰድ አለበት። የማስረጃ ምዘና መርህዓችን (ህግጋታችን) ከጥርጣሬ በፀዳ ሁኔታ (beyond reasonable doubt) ማስረዳት የሚጠይቅ ስለመሆኑ ስለማይገልፅ የጠበቃ መኖርን አስፈላጊ ያደርገዋል። የኮመን ሎዉ ህግ ፍልስፍና ብዛል የሆነዉ አንድ ንፁህ ሰዉ ከሚቀጣ መቶ እና አስር ወንጀለኞች ነፃ ቢለቀቁ ይሻላል የሚሉትም ለዚህ ነዉ።[76]

---

[75] የሰ.መ.ቁ. 120762 (ቅፅ 19)፣ ዐ/ህግ እና ዱባይ አዉቶ ጋለሪ (2 ሰዎች)፣ የካቲት 25/2008፣ ገፅ 279፣ የሰበር ሰሚ ችሎቱ በጠበቃ መወከልን አስመልክቶ በተሰጠው ትእዛዝ ላይ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚገባ የመጨረሻ ዉሳኔ አይደለም በማለት በመወሰኑ በጉዳዩ ላይ የህግ ትርጉም አልተሰጠበትም።

[76] The legal maxims that Tarun Jain pronounces 'let hundred guilty be acquitted but one innocent should not be convicted;' and also as William Black Stone pronounces 'it is better that ten guilty men should escape than one innocent man should suffer' have an important implications here.

ስለዚህ ክርክሩ ተከሳሽ በሌለበት የሚታይ ቢሆንም በጠበቃ የመወከል መብት ተከብሮ በጠበቃ ሊሰማ ያስፈልጋል ማለት ይቻላል። በከባድ ወንጀል የተከሰሱ ሰዎችም ክርክሩን በጠበቃ አማካኝነት ማስቀጠል አስፈላጊ ስለመሆኑ በዚህ ውሐፍ ካየነዉ ተሞክሮ አኳያም ተገቢ ይመስላል።

3.1 ተከሳሽ በሌለበት የሚታዩ የወንጀል ዓይነቶች እና የሚታዩበት ሁኔታ

ተከሳሽ በሌለበት የሚታዩ የወንጀል ዓይነቶች በወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ. 161(2) የተጠቀሱት ብቻ ናቸዉ። አንደኛዉ ሁኔታ በፊደል (ሀ) የተገለፀዉ ከአስራ ሁለት ዓመት በታች በማያንስ ፅኑ-እስራት የሚያሳስር ወንጀል የሰራ የሚለዉ ሲሆን ሁለተኛዉ ሁኔታ በፊደል (ለ) የተገለፀዉ በወ.መ.ህ.ቁ 354-365 ድረስ ያሉትን ወንጀሎች ፈፅሞ ፅኑ እስራት ወይም ከአምስት ሽህ ብር በላይ መቀጮ በሚያስቀጣ ወንጀል የተከሰሰ ሰዉ ሲሆን ነዉ። ይህ ድንጋጌ በቀላል እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል ተከሳሽ በሌለበት ነገሩ እንደማይሰማ ያስረዳል።

በወንጀል ጉዳዮች አከራካሪዉ ነጥብ ከ12 ዓመት በታች በማያንስ ፅኑ እስራት የሚያሳስር ወንጀል የሰራ የሚለዉ አገላለፅ ምን ማለት ነዉ የሚለዉ ነዉ። በዚህ ላይ ሶስት አይነት ሀሳቦች ይቀርባሉ።

- የመጀመሪያዉ ሀሳብ ተከሳሽ በሌለበት ክሱ ሊሰማ የሚገባዉ ተከሳሽ በተከሰሰበት ወንጀል ፍ/ቤቱ በተጨባጭ የሚወስነዉ ቅጣት 12 ዓመትና በላይ ሆኖ መገኘት ነዉ የሚል ሲሆን፤
- ሁለተኛዉ የወንጀሉ ድንጋጌ የቅጣት መነሻ 12 ዓመት ፅኑ እስራት በላይ ከሆነ ነዉ የሚል እና
- ሶስተኛዉ ደግሞ ተከሳሹ የተከሰሰበት ወንጀል መነሻ ቅጣት 12 ዓመት በታች ቢሆንም መድረሻ ቅጣቱ ከ12 ዓመት በላይ ሆኖ መገኘት ነዉ የሚሉ ናቸዉ።

የመጀመሪያዉን ሀሳብ የሚያራምዱትን በሚመለከት በወንጀል ክርክር ሂደት ማስረጃዉ ሳይሰማ አስቀድሞ የሚወሰነዉን ቅጣት ምን ያህል እንደሚሆን ማወቅ አይቻልም። ለምሳሌ በወ.ህ.ቁ. 27(1) እና 539 ከባድ ሰዉ ግድያ ሙከራ ወንጀል የተከሰሰ ሰዉ የወንጀሉ አፈፃፀም በማስረጃ ተመዝኖ ዝቅተኛዉን ቅጣት በ10 ዓመት ፅኑ እስራት ሊቀጣ ይችላል። በሌሎች ወንጀሎችም ተመሳሳይ ሁኔታ ይገጥማል። ይህ እንደሚሆን አስቀድሞ ማወቅ ስለማይቻል ድንጋጌዉ ይህን ሀሳብ የያዘ ነዉ ለማለት አይቻልም።

ሁለተኛዉን ሀሳብ ስንመለከት በወንጀል ህጋችን 12 ዓመት መነሻ ቅጣት ያለዉ ድንጋጌ የሌለ ስለሆነ ድንጋጌዉ ይህን ሀሳብ የሚደግፍ አላማና ይዘት የለዉም የሚል መከራከሪያ

ይቀርባል፡፡ በእርግጥ የድንጋጌዉ ንባብ "...ከ12 ዓመት በታች በማያንስ ፅኑ እስራት የሚያሳስር ወንጀል የሰራ..." የሚለዉ አነጋገር ተከሳሽ የተከሰሰበትን የወንጀል ድንጋጌ የቅጣት መነሻ የሚመለከት ይመስላል፡፡

ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክርክር የሚታየዉ በመርህ ደረጃ ሳይሆን በተወሰኑ ወንጀሎች ብቻ በልዩ ሁኔታ ነዉ፡፡ ድንጋጌዉም የሚያስነብበዉ በህጉ በተመለከቱት ከባድ ወንጀሎች ካልሆነ በቀር ተከሳሽ በሌለበት የወንጀል ክስ የማይሰማ መሆኑን ነዉ፡፡ በልዩ ሁኔታ በህግ የተደነገጉ ጉዳዮች ሊተረጎሙ የሚገባቸዉ በጠባቡ መሆኑን የህግ ፍልስፍና መርሆዎች ያስገነዝባሉ፡፡ የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ድንጋጌዎችን ስንመለከት መነሻ ቅጣታቸዉ 12 ዓመት የሚሆን ባይኖሩም ከዚህ በታች መነሻ ኖሯቸዉ እስከ እድሜ ልክ ወይም ሞት እስከሚደርስ የሚያስቀጡ በርካታ ድንጋጌዎች ይገኛሉ፡፡ ከ12 ዓመት በላይ መነሻ ያላቸዉ ማለትም ዕድሜ ልክ ወይም ሞት የሚያስቀጡ ድንጋጌዎች 522 (ከባድ ሰዉ ግድያ)፣ 638 (ዘረፋ)፣ 637 (ከባድ ዉንብድና)፣ 639 (የባህር ላይ ዉንብድና) እና 270 (በመንግስት ግዛት ሀገር የሚፈጸሙ ወንጀሎች) ናቸዉ፡፡ በ1996 በተሻሻለዉ የወንጀል ህግ መድረሻ ቅጣታቸዉ በ1949 ከነበረዉ 10 ዓመት ከፍ ብሎ ከ12 ዓመት በላይ የተደረጉ ድንጋጌዎችም አሉ (ለምሳሌ ከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ እና አስገድዶ መድፈር ወንጀልን መመልከት ይቻላል)፡፡

ተከሳሽ በሌለበት ክርክር በልዩ ሁኔታ የሚታይ ልዩ ስርዓት ከመሆኑ አኳያ የህጉ አላማና ይዘት የትኛዉን ሀሳብ የሚቀርብ እና የሚደግፍ እንደሆነ ማየቱ ጠቃሚ ነዉ፡፡ ስለሆነም ሶስተኛዉን ሃሳብ ስንመለከት ብዛት ያላቸዉን የወንጀል ጉዳዮችን የሚያቅፍ ስለሚሆን ተከሳሽ በሌለበት ክርክር ከልዩ ሁኔታ ይልቅ መርህ የሚያደርገዉ ይመስላል፡፡

በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ከቁጥር 354-365 ያሉት ድንጋጌዎች በ1996 ዓ.ም በወጣዉ የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ[77] የተሻሩ በመሆኑ እነዚህ ድንጋጌዎች በወንጀል ህጉ ከቁጥር 343-354 ተደንግገዉ የሚገኙ ሲሆን በርዕሰ አራት ስር በመንግስት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ተብለዉ በ12 ድንጋጌዎች ዝርዝር ተደንግገዉ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ የወንጀል ዓይነቶች ዉጭ ያሉት የወንጀል ጉዳዮች ተከሳሽ በሌለበት የሚታዩ አይሆኑም፡፡ እነዚህን ሂደቶች ስንመለከት ተከሳሽ ከመጀመሪያዉ ቀጠሮ ጀምሮ ሳይቀርብ በቀረ ጊዜ የሚፈፀም ሲሆን በእነዚህና በሌሎች ወንጀሎች ተከሳሽ ክርክሩን ከጀመረ በኋላ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ቢቀር ስላለዉ ሁኔታ ህጎቹ የሚሉት ነገር የለም፡፡ በዚህ ሀሳብ ላይ በፍ/ቤቶች ሁለት ዓይነት ክርክሮች ይቀርባሉ፡፡ አንደኛዉ ሀሳብ ተከሳሽ በመጀመሪያዉ

[77] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ (1997 ዓ.ም)፣ አዋጅ ቁጥር 414/1996 ዓ.ም

ቀጠሮ ቀርቦ ክርክሩን ከሰማ በኋላ በተለይ የዐ/ህግ ምስክሮች ተሰምተዉ ተከላከል ከተባለ በኋላ ከቀረ ክርክሩ በቀጥታ ይታያል፤ ተከሳሽ የመከላከል መብቱን አዉቆ የተወዉ በመሆኑ በሌለበት ታይቷል ሊባልም አይገባም የሚል ሃሳብ የሚያቀርቡ ይገኛሉ፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ተመሳሳይ አቋም በመያዝ ትርጉም ሰጥቷል፡፡[78] ይኸዉ ጉዳይ የቀረበለት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተከሳሽ ክርክሩን በራሱ ፍላጎት እንደተወ ስለሚቆጠር በሌለበት ታይቷል ሊባል ስለማይችል ወዲያዉኑ ፍርድ መስጠት እንደሚገባ ነዉ የወሰነዉ፡፡

ይሁን እንጅ ተከሳሽ ክርክሩን አዉቆና ፈልጎ ትቶታል ለማለት ፍ/ቤት ያልቀረበበትን ምክንያት መመርመር ያስፈልጋል፡፡ የተከሳሽ መከላከያ ማስረጃ ባልተሰማበት ሂደት ክርክሩ ተከሳሽ በሌለበት ታይቷል ሊባል አይችልም ማለት የወንጀል የክርክር ሂደትን አድማስ ያላገናዘበ ያደርገዋል፡፡ ይህም የአለም አቀፍ ህግጋትና የአለም አቀፍ ሰነዶች መርሆዎች ጋር የተጣጣመ ስለመሆኑ መመርመር የሚያስፈልግ ነዉ፡፡ በወንጀል ፍትህ ስርዓት ክርክሩ የሚያበቃዉ ፍትሀዊ የክርክር ሂደት መርሆዎች (principles of fair trial)[79] በተሟሉበት ሁኔታ ከክስ መሰማት እስከ ቅጣት ዉሳኔ ወይም የይግባኝ ክርክር ዉሳኔ ድረስ ያለዉን ሂደት ጨምሮ ነዉ፡፡[80] የተከሳሽ መሰረታዊ መብት ተደርጎ በህገ መንግስታችን አንቀፅ 20(4) የተደነገገዉ የመሰማትና የመከላከል መብት ሳይከበር የመከላከያ ማስረጃ ሳያቀርብ የሚሰጥ ፍርድ ተከሳሽ በሌለበት ታይቷል ሊባል አይችልም ማለት ፍትሃዊነት ይጎድለዋል፡፡ የተከሳሽን ንፁህ ሆኖ የመገመት እና የመሰማት መብት እንዲሁም በእኩል ሚዛን የመዳኘት መብትን (equality of arms) ያጣብባል፡፡

ስለሆነም በህግ ስርዓታችን ተከሳሽ ክርክሩን ትቸዋለሁ ማለት (waive the right to be present) የሚችል ስለመሆኑ የሚገልፅ የህግ ማዕቀፍ የሌለ ሲሆን በክርክር መሃል የቀረን ተከሳሽ የዐ/ህግ ማስረጃ በመሰማቱ ብቻ የተከሳሽ የመሰማት መብት ተከብሮለታል ማለት ፍትሃዊ የክርክር መብት መርህን ያልተከተለ ስለሚያደርገዉ ተገቢ አይሆንም፡፡ ተከሳሽ ከመጀመሪያዉ ቀጠሮ ጀምሮ የቀረ ሆነም በመሀል አቋርጦ የቀረ ወንጀሉ ተከሳሽ በሌለበት

---

[78] የሰ.መ.ቁ. 127313 (ቅፅ 22)፣ አብክመ ፍትህ ቢሮ ዐ/ህግ እና አንዱዓለም ገናናዉ፣ መስከረም 22/2010፣ ገፅ 187፤ ክሱ የወ.ህ.ቁ 555(1 ለ)ን የተመለከተ ሲሆን ተከሳሽ ተከላከል ከተባለ በኋላ አቋርጦ ቀርቷል፤ የወረዳ ፍ/ቤቱም ወንጀሉ በሌለበት ሊታይ የሚችል አይደለም ፖሊስ ተከሳሽን ያቅርብ በሚል መዘገቡን ዘግቷል፤ ይህም በከፍተኛ ፍ/ቤቱ እና በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት አግኝቶ ነበር፡፡

[79] See the detail criterias in Principles and Guidelines on the Right to A Fair Trial and Legal Assistance in Africa; at note 67 above; የክርክር ፍትሃዊነት መመዘኛዉ ብዙ ቢሆንም አንድን ክርክር ፍትሃዊ ነዉ ለማለት ቢያንስ የሀገራቱን የህግ ማዕቀፍ፣ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን እና የአለም አቀፍ ህግ ልምዶችን መሰረት ያደረገ ሂደትን የተከተለ ሊሆን ያስፈልጋል፤ Lawyers Committee፣ ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 6፣ ገፅ 2-3

[80] Paul Mahoney, Right To A Fair Trial In Criminal Matters Under Article 6 E.C.H.R., Judicial Studies Institute Journal, [4: 2004], ገፅ 109

የሚታይ እስካልሆነ ድረስ ተፈልጎ ቀርቦ ወይም በቀረበ ጊዜ ከሚታይ በቀር በሌለበት የሚታይ አይሆንም የሚል ሀሳብ ያላቸውም አሉ፡፡ ይህም ተከላከል ከተባለ በኋላ በቀጣይ የፍ/ቤት ሂደት ያልቀረበ ተከሳሽ ጉዳዩ በሌለበት ሊታይ የሚችል ከሆነም የቀረበት ምክንያት እስካልተረጋገጠ ድረስ ክርክሩን ባለመፈለግ እንደተወዉ ሊቆጠር አይችልም የሚሉ ናቸዉ፡፡ ከፍርድ በኋላ ቀርቦ የሚያቀርበዉ ክርክር ታይቶም እንደገና የመከላከል መብቱ ሊከበርለት የሚችልበትን ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት እንዲያስረዳ መብት ሊሰጠዉ ይገባል ማለት ነዉ፡፡

በተመሳሳይ ተከሳሽ መከላከያ ማስረጃዉን ካሰማ በኋላ በቀረ ጊዜ ፍ/ቤቱ የሚሰጠዉ ዉሳኔ በሌለበት የታዬ ክርክር ሊባል እንደማይችል የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡[81] ፍ/ቤቱ ይህን ሊወስን የቻለዉ የመከላከያ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ የቀረዉ የፍ/ቤቱ ስራ ብቻ ነዉ በሚል ምክንያት ቢሆንም የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ. 149(2 እና 3) ድንጋጌ እንደሚያስረዳዉ ተከሳሹ ጥፋተኛ በተባለ ጊዜ በቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ሀሳቦች ላይ ክርክር እና ማስረጃ (ምስክሮች) ሊሰማ እንደሚችል ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ አኳያ ክርክሩ ያበቃለትና ከፍ/ቤቱ ዉሳኔ ከመስጠት ያለፈ ተግባር (የሙግት) ሂደት እንደሌለ መገለፁ ተገቢ አይመስልም፡፡ የቅጣት ዉሳኔም ቢሆን እንደተገለፀዉ የክርክር አካል ሆኖ ምስክሮች ተሰምተዉ የሚወሰንበት ሂደት መሆኑን ድንጋጌዉ አስረጅ ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ስለቅጣቱ አስተያየት ተከሳሽ ክርክርና ማስረጃ የሚያቀርብበት ሂደት በመኖሩ ተከሳሽ ሳይቀርብ ጥፋተኛ ተብሎ የተሰጠ የቅጣት ክርክር እና የቅጣት ዉሳኔ ተከሳሽ በሌለበት ታይቷል ለማለት የሚያስችል አይደለም መባሉ ተገቢ አይመስልም፡፡ ይህም በክርክር መሃል አቋርጦ የቀረ ተከሳሽ የሚባለዉን ተከሳሽ በሌለበት የሚታይ የክርክር ዓይነትን የሚያመለክት በመሆኑ እንደ ክርክሩ ሁኔታ እየታዬ ከሚወሰን በቀር በጥቅሉ በሌለበት ታይቷል አይባልም የሚል ትርጉም መስጠት ህጋዊ አይሆንም፡፡

3.2 ተከሳሽ በሌለበት የተፈረደዉን ፍርድ ዉድቅ ስለማድረግ

3.2.1 የማመልከቻዉ አቀራረብ

በሌለበት ፍርድ የተሰጠበት ሰዉ ፍርዱ ዉድቅ እንዲሆንለት ፍርዱን ለፈረደበት ፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረብ የሚችል መሆኑን የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ. 197 ይደነግጋል፡፡[82] ማመልከቻ

[81] የሰ.መ.ቁ. 29325 (ቅፅ 7)፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ የካቲት 28/2000

[82] የዐ/ህግ ማስረጃ እና የመከላከያ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ የቀረ ተከሳሽ የመሰማት መብቱ የተከበረለት ስለሆነ በጥፋተኝነትና ቅጣት ዉሳኔዉ ሳይቀርብ ቢወሰን በሌለበት ታይቷል ሊባል እንደማይችል የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ዉሳኔ ያስረዳል፡፡ የሰ.መ.ቁ. 76909 (ቅጽ 13)፣ ወ/ሮ ፈትያ አወል እና ዐ/ህግ፣ ግንቦት 10/2004፣ ገፅ 305

የሚቀርበዉ በሌለበት የተፈረደበትን ፍርድ ካወቀበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ዉስጥ መሆኑን የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ. 198 ያስረዳል። ይኸዉ ቁጥር ማመልከቻዉ ፍርዱ ዉድቅ እንዲሆንለት የሚጠይቅበትን ምክንያት መግለፅ ያለበት መሆኑን ያስረዳል። በሌለበት የተፈረደበት ሰዉ ፍርዱ ዉድቅ የሚደረግለት ሁለት ነጥቦችን ማስረዳት ከቻለ መሆኑን የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ 199 ያስረዳል። አንደኛዉ ነጥብ የተከሰሰዉ ሰዉ እንዲቀርብ መጥሪያ ያልደረሰዉ[83] እንደሆነ ሲሆን ሁለተኛዉ ነጥብ ደግሞ ራሱ ወይም ጠበቃዉ ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት መቅረብ አለመቻሉን ያስረዳ እንደሆነ ስለመሆኑ ቁጥር 199 (ሀ እና ለ) ያስረዳሉ። በመሆኑም በቁጥር 199 (ሀ) መሰረት በወንጀል የክርክር ሂደት አንድ ተከሳሽ መጥሪያ ደረሰዉ ሊባል የሚችለዉ መጥሪያዉ ለራሱ የደረሰዉ ሲሆን ነዉ። ከዚህ ባለፈ ቤተሰቦችህ መከሰስክን ያዉቁ ነበር ወይም በህትመት ማስታወቂያ ተጠርተሃል በሚል ምክንያት ፍርዱ ይነሳልኝ ብሎ የሚያቀርበዉን አቤቱታ ዉድቅ ማድረግ የተከሳሽን በክርክር የመገኘት መሰረታዊ መብት የሚገድብ ነዉ ሊባል ይችላል። በሀገራችን የሥነ-ሥርዓት ህግ የተከሰሰ ሰዉ መከሰሱን እንዲያዉቀዉ ፍ/ቤቱ ተደራሽ ነዉ ብሎ በገመተዉ መንገድ ይጠራዋል ይበል እንጅ በሌለበት የተሰጠዉን ፍርድ ለማስነሳት በሆነ ጊዜ ግን መረጋገጥ ያለበት ለተከሳሽ "እንዲቀርብ መጥሪያ ያልደረሰዉ እንደሆነ (that he has not received a summons to appear)" ስለመሆኑ በግልፅ በአንቀፅ 199(ሀ) የተገለፀ ጉዳይ ነዉ።

በቁጥር 199 ፊደል "ሀ" እና "ለ" የተገለፁት ሁኔታዎች ተነጣጥለዉ የሚታዩ ሲሆኑ በፊደል (ሀ) የተጠቀሰዉን በተመለከተ የተከሰሰዉ ሰዉ እንዲቀርብ መጥሪያ ያልደረሰዉ መሆኑን ካስረዳ በሌለበት የተሰጠዉ ፍርድ ዉድቅ ተደርጎ ክርክሩ እንደገና ባለበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን የሚያስረዳ ነዉ። ከዚህ ላይ አንድ ተከሳሽ መጥሪያ ያልደረሰዉ መሆኑን እንዴት ማስረዳት ይችላል የሚለዉን ስንመለከት አስቀድሞ የፍ/ቤቱ መጥሪያ የደረሰዉ ለመሆኑ ማረጋገጫ ካልቀረበ እንዳልደረሰዉ የሚቆጠር ይሆናል። መጥሪያ ደርሷል የሚለዉንም ማረጋገጥ ያለበት መጥሪያ ደርሷል የሚለዉ አካል ይሆናል።

---

[83] የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ የሰ.መ.ቁ. 57632፣ (ቅፅ 12)፣ በሰማኸኝ በለዉ እና የፌደራል ዐ/ህግ፣ ታህሳስ 25/2003፣ ገፅ 179፤ ችሎቱ እንደገለፀዉ ተከሳሽ መከሰሱን ሚስቱ ታዉቅ ነበር በሚል እና ዉጭ አገር ሂዶ ከአንድ ዓመት በላይ ወደ አገሩ ሳይመለስ መቆየቱ ከፍትህ ማምለጡን (መሸሸን) ያሣያል በሚል ምክንያት በሌለሁበት የተሰጠዉ ፍርድ ይነሳልኝ አቤቱታ ዉድቅ መደረጉን ተገቢ ስለመሆኑ በፍርድ ሀተታዉ የገለጸ ሲሆን ይህ መጥሪያ የደረሰዉ መሆኑን ስለማያስረዳ ማመልከቻዉን ዉድቅ ለማድረግ በቂ አይሆንም። ምክንያቱም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህጉ በዚህ አማራጭ መጥሪያ የተላከለት ሰዉ እንደደረሰዉ ተቆጥሮ መብቶቹ የሚገደቡ ስለመሆኑ አይደነግግም። እነዚህ አማራጮች ፍ/ቤቱ ተከሳሹ መከሰሱን እንዲያዉቀዉ ለማድረግ ጥረት የሚያደርግበት መንገድ እንጅ ፍርዱ ዉድቅ ይደረግልኝ የሚለዉ ክርክር በተነሳ ጊዜ መከራከሪያ ሊሆኑ አይችሉም። አስቀድሞም ቢሆን በሌለበት ክርክር ልዩ ሁኔታ በመሆኑ የተከሳሽን ፍትሃዊ የክርክር መብት በመጠበቅ የተፈረደበት ሰዉ በቀረበ ጊዜ ወዲያዉኑ ወይም እንደጠየቀ ፍርዱ ተነስቶ እንደገና የመከራከር መብቱ ሊፈቀድ የሚገባ ነዉ፤ ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 34፣ ገፅ 254፣ (ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5 እንደተገለፀዉ፣ ገፅ 293-94)

ስለዚህ ሁለተኛውን ምክንያት ተከሳሽ እንዲያስረዳ ግዴታ የምንጥልበት መጥሪያው በአግባቡ ደርሶታል ብለን ባረጋገጥን ጊዜ ብቻ ነው። ይህ ሳይሆን መጥሪያ ያልደረሰውን ተከሳሽ ከአቅም በላይ መቅረቱን የሚያስረዳ ምክንያት አላቀረበም የምንል ከሆነ ከሥነ-ሥርዓት ህጉ ይዘት ውጭ ይሆናል። ራሱ ወይም ጠበቃው ከአቅም በላይ በሆነ ሀይል መቅረብ አለመቻሉን ያስረዳ እንደሆነ የሚለው አነጋገርም የሚያመለክተው መጥሪያ የደረሰው ተከሳሽ ክሱ በሚሰማበት ቀን ባለመቅረቡ ክርክሩ በሌለበት ተሰምቶ ፍርድ የተሰጠበት ሆኖ በተገኘ ጊዜ ያለውን ሂደት የሚመለከት ነው። የተከሳሹ ወይም የጠበቃው የቀሩበት ምክንያት በተናጠል የሚመዘን መሆኑን ከድንጋጌው አማራጭ አገላለፅ መረዳት ይቻላል። አንደኛው ያቀረበው ምክንያት በቂ ከሆነ ክርክሩ ተቀባይነትን ያገኛል ማለት ነው።

ይህን ለማስረዳት ተከሳሹ ወደ ፍ/ቤት እንዳይቀርብ የሚከለክል አካላዊ ወይም ተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሰራሽ ሀይል ተከስቶ በፍ/ቤቱ ቀጠሮዎች ያልተገኘን ተከሳሽ በበቂ ምክንያት ያልቀረበ ለመሆኑ እንደ አስረጅ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል ማለት ይሆናል። በምሳሌ ለመግለፅ ያህል አንድ የተከሰሰ ሰው ከባድ አደጋ ደርሶበት በቤት ውስጥ የሚውል ህመምተኛ (የአልጋ ቁራኛ) ሆኖ መቅረብ ባይችል እና በሌለበት ፍርድ ቢሰጥ ይህ ምክንያት ፍርዱን ውድቅ ለማድረግ የሚችል በቂ ምክንያት ሊሆነው ይችላል። ስለዚህ በትክክለኛ ሰው አእምሮ ግምት መነሻ አድርገን ምክንያቶችን ልንመዝን እንችላለን ማለት ነው። እነዚህን ሁኔታዎች ተከሳሽ በክርክሩ መሀል አቋርጦ በቀረ ጊዜም በተመሳሳይ ተፈፃሚ ልናደርጋቸው እንደሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል።

3.2.2 የነገሩ መሰማት

ተከሳሹ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ እንዲነሳለት የጠየቀበት የማመልከቻ ግልባጭ ለዐ/ህግ የሚላክለት ሲሆን የቀጠሮው ቀን ተነግሯቸው ተከሳሹ በቀጠሮው ቀን ካልቀረበ ማመልከቻው ውድቅ እንደሚሆንበት የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ. 200(1 እና 2) ይገልፃል። ነገሩ በሚሰማበት ቀን አመልካቹ ጠበቃ ካለውም ጠበቃው ማመልከቻውን በመደገፍ የሚናገር ሲሆን ዐ/ህጉም መልስ ይሰጥበታል። አመልካቹ ከፈለገ የመልስ መልስ የመስጠት መብት አለው። ይህ ክርክር ከተሰማ በኋላ ፍ/ቤቱ ውሳኔ የሚሰጥበት መሆኑን ቁጥር 201(2) ያስረዳል።

ፍ/ቤቱ የተከሳሹን ማመልከቻ ከተቀበለው ስልጣን ያለው ሌላ ፍ/ቤት ነገሩን እንደገና እንዲያየው ትዕዛዝ የሚሰጥ ሲሆን ዐ/ህጉም ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ክሱን እንደሚያቀርብ የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ. 202(1) ይደነግጋል። ይህ ድንጋጌ ግልፅነት የሚያስፈልገው ነው። ስልጣን ያለው ሌላ ፍ/ቤት የሚለው አገላለፅ ጉዳዩ በሌላ ፍ/ቤት እንደሚታይ የሚያመለክት

ሲሆን ዐ/ህግም ሌላ ክስ እንደሚያቀርብ የሚገልፅ ነዉ። የዚህ ድንጋጌ አላማ የዳኞችን ገለልተኛነት ለመጠበቅ ይመስላል። በአሰራር ግን ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠዉ ፍርድ ዉድቅ ከተደረገ ዐ/ህግ አዲስ ክስ ማዘጋጀት ሳያስፈልገዉ ክርክሩ በነበረዉ በቀድሞዉ ችሎት እና መዝገብ የሚቀጥል መሆኑን (ለምሳሌ በአማራ ክልል ፍ/ቤቶች እና በፌደራል ፍ/ቤቶች) ተገንዝቤያለሁ።

በእርግጥ ጉዳዩን የሚመለከተዉ ሌላ ፍ/ቤት በምን ሁኔታ እንደሚመረጥ በህጉ አመላካች ነገር የለም። ነገር ግን ክርክሩን በሌላ ችሎት በአዲስ ክስ ዐ/ህግ አቅርቦ እንዲታይ ማድረጉ የተሻለ ተመራጭ የሚያደርገዉ አስቀድሞ ጉዳዩን የተመለከተዉ ችሎት (ፍ/ቤት) መመልከቱ በክርክሩ ሂደት የተገማችነትና ገለልተኛነት ጥያቄ ስለሚያስነሳ በሌላ ፍ/ቤት ይቀርባል መባሉ ተገቢ ይሆናል። የተከሳሽም በነፃና ገለልተኛ ፍ/ቤት የመዳኘት መብቱን የተጠበቀ ያደርግለታል። ክርክሩን የሚመለከቱት ዳኞችም ቢሆን በቀድሞዉ ክርክርና ማስረጃ ተፅኖ ሳይፈጥርባቸዉ (without bias) ጉዳዩን እንዲመረምሩ ያግዛቸዋል። ስለሆነም ጉዳዩ ወደ ሌላ ፍ/ቤት መሄድ ባይቻል እንኳን በዚያዉ ፍ/ቤትም ሆኖ በሌላ ችሎት ክርክሩን መምራት አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

3.2.3 የማመልከቻዉ ዉድቅ መደረግ እና የይግባኝ መብት

በሌለበት ፍርድ የተሰጠበት ሰዉ ፍርዱ ዉድቅ እንዲሆንለት ያቀረበዉ ማመልከቻ ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረ ከሆነ በዚህ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ የማቅረብ መብት የለዉም በሚል የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ. 202(3) ይገልፃል። ይህም ማለት የቀረበዉ ማመልከቻ ላይ የሚሰጥ ዉሳኔ የመጨረሻ ነዉ ማለት ይሆናል።

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሌለበት የተሰጠዉ ፍርድ እንዲነሳለት ሳይጠይቅ በጥፋተኝነቱ እና በቅጣቱ ላይ ለሰበር ማቅረብ የመጨረሻ ፍርድ ሆኖ ስለማይቆጠር ፍርዱን ዉድቅ ካላደረገዉ በቀር በሰበር ለማሳረም እንደማይችል የወ.መ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ. 202(3) በመጥቀስ የይግባኝ መብትን የሚገድብ ነዉ በሚል ምክንያት የሰበር ቅሬታዉን የመመልከት ህገ መንግስታዊ ስልጣን የለኝም ሲል ወስኗል።[84] በዚህ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለዉ የሚባል ከሆነ ክርክሩን በሌለበት አይቶ ዉሳኔዉን የሰጠዉ የጠቅላይ ፍ/ቤት ስለሆነ የመጨረሻ ዉሳኔ በመሆኑ ለሰበር ችሎት

[84] ዝኒ ከማሁ፤ ይሁን እንጅ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የቅጣቱን ዉሳኔ በሚመለከት ከጥፋተኝነቱ ዉሳኔ ነጥሎ የመጨረሻ ዉሳኔ ነዉ በሚል ተመልክቶታል። እንዲህ ከሆነ የጥፋተኝነት ዉሳኔዉም የመጨረሻ በመሆኑ ተከሳሹ ክርክሩ እንደገና ባለሁበት ይታይልኝ የሚል ጥያቄ ባያነሳም ፍርዱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለመሆን አለመሆኑ እንደ ቅጣት ዉሳኔዉ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ሊመረምረዉ ይገባ ነበር።

ከማቅረብ የሚከለከል አይሆንም፡፡[85] ተከሳሹም ቢሆን ፍርዱ እንዲነሳለት አልጠየቀም በሚል በዋናዉ ፍርድ ላይ ብቻ ይግባኝ የማቅረብ መብቱ ሊከለከል አይገባዉም፡፡ ምክንያቱም ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠዉ ፍርድ እንዲነሳለት የሚጠይቀዉ ቀርቦ ተከራክሮ ነፃ ለመባል በመሆኑ አስቀድሞ በሌለሁበት በተደረገዉ ክርክር የቀረበብኝ ማስረጃም ቢሆን ጥፋተኛ አያሰኘኝም ነበር ብሎ ካመነ ፍርዱ እንዲነሳለት የመጠየቅ ግዴታ ሳይኖርበት በይግባኝ ሊያሳርም ይችላል መባል ይገባዋል፡፡

ይሁን እንጅ በሌለበት የተፈረደበት ፍርድ ዉድቅ እንዲሆንለት የጠየቀዉ ማመልከቻ ዉድቅ የተደረገበት ተከሳሽ የቅጣት ዉሳኔዉን በሚመለከት ብቻ ማመልከቻዉ ዉድቅ ከተደረገበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር በ15 ቀን ዉስጥ ይግባኝ የማለት መብት እንዳለዉ የወ.መ.ሥ.ሥ.ሀ.ቁ 202(3) ይደነግጋል፡፡ ይህ አገላለፅ በጥፋተኝነቱ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ እንዳይጠይቅ የሚከለክል ነዉን የሚለዉን ማየት ያስፈልጋል፡፡

የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ አላማዉ የተከሰሱ ሰዎችን የክርክር ሂደት በፍትሀዊነትና በአጭር ጊዜ የመዳኘት መብት መስጠት እንጅ የተከሳሽን መብት መገደብ ሊሆን አይችልም፡፡ በፍ/ቤቶች የይግባኝ ስርዓት መኖር አላማዉ የስር ፍ/ቤቶች በሚሰጡት ዉሳኔ የህግ ቁጥጥር በማድረግ ስህተቶችን ማረም ነዉ፡፡ በወንጀል ክርክር ጊዜ ሲሆን ደግሞ የህግ ስህተቶችን ከማረም ባለፈ የተፈረደባቸዉን ሰዎች ነፃነት (ንፅህና) በማረጋገጥ ነፃ መልቀቅ (aquital) የሚጨምር በመሆኑ መሰረታዊ መብት ነዉ፡፡ ይህን መሰረታዊ የተከሳሽ መብት በስነ-ስርዓት ህግ መገደብ የተፈረደባቸዉን ሰዎች ንፅህና ማጣበብ (መገደብ) ስለሚሆን ህገ መንግሰታዊ አይሆንም፡፡ አዲስ ክርክር የማቅረብ መብታቸዉ ቢገደብ እንኳን በዐ/ህግ የቀረበባቸዉ ማስረጃ ጥፋተኛ ሊያደርጋቸዉ የሚችል ስለመሆኑ በይግባኝ ተመርምሮ ዉሳኔ እንዲሰጣቸዉ ሊከለከሉ አይገባም ማለት ይቻላል፡፡ በእኔ እምነት በቅጣቱ ላይ ብቻ ይግባኝ ሊል ይችላል የሚለዉ አገላለፅ ክርክሩ ባለሁበት ይታይልኝ ብሎ ባቀረበዉ ማመልከቻ ዉድቅ መሆን ላይ (re-hearing or re-trial) ይግባኝ ማለት አለመቻሉን ለመግለፅ ነዉ፡፡ ምክንያቱም በቅጣቱ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ተፈቅዶ የሰዎችን ነፃነት የሚመለከተዉን የጥፋተኝነት ዉሳኔ በተመለከተ ይግባኝ የሚከለክል ነዉ ማለት ምክንያታዊ አያደርገዉም፡፡

ይህንን ጉዳይ ከሀገራችን የህግ ስርዓት አኳያ መመልከትም ተገቢ ይሆናል፡፡ የሥነ-ሥርዓት ህግጋት (የፍትሐብሔርም ይሁን የወንጀለኛ መቅጫ) አላማ በመሰረታዊነት ተመሳሳይ ይዘት ያላቸዉ መንገዶች በመሆናቸዉ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ክፍተት ያለባቸዉን ድንጋጌዎች ከፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህጉ ጋር በማጣመር መተርጎም ተገቢ

[85] አንቀፅ 80 ((3)ሀናለ)) የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸዉንም የመጨረሻ ዉሳኔ በሰበር የማረም ስልጣን ያለዉ መሆኑን ይደነግጋል፡፡

ይሆናል፡፡ ይህም ክፍትቱን ለመሙላት (gap-filling) የፍትሐብሔሩን ሥነ-ሥርዓት መዉሰዱ ዉጤታማ የሆነ ትርጉም ላይ እንድንደርስ ይረዳናል፡፡ በፍትሐብሔር የክርክር ሂደት ክርክሩ በሌለበት (ex-parte) የታየበት ተከሳሽ መጥሪያ ሳይደርሰኝ ክርክሩ በሌለሁበት ታይቶ የተወሰነዉ ይነሳልኝና ክርክሩ ባለሁበት ታይቶ ይወሰንልኝ በሚል በፍ.ሥ.ሥ.ህ.ቁ 78[86] መሰረት ቢያመለክትና ዉድቅ ቢደረግበት ወይም ፍርዱ ይነሳልኝ ብሎ ሳያመለክትም ቢሆን በቀጥታ በዋናዉ ፍርድ ላይ ይግባኝ ማለት ቢፈልግ ከመጠየቅ አይከለከልም፡፡[87] ይህ ከሆነ በወንጀል የክርክር ሂደትም ተከሳሹ በሌለበት የታየ ክርክር ቢሆንም በዋናዉ ፍርድ ይግባኝ ከመጠየቅ ሊከለከል አይገባዉም ማለት ወጥነት ያለዉ የህግ ስርዓት ትርጉም ያደርገዋል፡፡ ይህም በወንጀል ለተከሰሱ ሰዎች የመሰማት መብት እድል ይሰጣል እንዲሁም ነፃነትን ለማስከበር ያግዛል፡፡ ህጉም ቢሆን በወንጀል ለተከሰሱ ሰዎች የሰፋ መብት በመስጠት ነፃነታቸዉን እንዲያስጠብቁ ያግዛል እንጅ በገንዘብ ጥቅም ላይ ካተኮረዉ (ከተወሰነዉ) በፍትሐብሔር ከተከሰሱ ሰዎች ያነሰ የመብት ጥበቃ ያደርጋል ተብሎ አይታሰብም፡፡

በእርግጥ ህግ ትርጉም የሚያስፈልገዉ እንደዚህ ዓይነት ግልፅነት በጎደለዉና አሻሚ በሆነ አገላለፅ በተፃፈ ጊዜ በመሆኑ የተከሰሱ ሰዎችን መሰረታዊ መብት በሚያስጠብቅ መንገድ ሊተረጎም ይገባዋል፡፡ በዋናነት ፍ/ቤቶች የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ተከሳሽ በሌለበት የክርክር ሂደት የይግባኝ መብትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ይዘት በመቀበል (import) መሰረታዊ የተከሳሽ መብትን መሰረት ባደረገ ሁኔታ አጠቃላይ የሥነ-ሥርዓት ህጉን አላማና ይዘት መነሻ በማድረግ ዉሳኔ ሊሰጡ ይገባቸዋል እንጅ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህጉ ድንጋጌ ብቻ ተወስነዉ ሊወስኑ አይገባቸዉም፡፡

በፍ/ቤት ዉሳኔዎች የመጨረሻ እርምት የሚሰጡት ፍ/ቤቶችም ቢሆኑ እንደዚህ ያሉ ህጎችን መነሻ አድርገዉ በሚቀርቡ ይግባኞች ላይ መሰረታዊ የተከሰሱ ሰዎችን መብቶች በጠበቀ ደረጃ በዚህ ይዘት ትርጉም መስጠቱ አስፈለጊ ነዉ፡፡ በአዉሮፓ ሰብዓዊ መብት ፍ/ቤት ተከሳሽ በሌለበት የታየ ክርክር ወደ “process par defaut” አሰራር በመለወጥ የተከሳሽን መሰረታዊ መብት በማያጣጣብብ ሁኔታ ለምሳሌ በጠበቃ የመወከል መብትም ሆነ የይግባኝ መብት ሳይገደብ መፈፀም ያለበት መሆኑን ስለመወሰኑ በዚህ ዉሁፍ የተገለፀዉ ሀሳብ የሚያስገነዝበዉ ነዉ፡፡

---

[86] የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት፣ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ፣ 25ኛ ዓመት ቁጥር 3፣ ደንብ ቁጥር 52/1958 (መስከረም 28/1958)፡፡

[87] የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ የሰ.መ.ቁ. 36412፣ (ቅፅ 8)፣ ተስፋሁን ዋኘው እና ጃክ አግሮ ኮሜርሻል ኢንተርኘራይዝ፣ ጥቅምት 13/2001

ከይግባኝ መብት ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ሌላዉ ጉዳይ በአንድ የወንጀል ክርክር ቁጥራቸዉ ከአንድ በላይ የሆኑ ተከሳሾች ኖረዉበት ከፊሎቹ ክርክሩ በሌሉበት ታይቶ ፍርድ ቢሰጥ እና በክርክሩ ተካፋይ የነበሩት ተከሳሾች በፍርዱ ላይ ይግባኝ አቅርበዉ በነፃ ቢሰናበቱ ክርክሩ በሌሉበት የታየባቸዉ ተከሳሾች መብት ምን ይሆናል የሚለዉ ነዉ፡፡ ከእዚህ አኳያ የወ.መ.ሥ.ሥ.ሀ.ቁ 196((1)(ሀ እና ለ)) መሰረት በይግባኝ የተወሰነዉ ዉሳኔ የሚጠቅማቸዉ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ ክርክሩ በሌሉበት በታየባቸዉ ተከሳሾች ላይም ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባዉ ይሆናል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከአንድ በላይ የሆኑ ተከሳሾች ጥፋተኛ በተደረጉበት ዉሳኔ አንዱ ይግባኝ ጠይቆ በሰበር አጣሪ ችሎት ቢሰረዝበት እና በሌላ በኩል ያቀረቡት የሌሎቹ ተከሳሾች ዉሳኔ ቢሻሻልላቸዉ ዉድቅ የተደረገበት ተከሳሽም በዉሳኔዉ ተጠቃሚ ሊሆን እንደሚገባ ወስኗል፡፡[88] ይህ ትርጉም ህጉ በሁሉም ላይ በእኩልነት ተፈፃሚ እንዲሆን የማድረግ መርህን በሚያሳካ ሁኔታ ተከሳሽ በሌለበት በተሰጠ ዉሳኔ ላይም ተግባራዊ መደረግ ያለበት መሆኑን መገንዘብ የሚያስፈልግ ሲሆን ከፊሎቹ በሌሉበት ተፈርዶባቸዉ በክርክሩ የተገኙት ይግባኝ ጠይቀዉ ፍርዱ ቢለወጥ በሌሉበት የተፈረደባቸዉ ተከሳሾችም ቀርበዉ እስከሚጠይቁ ሳይጠበቅ በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 196(1) ፊደል (ሀ እና ለ) መሰረት የተለወጠዉ ፍርድ በቀጥታ ተፈፃሚ ሊሆንላቸዉ ይገባል ማለት ይቻላል፡፡

[88] የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ የሰ.መ.ቁ. 101003፣ (ቅፅ 20)፣ መክብብ ሞገስ እና ዐ/ህግ፣ ህዳር 23/2009፣ ገፅ 380

4. ማጠቃለያ

የወንጀል ክርክርን ተከሳሽ በሌለበት ለማየት ቅድሚያ መጥሪያ እንዲደርሰዉ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡ አንድ ክርክር ተከሳሽ በሌለበት ከታየ በኋላ ያለዉን ዉጤት በተመለከት በዋናዉ ፁሁፍ እንደተገለፀዉ መጥሪያ በአግባቡ መድረሱ እስካልተረጋገጠ ድረስ ፍርዱ ተነስቶ ክርክሩ እንደገና የሚታይ መሆኑን ሲሆን ይህም አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችና መርሆዎች የሚቀበሉት አሰራር በመሆኑ የሚደገፍ ነዉ፡፡ የሥነ-ሥርዓት ህጉም ቢሆን በግልፅ እንዳስቀመጠዉ ተከሳሹ ፍርዱ ይነሳልኝ ብሎ ከሚጠይቅበት ምክንያት አንዱ መጥሪያዉ በአግባቡ ያልደረሰዉ ሆኖ መገኘቱ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል መከሰሱን በተዘዋዋሪ በቤተሰቡ ወይም በጋዜጣ ጥሪ ተደርጓል በሚል በሌለበት ክርክሩ ለታየበት ተከሳሽ ከፍርድ በኋላ ተይዞ ቢቀርብና ክርክሩ እንደገና ባለሁበት ይታይልኝ ቢል ሊፈቀድለት የሚገባ ሲሆን ይህ ዐይነቱ አማራጭ የመጥሪያ ስርዓትም መጥሪያ ስለመድረሱ የሚያረጋግጥ ባለመሆኑ የመሰማት መብትን ለመገደብ አያበቃም፡፡

ተከሳሽ በሌለበት ክርክሩ ቢታይና ፍርዱ ተነስቶ ክርክሩ ባለሁበት ይታይልኝ የሚለዉ አቤቱታ ዉድቅ ቢደረግበት ይግባኝ የማቅረብ መብቱ በጥፋተኝነት ዉሳኔዉ ላይ ጭምር የተፈቀደ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ለቅጣቱ ዉሳኔ ተፈቅዶ ለጥፋተኝነቱ ዉሳኔ የሚከለከልበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም ተብሎ መታየት ይኖርበታል፡፡ ይህም ከተከሳሽ መሰረታዊ መብቶች አኳያ ዉጤታማ የህግ ትርጉም ያደርገዋል፡፡ ክርክሩ በሌለበት እንዲታይ በተባለ ጊዜም የተከሳሹ በጠበቃ የመወከል መብት ህገ መንግስታዊ እንዲሁም በአለምአቀፍ የሰብዓዊ መብት መርሆዎች የተረጋገጠ በመሆኑ በሌለበት ክርክሩ ሲታይም ቢሆን ጠበቃ መመደብ አስገዳጅ መሆኑን ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 13(2) አኳያ መገንዘብ ተገቢ ነዉ፡፡

በእኛ ህግ ክርክር በሌለበት ይታያል የሚለዉ በተለዩ ወንጀሎች ብቻ በመሆኑ ወንጀሉ በሌለበት የማይታይ ሆኖ ክርክሩ ከተጀመረ በኋላ በመሃል አቋርጠዉ የሚቀሩትን በሚመለከት በህግ ግልፅ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በህጉ ተለይተዉ በሌሉበት ይታያሉ የተባሉትም ሆኑ ከተባሉት ዉጭ ያሉትን ወንጀሎች በሚመለከት ህጉ አከራካሪ በመሆኑ ተከሳሽ በሌለበት የሚታዩ ወንጀሎች ተለይተዉ ሊገለፁ የሚገባ ሲሆን በሌለበት የማይታዩ ወንጀሎችን በተመለከተ ሂደቱ ምን መሆን እንዳለበት በግልፅ በህግ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ ክርክሩ ባለሁበት ይታይልኝ የሚለዉ አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ እንደገና ክርክሩ ይታያል በተባለ ጊዜ በተመሳሳይ ችሎት መታየቱ ቀርቶ በዐ/ህግ አዲስ ክስ ተዘጋጅቶ ሊቀርብ የሚገባ መሆኑን የሚገልፀዉ የሥነ-ሥርዓት ህጉ ድንጋጌም በተግባር ሊታይ የሚገባዉ ነዉ፡፡ የይግባኝ መብትም ቢሆን ከተከሳሽ መሰረታዊ መብት አንፃር ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉ

በመሆኑ ክርክሩ በሌለበት በመታየቱ ምክንያት ብቻ ክልከላ ልናስቀምጥ የሚገባን አይሆንም። ይህ ከሆነ የተከሳሹን ህገ መንግስታዊ እና መሰረታዊ መብት የሚጥስ ሊሆን ይችላል። ከዚሁ ጋር ሊታይ የሚገባዉ ነጥብ ክርክሩ በሌለሁበት ይታይልኝ ብሎ መተዉ (waive the right to be present) የተከሰሰ ሰዉ መብት ሊሆን ይገባዋል ወይ የሚለዉ ሲሆን በአፍሪካ ኮሚሽን የአሰራር ደንብ እና መመሪያ እንደተገለፀዉ በግልፅ እና በፅሁፍ ካመለከተና በጠበቃ የመወከል መብቱ ከተከበረለት የሚቻል መሆኑን ያስገነዝባል። ይሁን እንጅ በወንጀል ፍትህ ስርዓት ክርክርን ተከሳሽ ባለበት ማየት ከተከሳሽ መብት አንፃር ብቻ ሊታይ እንደማይችል የአለም አቀፉ ሰብአዊ መብት ኮሚቴ አስገንዝቧል።

ስለሆነም ክርክሩን ትቸዋለሁ (waiving of the right to be present) የሚል ወገን ዉጤቱን ተረድቶና ተቀብሎ በግልፅ ካላስፈቀደ በቀር ከክርክሩ ዉጭ መሆን እንደማይችልና ባለበት ሊታይ እንደሚገባ በመግቢያዉ አለም አቀፍ የህግ ደንቦችን ጠቅሰን ተመልክተናል። በመሆኑም የመቅረብ መብትን ትቸዋለሁ ማለት በራሱ የህግ ስርዓት የሚያስፈልገዉ ጉዳይ ሲሆን የአለም አቀፍ ህግ መርሆዎችን መመልከትና ከህጋችን ጋር አጣጥሞ መተርጎም ህገመንግስታዊ ኃላፊነት በመሆኑ ክርክሩን ተከሳሽ ባለመፈለግ ትቶታል ማለት የምንችልበት ስርዓት ላይ ግልፅ የህግ ማዕቀፍ ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ ተከሳሽ በሌለበት የሚታዩ ጉዳዮች በህግ በግልፅ ተለይተዉ መደንገግ ያስፈልጋቸዋል። የክርክሩ ሂደትም ቢሆን መርሁ የተከሳሹን ሰብዓዊ መብት የሚያስከብር እና የወንጀል ፍትህ ስርዓቱን ዉጤታማነት የሚያስጠብቅ እንዲሁም የህግ የበላይነትን በሚያረጋግጥ ደረጃ የህዝብ አመኔታን የሚያተርፍ (public legitimacy) የፍርድ ሂደት እንዲኖር ማድረግ የሚችል መሆን ይኖርበታል። ይህን አላማ በሚያሳካ ሁኔታ የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ ይሆናል።

የቋሚ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣንና አተገባበር ዳሰሳ

በምዕራብ አማራ ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ

አበበ ካሴ ወርቅነህ

አጽርኦተ-ጽሁፍ

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን የሚመለከቱ ህጎች (አዋጆች) ራሳቸውን ችለው መውጣታቸውን ተከትሎ በአዋጁ ተፈጻሚ የሚሆኑ በቅጥር ላይ የተመሰረቱ ግንኙነቶችን ከመለየት ጀምሮ በአሠሪውና በሠራተኛው መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች የሚፈቱበት ስርዓት ጭምር ተዘርግቷል። በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች አዋጅ ቁጥር 377/1996 ዓ.ም (በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 ዓ.ም እንደተሻረ) መሠረት የሚያጋጥሙ አለመግባባቶችን ከተቻለ በስምምነት ካልተቻለ ግን አለመግባባቶችን ***የግል እና የወል*** *የስራ ክርክሮች በሚል በመለየት የግል የስራ ክርክሮችን በመደበኛ ፍ/ቤቶች የሥራ ክርክር ችሎቶች እንዲሁም የወል የሥራ ክርክሮችን ደግሞ ካላቸው ልዩ ባህሪ የተነሳ ከጉዳዩ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ከፍተኛ ልምድ እና ልዩ ዕውቀት ባላቸው ባለሙያዎች እንዲታዩና ይበልጥ ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንዲቋጩ በማሰብ ለዚሁ ተብለው በአዋጁ መሰረት በተቋቋሙት ቦርዶች እንዲፈቱ ተደርገዋል። ይህ አጭር ጽሁፍም በተለይ የወል የሥራ ክርክሮችን ለመፍታት በክልላችን ከተቋቋሙት ቦርዶች መካከል አንዱ በሆነው የምዕራብ አማራ ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች ወሳኝ ቦርድ ላይ ትኩረት በማድረግ አጭር ዳሰሳ ለማድረግ ሞክሯል።*

በመሆኑም ከጉዳዩ ጋር የሚገናኙ የተለያዩ ፅሁፎች፣ ህጎች፣ አለም አቀፍ ስምምነቶች፣ ሪፖርቶች፣ ደብዳቤዎች፣ ከቦርድ አባላት የተሰበሰበን የፅሁፍ መጠይቅ እንዲሁም ፀሀፊው በቦርድ አባልነቱ ያገኛቸውን ትዝብቶችና የቦርዱን መዛግብት መሠረት በማድረግ አይነታዊ የጥናት ዘዴን ተከትሎ የቦርዱን አደረጃጀት እንዲሁም ስልጣንና ተግባር ዳሷል።

በዚህም መሠረት የዜጎችን ፍትህ የማግኘት ህገ መንግስታዊ መብት ከማረጋገጥ አንጻር የቦርዱ መቋቋም ካለው ከፍተኛ ፋይዳ ጀምሮ ቦርዱ ስልጣንና ተግባሩን በተገቢው መንገድ ለመወጣት ከቦርዱ ጽ/ቤት ሰራተኞች እስከ ቦርዱ አባላት ድረስ ከፍተኛ የሆነ የስራ ፍላጎትና ተነሳሽነት እንዲሁም በርካታ ጠንካራ ጎኖች ያሉት ቢሆንም የተወሰኑ ክፍተቶች ያሉበት መሆኑንም ለማረጋገጥ ተችሏል። ከሚስተዋሉ ውስንነቶች መካከልም የቦርዱ የስራ ጊዜ ማነስ፣ የቦርድ አባላት ስልጠና የሚያገኙበት እድል አናሳ መሆን፣ ከክስ አሰማም ሂደት አንጻር፣ ከውሳኔ አፈጻጸም አኳያ፣ ከህጉ ድንጋጌዎች አንጻር፣ ከቦርድ አባላት ክፍያ ጋር የተያያዙ ክፍተቶች መኖራቸውን እንዲሁም የጉዳዮች መብዛትም ቢሆን በመጠኑ ያለ መሆኑ በጽሁፉ ተዳሰዋል። በዚህም መሰረት ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ክፍተት ያለባቸው የአዋጅ ድንጋጌዎችም ቢሻሻሉ፣ የቦርዱ የስራ ጊዜ ወይም ሰዓት ቢጨመር፣ የቦርድ አባላት ስልጠናዎችን ቢያገኙ፣ ለቦርድ አባላት የሚፈጸመው የአበል መጠን ቢሻሻል የሚሉ እና በአጠቃላይ የቦርዱን ቅልጥፍናና ውጤታማነት ሊጨምሩ የሚችሉ ሌሎች ምክረ-ሀሳቦች ተሰንዝረውበታል።

ክፍል አንድ

የሥራ ግንኙነት ትርጉም እና ጽንሰ-ሀሳብ ከሀገር አቀፍ እና አለም አቀፍ የሕግ ማዕቀፎች አንጻር - እንደ መግቢያ

ማኛውም ሰው ለመተዳደሪያው የመረጠውን (የተቀበለውን/የፈለገውን) ሥራ የመሥራት መብት ያለውና መንግስታትም ለዚህ የግለሰቦች መብት መረጋገጥ ሕጋዊ ዕውቅና የመስጠት ግዴታ አለባቸው።[1] የዚህ አለም አቀፍ ስምምነት መነሻ እንደሆነ የሚቆጠረው ሁሉን አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ዲክላሬሽንም ቢሆን በዚህ ረገድ ከኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች አለም አቀፍ ስምምነት ይዘት ባልተናነሰ ሁኔታ ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሥራ የመስራት መብት ያለው ከመሆኑ ጀምሮ ሌሎች ከዚሁ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ሰፊ መብቶች ያሉት ከመሆኑም ባሻገር ሥራ-አጥ ከመሆን የመጠበቅ መብት ያለው መሆኑን ጨምሮ የሚያረጋግጡ ግልጽ የሆኑ ድንጋጌዎችን አካቷል።[2]

ይሁን እንጅ ከላይ ለጠቀስናቸው ሁለት አለም አቀፍ ስምምነቶችም ይሁን ለሌሎች ተዛማጅነት ላላቸው የአሠሪና ሠራተኛ ህጎች እነደ መነሻ ሆኖ የሚጠቀሰውና የአሠሪና ሠራተኛ ሕግን በተመለከተ የተለያዩና እጅግ በርካታ ዝቅተኛ የሥራ ሁኔታ መመዘኛዎችን/ስታንዳርዶች በማውጣት ለግለሰቦች ለመተዳደሪያቸው የመረጡትን ሥራ የመስራት መብትና በዚህም ምክንያት ተያይዘው ለሚመጡት መብቶችና ግዴታዎች መዳበር የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው ግን አለም አቀፉ የሥራ ድርጅት (International Labor Organization/ILO) መሆኑ ግልጽ ነው።[3]

---

[1] Article 6(1) of International Covenant on Economic, Social and Cultural Rights Adopted and opened for signature, ratification and accession by General Assembly resolution 2200A (XXI) of 16 December 1966, entry into force 3 January 1976 (Here in after will be mentioned as ICESCR.)

[2] Article 23 and 24 of Universal Declaration of Human Rights (UDHR), Adopted and proclaimed by General Assembly resolution 217 A (III) of December 10, 1948

[3] በ1919 እ.ኤ.አ በአለም ዙሪያ የሚገኙ ሰራተኞችን የስራ ስታንዳርድ ለማሻሻል አላማ ሲባል ከአሰሪና ሰራተኛ ጋር የተያያዙ አለም አቀፍ ስምምነቶችን እንዲያረቅ በቨርሳይለስ ፒስ ትራቲ የተቋቋመውና ስራውንም የሰራተኛ እናቶችን እንዲሁም የሴቶችን የማታ/የለሊት ስራዎችን በሚመለከት ቁጥር 3 እና 4 አለም አቀፍ ስምምነቶችን በማውጣት የጀመረውና 100ኛ አመቱን ያስቆጠረው አለም አቀፉ የስራ ድርጅት አባል ሀገራት በተለያዩ ጊዜያት አሰሪና ሰራተኛ ህጉን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ያደረጓቸው ስምምነቶችን መመልከቱ ለዚህ አንድ ማሳያ ሊሆን ይችላል። ይህ ድርጅት እስከ አሁን ድረስ 189 ያህል ከአሰሪና ሰራተኛ ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አለም አቀፍ ስምምነቶች እንዲኖሩ ያደረገ ከመሆኑም በላይ በአሁኑ ጊዜ የድርጅቱ አባል የሆኑም ይሁኑ አባል ያልሆኑ ሀገራትን ያለልዩነት የሚያስገድዱ ስምንት አለም አቀፍ ስምምነቶች ለአብነት ያህልም አስገድዶ ማሰራት የተከለከለ ስለመሆኑ፣ እድሜያቸው ለስራ ያልደረሱ ህጻናትን ማሰራት የተከለከለ መሆኑን፣ የሰራተኞች ማህበሮችን የማቋቋም መብትን እንዲሁም በሰራተኞች መካከል የሚደረግን የትኛውም አይነት ልዩነት የሚከለክሉት

ይህንን ሁኔታ በተመለከተ በአህጉራችን አፍሪካ ያለውን ሁኔታ ለመመልከት ስንሞክር ደግሞ ምንም እንኳ ከላይ እንደጠቀስነው አለም አቀፍ ስምምነት ሰፋ/ዘርዘር ያሉ ድንጋጌዎችን የያዘም ባይሆን ማንኛውም ሰው ተገቢና ምቹ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ሥራ የመስራት መብት ያለውና ለእኩል ሥራም እኩል ክፍያ ማግኘት የሚችል መሆኑን በግልጽ አስቀምጧል።[4] በተጨማሪም የቻርተሩ አባል ሀገራት በዚህ ቻርተር ለተቀመጡት መብቶችና ነጻነቶች እንዲሁም ግዴታዎች ህጋዊ ዕውቅና የመስጠትና ለውጤታማነታቸውም የተለያዩ ህግጋትን የማውጣት ወይም ሌሎች እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታዎች ያሉባቸው መሆኑን በማያሻማ አገላለጽ አስቀምጧል።[5]

ሀገራችን ኢትዮጵያም የዚህ አለም አቀፍ ስምምነት (ICESCR) ፈራሚና አጽዳቂ/ተቀባይ ሀገር እንደመሆኗ መጠን ከስምምነቱ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ስራ የመስራት መብት አለው"[6] በማለት አስቀምጧል። ከኢፌድሪ ሕገ-መንግስት በፊት የነበሩትን ህገ መንግስታት ለማየት ከሞከርንም ከላይ በተጠቀሰው ልክ ሰፊ የሆነ ሽፋን ተሰጥቶት ነበር ባይባልም በ1948 ዓ.ም ሕገ-መንግስት ማንኛውም ዜጋ በየትኛውም የሥራ ዘርፍ የመሰማራትና በሕግ አግባብም የሥራ ማህበራትን የመመስረትም ሆነ የመሳተፍ መብት ያለው መሆኑ በግልጽ ተካቷል።[7] በ1980 ዓ.ምቱ የደርግ ሕገ-መንግስትም ቢሆን ኢትዮጵያውያን የመስራት መብት እንዲሁም የእረፍት ጊዜ የማግኘት መብት ያላቸው ከመሆኑም በላይ መንግስት የሥራ ሰዓትን ከመወሰን ባሻገር ሀገሪቱ ያላትን የእድገት ደረጃ መሰረት ባደረገ ሁኔታ የስራ እድልን የማሳደግና ምቹ የስራ ሁኔታዎችን የመፍጠር ሀላፊነት ተጥሎበታል።[8] በዚህም መሰረት በሀገራችን ኢትዮጵያም የዜጎችን የመረጡትን ሥራ የመሥራትና ይህንኑ ተከትለው ሊመጡ የሚችሉትን ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ሰፊ መብቶችን ብሎም መብቶችን

ስምምነቶች ... ያሉት ሲሆን በዋናነትም ከስራ ጋር በተያያዘ መብቶች፣ በስራ ቦታ ተሳትፎ፣ በእኩልነት፣ በስራ ዋስትናና ከአስተዳደር ጋር የተያያዙ በድርጅቱ 187 አባል ሀገራት ላይ አስገዳጅነት ያላቸውና አሁን ላይ በስራ ላይ የሚገኙ ሌሎች 71 ስምምነቶች አሉት።

[4] Article 15 of African Charter on Human and Peoples' Rights, Adopted by the eighteenth Assembly of Heads of State and Government, June 1981, Nairobi, Kenya (Here in after will be mentioned as Africans Charter.)

[5] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 1።

[6] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 ዓ.ም አንቀጽ 41(1)፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 1፣ ነሀሴ 15 ቀን 1987 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ። (ከዚህ በኋላ የኢፌድሪ ህገ መንግስት ተብሎ የሚጠቀስ ይሆናል።)

[7] የተሻሻለው የኢትዮጵያ ህገ መንግስት አንቀጽ 47፣ ጥቅምት 24 ቀን 1948 ዓ.ም (4th November 1955 G.C)፣ አዲስ አበባ::

[8] የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህዝቦች ህገ መንግስት አንቀጽ 38 እና 39፣ ነጋሪት ጋዜጣ ቮሉዩም 47 ቁጥር 1፣ አዲስ አበባ 1980 ዓ.ም (12th September 1987 G.C)::

ለማግኘት ከዜጎች የሚጠበቁ ተነጻጻሪ ግዴታዎችን የሚያረጋግጡ ማለትም ሥራውን በሚሠራው ዜጋ/ግለሰብ እና ሥራውን በሚያሠራው አካል መካከል ሊኖር የሚችለውን የሥራ ግንኙነት ሊገዛ የሚችል ራሱን የቻለ የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ ወጥቶ በሥራ ላይ ይገኛል።[9] ይሁን እንጅ ከዚህ አሁን እየተሰራበት ካለው የአሠሪና ሠራተኛ ህጉ ቀደም ብሎ በ1952 ዓ.ም በወጣው የፍትሐብሄር ሕግ አንቀጽ 16 ተብሎ በተጠቀሰው ክፍል ውስጥ ከአንቀጽ/ከቁጥር 2512-2697 ድረስ የተለያዩ አይነት የሥራ ግንኙነቶችን የሚመለከቱ እጅግ በጣም በርካታ ድንጋጌዎችን የምናገኝ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።[10] ከዚህም በተጨማሪ በአጼ ሀይለስላሴ ግዜ የነበረው አዋጅ ቁጥር 210/1955 ዓ.ም፣ ይህንኑ አዋጅ የሻረውና በደርግ ዘመነ-መንግስት ጊዜ የነበረው አዋጅ ቁጥር 64/1968 ዓ.ም፣ አዋጅ ቁጥር 42/1985 ዓ.ም እና ማሻሻያው አዋጅ ቁጥር 88/1986 ዓ.ም[11] እንዲሁም ሌሎች በአገራችን አሁን ላይ ላለው የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት እንደ መነሻ ሊያገለግሉ የሚችሉ ሕጎች ናቸው።

በዚህ ጽሁፍ ለተነሳንበት አብይ ጉዳይ እንደመንደርደሪያ ያገለግለን ዘንድ ይህንን ያህል ካነሳን እንዲህ አይነቱን የሥራ ግንኙነት ተከትሎ የሚከሰቱ አለመግባባቶች ምንነትን እንዲሁም እነዚህ አለመግባባቶች/ክርክሮች የሚፈቱበትን ሁኔታ ደግሞ ምንም እንኳ ይህ ጽሁፍ ከተዘጋጀ በኋላ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ዓ.ም እና ማሻሻያዎቹን የሚተካ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ዓ.ም በኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቀን 27/10/2011 ዓ.ም ጸድቆ ከነሀሴ 30/2011 ዓ.ም ጀምሮ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በመውጣት ይህ ጽሁፍ ለህትመት ከመግባቱ ቀናት በፊት ስራ ላይ የዋለ ቢሆንም የዚህ ጽሁፍ ዋነኛ አላማ የቦርዱን አሰራር ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 ዓ.ም አንጻር መዳሰስ በመሆኑና ይህ መሆኑ ደግሞ በአዲስ አዋጅ መውጣት ብቻ ወዲያውኑ የሚቀየር ካለመሆኑ አንጻር ብዙም ለውጥ የማያመጣ መሆኑን በመገንዘብ በአዲሱ አዋጅ የተደረጉ መሰረታዊ ለውጦችን ጎን ለጎን በጨረፍታ በማንሳት የምንመለከት ይሆናል።

---

[9] የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ዓ.ም፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 12፣ የካቲት 18 ቀን 1996 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ። (ከዚህ በኋላ የቀድሞው አዋጅ በሚል የሚጠቀስ ይሆናል።) እንዲሁም ይህንን አዋጅ የተካው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ዓ.ም፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ 25ኛ አመት ቁጥር 89፣ ነሀሴ 30 ቀን 2011 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ። (ከዚህ በኋላ አዲሱ አዋጅ ተብሎ የሚጠቀስ ይሆናል።)

[10] የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የፍትሐብሄር ህግ፣ 1952 ዓ.ም፣ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 1/1952 ዓ.ም በተለይ የወጣ፣ አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ።

[11] Hiruy Wubie, the Settlement of Individual and Collective Labor Disputes under Ethiopian Labor Law, E-Journal of International and Comparative Labor Studies, University Press, Volume 2, No. 1 January 2013, p. 7. እንዲሁም ሳባ አበረ፣ የስራ ዋስትናን ከማስከበር አንጻር የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች ምዘና፣ የአማራ ክልል የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና ህግ ምርመር ኢንስቲትዩት የህግ መጽሔት፣ ቅጽ 2 ቁጥር 1፣ ገጽ 211

ክፍል ሁለት

የሥራ ክርክሮች ምንነትና የሚፈቱበት አግባብ

2.1 የሥራ ክርክሮች ምንነትና መነሻ ምክንያቶች

የሥራ ግንኙነቶቹ የግለሰብም ይሁኑ የወል መብቶችን፣ ከአንድ የሥራ ድርጅት፣ ከአንድ በላይ በሆኑ የሥራ ድርጅቶች፣ በክልልም ይሁን በፌዴራል/በሀገር አቀፍ ደረጃ ባሉ ድርጅቶች መካከል የሚነሱ መሆናቸው ግምት ውስጥ ሳይገባ በሠራተኞች፣ በአሠሪዎችና በስራ ድርጅቶች መካከል ለሚፈጠሩ አለመግባባቶች የጋራ የሆነ አንድና ትልቅ ምክንያት አላቸው፡፡ ይህ የጋራ የሆነው አወንታዊ ምክንያት መሰረቱ ድርጅቱን ለእድገትና ለትርፋማነት እንዲሁም ሠራተኞችን ደግሞ ደሞዝና የተለያዩ ጥቅማጥቅሞችን እንዲያገኙ የሚያደርገው የምርት ሂደት ውጤታማነት ሲሆን ለአለመግባባቱ ምንጭ የሆነው ደግሞ ምርታማና ውጤታማ የሆነው የድርጅቱን አሰራር ተከትሎ በሚገኘው ትርፍና ገቢ ክፍፍል ላይ የተንጠለጠለ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው፡፡ ይህንኑ ተጻራሪ የሆነ አላማ ለማሳካት ደግሞ በአንድ በኩል አሠሪዎች/ድርጅቶች ሠራተኞችን ከሥራ የመቀነስና የማባረር ያልተገደበ መብት እንዲኖራቸው ሲፈልጉ በሌላ በኩል ሰራተኞች ከዚህ አይነቱ ህገ-ወጥ አሰራሮች የመጠበቅ ፍላጎት አላቸው፡፡[12]

በዚህ አግባብ በአሠሪና ሠራተኛው መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች አስፈላጊ ያልሆኑ ግጭቶችን እንዳያስከትሉ እና የኢንዱስትሪውንም ሰላም ወደ ማወክ ደረጃ ከመድረሳቸው በፊት ከተቻለ በራሳቸው ካልተቻለ ደግሞ በአማራጭ በሶስተኛ ወገኖች (አስማሚዎች) ጣልቃ ገብነት በስምምነት እንዲያልቁ ይፈለጋል፡፡ ከዚህ አንጻር የሚነሱ ግጭቶችን በተሻለ ሁኔታ ለመፍታት በአንድ በኩል የተከራካሪ ወገኖችን (የሠራተኛውን፣ የአሠሪውን፣ የሠራተኞችን ማህበር፣ የአሠሪዎችን ማህበር፣ የሠራተኞች ማህበራት ፌደሬሽኖችን፣ የአሠሪዎች ማህበራት ፌደሬሽኖችን) ተፈጥሯዊ ባህሪያት ካላቸው የሀይል ሚዛን (position, technical competence and personality) እና ካሏቸው እሴቶች፣ በሌላ በኩል ደግሞ ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር (ፖለቲካዊ፣ ህጋዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ቴክኖሎጂያዊ እንዲሁም ማህበራዊና ባህላዊ ሀገራዊ

[12] Guidelines for improved performance Labor Dispute Systems, International Training Center of the ILO, p 6 Available at፡- https://www.ilo.org/ifpdial/informationresources/publications/WCMS.../index.htm accessed on 22 January, 2019 GC.

ሁኔታዎች) በአሠሪውና በሠራተኛው መካከል የተነሳውን አለመግባባት መመርመር ያስፈልጋል።[13]

በአንድም ይሁን በሌላ ምክንያት በአሠሪውና በሠራተኛው መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ደግሞ ***የግል የሥራ ክርክር*** (አንድ ሠራተኛ ተግባራዊ እያደረጋቸው ያሉትን መብቶች በተመለከተ ከአሠሪው ጋር የሚፈጥራቸውን አለመግባባቶችን የሚመለከት ሲሆን በዚሁ አለመግባባት በፈጠረው ጉዳይ ላይ ከአንድ በላይ የሆኑ ሠራተኞችም ራሳቸውን ችለው በግለሰብ ደረጃ የሚያነሱት ክርክር) አልያም ***የወል የሥራ ክርክር*** (ሁልግዜ ባይሆንም በአብዛኛው ሠራተኞች በጋራ አሁን ላይ ያላቸውን መብት ወይም ለወደፊት እንዲኖራቸው የሚፈልጓቸውን ጥቅሞች/መብቶች በተመለከተ በሠራተኛ ማህበራት በመወከል ከአሠሪው/ዎች ጋር የሚፈጥሯቸውን አለመግባባቶች) በሚል በሁለት አይነት ልንከፍላቸው እንችላለን።[14] ከዚህም በተጨማሪ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የሚፈጠሩት አለመግባባቶች ***የመብት ክርክሮች*** (በሠራተኛ/ዎች እና በአሠሪ መካከል በህግ፣ በህብረት ስምምነት ወይም በሥራ ውል የተካተቱ መብቶች ተጥሰዋል በሚል የሚቀርቡና አለመግባባት የተፈጠረባቸው ጉዳዮችም ከደመወዝ፣ ከትርፍ ሰዓት ክፍያ፣ ከበአላት ቀን እረፍት እንዲሁም ከምቹ የሥራ ሁኔታዎች ጋር የተገናኙና የግል ወይም የወል የሥራ ክርክሮች ሊሆኑ ይችላሉ።) እንዲሁም ***የፍላጎት/የጥቅም ክርክሮች*** (በሠራተኞችና በአሠሪው መካከል በተለይ የሥራ ውሎች ወደፊት በሚያስከትሉት መብትና ግዴታ ዙሪያ በሚደረገው የድርድር ሂደት አለመስማማትን ተከትሎ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን መሰረት ያደረጉ ሲሆን በባህሪያቸውም የወል የሥራ ክርክሮች ናቸው።) በሚል የሚደረጉ ክፍፍሎችም ያሉ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።[15]

2.2 የሥራ ክርክሮች የሚፈቱባቸው መንገዶች

በሠራተኛውና በአሠሪው መካከል ያለውን የሥራ ግንኙነት የተሻለና ጠንካራ በማድረግ በመካከላቸው ያለውን መተማመን ከማስቀጠል ባሻገር የኢንዱስትሪውን ሰላም ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ በሥራ ቦታዎች በተለይም ከክፍያና ጥቅማጥቅም፣ ከሥራ ቦታ ጤንነትና ደህንነት፣ ከሥራ ውል መቋረጥ፣ ህገ-ወጥ ልዩነትን ከሚፈጥሩ አሰራሮች እንዲሁም ከስራ ጋር የተገናኙ መሰረታዊ መብቶች ጋር የተያያዙ አለመግባባቶች እንዳይፈጠሩ ከተፈጠሩም

[13] ዝኒ ከማሁ ገጽ 7-11
[14] ዝኒ ከማሁ ገጽ 18
[15] ዝኒ ከማሁ

እንዳይባባሱ በማድረግ ረገድ ቀዳሚው ሀላፊነትም ሆነ ስልጣኑ የራሳቸው የተዋዋይ ወገኖች መሆኑ ይታወቃል። ይሁን እንጅ አለመግባቶች ከመጀመሪያውም ሙሉ በሙሉ እንዳይፈጠሩ ለማድረግ የማይቻል ከመሆኑ አንጻር በራሳቸው በተዋዋይ ወገኖች (በድርጅቱ) አማካኝነት እንዲፈቱ ማድረግ ያስፈልጋል[16]።

ያም ሆኖ ግን በራሳቸው በተዋዋይ ወገኖች የጋራ መግባባት መፈታት የማይችሉ ችግሮች ከመኖራቸው የተነሳ እንዲህ አይነቶቹን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ የተለያዩ አሠራሮች መዘርጋታቸው ግድ ነው። በመሆኑም ከአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነቶች ጋር የተያያዙ አለመግባባቶች እንደዬ ተዋዋይ ወገኖች ፍላጎትና ምርጫ እንዲሁም ህብረት ስምምነቶች/ሕጎች እንደሚፈቅዱት አግባብ ከተቻለ በራሳቸው በስምምነት /በድርድር ካልሆነ በሶስተኛ ወገኖች/ተቋማት ጣልቃ ገብነት በሽምግልና ወይም በዕርቅ የሚፈቱበት አግባብ ይኖራል። ነገር ግን አልፎ አልፎም ቢሆን እነዚህ ሁሉ አማራጮች ተሞክረው የማይፈቱ ችግሮች ሲያጋጥሙ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በአሠሪና ሠራተኛ ልዩ ፍርድ ቤቶች አለመግባባቶችን መፍታቱ የተለመደና ህጋዊም አሰራር ነው። በዚህም የተነሳ በመካከላቸው የተፈጠረውን አለመግባባት ለመቋጨት ተዋዋይ ወገኖቹ ጉዳያቸውን በዚህ አይነቱ መደበኛ፣ ህጋዊ፣ ወጭም ሆነ ጊዜ ቆጣቢ ወዳልሆነ እንዲሁም ሁለቱንም ተከራካሪ ወገኖች ሊያስደስት የማይችል ውሳኔ ሊሰጥ ወደሚችል የክርክር ሂደት እንዲወስዱ ይገደዳሉ።[17]

በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የሚፈጠርን አለመግባባት/ክርክር ከመፍታት አንጻር የአለም አቀፉ የሥራ ድርጅት አለመግባባቶች የሚፈቱበትን ስርዓት ውጤታማነት ለማሻሻል ያስችላል ያለውንና ቀደም ሲል የተጠቀሰውን የአሠራር ማኑዋለ (Guidline) ከማውጣቱ በፊት አለመግባባቶች የሚፈቱባቸው መንገዶችን ውጤታማነት ለመመዘን የሚያስችሉ ሁለት የተለያዩ መመሪያዎችን (Recommendations)[18] አውጥቶ ሥራ ላይ አውሎ የነበር መሆኑ ይታወቃል። በዚህም መሰረት መመሪያዎቹ ከአሠሪና ሠራተኛ ጋር በተያያዘ የሚፈቱ አለመግባባቶች አፈታት ሥርዓት ውጤታማነትን ለመመዘን የሚያስችሉ መርሆዎችን እና የአሠራር ስልቶችን

[16] ዝኒ ከማሁ
[17] ዝኒ ከማሁ ገጽ 189
[18] R130-Examination of Grievance Recommendation 1967 (No. 130); And R092-Voluntary Concilation and Arbitration Recommendation 1951 (No. 92), Geneva.
Available at https://www.ilo.org/dyn/normlex/en/f?p=1000:12020:::NO: Accessed on 7/10/2019.

አስቀምጠዋል።[19] ከዚህም ባሻገር በተለይ የወል የሥራ ክርክሮች ምንጭ የሚሆነውን በአሠሪዎችና ሠራተኞች (ተወካዮች) መካከል የሚደረገው የህብረት ስምምነትን የሚመለከቱ የተለያዩ አለም አቀፍ ስምምነቶችን ከ1949 እ.ኤ.አ. ጀምሮ (Conventions) እና መመሪያዎችን (Recommendations) አውጥቶ ሥራ ላይ ማዋሉንም መገንዘብ ይቻላል።[20]

በመሆኑም እንደ አለም አቀፉ የሥራ ድርጅት እሳቤ መሰረት አለመግባባትን በመፍታት ሂደት ላይ የሚኖረው የሠራተኞች እና የአሠሪዎች ተሳትፎ በእኩልነት መርህ ላይ መመስረት ተገቢነት የማዕዘን ድንጋይ መሆኑ በቅድሚያ ሲቀመጥ፣ የሚከሰቱ አለመግባባቶችን በመቀነስ መርህ ላይ ትኩረት በመስጠት በመግባባት እና በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ መፍትሄ ማግኘት ተገቢ በመሆኑ ለዚህም የግራ ቀኙ ተሳትፎ ወሳኝነት በሁለተኛ መስፈርትነት ሲሰፍር በመጨረሻም በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረቱት አለመግባባትን የመፍታት የሽምግልና/የዕርቅ ሂደቶች ከክፍያ ነጻ እንዲሁም ፈጣን እና ውጤታማ መሆን ያለባቸው መሆኑን ከመመሪያዎች መረዳት ይቻላል።[21] አለመግባባቶች የሚፈቱበት መንገድ ከየሀገራቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር መጣጣም ያለበት እንደመሆኑ መጠን ሁኔታዎቹ ከሀገር ሀገር የሚለያዩ ቢሆንም ቅሉ በዋነኝነት በሶስት ዋና ዋና መንገዶች የሚመደብ መሆኑን ለማየት ይቻላል።[22] በዚህም መሰረት በተለይም የግልግል እና ዕርቅ ሂደቶች በአሠሪና ሠራተኛ ምኒስቴር/ዲፓርትመንት አማካኝነት እንደ ሌሎቹ የመንግስት አገልግሎት አካል ተወስዶ አለመግባባቶችን የመከላከል እና የመፍታት ሀላፊነቱ ለዚሁ ለሚመለከተው የመንግስት አካል የሚሰጥበት አንደኛው መንገድ ነው። ይህ አይነቱ አሠራርም በአብዛኛው በአፍሪካ፣ በኤዢያ፣ በአውሮፓ፣ በአረብ እንዲሁም በአሜሪካን ሀገራት የተለመደ ነው።[23] አለመግባባቶችን የመከላከል እና የመፍታት ሥራዎችን የሚሠሩ ነጻና በሕግ የተቋቋሙ አካላት መኖራቸው ደግሞ ሌላውና ሁለተኛው አይነት ነው። በመሆኑም አለመግባባቶችን የመከላከሉ እና የመፍታቱ ሀላፊነት ነጻ እና ገለልተኛ እንዲሁም የመወሰን

---

[19] Corinne Lewis, Reflection on ILO; How can the effectiveness of dispute resolution system be assessed? Best practices in resolving employment disputes in international organizations. Conference proceedings, ILO, 15-16 September 2014
Availiable at https://www.ilo.org/dyn/normlex/en/f?p=1000:12020:::NO:: Accessed on 8/10/2019.

[20] C098 - Right to Organize and Collective Bargaining Convention, 1949 (No. 98) Geneva, 32nd ILC session on 01 Julay 1949; C154 - Collective Bargaining Convention 1981 (No. 154) Geneva, 67th ILC session on 03 June 1981; And R163 - Collective Bargaining Recommendation, 1981 (No. 163) Geneva, 67th ILC session on 19 June 1981.
Avialable at https://www.ilo.org/dyn/normlex/en/f?p=1000:12020:::NO::: Accessed on 7/10/2019.

[21] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 19

[22] ዝኒ ከማሁ ገጽ 28

[23] ዝኒ ከማሁ ገጽ 28-29

ሙሉ ስልጣን ባላቸው እና በራሳቸው ሕግ የሚተዳደሩ እና ራሱን በቻለ የአስተዳደር አካል ወይም ቦርድ የሚመሩ ኮሚሽኖች እና ባለስልጣን ተቋማት ላይ ያረፈ ይሆናል። የአሜሪካ የፌደራል የሽምግልና እና እርቅ አገልግሎት፣ የእንግሊዙ የግልግል እና ዕርቅ ማማከር አገልግለሎት፣ በቅርቡ የተቋቋመው የደቡብ አፍሪካውን የግልግል፣ ሽምግልና እና የዕርቅ ኮሚሽን፣ የጋና ብሄራዊ የአሠሪና ሠራተኛ ኮሚሽን እንዲሁም የታንዛኒያ የሽምግልና እና የግልግል ኮሚሽኖች በዚህ ረገድ ለአብነት ተጠቃሾች ናቸው።[24] ሌላውና ሶስተኛው ደግሞ የሚመለከተው የመንግስት አካል እና ገለልተኛ ተቋማት በቅንጅት ሥራዎችን የሚሠሩበት ሁኔታ ነው። በተለይም በዚህ አይነቱ የአሠራር ዘዴ የሠራተኞች እና የአሠሪዎች ማህበራት በብዛት የሚሳተፉበት ሁኔታ ከፍተኛ ነው። ይህ አይነቱ አሠራር በስፔን፣ በካምቦዲያ እንዲሁም በቤልጅየም ሀገራት የተለመደ ነው።[25]

በግለሰቦችም ይሁን በድርጅቶች ወይም በግለሰቦችና በድርጅቶች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በተመለከተ የኢፌድሪ ሕገ-መንግስት ነጻ የዳኝነት አካል ከማቋቋም ባለፈ የዳኝነት ስልጣኑም የፍርድ ቤቶች ብቻ እንደሆነ በግልጽ አስቀምጧል።[26] በመሆኑም በፌደራልም ይሁን በክልል ደረጃ የዳኝነት ስልጣኑ የፍርድ ቤቶች እንደሆነ ተመላክቷል። ይሁን እንጅ ሕገ-መንግስቱ በራሱ ይህንን ነጻ የዳኝነት ስልጣን ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ባሻገር በሕግ አግባብ ለሚቋቋሙ ሌሎች ተቋማትም በተጨማሪነት ሰጥቷል።[27]

ከዚህ አንጻር የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነትን ተከትሎ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችም በራሳቸው በባለጉዳዮቹ ወይም ራሳቸው በሚመርጧቸው ሶስተኛ ወገኖች ጣልቃ-ገብነት በስምምነት መፈታት ካልቻሉ በዚሁ ሕገ መንግስቱ ባስቀመጠው አግባብ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች እንዲሁም ጉዳዩን ለመዳኘት በሕግ አግባብ በተቋቋመ ቦርድ አማካኝነት እንደ አግባብነታቸው ይፈታሉ።[28] በዚህም መሰረት የአሠሪና ሠራተኛ ህጉን ተከትለው የሚነሱ አለመግባባቶች በስምምነት ማለቅ ሳይችሉ ቀርተው ወደ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም ወደ አሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርዶች የሚሄዱ ከሆነ የትኞቹ ጉዳዮች በቦርዱ የትኞቹ ጉዳዮችስ በፍርድ ቤቶች አማካኝነት ይዳኛሉ?

---

[24] ዝኒ ከማሁ

[25] ዝኒ ከማሁ ገጽ 29

[26] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 6 አንቀጽ 78(1) እና አንቀጽ 79(1)

[27] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 78(4)

[28] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9 አንቀጽ 136-156፣ እንዲሁም በአዲሱ አዋጅ ከአንቀጽ 137-162 ድረስ እንደተካተተው። (እንደ አዲሱ አዋጅ ከሆነ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በቀድሞው አዋጅ "በአስማሚ የሚፈቱበት ሁኔታ" የሚለውን *"በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች መፍታት የሚቻልበት ሁኔታ"* በሚል በግልጽ ተካቷል። አንቀጽ 141 እና ተከታዮቹ።)

ከሚለውም ባለፈ በየትኛው ቦርድና በየትኛው ፍርድ ቤትስ ነው? የሚለው ጥያቄም ሌላው መልስ ሊያገኝ የሚገባው ጉዳይ ነው።

በዚህም መሰረት የመደበኛ ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎቶች እንዲሁም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርዶች የተሰጧቸውን የዳኝነት ስልጣኖች ቀጥለን እንመለከታለን።

2.2.1 በመደበኛ ፍ/ቤቶች የሚዳኙ ጉዳዮች

በልዩ ሁኔታ ጉዳዮቹ በፍ/ቤት እንዳይታዩ የተከለከሉ ወይም ጉዳዮችን ለመመልከት ሌሎች አካላት የተቋቋሙ እስካልሆነ ድረስ በግለሰቦችና ግለሰቦች፣ በግለሰቦችና በድርጅቶች እንዲሁም በድርጅቶችና በድርጅቶች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በራሳቸው በባለጉዳዮች አልያም እነሱ በሚመርጧቸው ሌሎች ሶስተኛ ወገኖች አማካኝነት መፈታት ካልቻሉ ጉዳዮችን ለሚመለከታቸው መደበኛ ፍርድ ቤቶች ወስደው ፍትህን የሚያገኙ መሆኑ ሕገ-መንግስታዊ መብት መሆኑ ግልጽ ነው። በዚህ አግባብ በአሠሪና በሠራተኛ መካከል ከሚፈጠሩ አለመግባባቶች መካከል ከዚህ ቀጥለው የተዘረዘሩት ጉዳዮች የግል የሥራ ክርክር በመሆናቸው ምክንያት በእነዚሁ መደበኛ ፍርድ ቤቶች በቀጥታ ቀርበው የሚፈቱበት ህጋዊ ሥርዓት ተቀምጧል። ይሁን እንጅ ፍርድ ቤቶች በይግባኝ እና በሰበር ስልጣናቸው የወል የሥራ ክርክር በመሆናቸው ምክንያት በቀጥታ በቦርድ ቀርበው የሚታዩትን ጉዳዮችም የሚያዩ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል።

2.2.1.1 የመጀመሪያ ደረጃ/የወረዳ ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን[29]

የክልል ወረዳ ፍ/ቤቶች፡- የደሞዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን፣ ከሥራ ማስወጣትን ጨምሮ ሌሎች የዲሲፕሊን እርምጃዎችን፣ የሥራ ውል መቋረጥ/መሰረዝ፣ የሥራ ሰዓትን፣ የተከፋይ ሂሳብን፣ ፈቃድንና ዕረፍትን፣ የቅጥርና የስንብት ማስረጃ ሰርተፍኬት መስጠትን፣ የጉዳት ካሳን እና በዚህ አዋጅ በሌላ አኳኋን ካልተመለከተ በስተቀር በዚህ አዋጅ መሰረት የሚቀርብ ማናቸውም የወንጀልና ደንብ መተላለፍን የሚመለከቱ ክሶችን የመዳኘት ስልጣን ተሰጥቷቸዋል። *(ይሁን እንጅ በአዲሱ አዋጅ አንቀጽ 139(1)(ሠ) መሰረት የደረጃ ዕድገትን፣ ዝውውርን፣ ስልጠናና የመሳሰሉትን የሚመለከቱ ጉዳዮችንም የመዳኘት ስልጣንም ተሰጥቶታል።)*

[29] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 138(1) (አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 139)

2.2.1.2 የይግባኝ ሰሚ/ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን[30]

ከአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የይግባኝ ስልጣን ብቻ ነው ያላቸው። በዚህም መሰረት፡- የመጀመሪያ ደረጃ/የወረዳ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም፣ አንድን ጉዳይ ለማየት ያለውን ስልጣን በመቃወም፣ የማህበር ምዝገባን/ስረዛን በመቃወም ምኒስቴሩ የሚሰጠውን ውሳኔ በመቃወም፣ የሥራ ሁኔታ ተቆጣጣሪ የሚሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም እንዲሁም በአንቀጽ 20(3) መሰረት /መብትና ግዴታዎችን ለጊዜው ማገድን ተከትሎ/ ምኒስቴሩ (በክልል ደረጃ ደግሞ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ) የሚሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የሚቀርቡ ይግባኞችን የማየት ስልጣን አላቸው። *(ይሁን እንጅ በአዲሱ አዋጅ አንቀጽ 140(1)(ሰ) መሰረት የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ በሰጠው ውሳኔ **የህግ ነጥብ** ላይ የሚቀርብ ይግባኝም ለዚሁ ፍ/ቤት ተሰጥቷል።)*

ከዚህም በተጨማሪ ይግባኝ ሰሚው /ከፍተኛ/ ፍ/ቤት በይግባኝ አይቶ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው።[31]

2.2.2 በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርዶች የሚታዩ ጉዳዮች

ከዚህ በላይ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች እንዲታዩ ከተቀመጡት በአሠሪና ሠራተኛ መካከል ከሚፈጠሩ አለመግባባቶች መካከል ደግሞ ከዚህ ቀጥለው የተመለከቱት የወል የሥራ ክርክሮች በይግባኝ ወይም በሰበር ወደ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ሊሄዱ የሚችሉበት ሁኔታም መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ በመደበኛው ፍርድ ቤት ከሚታዩ ጉዳዮች በተለየ ሁኔታ ጉዳዮቹ ካላቸው ልዩ ባህሪ የተነሳ ከጉዳዩ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ከፍተኛ ልምድ እና ልዩ ዕውቀት ባላቸው ባለሙያዎች እንዲታዩና ይበልጥ ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንዲቋጩ በማሰብ ለዚሁ ተብለው በተቋቋሙ ቦርዶች እንዲታዩ ተደርገዋል።

2.2.2.1 የጊዜያዊ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች ወሳኝ ቦርድ ስልጣን

ጊዜያዊ ቦርዱ የአየር መንገድ አገልግሎት፣ የኤሌክትሪክ መብራትና ሀይል አገልግሎት፣ የውሃና የከተማ ጽዳት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት፣ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት፣ ሆስፒታሎች፣ ክሊኒኮች፣ የመድሀኒት ማከፋፈያ ድርጅቶችና የመድሀኒት መሸጫ ቤቶች፣

[30] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 139 (አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 140)
[31] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 139(2) (አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 140(2))

የእሳት አደጋ አገልግሎት እና የቴሌ ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ድርጅቶችን በተመለከተ የሚነሱ የደሞዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የማየት ስልጣን አለው።[32] *(በአዲሱ አዋጅ አንቀጽ 137(2)(መ) መሰረት የከተማ ቀላል ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ተጨምሯል።)*

2.2.3.2 የቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች ወሳኝ ቦርድ ስልጣን[33]

ጉዳዮች በቅድሚያ በአስማሚው አካል ታይተው ካልተፈቱ በአንቀጽ 136 *(በአዲሱ አዋጅ አንቀጽ 137)* ላይ የተመለከቱትን (ህዝባዊ አገልግሎት የሚሰጡ) ድርጅቶች ጨምሮ ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች ወሳኝ ቦርድ የሚከተሉትን ጉዳዮች ተቀብሎ የማከራከርና የመወሰን ስልጣን ተሰጥቶታል። እነዚህም፡- አዲስ የስራ ሁኔታዎችን መመስረት፣ የህብረት ስምምነት መዋዋልን፣ ማሻሻልን፣ ፀንቶ የሚቆይበትንና የሚፈርስበትን፣ በህ/ስምምነት /በሥራ ደንብ/ ድንጋጌዎች ላይ የሚነሱ የትርጉም ክርክሮች፣ የሠራተኞች አቀጣጠር፣ ዕድገት አሰጣጥን እና ስልጠና፣ አጠቃላይ የሠራተኞችንና የድርጅቱን ህልውና የሚነኩ ጉዳዮች፣ ዕድገትን፣ ዝውውርንና ስልጠናን በተመለከተ አሠሪው የሚወስዳቸውን ዕርምጃዎች *(በአዲሱ አዋጅ አንቀጽ 143(1)(ሰ) መሰረት ዕድገት፣ ዝውውርና ስልጠናን አስመልክቶ አሠሪው በሚያወጣቸው የአፈጻጸም ስርዓቶች ላይ የሚቀርቡ ክሶች በሚል ተገልጿል።)*፣ የሠራተኞችን ቅነሳ እንዲሁም በአንቀጽ 160 *(በአዲሱ አዋጅ አንቀጽ 161)* ላይ የተመለከቱትን ህገ-ወጥ ተግባራት (ከውሳኔ በፊት የሚደረግን የሥራ ማቆም/መዝጋትን፣ የተሰጠን ውሳኔ ላለመፈጸም የሚደረግ እምቢተኝነትን/የሥራ ማቆምን) በተመለከተ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ቋሚ ቦርዱ የማየት የስረ-ነገር ስልጣን ይኖረዋል።

ሌላው መረሳት የሌለበት ነገር ቢኖር በእነዚህ ቦርዶች ማለትም በቋሚም ይሁን በጊዜያዊ ቦርዶች በክርክር ሂደት የተረጋገጡ ፍሬ-ነገሮች ሁሉ የመጨረሻ በመሆናቸው በይግባኝ ችሎቱ ክርክር የማይነሳባቸው መሆኑ ነው።[34]

---

[32] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 136፣ 142(3)፣ 147(2) *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 139፣ 143(2) እና 148(2))*፣ እንዲሁም *(ምንምኳ በአዲሱ አዋጅ የተሻረ ቢሆንም)* የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 466/1997 ዓ.ም አንቀጽ 2(1) እና (2))፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አስረኛ አመት ቁጥር 56፣ ሰኔ 23 ቀን 1997 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።

[33] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9 አንቀጽ 142(1) እና አንቀጽ 147(1) *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 143(1) እና 148(1))*

[34] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 153 *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 154)*

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች በግል ስምምነት/በአስማሚ ጥረት መቋጨት ካልቻሉና ወደ ሥራ ክርክር ችሎቶች መምጣታቸው የግድ ከሆነ ጉዳዮችን የሚዳኙ አካላትን ማንነት ለመወሰን ግምት ውስጥ የሚገባው የቀረበው ጉዳይ ***የግል*** አልያም ***የወል የሥራ ክርክር*** መሆኑን መሰረት በማድረግ ብቻ ነው። በዚህም መሰረት ጉዳዩ የግል የሥራ ክርክር ከሆነ መደበኛ ፍ/ቤቶች እንዲሁም ጉዳዩ የወል የሥራ ክርክር ከሆነ ደግሞ የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርዶች ስልጣን ይኖራቸዋል። በዚህ ረገድ ጉዳዩ የቀረበላቸውና የመዳኘት ስልጣን የተሰጣቸው አካላት የቀረበው ጉዳይ በቅድሚያ በአዋጁ የሚሸፈን መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ የመዳኘት ስልጣን ያላቸው መሆን አለመሆኑን የሚወስኑት በአዋጁ[35] መሰረት የግል አልያም የወል የሥራ ክርክር መሆኑን በማረጋገጥ ብቻ ይሆናል ማለት ነው።

ይሁን እንጅ የሥራ ክርክሮችን የግል ወይም የወል በሚል ለመክፈል በክርክሩ ውስጥ የሚሳተፉትን ሠራተኞች ቁጥርም ሆነ በእነዚህ ድንጋጌዎች በተቀመጠው ክፍፍል መሰረት ለመለየት ቀላልም ተገቢም አይሆንም። ይልቁንስ የሥራ ክርክሮች ይዘውት የመጡትን ጉዳይ እንደዬ ሁኔታው በማየት መክፈሉ ተገቢና ለቀረቡት ጉዳዮች ትክክለኛ መፍትሔ ለመስጠት ያስችላል። ለምን ቢባል አንድ ሠራተኛ ይዞት የቀረበው የሥራ ክርክር ሌሎች ሠራተኞችን ሊነካ የሚችልበት ሁኔታም ሆነ በአዋጁ አንቀጽ 138(1) ከፊደል (ሀ-ረ) ድረስ የተዘረዘሩትና የግል የሥራ ክርክር ተብለው የተለዩት ጉዳዮች በሂደት ሌሎቹ ሠራተኞችንም በጥቅል የሚነኩ ሆነው በአንቀጽ 142(1) ከፊደል (ሀ-ሸ) ድረስ የወል የሥራ ክርክሮች ተብለው የተለዩትን ጉዳዮች የሚመለከቱበትን አጋጣሚ ሊፈጥሩ የሚችሉበት ሁኔታ ዝግ አይደለም። ከዚህም ባሻገር በአንቀጽ 138ም ሆነ በአንቀጽ 142 *(በአዲሱ አዋጅ አንቀጽ 139 እና 143)* የተቀመጡት የግልም ይሁን የወል የሥራ ክርክሮች ለማሳያነት የተጠቀሱ እንጅ ብቸኛ አለመሆናቸውንም ድንጋጌዎች በግልጽ "...ከዚህ በታች የተመለከቱትንና ሌሎች ተመሳሳይ የግል/የወል የሥራ ክርክር ጉዳዮች..." በሚል ያስቀምጣሉ።[36] የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በዚህ ረገድ ያለውን አቋም ለማየት ብንሞክር የምናገኘው ከዚህ የተለዬ አይደለም። እንደ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ፦

> *"የወል የሚለው ቃል አገላለጽ የጋራ የሆነ ጉዳይ መኖሩን ለማመልከት ያህል የሚበቃ መሆኑም እርግጥ ነው። ይሁን እንጂ የወሉን ከግል ለመለየት የተከራካሪዎቹን ሠራተኞች ቁጥር እንደመለያ መስፈርት መውሰድ እንደምንችል የሚጠቁመን የሕግ*

[35] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 138 እና 142 *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 139 እና 143)*
[36] ዝኒ ከማሁ

ድንጋጌ የለም። ይህ ደግሞ ሕጉ ሁለቱን ክርክሮች ለመለየት የፈለገበትን ሌላ መንገድ እንድንፈትሽ ያደርገናል። ለዚህም ሁለቱ የክርክር አይነቶች በምሣሌነት በተናጥል የተዘረዘሩበትን የአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 142/1/ን እና 138/1/ን መሠረት ማድረጉ አሳማኝነት ያለው መደምደሚያ ላይ እንድንደርስ ይጠቅመናል። **በማለት የድንጋጌውን ይዘት ካስቀመጠ በኋላ እንደዚሁም አብዛኛዎቹ የድንጋጌው ክፍሎች በውጤታቸው የሁሉንም ሠራተኞች መብትና ጥቅም የሚመለከቱ ጉዳዮችን ያቀፉ መሆናቸውን በግልጽ አመላክተውናል።** *ለምሣሌነት በንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/፣ /ለ/፣ /ሐ/፣ /ሠ/፣ /ረ/ እና /ሸ/ የተጠቀሱትን የሥራ ክርክር አይነቶች መመልከት ይቻላል። እነዚህ የድንጋጌው አብዛኛው ንዑስ አንቀጾች ክርክሩ የወል ለመባል የጋራ የሆነን የሠራተኞቹን መብትና ጥቅም የሚመለከት ሊሆን እንደሚገባ በግልጽ ካሣዩን ደግሞ በቀሪዎቹ ንዑስ አንቀጾች ላይ የተጠቀሱትንና ሌሎችንም በድንጋጌው ያልተካተቱትን ተመሳሳይ የሥራ ክርክሮችን የወልነት ፀባይ ከሠራተኞቹ የጋራ መብትና ጥቅም ጋር ካለው ግንኙነት አኳያ ልንመዘነው የሚገባን ይሆናል። ስለሆነም ጥያቄው የደመወዝም ሆነ የሥልጠና፣ የሕግ ትርጉም ነክም ሆነ ወይም ሌላ የወል የሚሰኘው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ሊሆን ይገባዋል። በሚል አሁንም የድንጋጌውን ዝርዝር ካስቀመጠ በኋላ የዚህ ድንጋጌ ይዘት ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ድንጋጌ የጋራ የሆነን የሠራተኞች ጉዳይ እንደሚያጠቃልል የሚገልጽ አይደለም። ስለሆነም ሥራ ክርክሩ በእነዚህ በተዘረዘሩትም ሆነ በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ተመስርቶ ሲቀርብ ከግል አልፎ በጋራ መብት ላይ የሚያመጣው ለውጥ ያለመኖሩ ጉዳይ ክርክሩን የወል ሳይሆን የግል የሥራ ክርክር እንዲሆን ያደርገዋል። እንግዲህ አንድ የሥራ ክርክር በአንድ ወይም በብዙ ሠራተኞች መቅረቡ ጉዳዩ የወል ወይም የግል የሥራ ክርክር መሆኑን የሚያረጋግጥልን አይደለም። ይልቁንም ክርክሩ የወል መሆኑን የሚያሳየን ውጤቱ ከግል አልፎ የሠራተኞቹን የጋራ መብትና ጥቅም የሚነካ የመሆኑ ጉዳይ ሲሆን ክርክሩ የግል ነው የምንለው ደግሞ ውጤቱ በተከራካሪው ሠራተኛ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሆኖ ስናገኘው ነው።*[37] **በማለት ካብራራ በኋላ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ሰጥቷል።**

ከዚህም ባሻገር የግል የሥራ ክርክሮች በሂደት የወል የሥራ ክርክሮች ሆነው ሊመጡ የሚችሉበት አግባብ ከመኖሩም በተጨማሪ የወል የሥራ ክርክሮችም በሂደት የግል የሥራ

[37] የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች የኬኬ ብርድ ልብስ ፋብሪካ መሰረታዊ የሰራተኞች ማህበር (56 ሰዎች) ወኪል ሰይድ ሀሚድ እና በተጠሪ የኬኬ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ፣ የሰ/መ/ቁ/ 18180፣ ቅጽ 1፣ ሀምሌ 29 ቀን 1997 ዓ.ም።

ክርክር ሊሆኑ የሚችሉበት አጋጣሚ መኖሩንም ጭምር የሚደግፉ ባለሞያዎች[38] መኖራቸው በእርግጥም በግል እና በወል የሥራ ክርክሮች መካከል ያለውን ልዩነት በቀላሉ ላለማስቀመጥ በቂ ማሳያ ነው። ለአብነት ያህል ከቅጥርና ከደረጃ ዕድገት ጋር የተገናኙ አለመግባባቶችን (ክርክሮችን) ለመፍታት ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ የስረ-ነገር ስልጣን ያለው መሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 142(ሠ) ድንጋጌ በቀላሉ መረዳት ይቻላል። ይሁን እንጅ ይህ የቅጥርና የደረጃ ዕድገት አሰጣጥ ሂደቱ/ስርዓቱ ከተዘረጋ በኋላ እያንዳንዱ ተወዳዳሪ/ሠራተኛ በግሉ የደረጃ ዕድገት/ቅጥር ተከለከልኩኝ በሚል የሚያነሳው ጉዳይ ይህንኑ ሰው ብቻ እንጅ ሌሎችን የሚመለከት ባለመሆኑ የወል ሳይሆን የግል የሥራ ክርክር ሊሆን ይገባዋል የሚል ነው።[39] ይሁን እንጅ ክርክርሩን ያቀረበው ሠራተኛ አንድ ብቻውን ቢሆንም እንኳ ለክርክሩ ምክንያት መነሻ የሚሆነው ይሔው የወል የሥራ ክርክር የሆነው የደረጃና ዕድገት አሰጣጥ ሥርዓት ከመሆኑም በላይ ለክርክሩም ቢሆን መንስዔ የሚሆነው ይሔው የደረጃና ዕድገት ሥርዓት በአንድም ይሁን በሌላ ሁኔታ ተጥሶ መብቱ ተነፍጎብኛል የሚል ይዘትን መሰረት ያደረገ ነው። ከዚህም በላይ ምንም እንኳ ክርክሩን ያነሳው አንድ ሠራተኛ ብቻ ቢሆንም የክርክሩ ዋና ማጠንጠኛ የሚሆነው የድርጅቱ የደረጃና የዕድገት አሰጣጥ ሥርዓቱ ነው። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ ሠራተኛው የደረጃ ዕድገት መከልከሉ ከደረጃና ዕድገት አሰጣጥ ሥርዓቱ/መመሪያው አንጻር ታይቶ እልባት የሚያገኝ እንጅ ከዚህ ተነጥሎ የሚታይም ሆነ ምላሽ የሚያገኝ አይሆንም። ይህ በሆነ ቁጥር ደግሞ የወል የሥራ ክርክር የሆነው የደረጃና ዕድገት አሰጣጥ ስርዓቱ/መመሪያው የክርክር ሂደቱ ዋና ማጠንጠኛ ሆኖ መቅረቡ የማይቀርና በዚህ ረገድ በሠራተኛውና በአሠሪው መካከል የሚደረገው ክርክርም ሆነ ይህንኑ ተከትሎ የሚሰጠው ውሳኔ የሌሎችን ሠራተኞች መብትና ጥቅም የሚነካበት አጋጣሚ ሊፈጠር መቻሉ የማይቀር ጉዳይ ነው። ከዚህ አንጻር እንዲህ አይነት ክርክሮች በአንድ አልያም የተወሰነ ቁጥር ባላቸው ሠራተኞች መቅረባቸው ብቻ ከጠቅላላው የደረጃና የዕድገት አሰጣጥ ሥርዓቱ ተነጥለው ብቻቸውን ሊቆሙና ወደ ግል የሥራ ክርክር ሊመጡ ይችላሉ ወደሚል መደምደሚያ በቀላሉ ለመድረስ የሚያበቁ ይሆናሉ የሚል እምነት ፀሀፊው የለውም።

ከዚህም ባሻገር በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቱም ቢሆን እየተሰጡ ያሉት የተለያዩ ውሳኔዎች የወል እና የግል የሥራ ክርክር ምንነትን በሰፊው በማብራራት ውሳኔ

[38] ፀጋዬ ወርቅአየሁ፣ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ፣ ለወረዳ ዳኞችና ዓቃብያነ ሕግ ስልጠና የተዘጋጀ ማሰልጠኛ ሞጁል (ክፍል ሁለት) ገጽ 44-45፣ የፌደራል የፍትህ አካላት ማሰልጠኛ ማዕከል፣ ሰኔ 2000 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ። (ያልታተመ)

[39] ገዙ ከማሁ

የሰጠበትን የሰ/መ/ቁ/ 18180ን መሰረት የሚያደርጉ እንጅ በዚህ አግባብ እንዲህ አይነቶችን ጉዳዮች ነጥሎ በማውጣት የግል የሥራ ክርክር በማድረግ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች የሥራ ክርክር ችሎቶች የሚዳኙ ስለመሆናቸው አልያም በቦርዶች በዚህ ረገድ የስረ-ነገር ስልጣን አለኝ በማለት የሚሰጡ ውሳኔዎች የተሻሩበትን አጋጣሚም ቢሆን አንድ ሁለት ብሎ ለመጥቀስም እድሉ ሰፊ አይደለም፡፡

ይህ አይነቱ ክርክር በተጨባጭም ሊያጋጥም የሚችል መሆኑን ለማሳየት ደግሞ በዚሁ ቦርድ በ2011 ዓ.ም በነበረው የደረጃ ዕድገትን የተመለከተ ክርክር[40] ከሳሹ ያቀረበው ዋነኛ ጥያቄ "ተከሳሽ ድርጅት በፈተና እርማት ወቅት የጥያቄው መልስ 'እውነት' ሆኖ እያለ በስህተት 'ሀሰት' በሚል በማረሙ ምክንያት አላግባብ 1.5% ውጤት እንዳጣ ሌሎቹ ደግሞ ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ ይህንኑ ውጤት እንዲያገኙ በመደረጉ ምክንያት በሌላ ተወዳዳሪ እንድበለጥ ተደርጌያለሁ" የሚል ነው፡፡ ተከሳሽ በበኩሉ ይህንኑ ክስ ተከትሎ ባቀረበው መልስ ክርክሩ መሰረት ያደረገው በትክክልም የደረጃ ዕድገት ውድድሩን መነሻ አድርጎ ቢሆንም የቀረበው ክስም ሆነ የተጠየቀው ዳኝነት ግን በእርግጥም የከሳሹን ብቻ እንጅ የሌሎችን ሠራተኞች/ተወዳዳሪዎች መብትና ጥቅም የማይነካ በመሆኑ የግል እንጅ የወል የሥራ ክርክር ሊሆን ስለማይችል ቦርዱ ጉዳዩን የማየት የስረ-ነገር ስልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዲያነሳ ምክንያት ሆኗል፡፡ ያም ሆኖ ግን ቦርዱ በቀን 28/09/2011 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በአዋጁ አንቀጽ 142(1)(ሠ) መሰረት የቅጥር እና የደረጃ እድገትን የሚመለከቱ ጉዳዮች የቦርዱ ስልጣን ናቸው በሚል ምክንያ በዚህ ረገድ የተነሳውን የተከሳሽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ባለመቀበል የፍሬ-ነገር ክርክሩን መሰረት በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

(በተለይም ከአዲሱ አዋጅ አንቀጽ 139(1)(ሠ) እና 143(1)(ሠ እና ሰ) አንጻር ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ከዝውውር፣ ከደረጃና ዕድገት እንዲሁም ከስልጠና ጋር የተገናኙ ጉዳዮችን ተከትለው የሚቀርቡ ክርክሮችን የማየት ስልጣኑ ለፍ/ቤትም ለቦርድም የተሰጠ ከመሆኑ አንጻር ምን አልባት ከድንጋጌዎቹ አቀራረጽ አኳያ ከዝውውር እና ከስልጠና ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮችን ***የግል*** *እና* ***የወል*** *በማለት ከፋፍሎ ለማስተናገድ አስቦ ይሆናል የሚል ሀሳብን ማንጸባረቅ ቢቻልኳ* ***የደረጃ ዕድገትን*** *ተከትለው የሚነሱ ክርክሮች ግን በግልጽ ለሁለቱም አካላት በተመሳሳይ ሁኔታ የተሰጡ ከመሆኑ አንጻር በዚህ አግባብ ለማስተናገድም ዕድሉን*

[40] በከሳሽ አቶ ጥላሁን ባዬ እና በተከሳሽ ጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት መካከል የነበረ ክርክር፡፡

የማይሰጥ በመሆኑ ችግሩን "ከድጡ ወደ ማጡ" የሚወስድ ካልሆነ በስተቀር መፍትሔ የሚሰጥ አይመስልም።)

ከዚህ ውጭ ግን ከሌሎቹ ጉዳዮች በተለየ ሁኔታ የተከራካሪ ወገኖች ማንነት የፍ/ቤቶችን የስረ-ነገር ስልጣን የማይወስኑና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 ዓ.ም አንድምታ ውጭ የቀረበው ጉዳይ የፌደራል ነው ወይስ የክልል የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ሳይጠበቅባቸው ጉዳዩን የማየት ስልጣን አላቸው። ይህም ማለት የተከራካሪ ወገኖች ማንነት የዳኝነት ስልጣኑን የክልል ወይም የፌደራል በሚል ለመከፋፈል መሰረት ሊሆን አይችልም ማለት ነው።[41]

2.2.3.3 የፌደራል ከፍተኛ /የክልል ጠቅላይ/ ፍርድ ቤት ስልጣን

የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በቋሚ ወይም በጊዜያዊ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በተሰጠ ውሳኔ ላይ በህግ ነጥብ ላይ (በህግ በኩል ስህተት ተሰርቶ ውሳኔው ተዛብቷል በሚል) /question of law/[42] የሚቀርብ ይግባኝን የማየት ስልጣን አላቸው። በዚህ አግባብ በይግባኝ የሚሰጥ ውሳኔም የመጨረሻ ነው በሚል ተቀምጧል።[43] ይሁን እንጅ ክርክሮች የሚፈቱበትን መንገድ ካስቀመጠበትና ለክልል ወረዳ ፍ/ቤቶች ስልጣን ከሰጠበት አላማ አንጻር በልዩ ሁኔታ የቦርዶችን ውሳኔ በይግባኝ የማየት ብቸኛ ስልጣን ያለው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሆን ያደረገበት ምክንያት ግን ግልጽ አይደለም። ለምን ቢባል ከመጀመሪያውኑም ሕገ-መንግስቱ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር/ለመገንባት ያስቀመጠውን አላማ ዕውን ለማድረግ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይን የሚመለከቱ ህጎችን የማውጣት ስልጣኑን ለፌደራል መንግስቱ የህግ አውጭ አካል የሰጠ መሆኑ ግልጽ ነው።[44] በሌላ በኩል በግለሰቦች አልያም በተቋማት መካከል የሚፈጠሩ የፍትሐብሄር አለመግባባቶች ሊፈቱ የሚችሉበት ሁኔታን ደግሞ የፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅ[45] የዳኝነት ስልጣንን የፌደራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች በሚል አከፋፍሏል። በዚህም ምክንያት የክልል ፍ/ቤቶች ሁሉንም ጉዳዮች ያለምንም ገደብ የማየት ስልጣን ያልተሰጣቸው ከመሆኑ አንጻር የፌደራል ፍ/ቤት ስልጣን የሆኑትን ጉዳዮች የሚያዩበት ስልጣን የሚመነጨው በሕገ-መንግስቱ አግባብ

---

[41] የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 17 ሰ/መ/ቁ/ 95638 በአመልካች ኢስት ሲምንት አ/ማ እና በተጠሪ አቶ ዘላለም ታደሰ መካከል በነበረው ጉዳይ የሰጠው ውሳኔ።

[42] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9 አንቀጽ 140(1) እና አንቀጽ 154

[43] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 140(2)

[44] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 6 አንቀጽ 55(3)

[45] የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 25/1988 ዓ.ም አንቀጽ 5፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 2ኛ አመት ቁጥር 13፣ የካቲት 7 ቀን 1988 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።

በተሰጣቸው የውክልና ስልጣን ነው።[46] ይሁን እንጅ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ ከዚህ በተለዩ ሁኔታ ክርክሮች ከክልል የወረዳ ፍ/ቤቶች ጀምሮ በቀጥታ እንዲታዩ አድርጓል። ከዚህ በተቃራኒው ግን በየክልሎች የተቋቋሙት ጊዜያዊና ቋሚ ቦርዶች የሚሰጧቸውን ውሳኔዎች በይግባኝ የማየት ስልጣኑን ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብቻ ነው የሰጠው። በዚህም ምክንያት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በቦርዶች የሚሰጡ ውሳኔዎችን የሚያዩበት ስልጣን የሚመነጨው በቀጥታ ከአሠሪና ሠራተኛ አዋጁ ሳይሆን በሕገ-መንግስቱ በተቀመጠው የውክልና ስልጣን መሰረት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ይህ አይነቱ አሠራር ደግሞ አዋጁ ከመነሻውም የሚነሱ የሥራ ክርክሮች በክልል የወረዳ ፍ/ቤቶች የሚዳኙበትን ሥርዓት ከዘረጋ በኋላ ከዚህ በተቃራኒው የቦርዱን ውሳኔዎች የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲያይ ማድረጉን ተከትሎ ጉዳዮች በቀጥታ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ የሚታዩበትን አጋጣሚ ከማሳጣቱም በላይ ለሰበር የሚቀርቡ ጉዳዮች ደግሞ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚታዩበትን እድልም የነፈገም ነበር። ይሁን እንጅ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ ያያቸውን ጉዳዮች የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር የማየት ስልጣን ሊኖረው ይገባል በማለት ጉዳዮችን መልሶ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መላኩን ተከትሎ በሰበር የሚቀርቡ ጉዳዮችን የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የማየት ስልጣን ያገኘ እና በዚሁ አግባብ እንዲሠራ እየተደረገ የሚገኝ መሆኑ ምን አልባትም ከዚህ ጋር በተያያዘ በአዋጁ የሚስተዋለው ችግር በመጠኑም ቢሆን በፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ/ትዕዛዝ መፍትሔ ያገኘ ይመስላል።[47]

(ምን አልባት በአዲሱ አዋጅ አንቀጽ 140(1)(ሰ) መሰረት ይህ ስልጣን ለይግባኝ ሰሚው /ለፌደራሉም ለክልሉም ከፍተኛ/ ፍ/ቤት የተሰጠ በመሆኑ በቀጣይ ራሱን የቻለ ሌላ ጥያቄ ማስከተሉ የማይቀር መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በላይ የተነሳው ችግር ግን ምላሽ አግኝቷል ለማለት ይቻላል።)

እዚህ ላይ ሌላው ሊነሳ የሚችለው ዋና ጥያቄ በቦርዱ በክርክር ሂደት የተረጋገጡ ፍሬ-ነገሮች ሁሉ የመጨረሻ ከሆኑና በይግባኝ ችሎቱ ክርክር አይነሳባቸውም ከተባለ በእነዚህ ፍ/ቤቶች የይግባኝ ምክንያት የሚሆነው የሕግ ነጥብ (በሕግ በኩል ስህተት ተሰርቶ ውሳኔው ተዛብቷል

[46] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11 አንቀጽ 80(2)

[47] ከአቶ ሀብታሙ እርቂሁን፣ የአብክመ ጠ/ፍ/ቤት ዳኛ (በአሁኑ ሰዓት የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ዳኛ የሆኑ)፣ ጋር በስልክ የተደረገ ውይይት።

የሚያስብለው) ምን አይነት ነው? በይግባኝ የሚሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ነው ማለትስ ምን ማለት ነው? የሚለው ጉዳይ ነው። ምን አልባት ጥያቄውን ከማየት በፊት የድንጋጌውን ይዘት ምንነት ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ተቀራራቢ የድንጋጌ አቀራረጽ ያለው አብነት መጥቀሱ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

ከዚህ አንጻር የፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅን ለማየት ብንሞክር "የአስተዳደር ፍ/ቤቱ በፍራ-ነገር ክርክር የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል። ሆኖም የአስተዳደር ፍ/ቤቱ ውሳኔ የሕግ ስህተት /error of law/ አለበት ብሎ የሚከራከር ወገን የፍ/ቤቱ ውሳኔ በደረሰው በ60 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል[48] በሚል ደንግጓል። የክልሉን ተመሳሳይ አዋጅ ስንመለከት ግን ከዚህ በተለዬ ሁኔታ "የአስተዳደር ፍ/ቤቱ በፍራ-ነገር ክርክር የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል። ሆኖም የአስተዳደር ፍ/ቤቱ ውሳኔ የህግ ስህተት /error of law/ አለበት ብሎ የሚከራከር ወገን የፍ/ቤቱ ውሳኔ በደረሰው በ60 ቀን ውስጥ <u>ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት</u> (ሰረዝ የተጨመረ) ማቅረብ ይችላል[49] በማለት አስቀምጦ እናገኘዋለን። (ያም ሆኖ ግን ከዚህ በፊት ስራ ላይ የነበረውና በዚሁ አዋጅ የተተካው አዋጅ ቁጥር 171/2002 ዓ.ም (አንቀጽ 74(3)) ከፌደራሉ አዋጅ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አቀራረጽ የነበረው መሆኑ የሚዘነጋ አይደለም።) ይሁን እንጅ የክልሉ አዲስ አዋጅ በዚህ መልኩ ያስቀመጠ ቢሆንም የዜጎችን ሕገ-መንግስታዊ የይግባኝ መብት ለማረጋገጥ ሲባል እንዲሁም አዋጁ በራሱ ***ይግባኙን እንጅ የሰበር አቤቱታውን ስለማይልና*** ጉዳዮችን ደግሞ በይግባኝ የማየት ስልጣን ያለው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት እንጅ ሰበር ሰሚ ችሎቱ አይደለም የሚሉትን መነሻ ምክንያቶች በመያዝ በአስተዳደር ፍ/ቤቱ በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሕግ ስህተት አለባቸው በሚል የሚቀርቡ ጉዳዮችን ከሰበር ሰሚ ችሎቱ በፊት ጠ/ፍ/ቤቱ በይግባኝ እያያቸው ይገኛሉ።[50] ይሁን እንጅ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ከመደበኛው ፍርድ ቤት በተለዬ ሁኔታ የመንግስት ሠራተኞችን ጉዳይ በልዩ ሁኔታ አይቶ ዳኝነት እንዲሰጥ ተደርጎ እንዲደራጅ ካስፈለገበት አላማም ሆነ ድንጋጌው ሊያስተላልፍ ከፈለገው አላማ አንጻር በግልጽ "... **ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት**" በሚል የተቀመጠውን ወደ ጎን በመተው "**ይግባኙን ...**"

---

[48] የፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064 አንቀጽ 81(5)፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ሀያ አራተኛ አመት ቁጥር 12፣ ታህሳስ 6 ቀን 2010 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ።

[49] የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 253/2010 ዓ.ም አንቀጽ 80(5)፣ ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ቁጥር 14፣ መስከረም 6 ቀን 2011 ዓ.ም ባህር ዳር።

[50] አቶ ፀጋዬ ወርቅአየሁ፣ የአብክመ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስተባባሪ ዳኛ፣ በስልክ የተደረገ ውይይት። እንዲሁም የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 47።

የሚለውን አንድ ቃል ብቻ መዞ በማውጣት ስህተቱ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚለው እንጅ ይግባኝ የሚለው አይደለም በሚል የአስተዳደር ፍርድ ቤቱን ውሳኔዎች በይግባኝ ጭምር ለማየት መሞከር እንደ ፀሀፊው እምነት የድንጋጌውን መንፈስ የተከተለ ነው ለማለት አያስደፍርም።

ከመደበኛ ፍ/ቤቶች በተለዬ ሁኔታ የተወሰኑ ጉዳዮችን እንዲያዩ (አከራክረው ውሳኔ እንዲሰጡ) የሚቋቋሙ አካላት አልፎ አልፎም ቢሆን በሀገራችን የፍትሐብሄር የፍትህ ስርዓት ውስጥ መኖራቸው ግልጽ ነው። ጉዳዮች በተለይ ካላቸው ልዩ ባህሪ አንጻር መደበኛ ፍ/ቤቶች ከሚያዩአቸው ይልቅ በጉዳዮቹ ላይ የተሻለ ሙያዊ ቅርበትና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች የተሰባሰቡበት አካል እንዲያያቸው የሚደረግበት አንዱና ዋነኛው አላማ በተነጻጻሪ ክርክሩም ቢሆን ለጉዳዮቹ የተሻለ መፍትሔ ያስገኛል የሚል መሆኑ ይታወቃል። በዚህ መልኩ ከተደራጁት አካላት መካከል ደግሞ ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አንዱ ነው። በመሆኑም ቦርዱ በፍሬ-ነገር ረገድ ያረጋገጣቸውን ጉዳዮች መደበኛ ፍ/ቤቶች በይግባኝ ስልጣናቸው ይመልከቱት ቢባል ቀደም ሲል የተጠቀሰውን አላማ የሚቃረን ይሆናል። በመሆኑም ይህ ጠቅላላ አላማ ይሳካ ዘንድ ቦርዱ በፍሬ-ነገር ደረጃ የሚያረጋግጣቸው ጉዳዮች ለይግባኝ ምክንያት አለመሆናቸው ያን ያህል ጥያቄ የሚያስነሳ ጉዳይ አይሆንም። ያም ሆኖ ግን የህግ ስህተትን ለማረም በሚደረገው የይግባኝ ሂደት በፍሬ-ነገር ደረጃ ቦርዱ ያረጋገጣቸው ጉዳዮች የሚነኩበት ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ዝግ ነው ለማለት አያስደፍርም።

ከዚህ በተለዬ ሁኔታ ቦርዱ የሚሰጠው ውሳኔ የህግ ስህተት አለበት የሚል ተከራካሪ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ወይም ለክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ የሚችልበት ሥርዓት የተዘረጋበት አግባብነት ግን በእርግጥም ጥያቄ ያስነሳል። የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መሰረታዊ የህግ ስህተት (fundamental error of law) ያለባቸውን ጉዳዮች በሰበር አይቶ ከሚወስንባቸው መካከል የፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸው ጉዳዮች በቀዳሚነት የሚጠቀሱ መሆኑ ግልጽ ነው።[51] የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት <u>የሰጠውን ውሳኔ</u> (ሰረዝ የተጨመረ) በይግባኝ የማየት ስልጣን ያለው መሆኑንም በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል።[52]

ከዚህ አንጻር የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ጨምሮ የይግባኝ ስልጣን የተሰጣቸው ፍ/ቤቶች ይህ አይነቱ የይግባኝ ስልጣናቸው የሚመነጨው የስር ፍ/ቤቶች ከሚሰጧቸው ውሳኔዎች መሆኑም

[51] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 45 አንቀጽ 10(1)
[52] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 13

አጠያያቂ አይደለም። አንድ ውሳኔ በይግባኝም ሆነ በሰበር ለመታየት እንዲችል ከላይ ያየናቸው ምክንያቶች መሰረት ሆነው ሳለ ቦርዱ የሚሰጠውን ውሳኔ ግን በፍሬ-ነገርና በህግ ስህተት በሚል ከፋፍሎ በፍሬ-ነገር ክርክር ቦርዱ ያረጋገጣቸው መደምደሚያዎች በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ክርክር እንዳይደረግባቸው ከከለከለ በኋላ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ከተባለ ግን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ጉዳዩን እንዲያየው የተደረገበት አሠራር ብዙም ግልጽ አይደለም። ለምን ቢባል ይህ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በይግባኝ የሚያየው የህግ ስህተትን ከሆነ ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር ሊያይ የሚችለው የትኛውን የህግ ስህተት ነው? ወይስ ድጋሚ ሰበር በልዩ ሁኔታ ተፈቅዷል ማለት ይሆን? የሚሉት ጥያቄዎች አፍጥጠው ይወጣሉ። (በክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎቶችና በፌደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች መካከል ሕገ-መንግስቱን እና የፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅን መሰረት አድርጎ ድጋሚ ሰበርን በተመለከተ የሚነሳው ክርክር እንደተጠበቀ ሆኖ።) ከዚህም ባለፈ የሕግ ስህተት /error of law/ እና መሰረታዊ የሕግ ስህተት /fundamental error of law/ የሚሉት አገላለጾች በትክክልም አንዱን ይግባኝ ሌላውን ደግሞ ሰበር ለማሰኘት በቂና አሳማኝ ምክንያቶችስ ሊሆኑ ይችላሉ ወይ? የሚለው ጥያቄም ቢሆን መከተሉ አይቀርም። ከዚህም በተጨማሪ ጉዳዮች በመጨረሻ በሰበር መታየታቸው የማይቀር ከሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ነጥሎ የሕግ ስህተትን እንዲያይ ማድረጉ ምን አልባት በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በሚታረመው የህግ ስህተት ምክንያት መፍትሔ አግኝተው ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ሊቀርብ የሚችለውን የጉዳይ ፍሰት የመቀነስ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

ከዚህም በላይ ምንም እንኳ አሁን ላይ በተግባር ያለው የሰበር ሰሚ ችሎቱ አሰራር በህጉ በግልጽ ከተቀመጠው የሰበር አላማና ትርጉም ሰፋ ባለ ሁኔታ ጉዳዮችን የሚያይበት ሁኔታ እየተለመደ ከመምጣቱ አንጻር የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሕግ ስህተትን ለማረም ከሚያይበት አሠራር አንጻር ተቀራራቢና ተመሳሳይ እያደረገው የመጣ ቢሆንም በሁለቱ መካከል ግን የአላማ ልዩነት አለ።[53] በሰበር እንዲታዩ የሚፈለጉትን ነገሮች ያለ ምንም ልዩነትና ችግር አንድ ሁለት ብሎ ቆጥሮ ማስቀመጥ አስቸጋሪ ቢሆንም በዋናነት ሕገ-መንግስታዊ የመብት ጥሰትን የሚያስከትሉ የሕግ ስህተቶችን እንዲሁም/ወይም መሰረታዊ የሆኑ የክርክር አፈታት ሂደትን የሚጥሱ የሥነ-ሥርዓት ሕግና የማስረጃ ምዘና ጥሰቶችን የሚመለከቱና በሚያስከትሉት ውጤትም ቢሆን ከተያዘው ጉዳይም ያለፈ ሚና ያላቸው መሆኑ ግን ግልጽ ነው።[54] በመሆኑም በቦርዱ የሚሰጡ ውሳኔዎች የሕግ ስህተት ካለባቸው እነዚህን የሕግ ስህተቶች ጠቅላይ ፍርድ

[53] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 47
[54] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 50

ቤቱ በይግባኝ እንዲያያቸው የተዘረጋው አሠራር ተገቢነት አለው፡፡ ከዚህም ባሻገር ሁሉም የሕግ ስህተቶች መሰረታዊ የሕግ ስህተቶች የማይሆኑበትና በሰበር ችሎቱ ሊታዩ የማይችሉበት አጋጣሚ ሊኖር ስለሚችል ከሰበር ሰሚ ችሎቱ በፊት እንዲህ አይነት የሕግ ስህተቶችን በይግባኝ ደረጃ ማየቱ ትክክለኛ አካሄድ ነው፡፡[55]

ያም ሆኖ ግን ምንም እንኳ ልምዱ ወደ ህጉ እንዲቀየር እንጅ ህጉ ወደ ልማዳዊ አሠራሩ እንዲመጣ የሚመከር ካለመሆኑ አንጻር በተለይ የሰበር ሰሚ ችሎቱ የዜጎችን ፍትህ የማግኘት መብት ታሳቢ በማድረግ የሚቀርቡ ጉዳዮችን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሚለውን አጥብበን መመልከት አይገባም የሚል ሀሳብ ጭምር የሚንጸባረቅበት ብቻም ሳይሆን ይህንን ሀሳብ በሚያመላክት ሁኔታም ጭምር ጉዳዮችን በሰበር የሚያይበት እና ትርጉም የሚሰጥባቸው አጋጣሚዎችም ከመኖራቸው አኳያ ሲታይ[56] ግን በይግባኝ እየተስተካከሉ ባሉት የሕግ ስህተቶች እና በሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰበር ትርጉም እየተሰጠባቸው በሚገኙት መሰረታዊ የሕግ ስህተቶች መካከል ይግባኝ እና ሰበር በሚል የስም ልዩነት ጉዳዮች ሁለት ጊዜ የሚታዩበትን እድል የሚፈጥር (የዜጎችን የይግባኝ መብት የሚያሰፋ) ነው ካልተባለ በስተቀር ያን ያህል የጎላ ልዩነት አለ ለማለት ግን አያስደፍርም፡፡ ከዚህም በተረፈ ጉዳዮች ፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የሚሄዱበትም አጋጣሚ ያለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ችግሩን የጎላ ያደርገዋል፡፡

የተያዘውን ጉዳይ ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ያህል የሠራተኞች ቅነሳን አስመልክቶ በተነሳ ክርክር[57] ቦርዱ ቅነሳው ሕጉን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ከሳሾች ወደ ሥራ ሊመለሱ ይገባል በሚል ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ከሳሾች ውሳኔውን መሰረት አድርገው ከዚህ በኋላ ከድርጅቱ ጋር አብረን መቀጠል ስለማንፈልግ ተገቢው ካሳ ተከፍሎን ከሥራ ልንሰናበት ይገባናል በሚል ጠየቁ፡፡ ይሁን እንጅ ቦርዱ ይህ የመደበኛ ፍ/ቤት እንጅ የቦርዱ ስልጣን ባለመሆኑ ከውሳኔው በኋላ የቀረበውን "ካሳ ተከፍሎን ከሥራ ልንሰናበት ይገባናል" የሚል ጥያቄ ሳይቀበለው መቅረቱን ተከትሎ የሕግ ስህተትን በይግባኝ የሚመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ቦርዱ የሰጠው ውሳኔ የአዋጁን አንቀጽ 43(3) ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ስላለው የቀረበውን ጥያቄ ተመልክቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት መዝገቡን መልሶ የላከበትን

[55] ዝኒ ከማሁ

[56] ሳባ ደመቀ፣ የአብክመ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዳሰሳ፣ የአማራ ክልል የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና ህግ ምርምር ኢንስቲትዩት የህግ መጽሔት፣ ቅጽ 4፣ ሰኔ 2009 ዓ.ም፣ ገጽ 106-109፡፡

[57] በከሳሾች እነ ወ/ሮ ብዙአየሁ ተሰማ (10 ሰዎች) እና በተከሳሽ ሳባ ኢንጅነሪንግ ሀ/የተ/የግ/ማ/ መካከል የነበረ ክርክር፡፡

አጋጣሚ ለአብነት ማንሳት ይቻላል። ታዲያ እንዲህ አይነት ጉዳዮች የሕግ ስህተት /error of law/ አለባቸው ተብለው በይግባኝ ደረጃ የሚታዩ ከሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት /fundamental error of law/ ናቸው በሚል በሰበር ደረጃ ከሚታዩት ጉዳዮች የሚለዩት በምንድን ነው? በሌላ አገላለጽ በጠ/ፍ/ቤቱ በይግባኝ ደረጃ የታረመው ይህ የሕግ ስህተት በጠ/ፍ/ቤቱ ሰበር ሰሚ ችሎት በቀጥታ ታይቶ እንዳይታረም ምን የሚከለክለው የሕግ ገደብ አለ?

ከዚህ አንጻር በግልጽ የሕግ ስህተት አለባቸው ተብለው በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በይግባኝ በሚስተካከሉት እና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተብለው በሰበር ሰሚ ችሎቱ በሚታረሙት ጉዳዮች መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት ተቀምጦላቸው ድግግሞሽ የሚመስለው አሰራር እስካልተስተካከለ ድረስ በአንድ በኩል ቦርዱ የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች የሕግ ስህተት አለባቸው በሚል በይግባኝ እንዲታዩ ማድረጉ በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህም ውሳኔዎች ቢሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለተፈጸመባቸው በሰበር ሊታዩ ይገባል የሚለው አካሄድ ከችግር የነጻና ሙሉ በሙሉ ተገቢ ነው ለማለት አያስደፍርም። ከዚህም ሌላ ምን አልባትም ቦርዱ በፍሬ-ነገር ረገድ የደረሰባቸው መደምደሚያዎች የመጨረሻ እና ይግባኝ የማይባልባቸው ናቸው ከሚለው የአዋጁ መንፈስም ጋር ሊጣረስ የሚችልበትንም አጋጣሚ የሚፈጥር ነው። ለምን ቢባል የሕግ ስህተት በሚል በይግባኝ የሚስተካከሉ ጉዳዮች ይቅሩና አሁን ላይ በሰበር የሚወሰኑ ውሳኔዎች ሳይቀሩ የዜጎችን ፍትህ የማግኘት መብት ከማረጋገጥ አላማ አንጻር ዳኞች እውነታውን የመፈለግም የራሳቸው ድርሻ አላቸው በሚለው ፍልስፍና የተነሳ መሰረታዊ የሕግ ስህተቶች ላይ ብቻ ተወስነው የሚቀሩ ሳይሆን ከዚህ ሰፋ ባለ ሁኔታ የተፈጸሙ ስህተቶችን ሁሉ እያረሙ ከመሆኑ አኳያ ሲታይ በሁለቱ የይግባኝ እና የሰበር ሂደቶች መካከል ያለውን ልዩነት አጉልቶ ለማሳየት ያስቸግራል። በአጠቃላይ ከእነዚህና ከመሰል ሁኔታዎች አንጻር ሲታይ በዚህ መልኩ ሕጉ የተከተለው የይግባኝ ስርዓት አቀራረጽ ችግር የሚስተዋልበትና ሊስተካከልም የሚገባው ነው የሚል እምነት ፀሀፊው አለው።

ከዚህ አንጻር ምን አልባት በዚህ አዋጅ የተተካው አዋጅ[58] የቦርዱን ውሳኔ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል የሚቀርብን ይግባኝ የማየት ስልጣን የነበረው የማዕከላዊው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ምን አልባት የተሰራው የሕግ ስህተት በፍሬ-ነገር ረገድ ለተደረሰበት መደምደሚያ ምክንያት ሆኗል የሚል እምነት ሲኖረው በዚሁ ረገድ ቦርዱ ውሳኔውን እንዲያርም መዝገቡን መልሶ የሚልክለት እንጅ የቦርዱን ውሳኔ በራሱ የማያሻሽል ወይም የማይሽር የነበረ ከመሆኑ

[58] የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 42/1985 ዓ.ም አንቀጽ 154(2)

አንጻር ከመዝገብ /ከባለጉዳዮች/ መመላለስ አንጻር ሌላ ችግር ያስከትላል ካልተባለ በስተቀር ከላይ ከተነሳው ጥያቄ አኳያ ግን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የተሻለ ነበር ለማለት ያስደፍራል፡፡ (ያውም የተሰጡ ውሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለባቸው በሚል እንኳ በሰበር የሚታዩበት አሰራር ከመዘርጋቱ በፊት የወጣ አዋጅ፡፡) *(አሁን ላይ የአዲሱን አዋጅ መውጣት ተከትሎ በአንቀጽ 155 መሰረት ይህ በህግ አተረጓጎም ስህተት ምክንያት የሚቀርበው ይግባኝ የይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት ስልጣን መሆኑን ተከትሎ ምንአልባት በከፍተኛ ፍ/ቤቱ እና በሰበር ሰሚ ችሎቱ መካከል ሰፊና ግልፅ የሆነ የስልጣን ልዩነት መኖሩን ተከትሎ በተለይ በከፍተኛ ፍ/ቤቱ የሚታለፉ ጉዳዮችንም ከማረም አንጻር ያለው ሚና የጎላ ከመሆኑ አንጻር ከላይ የተነሳውን ሀሳብ የመቀነስ ዕድል ሊኖረው ይችላል፡፡)*

በሌላ በኩል በይግባኝ ታይተው የሚሰጡ ውሳኔዎች የመጨረሻ ናቸው የሚለው አገላለጽም ቢሆን ራሱን የቻለ ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም፡፡ ምን አልባት በዚህ አግባብ በይግባኝ ታይተው የሚሰጡ ውሳኔዎች የመጨረሻ ናቸው መባሉ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በከፊል አልያም ሙሉ በሙሉ የተለወጠበት ተከራካሪ ወገን ቢኖር በሌሎቹ የክርክር ሂደቶች ሊያነሳ የሚችለውን የይግባኝ መብት የሚነፍግ መሆኑን እንጅ የሰበር አቤቱታ ማቅረብን የማይከለክል መሆኑን መገንዘብ ይቻል ይሆናል፡፡ በተግባርም ቢሆን እየተሰራበት ያለው ይሔው ነው፡፡ ይሁን እንጅ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ስልጣን የሕግ ስህተትን እንጅ እንደሌሎች ጉዳዮች በስር ፍ/ቤት የተሰጠን ውሳኔ መሰረት አድርጎ የሚመነጭ ካለመሆኑ አንጻር ጥያቄ የሚያስነሳ ከመሆነ አኳያ ምላሽ ማግኘት ያለበት በዚሁ አግባብ ሊሆን ይገባል፡፡ *(በተለይ በአዲሱ አዋጅ ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ላይ የሚነሳውንም የህግ ስህተት በይግባኝ የማየት ስልጣኑ ለከፍተኛ ፍ/ቤቶች የተሰጠ ከመሆኑ ባሻገር ይህ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በመደበኛ ፍ/ቤት ታይቶ በይግባኝ ለዚሁ ፍ/ቤት እንደሚቀርብ ጉዳይ በግልጽ የመጨረሻ መሆን አለመሆኑ ያልተገለጸ ከመሆኑ አንጻር በጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ ሊታይ የሚችልበት ሁኔታ መኖር አለመኖሩም ገና በሂደት መልስ እስከሚያገኝ ድረስ ጥያቄ ውስጥ መቆየቱ አይቀሬ ነው፡፡)*

የአሠሪና ሠራተኛ አዋጁን ተከትለው የሚነሱ የሥራ ክርክሮችን ከመፍታት አንጻር ስልጣን የተሰጣቸውን አካላት ስልጣንና ተግባር ጠቅለል ባለ ሁኔታ በዚህ መልኩ ለማየት ከሞከርን በመቀጠል የዚህ ጽሁፍ ዋና አላማ ከሆነው የቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች ወሳኝ ቦርድ አንጻር ቦርዱ ካለው አደረጃጀት ጀምሮ በተለይም ከምዕራብ አማራ ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አኳያ የተወሰኑ ጉዳዮችን በትኩረት ለማየት እንሞክራለን፡፡

2.3 የቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አደረጃጀት

በእያንዳንዱ ክልል አንድ ወይም ከአንድ በላይ ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ሊቋቋም <u>ይችላል</u> (ሰረዝ የተጨመረ) በሚል በግልጽ ተደንግጓል።[59] ከዚህ አንጻር እንዲህ አይነቶችን ቋሚ ቦርዶች በየክልሉ ማቋቋም በአስገዳጅነት የሚፈጸም ተግባር ሳይሆን እንደአስፈላጊነቱ ብቻ ሊከናወን የሚችል መሆኑን ከድንጋጌው አቀራረጽ በቀላሉ ለመረዳት ይቻላል። ይሁን እንጅ ከዚህ በተለዬ ሁኔታ በአዲስ አበባ ከተማ በፌደራል መንግስቱ ስር የሚተዳደሩ ድርጅቶችን ጉዳይ የሚያይና የሚወስን ቦርድ እንደሚቋቋም በአማራጭ ሳይሆን በአስገዳጅነት ተቀምጧል።[60] ነገር ግን ከሀገሪቱ የፌደራል መንግስት አወቃቀር አንጻር በአዲስ አበባ ከተማ በፌደራል መንግስቱ ስር የሚተዳደሩ ድርጅቶችን ጉዳይ ለማየት ከክልሎቹ በተለዬ ሁኔታ ቦርድ እንደሚቋቋም ሲያስቀምጥ በድሬዳዋ ከተማ የሚገኙ ድርጅቶችን ጉዳይ በተመለከተ ስለሚታዩበትና ስለሚወሰኑበት (ጉዳዮችን የሚያዩ ቦርዶች ስለሚቋቋሙበት) ሁኔታ ምንም ሳይል መታለፉ የአዋጁን ምልዑነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነበረ። *(ቢሆንም በአዲሱ አዋጅ ግን በግልጽ እንዲካተት በመደረጉ ክፍተቱ ተሞልቷል።)* በየክልሎቹ የሚቋቋሙት ቋሚም ይሁኑ ጊዜያዊ የአሠሪና ሠራተኛ ወሳኝ ቦርዶች በየክልሎቹ የአሠሪና ሠራተኛ ህጎችን ለማስፈጸም ስልጣን በተሰጠው የአስፈጻሚ አካል ስር የሚደራጁ[61] ሲሆን በፌደራል መንግስቱ ስር የሚተዳደሩ ድርጅቶችን ጉዳይ ለማየትና ለመወሰን የሚቋቋሙት ቋሚም ሆነ ጊዜያዊ ቦርዶች ደግሞ በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ስር ይደራጃል።[62]

በዚህም መሰረት የምዕራብ አማራ እና የምስራቅ አማራ በሚል ክፍፍል በክልሉ ሁለት ቋሚና ጊዜያዊ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርዶች የሀገሪቱ የሠራተኛ ማህበራዊ ፖሊሲዎችና ሕጎች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ፣ አሠሪና ሠራተኛን በሚመለከት የወጡ ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን እንዲያረጋግጥ እንዲሁም የሥራ ክርክሮች በሕግ የተዘረጋውን ሥርዓት ተከትለው በተቀላጠፈ ሁኔታ ፍጻሜ እንዲያገኙ

---

[59] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9 አንቀጽ 144 *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 145)*

[60] የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 466/1997 ዓ.ም አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1(1)፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አስረኛ አመት ቁጥር 56፣ ሰኔ 23 ቀን 1997 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ። (ምንም እንኳ በአዲሱ አዋጅ አንቀጽ 145 ላይ በመካተቱ ምክንያት አዋጁ የተሻረ ቢሆንም።)

[61] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9 አንቀጽ 144(3)

[62] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 60 አንቀጽ 2(2) *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 145(4))*

አስፈላጊውን ጥረት ማድረግን[63] ጨምሮ ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ስልጣንና ተግባራት በተሰጠው በክልሉ የሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ስር ተቋቁመው በስልጣናቸው ስር የሚወድቁ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክሮችን የማየትና የመወሰን ተግባራቸውን እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡

2.4 የቦርድ አባላት አሰያየምና ስብጥር

የቦርዱ አባላት ስብጥርን በተመለከተም አዋጁ ሊደርስበት ያሰበውን አላማ ለማሳካት ያስችል ዘንድ የሶስትዮሽ ግንኙነቱን (Triparitate) በጠበቀ መልኩ የመንግስትን፣ የአሠሪውን እንዲሁም የሠራተኛውን ጥምር ፍላጎት በሚያሳካ ሁኔታ እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት በክልል ደረጃ የሚቋቋሙት ቦርዶች በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በሚሰየሙ አንድ የቦርድ ሰብሳቢ፣ ሁለት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው አባላት እንዲሁም የአሠሪውን እና የሠራተኛውን ድምጽ በብዛት ከሚወክሉ የአሠሪ እና የሠራተኛ ማህበራት የሚወከሉ ሁለት የአሠሪ እና ሁለት የሠራተኛ ተወካዮች በድምሩ ሰባት አባላትን የሚያካትቱ ሆነው የተደራጁ ናቸው፡፡[64] ከዚህም ባሻገር በተለያዩ አጋጣሚዎች እነዚህ ተወካዮች በማይኖሩበት ጊዜ እነሱን ተክተው የሚሰሩ ከሁለቱ ማህበራት አንድ አንድ ተተኪ አባላት በተጨማሪነት የሚመረጡበትን አሰራርም አዋጁ በግልጽ አካቷል፡፡[65] በፌደራል መንግስቱ የሚቋቋሙ ቦርዶች አባላትም ቢሆን የመንግስት ተወካዮቹ በሚኒስትር መስሪያ ቤቱ የሚሰየሙ ከመሆናቸው ባለፈ ምንም አይነት ልዩነት የላቸውም[66]፡፡

የቦርዱ አባላት ለሶስት አመታት ለሚቆይ የአገልግለት ዘመን የቆይታ ጊዜ ያላቸው ሲሆን የአባላቱን የአገልግሎት ዘመን ማብቂያ ጊዜን ለመለያየትና ልምድ ያላቸው አባላት በአንድ ጊዜ እንዳይለቁ ለመከላከል አላማ ሲባል ከነተተኪዎች የአባላቱን የአገልግሎት ዘመን ለአንድ፣ ለሁለትና ለሶስት አመት የአገልግሎት ዘመን በመከፋፈል በየአመቱ የአገልግሎት ዘመናቸው የሚያበቁ የቦርድ አባላት ቁጥር ከአንድ ሶስተኛ በላይ እንዳይሆን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓትንም አዋጁ በግልጽ ዘርግቷል[67]፡፡ ተተኪዎችን ጨምሮ የቦርዱ አባላት ያለ ደሞዝ በከፊል ጊዜ የሚሰሩ ሲሆን ቢሮው/ሚኒስትሩ ግን አባላቱ <u>በቦርድ ስብሰባ</u> (ሰረዝ የተጨመረ)

---

[63] በአብክመ የተሻሻለው የአስፈጻሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 264/2011 ዓ.ም፣ 24ኛ አመት ቁጥር 03፣ የካቲት 30 ቀን 2011 ዓ.ም፣ ባህር ዳር፡፡

[64] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9 አንቀጽ 145(1) እና (2) *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 146(1) እና (2))*

[65] ዝኒ ከማሁ

[66] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 60 አንቀጽ 1(1)(1) እና የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9 አንቀጽ 144(3) ጥምር ንባብ *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 145(3)*

[67] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9 አንቀጽ 145(5) *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 146(5))*

ለሚገኙበት ጊዜ አንድ ወጥ የሆነ አበል ሊወስንላቸው እንደሚችል በግልጽ ተመላክቷል። በመሆኑም ቦርዱ ከሳምንት ሁለት ቀናት ማለትም ማክሰኞ እና ሀሙስ ከ9፡00-11፡00 ድረስ ባለው ጊዜ በቋሚነት ሥራውን እያከናወነ ይገኛል። ለዚህ ሥራቸውም ለሰብሳቢው 150.00 (አንድ መቶ ሀምሳ ብር) ለሌሎቹ አባላት ደግሞ 125.00 (አንድ መቶ ሀያ አምስት ብር) አባላቱ በተገኙበት ቀን ብቻ እየታሰበ የሚከፈል ክፍያ ይፈጸምላቸዋል። ከእነዚህ አባላት በተጨማሪ አንድ ፀሀፊ እና ሌሎች ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን ሚኒስትሩ/ቢሮው እንደሚመድብም ህጉ በግልጽ ያስቀምጣል።[68] በዚህም መሰረት ቦርዱ ከላይ ከተጠቀሱት አባላትና ተተኪዎች ባሻገር በአንድ የቦርዱ ጽ/ቤት ሀላፊ፣ በአንድ ችሎት ፀሀፊ፣ በአንድ የጽ/ቤቱ ፀሀፊ/ሴክሬታሪ እንዲሁም በአንድ ችሎት አስከባሪ ባለሙያዎች ተደራጅቷል።

2.5 የቦርዱ ተግባር አመራር ሥነ-ሥርዓት

የቦርዱ ሥራ በሰብሳቢው አማካኝነት የሚመራ ሲሆን እሱ በማይኖርበት ጊዜ ደግሞ በእሱ የተወከለው ተጠባባቂ ሰብሳቢ አማካኝነት የሚመራ ይሆናል። ሁለቱም በማይኖሩበት ጊዜ ደግሞ በወቅቱ ከተገኙት አባላት መካከል በቦርዱ ቆይታ የበለጠ የአገልግሎት ጊዜ ባለው አባል አማካኝነት ቦርዱን የመምራት ሥራው ይከናወናል። ቦርዱ ተግባሩን በሚያከናውንበት ወቅት አንድ አባል የቀረ ከሆነ ሰብሳቢው በቀረው አባል ምትክ ከተተኪ አባሎች የሚተካና ተተኪውም በተተካበት ወቅት ቦርዱ ለሚያከናውነው ተግባር እንደ አባል ይቆጠራል። ቢያንስ ከአሠሪና ሠራተኛ አንድ አንድ ተወካዮች እስከተገኙ ድረስ የቦርዱ አባላት ሙሉ በሙሉ ባይሟሉም እንኳ አራቱ ከተሟሉ ቦርዱ ተግባሩን ማከናወን ይችላል። የድምጽ እኩልነት አጋጥሞ የቦርዱ ሰብሳቢ የደገፈው ውሳኔ ገዥ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በቦርዱ በተገኙት አባላት አብዛኛው ድምጽ ድጋፍ ያገኘው ሀሳብ የቦርዱ ውሳኔ ሆኖ ተግባራዊ ይደረጋል።[69] እዚህ ላይ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ የአሠሪውና የሠራተኛው አንድ አንድ ተወካዮች እስከተሟሉ ድረስ አራት አባላት መገኘታቸው ቦርዱ ተግባሩን እንዲያከናውን የሚያስችለው ከሆነና ቅድመ-ሁኔታዎች የአሠሪና የሠራተኛው ተወካዮች በልዩ ሁኔታ መገኘት ከሆነ የሠራተኛውና የአሠሪው አራቱም ተወካዮች ተገኝተው ነገር ግን አንድም የመንግስት ተወካይ ባይገኝ የቦርዱ አባላት ምልዐተ-ጉባዔ እንደተሟላ ተቆጥሮ ተግባሩን ሊያከናውን ይችላል ወይ? የሚለው ነው። ምን አልባት በመንግስት ከሚሰየሙት ሶስት የቦርዱ አባላት ቁጥር ይልቅ ከሠራተኛ እና ከአሠሪ ማህበራት

[68] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 145(3) እና (4) *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 146 (3) እና (4)*
[69] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 146 *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 147)*

የሚመረጡት አባላት ቁጥር ዝቅተኛ ከመሆኑም ባሻገር እነዚህ የአሠሪውና የሠራተኛው ተወካዮች በሁለት ዕንፍ የተሰለፉ ተቃራኒ ፍላጎቶችን የሚወክሉ ከመሆኑ አንጻር ሁለቱም የሠራተኛው ወይም የአሠሪው ተወካዮች በሌሉበት ሁኔታም ምልዓተ-ጉባዔው ሊሟላ የሚችል ቢሆንም ቅሉ ቢያንስ አንዱ እንኳ የአሠሪው ወይም የሠራተኛው ተወካይ በሌለበት ውሳኔ ቢሰጥ የሚሰጠው ውሳኔ የፍትሐዊነት ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። በመሆኑም ይህንኑ ስጋት ቀድሞ ለመከላከል በልዩ ሁኔታ የተቀመጠ ነው ካልተባለ በስተቀር የድንጋጌውን ተቃራኒ ንባብ በቀጥታ በመውሰድና ሕጉ የመንግስትን ተወካይ መገኘት በቅድመ-ሁኔታ ሳያስቀምጥ ያለፈው ሆነ ብሎ ነው የሚለውን ሀሳብ በመያዝ ምልዓተ-ጉባዔው እስከተሟላ ድረስ አንድም የመንግስት ተወካይ ባይገኝም ቦርዱ ተግባሩን ማከናወን ይችላል የሚለው መደምደሚያ ላይ ለመድረስ መሞከር ግን ብዙም አዋጭ አይመስልም።

ለምን ቢባል በአሠሪውና በሠራተኛው መካከል ሊኖር የሚችለውን የጥቅም ግጭት መሰረት አድርጎ ሕጉ ይሔንን ያህል ከተጨነቀ የመንግስት ተወካዮች ባለመገኘታቸው ሊከሰት ስለሚችለው ክፍተት ደንታ አይሰጠውም ለማለት አይቻልም። ምክንያቱም ቀደም ሲል ለማየት እንደሞከርነው ምንም እንኳ በሂደት በጉዳዩ ላይ ዕውቀቱና ልምዱ ሊኖራቸው እንደሚችል ቢገመትም በአስገዳጅነት /በመርህ ደረጃ ግን በህጉ/ ስለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ልምድና ዕውቀት ያላቸው እንዲሆኑ የሚጠበቅባቸው የቦርዱ አባላት ግን ሁለቱ የመንግስት ተወካዮች መሆናቸውን አዋጁ በግልጽ አስቀምጧል።[70] የሚቀርቡ ጉዳዮችን ተቀብሎ የዜጎችን ፍትህ የማግኘት ሕገ-መንግስታዊ መብት ባረጋገጠና ተገቢውን የክርክር ሂደት በጠበቀ መልኩ ውሳኔዎችን ለመስጠት ደግሞ አይደለም በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች ላይ በሌሎች መሰረታዊና ሥነ-ሥርዓታዊ ሕጎችም ላይ ልምዱና ዕውቀቱ ሊኖር ይገባል። ይህ በሆነበት ሁኔታ አንድም የመንግስት ተወካይ በሌለበት ሁኔታ ምልዓተ-ጉባዔው ስለተሟላ ብቻ ጉዳዮችን ተመልክቶ ውሳኔዎች እንዲሰጡ መፍቀዱ የቦርዱ አባላት በሌሎች ሕጎች ይቅርና በአዋጁም ላይ ቢሆን ዕውቀትና ልምድ እንዲኖራቸው አይጠበቅባቸውም የማለት ያህል ነው። ይህ ደግሞ የዜጎችን ፍትህ የማግኘት መብት የማጣበብ እድሉ ሰፊ ከመሆኑ አንጻር ሕጉ በግልጽ ያላስቀመጠና ቦርዱም በዚሁ አግባብ እየሰራ የሚገኝ ቢሆንም እንኳ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች ዕውቀትና ልምድ እንዲኖራቸው ከሚጠበቅባቸው ብቸኛ ሁለት የመንግስት ተወካይ ባለሙያዎች መካከል ግን ቢያንስ የአንዱ መኖር አስገዳጅ ሊሆን ይገባል።

[70] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 145(1) (አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 146(1)

2.6 የክስ መስማት፣ የውሳኔ አሰጣጥና አፈጻጸም ሂደት

በተለይ በአሠሪውና በሠራተኛው መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች ከሚያስከትሉት ዘርፈ ብዙ ችግሮች የተነሳ ቦርዱ የሚቀርቡለትን ጉዳዮች ማናቸውንም የማስማሚያ ዘዴዎች በመጠቀም በተቻለ መጠን ሁሉ በስምምነት ለመፍታት የበኩሉን ጥረት ማድረግ ያለበት መሆኑ በአማራጭ ሳይሆን በመርህ ደረጃ የተቀመጠበትን ሁኔታ ከአዋጁ በግልጽ ለመረዳት ይቻላል።[71] ይሁን እንጅ ጉዳዩን በስምምነት ለመፍታት የማይቻል ከሆነ በቂ ምክንያት በመኖሩ የተነሳ በልዩ ሁኔታ በቦርዱ/በችሎቱ ሰብሳቢ በዝግ ችሎት እንዲቀጥል ካልተወሰነ በስተቀር ጉዳዮች በግልጽ ችሎት የመሰማታቸውን መርህ በጠበቀ ሁኔታ ክርክሩ የሚሰማበትን ቦታ፣ ቀን እና ሰዓት ከ3 የስራ ቀናት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ *(በተለይም በ30 ቀናት ውስጥ ጉዳዩን ለመጨረስ አንጻር በሂደት ሌላ ችግር ማስከተሉ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዲሱ አዋጅ አንቀጽ 150(1) መሰረት 10 የስራ ቀናት በመሆን ተሻሽሏል።)* በጽሁፍ እንዲያውቁት በማድረግ በቀረበው ጉዳይ ላይ ተገቢውን ክርክር እንዲያደርጉ ዕድል የመስጠት ግዴታም ተጥሎበታል።[72] ቦርዱ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው ተከራካሪዎች ባሻገር ተከራካሪዎቹ የሚገኙበት አካባቢ የሚኖሩ የማ/ሰብ ክፍሎችን እንዲሁም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ ተገቢ ነው ብሎ ካመነ ደግሞ የሚመለከተው የመንግስት አካልም በክርክሩ ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆን ሊያደርግ የሚችልበትን ሥርዓትም ህጉ ይፈቅድለታል።[73] ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ ተገቢው ጥሪ ከተደረገለት በኋላ በራሱ ጥፋት ባልሆነ ምክንያት በመቅረቱ የተነሳ እንዲቀርብ በድጋሚ የሚጠራ ካልሆነ በስተቀር ቦርዱ ተከራካሪው ወገን ባይቀርብም ክሱን/ጉዳዩን መስማቱን ይቀጥላል። ተከራካሪ ወገን በሌለበት ክሱን ለመስማትም ይሁን ተከራካሪው ድጋሚ እንዲቀርብ ቦርዱ የሚሰጠው ትዕዛዝም ይግባኝ የማለት መብትን አያጎናጽፍም።[74]

ቦርዱ በየትኞቹም ፍ/ቤቶች ቢሆን የሚሰሩባቸውን የሥነ-ሥርዓትም ይሁን የማስረጃ አቀራረብ ደንቦች ሳይከተል የራሱን የተሻለ የአሠራር ዘዴ መጠቀም የሚችል[75] ከመሆኑም ባሻገር ቦርዱ ስራውን የሚመራበት የሥነ-ሥርዓትና <u>የመረጃ</u> (ሰረዝ የተጨመረ) /evidence/ አቀራረብ ደንቦችን እንደሚያወጣም በግልጽ ተመላክቷል።[76] *(ይሁን እንጅ ይህ በሌለበት ሁኔታ ግን*

[71] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 150(1) *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 151(1))*
[72] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 149(1) *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 150(1))*
[73] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 150(2) *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 151(2))*
[74] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 149(3) *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 150(3))*
[75] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 149(5) *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 150(5))*
[76] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 148 *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 149)*

በፍትሐብሄር ስነ-ስርዓት ህግ መሰረት መመራት እንደሚገባው ከነባሩ አዋጅ በተለየ መልኩ በአዲሱ አዋጅ በአሰገዳጅ ሁኔታ ተቀምጧል።) ምን አልባት የከሳሾችን መብት ይበልጥ ለማስፋት አላማ ሲባል ተከሳሾች ባቀረቡት የክስ መልስ ላይ ከሳሾች የመልስ መልሳቸውን በጽሁፍ የሚያቀርቡበትን ሥርዓት ተግባራዊ እያደረገ ያለበትን ሁኔታ ለአብነት መጥቀስ የሚቻልበት አጋጣሚ ከሌለ በስተቀር በዚህ ረገድ ግን ቦርዱ በጽሁፍም ይሁን በተግባር ያዳበረው የራሱ የሆነ የተለየ የአሠራር ደንብ ግን የለውም። ከዚህም ሌላ ሌሎች ፍ/ቤቶች የሚመሩበትን <u>የሕግ መሰረታዊ ደንቦች</u> (ሰረዝ የተጨመረ) /Principles of substantive laws/ በቀጥታ ሳይከተል <u>የቀረበለት ክርክር በተለይ የተመሰረተበትን ዋና ጉዳይ ብቻ አይቶ</u> (ሰረዝ የተጨመረ) /the board shall take in to account the substantive merits of the case, and need not follow strictly the principles of substantive laws followed by civil courts/ ሊወስን የሚችል መሆኑንም አዋጁ በግልጽ ስልጣን ሰጥቶታል።[77]

በዚህ አግባብ ቦርዱ የቀረበለትን ጉዳይ በተከራካሪ ወገኖችም ይሁን በራሱ በሚያደርገው ጥረት በስምምነት የማይቋጭ ከሆነ በቀረበለት በ30 ቀናት ውስጥ በውሳኔ መጨረስ ያለበት መሆኑም በግልጽ ተመላክቷል።[78] የተለዩ የውሳኔ ሀሳብ ካለ ይህንኑ የልዩነት ሀሳብ ጭምር ባካተተ ሁኔታ ውሳኔውም በጽሁፍ መሆን ያለበትና በችሎቱ አባላት የተፈረመበት እንዲሆን ሕጉ በግልጽ ያስቀምጣል።[79] ውሳኔውም ቦርዱ የቀረበለትን ክርክር ወይም ጭብጥ፣ የቀረቡትን አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎችና ምስክሮች ተሰምተው ከሆነም የምስክሮችን ቃል ፍሬ-ነገርና የተገኘበትን ምንጭ፣ ለውሳኔ ያበቁትን ፍሬ ነገሮችና ያመዛዘናቸውን ጉዳዮች፣ በእያንዳንዱ ጭብጥ/ክርክር ላይ የሰጠውን ውሳኔ እንዲሁም በሰጠው ውሳኔ መሰረት ሊወሰዱ የሚገባቸውን ዕርምጃዎች ጭምር ባካተተ መልኩ መጻፍ ይኖርበታል።[80] የውሳኔው ግልባጭም በ5 ቀናት ውስጥ ለተከራካሪ ወገኖች የሚሰጥ ይሆናል።[81]

ቦርዱ በክርክር ሂደት ያረጋገጣቸው ፍሬ-ነገሮች ሁሉ የመጨረሻና ክርክር የማይደረግባቸው ቢሆኑም[82] የቦርዱ ውሳኔ <u>በህግ በኩል ስህተት የተፈጸመበት</u> (ሰረዝ የተጨመረ) በመሆኑ ምክንያት ውሳኔው ተሳብቷል የሚል ቅሬታ ያለው ተከራካሪ ወገን ግን ውሳኔው በይፋ ከተነበበ

[77] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 150(3) *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 151(3))*
[78] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 151(1) *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 152(1))*
[79] ዝኒ ከማሁ ንዑስ ቁጥር 2
[80] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 151(3) *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 152(3))*
[81] ዝኒ ከማሁ ንዑስ ቁጥር 4
[82] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 153 *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 154)*

ወይም ለተከራካሪ ወገኖች ከተሰጠ በኋላ ከሁለቱ ድርጊቶች የቀደመው ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ *(በአዲሱ አዋጅ አንቀጽ 155(1) መሰረት ለተከራካሪ ወገኖች ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በሚል ተሻሽሏል።)* ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎት የማቅረብ መብቱ ግን የተጠበቀ ነው።[83] (በዚህ መልኩ ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ የይግባኝ ክርክሮችን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሚያይበትን አግባብ ቀደም ሲል በክፍል 2.2.3.3 የፌደራል ከፍተኛ /የክልል ጠቅላይ/ ፍርድ ቤት ስልጣን በሚለው ስር የተገለጸውን ልብ ይሏል። *(በአዲሱ አዋጅ አንቀጽ 155(2) መሰረት ስልጣኑ ለክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሆኖ የተሻሻለ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ።)*) ፍርድ ቤቱም የቀረበለትን ይግባኝ ከተመለከተ በኋላ ይግባኙ በቀረበለት በ30 ቀናት ውስጥ የቦርዱን ውሳኔ በማጽናት፣ በማሻሻል ወይም በመሻር ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ተሰጥቶታል።[84] ቦርዱ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች ከላይ በተገለጸው ሁኔታ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ወይም በሰበር ሰሚ ችሎቱ ካልተለወጡ በስተቀር ወዲያውኑ የሚፈጸሙ ይሆናሉ።[85] ቦርዱ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች የሥራ ሁኔታዎችን መሰረት ያደረጉ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ በሚመለከታቸው አሠሪና ሠራተኛ መካከል እንደ ሥራ ውል የሚቆጠሩና በዚሁ ውል መሰረት በሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባቸው የአቆጣጠር ውሎች ሁኔታዎች በውሳኔዎቹ መሰረት የሚስተካከሉ ይሆናሉ።[86]

[83] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 154(1) *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 155(1))*
[84] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 154(2 እና 3) *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 155(2 እና 3))*
[85] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 152(1) *(አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 153(1))*
[86] ዝኒ ከማሁ ንዑስ ቁጥር 2

ክፍል ሶስት

ከቦርዱ አሠራር አንጻር የሚስተዋሉ ክፍተቶች

3.1 በአዋጁ የተሰጠው የትኩረት ማነስ

ቦርዱ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች መደበኛ ፍ/ቤቶች በሚሰጧቸው ውሳኔዎች አግባብ የሚፈጸሙ እንደመሆናቸው መጠን እንዲህ አይነት አስገዳጅነት ያለው ውሳኔ ለመስጠት የጉዳይ/ክስ መስማቱ ሂደትም መሰረታዊ የሆኑ የሥነ-ሥርዓት ደንቦችን ተከትሎ መከናወን ያለበት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም በተለይ በክስ መስማት ወቅት የሚሰጣቸው የተለያዩ ትዕዛዛትም ይሁኑ ቦርዱ በመጨረሻ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች በአፋጣኝና በአግባቡ በሚመለከታቸው አካላት ዘንድ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ቦርዱ ሊሰጠው የሚገባውን ትኩረት አዋጁ እራሱ ልዩ ትኩረት በመስጠት ማደራጀት ሲገባው "ጌታው ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳው አይቀበለውም፡፡" እንዲሉት በዚህ መልክ ማስቀመጡ መጠነኛም ቢሆን ክፍተት ማስከተሉ አይቀርም፡፡ በሌላ አገላለጽ ለመጥቀስ ያህል 'ቦርዱ ባደረገው ስብሰባ የሰጠው ትዕዛዝ/ውሳኔ' እና 'ቦርዱ በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ/ውሳኔ' (ቦርድ ከሚለው አኳያ ይጣረሳል ካልተባለ በስተቀር) የሚሉት አገላለጾች በተለይ ሁሉም ባይባል እንኳ ማህበረሰቡ አሁን ላይ 'ስብሰባ' ለሚለው ቃል ካለው የተሳሳተ ግንዛቤ/አመለካከት አንጻር እኩል ክብደት ይኖራቸዋል ለማለት ስለሚያስቸግር የቦርዱ ውሳኔ ላይ ባለጉዳዮቹ የሚሰጡት ክብደት ላይ ምንም አይነት ችግር አያስከትልም ለማለት አይቻልም፡፡

ከዚህ ባለፈ የቦርዱን አባላት አሰያየም በተመለከተ ቀደም ሲል ለማየት እንደሞከርነው ከሰባቱ አባላት መካከል በዋናነት በሌሎቹ መሰረታዊና ሥነ-ሥርዓታዊ ሕጎች ይቅርና በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ላይ ዕውቀትና ልምድ እንዲኖራቸው የሚጠበቀው ሁለቱ የመንግስት ተወካይ ባለሙያዎች ብቻ እንዲሆን መደረጉ ትልቅ ስህተት ነው፡፡ ምንምኳ ሌሎች የቦርድ አባላት በስራቸው አጋጣሚ በጉዳዮች ላይ ሰፊ ልምድና ዕውቀት ሊኖራቸው የሚችልበት አጋጣሚ ሰፊ ቢሆንም ይህ ግን የሕግ አስገዳጅነት የሌለው እና እንደ አባላቱ ግላዊ ሁኔታ የሚወሰን ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የሚቀርቡትን ጉዳዮች ከአዋጁ፣ ከህብረት ስምምነቶች፣ ከሥራ ደንቦች፣ ከሥራ ውሎች ይዘትና መስፈርቶች፣ ከስነ-ስርዓት ህጉ፣ ማስረጃን ከሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንዲሁም አስገዳጅነት ካላቸው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎቱ ውሳኔዎች አንጻር የክርክሩን ሂደት ለመምራትና የቀረበውን ክስ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ-ነገሮች ከሕግና ማስረጃ

ጋር አገናዝቦ ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት ሕጉ ለሕግ ባለሙያ የቦርድ አባላት የሰጠው ትኩረት በጣም ዝቅተኛ ነው ለማለት ያስችላል።

ከአዋጁ ጋር በተያያዘ ከሚነሱት ችግሮች ባለፈም ቢሮው የቦርዱን ጽ/ቤት ያደራጀበት አግባብ በራሱ ለጽ/ቤቱ የተሰጠውን የትኩረት ማነስ አመላካች ነው። በተለይ ቦርዱ የተሰጠውን ተግባርና ሀላፊነት በመወጣት ረገድ ከቦርዱ አባላት ባለፈ በተለያዩ ባለሙያዎች ጽ/ቤቱን የማደራጀት ሥራ ቢሮው ያከናወነ መሆኑ ቀደም ሲል በመልካም ጎኑ የተነሳ መሆኑ ይታወሳል። ይሁን እንጅ የጽ/ቤቱ ሀላፊ የሥራ መደብ ተጠሪነቱ ለቢሮው ሀላፊ ነው ወይስ በቢሮው ስር ለሚገኘው ለኢንዱስትሪ ሰላም ዳይሬክቶሬት ነው ከሚለው ጥያቄ ጀምሮ የጽ/ቤት ሀላፊ፣ የችሎት ፀሀፊ እና የችሎት ሥነ-ሥርዓት አስከባሪ የሥራ መደቦች ከሚያከናውኑት ተግባር አንጻር በሀገር አቀፍ ደረጃ በተተገበረው የሥራ ምዘናና ደረጃ አሠራር የተሰጣቸው ደረጃ ዝቅተኛ ነው የሚል ውስንነትም በጽ/ቤቱ በኩል ይነሳል።[87]

3.2 የጉዳዮች መብዛት እና የችሎት ጊዜው ማነስ

ቦርዱ ላይ የሚቀርቡት ጉዳዮች ከመጀመሪያውም የወል የሥራ ክርክሮች ከመሆናቸው አንጻር የጋራ በሆኑ መብትና ግዴታዎች ላይ የተመሰረቱ እንደመሆናቸው መጠን እያንዳንዱ አሠሪና ሠራተኛ ይዟቸው ከሚቀርቡት የግል የሥራ ክርክሮች በተለዬ ሁኔታ የሚቀርቡት ጉዳዮች ቁጥር አነስተኛ እንደሚሆን በማሰብም ይሁን በሌሎች ምክንያቶች ቦርዱ ሲደራጅም ሆነ ተግባሩን ሲያከናውን በተወሰነ/በተገደበ የሥራ ጊዜ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ቀደም ሲል ማየታችን ይታወሳል። በዚህም መሰረት ቦርዱ ማክሰኞና ሀሙስ ከ9፡00-11፡30 ድረስ የክስ መስማት ተግባሩን እያከናወነ ይገኛል። ይሁን እንጅ አሁን ላይ ለቦርዱ እየቀረቡ ካሉት ጉዳዮች መበራከት አንጻር ቦርዱ በእነዚህ ቀናትና ሰዓታት ብቻ ተወስኖ ስራውን ለማከናወን የማይችልበት ደረጃ ላይ እየደረሰ ለመምጣቱ የቦርድ አባላትም የሚስማሙበት ከመሆኑም ባሻገር ቀጣዩን የመዛግብት አዛዝ በማየትም በቀላሉ ለመገንዘብ ይቻላል።

በዚህም መሰረት በየአመቱ ለቦርዱ የሚቀርቡ ጉዳዮች እየጨመሩ መምጣታቸውን ተከትሎ በአፈጻጸም የሚቀርቡትን ከ30 በላይ የአፈጻጸም መዛግብት ሳይጨምር የሚቀርቡለትን በአመት

[87] የምዕ/አማራ ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ጽ/ቤት ለቢሮው በቁጥር ጠጉ17-25126 በቀን 07/08/2011 ዓ.ም በቦርዱ አሠራር ላይ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን ለማቅረብ የጻፈው 2 ገጽ ደብዳቤ።

ከ80[88] በላይ የሆኑ አዲስ መዛግብት/ጉዳዮች ከማስማማት ጀምሮ ውሳኔ እስከመስጠት ድረስ የሚኖሩትን የክስ መስማት ሂደት በአግባቡ አከናውኖ ውሳኔ ለመስጠት ይችል ዘንድ በዝግ ምክንያት የሚባክኑ የችሎት ቀናትን በተለዋጭ ቀን ከመስራት ባለፈ ቦርዱ በራሱ መልካም ፈቃደኝነት 9፡00 ይጀምር የነበረውን 8፡00 በመጀመር የተወሰነ ለውጥ ለማድረግ ጥረት አድርጓል። እንዲህም ሆኖ ግን አሁንም ቢሆን ችግሩ ሙሉ በሙሉ ተቀርፏል ለማለት አይቻልም።

በሌላ በኩል በተቻለ መጠን ያሉትን መዛግብት/ጉዳዮች ባሉት የችሎት ቀናት ከፋፍሎ (የቀጠሮ ፖሊሲን በመጠቀም) ለማስተናገድ የሚደረገው ፍላጎትም ሆነ ጥረት ከፍተኛ ቢሆንም ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች ማለትም የመዛግብት ቁጥርና የችሎት ጊዜው አለመመጣጠን ተከትሎ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ሁሉንም ሕጉ ባስቀመጠው የ30 ቀናት የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማጠናቀቅ አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሳ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የሚዘገዩ ጉዳዮች መኖራቸው አይቀሬ ነው።[89] የጉዳዮቹ የመጥራት /በተቀመጠው የጊዜ ገደብ የመቋጨት/ ምጣኔ በቀነሰ ቁጥር ደግሞ የጉዳዮቹ ክምችት እንዳለ የሚቀጥል በመሆኑ ከመጀመሪያውም ከመብዛታቸው ጋር ተዳምሮ በአንድ የችሎት ቀን የተወሰኑ ቁጥር ያላቸውን ጉዳዮች ብቻ በተረጋጋ ሁኔታ ለማስተናገድም እንቅፋት እየሆነ መጥቷል። ሁልግዜም ተመሳሳይ ባይሆንም ከ10 ጉዳዮች በላይ በአንድ የችሎት ቀን በተጠቀሰው የችሎት ሰዓት ለማስተናገድ የሚገደድበት ሁኔታም ያጋጥማል።

3.3 ከክስ መስማት ሂደት ጋር በተያያዘ

ቦርዱ በማናቸውም ፍ/ቤቶች የሚሰራባቸውን የስነ-ስርዓትና የማስረጃ አቀራረብ ደንቦች ሳይወሰን የተሻለ መስሎ የሚታየውን ዘዴ በመጠቀም የክስ መስማት ሂደቱን ማከናወን የሚችል መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ማለት ግን መሰረታዊ የሆኑ የስነ-ስርዓት መርሆዎችን መጠበቅ የለበትም ማለት አይደለም። በዚህም መሰረት ቦርዱ የሚቀርቡለትን ጉዳዮች ከመጀመሪያውኑ ሲቀበል ጀምሮ የሰጠውን ውሳኔ እስከማስፈጸም ድረስ ያለውን ሂደት በተገቢው መንገድ መምራት ያለበት መሆኑ ግልጽ ነው። በዚህም መሰረት ከመጀመሪያው የሚቀርቡ

[88] የምዕራብ አማራ ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የ2011 ዓ.ም የ11 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት።
[89] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 87

ክሶች በትክክልም ከሳሹ ለመክሰስ ችሎታ ያለው[90] ለመሆኑ እንዲሁም ከክሱ ጋር ለክሱ መነሻ መሰረት የሆነውን ሰነድ ወይም ትክክለኛ ግልባጭ ከማቅረብ[91] አንጻር መሟላት ያለባቸውን ነገሮች በትክክልም በማስረጃ አስደግፎ ያቀረበ መሆኑን በማረጋገጥ ረገድ የተወሰነም ቢሆን ክፍተት ይታያል። ይሁን እንጅ በአብዛኛው ከሳሽ ሆነው የሚቀርቡት ሰራተኞች እንደመሆናቸው መጠን በተለይ አሠሪውና ሠራተኛው ያላቸውን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ሠራተኛው የሚያቀርበውን ክስ በትክክልም ክሱን ለማቅረብ የሚችል መሆኑን ለማረጋገጥ በበቂ ምክንያት አስደግፎ ማቅረብ ሲገባው ለዚህ አላማ የሚሆኑትን የተለያዩ ማስረጃዎች ማግኘት ስላልቻልኩ በሚል ምክንያት እንዲሁ ክስ የሚያቀርብበትና የሚፈቀድበት ሁኔታ ያጋጥማል።

ለአብነት ለመጥቀስ ያህል በተለይ "አሠሪው የውስጥ የደረጃ እድገት ማስታወቂያ ማውጣት ሲገባው የውጭ ቅጥር ማስታወቂያ/ውድድር በማውጣቱ ምክንያት የእኛ የድርጅቱ የውስጥ ሠራተኞች ተወዳድሮ የማለፍ መብት ተጣሷል"[92] በሚል የሚቀርቡ ክሶች በእርግጥም ይህ ስለመሆኑ ቀላል ማስረጃ የሚሆነው አየር ላይ የዋለውን የውጭ ቅጥር ማስታወቂያ እንኳ ተገንጥሏል/ተቀዷል ወይም ማግኘት አልቻልንም በሚሉ የተለያዩ ምክንያቶች ከክሳቸው ጋር አያይዘው የማያቀርቡበትን ሁኔታ ማንሳት ይቻላል። በእርግጥም ይህ አይነቱ አጋጣሚ የሚፈጠረው የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ድንጋጌዎች ባለማወቅ ብቻ ሳይሆን በትክክልም ሠራተኞች/ከሳሾች እንዲህ አይነት ማስረጃዎችን የማግኘት እድላቸው የተጣበበ ስለሆነ ክሱን ተቀብሎ ተከሳሹ/አሠሪው በመከላከያ መልሱ ላይ የሚያቀርበውን መቃወሚያ ማየቱ ለከሳሾች የተሻለ ይሆናል በሚል ነው። ያም ሆኖ ግን በተለይ እንዲህ አይነት ክሶች በመጨረሻ ከሚያስከትሉት ውሳኔ ውጤት በፊት የተለያዩ የዕግድ ትዕዛዛትን አስቀድመው የሚያሰጡ ከመሆናቸውም አንጻር አሉታዊ ውጤትን በአሠሪውም ላይ ቢሆን እንዳያስከትሉ ተገቢውን ጥንቃቄ ከማድረግም ባለፈ ተከሳሹ ለቀረበበት ክስ የመከላከያ መልስ እንዲሰጥ መጥሪያ እንዲላክለት ከመጀመሪያውም የቀረበው ክስ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ[93] መሰረት ማሟላት ያለበትን ቅድመ-ሁኔታዎች አሟልቶ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ ብቻ መሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል።

---

[90] የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የፍትሐብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ አንቀጽ 33፣ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 3፣ 1958 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ።

[91] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 223(1)(ለ)

[92] በከሳሾች እነ ወ/ሮ አበባይቱ ቢወጣ (2 ሰዎች) እና የባህር ዳር ጨርቃ ጨርቅ አክ/ማ መካከል የነበረ ክርክር።

[93] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 90 አንቀጽ 233

በሌላ በኩል የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ከሳሽ ባቀረበው ክስና ማስረጃ ላይ ተከሳሹ የመከላከያ መልሱን እንዲያቀርብ ከተደረገ በኋላ ክሱን ለመስማት በተቀጠረበት እለት የባለጉዳዮች መቅረብ ከተረጋገጠ በኋላ ፍ/ቤቱ/ዳኛው ተከራካሪዎችን የመመርመር[94] ሥራውን እንደሚጀምር ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጅ የከሳሾችን ዕድል ለማስፋት ሲባል ምን አልባት በመጀመሪያ ክሳቸው ላይ ያላነሱት ነገር በተከሳሽ መልስ ላይ ተነስቶ ከሆነ ከቀረበው የመከላከያ መልስ ተነስተው የመልስ መልስ እንዲያቀርቡ የሚደረግበትን ስርዓት ዘርግቶ ቦርዱ ተግባራዊ እያደረገው ለመሆኑ አንድ እና ሁለት ብቻም ሳይሆን በቦርዱ ሙሉ መዛግብት ላይ የመልስ መልስ እንዲቀርብ የሰጣቸውን ትዕዛዛትም ብቻ ሳይሆን በዚሁ መልክ የሚቀርቡትን የመልስ መልሶችም በማየት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ቦርዱ ይህንን የክስ መስማት ሂደት ሲያከናውን የሥነ-ሥርዓት ህጉ በሚፈቅደው አግባብ ተከሳሹ በመከላከያ መልሱ ላይ በቀጥታ ወይም በነገሩ አካባቢያዊ ሁኔታ እንደተካደ የሚቆጠረውን ነገር ያምን እንደሆነ መጠየቅን ጨምሮ ሌሎች በቦርዱም ሆነ በተከራካሪ ወገኖች ሊጠየቁ የሚገባቸው ጥያቄዎች ካሉ ተነስተው መልስ እንዲያገኙ ማድረግም ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን በመደበኛ ፍ/ቤቶችም እንደሚስተዋለው ሁሉ በቦርዱም ዘንድ የዚህን ድንጋጌ አላማ ባላገናዘበ ሁኔታ "የቃል ክርክር" በሚል በተፈረጀ የክስ መስማት ሂደት ተከራካሪ ወገኖች በክሳቸው፣ በመከላከያ መልሳቸው እንዲሁም በመልስ መልሳቸው ያቀረቡትን ነገር መልሰው የሚደግሙበትን አሰራር የመከተል ዝንባሌ የሚንጸባረቅ መሆኑን ፀሀፊው በቦርድ አባልነቱ በተደጋጋሚ ለመታዘብ ችሏል፡፡ ምንም እንኳ ለችግሩ መቀጠል የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ያለማወቅ መነሻ ነው ቢባል እንኳ ዋነኛው ምክንያት ግን ይህ ሳይሆን የችሎት ቀናትና ሰዓታት ማነስ ካለው የመዝገብ ፍሰት ጋር ተዳምረው የቦርድ አባላት የቀረበውን ክስ፣ የመከላከያ መልስና የመልስ መልስ አስቀድመው በመመርመር በዚህ የክስ መስማት ሂደት መጣራት ያለባቸውን ነገሮች በመለየት ድንጋጌው በሚፈቅደው ልክ ለመምራት የሚያስችል ዕድል ማጣታቸውም ጭምር እንጅ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ እዚሁ ሳይነሳ ሊታለፍ የማይገባው ነገር ቢኖር ተከሳሾች ለቀረበባቸው ክስ በሚያቀርቡት የመከላከያ መልስ ላይ ምን አልባት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በሚያቀርቡበት ጊዜ ቦርዱ ሊያከናውነው የሚገባው ተግባር ነው፡፡ እንዲህ አይነት ሁኔታዎች ሲኖሩ ክርክሩን የሚሰማው ፍ/ቤት /ሌላ አካል/ በቀጣይ በሚደረገው የክርክር ሂደት ተጣርተው በሚወሰኑ ጉዳዮች/ጭብጦች ላይ ማስረጃ/ምስክር ከመስማቱ በፊት በቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ

[94] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 90 አንቀጽ 241

መቃወሚያዎች ላይ ውሳኔ መስጠት ይገባዋል።[95] ይሁን እንጅ በዋናነት ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የሥራ ጫና እና ሌሎች አጋር ምክንያቶች ተጨምረውበት ቦርዱ የሚቀርቡ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን አስቀድሞ በመለየትና ተገቢው ክርክር እንዲካሔድበት በማድረግ ውሳኔ ሰጥቶ በዝርዝር ሊጣሩ ወደሚገባቸው ክርክሮች በመግባት ረገድ ውስንነት ይታይበታል። ምን አልባትም የሚቀርቡ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ቦርዱ ክሱን ያቀረበው ሰው የሥራ መሪ በመሆኑ፣ ጉዳዩ የግል የሥራ ክርክር እንጅ የወል የሥራ ክርክር ባለመሆኑ ወይም በሌላ ምክንያት ቦርዱ የቀረበውን ክርክር የማየት ስልጣን የለውም የሚሉና በትክክልም መቃወሚያዎች ተቀባይነት ካገኙ የቀረበውን ክርክር ባለበት ሊያቋርጡ የሚያስችሉም ይሆናሉ። ያም ሆኖ ግን አልፎ አልፎም ቢሆን ክርክሩ አብቅቶ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ እንዲህ አይነት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችም ቀድመው ሳይወሰኑ የሚቆዩበትና አብረው ውሳኔ የሚያገኙበት አጋጣሚ ይስተዋላል።[96]

3.4 በስምምነት ከመፍታት አኳያ

ጉዳዮችን በስምምነት መፍታት መቻል ለቦርዱ በአማራጭነት ብቻም ሳይሆን በቅድሚያ ተግባርነትም ጭምር የተሰጠው ሀላፊነት መሆኑን ቀደም ሲል ለማየት ሞክረናል። በዚህም መሰረት በተቻለ መጠን የሚቀርቡ ጉዳዮችን በስምምነት ለመፍታትና በመጨረሻ ውሳኔ የሚያስከትለውን አሉታዊ ጎን ለመቀነስ ሲባል ቦርዱ በተቻለ መጠን እስከ ክርክሩ ማብቂያ ድረስ ተከራካሪዎች ይህንን እንዲያደርጉ ተገቢውን ጥረት የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ በተቻለ መጠን ከሶስቱም አካላት ተወካይ የቦርድ አባላትን ከጽ/ቤት ሀላፊዋ ጋር ጭምር ክርክሩ ከተነሳበት ድርጅት ድረስ በመላክ የሚመለከታቸው የድርጅቱ የበላይ ሀላፊዎች በተገኙበት በስምምነት ለመፍታት የሚደረገው ቁርጠኝነት ከፍተኛ ነው።

ያም ሆኖ ግን በተለይ ድርጅቶች የሚሠሩትን መዋቅራዊ ለውጥ ተከትሎ የሚነሱ ክርክሮችን በዚህ አግባብ ለመፍታት እጅግ ፈታኝ የሚሆንበት አጋጣሚ ቀላል አይደለም። እንዲህ አይነት መዋቅሮች በዋናነት/በቅድሚያ ታሳቢ የሚያደርጉት ድርጅቱ አዲሱን መዋቅር ተከትሎ ወደፊት

[95] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 144(1) እና አንቀጽ 145

[96] በከሳሾች እነ ወ/ሮ ውዴ በላይ (2 ሰዎች) እና በተከሳሽ አውስኮድ፣ በከሳሽ አቶ ጥላሁን ባዬ እና በተከሳሽ ጣና በለስ ስኳር ልማት ፕሮጀክት እንዲሁም በከሳሽ ሊቀ ትጉኃን ቆሞስ አባ ገ/ሚካኤል ጫኔ እና በተከሳሽ የባ/ዳር ከተማ ሀገረ-ስብከት መካከል በነበሩት ክርክሮች ላይ በተለያዩ ምክንያቶች ቦርዱ ጉዳዩን የማየት የስረ-ነገር ስልጣን የለውም የሚሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ምንም እንኳ በመጨረሻም ቢሆን በቦርዱ ተቀባይነት ያገኙ ባይሆኑም ቅሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎቹ ላይ ብይን ሳይሰጥ ታልፎ በክርክሩ ማብቂያ አብረው ውሳኔ ካገኙ መዛግብት/ጉዳዮች መካከል ለማሳያነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

ሊያሳካ የሚችለውን አላማ/ትርፍ እንደመሆኑ መጠን በድርጅቱ ውስጥ ያሉትን ሠራተኞች የትምህርት ዝግጅትም ሆነ የሥራ ልምድ ሙሉ በሙሉ ታሳቢ ያደረጉ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታዎች በተለይም ዝቅተኛ የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ ያላቸው ሠራተኞች ዕጣ ፈንታ አደጋ ላይ የሚወድቅበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡ በዚህ ጊዜ መዋቅሩ በሚጠይቀው መስፈርት አግባብ የሚፈልጉትን ቦታ ያጡ ሠራተኞችን በአዋጁ መሰረት ተገቢውን ክፍያ በመፈጸም ከማሰናበት ይሻላል በሚል ቅን ልቦና ድርጅቱ ይመጥናል ያለውን የሥራ መደብ በፍረጃም ይሁን በሌላ ሁኔታ የሚያደርገውን ምደባ እንዲሁም መዋቅሮች በራሳቸው አዋጁ ለሠራተኞች የሚሰጠውን ነጻ የውድድር መብት በሚጥስ መልኩ መጠናታቸውንና መተግበራቸውን ተከትሎ የሚነሱት ክርክሮች ቀላል አይደሉም[97]፡፡

በሠራተኞቹ የቀረቡት ክርክሮቹ በቦርዱ ዘንድ ተቀባይነትን አግኝተው ሲወሰኑ ደግሞ ሠራተኞች የሚጠይቋቸው የሥራ መደቦችና ደረጃዎች በሌሎች ሠራተኞች ቀድመው የሚያዙበት አጋጣሚ ሰፊ ከመሆኑ አንጻር የሚሰጡ ውሳኔዎችን መፈጸም እጅግ ፈታኝና ጠቅላላ የተሰራውን ሥራ የሚነካበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ እንዲህ አይነት ስጋቶችን በመፍራትም በአሠሪ ድርጅቶች ዘንድ መዋቅሮችን እስከማስተካከል ደረጃም ድረስ አስፈላጊው ርምጃ ተወስዶ ጉዳዮችን በስምምነት ለመፍታት ፍቃደኛ ቢሆኑም ይህንን ለማድረግ ግን የሚጠይቁት ጊዜ የቀረበውን ጉዳይ አዋጁ ባስቀመጠው የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለመጨረስ ይቅርና ቦርዱ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ለመስጠትም አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡[98] ከዚህም ባለፈ ይባስ ብለው ስህተታቸውን አይተው ለማረምና ከሠራተኞች ጋር ተግባብተው ጉዳዩን በስምምነት ለመጨረስ ቸልተኛ የሚሆኑና ቦርዱ ጉዳዮችን በስምምነት ለመጨረስ የሚያደርገውን ከልክ ያለፈ ትዕግስትና ከተገቢው በላይ የሆነ ጊዜ መስጠትም ሳይቀር ዋጋ የሚያሳጡ ድርጅቶችም የሚያጋጥሙ መሆኑን ፀሀፊው በሥራው አጋጣሚ ለመታዘብ ችሏል፡፡

ከዚህም ባሻገር የቦርድ አባላት የቀረቡ ጉዳዮችን በስምምነት ለመጨረስ የተጣለባቸውን ከባድ ሀላፊነት ከመወጣትም ባለፈ በተለይ የቀረቡት ጉዳዮች በውሳኔ ቢያልቁ በድርጅቱ የኢንዱስትሪ

[97] በከሳሽ እነ አቶ ባዩ በቃሉ (7 ሰዎች) እና በተከሳሽ የአማራ ዲዛይንና ቁጥጥር ሥራዎች ድርጅት መካከል መዋቅርን ተከትሎ የተነሳውን ከምደባ ጋር የተያያዘ ክርክር ለአብነት ብንመለከት ቦርዱ ከአንድም ሁለት ጊዜ ያደረገውን የማስማማት ጥረት ተከትሎ ግራ ቀኙ ጉዳዩን በሂደት (በተወሰኑ ወራት ውስጥ) በስምምነት ለመፍታት በደረሱት ስምምነት መሰረት (ስምምነቱ ከመጀመሪያውም የራሱ የሆነ ውስንነት የነበረው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ) ቦርዱ መዝገቡን ዘግቶት የነበረ ቢሆንም አሠሪው ሊፈጽምላቸው ባለመቻሉ ምክንያት ተመልሰው ወደ ቦርዱ የመጡበትን አጋጣሚ ለአብነት ማንሳት ይቻላል፡፡ እንዲሁም የተወሰኑ የድርጅቱ ሰራተኞች ከሳሽ የነበሩበት እና በተከሳሹ የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ አክሲዮን ማህበር መካከል የነበረ ክርክር፣ 2011 ዓ.ም፡፡

[98] ዝኒ ከማሁ

ሰላም ላይ ትልቅ ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ ተብለው በሚታመኑት ላይ የጉዳዮቹ ባለቤቶችና የድርጅቶች ሀላፊዎች በተገኙበት በስምምነት ለመጨረስ ይደረግ የነበረው የከተማ ውስጥ እንቅስቃሴ አበል እንዲከፈል ከተፈቀደባቸው የችሎት ቀናት ውጭ ነው በሚል ክፍያ ላለመፈጸም በቢሮው ፋይናንስ በኩል የተደረሰበት ውሳኔም ሌላው መጠነኛ ችግር ነው፡፡ ምንም እንኳ ስምምነቱ ከሚከናወንበት አላማ እንዲሁም የቀረቡ ጉዳዮችን በተቻለ ፍጥነት ከመቋጨት አንጻር ያለው ፋይዳ ከፍተኛ በመሆኑ ያለ አበልም ቢሆን ሥራው እየተሠራ የሚገኝ ቢሆንም ቢያንስ የሥራ ተነሳሽነትን በመቀነስ ረገድ ግን ችግር ማስከተሉ አይቀርም፡፡ በተለይ ደግሞ በሁለቱ ቀናት ብቻ ሥራዎች ተሰርተው የማያልቁ ከመሆኑ አንጻር በዚህ ምክንያት የተፈጠረው መጠነኛ ችግርም ቢሆን እንዲቀረፍ ጽ/ቤቱ ለቢሮው ለማሳወቅም[99] ተገዷል፡፡ ይሁን እንጅ ቢሮውም ቢሆን ከጽ/ቤቱ የተለዩ ሀሳብ የሌለው መሆኑን ተከትሎ የተለያዩ የማስተካከያ ዕርምጃዎች እንዲወሰዱ የበኩሉን ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡[100]

3.5 ውሳኔዎችን ከማስፈጸም አንጻር

ቦርዱ በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኝ ካልጠየቀ በስተቀር የሚሰጠው ውሳኔ ወዲያውኑ ተፈጻሚነት የሚኖረው መሆኑን ቀደም ሲል ተመልክተናል፡፡ በመደበኛው ፍ/ቤት የሚሰጡ ውሳኔዎችም ቢሆኑ በራሳቸው ውጤት ካለመሆናቸው የተነሳ በክርክሩ ሂደት ረች የሆነው ወገን የሚፈልገውን ውጤት ያገኝ ዘንድ የተሰጠው ውሳኔ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ አሠሪና ሠራተኛን የሚመለከቱ ክርክሮች ደግሞ ካላቸው ልዩ ባህሪ የተነሳ በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ መቋጨት አለባቸው፡፡ ለዚህም ነው ክርክሮቹ በምን ያህል ጊዜ ውሳኔ ማግኘት እንዳለባቸው የጊዜ ገደብ እንደተቀመጠው ሁሉ የተሰጡ ውሳኔዎችም በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ካልተፈጸሙ በይርጋ ቀሪ ሊሆኑ እንደሚችሉ ህጉ ያስቀመጠው፡፡[101] ይሁን እንጅ ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረውም በተለይ ድርጅቶች የሚተገብሩትን አዲስ መዋቅር ተከትሎ የሚነሱ ክርክሮች በስምምነት ካላለቁ በስተቀር ለሠራተኞች የሚወሰኑ ውሳኔዎችን ለማስፈጸም ፈተናዎች ብዙ ናቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ ዋነኛው ምክንያት ከሳሾች የሚጠይቋቸው ቦታዎች (የሥራ መደቦችና ደረጃዎች) መዋቅሩን ተከትለው ቀድመው በሌሎች ሠራተኞች የሚያዙ

---

[99] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 87

[100] በቢሮው አዘጋጅነት ከምዕራብ እና ምስራቅ አማራ ቋሚ እና ጊዜያዊ ቦርዶች አባላት ጋር የተደረገ ውይይት፣ ሰኔ 28 ቀን 2011 ዓ.ም፣ እንጅባራ-ኮሶበር፡፡

[101] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9 አንቀጽ 162(1) (አዲሱ አዋጅ አንቀጽ 163(1)፡፡ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 11 በሰ/መ/ቁ/ 53527 በአመልካች የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና በተጠሪ አቶ በዳሶ መልካቶ መካከል በነበረው ክርክር በቀን 27/01/2003 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፡፡

መሆናቸው ነው። ከዚህም ሌላ የተወሰኑ የአፈጻጸም ባለዕዳ የሆኑ ድርጅቶች ቅርንጫፎቹ ባህር ዳር ከተማ የሚገኙ ቢሆኑም እንኳ ዋና መስሪያ ቤቶች አዲስ አበባ የሚገኙ ከመሆኑም ጋር በተያዘ የሚኖረውን የመላላክና የመጻጻፍ ሂደት ተከትሎ ውሳኔዎቹን ወዲያውኑ ለመፈጸም እንዳይቻል ከሚያደርጉት ተጨማሪ ሳንካዎች መካከል አንዱ ነው። በዚህም የተነሳ ምንም እንኳ ውሳኔዎች የኋላ ኋላ መፈጸማቸው የማይቀሩ ቢሆንም በመካከሉ የሚወስዱት ጊዜም ሆነ የውሳኔ ባለመብት በሆኑ ሠራተኞች ላይ የሚፈጥሩት እንግልት ግን ቀላል አይደለም።[102]

ከዚህም ባሻገር ቦርዱ በከፍተኛ ድካም እና እንግልት በስምምነት እንዲቋጩ ተገቢው መግባባት ላይ ሳይቀር የተደረሰባቸውን ጉዳዮችም ቢሆን በስምምነቱ ወቅት በነበረው ፍላጎትና ቅንነት ልክ ከመፈጸም ይልቅ የተለያዩ ምክንያቶችን በመፍጠር ስምምነቶችን ወደ ጎን የሚተዉ አሠሪዎችም አይጠፉም።[103]

3.6 ከአባላት ተሟልቶ መገኘት አንጻር

ቦርዱ የሚቀርቡለትን ጉዳዮች አይቶ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ ለመስጠትም ይሁን የክርክር ሂደቱን በአግባቡ ለመምራት አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ከቦርድ አባላት መካከል የተወሰኑት መገኘት ያለባቸው እና ምልዓተ-ጉባዔው መሟላት የሚገባው መሆኑን ቀደም ሲል ለማየት ሞክረናል። ከዚህም ባሻገር የቦርዱን አባላት ምልዓተ-ጉባዔ ከማሟላት በተጨማሪ የክርክር ሂደቱን በአግባቡ ለመምራትም ሆነ የሚሰጡ ትዕዛዛት እና ውሳኔዎች በተለያዩ የቦርድ አባላት ሀሳብ የዳበሩ እንዲሆኑ ለማስቻል የአባላቱ መሟላት ፋይዳው የጎላ ነው። ይሁን እንጅ የቦርድ አባላት ይህንን ስራ የሚያከናውኑት ካላቸው መደበኛ ሥራ በተጨማሪነት እንደመሆኑ መጠን በሥራ መደራረብና በሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች የአባላት በችሎት ቀን ተሟልቶ አለመገኘት አንዱ ችግር ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ጉዳዮችን በስምምነት ለመጨረስ አይደለም ለችሎት ቀናት እንኳ ለመገኘት አስቸጋሪ የሆነበት የቦርድ አባልን አሠሪ ተቋም የሚመለከተው አካል ቦርዱ ጠርቶ ችግሩን ለመፍታት የተሞከረበትን አጋጣሚ ሳይቀር ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።[104]

---

[102] በአፈ/ከሳሾች እነ አቶ ገብሬ ማሬ (3 ሰዎች) እና በአፈ/ተከሳሽ የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ድርጅት ባህር ዳር ቅርንጫፍ መካከል ምደባን በተመለከተ የቀረበውን ክርክር ተከትሎ የተሰጠውን ውሳኔ ለመፈጸም የፈጀው ጊዜ ቀላል የሚባል አይደለም። (በመሀል የተወሰነ ጊዜ ተፈጽሟል በሚል ተቋርጦ የቆየ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ውሳኔው ሙሉ በሙሉ በአግባቡ እንዲፈጸም ግን ከ5 ወራት ያላነሰ ጊዜ የፈጀ መሆኑን ለመታዘብ ይቻላል።)

[103] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 97

[104] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 100

3.7 ከቦርድ አባላት ክፍያ አኳያ

የምዕራብ አማራ ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ከመደበኛ ፍ/ቤቶችም ሆነ ከሌሎች የአስተዳደር ፍ/ቤቶች በተለዬ ሁኔታ መደበኛ ተግባሩን የሚያከናውነው ከሳምንት ሁለት ቀናት ብቻ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ቦርዱ በመደበኛነት የሚሰሩ ዳኞች የሌሉት መሆኑን ተከትሎ በእነዚሁ የተወሰኑ ቀናት ብቻ ተገኝተው የቦርዱን ሥራ በሚያከናውኑ የቦርድ አባላት አማካኝነት ሀላፊነቱን እንዲወጣ ተደርጎ ተደራጅቷል፡፡ በመሆኑም ከመደበኛ ሥራዎቻቸው ባሻገር ይህንን የቦርድ ተግባር ለሚያከናውኑ የቦርዱ አባላት የተወሰነ አበል ሥራዎቻቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ብቻ የሚከፈል መሆኑንም ቀደም ሲል ለማየት ተሞክሯል፡፡

ምንም እንኳ የክልሉን የመክፈል አቅም መሰረት በማድረግ ለተለያዩ ሥራዎች የተለያዩ የክፍያ መጠኖች የሚወሰኑ ቢሆንም በተለይ ቦርዱ ከሚያከናውነው ተግባር አንጻር ሲታይ ግን ይህ የአበል ክፍያ በየትኛውም መመዘኛ ቢሆን በቂ ነው ሊባል አይችልም፡፡ የክፍያው ማነስ የቦርድ አባላቱ ሥራቸውን በአግባቡ እንዳይወጡና በሥራውም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አድርጓል ባይባልም በተለይ አሁን ላይ ካለው የገንዘብ የመግዛት አቅም አንጻር ሲታይ የሚከፈለው የአበል መጠን በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ግልጽና የቦርድ አባላትም የሚስማሙበት ሀቅ ለመሆኑ ለዚሁ ዕሁፍ አላማ ከሞሉት የጽሁፍ መጠይቅ በቀላሉ መታዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም ባሻገር የችግሩን መኖር ተገንዝቦ ጽ/ቤቱ ለቢሮው እያቀረበ[105] የሚገኝ ከመሆኑም በላይ ቢሮውም ቢሆን የጥያቄውን ተገቢነት ተቀብሎ ሌላው ቢቀር እንኳን ቢያንስ ቢያንስ በ2009 ዓ.ም በቢሮው በኩል እንደመነሻ ቀርቦ ነገር ግን ከ58% በታች ተቀንሶ ተግባራዊ እንዲደረግ የተወሰነውን የክፍያ መጠን ዛሬም ቢሆን ተፈጻሚ እንዲሆን ጥያቄውን በድጋሚ ለሚመለከተው አካል እያቀረበ ያለ መሆኑ ሲታይ የችግሩን መኖር ለማረጋገጥ ተጨማሪ ማሳያ ነው፡፡[106]

[105] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 87

[106] የክልሉ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በቁጥር ሠማጉ/ምዲ/ልዩ-1/10384 በቀን 21/10/2011 ዓ.ም ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ የጻፈው 4 ገጽ ደብዳቤ፡፡

ክፍል አራት
ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሀሳቦች

4.1 ማጠቃለያ

የምዕራብ አማራ ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በአዋጁ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በተቀላጠፈና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማከናወን ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ ይህንን ሀላፊነት ለመወጣትም የቦርዱ ጽ/ቤት ሀላፊ ጉዳዮችን ለአባላቱ ግልጽ (ብሪፍ) ማድረግና የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብን ጨምሮ እያከናወኑ ያሉት ተግባር፣ በጽ/ቤቱ ስር የሚገኙ ሌሎች ባለሙያዎች የጽ/ቤቱን ሥራ በቅልጥፍናና በውጤታማነት ከማከናወን አንጻር ያላቸው ቅንነትና የሥራ ተነሳሽነት፣ የቦርድ አባላት የትኞቹንም አይነት አሉታዊ ምክንያቶች ግምት ውስጥ ሳያስገቡ መደበኛውና ተቋማዊ ሀላፊነታቸው ሳይገድባቸው የቦርዱን ተግባር ውጤታማ ለማድረግ በተቻለ መጠን ሁሉ እያደረጉት የሚገኘው እንቅስቃሴ እንዲሁም ጉዳዮችን በስምምነት መቋጨት ያለውን ከፍተኛ ፋይዳ ግምት ውስጥ በማስገባት የሚቀርቡ ክርክሮችን ከቦታው ድረስ በመሄድ በስምምነት ለመፍታት የሚከናወኑት ተግባራት ለቦርዱ በከፍተኛ ጥንካሬ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ይሁን እንጅ ቦርዱ ስልጣንና ተግባሩን ከዚህም በላይ በሆነ ደረጃ ለመፈጸም ይችል ዘንድ በህጉ ከተሰጠው ትኩረት ማነስ ጀምሮ እስከ ውሳኔዎች አፈጻጸም ድረስ የሚስተዋሉ ውስን ክፍተቶች መኖራቸውን ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ውስንነቶች በመድፈን እንዲሁም ያሉትን በርካታ ጥንካሬዎች ደግሞ ይበልጥ በማጠናከር የዜጎችን ፍትህ የማግኘት መብት በማረጋገጥ ረገድ ድርሻውን ያበረክት ዘንድ የአብክመ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮን ጨምሮ ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ሊያደርጉለት ይገባል፡፡

4.2 የመፍትሔ ሀሳቦች

በምዕራብ አማራ ቋሚ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የሚስተዋሉ ውስን ክፍተቶች በቀጣይ በሚወሰዱ አወንታዊ ርምጃዎች አማካኝነት ታግዘው ቦርዱ አሁን ላይ ካለውም ከፍተኛ አፈጻጸም ይበልጥ ተጠናክሮ ተከራካሪዎች የሚተማመኑበትና የሚኮሩበትም ብቻ ሳይሆን ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ይሆን ዘንድ በመጠኑም ቢሆን ከላይ ለተጠቃቀሱ ውስንነቶችና ሌሎችንም ያልተነሱ ቀዳዳዎችን ለመድፈን ያመች ዘንድ የሚከተሉት የመፍትሔ ሀሳቦች በአጭሩ ቀርበዋል፡፡

፩. የቦርዱን ስልጣንና ተግባር ከመወሰን፣ ከማደራጀት፣ ከተተኪ የቦርድ አባላት፣ ከምልዓተ-ጉባዔ፣ ከይግባኝ አንጻር እንዲሁም ከዚህ በፊት ከአዋጁ ድንጋጌ አኳያ የተነሱ ውስንነቶችን በሚሞላ መልኩ ከማደራጀት አንጻር ጠንካራ የሆነ ቦርድ እንዲደራጅ ቢያደርግ ከእስካሁኑም በላይ መልካም ሥራ ሊሠራ ይችላል፡፡ *(ይሁን እንጅ አዲሱም አዋጅ ቢሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ የለወጠው ነገር ካለመኖሩ አንጻር በዚህ ረገድ የሚነሱት ችግሮች መቀጠላቸው የሚቀር አይመስልም፡፡)* በተለይም የቦርድ አባላትን ስብጥር አስመልክቶ በቂ የሕግ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች በበቂ ሁኔታ የቦርዱ አባል እንዲሆኑ ከማድረግ ባለፈ ከአሠሪውም ይሁን ከሠራተኛው የሚኖረው ውክልናም ቢሆን በተቻለ መጠን ይህንንም በተጨማሪነት ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ቢችል በሁለት ስለት እንደመቁረጥ የሚቆጠር እንጅ የተለየ ችግር የማያስከትል እስከሆነ ድረስ ከዚህ አንጻር ያለው ውስንነት በትኩረት ሊታይ ይገባዋል፡፡

፪. በተለይ ቦርዱ ከሳምንት ለሁለት ግማሽ ቀናት ብቻ የሚሠራ መሆኑን ተከትሎ አሁን ላይ እየቀረቡ ያሉትን ጉዳዮች አዋጁ እንዲቋጩ በሚፈልገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ አዳጋች እየሆነ የመጣ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም ለዚሁ የሚመጥነውን ክፍያ በማመቻቸት የቦርዱን የሥራ ጊዜ/ቀናት መጨመር፣ የችሎቶችን ቁጥር መጨመር እንዲሁም የቦርድ ጽ/ቤቶችን ቁጥር ማብዛት ድረስ ያሉት አማራጮችን ግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ረገድ ያለውንም ሆነ ሌሎች ተያይዘው የሚነሱ ችግሮችን ዘላቂነት ባለው ሁኔታ ለመፍታት የሚያስችሉ አማራጮችን ለመጠቀም የሚያስችሉ ሥራዎች ሊሠሩ ይገባል፡፡

፫. የቦርዱን ትዕዛዛትና ውሳኔዎች በተሻለ ሁኔታ ለማስፈጸምም ይረዳ ዘንድ በመደበኛነትም ይሁን በተወሰነ ጊዜ የሚሠራ የፖሊስ ባልደረባ ችሎት አስከባሪ እንደ አዲስ አበባው ተመሳሳይ ቦርድ ሁሉ ቢመደብለት፡፡ የዚህ ችግር መፈታት ምን አልባትም ቦርዱ የችሎት ሥራውን

በሚያከናውንባቸው ቀናት ከሚኖረው ጠቀሜታ ባሻገር በተለይ ከአፈጻጸም ጋር በተያያዘ ተገደው እንዲቀርቡ የግድ በሚሉ ሁኔታዎች ላይ የሚመለከታቸውን የአፈ/ተከሳሾች (የድርጅት ሀላፊዎች) እንዲቀርቡ በማድረግ ረገድ ከሌሎች የፖሊስ ተቋማት ጋር የሚደረገውን መላላክ/መጻጻፍ በመቀነስ በኩልም የሚኖረው ፋይዳ የጎላ ነው።

፬. ምንም እንኳ የቦርድ አባላት በአሠሪና ሠራተኛ ህጎች ዙሪያ በቂ ዕውቀትና ልምድ ኑሯቸው የሚመረጡና ከሥራ ቆይታም አንጻር ልምድ ያካበቱ እንደሚሆኑ ቢታወቅም ስልጠናዎችን የማግኘት ዕድላቸው እጅግ የተመናመነ ከመሆኑ አንጻር በተለይ የፍ/ሔር ሥነ-ሥርዓት ህጉን እንዲሁም የአሠሪና ሠራተኛ አዋጆችን ጨምሮ በተለይም ከቦርዱ ስልጣን ጋር በተገናኘ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰ/ሰ/ችሎቱ በሚሰጣቸው አስገዳጅነት ያላቸው ውሳኔዎች ዙሪያ የሚመለከታቸው አካላት በተናጠልም ይሁን በጋራ በመሆን ስልጠና እንዲያገኙ ቢደረግ የተሻለ ይሆናል። ከዚህም ባሻገር የቦርድ አባላቱን ስብጥር ቀደም ሲል ለማየት እንደሞከርነው ከሰባቱ አራቱ ከአሠሪውና ከሠራተኛው አካል የሚወከሉ ከመሆናቸው አንጻር ምን አልባት በአዋጁ ዙሪያ በቂ ዕውቀትና ልምድ የሚኖራቸው መሆኑ ግምት ውስጥ የሚገባ ከመሆኑ ባሻገር የሕግ ባለሙያ እንዲሆኑ የማይጠበቅባቸው ከመሆኑም በላይ የሕግ ባለሙያ የሆኑ ከሠራተኛውም ይሁን ከአሠሪው አካል ቢኖሩም እንኳ በተለያዩ አጋጣሚዎች ላይመረጡ የሚችሉበት ባስ ሲልም ላይኖሩም የሚችሉበት አጋጣሚ ይኖራል። ከዚህ አንጻር በተለይ የፍ/ሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ እንዲሁም የማስረጃ አቀባበል እና ምዘናን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ላይ የተወሰነም ቢሆን ውስንነት ሊያጋጥማቸው የሚችል መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ደግሞ ምን አልባት የመጨረሻው ውሳኔ አዋጁ ላይ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መከበርና መጣስ አንጻር መሰረት አድርጎ የሚወሰን ከመሆኑ አኳያ በውጤት ደረጃ ለውጥ (የመብት ጥሰት) ላይፈጥር የሚችልበት አጋጣሚ ቢኖር እንኳ ከሥነ-ሥርዓት እና ከማስረጃ ሕጋችን አንጻር ያሉትን ድንጋጌዎች በአግባቡ ስራ ላይ ባለማዋል ምክንያት ግን ሁልጊዜም ቢሆን የሚፈጠር ችግር የለም ብሎ መደምደም አያስችልም። በመሆኑም ለዚህ ሲባል ሁሉም የቦርድ አባላት የሕግ ባለሙያ መሆን አለባቸው የሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ባይቻልም ቢያንስ ቢያንስ ግን መሰረታዊ የሆኑ ድንጋጌዎች (ህጎች) ላይ ግን ተከታታይነት ባለው ሁኔታ አጫጭር ስልጠናዎችን ሊያገኙ ይገባቸዋል።

፭. በቦርድ አባልነት የሚያገለግሉ ባለሙያዎች ከሚሰሩባቸው ተቋማት ጋር ጥብቅ የሆነ ግንኙነት በመፍጠር በተቻለ መጠን ለችሎት ቀናትም ይሁን ቦርዱ ጉዳዮችን በስምምነት ለመጨረስ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ተቋማቱ ተገቢው ዕውቅና ኑሯቸው አባላቱ ሳይሳቀቁ

ሥራቸውን የሚሠሩበትን ሁኔታ ጽ/ቤቱ ወይም ቢሮው የበኩሉን ጥረት ቢያደርግ መልካም ነው፡፡ ምንም እንኳ በተለያዩ ተቋማዊ ሀላፊነቶች እና ሌሎች ምክንያቶች የተነሳ የቦርድ አባላት ከችሎት የሚቀሩበት አጋጣሚ መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ በተቻለ መጠን አባላቱ ሙሉ በሙሉ በችሎት መገኘታቸው ካለው ከፍተኛ ፋይዳ አንጻር አባላቱም ቢሆኑ ከአቅም በላይ እስካልሆነባቸው ድረስ ለመገኘት የሚያደርጉትን ከፍተኛ ጥረት አጠናክረው መገኘት ቢችሉ መልካም ነው፡፡

፮. ልምድ ያላቸው የቦርድ አባላት በተመሳሳይ ጊዜ በሚለቁበት ጊዜ የሚፈጠረውን ክፍተት ከመቀነስ አንጻር መነሳት ያለበት ነገር ቢኖር የአባላት የሥራ ዘመን በአመት በአመት የተከፋፈለ እንዲሆን አዋጁም ቢሆን በግልጽ ቢያስቀምጥም ቅሉ በወራትም ጭምር መለያየቱ ግን ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ ለአብነት በ2011 በጀት አመት 3ቱ የአገልግሎት ዘመናቸው በማብቃቱ አንዱ ደግሞ የሥራ ቦታ በመቀየሩ የተነሳ በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ 4ቱ የቦርድ አባላት የለቀቁበት ሁኔታ በተቻለ መጠን ወደፊት እንዳይከሰት ተገቢው ጥንቃቄ ቢደረግ መልካም ነው፡፡

፯. ጉዳዮችን በስምምነት ለመጨረስ የሚደረገው ጥረት እንደተጠበቀ ሆኖ ምን አልባት ጉዳዮች በስምምነት ማለቅ ካልቻሉ በመጨረሻ የሚሰጠው ውሳኔ የድርጅቱን ጠቅላላ የሥራ እንቅስቃሴ ሊጎዳ ይችላል በሚል በተለይ ከመዋቅር ጋር በተያያዘ በሚነሱ ክርክሮች አልፎ አልፎም ቢሆን ጉዳዮችን በስምምነት እንዲጨርሱ ሲባል የሚሰጠው ረዘም ያለ ጊዜና ከመጠን ያለፈ ትዕግስት በመጠኑም ቢሆን ሊታሰብበት ይገባል፡፡ ለዚህ ደግሞ በተለይ የአሠሪ ድርጅቶች የበላይ አመራሮች/ሀላፊዎች ትልቅ ትኩረት ሰጥተው ከተቻለ በአጭር ጊዜ ጉዳዮችን በስምምነት ለመጨረስ መሞከር ካልተቻለ ደግሞ ቦርዱ የሚሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ ለመፈጸም ዝግጁ ሊሆኑ ይገባል፡፡

፰. ቦርዱ ተግባሩን የሚያከናውነው በተወሰነ ጊዜ እንደመሆኑ መጠን አባላቱም ችሎት ለሚገኙበት ቀን የተወሰነ ክፍያ የሚፈጸምላቸው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጅ የክፍያው መጠን ያን ያህል የአባላቱ የመጀመሪያውና አንገብጋቢው ጉዳይ/ሀሳብ ባይሆንም ክፍያ ይፈጸማል እስከተባለ ድረስ ግን በተቻለ መጠን ወቅቱን ያገናዘበ ክፍያ ቢፈጸም የተሻለ ስለሚሆን የክልሉ/የቢሮው የመክፈል አቅም እንደተጠበቀ ሆኖ ማስተካከያ ቢደረግበት መልካም ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቦርድ አባላት በከተማው ውስጥ ለስምምነት በየተቋማቱ

በሚንቀሳቀሱበት ወቅት ይፈጸም የነበረውን ይህንንም ክፍያ ከችሎት ቀናት ውጭ ስለሆነ በሚል እንዲቀር የተደረገበት ሁኔታም ቢሆን ችግሩን ከድጡ ወደ ማጡ እንዲሉት የማድረግ እድልም ስለሚኖረው ቢታሰብበት መልካም ነው።

፱. ቦርዱ የሚያስችልበት (መደበኛ ሥራውን የሚያከናውንበት) ቢሮ ለዚሁ አላማ ታስቦ ያልተሠራ እንደመሆኑ መጠን እንኳንስ በርከት ያለ ቁጥር ያላቸው ተከራካሪዎች ተጨምረውበት 7ቱ የቦርድ አባላት፣ የጽ/ቤት ሀላፊዋን እንዲሁም ችሎት ፀሀፊውንም በአግባቡ ለማስተናገድ የሚችል ስፋት የለውም። በመሆኑም በተቻለ መጠን ቢሮው ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ሰፋ ያለና ለባለጉዳዮች ምቾት የሚሰጥ ቢሮ/አዳራሽ ቢያመቻችለት መልካም ነው። ከዚህም ሲብስ ተከራካሪ ወገኖች ቆመው የክስ ሂደቱን የሚከታተሉበት ቦታ የሚያፈስ መሆኑን ተከትሎ በተለይ በክረምት ወቅት በተከራካሪ ወገኖችም ሆነ በችሎቱ ሥራ ላይ የሚፈጥረው ተጽዕኖ ቀላል ባለመሆኑ አፋጣኝ መፍትሔ የሚሻ ጉዳይ ነው።

ትርጓሜያዊ የማግለል ጽንሰ-ሃሳብ በኢትዮጵያ የአሠሪ እና ሠራተኛ ሕግ

በወርቁ ካሳው ጸጋዬ♣

አህጽሮተ ይዘት

በአሠሪ እና ሠራተኛ ሕግ ውስጥ ማግለል ማለት የተወሰኑ አሠሪዎችን እና ሠራተኞችን ከሕጉ የሚመነጩ መብቶችን፣ ጥቅሞችን እና ጥበቃዎችን መከልከል ማለት ሲሆን አንድ የሥራ ግንኙነት በአሠሪ እና ሠራተኛ መካከል መደረጉ፣ የስራ ግንኙነቱ በቅጥር ላይ ተመስርቶ መፈጸሙ እና የሥራ ውል መኖሩ ብቻውን በአሠሪ እና ሠራተኛ ሕግ የሚዳኝ የስራ ግንኙነት አያደርገውም። ይልቁንም ይህ የሥራ ግንኙነት በሕጉ የትርጉም ክፍል አሠሪ፣ ሠራተኛ እና የሥራ ውል ለሚሉት ነጥቦች የተሰጠውን ትርጓሜ ያሟላል ወይስ አያሟላም፣ የሚያሟላስ ከሆነ የሕጉን የተፈጻሚነት ወሰን በሚደነግገው ክፍል ስር በቀጥታ ወይም በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሰረተ የማግለል ተግባር ተፈጽሞበታል ወይስ አልተፈጸመበትም የሚሉትን ነጥቦች ማየት ተገቢ ይሆናል። በአዋጁ የትርጉም ክፍል አሠሪ፣ ሠራተኛ እና የሥራ ውል ለሚሉት ነጥቦች የተሰጠውን ትርጉም የሚያሟሉት በቅጥር ላይ የተመሰረቱ የሥራ ግንኙነቶች ላይ አዋጁ በቀጥታ ወይም በቅድመ-ሁኔታ ላይ ተመስርቶ እስካላገለላቸው ድረስ አዋጁ ተፈጻሚ ይሆናል። በሌላ በኩል በአዋጁ የትርጉም ክፍል አሠሪ፣ ሠራተኛ እና የሥራ ውል ለሚሉት ነጥቦች የተሰጠውን ትርጉም የማያሟሉት በቅጥር ላይ የተመሰረቱ የሥራ ግንኙነቶች ትርጓሜያዊ በሆነ መንገድ የተገለሉ ስለሆኑ አዋጁ ተፈጻሚነት አይኖረውም። ሕጉ "አሠሪ"፣ "ሠራተኛ" እና "የሥራ ውል" ለሚሉት ነጥቦች የሰጠው ትርጉም ግልጽነት የጎደለው በመሆኑ በተለይም አንድን ቀጣሪ ድርጅት ብሎም አሠሪ ለማለት በምሑራን ዘንድ "ድርጅት"፣ "ሕጋዊ ሰውነት"፣ "ለትርፍ መቋቋም"፣ "ሕጋዊ ዓላማ" እና "የአንድ አመራር ጽንሰ-ሃሳብ" የሚሉት ነጥቦች የተለያየ አቋም የሚያዝባቸው እና አሻሚ የሆኑ ሐረጋት ናቸው። ከዚህ በመነሳትም ይሕ ጥናታዊ ጽሑፍ ትርጓሜያዊ ማግለልን በመወሰን ረገድ አዋጁ አሠሪ፣ ሠራተኛ እና የሥራ ውል ለሚሉት ቃላት ከሰጣቸው ትርጓሜያት አንጻር ከሕጉ የሚመዘዙ አንኳር የሕግ እና የፖሊሲ ጥያቄዎችን ከተለያየ አቅጣጫ በማንሳት ጽንሰ-ሃሳባዊ በሆነ የጥናት ዘዴ (Doctrinal Research Methodology) ጽንሰ-ሃሳቡን ተቀባይነት ካላቸው መርሆች ጋር በማዛመድ የሚመረምር እና የመፍትሔ ሃሳቦችን የሚያቀርብ ይሆናል።

ቁልፍ ቃላት፡- ... **የሥራ ውል፣ የሥራ ግንኙነት፣ ማግለል፣ አሠሪ፣ ሠራተኛ፣ ድርጅት**

♣ የጽሑፉ አዘጋጅ (LLB, LLM in Business and Corporate Law) በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የህግ ትምህርት ቤት የሕግ መምሕር፣ በማናቸውም የፌዴራል እና የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች ጠበቃ እና የሕግ አማካሪ ናቸው። ይህን ጽሑፍ በተመለከተ ማናቸውንም አይነት አስተያየት በኢ-ሜይል አድራሻ bereketeworku@gmail.com ለጸሐፊው መላክ ይቻልል። የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅም ለጽሑፉ መሳካት ገንቢ አስተያየትን በመስጠት አስተዋጽኦ ላበረከቱት የሕግ መጽሔቱ ኤዲቶሪያል ኮሚቴ አባላት ላቅ ያለ ምስጋናን ያቀርባል።

1. መግቢያ

የአሠሪ እና ሠራተኛ ሕግ[1] አሠሪና ሠራተኛ የጋራ ራዕይ ኖሯቸው የሥራ ግንኙነቶቻቸውን መሠረታዊ በሆኑና በሕግ በተደነገጉ መብቶችና ግዴታዎች ላይ በመመስረት አስተማማኝ የኢንዱስትሪ ሰላም፣ ዘላቂ ምርታማነት እና የገበያ ተወዳዳሪነት አቅም በመፍጠር ሀገራችን ለተያያዘችው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የማስመዝገብ ብሔራዊ ግብ በትብብርና በጋራ እንዲሰሩ የማድረግ ዓላማ እና ግብ ይዞ በመነሳት አነስተኛ የመዋዋል ነጻነት ያለውን ሠራተኛ ከፍተኛ የመደራደር አቅም ካለው አሠሪ ኢ-ፍትሐዊ ተፅዕኖ ለመከላከል አስገዳጅ የሆኑ አነስተኛ የሥራ ሁኔታዎችን የሚደነግግ የሕግ ክፍል ነው[2]። ይሕ የሕግ ክፍል መነሻው በቅጥር ላይ የሚመሠረት የሥራ ግንኙነት ሲሆን ለዚህ የሥራ ግንኙነትም የተዋዋይ ወገኖች የመደራደር

---

[1] የኢፌዴሪ የአሠሪ እና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ዓ.ም በነጋሪት ጋዜጣ በተለየ የወጣ 25ኛ ዓመት፣ ቁጥር 89 (ከዚህ በኋላ ሕጉ ወይም አዋጁ ተብሎ የሚጠራ)

[2] Tamru & et al, Ethiopian Labour Law, Kluwar Law School, 2004, pp. 22-36, accessed on June 21,2019, available at http://library.stic.et/documents/30479/2414785/Employment+and+Labor+Law.pdf/83b7c2ed-d814-7bd6-0b58-18de955db42d?version=1.0&download=true; Mehari Redae, A Simplified Guide to Ethiopian Labour Law , 2008, pp.4-11; accessed on June11, 2018 available at https://www.academia.edu/7689577/LL_M._Thesis_PDF_in_one_file;
Mehari Redae in his paper stated that traditionally labour relation was considered as economic relation and was left to private regulation through contract. The role of the government in such relations was intended to be nothing more or less than enforcement of promises of the parties. Nevertheless, the principle of freedom of contract failed to bring about equitable outcome in employment relations due to the bargaining position of the parties. It should also be underlined that freedom of contract between economic unequals (i.e. capital & labour) will have the effect of perpetuating inequality. As an expression of the failure of the arrangement, organized and disorganized social unrest begun to crop up here and there. Thus the situation called for state intervention and internationally concerted action. In this regard, the level of government intervention in the free market economy, concerning the bargaining power of the two economically unequals-labour and capital, ranges from lassiez-faire to market meccanisms. In the self-governing markets, there is no government intervention, only the market decides everything. In the market mechanisms, there is government intervention but the level of intervention among other things includes private laws (which is a liberal approach), Competiation policy and Law (which is a prohibition approach), Regulation (which is a prescription approach) and administration (which is an ownership approach). Inorder to tackle the failure of freedom of contract, the government of Ethiopia intervens in the market following different degrre of interventions Firstly, it enacts labour law as a private law and dictates the respective rights and obligations of the parties to the contract of employment, secondly, it enacts labour law as a completion law and makes room for plurality of employers and workers to bargain on the terms and conditions of their contract of employment and makes prohibition on anti-competiative conducts, thirdly, it enacts labour law as a regulatory law and regulates the conducts of the employer and the worker by prescribing legally stipulated minimum working conditions of work.

አቅም እና ልውውጥ ዋነኛ መገለጫ ባሕሪያት ናቸው[3]። በልውውጥ ግንኙነት ሠራተኛው ለሚሰጠው አገልግሎት ከአሠሪው ዘንድ ክፍያ ይሰጠዋል፤ አሠሪውም ለከፈለው ክፍያ አገልግሎትን ያገኛል። ይህ የሰጥቶ መቀበል ግንኙነትም የተዋዋይ ወገኖችን ፈቃድ እና ስምምነት መሠረት ያደረገ ነው።

በቅጥር ላይ የሚመሠረተው የሥራ ግንኙነት ምንም እንኳ በመርሕ ደረጃ በተዋዋይ ወገኖች ውዴታ እና ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ቢሆንም አሠሪው እና ሠራተኛው የግንኙነት ይዘታቸውን ለመወሰን ያላቸውን ነጻነት እና የመደራደር አቅም ስንመለከት ግን እጅግ ሰፊ የሆነ ልዩነት ይታይበታል።[4] በሥራ ገበያው ላይ ያለው የገዘፈ የአቅርቦት እና ፍላጎት ልዩነት ሠራተኛውን ፈላጊ አሠሪውን ተፈላጊ አድርጓቸዋል። በዚህ መጠነ ሰፊ የመደራደር አቅም ልዩነት ባለበት የሥራ ገበያ የሥራ ቅጥር ለሠራተኛው ዕድል ለአሠሪው ደግሞ ውሳኔ ሆኖ እናገኘዋለን። ሠራተኛው ለመቀጠር ሲወስን ሳይሆን የሥራ ዕድል ሲያገኝ ይቀጠራል፤ አሠሪው ደግሞ ሠራተኛን የመቅጠር ውሳኔ እንጂ ዕድል አያስፈልገውም፤ የአሠሪው የኢኮኖሚ የበላይነት የግንኙነቱን ዝርዝር ይዘት ብቻውን በተናጥል እንዲወስን ምቹ ሁኔታን ይፈጥርለታል። ይህን የመደራደር አቅም ልዩነት መኖር መንግሥት በስምምነት ሊቀየሩ የማይችሉ አነስተኛ የሥራ ሁኔታዎችንና ደረጃዎችን (Legally stipulated minimum working conditions) በሕግ በመወሰን የሥራ ግንኙነቱ ውስጥ ጣልቃ ገብቶ እንዲቆጣጠረው አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ የአሠሪ እና ሠራተኛ ሕግን ማውጣት አስፈልጓል።[5]

የአሠሪ እና ሠራተኛ ሕግ እንደ አንድ የሕግ ዘርፍ ሲጠነሰስ ጀምሮ መሠረቱ ተተክሎ የቆመው በአሠሪ እና ሠራተኛ መካከል በሚፈጠረው የሁለትዮሽ ግንኙነት (Bilateral Labour Relation) እንደሆነ በዘርፉ ያሉ ምሑራን ይስማማሉ። የአሠሪ እና ሠራተኛ ሕግን የተፈጻሚነት ወሰን የሚያትቱት የሕጉ ክፍሎች ሕጉ በመርሕ ደረጃ በአሠሪ እና ሠራተኛ መካከል በሚደረግ

[3] Deakin and Frank Wilkinson, The Law of the Labour Market: Industrialization,Employment and Legal Evolution, Oxford: Oxford University Press, 2005, pp. 25-36, accessed on July 13, 2019, available at https://law.unimelb.edu.au/__data/assets/pdf_file/0009/1522449/law_research_report_20061.pdf

[4] Wank Rolf, Labor Law in Motion: Germany, in Roger Blanpain ed., Bulleti of Comparative Labor Relations, 2005, pp. 53, accessed on February 27, 2019, available at https://trove.nla.gov.au/version/8978601; አብርሃም ዮሐንስ፣ አሠሪ እና ሠራተኛ ሕግ ቅጽ 1፣ ድሬዳዋ ኢትዮጵያ፣ 2009 ዓ.ም፣ ገጽ 1-3

[5] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 4 አብርሐም ዮሐንስ ገጽ 3-8.

በቅጥር ላይ በተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን እና በልዩ ሁኔታም የተወሰኑት የሥራ ግንኙነቶች ከሕጉ የተፈጻሚነት ወሰን የተገለሉ እንደሆኑ ይደነግጋሉ።[6]

ሕጉ "አሠሪ"፣ "ሠራተኛ" እና "የሥራ ውል" ለሚሉት ነጥቦች የሰጠው ትርጉም ግልጽነት የጎደለው በመሆኑ በተለይም አንድን ቀጣሪ ድርጅት ብሎም አሠሪ ለማለት በምሑራን ዘንድ "ድርጅት"፣ "ሕጋዊ ሰውነት"፣ "ለትርፍ መቋቋም"፣ "ሕጋዊ ዓላማ" እና "የአንድ አመራር ጽንሰ-ሃሳብ" የሚሉት ነጥቦች የተለያየ አቋም የሚያዝባቸው እና አሻሚ የሆኑ ሐረጋት ስለሆኑ እና እነዚህን ሐረጋት በተመለከተ በባለሙያዎች ዘንድ የተለያየ ትርጉም መሰጠቱ በአሠሪ እና ሠራተኛ መብቶች እና ግዴታዎች ዙሪያ ወጥነት ያለው ፍርድን በመስጠት ረገድ ውስንነትን እና ልዩነትን ይፈጥራል። ይህ የትርጉም ልዩነትም የአሠሪዎችን እና ሠራተኞችን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚያጣብብ ሆኖ እናገኘዋለን። ከዚህ በመነሳትም ይሕ ጥናታዊ ጽሑፍ ትርጓሜያዊ ማግለልን በመወሰን ረገድ አዋጁ አሠሪ፣ ሠራተኛ እና የሥራ ውል ለሚሉት ቃላት ከሰጣቸው ትርጓሜያት አንጻር ከሕጉ የሚመዘዙ አንኳር የሕግ እና የፖሊሲ ጥያቄዎችን ከተለያየ አቅጣጫ በማንሳት ጽንሰ-ሃሳባዊ በሆነ የጥናት ዘዴ (Doctrinal Research Methodology) ጽንሰ-ሃሳቡን ተቀባይነት ካላቸው መርሆች ጋር በማዛመድ የሚመረምር እና የመፍትሔ ሃሳቦችን የሚያቀርብ ይሆናል።

ይህ ጽሑፍ ስለ ጉዳዩ መነሻ ቢሆን እንጅ ምሉዕ አይደለም። በተለይም ትርጓሜያዊ ማግለልን በተመለከተ በጽንሰ-ሃሳቡ እና በተግባሩ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው የሚለውን ለማጥናት ሁሉንም የታተሙትን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎችን ለማየት ሙከራ የተደረገ ቢሆንም ከተያዘው ጭብጥ አንጻር የተወሰነ ውሳኔን ለማግኜት አልተቻለም። ይህ ጽሑፍ ስለቀጥተኛ እና በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሰረቱ የማግለል አይነቶች አይዳስስም።

ይሕ ጽሑፍ በስራው ዓለም ላይ የሚገኙ አሠሪዎች እና ሠራተኞች ከአዋጁ የተፈጻሚነት ወሰን አንጻር የስራ ግንኙነታቸው በቅጥር ላይ ተመስርቶ መፈጸሙ እና የሥራ ውል መኖሩ ብቻውን በሕጉ የሚዳኝ የሥራ ግንኙነት ስለማያደርገው በሕጉ አሠሪ፣ ሠራተኛ እና የሥራ ውል ለሚሉት ነጥቦች የተሰጠውን ትርጉም በመገንዘብ አሠሪነታቸው፣ ሠራተኛነታቸው እና የሥራ ውላቸው ትርጓሜያዊ በሆነ መልኩ ከሕጉ የተፈጻሚነት ወሰን የተገለለ መሆኑን ወይም አለመሆኑን እንዲያውቁ እና መብት እና ግዴታቸውን በተገቢው መንገድ እንዲያስከብሩ

[6] በላቸው መኩሪያ፣ <u>የኢትዮጵያ የአሠሪ እና ሠራተኛ ሕግ መሰረታዊ ነጥቦች፣</u> ጥር 24 ቀን 2004 ዓ.ም፣ ገጽ 3-12.

በማስቻል ረገድ ጠቀሜታው የጎላ ነው። በተጨማሪም ሕግን በማውጣት፣ በመተርጎም እና በማስፈጸም ላይ የተሰማሩ የሕግ ባለሙያዎች፣ ሕግ እና ፖሊሲ አውጭዎች፣ ዳኞች፣ ጠበቆች፣ አስፈጻሚ አካላት እንዲሁም በመስኩ የተሰማሩ የሕግ መምህራን እና ተማሪዎች ሕጉን እንዲያጎለብቱ እና ተጨማሪ ጥናት እና ምርምርን እንዲያከናውኑ አንደ መነሻ እና ማጣቀሻ ያገለግላል።

2) የማግለል ጽንሰ-ሃሳብ በኢትዮጵያ የአሠሪ እና ሠራተኛ ሕግ

በአሠሪ እና ሠራተኛ ሕግ ውስጥ ማግለል ማለት የተወሰኑ አሠሪዎችን እና ሠራተኞችን ከሕጉ የሚመነጩ መብቶችን፣ ጥቅሞችን እና ጥበቃዎችን መከልከል ማለት ነው።[7] በዚህም ረገድ አንድ የሥራ ግንኙነት በአሠሪ እና ሠራተኛ መካከል መደረጉ፣ የሥራ ግንኙነቱ በቅጥር ላይ ተመሥርቶ መፈጸሙ እና የሥራ ውል መኖሩ ብቻውን በአሠሪ እና ሠራተኛ ሕግ የሚዳኝ የሥራ ግንኙነት አያደርገውም፤ ይልቁንም ይህ የሥራ ግንኙነት በሕጉ የትርጉም ክፍል ለአሠሪ፣ ሠራተኛ እና የሥራ ውል ለሚሉት ነጥቦች የተሰጠውን ትርጓሜ ያሟላል ወይስ አያሟላም፣ የሚያሟላስ ከሆነ የሕጉን የተፈጻሚነት ወሰን በሚደነግገው ክፍል ስር በቀጥታ ወይም በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሠረተ የማግለል ተግባር ተፈጽሞበታል ወይስ አልተፈጸመበትም የሚሉትን ነጥቦች ማየት ተገቢ ይሆናል። የማግለል ጽንሰ-ሃሳብም የሚነሳው ከዚህ ነጥብ ላይ ነው። አንድ በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ላይ ያሉ ተዋዋይ ወገኖች በሕጉ የትርጓሜ ክፍል ላይ አሠሪ እና ሠራተኛ ለሚሉት ነጥቦች የተሰጠውን ትርጉም የማያሟሉ ከሆነ ይህ የሥራ ግንኙነት ከትርጓሜ አንጻር ከሕጉ ተፈጻሚነት የተገለለ የሥራ ግንኙነት ይሆናል።[8] ከላይ በተጠቀሰው መንገድ የሥራ ግንኙነቱ ላይ ያሉት ተዋዋይ ወገኖች በሕጉ የትርጓሜ ክፍል ላይ አሠሪ እና ሠራተኛ ለሚሉት ነጥቦች የተሰጠውን ትርጉም የሚያሟሉ ስለሆነ ብቻም ሕጉ ተፈጻሚ አይሆንም ይልቁንም የሥራ ግንኙነቱ በዚሁ የሕግ ክፍል ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ወይም በቅድመ-ሁኔታ ላይ ተመሥርቶ የተገለለ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ይገባል።[9] ከዚህም በመነሳት አንድ የሥራ ግንኙነት በቅጥር ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ብቻ ሙሉ በሙሉ ሕጉ ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል አይባልም በሌላ በኩልም

[7] Lenard R. Berlanstein, The Industrial Revolution and Work in Nineteenth Century Europe, London: Routledge, 1992, pp. 144-152, accesed on May 23, 2019 available at https://services.wwnorton.com/get_content.php?sitecode=westciv19&siteversion=demo&file=/wwnorton.college.public/history/wciv/docs/west19-ch19-im.pdf.

[8] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 1፣ አንቀጽ 2(1,2,3)፣ 3(1,2,3) እና 4(1)

[9] ዝኒ ከማሁ

ሁሉም የሥራ ግንኙነቶች ከሕጉ ተፈጻሚነት የተገለሉ ናቸው ማለት አይቻልም፤ ይልቁንም የትኛው የሥራ ግንኙነት ሕጉ ተፈጻሚ ይሆንበታል የትኛውስ ላይ ተፈጻሚነቱ ይገለላል የሚለውን የሕጉን የተፈጻሚነት ወሰን ማየት ተገቢ ይሆናል።

3) በኢትዮጵያ የአሠሪ እና ሠራተኛ ሕግ የተካተቱ የማግለል አይነቶች

ከላይ እንደተመለከትነው የሕጉ አንቀጽ 3[10] ድንጋጌ በቅጥር ላይ ከተመሠረቱት የሥራ ግንኙነቶች መካከል የትኞቹ በሕጉ ይዳኛሉ የትኞቹስ ከሕጉ የተፈጻሚነት ወሰን የተገለሉ ናቸው የሚለውን ጽንሰ-ሃሳብ ያትታል።

ይህ የሕግ ድንጋጌም በመርሕ ደረጃ ሕጉ በቅጥር ላይ በተመሠረቱ የሥራ ግንኙነቶች ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን ቢያስቀምጥም በልዩ ሁኔታ ግን ሕጉ ተፈጻሚ ሊሆን የማይችልባቸውን እና የተገለሉ የሥራ ግንኙነቶችንም በተነጻጻሪነት መደንገጉን እናስተውላለን። በተነጻጻሪነት ሕጉ ተግባራዊ እንዳይሆንባቸው እና ከሕጉ የተፈጻሚነት ወሰን እንዲገለሉ የተደረጉ በቅጥር ላይ

---

[10] **አንቀጽ ፫ <u>የሕጉ የተፈጻሚነት ወሰን</u> (Scope of Applications)**

፩) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ በአሠሪ እና ሠራተኛ መካከል በሚደረግ በቅጥር ላይ በተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

፪) ይህ አዋጅ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት በቅጥር ላይ በተመሠረቱ የሥራ ግንኙነቶች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

ሀ) ለአስተዳደግ ሲባል፣ ለሕክምና ወይም ከሕመም ለመዳን ወይም እንደገና ለመቋቋም ሲሆን፣

ለ) የሙያ መልመጃ ትምህርትን ሳይጨምር ለመማር ወይም ለመሠልጠን ሲሆን፣

ሐ) የሥራ መሪን ማለትም በሕግ ወይም እንደ ድርጅቱ የሥራ ፀባይ በአሠሪው በተሰጠ የውክልና ሥልጣን መሠረት የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣትና የማስፈጸም ከእነዚሁ በተጨማሪ ወይም እነዚህኑ ሳይጨምር ሠራተኛን የመቅጠር፣ የማዘዋወር፣ የማገድ፣ የማሰናበት፣ የመመደብ፣ ወይም የሥነ-ሥርዓት እርምጃን የመውሰድ ተግባሮችን የሚያከናውንና የሚወስን ግለሰብን የሚመለከቱ ሲሆን እንዲሁም እነዚህን የሥራ አመራር ጉዳዮችን አስመልክቶ የአሠሪውን ጥቅም ለመጠበቅ አሠሪው ሊወስደው ስለሚገባው እርምጃ በራሱ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ ባለሙያ የሥራ ኃላፊንም ይጨምራል፣

መ) ለትርፍ በሚካሄድ ሥራ ላይ ያልተመሠረተ የግል አገልግሎት ቅጥር ሲሆን፣

ሠ) በልዩ ሕግ የሚተዳደሩ እንደ ጦር ኃይል ባልደረቦች፣ የፖሊስ ኃይል ባልደረቦች፣ የመንግሥት አሠተዳደር ሠራተኞች፣ የፍርድ ቤት ዳኞች፣ የዓቃብያነ ሕግ እና ሌሎችንም የሚመለከት ሲሆን፣

ረ) አንድ ተዋዋይ ወገን ዋጋ እየተከፈለው በራሱ የንግድ ሥራ ወይም በራሱ የሙያ ኃላፊነት የሚሠራ ሥራ የሚያከናውን ሲሆን፣

፫) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም፡-

ሀ) ሥራቸውን በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የሚያከናውኑ የውጭ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ከኢትዮጵያውያን ጋር በሚመሠርቱት የሥራ ግንኙነቶች ላይ ተፈጻሚ እንዳይሆን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ወይም ኢትዮጵያ በምትፈራረማቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሊወሰን ይችላል።

ለ) የሃይማኖት ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በሚመሠርቱት የሥራ ግንኙነቶች ላይ ተፈጻሚ እንዳይሆን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

ሐ) ስለ ግል አገልግሎት የሥራ ሁኔታ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ያወጣል።

የተመሰረቱ የስራ ግንኙነቶችም በርካታ ሲሆኑ ለጥናት ያመች ዘንድ በሦስት ከፍለን እናያቸዋለን፡፡ በዚሕ ሕግ ውስጥ የተካተቱት የማግለል አይነቶችም፡-

1. ቀጥተኛ ማግለል (Outright Exclusions)
2. በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ማግለል (Conditional Exclusions)
3. ትርጓሜያዊ ማግለል (Definitional Exclusions) ናቸው፡፡

4) ትርጓሜያዊ የማግለል ጽንሰ-ሃሳብ በኢትዮጵያ የአሠሪ እና ሠራተኛ ሕግ (The Concepts of Definitional Exclusions under Ethiopian Labour Law)

ለዚህ የማግለል ጽንሰ-ሃሳብ መነሻው በሕጉ አንቀጽ 3(1) ላይ "*የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ በአሠሪ እና ሠራተኛ መካከል በሚደረግ በቅጥር ላይ በተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል*" የሚለው ድንጋጌ ሲሆን በዚህ ረገድም አዋጁ አሠሪ እና ሠራተኛ ለሚሉት ነጥቦች በሕጉ የትርጓሜ ክፍል የሰጠውን ትርጉም የማያሟሉትን ተዋዋይ ወገኖች ምንም እንኳ የሥራ ግንኙነታቸው በቅጥር ላይ የተመሠረተ ቢሆንም በትርጉም ከሕጉ የተፈጻሚነት ወሰን ያገለላቸው ሲሆን ትርጓሜውን ያሟሉትን ተዋዋይ ወገኖች የሥራ ውላቸው በቅጥር ላይ የተመሠረተ መሆኑን በማረጋገጥ ተፈጻሚ የሚሆንበት አግባብ እንዳለ እንገነዘባለን፡፡[11] ከዚህም በመነሳት አንድ በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ግንኙነት በትርጉም ደረጃ ከሕጉ የተፈጻሚነት ወሰን የተገለለ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን በሕጉ የትርጉም ክፍል "የሥራ ውል"፣ "አሠሪ" እና "ሠራተኛ" ለሚሉት ነጥቦች የሰጠውን ትርጉም ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡

4.1. የሥራ ውል (Contract of Employment)

የሥራ ውልን በተመለከተ አዋጁ ትርጉምን ከመስጠት ይልቅ አንድ የሥራ ውል በይዘት ደረጃ ሊያሟላቸው የሚገቡ የሥራ ውል ዓለባውያን (Elements of Contract of employment) ዝርዝር ማስቀመጥን መርጧል፡፡ በአሠሪ እና ሠራተኛ መካከል የሥራ ውል አለ ወይስ የለም

[11] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 1፣ አንቀጽ 2(1,2,3)፣ 3(1,2,3) እና 4(1)፤ Worku Kassaw, The applicability or not of Labour Proclamationon up on employment relations established between Ethiopia Orthodox Tewahido Church and its Ministers of Religion, LLB Thesis, Haramaya University, Drie Dawa Ethiopia, June 2006, pp. 12-18 (Unpublished); አንዳርጌ ካሴ፣ የኢትዮጵያ አሠሪ እና ሠራተኛ ሕጎች ማብራሪያ፣ ግንቦት 2008፣ አዲስ አበባ፣ ገጽ 1-38፡፡

የሚለውን ነጥብ ለመመለስም እነዚህ አላባውያን እንደመመዘኛ ሆነው ያገለግላሉ። ከዚህ በመነሳትም የአዋጁን አንቀጽ 4(1) ድንጋጌ ስንመለከተው የሥራ ውል ሠራተኛው ሥራን ለመሥራት አሠሪው ደግሞ ለተሠራው ሥራ ክፍያን ለመክፈል ግዴታ የሚገቡበት ስምምነት መሆኑን እንረዳለን። የአዋጁ አንቀጽ 4(1) ድንጋጌ እንዲህ ይነበባል።

> *"ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሠሪው መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ሥራን ለአሠሪው ለመሥራት ቢስማማ በሁለቱ መካከል የሥራ ውል ይመሠረታል።"*

ስለ ሥራ ውል ስናነሳ የተዋዋይ ወገኖች ችሎታ እና ፈቃድ እንዲሁም የውለታው ጉዳይ ሕጋዊነትን ማንሳት ተገቢ ቢሆንም እነዚህ ጉዳዮች ግን የሥራ ውልን ሊያቋቁሙ የሚችሉ ሁኔታዎች (Definitional Elements of contract) ሳይሆኑ የውል ብቃት መመዘኛዎች (Validity Elements of a Contract)[12] ናቸው።

የአዋጁን አንቀጽ 4(1) ድንጋጌ ስንመለከት የሥራ ውል አለ ወይስ የለም የሚለውን ነጥብ ለመወሰን መሟላት ስላለባቸው የሥራ ውል አለባውያን ደንግጎ እናገኛለን። ውሉ በተሟላ ሁኔታ ተፈጽሟል ለማለትም የሚከተሉት አለባውያን በጣምራ ተሟልተው ሊገኙ ይገባል። እነርሱም የሥራ ውል ተዋዋይ ወገኖች፣ ደመወዝ፣ ሥራ መሥራት፣ የአሠሪው መሪነት እና የሥራ ውል የቆይታ ጊዜ የሚሉት ናቸው።[13]

---

[12] ፕሮፌሰር ጥላሁን ተሾመ የኢትዮጵያ የውል ሕግ መሰረተ ሃሳቦች በሚለው መጽሐፋቸው የፍ/ሕ/ቁ. 1678 ድንጋጌን በመጥቀስ አንድ ውል በሕግ ፊት የሚጸና ነው ለማለት ከአራት መሰረታዊ መለኪያዎች አንጻር ተቀባይነትን ሊያገኝ ይገባል ይላሉ። እነርሱም የተዋዋይ ወገኖች የመዋዋል ችሎታ፣ የተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ እንከን በሌለበት መንገድ የተገለጸ መሆን፣ ተዋዋዮቹ የሚዋዋሉበት ጉዳይ ጸንቶ ባለ ሕግ ያልተከለከለ፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ለመልካም ስነ-ምግባር ተቃራኒ ነው ተብሎ ያልተወሰደ፣ አፈጻጸሙ በተዋዋይ ወገኖች አቅም ተግባራዊ ሊሆን የሚችል እና በእርግጠኝነትም ሕግ ሲጠይቅ ደግሞ የውሉ አቀራረጽ በተጠየቀው ስርዓት መሰረት የተዘጋጀ መሆን ናቸው ይላሉ። እነዚህ መለኪያዎች ደግሞ የውል ብቃት መመዘኛ መስፈርቶች እንደመሆናቸው መጠን ከእነርሱ አንዱ ወይም ሁሉም አለመሟላታቸው ውሉን ውጤት አልባ ሊያደርገው ይችላል። የፍትሐብሔር ሕጋችን አራተኛ መጽሐፍ ጠቅላላ የሆኑ የውል መርሆዎችን የያዘ ሲሆን በዚሁ ሕግ አምስተኛው መጽሐፍ፣ በንግድ እና የባሕር ሕጎች እንዲሁም በሌሎች አዋጆች የተለያዩ ልዩ ውሎች ይገኛሉ። ጠቅላላ የውል መርሆዎችም በልዩ የውል ሕጎች ውስጥ የተያዘ ጉዳይን የሚሸፍን ልዩ የውል ድንጋጌ በሌለ ጊዜ የልዩ ውሉን ክፍተት ለመሙላት ተፈጻሚ እንደሚሆኑ የፍ/ሕ/ቁ/ 1676 ድንጋጌ ያስረዳል። በአሠሪ እና ሠራተኛ መካከል የሚመሰረተው የሥራ ውልም ልዩ ውል እንደመሆኑ መጠን በሕግ ፊት የጸና ይሆን ዘንድ ከላይ ያየናቸው የውል ብቃት መመዘኛ መስፈርቶችን ሊያሟላ ይገባል። እነዚህ የውል ብቃት መመዘኛዎች በራሱ በአዋጁ ውስጥ የተካተቱ ከሆነ የውል አመሰራረት ጋር ተያይዞ የሚነሱ አለመግባባቶች በአዋጁ ድንጋጌዎች የሚዳኙ ይሆናል። አዋጁ ግን በዚህ ነጥብ ላይ ክፍተት ካለበት በፍ/ሕ/ቁ/ 1676 ድንጋጌ መሰረት የውል አመሰራረትን የሚመለከቱት የጠቅላላ ውል መርሆዎች በአዋጁ ባልተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

[13] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 4 ገጽ 11-15፣ በላቸው መኩሪያ ገጽ 26-29

4.1.1. የሥራ ውል እና ተዋዋይ ወገኖቹ

የአዋጁን አንቀጽ 4(1)፣ 2((1)፣ (2)፣ (3)፣ (18)) ድንጋጌዎችን ስንመለከት የሥራ ውል ተዋዋይ ወገኖች ሁልጊዜም ሁለት እንደሆኑ እና እነርሱም አሠሪ እና ሠራተኛ እንደሆኑ ይገልጻል። አሠሪ ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 በተመለከተው መሠረት ቀጥሮ የሚያሠራ ግለሰብ ወይም ድርጅት እንደሆነ፤ ድርጅት ማለት ደግሞ ለንግድ፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለእርሻ፣ ለኮንስትራክሽን ወይም ለሌላ ሕጋዊ ዓላማ የተቋቋመ በአንድ አመራር የሚካሄድ ተቋም እንደሆነ የድርጅቱን ተግባር ለማከናወን ከዋናው ድርጅት ተለይቶ የተሰየመ በአሠራሩ ወይም በአቋሙ ራሱን የቻለ ሥልጣን ያለው የድርጅት ቅርንጫፍ ራሱን የቻለ ድርጅት ሆኖ እንደሚቆጠር ይደነግጋል። ይህ አሠሪም (ወደፊት አሠሪ በሚለው ክፍል አሠሪነት እና ሕጋዊ ሰውነት በሚል የምናነሳው ክርክር እንደተጠበቀ ሆኖ) የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው ሊሆን እንደሚችል ከድንጋጌው ይዘት መረዳት ይቻላል።

ሌላኛው ተዋዋይ ወገን ሠራተኛ ሲሆን በትርጉም ደረጃም ከአሠሪ ጋር በቅጥር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ያለው ግለሰብ እንደሆነ የአዋጁ አንቀጽ 4(1) እና 2(3) ድንጋጌዎች ይገልጻሉ። በሕጉ ለሠራተኛ የተሰጠውን ትርጉም በአዋጁ አንቀጽ 13(1) ላይ ከተቀመጠው ግላዊ የመሥራት ግዴታ አንጻር ስንመለከተው ምንም እንኳ የአዋጁ አንቀጽ 2(18) ላይ እንደተቀመጠው ሰው ማለት የተፈጥሮም ይሁን በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው በሚል የተተረጎመ ቢሆንም ከሥራው ባሕርይ አንጻር ሠራተኛ ሁልጊዜም የተፈጥሮ ሰው ብቻ ሊሆን እንደሚገባ እና በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላትን እንደማያካትት የአዋጁ አንቀጽ 4(1) ድንጋጌ በግልጽ ያስረዳል።

4.1.2. የሥራ ውል እና ደመወዝ

ከሥራ ውል መሠረታዊ አለባውያን መካከል አንዱ ደመወዝ ሲሆን ይኸውም በአዋጁ አንቀጽ 53(1) ላይ እንደተገለጸው ደመወዝ ማለት አንድ ሠራተኛ በሥራ ውሉ መሠረት ለሚያከናውነው ሥራ የሚከፈለው መደበኛ ክፍያ ነው። የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌን ስንመለከትም በስሩ እንደ ደመወዝ ሊቆጠሩ የማይችሉ ክፍያዎችን ይዟል።

4.1.3. የሥራ ውል እና ሥራ መሥራት

የሥራ ውልን ከሚያቋቁሙት መሠረታዊ አለባውያን መካከል አንዱ ሥራ መሥራት ሲሆን ይህም ሠራተኛው የሥራ ውሉን መሠረት ያደረገ ሥራን ሲሠራ ደመወዝ ይከፈለዋል። የሥራ ውል ለአሠሪው ደመወዝ የመክፈል ለሠራተኛው ደግሞ ሥራ የመሥራት ግዴታን የሚጥል

ሲሆን የመሥራት ግዴታ በሌለበት የሥራ ውል ሊኖር አይችልም። በአሠሪው እና ሠራተኛው መካከል መብት እና ግዴታ የሚፈጠረው በተዋዋይ ወገኖች መካከል ሥራን ለመሥራት ስምምነት ሲኖር መሆኑን እንገነዘባለን።

4.1.4. የሥራ ውል እና የአሠሪው መሪነት

የአሠሪው መሪነት የሥራ ውልን ከሚያቋቁሙት አለባውያን መካከል አንዱ ሲሆን ሥራውን አሠሪው ይመራዋል ሲባል በአሠሪው እና ሠራተኛው መካከል የጌታ እና የሎሌ ግንኙነት አለ ማለት ሳይሆን ከአሠሪነት ባሕርይ የሚመነጨ አሠሪው የሥራውን አይነት፣ አኳኋን፣ ጊዜ እና ቦታ ለሠራተኛው መመሪያን እየሰጠ እንዲያሠራ የሚያደርግ ከውል የመነጨ መብት ነው። ይህ የአሠሪው ሥራውን የመምራት ሥልጣን ከውክልና ውል አንጻር አሠሪውን ከወካይ እና ሠራተኛውን ከተወካይ የተለየ፣ ከባለቤት-ተቋራጭ ግንኙነት አንጻር ሠራተኛው ከተቋራጭ የተለየ መሆኑ የሚረጋገጥበት መለያ መስፈርት ነው።[14]

4.1.5. የሥራ ውል እና የቆይታ ጊዜው

የሥራ ውል ከሌሎች ውሎች ከሚለይባቸው መሠረታዊ ነጥቦች መካከል አንዱ ውሉን የሚመለከተው የጊዜ መጠን ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ሕጉ ሁሉም አይነት በቅጥር ላይ የሚመሠረቱ የሥራ ውሎች በመርሕ ደረጃ ላልተወሰነ ጊዜ እንደሚደረጉ ከወሰነ በኋላ ሌሎች የሥራ ውሎች ግን በልዩ ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ ሊደረጉ እንደሚችሉ በማያሻማ ሁኔታ አስቀምጧል።[15]

አንድ የሥራ ግንኙነት በአሠሪ እና ሠራተኛ መካከል መደረጉ፣ የስራ ግንኙነቱ በቅጥር ላይ ተመስርቶ መፈጸሙ እና የስራ ውል መኖሩ ብቻውን በአሠሪ እና ሠራተኛ ሕግ የሚዳኝ የስራ ግንኙነት አያደርገውም። ይልቁንም በሕጉ አንቀጽ 4(1) ስር የተቀመጡት እና የሥራ ውል በሚለው የጽሑፉ ክፍል ዘርዘር አድርገን የተመለከትናቸውን የሥራ ውልን ሊያቋቁሙ የሚችሉ ሁኔታዎች ተሟልተው ከተገኙ የሥራ ውል በትርጉም ደረጃ ስለተሟላ ትርጓሜያዊ ማግለል አይኖርም። በአሠሪ እና ሠራተኛ መካከል በቅጥር ላይ የተመሰረተ የሥራ ግንኙነት ላይም የሥራ ውሉን መሰረት አድርጎ (ሌሎች መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ) አዋጁ ተፈጻሚ ይሆናል። ከላይ የተመለከትናቸውን የሥራ ውልን ሊያቋቁሙ የሚችሉ ሁኔታዎች ተሟልተው ካልተገኙ የሥራ ውል የሚለው ትርጉም አይሟላም። እነዚህ ሁኔታዎች ተሟልተው ባልተገኙበት ሁኔታ የሥራ ግንኙነቱ በአሠሪ እና ሠራተኛ መካከል በቅጥር ላይ ተመስርቶ

[14] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 4 ገጽ 11-15
[15] ዝኒ ከማሁ

ቢፈጸምም ይህ ግንኙነት ለአዋጁ ዓላማ የሥራ ውል የሚለውን ትርጉም ስለማያሟላ ከአዋጁ ተፈጻሚነት በትርጉም የተገለለ የሥራ ግንኙነት እንደሆነ እንረዳለን፡፡

4.2. የአሠሪነት ትርጉም

በአዋጁ አንቀጽ 2(1) እና (2) አገላለጽ ለአሠሪ የተሰጠውን ትርጉም ስንመለከት አሠሪ ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 በተመለከተው መሠረት ቀጥሮ የሚያሠራ ግለሰብ ወይም ድርጅት እንደሆነ፤ ድርጅት ማለት ደግሞ ለንግድ፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለእርሻ፣ ለኮንስትራክሽን ወይም ለሌላ ሕጋዊ ዓላማ የተቋቋመ በአንድ አመራር የሚካሄድ ተቋም እንደሆነ የድርጅቱን ተግባር ለማከናወን ከዋናው ድርጅት ተለይቶ የተሰየመ በአሠራሩ ወይም በአቋሙ ራሱን የቻለ ሥልጣን ያለው የድርጅት ቅርንጫፍ ራሱን የቻለ ድርጅት ሆኖ እንደሚቆጠር ይደነግጋል፡፡

4.2.1. ድርጅት እና ሕጋዊ ሰውነት

ከዚህ በላይ በተቀመጠው ትርጉም ውስጥ አሠሪ የተፈጥሮ ሰው ወይም ድርጅት ሊሆን እንደሚችል የተቀመጠ ሲሆን ቀጣሪው ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ ይህ ድርጅት አሠሪ ተብሎ ለመጠራት ሕጋዊ ሰውነት ያስፈልገዋል ወይስ አያስፈልገውም በሚለው ጉዳይ ላይ ጸሐፍት ሁለት አይነት አመክንዮን ያቀርባሉ፡፡[16] በአንድ ወገን ያሉት[17] አንድ ቀጣሪ ድርጅት ብሎም አሠሪ ለመሆን በአዋጁ አንቀጽ 2(2) ድንጋጌ ስር የተቀመጡትን ተግባራት የሚያከናውን ሊሆን እንደሚገባ እና እነዚህንም ተግባራት ለማከናወን የግድ ሕጋዊ ሰውነት እንደሚያስፈልግ እና ሕጋዊ ሰውነት የሌለው አደረጃጀት ደግሞ ድርጅት በሚለው ትርጉም ውስጥ ሊገባ እንደማይችል ሲገልጹ በሌላ በኩል ያሉት[18] ደግሞ ቀጣሪውም ድርጅት ብሎም አሠሪ ተብሎ

---

[16] Belayneh Ketsela & Zelalem Demelash, Labour Law Distance teaching materials, Bahir Dar University, Faculty of Law, July 2008, pp. 48-57, accesed on June 21, 2019, available at https://www.academia.edu/33348722/Labour_Law_Module

[17] Mehari Redai, Notes and Materials on Employment Law: Law Teaching Materials, Justice and legal system research institute of Ethiopia, 2009, pp. 3-22; accessed on March 13, 2018, available at https://chilot.me/teaching-materials/?download=6233 Linder Marc, The Employment Relationship in Anglo-American Law: A Historical Perspective, 1989, pp. 185-211, accessed on March 12, 2018, available at https://ir.uiowa.edu/cgi/viewcontent.cgi?referer=&httpsredir=1&article=1014&context=books

[18] ክላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 4 ገጽ 7-8, David P. Twomey, Labour and Employment Law: Text and Cases 15th edition, USA, 2013, pp. 572-597, accessed on August 23, 2018, available at https://www.amazon.com/Labor-Employment-Law-Text-Cases/dp/0538854391

ለመጠራት ሕጋዊ ሰውነት የግድ አስፈላጊ እንዳልሆነ እና ከላይ በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር ያሉት ተግባራት ሕጋዊ ሰውነት ባለውም ሆነ በሌለው ድርጅት ሊሠሩ እንደሚችሉ ይሞግታሉ።

በጸሐፊው አመለካከት ድርጅት ከሕጋዊ ሰውነት ጋር ሊቆራኝ ይገባል ወይስ አይገባም በሚለው ነጥብ ላይ ሁለተኛው አመክንዮ ሚዛን ይደፋል። ትርፍ በማግኘት ዓላማ በንግድ እንቅስቃሴ ተሰማርቶ የሚገኝ ግለሰብ የራሱ ድርጅት ሊኖረው ላይኖረው ይችላል፤ ከላይ የተገለጹትን ተግባራት ለማከናወን የንግድ ፈቃድ እና ምዝገባ እንጂ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም የግድ ሊሆን አይችልም። እነዚህ ተግባራት ባለቤትነቱ በአንድ ግለሰብ በተያዘ ድርጅት፣ ሕጋዊ ሰውነት ባለውም ሆነ በሌለው ድርጅት ወይም የድርጅትነት ባሕርይ በሌለው የተፈጥሮ ሰው ሊከናወኑ ስለሚችሉ አንድ ቀጣሪ ድርጅት ብሎም አሠሪ ለመሆን ሕጋዊ ሰውነት የግድ አይደለም። እንደማሳያም ድርጅት የሚለው ቃል ከሕጋዊ ሰውነት ጋር የሚቆራኝ ከሆነ ድርጅት የሚለውን ቃል የሚጠቅሱ የተለያዩ የሕጉ ክፍሎች ተፈጻሚነታቸው የተዛባ ይሆናል፤ በዚህ ረገድም ሠራተኛው መብቱ የሚጣበብበት ሁኔታ ይፈጠራል። ለምሳሌ ያክል የአዋጁን አንቀጽ 16 እና 23 ድንጋጌዎች ብንመለከት የድርጅት መቀላቀል፣ መከፋፈል ወይም የባለቤትነት መብት መተላለፍ የሥራ ውልን የማሻሻልም ሆነ የማቋረጥ ውጤት እንደሌለው ስለሚደነግጉ እና እነዚህ ተግባራት ደግሞ ሕጋዊ ሰውነት በሌለው ድርጅት ላይ ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጉ ለሠራተኛው የሰጠውን ሕጋዊ ከለላ እጅግ ያሳንሰዋል። ከዚህም አንጻር አንድ ቀጣሪ ድርጅት ብሎም አሠሪ ለመሆን የግድ ሕጋዊ ሰውነት ሊኖረው አይገባም የሚለው ሚዛን የሚደፋ አመክንዮ ሆኖ እናገኘዋለን።[19]

4.2.2. ድርጅት እና ሕጋዊ ዓላማ

አንድ ቀጣሪ የድርጅትን ብሎም የአሠሪነትን ትርጉም ያሟላ ዘንድ ከተቀመጡት መስፈርቶች አንዱ ለሕጋዊ ዓላማ መቋቋም ነው። የድርጅትን የዓላማ ሕጋዊነት በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 2(2)... ወይም ለሌላ ሕጋዊ ዓላማ የተቋቋመ... የሚለውን ነጥብ እንዲሁም ምን ምን ተግባራት ናቸው ሌላ ሕጋዊ ዓላማ በሚለው ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉት በሚለው ጉዳይ ላይ

[19] በንግድ ሕጋችን አንቀጽ 210 ስር ከእሽመር ሽርክና ማኅበር ውጭ ሁሉም የንግድ ማኅበራት ሕጋዊ ሰውነት ሊኖራቸው እንደሚገባ በግልጽ የተደነገገ ሲሆን እነዚህ ማኅበራትም ሕጋዊ ሰውነትን የሚያገኙት ከተመሰረቱ በኋላ በንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 ዓ.ም አንቀጽ 7 ስር በተመለከተው አግባብ በንግድ መዝገብ ውስጥ ሲመዘገቡ እንደሆነ ተደንግጓል። ከእነዚህ ድንጋጌዎች እንደምንረዳው ሕጋዊ ሰውነት የሌላቸው ነገር ግን የድርጅትነት ባሕሪ ያላቸው እንደ እሽመር ማኅበር ያሉ የንግድ ማኅበራት በአዋጁ አንቀጽ 2(2) እና አንቀጽ 4 በተመለከተው መሠረት ሠራተኛን ቀጥረው የንግድ፣ የኢንዱስትሪ፣ የእርሻ፣ የኮንስትራክሽን ወይም ሌላ ሕጋዊ ዓላማ ያለው ተግባርን ቢፈጽሙ እና ከእነዚህ ማኅበራት ጋር የሥራ ውል የወሰዱ ሠራተኞች ማኅበራቱ ሕጋዊ ሰውነት ስለሌላቸው ድርጅት እና አሠሪ የመሆን ችሎታ የላቸውም ሊባል አይገባም።

በጸሐፍት ዘንድ ሁለት አይነት አስተሳሰቦች አሉ።[20] የመጀመሪያውን አስተሳሰብ የሚያራምዱት ጸሐፍት[21] ሌላ ሕጋዊ ዓላማ የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ በድርጅቱ የሚከናወኑት ተግባራት በይዘት ደረጃ ኢኮኖሚያዊ በዓላማ ደግሞ ትርፍን መሠረት ያደረጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ በቂ ነው ይላሉ፤ ለዚህም እንደ አስረጅነት የሚያቀርቡት ምክንያት ሕጋዊ ዓላማ የሚለው መተርጎም ያለበት የሕጉን ታሪካዊ ዳራ እና በአዋጁ አንቀጽ 2(2) ስር የተዘረዘሩትን ምሳሌዎች በማጣቀስ እና በማስተሳሰር ሊሆን ይገባል ይላሉ። ይህንንም አቋማቸውን ድርጅት በሚለው ትርጉም ስር የተካተቱትን ምሳሌዎች ዝርዝር ስንመለከት በዓላማ ደረጃ ትርፍን መሠረት አድርገው የተቋቋሙ በይዘት ደረጃ ኢኮኖሚያዊ እንደሆኑ እና ሕግ አውጭው ...ለእርሻ፣ ለኮንስትራክሽን... እያለ ሲጠቃቅስ ሁሉንም ለመዘርዘር አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሳ ምሳሌን በመስጠት የእነዚህ ተቋማት የጋራ ባሕርይ ለድርጅት ትርጓሜ እንደ መስፈርትነት እንዲያገለግል አስቦ ነው በሚል ያስረዳሉ።[22]

ሁለተኛውን አስተሳሰብ የሚያራምዱት ጸሐፍት[23] የመጀመሪያውን አስተሳሰብ አይቀበሉም። ይልቁንም ...ሌላ ሕጋዊ ዓላማ... የሚለው ጽንሰ-ሃሳብ ሊተረጎም የሚገባው በድርጅቱ የሚከናወኑት ተግባራትን ሕጋዊነት እና ሕጋዊ ከሆኑ በኋላም በአዋጁ የማግለያ ክፍል ያልተገለሉ መሆናቸውን እንደ መስፈርት በመያዝ መሆን አለበት ብለው ይሞግታሉ። በሁለተኛው መንገድ መግትን የሚያቀርቡት አካላት አንድን ቀጣሪ ድርጅት ብሎም አሠሪ ብሎ ለመውሰድ ኢኮኖሚያዊ ይዘት እና ለትርፍ መቋቋምን እንደ መስፈርት መውሰድ ሕግን መሠረት ያላደረገ ትርጉም ነው፤ መስፈርቱ ሊሆን የሚገባው የተግባራቱ ሕጋዊነት እና ከአዋጁ የተፈጻሚነት ወሰን አለመገለል ነው። በመሆኑም ማንኛውም ሕጋዊ እና ከአዋጁ የተፈጻሚነት ወሰን ያልተገለለ ተግባር ለሌላ ሕጋዊ ዓላማ የተቋቋመ ድርጅት የሚለውን የምንተረጉምበት መስፈርት ነው በማለት ይሞግታሉ።[24]

ከላይ ያነሳናቸውን ክርክሮች በተመለከተ ጸሐፊው ቀጣሪን ድርጅት ብሎም አሠሪ ብሎ ለመወሰን ለትርፍ መቋቋምን እንደ መስፈርት መውሰድ ሚዛን የማይደፋ ክርክር መሆኑን

---

[20] ዝኒ ከማሁ አብርሐም ዮሐንስ ገጽ 8-10፣ ዝኒ ከማሁ Belayneh Ketsela ገጽ 48-68

[21] በላቸው መኩሪያ፣ <u>የኢትዮጵያ አሠሪ እና ሠራተኛ ሕግ መሰረታዊ ነጥቦች</u>፣ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፣ ጥር 2004፣ ገጽ 21-28

[22] ዝኒ ከማሁ

[23] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 4፣ አብርሐም ዮሐንስ ገጽ 8-11፣ International Labour Conference, <u>The Employment Relationship: Report V(1).</u> Geveva: International Labor Office Publications 7, 2005, pp. 24-25, accessed on August 10, 2018, available at https://www.ilo.org/public/english/standards/relm/ilc/ilc95/pdf/rep-v-1.pdf

[24] ዝኒ ከማሁ

የሚያመላክቱ የአዋጁን ክፍሎች በማንሳት ሙግቱን እንደሚከተለው ያቀርባል። የአዋጁን አንቀጽ 3(3)(ለ) ድንጋጌን ስንመለከት ድርጅት በአንድ አመራር የሚካሄድ ሕጋዊ ተቋምን በሙሉ ክፍተት በሌለው መልኩ እንደሚያካትት እንደ በቂ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ይህ ድንጋጌ የሃይማኖት ተቋማት እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በሚመሠርቱት የሥራ ግንኙነት ላይ አዋጁ ተፈጻሚ እንዳይሆን ደንብ አውጥቶ እንዲወስን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣን የሰጠ ሲሆን ምክር ቤቱም ይህንን መሠረት አድርጎ ከአዋጁ የተገለሉ የእነዚህን ተቋማት ሠራተኞች ለይቶ በመወሰን ደንብን አውጥቷል።[25]

የድርጅት ትርጓሜ ትርፍን ለማግኘት የተቋቋመ ድርጅት በሚል ከተገደበ የአዋጁ አንቀጽ 3(3)(ለ) ድንጋጌም ሆነ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ አላስፈላጊ እና ጥቅም አልባ ሆኖ ይቀራል። ለዚህ ደግሞ እንደ አስረጅ ሊሆን የሚችለው የሃይማኖት ተቋማትም ሆነ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ለትርፍ ባለመቋቋማቸው በድርጅት እና በአሠሪ ትርጉም ውስጥ ስለማይካተቱ ከመነሻውም ከእነዚህ ተቋማት ጋር የሥራ ውል ሊመሰረት አይችልም። የሥራ ውል በሌለበት ሁኔታ አዋጁ ተፈጻሚ ስለማይሆን ከጅምሩ ተፈጻሚነት በሌለው የሥራ ግንኙነት ላይ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አዋጁ ተፈጻሚ እንዳይሆን እንዲወስን ስልጣን የሚሰጥ ድንጋጌ ፋይዳ አይኖረውም። ከላይ የጠቀስናቸው ተቋማት ለትርፍ ባለመቋቋማቸው በድርጅት ብሎም በአሠሪ ትርጉም ውስጥ አይካተቱም፤ ከእነርሱም ጋር ሊመሠረት የሚችል የሥራ ውል አይኖርም። የሥራ ውል በሌለበት ሁኔታ ደግሞ ስለ አዋጁ ተፈጻሚነት እና የማግለል ጽንሰ-ሃሳብ ልናወራ አንችልም። በመሆኑም የአዋጁ አንቀጽ 3(3)(ለ) ድንጋጌ ጣዕም እንዲኖረው የድርጅት ትርጓሜ ትርፍ ከማግኘት ዓላማ ጋር አንዳችም ግንኙነት ሊኖረው አይገባም። በሌላ መልኩ ስናየውም ድርጅትን ትርፍ ከማግኘት ዓላማ ጋር ካቆራኘነው የተወሰኑ የሥራ ግንኙነቶች ያለአንዳች የሕግ ማዕቀፍ ተንጠልጥለው እንዲቀሩ ያደርጋል።[26]

በአዋጁ አንቀጽ 2(2) ድንጋጌ መሠረት ለድርጅት ትርጉም እንደ አንድ መስፈርት ከተቀመጡት ሁኔታዎች አንዱ ለሕጋዊ ዓላማ መቋቋም ነው። ድንጋጌው ለሕገ-ወጥ ዓላማ ከተቋቋመ ድርጅት ጋር የሥራ ውል ውጤት ምን እንደሆነ ያስቀመጠው ነገር ባይኖርም ለሕገ-ወጥ ዓላማ

---

[25] የሃይማኖት ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በቅጥር ላይ የተመሰረቱ የስራ ግንኙነቶች፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ፣ ደንብ ቁጥር 342/2007 ዓ.ም

[26] ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ስንል የሃይማኖት እና በጎ አድራጎት ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሙያ ማኅበራት፣ የኅብረት ስራ ማኅበራት፣ የሠራተኞች ማኅበራት፣ የአሠሪዎች ፌዴሬሽን እና ኮንፌዴሬሽኖች፣ የተለያዩ የስፖርት ፌዴሬሽኖችን እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል። እነዚህ ተቋማት ለትርፍ ባለመቋቋማቸው ሕጉ ድርጅት ብሎም አሠሪ በሚል በሰጠው ውሳኔ የማይሸፈኑ ከሆነ እነዚህ ተቋማት ከሠራተኞቻቸው ጋር የሚመሰርቱት የስራ ግንኙነት የሚዳኝበት ሕግ አይኖርም፤ ይህ ደግሞ የሕጉ ዓላማ አይደለም።

የተቋቋመ ተቋም የድርጅትንም ሆነ የአሠሪን ትርጉም ስለማያሟላ ከሚቀጥራቸው ሠራተኞች ጋር የሚኖረው ግንኙነት በአዋጁ አይገዛም።

4.2.3. ድርጅት እና የአንድ አመራር ጽንሰ-ሃሳብ

የአዋጁን አንቀጽ 2(2) ድንጋጌ ስንመለከተው የአንድ አመራር መኖር ጽንሰ-ሃሳብ ለድርጅት ብሎም ለአሠሪ ትርጓሜ ዋነኛ መስፈርት ተደርጎ ተወስዷል። ሕጉ በዋናው ድርጅት እና በስሩ በሚገኝ ራሱን የቻለ ቅርንጫፍ መካከል ያለውን ተጠያቂነት ለሁለት ሰንጥቆታል። ይህ የሕግ ክፍል ለድርጅት የሰጠውን ትርጓሜ ከባለቤትነት አንጻር አሃዳዊ ቅርጽ ያለውን የንግድ ተቋም ከአንድ በላይ የአሠሪነት ሚና እና ኃላፊነት እንዲላበስ ያደርገዋል።[27] ይሁን እንጅ በዚህ መንገድ አንድን ቅርንጫፍ ራሱን እንደቻለ አሠሪ ድርጅት መቁጠር በሕጉ አፈጻጸም ላይ የራሱ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ይኖሩታል። ለምሳሌ ያክል ተጠያቂነትን በመወሰን ረገድ ዋናውን እና ቅርንጫፉን የሚያገናኝ ገመድ ሳይበጅ አንድን አሠሪ ለሁለት መሰንጠቅ ለሠራተኛው በሕጉ የተጠበቁለትን መብቶች እና ከለላዎች ተፈጻሚነት አድማስ ያጠበዋል።[28]

4.3. የሠራተኛነት ትርጉም

ሠራተኛ ማነው የሚለውን ነጥብ በተመለከተ አዋጁ በአንቀጽ 4(1)፣ (2) እና (3) ድንጋጌዎች ላይ ከአሠሪ ጋር በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ ነው በሚል የተረጎመ ሲሆን ይህን ትርጉም ስንመለከተውም አዋጁ ሠራተኛ የሚለውን ጽንሰ-ሃሳብ ከሥራ ውል ትርጓሜ ጋር በማስተሳሰር የተረጎመበት መንገድ የስራ ውል መኖር ሠራተኛ ማን ነው የሚለውን ጉዳይ ለመወሰን እንደ አንድ መስፈርት እንደወሰደው ያስረዳል። የአዋጁ አንቀጽ 4(1) ድንጋጌ ሠራተኛን በተመለከተ ማንኛውም ግለሰብ ደመወዝ እየተከፈለው በአሠሪው

---

[27] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 4 ገጽ 11-15፣ ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 16 Belayneh Ketsela ገጽ 48-68።

[28] ለምሳሌ ድርጅቱ በአጠቃላይ እንቅስቃሴው ትርፋማ ሆኖ በስሩ ያለ ራሱን የቻለ ቅርንጫፍ ኪሳራን ካሳየ ሠራተኞቹ አላግባብ የሚቀነሱበት ሁኔታ ይፈጠራል። በተጨማሪም ቅርንጫፉ በስሩ ለሚገኙ ሠራተኞች ባለዕዳ ሲሆን ዋናው ድርጅት ከጋራ ተጠያቂነት ያመልጣል። በሌላ በኩል የራሳቸው ሕጋዊ ሰውነት ባላቸው አህት ድርጅቶች መካከል የጋራ ተጠያቂነት የሚኖርበት ቀዳዳ አይኖርም። የባለቤትነት ለውጥ ባይኖርም እያንዳንዱ ድርጅት ለሚቀጥራቸው ሠራተኞች አሠሪ ይሆናል። ሆኖም በድርጅቶቹ መካከል በፈቃድ ላይ የተመሰረተ የሠራተኛ ዝውውር ሲፈጸም አሠሪውን ነጥሎ መለየት ያዳግታል። እንበልና ከዝውውሩ በኋላ ሠራተኛው ለአንድ ዓመት ያክል አገልግሎ የሥራ ውሉ በሕገ-ወጥ መንገድ ቢቋረጥ ካሳ እና ሌሎች ከስራ ውል በሕገ-ወጥ መንገድ መቋረጥ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ጥቅማጥቅሞችን የመክፈል ግዴታ ያለበት አሠሪ የትኛው ነው? ለዓመት ፈቃድ እና ለሥራ ስንብት ክፍያ ሲባል የአገልግሎት ዘመናቸው የሚቆጠረው እንዴት ነው? ሠራተኛው ከዝውውር በፊትም ሆነ በኋላ የሰራባቸው ድርጅቶች እህት ኩባንያዎች ቢሆኑም ሁለቱም የተለያየ ሕጋዊ ሰውነት አላቸው። ዝውውሩ የሠራተኛውን የሥራ ውል አላቋረጠውም ስለሆነም ሠራተኛው በመርህ ደረጃ ለሁለት የተለያዩ አሠሪዎች አገልግሎትን ቢሰጥም የስራ ውሉ ቀጣይነት ያለው አንድ ውል እንጅ በአሠሪው መለያየት ምክንያት ሁለት ውል አይኖረውም። እነዚህን እና ሌሎች ከዚህ ጋር በተያያዘ ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎችን በመፍታት ረገድ ሁለቱንም አሠሪዎች የሚያስተሳስር የሕግ ማዕቀፍም የለም።

መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሁለቱ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ሥራ ለአሠሪው ለመሥራት ቢስማማ በሁለቱ መካከል የሥራ ውል ይመሠረታል በሚል ይዘቱን ሲያስቀምጥ ማንኛውም ግለሰብ የሚለው ሐረግ የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከት እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ይሁን እንጂ ምንም እንኳ የሥራ ውል ከማንኛውም ግለሰብ ጋር ሊመሠረት እንደሚችል ሕጉ ቢደነግግም በዚሁ ሕግ እና በሌሎች ደንቦች ላይ ሁሉም ግለሰቦች የሥራ ውል ስላላቸው ብቻ ሠራተኛ እንደማይሆኑ መረዳት የሚቻልበትን አግባብ አስቀምጧል፡፡ ከላይ ያነሳነውን ነጥብ በተመለከተም በተለያዩ ሕጎች ከተቀመጡት ሠራተኛነትን ከሚመለከቱ ትርጓሜያዊ ማግለሎች ውስጥ የሚከተሉትን እንደ ምሳሌ ማስቀመጥ ይቻላል[29]፡፡ ከዚህ በላይ ከተነሱት ነጥቦች በተጨማሪ በአዋጁ ቀጥተኛ ማግለል የተደረገባቸው እና በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ማግለል የተፈጸመባቸው የሥራ ግንኙነቶች ላይ ያሉ ተዋዋይ ወገኖችም ምንም እንኳ የሥራ ውል ቢኖራቸውም በዚህ ሥራ ላይ ተቀጥረው የሚሠሩ ግለሰቦች ለአዋጁ ዓላማ ሠራተኛ የሚለውን ነጥብ አያሟሉም፡፡[30]

---

[29] የአዋጁ አንቀጽ 89(2) ድንጋጌ ዕድሜው ከ14 ዓመት በታች የሆነን ግለሰብ በሠራተኛነት መቅጠር አይቻልም በሚል ይደነግጋል፤ ለውጭ አገር ዜጎች የስራ ፈቃድ ስለሚሰጥበት ሁኔታ ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣው መመሪያ ቁጥር 2/2002 አንቀጽ 4(1) ሕጋዊ የስራ ፈቃድ የሌለው የውጭ አገር ዜጋ በሠራተኛነት ሊቀጠር እንደማይችል ይደነግጋል፣ የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችን በተመለከተም የንግድ ሕጉ በሠራተኛነት ጎራ የሚመደቡትን የንግድ ሠራተኞች፣ የንግድ ተላላኪዎች እና የንግድ እንደራሴዎች (የንግድ ሕግ ቁጥር 28፣ 37 እና 38 ድንጋጌዎች እንደቅደም ተከተላቸው) በሠራተኛነት እውቅና የሰጠ ሲሆን በራሳቸው የሙያ ኃላፊነት የሚሰሩትን የንግድ ሥራ ተቋራጮች፣ የንግድ ወኪሎች፣ ደላሎች እና ባለኮሚሲየኖች (የንግድ ሕግ ቁጥር 44፣ 56 እና 60 እንደየቅደም-ተከተላቸው) የሥራ ውል እንደሌላቸው በሕግ አስቀድሞ በመወሰኑ ሠራተኛ የሚለውን ትርጉም አያሟሉም፡፡

[30] Linder, Marc, Dependent and Indepпendent Contractors in Recent U.S. Labor Law: An Ambiguous Dichotomy Rooted in Simulated Statutory Purposelessness" 21 Comparative Labor Law and Policy Journal, 1999, pp. 187, accessed on July 17, 2019, available at https://ir.uiowa.edu/cgi/viewcontent.cgi?article=1010&context=law_pubs;
በተጨማሪም የአዋጁ አንቀጽ 3(2) ድንጋጌ ስር ስድስት አይነት በቅጥር ላይ የተመሰረቱ የስራ ግንኙነቶች እንዳሉ እና እነዚህም የሥራ ግንኙነቶች ከአዋጁ የተፈጻሚነት ወሰን ቀጥተኛ በሆነ መንገድ እንደተገለሉ ያትታል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 3(3) ድንጋጌ ስርም አራት አይነት በቅጥር ላይ የተመሰረቱ የስራ ግንኙነቶች እንዳሉ እና እነዚህም የሥራ ግንኙነቶች በቅድመ-ሁኔታ ላይ በተመሰረተ መንገድ ከአዋጁ የተፈጻሚነት ወሰን እንደተገለሉ ተደንግጎ እናገኘዋለን፡፡ ከዚህ ላይም ምንም እንኳ እነዚህ የሥራ ግንኙነቶች በቅጥር ላይ የተመሰረቱ የሥራ ግንኙነቶች ቢሆኑም ለዚህ አዋጅ ዓላማ በእነዚህ የሥራ ግንኙነቶች ላይ ተዋዋይ ወገን የሆኑት ሠራተኞችም ሠራተኛ የሚለውን ትርጉም አያሟሉም ማለት ነው፡፡

5. ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሃሳቦች

5.1. ማጠቃለያ

አዋጁ የተፈጻሚነት ወሰኑን በተመለከተ በመርሕ ደረጃ ሕጉ በቅጥር ላይ በተመሠረቱ የሥራ ግንኙነቶች ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን ቢያስቀምጥም በልዩ ሁኔታ ግን ሕጉ ተፈጻሚ ሊሆን የማይችልባቸውን እና የተገለሉ የሥራ ግንኙነቶችንም በተነጻጻሪነት ደንግጎ ይገኛል፡፡ በአዋጁ ማግለል ማለት የተወሰኑ አሠሪዎችን እና ሠራተኞችን ከሕጉ የሚመነጩ መብቶችን፣ ጥቅሞችን እና ጥበቃዎችን መከልከል ማለት ሲሆን አንድ የሥራ ግንኙነት በአሠሪ እና ሠራተኛ መካከል መደረጉ፣ የሥራ ግንኙነቱ በቅጥር ላይ ተመሥርቶ መፈጸሙ እና የሥራ ውል መኖሩ ብቻውን በአሠሪ እና ሠራተኛ ሕግ የሚዳኝ የሥራ ግንኙነት አያደርገውም፡፡

በአዋጁ ውስጥ ሶስት አይነት የማግለል አይነቶች ተካተዋል፡፡ የመጀመሪያው ትርጓሜያዊ ማግለል ሲሆን አንድ በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ግንኙነት በሕጉ የትርጉም ክፍል አሠሪ፣ ሠራተኛ እና የሥራ ውል ለሚሉት ነጥቦች የተሰጠውን ትርጓሜ ያሟላል ወይስ አያሟላም የሚለውን ነጥብ እንደ ጭብጥ በመያዝ የሚያሟሉት በሕጉ እንዲዳኙ የማያሟሉት ከሕጉ የተፈጻሚነት ወሰን እንዲገለሉ የሚያደርግ የማግለል ዘርፍ ነው፡፡

ሁለተኛው እና ሶስተኛው ደግሞ በሕጉ የትርጉም ክፍል ለአሠሪ፣ ሠራተኛ እና የሥራ ውል ለሚሉት ነጥቦች የተሰጠውን ትርጉም የሚያሟላ ሆኖ ነገር ግን የሕጉን የተፈጻሚነት ወሰን በሚደነግገው ክፍል ስር በቀጥታ ወይም በቅድመ-ሁኔታ ላይ የተመሠረተ የማግለል ተግባር ተፈጽሞበት እነዚህ የሥራ ግንኙነቶች በሕጉ እንዳይዳኙ ገደብን የሚጥሉ እና ከሕጉ የተፈጻሚነት ወሰን ውጭ የሚያደርጉ የማግለል አይነቶች ናቸው፡፡

በአዋጁ የትርጉም ክፍል አሠሪ፣ ሠራተኛ እና የሥራ ውል ለሚሉት ነጥቦች የተሰጠውን ትርጉም የሚያሟሉት በቅጥር ላይ የተመሰረቱ የሥራ ግንኙነቶች ላይ አዋጁ በቀጥታ ወይም በቅድመ-ሁኔታ ላይ ተመስርቶ እስካላገለላቸው ድረስ አዋጁ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል በአዋጁ የትርጉም ክፍል አሠሪ፣ ሠራተኛ እና የሥራ ውል ለሚሉት ነጥቦች የተሰጠውን ትርጉም የማያሟሉት በቅጥር ላይ የተመሰረቱ የሥራ ግንኙነቶች ትርጓሜያዊ በሆነ መንገድ የተገለሉ ስለሆኑ አዋጁ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

5.2. የመፍትሔ ሃሳቦች

አንድን ቀጣሪ ድርጅት ብሎም አሠሪ ለማለት በምሑራን ዘንድ ድርጅት፣ ሕጋዊ ሰውነት፣ ለትርፍ መቋቋም፣ ሕጋዊ ዓላማ እና የአንድ አመራር ጽንሰ-ሃሳብ የሚሉት ነጥቦች የተለያየ አቋም የሚያዝባቸው እና አሻሚ የሆኑ ሐረጋት እንደሆኑ ከላይ አሠሪነት እና ድርጅት የሚለውን የትርጉም ክፍል ስናይ ለመረዳት ችለናል። ስለሆነም በባለሙያዎች ዘንድ የተለያየ ትርጉም መሰጠቱ በአሠሪ እና ሠራተኛ መብቶች እና ግዴታዎች ዙሪያ ወጥነት ያለው ፍርድን በመስጠት ረገድ ውስንነትን እና ልዩነትን እንዳይፈጠር እና የአሠሪዎች እና ሠራተኞች ፍትሕ የማግኘት መብት እንዳይጣበብ እንዲሁም ሕጉ የታሰበለትን ዓላማ ያሳካ ዘንድ ለእነዚህ ነጥቦች በተጠና መልኩ የሕግ ማሻሻያን ማድረግ አሠሪ ማን ነው የሚለውን ነጥብ በቀላሉ መለየት ስለሚያስችል ሕግ አውጭው አካል ድርጅት የሚለው የአዋጁ ክፍል ላይ ማሻሻያን ማድረግ ለነገ የማይባል የሕግ አውጭው ተግባር ሊሆን ይገባል።

በስራው ዓለም ላይ የሚገኙ አሠሪዎች እና ሠራተኞች ከአዋጁ የተፈጻሚነት ወሰን አንጻር የስራ ግንኙነታቸው በቅጥር ላይ ተመስርቶ መፈጸሙ እና የሥራ ውል መኖሩ ብቻውን በሕጉ የሚዳኝ የሥራ ግንኙነት ስለማያደርገው በሕጉ አሠሪ፣ ሠራተኛ እና የሥራ ውል ለሚሉት ነጥቦች የተሰጠውን ትርጉም በመገንዘብ አሠሪነታቸው፣ ሠራተኛነታቸው እና የሥራ ውላቸው ትርጓሜያዊ በሆነ መልኩ ከሕጉ የተፈጻሚነት ወሰን የተገለለ መሆኑን ወይም አለመሆኑን እንዲያውቁ እና መብት እና ግዴታቸውን በተገቢው መንገድ እንዲያስከብሩ ሰፊ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሊሰራ ይገባል።

በተጨማሪም ሕግን በማውጣት፣ በመተርጎም እና በማስፈጸም ላይ የተሰማሩ የሕግ ባለሙያዎች፣ ሕግ እና ፖሊሲ አውጭዎች፣ ዳኞች፣ ጠበቆች፣ አስፈጻሚ አካላት እንዲሁም በመስኩ የተሰማሩ የሕግ መምህራን እና ተማሪዎች ሕጉ የበለጠ ይጎለብት ዘንድ ይህን ጽሑፍ እንደ መነሻ በመጠቀም ተጨማሪ ጥናት እና ምርምርን እንዲያከናውኑ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሁኔታዎችን ሊያመቻቹ ይገባል።

ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ስርዓት፡-

(Standard of proof under Ethiopian criminal justice system)

የአማራ ክልል ተግባራዊ አፈጻጸም

ይማም ሰይድ ሀሰን*

አህጽሮተ ይዘት

በወንጀል ጉዳዮች ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ በፍትህ አሰተዳደሩ ዉስጥ የሚጫወተዉ ሚና ቀላል የሚባል አይደለም። በክርክር ሂደት ዉስጥ ሊረጋገጥ የተፈለገዉን ፍሬ-ነገር በምን ያህል ደረጃ መረጋገጥ እንዳለበት በህግ ቀድሞ መደንገግ ወጥ እና ፍትሀዊ ለሆነ ዉሳኔ መሰረት ከመሆኑም ባሻገር በህግ የበላይነት የሚያምን ዜጋ ለመፍጠርም ያስችላል። በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ አሰተዳደር ጥፋተኝነትን ለማስረዳት የምንጠቀምበት መመዘኛ በግልጽ ተቀምጦ አናገኘዉም። ነገር ግን በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ስር የሚገኙ በየደረጃዉ ያሉ ፍርድ ቤቶች "ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ" ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃን መጠቀም እንዳለባቸዉ ያምናሉ።

ስለሆነም ይህ ጽሁፍ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ማለት ምን ማለት ነዉ? በኢትዮጵያ የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት መመዘኛ የትኛዉ ነዉ? ተግባራዊ አፈጻጸሙ በአማራ ክልል ምን ይመስላል? የሚሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን፣ ጽሁፎችን፣ በ1987 ዓ.ም የወጣዉን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ከዚህ በኋላ ኢፌዲሪ ተብሎ የሚገለጸዉ) ህገ መንግስት፣ በ1954 ዓ.ም የወጣዉን የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ፣ ረቂቁን የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ እንዲሁም በ2003 ዓ.ም የወጣዉን የኢፌድሪ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ ዳሷል።

የጥናቱ ዘዴ አይነታዊ ሲሆን ለጥናቱም የደቡብ ወሎ ዞን፣ ሰሜን ጎንደር ዞን እንዲሁም የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤቶችን ለማካተት የተሞከረ ሲሆን በተጨማሪም በእነዚሁ ዞኖች የሚገኙ የተመረጡ የወረዳ ፍ/ቤቶች ተግባራዊ አሠራር ተዳሷል። ዉሳኔ ያገኙ የወንጀል መዛግብት ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ፣ የፅሁፍ መጠይቅ እና የቡድን ተኮር ውይይት ለመረጃ መሠብሠቢያነት ተጠቅሟል።

በወንጀል ጉዳዮች ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ የትኛዉ እንደሆነ በግልጽ ፍርድ ቤቶቻችን በሚወስኗቸዉ መዛግብት እየታየ አይደለም። በዚህም የተነሳ በአፈጻጸም ወጥ የሆነ መመዘኛ ስለመኖሩም ማደማደም አይቻልም። ስለሆነም ይህ ጽሁፍ በኢትዮጵያ የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ግልጽ እና አሳማኝ ማስረጃ መሆኑን እና በአፈጻጸም እየታዩ ያሉ ችግሮችን በመጠቆም ተገቢ ናቸዉ የተባሉ መፍትሄዎችን ለማካተት ሞክሯል።

ቁልፍ ቃላት፡- ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ፣ የማስረዳት ሸክም፣ እንደ ንጹህ የመቆጠር መብት፣ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ማስረዳት፣ ግልጽ እና አሳማኝ ማስረጃ

---

* LLB, LLM በአብክመ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የህግ ምርምር ኢንስቲትዩት አሰልጣኝ እና ተመራማሪ። ጊዜያችሁን፣ የተለያዩ ጽሁፎችን እንዲሁም እዉቀታችሁን ሳትሰስቱ ላጋራችሁኝ ሁሉ ምስጋናዬ እጅግ የላቀ ነዉ። በYimamlaw@gmail.com ኢሜል አድራሻዬ ገንቢ አስተያየት ብታደርሱኝ በደስታ እቀበላለሁ።

1. መግቢያ

ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ማለት በክርክር ሂደቱ ውስጥ ሊረጋገጥ የታሰበዉ ፍሬ-ነገር በህጉ መሰረት ምን ያህል ተረጋግጧል ወይም አልተረጋገጠም የሚለዉን የምናዉቅበት ሚዛን ነዉ።[1] ይህ ሚዛን በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ስርዓቱ ዉስጥ ፍትሀዊነትን ለማስፈን፣ ንጹሀንን ለመጠበቅ እና ስህተቶችን ለመቀነስ ሚናዉ የጎላ ነዉ።

የወንጀል ክርክሮች ወደ ፍርድ ቤት ከመጡ በኋላ ለክርክር ምክንያት የሆነዉን ፍሬ ጉዳይ እልባት ለመስጠት ማስረጃዎች የማይተካ አስተዋጽዖ አላቸዉ። የማስረጃዎች አግባብነት፣ ተቀባይነት እና ተአማኒነት እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቱ በያዘዉ ጉዳይ ላይ ትክክለኛ እና ፍትሀዊ ዉሳኔ ሰጥቷል የሚባለዉ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ የቀረቡት ማስረጃዎች ለክርክር ምክንያት የሆነዉን ፍሬ ጉዳይ በምን ያህል ደረጃ ሲያስረዱ ነዉ? የሚለዉ በግልጽ ሲቀመጥ እና መመዘኛዉም ፍትሀዊነትን የሚያሰፍን፣ ንጹሀንን የሚጠብቅ እንዲሁም ስህተቶችን የሚቀንስ ሲሆን ነዉ።

ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ስርዓት ዉስጥ በግልጽ ተቀምጦ አናገኘዉም። በዚህም የተነሳ ፍርድ ቤቶቻችን ወጥ የሆነ የአመዛዘን ስርዓት የላቸዉም። ይህ ደግሞ በጠቅላላ የወንጀል ፍትህ ስርዓቱም ሆነ በተከራካሪ ወገኖች ላይ የሚያመጣዉ ጉዳት ቀላል አይሆንም።

ስለሆነም የዚህ ጽሁፍ ዓላማ የኢፌድሪ ህገ መንግስት፣ የኢትዮጵያ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ፣ ረቂቁን የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ፣ የኢፌድሪ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ፣ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን እና ጽሁፎችን በመዳሰስ በኢትዮጵያ የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ የትኛዉ ነዉ የሚለዉን መጠቆም እና በተግባር ፍርድ ቤቶቻችን ማስረጃዎችን እየመዘኑበት ያለዉን ደረጃ መዳሰስ ነዉ።

የዚህ ጽሁፍ የመጀመሪያዉ ክፍል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ምንነት እና ጽንስ-ሀሳብ፣ የትኛዉ የማስረዳት ደረጃ የተሻለ ነዉ የሚሉትን እና ወጥ የሆነ የማስረዳት ደረጃን አስፈላጊነት የተዳሰሰበት ነዉ። ሁለተኛዉ ክፍል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃዎችን እና የእነዚሁ የማስረዳት ደረጃዎች የጀርባ አጥንት የሆነዉን ነጻ ሆኖ የመገመት መብትን ዘርዘር ባለ ሁኔታ

[1] Clermont, Kevin M. Standard of Proof in Japan and the United States, Cornell Law School Working Paper series, Paper 5 (2003) <http://15r.nellco.ors/cornell/clsops/papers/5>

የታየበት ነዉ። ሶስተኛዉ ክፍል ደግሞ በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ በኢትዮጵያ ህግ ምን እንደሚመስል ለመጠቆም የተሞከረበት ሲሆን የመጨረሻዉ እና አራተኛዉ ክፍል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ተግባራዊ አፈጻጸም በአማራ ክልል ምን እንደሚመስል ተዳሶበታል። በመጨረሻም በኢትዮጵያ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 141 ስር "በቂ ማስረጃ" በሚል የተቀመጠዉ ግልጽ እና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃን የሚያመላክት እንደሆነ በማጠቃለያነት ተቀምጧል።

1.1. ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ምንነት እና ጽንሰ-ሀሳብ

አንድ ግለሰብ በወንጀል ተጠርጥሮ ክስ ከተመሰረተበት የተከሳሽን የወንጀል ድርጊት ያስረዳሉ ተብለዉ የሚታሰቡ ማስረጃዎች ቀርበዉ ከተመዘኑ በኋላ እንደማስረጃዎቹ የማስረዳት ብቃት ተጠርጣሪዉ ላይ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ ፍርድ ቤት ያስተላልፋል። ፍርድ ቤትም የቀረበለትን ማስረጃ ሲመዝን ሊረጋገጥ የታሰበዉን ፍሬ-ነገር በተገቢዉ ሁኔታ አስረድቷል ወይስ አላስረዳም የሚለዉን በትኩረት የሚያይ ይሆናል። የቀረበዉን ማስረጃ ሊረጋገጥ ከታሰበዉ ፍሬ-ነገር አንጻር ማገናዘብ እና መመርመር ጥንቃቄ የሚሻ ጉዳይ ነዉ።

በክርክር ሂደት ዉስጥ ሊረጋገጥ የታሰበዉ ፍሬ-ነገር በህጉ መሰረት ምን ያህል ተረጋግጧል ወይም አልተረጋገጠም የሚለዉን የምናዉቅበት ሚዛን ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ (Standard of proof) ይባላል።[2] ስለሆነም ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ማለት የማስረዳት ሸክም ያለበት ተከራካሪ ወገን የክርክሩን ፍሬ-ነገር ያስረዳበትን ዳራ ማሳያ ነዉ።[3]

የብዙ አገራት የወንጀል ህጎች በክርክር የተያዘዉ ጉዳይ በበቂ ሁኔታ ሲረጋገጥ ዉሳኔ ማረፍ እንዳለበት ከመግለጽ ዉጪ ጥፋተኝነትን የማስረዳት መመዘኛዎችን በግልጽ ከመተርጎም የተቆጠቡ ናቸዉ።[4] ይህ ማለት ጥፋተኝነትን የማስረዳት መመዘኛ ዓይነትን ከመወሰን በመለስ ያለዉ ጉዳይ ለህግ ተርጓሚዉ አካል የተተወ ይመስላል።

[2] ዝኒ ከማሁ
[3] Bryan A Garner, eds, Black law dictionary 8th edition (St, Paul, Thomson west, 2004)
[4] Christian Diesen, Beyond Reasonable Doubt Standard of Proof and Evaluation of Evidence in Criminal Cases, Stockholm Institute for Scandianvian Law 1957-2009, p.170. < http://www.scandinavianlaw.se/pdf/40-7.pdf >

ሊረጋገጡ የተፈለጉትን ፍሬ-ነገሮች በተገቢዉ ማስረጃ ፍርድ ቤትን የማሳመን ሀላፊነት የተጣለዉ የማስረዳት ሸክም በህግ የተጣለበት ተከራካሪ ወገን ላይ ነዉ።[5] የማስረዳት ሸክም የሚለዉ ሀረግ ሁለት የተለያዩ ግዴታዎችን ያቀፈ ነዉ። አንደኛዉ የማስረዳት ሸክም ወይም ማስረጃ የማቅረብ ሸክም ሲሆን ሁለተኛዉ የማሳመን ሸክም ነዉ። ማስረጃ የማቅረብ ሸክም ክሱ በተጀመረ ጊዜ በክሱ ዉስጥ የሚነሱትን የተለያዩ ጭብጦች ለማስረዳት በህጉ መሰረት በቅድሚያ ማስረጃ ማቅረብ ያለበትን ተከራካሪ ወገን አመላካች ነዉ።[6]

በእርግጥ ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ የተጣለበት ተከራካሪ ወገን ባቀረበዉ ማስረጃ መሰረት ፍርድ ቤቱን ማሳመን ይኖርበታል። ሆኖም ግን ማስረጃ የማቅረብ ሸክም ከማሳመን ሸክም ከሚለይባቸዉ ምክንያቶች ዉስጥ ዋነኛዉ ማስረጃ የማቅረብ ሸክም ከአንዱ ወደ ሌላዉ የሚተላለፍ መሆኑ ነዉ። የማሳመን ሸክም የሚባለዉ ፍርድ ቤቱን በቀረበዉ ማስረጃ ክርክር ያስነሳዉ እዉቅ ነገር እዉነት መሆኑን እንዲቀበል ይበልጥ አሳማኝ ማስረጃ በማቅረብ ፍርድ ቤቱ ማስረጃዉን እንዲያምን ማድረግ ነዉ።[7]

ለክርክር የቀረበዉን ፍሬ ጉዳይ ማስረጃዉ አስረድቷል ወይም አላስረዳም ለማለት የሆነ መለኪያ ወይም ደረጃ ማበጀት የሚያስፈልግ ሲሆን ደረጃዉን ያሟላ ጉዳዩን በበቂ ሁኔታ አስረድቷል ሲባል ደረጃዉን ያላሟላ ደግሞ አላስረዳም ለማለት ደረጃዉን ቀድሞ መወሰን ተገቢም ፍትሀዊም ነዉ።[8]

ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ በሚመለከት በህግ የሚወሰደዉ አቋም እንደየአገሩ የህግ ስርዓት እና እንደየጉዳዩ አይነት ይለያያል። የአንግሎ አሜሪካን (Common Law) የህግ ስርዓት ተከታይ አገሮች ማስረጃን አስረድቷል የሚሉበት ደረጃ ከአህጉራዊዉ አዉሮፓ (Civil Law) የህግ ስርዓት ተከታይ አገሮች ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ የሚለይ ነዉ።[9]

የአንግሎ አሜሪካን የህግ ስርዓት ተከታይ አገሮች ሦስት አይነት ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ሲኖራቸዉ ይኸዉም፡-

---

[5] የኢፌድሪ የማስረጃ ህግ (ሁለተኛ ረቂቅ) ማብራሪያ፣ በፍትህ እና የህግ ስርዓት ኢንስቲትዩት የተዘጋጀ፣ ነሀሴ 1996 ዓ.ም (አዲስ አበባ)፣ ገጽ 13

[6] ዝኒ ከማሁ ገጽ 14

[7] ዝኒ ከማሁ

[8] ዝኒ ከማሁ

[9] Jon O. Newman, Beyoned Reasonable Doubt, Newyork University Law Review, Nove 1993, Volume 68, No 5 , p.4. < https://www.law.nyu.edu/sites/default/files/ECM_PRO_059253.pdf >

1. ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ (Beyond reasonable doubt standard) ሙሉ ለሙሉ የወንጀል ጉዳዮችን ብቻ ለመመዘን የሚያገለግል ሲሆን፤
2. ግልጽ እና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ሀላፊነትን የማስረዳት ደረጃ (Clear and convincing evidence standard) ከበድ ላሉ እና የተወሰኑ የፍትሀብሄር ጉዳዮችን ለመመዘን ያገለግላል፤
3. በተሻለ ሁኔታ በማሳመን ሀላፊነትን የማስረዳት ደረጃ (Preponderance of evidence standard) ለብዙዎቹ የፍትሀብሄር ጉዳዮች መመዘኛነት የሚያገለግል ነዉ።

ሀገራት የህግ ስርዓታቸዉ እያደገ እና እየዘመነ በሄደ ቁጥር ለእዉነት የቀረቡ እና ስህተታቸዉ በጣም የቀነሱ የማስረጃ ዓይነቶችን በወንጀል ምርመራ ጊዜ ይጠቀማሉ። ይህ ማለት ደግሞ የሚጠቀሙት ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ በዚያዉ ልክ ከፍ ይላል ማለት ነዉ።[10]

1.2. በወንጀል ህግ የትኛዉ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ የተሻለ ነዉ?

ይህን ጥያቄ ለመመለስ ማጠንጠኛ ነጥብ መሆን ያለበት አጥፊዎችን ጥፋተኛ ለማለት እና ንጹሀኖችን ነጻ ለማዉጣት የትኛዉ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ይበልጥ ትክክል (accurate) ነዉ የሚለዉ ነዉ። የትኛዉም ስርዓት ፍጹም አይደለም። ነገር ግን ወደ ፍጹም የተጠጋዉ መለኪያ የተሻለ ተመራጭ ይሆናል።[11] ስለሆነም ምንም እንኳን ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ተደረገ የተባለዉን ወንጀል ለማሳመን በሚቀርቡ ማስረጃዎች ላይ የተንጠለጠለ ቢሆንም የተጠርጣሪን ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብትን ሳይጥስ ንጹሀኖች ያለአግባብ ወደ ወንጀል ክርክሩ ገብተዉ በተሳሳተ የጥፋተኝነት ዉሳኔ ተጎጅ እንዳይሆኑ ይበልጥ ጥበቃ የሚያደርግ እና ትክክለኛ ወንጀል ፈጻሚዎችም ያለአግባብ ከፍትህ እንዳያመልጡ የሚያደርግ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ የተሻለ ነዉ።

1.3. ወጥ የሆነ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ለምን አስፈለገ?

ጥፋተኝነት የሚገመት ሳይሆን የሚረጋገጥ መሆን አለበት። አንድ ተጠርጣሪ ጥፋተኝነቱም ሆነ ነጻነቱ በፍትህ አደባባይ የጉዳዩን ፍሬ-ነገር በሚያስረዱ ማስረጃዎች እንዲረጋገጥ ማድረግ የዘመናዊ ፍትህ ስርዓት መገለጫ ነዉ። የተጠርጣሪዉን ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ

[10] ዝኒ ከማሁ
[11] Thomas Christopher Rider, What is the most useful standard of proof in Criminal Law, pragmatism Tomorrow 2013, Issue1, No 9, p.1. < https://www.pragmatismtomorrow.org/downloads/Essay009-RiderTC.pdf >

መብትን መርህ አድርጎ ንጹሀኖችን የሚጠብቅ እና አጥፊዎችን ለጠቅላላ ማህበረሰቡ ጥቅም ሲባል የሚቀጣ ስርዓት ማበጀት የየሀገራት ድርሻም ግዴታም ነዉ። እንደየጉዳዮቹ ባህሪ (ወንጀል/ፍትሐብሄር) አጥፊዎችን ወይም ሀላፊዎችን የምንለይበት ደረጃ መኖሩ የግድ ሲሆን ደረጃዉም ወጥ መሆን ይጠበቅበታል።

ህግ ከመነሻዉ ፍትሀዊ መሆን አለበት። ወጥነት ሳይኖር ፍትሀዊነትን ልንጠብቅ አንችልም። ስለሆነም ወጥነት ከተጓደለ የፍትሀዊነት ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነዉ። ወጥነት የጥሩ ህግ ስርዓት መገለጫ ነዉ። ወጥ የሆነ ህግ ወይም ስርዓት አለ ማለት ይህንኑ ተከትሎ ወጥ የሆነ የዉሳኔ አሰጣጥ ስርዓት ይኖራል ማለት ነዉ። ይህ ደግሞ ህግን አክባሪ ማህበረሰብ እንዲፈጠር የራሱ የሆነ አስተዋጽዖ ይኖረዋል። የየትኛዉም አገር የህግ ስርዓት የመጨረሻ ግቡ በህግ የበላይነት የሚያምን እና ህግን አክባሪ ማህበረሰብ መፍጠር ነዉ።[12] ስለሆነም ይህንን ትልቅ ግብ ለማሳካት ወጥ የሆነ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ መኖር የራሱ ድርሻ ይኖረዋል። ስለሆነም በአንድ አገር ወጥ የሆነ የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ መኖር ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሞች እንዲኖሩት ያስችላል።

2. የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃዎች

ምንም እንኳን የአገራት የማህበረሰብ እድገት ደረጃ፣ የወንጀል ምርመራ አቅም፣ የአገራት የኢኮኖሚ አቅም፣ የህግ ባለሙያዎች የዕዉቀት ደረጃ፣ የአገራት የህግ ስርዓትና እድገት እንዲሁም መሰል ጉዳዮች ለምንመርጠዉ የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ መሰረታዊ ጉዳዮች ቢሆኑም የወንጀል ጥፋተኝነትን ለማስረዳት ሁለት እዉቅ እና ትልልቅ ደረጃዎች አሉን። ይኸዉም የአንግሎ አሜሪካ የህግ ስርዓት ተከታይ አገሮች በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ "ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ" ማስረዳት ሲሆን የአህጉራዊዉ አዉሮፓ የህግ ስርዓት ተከታይ አገሮች የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ደግሞ ግልጽ እና አሳማኝ በሆነ መንገድ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ነዉ።

2.1. ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ

ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ እንደአሁኑ የወንጀል ፍትህ ስርዓቱ ዓምድ ከመሆኑ በፊት በ12ኛዉ ክፍለ ዘመን በእንግሊዝ አገር መሰረቱን እንደጣለ ይነገራል።[13]

[12] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 2
[13] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 199

ከ16ኛዉ ክፍለ ዘመን በፊት ጁሪዎች በዋናነት የሰዉ እና ሌሎች ማስረጃዎችን መሰረት አድርገዉ ሳይሆን ራሳቸዉ ጉዳዩን በተረዱት፣ ባወቁት እና በዙሪያቸዉ ያለን እዉነታ መሰረት አድርገዉ የዉሳኔ ሀሳብ ያቀርቡ ነበር። ከ16ኛዉ ክፍለ ዘመን በኋላ የሰዉ እና ሌሎች ማስረጃዎች ለወንጀል ፍትህ ስርዓቱ ዋነኛ አስረጅ ሆነዉ ብቅ አሉ።[14] ስለሆነም ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ይበልጥ ትኩረት እያገኘ መጥቶ አሁን ያለዉን ቅርጽ ይዟል። ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ መነሻዉ እና እድገቱ እንግሊዝ፣ አሜሪካ ወይስ ሁለቱም አገራት ናቸዉ የሚለዉ የጸሀፊዎች ክርክር እንደተጠበቀ ሆኖ በ19ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ በሰፊዉ ተቀባይነትን ያገኘ የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ለመሆን በቅቷል።

ምክንያታዊ ጥርጣሬን ለመተርጎም በአንዳንድ የህግ ሊህቃን የተሞከረ ቢሆንም ከመነሻዉ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ መተርጎም አለበት በሚሉ እና ትርጉም አያስፈልገዉም በሚሉት መካከል ያለዉ ክርክር እና የመከራከሪያ ምክንያት የብዙ ህግ ባለሙያዎችን ቀልብ እየሳበ መጥቷል።[15]

ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ መተርጎሙ አንዱን ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ከሌላኛዉ ለመለየት ከማስቻሉም በላይ የአንግሎ አሜሪካን የህግ ስርዓት አገራት ጁረሮች የህግ እዉቀት የሌላቸዉ ግለሰቦች ከመሆናቸዉ አንጻር እንደፈለጉ የራሳቸዉን ትርጉም እየፈጠሩ ያልተገባ መመዘኛ እንዳይጠቀሙ ይረዳል ብለዉ የሚያምኑ የህግ ሙህራን እንዳሉ ሁሉ በተቃራኒዉ ደግሞ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃዉ ሲተረጎም የምንጠቀማቸዉ ቃላቶች በተፈጥሯቸዉ አሻሚ እና ተተንትነዉ የማያልቁ በመሆናቸዉ ጁረሮችን ማደናገር ስለሚሆን አለመተርጎሙ የተሻለ ነዉ የሚሉም አሉ።[16]

ምክንያታዊ ጥርጣሬ ትርጉም ሊኖረዉ ይገባል ብለዉ የሚያስቡ የህግ ምሁራን ምክንያታዊ ጥርጣሬ ማለት አንድ ምክንያታዊ እና ጠንቃቃ ሰዉ በህይወቱ ለመወሰን ፈርቶ ያቆማቸዉን ከባድ እና በጣም አስፈላጊ ኩነቶች ተገቢነት ባለዉ ማስረጃ አስደግፎ የሚደርስበት ድምዳሜ ማለት ነዉ ብለዉ ሲተረጉሙት፡-

[14] Thomas V. Mulrine, Reasonable Doubt: How in the World Is It Defined,online, American University International Law Review,Volume 12, issue 1, 1997, p.197.< https://digitalcommons.wcl.american.edu/auilr >
[15] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 199
[16] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 210

> Reasonable doubt' is such a doubt as would cause a reasonable and prudent person, in one of the graver and more important transactions of life, to pause and hesitate before taking the represented facts as true and relying and acting thereon.[17]

ሌሎቹ ደግሞ በተቀራረበ አገላለጽ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ማለት አንድ ምክንያታዊ ሰዉ ለራሱ አስፈላጊ ነዉ ባለዉ ጉዳይ በበቂ ምክንያት አምኖበት ከመወሰን ወደ ኋላ የማይለዉ ማለት ነዉ ይላሉ፡፡

> Beyond reasonable doubt has been explained to mean proof of such a convincing character that a reasonable person would not hesitate to act upon it in the most important of his or her own affairs.[18]

ጀስቲስ ጊንስበርግ (Justice Ginsburg) **የተባለች ጸሀፊ በበኩሏ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ትርጉም ሊኖረዉ እንደሚገባ ተስማምታ ነገር ግን ስንተረጉም አሻሚ በሆኑ እንደ "በህይወትህ አስፈላጊ የሆኑ ዉሳኔዎች"** (important transactions of life)፣ "**ለመወሰን መወላወል**" (hesitation to act) **እና መሰል ቃላቶች ጁሪዎች እንዲደናገሩ ከማድረግ ይልቅ ግልጽ እና ቀጥተኛ የሆነ ትርጉም መኖር አለበት በሚል እሳቤ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ማስረዳት ማለት ተጠርጣሪዉ ጥፋተኛ ስለመሆኑ በእርግጠኝነት ማመን መቻል ነዉ** (proof beyond a reasonable doubt is proof that leaves you firmly convinced of the defendant's guilt.)[19] **ስትል ትገልጸዋለች፡፡**

ስለሆነም ዐቃቤ ህግ ወደ ፍርድ ቤት ይዞት የቀረበዉን ጉዳይ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ማስረዳት አለበት ሲባል ይዟቸዉ የቀረባቸዉ ማስረጃዎች ተከሳሹ ድርጊቱን መፈጸሙን ወደ ፍጹምነት በተጠጋ ሁኔታ ማረጋገጥ አለበት ማለት ነዉ፡፡ ፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪዉ ጥፋተኛ ስለመሆኑ ጥርጣሬ ስላለዉ ብቻ ተጠርጣሪዉ ነጻ ይሆናል ማለት አይደለም፡፡ ጥርጣሬዉ ከስሜት፣ ከግለሰባዊነት እና ጉዳይ ተኮር ከመሆን የጸዳ እና ምክንያታዊ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ማለት ጥርጣሬ አልባ ማለት አይደለም (Beyond reasonable doubt doesn't mean that beyond the shadow of doubt) **የሰዉ ልጆች በዚህ አለም ላይ ሲኖሩ እርግጠኛ**

---

[17] Bobby Greene, Reasonable Doubt: Is it defined by whatever is at the Top of the Google Page? Online, The John Marshall Law Review, Volume 50, issue 4, Summer 2017, p.937. <https://repository.jmls.edu/lawreview >

[18] William Twining and Alex Stein, eds, *Evidence and Proof* (New York: New York University Press, 1992) cambrige Journal , volume 52, issue 2, 1993, p. 346 . <https://doi.org/10.1017/S0008197300095350 >

[19] Thomas Christopher Rider **ክላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11፣ ገጽ** 209

ሆነዉ የማያዉቋቸዉ ነገሮች ከሚያዉቋቸዉ በቁጥር እጅጉን የላቁ ናቸዉ። ስለሆነም የትኛዉም የወንጀል ህግ ተከራካሪ ወገኖች ጥርጣሬ አልባ በሆነ መንገድ የወንጀልን ጉዳይ እንዲያስረዱ አይጠበቅም። በሌላ በኩል ደግሞ ከወንጀል ጉዳዮች ተፈጥሯዊ ባህሪ እና እንደ ንጹህ የመቆጠር መብት አንጻር በቀላሉ ወንጀለኛ (Probably Guilty) የሚያደርግ መለኪያም መጠቀም እንደሌለብንም እሙን ነዉ።[20]

በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ መሰረት ፍርድ ቤቶች በተጠርጣሪዎች እጣ ፈንታ ከመወሰናቸዉ በፊት ለሁለት ጥያቄዎች ምላሽ ሊኖራቸዉ ይገባል።[21]

- የመጀመሪያዉ ተከሳሹ ጥፋተኛ ነዉን? የሚለዉ ሲሆን
- ሁለተኛዉ ደግሞ ጥፋተኛ ከሆነ ምን ያህል እርግጠኛ ነን? ጥፋተኝነቱ ከምንከተለዉ የማስረዳት ደረጃ አንጻር ተረጋግጧልን? የሚሉት ናቸዉ።

ፕሮፌሰር በርበራ ጆ ሻፒሮ የተባለች ጸሀፊ "Reasonable doubt and probable cause" በተባለ መጽሀፏ ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮችን መረዳት እንዳለብን ትገልጻለች። ይኸዉም የሰዉ ልጅ ነገሮችን የሚለይበት ሁለት የእዉቀት ክፍል ያለዉ መሆኑን እና የመጀመሪያዉ ሂሳባዊ ቀመር ሲሆን በቀላሉ ፍጹም እርግጠኛ የምንሆንበት የእዉቀት ዘርፍ እንደሆነና ሁለተኛዉ ደግሞ በተሞክሮ ወይም በልምድ የምናገኘዉ እዉቀት በመሆኑ እንደ ሂሳብ ቀመር አንድ ሲደመር አንድ እኩል ይሆናል ሁለት (1+1=2) ብለን ፍጹም እርግጠኛ መሆን ስለማንችል ወደዚህ እርግጠኝነት የቀረበ ሞራላዊ እርግጠኝነትን (Moral certainity) መጠቀም እንዳለብን ትጠቁማለች። ስለሆነም ፍርድ ቤቶች ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ሲለኩ ሞራላዊ እርግጠኝነት መሰረታዊ ጉዳይ መሆን እንዳለበትም ትነግረናለች።[22]

ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ዳኞች ሞራላዊ እርግጠኝነት ላይ እንዲደርሱ የሚያደርግ ነዉ። ሞራላዊ እርግጠኝነት በሂሳብ ቀመር መድረስ ያልቻልነዉን እርግጠኝነት የምናይበት ከፍተኛዉ የእርግጠኝነት ልኬት ነዉ። ምክንያታዊ ጥርጣሬ

[20] Presumption of innocence, Burden of proof (in case without an affirmative defense), proof beyond reasonable doubt, P. 2 < https://lawofselfdefense.com/jury-instruction/ny>
[21] Yali corea-levy, making sense of reasonable doubt: Understanding certainty, doubt and Rule based Bias Filtering, American University Criminal Law Brief, Volume 8, Article 4, Issue 1, (2012) p.1.
https://works.bepress.com› yali corealvy>
[22] Thomas Christopher Rider ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11፣ ገጽ 202

ከእርግጠኝነት ስሜት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነዉ። ይህ ስሜት ሁላችንም ጋር አለ። የእርግጠኝነት ስሜቱ መነሻ ደግሞ በቂ መሰረት ያለዉ ምክንያታዊነት ነዉ።[23]

ስለሆነም ጥርጣሬዉን ምክንያታዊ ለማለት የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸዉ።[24]

1. ጥርጣሬዉ በአመክንዮ የተደገፈ መሆን አለበት (It is rational, i.e. it can be logically justified) ከአስረጅነት ሚዛኑ ስያሜ ብንነሳ እንኳን ጥርጣሬያችን ምክንያታዊ ሊሆን እንደሚገባ በቀላሉ ለመረዳት እንችላለን። ጥርጣሬዉ ተራ ጥርጣሬ ሊሆን አይገባም፤ ጥርጣሬዉ ሊረጋገጥ ከተፈለገዉ ፍሬ-ነገር ጋር ያለዉ ቁርኝት በአግባቡ መፈተሽ አለበት። በአሳማኝ ምክንያት የተረጋገጠ ጥርጣሬ እንዲሆንም ይጠበቃል።
2. ተጨባጭ የሆነ ጥርጣሬ (It is concrete, i.e. it is found on the facts of the case) ጥርጣሬዉ በርግጥም እንዲረጋገጥ ከተፈለገዉ ፍሬ-ነገር የተገኘ ተጨባጭ የሆነ ጥርጣሬ መሆን አለበት። ለክርክር ምክንያት ከሆነዉ ፍሬ-ነገር ዉጪ ወይም ለክርክር ምክንያት ከሆነዉ ፍሬ-ነገር ጋር የማይገናኙ ጉዳዮችን ወይም ማስረጃዎችን እየመዘገን ለጥርጣሬ ምክንያት መፍጠር አይቻልም።
3. ጥርጣሬዉ ከጉዳዩ ዳራ እና ተፈጥሯዊ ባህሪ ጋር ቁርኝት ሊኖረዉ ይገባል (It is relative i.e. the determination of reasonableness has been made with the scope and the nature of the case. (investigation requirement) ከወንጀሉ ተፈጥሯዊ ባህሪ ጋር ቁርኝት ያለዉ ጥርጣሬ የዚሁ የምክንያታዊ ጥርጣሬ አካል ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ይኸዉም በመዝገብ በምርመራ ሂደት ዉስጥ ከምናየዉ የጉዳዩ ተፈጥሯዊ ባህሪ አንጻር የሚዳሰስ ነዉ። የማስረጃ አመዛዘናችንን ይበልጥ የምናጠራበት እና የንጹሀንን መቀጣት የምናስወግድበት ተቀዳሚ ስራ ነዉ። ከወንጀሉ ክብደት እና ቅለት፣ ከተከሳሹ ባህሪ፣ ከወንጀሉ አይነት እና ከወንጀሉ አፈጻጸም አንጻር የሚታይ ነዉ።[25] ይህ ማለት በጉዳዮች መካከል የተለያየ የምዘና ልኬት እንጠቀማለን ማለት አይደለም። ኢ-ፍትሀዊ በሆነ መንገድ የሚወሰኑ ዉሳኔዎች ከቀላሎቹ ወንጀሎች ይልቅ ከባዶቹ ወንጀሎች ህመማቸዉ የከበደ ነዉ የሚል መነሻም የለዉም። መሰመር ያለበት ጉዳይ የትኛዉም ንጹህ ሰዉ ከወንጀል ቅጣት የተጠበቀ መሆን አለበት የሚለዉ ነዉ። ስለሆነም በመዝገብ ምርመራ ሂደት ያሉትን አንዳንድ ነጥቦች ፍርድ ቤቱ በጥልቀት መመልከቱ ለምንከተለዉ

[23] ዝኒ ከማሁ ገጽ 4
[24] Christian Diesen ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 4፣ ገጽ 170
[25] ዝኒ ከማሁ ገጽ 3

ጥፋተኝነትን የማስረዳት መመዘኛ በቂ እና የጠራ ማስረጃ እንድናገኝ የሚያስችለን በመሆኑ ይበል የሚያሰኝ ዘዴ ነዉ።[26]

በወንጀል የፍትህ ስርዓት ተፈላጊዉ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ "ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ" ማስረዳት እንዲሆን ያስፈለገበት ምክንያት በወንጀል የተከሰሰ ሰዉ ድርጊቱን መፈጸሙ በሚገባ እስኪረጋገጥ ነጻ ሆኖ የመቆጠር መብት አለዉ የሚለዉን ትልቅ መብት ለመጠበቅ እንደሆነ መመዘኛዉን የሚጠቀሙ አገራት እንደ ምክንያት የሚያቀርቡት ነዉ።

በሌላ በኩል በኮንትኔንታል የህግ ስርዓት (Civil law legal system) ተከታይ አገሮች በወንጀል እና በፍትሐብሄር ጉዳዮች መካካል ጥፋተኝነትን/ሀላፊነትን የማስረዳት ደረጃ ልዩነት አይታይም። ይህም ማለት የተፈለገዉ ፍሬ-ነገር መኖሩን ወይም አለመኖሩን ለማረጋገጥ የሚጠቀመዉ የማስረጃ ደረጃ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይም በሆነ ከፍተኛ የማስረጃ ደረጃ ሳይሆን በተሻለ ደረጃ ያስረዳ በሚልም የወረደ መመዘኛም ዝቅ ሳይል ግልጽ እና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ (Clear and convincing evidence standard of proof) ተፈላጊዉ ፍሬ-ነገር ስለመኖሩ ወይም አለመኖሩ ሊያስረዳ ይገባል በሚል የተቀረጸ ነዉ።[27]

2.2. ግልጽ እና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ

ግልጽ እና አሳማኝ ማስረጃን በተለያየ መንገድ ሲገለጽ ማየት የተለመደ ነዉ። ከእነዚህም ዉስጥ ግልጽ፣ የሚያረካ እና አሳማኝ፣ ግልጽ እና የሚያረካ፣ ግልጽ እና አሳማኝ፣ በጣም የሚያረካ፣ ጠንካራ እና አሳማኝ፣ ግልጽ፣ የማያጠራጥር እና አሳማኝ፣ የታወቀ እና የማያጠራጥር፣ መሰረታዊ ጥርጣሬ ስላለመኖሩ የማያሻማ እና በጥልቀት አስበን በየትኛዉም ምክንያታዊ ሰዉ አስተሳሰብ የማያወላዉል ጠንካራ ዉሳኔ ላይ የሚያደርሰን እና ወዘተ[28] እየተባለ ይገለጻል።

---

[26] ዝኒ ክማሁ

[27] Adrian Keane and paul Mckeown, The Modern Law of Evidence, 9th Edition, Oxfored University press, Great Clarendon Street, Oxford United Kingdom, 2012, p.105. < https://global.oup.com/academic/product/the-modern-law-of-evidence-9780198811855 >

[28] Robin Meadow, Clear and Convincing Evidence: How Much Is Enough?, may 1999, p.116. <https://www.gmsr.com/wp-content/uploads/2016/06/Clear-and-Convincing-Evidence-How-Much-is-Enough.pdf >

Robin Meadow is a partner in the Beverly Hills law firm of Greines, Martin, Stein & Richland, which specializes in appellate practice. Mr. Meadow, who is a member of the California Academy of Appellate Lawyers, was cocounsel for the plaintiff in Mattco Forge, Inc. u Arthur Young & Co, (1997) 52 Cal.App.4th 820, 60 Cal.Rptr.2d 780, which unequivocally approved BAJI No. 2.62!s definition of clear and convincing evidence.

በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኝነትን ከምናስረዳባቸዉ መለኪያዎች መካከል ግልጽና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ጥፋተኝነትን ማረጋገጥ አነዱ ነዉ። ግልጽና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ በኮንትኔንታል የህግ ስርዓት ተከታይ ሀገራት ዋነኛዉ መመዘኛ ነዉ። ይሁንና ግልጽ እና አሳማኝ ማስረጃ ማለት ምን ማለት ነዉ? የሚለዉን ስንመለከት በተለያዩ ጊዜያት ወጥ ያልሆኑ እና የተለያዩ ትርጉሞች ተሰጥተዉ እናገኛለን።

ከትርጉሞቹ መካከል የመጀመሪያዉ ግልጽና አሳማኝ ማስረጃ ማለት በአእምሯችን ጠንካራ እምነት እንድናሳድር የሚያደርገን ወይም በክርክር ሂደት ጥፋተኝነቱን በእዉነት የሚያረጋግጥ እንደሆነ የሚነግረን ነዉ። ስለሆነም ማስረጃዉ በጣም ግልጽ፣ ቀጥተኛ፣ በጥራቱ ሚዛን የሚደፋ እና ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ጉዳይ በግልጽ የሚያስረዳና የጥፋተኝነት ዉሳኔዉ ትክክል ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ የሚያደርሰን መሆን አለበት። ግልጽ እና አሳማኝ ማስረጃ ስንል የጥርጣሬ ወይም የጉዳዩን የመፈጸም እድልን መሰረት አድርጎ የሚለካ ሳይሆን የማስረጃዉን ግልጽነት እና አሳማኝነት ብቻ የሚታይበት እንደሆነ አድርጎ ሲተረጎምም ይታያል።[29]

ሁለተኛዉ ትርጉም ደግሞ ግልጽ እና አሳማኝ ማስረጃ ማለት መሰረታዊ ጥርጣሬ ስላለመኖሩ የማያሻማ እና በጥልቀት አስበን በየትኛዉም ምክንያታዊ ሰዉ አስተሳሰብ የማያወላዉል ጠንካራ ዉሳኔ ላይ የሚያደርሰን መሆኑን የሚገልጽ ነዉ።[30] ማስረጃዉ ግልጽ እና አሳማኝ ነዉ የሚባለዉ መሰረታዊ ወይም ጽኑ ጥርጣሬ ሳይኖር ትክክለኛ ዉሳኔ ላይ እንድንደርስ ካደረገን ነዉ።[31] እዚህ ላይ የሚነሳዉ መሰረታዊ (ጠንካራ) ጥርጣሬ (substantial doubt) ማለት ምን ማለት ነዉ? የሚለዉ ሲሆን ይህም ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ የማስረዳት ደረጃ ጋር የተቀራረበ እና ለህግ ተርጓሚዎች አደናጋሪ አገላለጽ መሆኑ ነዉ።

ግልጽ እና አሳማኝ ማስረጃ ማለት ከቀረበዉ ተቃራኒ ማስረጃ ጋር ሲወዳደር እንዲረጋገጥ የተፈለገዉ ጉዳይ የመፈጸሙን እድል የማሳመን አቅም ያለዉ ነዉ። እንዲህ አይነት ማስረጃ በተሻለ ሁኔታ በማሳመን ሀላፊነትን ከማስረዳት (Preponderance of evidence) ከፍ ያለ ሚዛን

---

[29]Burden of Proof-Clear and Convincing evidence (Approved 4/1988; Revised 8/2011) p.1. <https://www.njcourts.gov/attorneys/assets/civilcharges/1.19.pdf?cacheID=GCYZeg9 >

[30] Robin Meadow ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 28፣ ገጽ 117

[31] Whitney Durand, Clear and Convincing Evidence: A Broadly Applicable Standard of Proof, published in the Tennessee Trial Lawyer. Copy right 2005, p.1. <http://www.lawchatta.com/files/Clear%20and%20Convincing%20Evidence.pdf >

ያለዉ ነዉ።[32] ፕሮፌሰር ማክቤን የተባሉ ምሁር ግልጽ እና አሳማኝ ማስረጃ ማለት ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ በማስረዳት እና በተሻለ ሁኔታ ማሳመን መካከል ያለ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ነዉ[33] ሲሉ ይተረጉሙታል። በሌላ በኩል ደግሞ ግልጽ እና አሳማኝ በሆነ ማስረጃ የማሳመን ደረጃ በተሻለ ሁኔታ ከማሳመን ይለቅ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ወደ ማስረዳት ደረጃ የተጠጋ ስርዓት ነዉ የሚሉም አሉ።[34]

ግልጽ እና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ የተለያየ ትርጉም የተሠጠዉ መሆኑን ከላይ አይተናል። ነገር ግን ብዙዎቹ ትርጉሞች ከሌሎች ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ጋር ተቀራራቢ አገላለጽን በመጠቀም ተተርጉመዉ የምናገኛቸዉ ናቸዉ። ይህ ደግሞ ለህግ ተርጓሚዎች ማደናገርን የሚፈጥር እና ከሌሎች የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ለመለየት አዳጋች ይሆናል። ስለሆነም ምንም እንኳ ትርጉሙ በሌሎች ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ላይ የተንጠለጠለ ቢሆንም ፕሮፌሰር ማክቤን የሰጡት ትርጉም ሚዛን የሚደፋ እንደሆነ ጸሀፊዉ ያምናል።

2.3. ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብት

ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብት በወንጀል ፍትህ ስርዓት መሰረታዊ ከሚባሉ መርሆዎች ዉስጥ አንዱ ነዉ።[35] ይህ መብት ክርስቶስ ከመወለዱ 350 (ሶስት መቶ ሀምሳ) ዓመት በፊት በሮማዉያን ህግ ዉስጥ ተካቶ እንደነበር *Corpus Juris Civilis* በተባለ የሮማዉያን የህግ ስብስብ ዉስጥ ተካቶ ይገኛል። የአሁኑን ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብት ለመጠበቅ ሲባል በጀስትንያን ህግ መሰረት ዐቃቤ ህግ አንድን የወንጀል ጉዳይ ጥያቄ በማያስነሳ እና በትክክል ክስና ማስረጃዉን የማስረዳት ሀለፊነት ነበረበት።[36]

በአንግሎ አሜሪካን እና በኮንትኔታል የህግ ስርዓት ዉስጥ ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብት ታሪካዊ መነሻ እና እድገቱ የተለያየ ነዉ። የኮንትኔታል የህግ ስርዓት መነሻዉ ከብዙ በጥቂቱ ከጥንታዊ ሮማ ሲሆን ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብትንም

[32] ዝኒ ከማሁ

[33] McBaine, Burden of Proof Presumptions, University of California Law Review. 1954, volume 13, pp. 18-20 <https://opendocs.ids.ac.uk/opendocs/bitstream/handle>

[34] Robin Meadow ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 28፣ ገጽ 118

[35] Ferry de Jong and Leonie van Lent, The Presumption of Innocence as a Counterfactual Principle, online, Utrecht Law review, Volume 12, Issue 1, January 2016 p. 32. <http://doi.org/10.18352/ulr>

[36] Justinian Code, Book IV, Title 19, Clauses 23 and 25. George W. Hopper Law Library, College of Law, University of Wyoming. www.uwyo.edu/lawlib/blume-justinian/ajc-edition-1/book-4.html (24.4.2017)

የወሰዱት ከጥንታዊ ሮማ ህግ ነዉ። ከ1207 ዓ.ም በፊት የሮማዉያን ህግ ቦታዉን ለሀይማኖታዊ ህግ ለቆ ነበር። በዚህም ጊዜ በህግ፣ በማስረጃ እና በመርህ ከመመራት ይልቅ ኋላ ቀር፣ አደገኛ እና አሳማሚ በሆነ ነገር በመፈተን (trial by ordeal) ጥፋተኝነትን የማረጋገጥ ስርዓትን ይከተሉ ነበር። በ1207 ዓ.ም ይህ ሀይማኖታዊ ህግ በአለማዊ ህግ መልሶ እንዲተካ ከመደረጉም ባሻገር የወንጀል ክርክሮች በማስረጃ እና በመርህ እየተመሩ ጥፋተኝነት የሚገመት ሳይሆን የሚረጋገጥ እንዲሆን ተደርጓል።[37]

የአንግሎ አሜሪካን (common law) የህግ ስርዓት የተወሰደዉ በመካካለኛዉ ዘመን (500-1500 A.D) መጀመሪያ አካባቢ ከእንግሊዝ እንደሆነ ይታወቃል። በዚህን ጊዜ የህግ ጉዳይ የሚመራዉም ሆነ ስልጣንን ጠቅልሎ የያዘዉ ንጉሱ ነበር። ነገር ግን ግዛቱን እያስፋፋ ሲሄድ የህግ መርሆዎችን እየተከተሉ አዳዲስ ክርክሮችን መፍትሄ እንዲሰጡ ስልጣኑን ለፍርድ ቤቶች ሰጠ። የአንግሎ አሜሪካን የህግ ስርዓት ትንሽ የማይባሉ ተሞክሮዎችን እና መርሆዎችን ከጥንታዊ ሮማ ህግ የወሰደ ቢሆንም ይበልጥ የህግ ስርዓቱ የዳበረዉ የቀደሙ ዉሳኔዎችን እንደ ህግ በመጠቀም እና በዳበረ ነገር ግን ያልተጻፈ ህግ መርሆዎችን መሰረት አድርጎ ነዉ።[38] በአንግሎ አሜሪካን የህግ ስርዓት ታሪክ ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመቆጠር መብትን በግልጽ በዉሳኔዉ ያሳየዉ በ1305 ዓ.ም የሞተዉ ጆሃንስ ሞናቸስ (Johannes Monachus) የተባለ ሀይማኖታዊ የህግ ባለሙያ ሲሆን ዊሊያም ብላክስቶን (William Blackstone) በ1758 ዓ.ም ባሳተመዉ እና የእንግሊዝ ህጎችን የሚተቹ ታዋቂ የጽሁፎቹ ስብስብ ዉስጥ ንጹህንን መቅጣት የከፋዉ ኢ-ፍትሀዊነት መሆኑን በመግለጽ አንድ በወንጀል የተከሰሰ ሰዉ የተባለዉን ወንጀል ፈጽሟል ለማለት እርግጠኞች መሆን እንዳለብን ጽኑ ፍላጎቱ መሆኑን ጠቁሟል።[39]

በ18ኛዉ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብትን ማንሳት እየተለመደ መምጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ተከላካይ ጠበቆች በክርክር ጥፋተኝነትን የማረጋገጥ አስፈላጊነት ጋር በማስተሳሰር ማንሳት የጀመሩበትም ጊዜ ነበር። ከዚያም ዳኞች በሂደት እየተቀበሉት እና እዉቅና እየሰጡት መጡ። በአንግሎ አሜሪካን እና በኮንትኔታል የህግ ስርዓት ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመቆጠር መብት መነሻ እና እድገት የተለያየ ቢሆንም በ18ኛዉ

[37] Stumer A. The Presumption of Innocence – Evidential and Human Rights Perspectives. Oxford, Hart Publishing 2010, p. 2 <https://pdfs.semanticscholar.org/b153/07cb6c8016f6a617ce008bd9f679e5589ea2.pdf >
[38] The Robbins Collection. The Common Law and Civil Law Traditions. School of Law, University of California at Berkeley (24.4.2017)
<https://www.law.berkeley.edu/wpcontent/uploads/2017/11/CommonLawCivilLawTraditions.pdf>
[39] Justinian Code ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 36፣ ገጽ 4

ክፍለ ዘመን መጨረሻ በሁለቱም የህግ ስርዓቶች እውቅናን ያገኘ ሲሆን አሁን ያለዉን ተቀባይነት ያገኘዉ ግን በ20ኛዉ ክፍለ ዘመን መሰረታዊ የሰብዓዊ መብቶች ፍልስፍና ብቅ ማለቱን ተከትሎ ነዉ።[40]

ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብት ከመሰረታዊ የሰብዓዊ መብቶች ዉስጥ አንዱ ሲሆን ይኸዉም በተለያዩ ዓለም አቀፍ እና አህጉር አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች፣ የቃል ኪዳን ሰነዶች እንዲሁም የጋራ ስምምነቶች ተካተዉ እናገኛቸዋለን። ከእነዚህም ዓለም አቀፍ ሰነዶች መካከል በ1940 ዓ.ም የወጣዉ የሰብዓዊ መብቶች ዓለም አቀፋዊ መግለጫ አንዱ ሲሆን በአንቀጽ 11(1) ስርም "በወንጀል የተከሰሰ ማንኛዉም ሰዉ ክሱ በይፋ በሚሰማበት ግልጽ ፍርድ ቤት በህግ መሰረት የመከላከል መብቱ ተጠብቆለት ጥፋተኛ መሆኑ እስኪረጋገጥ ድረስ እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት አለዉ።" የሚል ነዉ። ተመሳሳይ በሚባል አገላለጽ 169 ሀገራት የፈረሙት እና ያጸደቁት የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ 14(2) በበኩሉ "ማንኛዉም በወንጀል ጥፋት የተከሰሰ ሰዉ በህጉ መሰረት ጥፋተኝነቱ እስከሚረጋገጥ ድረስ እንደ ንጹህ ሰዉ የመቆጠር መብት አለዉ" በማለት ይደነግጋል። ሌላዉ እና ሶስተኛዉ ሰነድ የአፍሪካ የሰዎችና የህዝቦች መብቶች ቻርተር ሲሆን "ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ወይም የፍርድ አካል ጥፋተኛ መሆኑ እስኪረጋገጥ ድረስ ጥፋተኛ ተደርጎ ያለመወሰድ መብት" መኖሩን አንቀጽ 7(1)(ለ) ይገልጻል።

ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብት ያለ አድሎ ወይም በፍትሀዊነት ለመዳኘት አይነተኛ መርህ ነዉ። በፍትሀዊነት መዳኘት ደግሞ የህግ የበላይነትን ከምናረጋግጥባቸዉ መንገዶች አንዱ ነዉ። ስለሆነም ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብት የህግ የበላይነትን ለማስከበር ከፍ ያለ አስተዋጽዖ አለዉ።[41]

ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብት በዓለም አቀፍ ሰነዶች፣ አህጉር አቀፍ ስምምነቶች እና በተለያዩ አገራት ህገ መንግስታትና ተጨማሪ ህጎች ስር እንዲካተት እና በተለይም ከሁለተኛዉ የዓለም ጦርነት በኋላ የተለየ ትኩረት እንዲሰጠዉ ያደረጉት የራሱ ምክንያቶች አሉ። ከእነዚህም ምክንያቶች መካከል ዋናዉ ንጹሀንን መጠበቅ ነዉ። ይህ ማለት አንድ በወንጀል የተጠረጠረ ሰዉ ጥፋተኝነቱን ሊያስረዳ በሚችል ደረጃ እስካልተመሰከረበት ድረስ

[40] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 5

[41] Lautenbach, G. The Concept of the Rule of Law and the European Court of Human Rights. Oxford, Oxford University Press 2013, p. 126. https://global.oup.com/academic/covers/pop-up/9780199671199

እንደ ነጻ ሰዉ ይገመታል ወይም ይታሰባል። ስለሆነም ነጻነቱ በህግ ግምት የሚወሰድበት እንጅ ተጠርጣሪዉ ማስረጃ አቅርቦ የሚያረጋግጠዉ አይደለም። በተቃራኒዉ አቃቤ ህግ ተጠርጣሪዉ ወንጀል ተግባር ላይ ስለመሳተፉ ጥፋተኝነቱን ሊያስረዳ በሚችል ደረጃ የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት። ተጠርጣሪ ወንጀሉን አለመፈጸሙ ሲረጋገጥ ብቻ ሳይሆን በእርግጥም ወንጀሉ በተጠርጣሪዉ ተፈጽሞ ነገር ግን በቂ ማስረጃ ባለመኖሩ ወይም አቃቤ ህግ በቂ ክርክር ሳያደርግ በመቅረቱ በሚፈጠረዉ ጥርጣሬ ተጠቃሚ መሆን ያለበት ተጠርጣሪዉ ነዉ።[42]

ስለሆነም አቃቤ ህግ ይህንን "ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብት" ለማስተባበል ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል የሚያቋቁሙ ነገሮችን ጥፋተኝነቱን ሊያስረዳ በሚችል ደረጃ ማስረዳት እና ተከሳሹ ጥፋተኛ መሆኑን ማሳመን ይጠበቅበታል። እንዲሁም በወንጀል ጉዳይ በማስረጃ ምዘና ወቅት በሚፈጸም ስህተት ምክንያት ወንጀሉን ያልፈጸመ ሰዉ በስህተት ወይም ባልተረጋገጠ ማስረጃ ምክንያት ጥፋተኛ እንዳይሆን መከላከል ነጻ ሆኖ የመገመት ተቀዳሚ አላማ ነዉ። በአንግሎ አሜሪካ የህግ ስርዓት መሰረት ወንጀል ያልፈጸመ እና ነጻ ሊሆን የሚገባዉ ሰዉ በስህተት ጥፋተኛ ማድረግ የሚያስከትለዉ ኪሳራ ጥፋተኛ ሊባል የነበረን ሰዉ በስህተት በነጻ ማሰናበት ከሚያስከትለዉ ኪሳራ ሲነጻጸር እጅግ የከፋ ተደርጎ ይወሰዳል።[43]

የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ 14(2) ስር "ማንኛዉም በወንጀል ጥፋት የተከሰሰ ሰዉ በህጉ መሰረት ጥፋተኝነቱ እስከሚረጋገጥ ድረስ እንደ ንጹህ ሰዉ የመቆጠር መብት አለዉ" የሚለዉን መሰረታዊ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌ የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ኮሚቴ ትንታኔ ሰጥቶበት እናገኘዋለን። ይኸዉም ማንኛዉም በወንጀል ጥፋት የተከሰሰ ሰዉ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ እስካልተረጋገጠበት ድረስ ነጻ ሆኖ ይቆጠራል ሲል ሙህራዊ ትንታኔ ሰጥቷል።[44]

> The presumption of innocence, which is fundamental to the protection of human rights, imposes on the prosecution the burden of proving the charge, guarantees that no guilt can be presumed until the charge has been proved beyond reasonable doubt …

[42] Pamela R. Ferguson, The presumption of innocence and its role in the criminal process. Criminal Law Forum 2016, pp 131-158 and PP 133-134

[43] Jon O. Newman ክላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9፣ ገጽ 3

[44] UN Human Rights Committee (2007), General comment no. 32, Article 14, Right to equality before courts and tribunals and to fair trial, (23 August 2007, CCPR/C/GC/32), para. 30

በተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ኮሚቴ ትንታኔ መሰረትም ነጻ ሆኖ የመገመት መብትን ይበልጥ ጥበቃ ለመስጠት የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ መሆን እንዳለበት በግልጽ ተቀምጧል። ነገር ግን የተባበሩት መንግስታት ሰብአዊ መብት ኮሚቴ ነጻ ሆኖ የመገመት መብት ላይ የሰጡት ትንታኔ አስገዳጅ ሳይሆን የህግ ሙህራን አስተያየት ተደርጎ መወሰድ ያለበት ነዉ። ስለሆነም ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃን እንደ መመዘኛ ለመዉሰድ ከአስተያየት የዘለለ በቂ የህግ ድጋፍ ሊኖረን ይገባል።

ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብት ስነ-ስርዓታዊ መብት ሲሆን ይህ መብት ከትችት እና ከክርክር ነጻ ባይሆንም ብዙም አከራካሪ ያልሆኑ ሰብዓዊ መብቶች ከሚባሉት ዉስጥ የሚመደብ ነዉ። አሁን አሁን ጭራቸዉ የማይያዙ ወንጀሎች መበራከት፣ ክርክሩን በአንድ በኩል ከሚመራዉ አቃቤ ህግ ይልቅ ተጠርጣሪዎች ማስረጃዎችን የማግኘትም የማጥፋትም አቅም ያላቸዉ መሆን፣ ከትላልቅ ወንጀሎች ጀርባ የመንግስት ባለስልጣናት መኖር፣ አንዳንድ ወንጀሎች በባህሪያቸዉ አቃቤ ህግ በማስረጃ የማይደርስባቸዉ መሆናቸዉ እና እነዚሁ ወንጀሎች ህዝብን እና አገርን በእጅጉ የሚጎዱ ከመሆናቸዉ ጋር ተያይዞ ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብት ፈተናዎች እየተጋረጡበት ይገኛል። ስለሆነም አንዳንድ ወንጀሎች ተከሳሽ ነጻነቱን እንዲያረጋግጥ የማስረዳት ሸክም የሚጥሉም ጭምር እየሆኑ መጥተዋል።[45]

ሌላኛዉ ችግር ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብት በሰብዓዊ መብት ሰነዶች በግልጽ ትርጉም አለመሰጠቱ ነዉ። በዚህም የተነሳ ይህ መብት ተፈጻሚ የሚሆነዉ በፍርድ ቤት ክርክር ጊዜ ብቻ እንደሆነ ተደርጎ በጠባቡ ሲተረጎም በሌላ በኩል ደግሞ ተጠርጣሪዉ ከፍርድ ቤት ክርክር በፊት መታሰሩ የማይቀር ከሆነ እና ከፍርድ ቤት ክርክር በኋላ ተጠርጣሪዉ በተለያየ ምክንያት የሚለቀቅ ከሆነ ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብት እንዳለዉ ተደርጎ በሰፊዉ ይተረጎማል።[46] በእርግጥ ይህ መብት ተለጥጦ መተርጎሙ የተደነገገበትን

[45] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ፣ ፍትህ ሚኒስቴር፣ የካቲት 25/2003 ዓ.ም፣ ገጽ 33
ማንም ሰዉ በወንጀል ጥፋተኛ ሊሰኝ የሚችለዉ ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት አቃቤ ህግ በሚያቀርበዉ ማስረጃ ጥፋተኝነቱ ሲረጋገጥ ብቻ ነዉ። ይሁንና ተከሳሹ በህገ መንግስታዊ ስርዓቱ ላይ አደጋ ማድረስ፣ እንደ ሽብርተኝነት፣ ሙስና ወይም በተደራጁ ቡድኖች የሚፈጸሙ ወንጀሎች የተከሰሰ እንደሆነ ዐቃቤ ህግ የማስረዳት ሸክሙን ወደ ተከሳሽ ለማዛወር የሚችል መሰረታዊ ፍራ-ነገሮችን ካስረዳ የማስረዳት ሸክም ወደ ተከሳሹ ሊዛወር የሚችልበትን ስርዓት የሚመለከቱ ድንጋጌዎች አግባብ ባላቸዉ ህጎች ዉስጥ እንደሚካተቱ ይገልጻል።
[46] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 42፣ ገጽ 142

ዓላማ ይስታል ብለዉ የሚከራከሩ እንዳሉም ሊዘነጋ አይገባም።[47] ሆኖም ግን ምንም እንኳን ትንታኔዉ ወይም አስተያየቱ አስገዳጅ ባይሆንም ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ኮሚቴ ነጻ ሆኖ ስለመገመት መብት በሰጠዉ ትንታኔ (General comment) ከፍርድ ቤት ክርክር በፊት የታሰረ እንደሆነ፣ የዋስትና መብቱ በመነፈጉ እና በፍትሐብሄር ጉዳይ ሀላፊ መባሉ ነጻ ሆኖ የመገመት መብቱን እንደማያሳጣዉ ይገልጻል።[48]

ሌላዉ ነጻ ሆኖ የመገመት መብት በሚል የተገለጸዉ ትልቅ መብት ከመነሻዉ አገላለጹ ትክክል አይደለም የሚሉ ጸሀፍት አሉ። ምክንያታቸዉን ሲያስቀምጡ በወንጀል ተጠርጥረዉ የተያዙ እና የተከሰሱ ሰዎች ፍርድ ቤት ቀርበዉ የጥፋተኝነት ዉሳኔ የሚተላለፍባቸዉ በነጻ ከሚለቀቁት በቁጥር በእጅጉ የበለጡ በመሆናቸዉ አንድ ሰዉ ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ሲከሰስ ለመቀጣት የቀረበ መሆኑን አመላካች ነዉ። ስለሆነም አንድ በወንጀል የተከሰሰ ሰዉ የመጨረሻ ዉሳኔ በሚሰጠዉ ፍርድ ቤት በህጉ መሰረት «ጥፋተኛ እስካልተባለ ድረስ ነጻ ሆኖ ይገመታል» ከማለት ይልቅ ነጻ ሆኖ ይታሰባል (assume that he is innocence) የሚለዉ አባባል ይበልጥ ገላጭ ነዉ[49]ይላሉ። በተጨማሪም አንድን ግለሰብ ፖሊስ በወንጀል ተሳትፈሀል ብሎ ወደ ፖሊስ እንዲቀርብ ሲያዘዉ ይህ ግለሰብ ወንጀል ስለመፈጸሙ ፖሊስ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ኖሮት ነዉ። ስለሆነም ይህ ግለሰብ በነጻ ሰዉ እና በጥፋተኛ መካከል ያለ ተጠርጣሪ በመሆኑ ወደ ኋላ ተመልሶ ነጻ ሆኖ የመቆጠር መብት ሳይሆን ወደፊት በማስረጃ ሊረጋገጥ ከሚገባዉ ጥፋተኝነት የመጠበቅ መብት ይኖረዋል። ስለዚህ አንድ በወንጀል የተጠረጠረ ሰዉ እንደ ንጹህ የመቆጠር ሳይሆን እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት ነዉ ያለዉ። የጸሀፊዉም እምነትም ከላይ ከተገለጸዉ የተለየ አይደለም።

3. በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ በኢትዮጵያ ህግ

በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ስርዓት አሁን በስራ ላይ ያሉ ህጎች ጥፋተኝነትን ለማስረዳት መጠቀም ያለብንን መመዘኛ በግልጽ አስቀምጠዋል ለማለት የሚያስደፍር አይደለም። በእርግጥ አሁን ያሉን የማስረጃ ህጎች በአንድ ላይ ያልተጠቃለሉ እና ተበታትነዉ የሚገኙ በመሆናቸዉ እነዚህኑ ህጎች ከተለያዩ ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸዉ እንዲሁም አስገዳጅ ከሆኑ ዓለም አቀፍ

[47] Weigend, T. There is Only One Presumption of Innocence. Netherlands Journal of Legal Philosophy, 2013. 3 (42), p 193 and 196.
[48] ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 43
[49] William F. Fox Jr.The "Presumption of Innocence" as Constitutional Doctrine, 28 Cath. U. L. Rev. 253 (1979). Available at: http://scholarship.law.edu/lawreview/vol28/iss2/3

ስምምነቶች ጋር አጣምሮ በማየት ጥፋተኝነትን ለማስረዳት መጠቀም ያለብንን መመዘኛ መለየት ተገቢ ይሆናል።

3.1. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት

በ1987 ዓ.ም የወጣዉ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ለፍትሀዊ የወንጀል ክርክር ሂደት መነሻ የሆነዉን የማስረዳት ሸክም ያለበትን አካል ለመወሰን የምንጠቀምበትን እና በብዙ የአንግሎ አሜሪካን የህግ ስርዓት ተከታይ አገራት ህጎች ዙሪያ የሚጽፉ ጸሀፍት ጥፋተኝነትን ለማስረዳት የምንጠቀምበትን መመዘኛ ለመወሰን ዋነኛ ነጥብ ነዉ ብለዉ የሚያስቡትን ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብት በአንቀጽ 20(3) ስር በግልጽ አካቶ እናገኘዋለን።[50]

ሆኖም ግን ይህ ድንጋጌ በአማረኛዉ እና በእንግሊዝኛዉ ቅጅ መካከል የአገላለጽ ልዩነት ይስተዋልበታል። የኢፌድሪ ህገ መንግስት አማረኛዉ ቅጅ አንቀጽ 20(3) በወንጀል የተከሰሰ ሰዉ በፍርድ ሂደት ባለበት ጊዜ "እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት" አለዉ የሚል ሲሆን የእንግሊዝኛዉ ቅጅ በበኩሉ በወንጀል ተከሶ በክርክር ሂደት ያለ ሰዉ በህግ መሰረት ጥፋተኛ እስከሚባል ድረስ እንደ ንጹህ ይቆጠራል (During procceding accused person have the right to be presumed innocent until proved guilty according to law) ይላል። በሁለቱ ቅጅዎች መካከል ልዩነት መኖሩ ግልጽ ነዉ። በአማርኛዉ እና በእንግሊዝኛው ቅጅ መካከል ልዩነት ባለ ጊዜ የአማርኛዉ ቅጅ የመጨረሻ ህጋዊ እዉቅና ያለዉ መሆኑ በዚሁ ህገ መንግስት አንቀጽ 106 ስር ተገልጾ እናገኘዋለን። ይኸዉ የአማርኛ ቅጅ ከሰብዓዊ መብቶች አለም አቀፋዊ መግለጫ በአንቀጽ 11(1) ስር ከተገለጸዉ "በወንጀል የተከሰሰ ማንኛዉም ሰዉ ክሱ በይፋ በሚሰማበት ግልጽ ፍርድ ቤት በህግ መሰረት የመከላከል መብቱ ተጠብቆለት ጥፋተኛ መሆኑ እስኪረጋገጥ ድረስ እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት አለዉ።" ከሚለዉ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን 169 ሀገራት የፈረሙት እና ያጸደቁት የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ 14(2) በበኩሉ "ማንኛዉም በወንጀል ጥፋት የተከሰሰ ሰዉ በህጉ መሰረት ጥፋተኝነቱ እስከሚረጋገጥ ድረስ እንደ ንጹህ ሰዉ የመቆጠር መብት አለዉ" በማለት ይደነግጋል። ሌላዉ እና ሶስተኛዉ ሰነድ የአፍሪካ የሰዎችና የህዝቦች መብቶች ቻርተር ሲሆን "ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ወይም

[50] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞካራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት፣ 1987 ዓ.ም፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 1/1987፣ አንደኛ አመት ቁጥር አንድ፣ አንቀጽ 20(3)

የፍርድ አካል ጥፋተኛ መሆኑ እስኪረጋገጥ ድረስ ጥፋተኛ ተደርጎ ያለመወሰድ መብት" መኖሩን አንቀጽ 7(1)(ለ) ይገልጻል።

ነገር ግን ይህ የህገ መንግስት ድንጋጌ ብቻውን በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኝነትን ለማስረዳት መጠቀም ያለብን ደረጃ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ብቻ ስለመሆኑ አመላካች አይደለም። ምክንያቱም ዓለም ላይ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ የማስረዳት ደረጃ በተጨማሪ የኮንትኔታል (civil law) የህግ ስርዓት ተከታይ ሀገራት ግልጽ እና አሳማኝ ማስረጃን የወንጀል ጥፋተኝነትን ለማስረዳት የሚጠቀሙበት መመዘኛ በመሆኑ እና ከሁለቱም ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ጀርባ ያለዉ ትልቅ መብት ነጻ ሆኖ የመቆጠር ወይም የመታሰብ መብት በመሆኑ ነዉ።[51]

3.2. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ

ኢትዮጵያ እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ ስለወንጀል ፍትህ ስርዓት አስተዳደሩ የሚገልጽም ሆነ የወደፊት አቅጣጫን የሚያስቀምጥ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ አልነበራትም። የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ.ም በፍትህ ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ ስራ ላይ ዋለ። በዚህ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ ዉስጥ የወንጀል ጥፋተኝነትን ለማስረዳት ስለምንጠቀምበት ደረጃ በግልጽ የሚያመላክት ነገር የለም። ነገር ግን ከፖሊስ ምርመራቸዉ ተጠናቀዉ የሚመጡ የወንጀል መዛግብቶች ላይ ዐቃቤ ህግ የክስ ይመስረት ዉሳኔ ሲወስን ጉዳዩ ፍርድ ቤት ቢቀርብ ተከሳሹን ጥፋተኛ ሊያደርገዉ የሚችል በቂ ማስረጃ መኖሩን ማረጋገጥ እንዳለበት በግልጽ ተመላክቶ እናገኘዋለን።[52] በተቃራኒዉ የክስ አያስመሰርትም ዉሳኔ ሲወሰንም ተጠርጣሪዉን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚችል በቂ የሆነ ማስረጃ የሌለ መሆኑን ማረጋገጥ የሚጠበቅበት መሆኑንም እንደዚሁ። ይህ ማለት በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 42(1)(ሀ) እንደተገለጸዉ ለወንጀል ክስ ምስረታ አቃቤ ህግ የሚጠቀምበትን የማስረጃ ምዘና ደረጃን የሚያመላክት እንጅ ፍርድ ቤት ተጠርጣሪን ጥፋተኛ ለማለት የሚጠቀምበትን ደረጃ አመላካች አይደለም። ስለሆነም የኢትዮጵያ የወንጀል

[51] Worku Yaze Wodage, Burdens of Proof, Presumptions and Standards of Proof in Criminal Cases, Mizan Law Review, Vol. 8, No.1, September 2014, pp. 265-269, http://dx.doi.org/10.4314/mlr.v8i1.8
ረዳት ፕሮፌሰር ወርቁ ያዜ ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብት ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃን የምንወስንበት ትልቅ መርህ እንደሆነ፣ የኢትዮጵያ የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ማስረዳት መሆኑን እና ይህም የማስረዳት ደረጃ ንጹሀንን ለመጠበቅ እና በተከራካሪ ወገኖች መካከል ያለዉን አቅም ሚዛን የሚጠብቅ እንደሆነ ይገልጻል።

[52] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ፣ ፍትህ ሚኒስቴር፣ የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ.ም፣ ገጽ 13 እና 14

ፍትህ ፖሊሲ የወንጀል ጥፋተኝነትን ለማስረዳት መጠቀም ስላለብን ደረጃ ምንም የሚለዉ ነገር የለም።

3.3. የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ

አንድ ተከሳሽ ተጠርጥሮ በተከሰሰበት ጉዳይ የክሱን የታወቀ ፍሬ-ነገር ስለመኖሩ ወይም አለመኖሩን የማስረዳት ሸክም የተጣለበት ተከራካሪ ወገን ባስረዳዉ ልክ ፍርድ ቤቱ ዉሳኔ ማሳረፍ እንዳለበት ይታወቃል። ይህንንም ዉሳኔ ፍርድ ቤቱ ሲወስን በ1954 ዓ.ም የወጣዉን የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 141፣ 134(1)፣ 149(1) እና 149(2) መሰረት ይሆናል።[53]

ልዩ ሁኔታዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በመርህ ደረጃ ፍትህ ጠያቂ አካል በክሱ መሰረት ፍሬ-ነገሩን የማስረዳት ሸክም እና ፍርድ ቤቱን የማሳመን ግዴታ አለበት። ስለሆነም ዐቃቤ ህግ የጉዳዩን ፍሬ-ነገር ባቀረባቸዉ ማስረጃዎች ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገዉ ሆኖ ባልተገኘ ጊዜ እና "ማስረጃዉ በቂ ሆኖ ሳያገኘዉ የቀረ እንደሆነ ተከሳሹ በነጻ እንዲለቀቅ ፍርድ ቤቱ ያዛል"።[54] ነገር ግን የቀረቡት ማስረጃዎች በቂ ሆነዉ የተገኙ እንደሆነ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 142 መሰረት ፍርድ ቤቱ በተከሳሽ ላይ የይከላከል ዉሳኔ አስተላልፎ የተከሳሽን መከላከያ ማስረጃ አስቀርቦ እንዲያሰማ እንደሚያደርገዉ ሁለቱን ድንጋጌዎች አጣምሮ በማየት በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ ይከላከል ብሎ ከወሰነ በኋላ ግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ በአቃቤ ህግ የቀረበዉን ማስረጃ ተከሳሹ በበቂ ሁኔታ ባስተባበለ ጊዜ "ተከሳሹ ጥፋተኛ አይደለም" ብሎ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 149(2) መሰረት በነጻ ያሰናብተዋል። ነገር ግን በቀረቡት ማስረጃዎች መሰረት ተከሳሹ ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከሰማ በኋላ አስተማሪ ነዉ ያለዉን ቅጣት ፍርድ ቤቱ በተከሳሹ ላይ ያስተላልፋል።

ጠቅለል አድርገን ስናየዉ ተከሳሽ መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚታዘዘዉ ተከሳሽ "በቀረበበት ማስረጃ መሰረት የተመሰከረበት" ከሆነ ነዉ። ተከሳሽ በቀረበበት ማስረጃ መሰረት

[53] የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ፣ 1954 ዓ.ም፣ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 1/1954 በተለይ የወጣ፣ ሰላሳ አንደኛ አመት፣ አንቀጽ 141፣ 134(1)፣ 149 (1) እና 149(2)
[54] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 141

ተመስክሮበታል የሚባለዉ ደግሞ የዐቃቤ ህግ ማስረጃ "ተከሳሽን ጥፋተኛ የሚያደርገዉ" ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ነዉ። ማስረጃዉ ተከሳሹን ጥፋተኛ ሊያደርገዉ የሚችለዉ ደግሞ በፍርድ ቤቱ ምልከታ ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማድረግ "በቂ ሆኖ" ሲገኝ ነዉ። ከዚህ የምንረዳዉ ማስረጃዉ ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማድረግ በቂ ነዉ አይደለም የሚለዉን የሚወስነዉ ፍርድ ቤቱ መሆኑን ነዉ። ተከሳሽን ጥፋተኛ ለማሰኘት "በቂ ማስረጃ" እንደሚያስፈልግ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህጋችን በግልጽ ይደነግጋል። በቂ ማስረጃ ሲባል ምን ማለት እንደሆነ በስነ-ስርዓት ህጉ ዉስጥ አመላካች ነገር የለም። በቂ ሲባል ስለ የትኛዉ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ በቂነት እንደሚያወራ ግልጽ አይደለም። ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ማስረዳት? ወይስ ግልጽና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ማስረዳት? የሚለዉ ትልቁ ጥያቄ ነዉ።

የአገራችን ዳኞች የህግ ትምህርት ቤቶቻችን ዉጤቶች ናቸዉ። የመጀመሪዉ የኢትዮጵያ የህግ ትምህርት ቤትን ጨምሮ የህግ መምህራን ይመጡ የነበሩት ከአንግሎ አሜሪካን የህግ ስርዓት ተከታይ አገራት ስለነበር ዳኞቻችን የአንግሎ አሜሪካን የወንጀል ጥፋተኝነት መመዘኛ የሆነዉን ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ የአስረጅነት ሚዛን በመርህ ደረጃ የሚቀበሉ ናቸዉ። በዚህም የተነሳ ፍርድ ቤቶቻችን ዐቃቤ ህግ በሚያቀርበዉ ማስረጃ ተከሳሹ ወንጀሉን ስለመፈጸሙ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ማስረዳት እንደሚገባዉ ያምናሉ።[55]

ሆኖም ግን የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 141 ላይ የተደነገገዉ "በቂ ማስረጃ" የሚለዉ አገላለጽ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ የአስረጅነት መመዘኛ ለማመላከት ነዉ ብሎ ለማደማደም የሚቻል አይደለም። ምክንያቱም የተከሳሽን መከላከያ ማስረጃ መጠበቅ ሳያስፈልግ የከሳሽ ወይም የዐቃቤ ህግ ማስረጃዎች የወንጀል ጥፋተኝነትን ለማስረዳት በተቀመጠዉ ደረጃ ልክ አላስረዱም ማለት እንጅ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ

---

[55] የኢፌዴሪ የማስረጃ ህግ (ሁለተኛ ረቂቅ) ማብራሪያ፣ ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5፣ ገጽ 14
-ከመብራቱ ይማም ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፣ የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ፣ የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ፣ ጥር 21 ቀን 2011 ዓ.ም
-ከደሴ ከተማ አስተዳደር ወረዳ ፍርድ ቤት ደኞች ጋር የተደረገ የቡድን ተኮር ዉይይት፣ የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ፣ ጥር 30 ቀን 2011 ዓ.ም
-ከጎንደር ከተማ አስተዳደር ወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች ጋር የተደረገ የቡድን ተኮር ዉይይት፣ የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ፣ ታህሳስ 15 ቀን 2011 ዓ.ም
Simeneh Kiros Assefa, The principle of the Presumption of Innocence and its challenges in the Ethiopian Criminal process, Mizan Law Review Vol. 6 No.2, December 2012, p. 293&294, http://dx.doi.org/10.4314/mlr.v6i2.4
አቶ ስሜነህ ኪሮስ በጻፉት አጭር ጥናታዊ ጽሁፍ The Courts in Ethiopia were applying the "beyond a reasonable doubt" standard of proof in criminal matters which was presumably introduced by British judges and government advisors. It appears that the proof beyond a reasonable doubt principle has been taken to heart, and our judges were consistently using the words when they enter judgment whether it is acquittal or conviction of defendant. **በሚል አስቀምጠዋል።**

አንቀጽ 141 በዉስጠ ታዋቂነት ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ የማስረዳት ደረጃን አካቷል ሊያስብል የሚችል ህጋዊ መሰረት የለንም።

ማንኛዉም በወንጀል ድርጊት ተጠርጥሮ የተከሰሰ ሰዉ የመጨረሻዉ የጥፋተኝነት ዉሳኔ የመጨረሻ ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት እስካልተወሰነበት ድረስ እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት እንዳለዉ በ1987 ዓ.ም የወጣዉ የኢፌድሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 20(3) በግልጽ የሚያስቀምጥ ቢሆንም ይህ ማለት ግን የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 141 ስር በግልጽ የተቀመጠዉን የአስረጅነት መመዘኛ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ የአስረጅነት መመዘኛን ለማለት ተፈልጎ ነዉ ብለን እንድንተረጉም ምክንያት አይሆንም።

የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 141 የተወሰደዉ ከማላያን የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ (section) 180 ሲሆን ይኸዉም ከየትኛዉም ምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ማስረዳት እስካልተቻለ ድረስ በወንጀል የተጠረጠረን ሰዉ ጥፋተኛ ነዉ ለማለት አይቻልም (The evidence produced is not strong enough to warrant a conviction, and only evidence beyond all reasonable doubt is of that nature.)[56] ሲል ይገልጸዋል። ይህ የሚያሳየዉ አንድ ተጠርጥሮ የተከሰሰ ሰዉ ጥፋተኛ ለመባል "ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ" ብቻ ሳይሆን "ከየትኛዉም ምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ" ማስረዳትን የሚጠይቅ መሆኑን ነዉ። ምን አልባትም ይህ መመዘኛ ከጥርጣሬ በጸዳ ማስረዳትን (beyond The shadow of doubt) አመላካች ይመስላል። ስለሆነም የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 141 ስር የተካተተዉ ጥፋተኝነትን የማስረዳት መመዘኛ አሁን ባለዉ ይዘት "ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ" ምዘናን በእርግጥ ለማሳየት ሲባል የተቀረጸ ነዉ ብሎ ለማደማደም የሚቻል አይደለም። የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 141 "ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ" የማስረዳት ደረጃን ማካተት ቢፈልግ ኖሮ እንደ ማላያን ህግ በግልጽ ማስቀመጥ በተቻለ ነበር።

3.4. ረቂቁ የኢትዮጵያ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ

በ1954 ዓ.ም የወጣዉን የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ ለማሻሻል በረቂቅ ላይ ያለዉ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 428 የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ግልጽ እና አሳማኝ ማስረጃ (Clear and convincing evidence) መሆን እንዳለበት በግልጽ ይደነግጋል።[57]

[56] Stanley Z Fisher, Ethiopian criminal procedure,a source book, 1969, p.311

[57] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ ረቂቅ፣ አንቀጽ 428

ስለሆነም ከመጀመሪያዉም ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸዉ አለም አቀፍ ድንጋጌዎች፣ ከ1987ቱ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 20(3) እና የአንግሎ አሜሪካን የህግ ስርዓት ተከታይ ሀገራት መሰረት በማድረግ በወንጀል ጉዳዮች አስረጅነት መመዘኛ ዙሪያ በተጻፉ ጽሁፎች መነሻነት በወንጀል ድርጊት ተጠርጥሮ የተከሰሰ ሰዉ ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት እስካልተወሰነበት ድረስ እንደ ንጹህ የመቆጠር ወይም የመታሰብ መብትን ዓላማ ለመጠበቅ በመሻት በሰፊዉ ስራ ላይ ያለዉን እና ይበልጥ ተቀባይ የሆነዉን የወንጀል ጉዳዮች የአስረጅነት መመዘኛ ወደ እኛ አገር አምጥተን ተግባራዊ ለማድረግ እየሞከርን ቢሆንም ምንም ዓይነት የህግ ድጋፍ የለንም። ግልጽ እና አሳማኝ ማስረጃ (Clear and convincing evidence) መመዘኛም ቢሆን እንደ ንጹህ የመቆጠር መብትን ዓላማ በምንም መስፈርት የሚሸረሽርም ሆነ የሚቃረን አይደለም።

በ1954 ዓ.ም የወጣዉን የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ ለማሻሻል በረቂቅ ደረጃ ያለዉ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ዉይይት ያልተደረገበት እና የህግ አዉጪዉን ሀሳብ የማያሳይ ቢሆንም ረቂቁ በተደጋጋሚ ጊዜ በተለያዩ የህግ ሙህራኖች (ባለሙያዎች) ዉይይት ተደርጎበት አሁን ያለዉን ቅርጽ ይዞ ሊጸድቅ መሆኑ ሲታሰብ በርግጥም የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 141 ስር ያለዉ "በቂ ማስረጃ" ግልጽ እና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ወሳይ እንደነበረ መገንዘብ ይቻላል።

4. በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ አፈጻጸም በአማራ ክልል

እንደሚታወቀዉ የኢትዮጵያ መሰረታዊ ህጎች የተወሰዱት የኮንትኔንታል ስርዓት ከሚከተሉ ሀገሮች በተለይም ከፈረንሳይ በመሆኑ በህጎቻችን ዉስጥ ተበታትነዉ የሚገኙ የማስረጃ ህግ ድንጋጌዎች ይገኛሉ። በተቃራኒዉ የፍትሐብሄር እና የወንጀል ስነ-ስርዓት ህጎቻችን የተወሰዱት የአንግሎ አሜሪካን የህግ ስርዓት ከሚከተሉ ሀገሮች በመሆኑ በእነዚህ ህጎች ዉስጥ የአንግሎ አሜሪካን የማስረጃ አቀራረብ እና ጥፋተኝነት ወይም ሀላፊነትን የምናስረዳበት ስርዓት ላለፉት አምሳና ከዚያ በላይ አመታት ፍርድ ቤቶቻችን እንዳለ ተቀብለዉ ሲሰሩበት ቆይተዋል።[58]

ንጹሀንን መቅጣትም ሆነ አጥፊዎችን በነጻ መልቀቅ ሁለቱም የወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ ተቀዳሚ አላማዎች አይደሉም። የማይበረታቱ ስህተቶችም ናቸዉ። ስለሆነም ንጹሀኖች ያለአግባብ በወንጀል ጉዳዮች እንዳይከሰሱ፤ ተከሰዉም በተገኙ ጊዜ በወንጀል ጥፋተኛ ተብለዉ

[58] የኢፌዴሪ የማስረጃ ህግ (ሁለተኛ ረቂቅ) ማብራሪያ፣ ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5፣ ገጽ 15

እንዳይቀጡ እና አላግባብ ከገቡበት ክርክር ሂደት ውስጥ በተዘረጋው የህግ ስርዓት መሰረት ሳይዘገዩ እንዲወጡ ማድረግ በየደረጃው ያሉ የፍትህ ተቋማት ድርሻ ነው።[59] ምንም እንኳን ንጹሀንን መቅጣትም ሆነ አጥፊዎችን በነጻ መልቀቅ ሁለቱም መጥፎዎች ቢሆኑም ሁለቱም በአንድ ጊዜ የሚከሰቱ ሲሆን ከበጣም መጥፎው መጥፎውን መምረጥ ስላለብን አንድ ንጹህ ከሚቀጣ ብዙ ወንጀለኞች ቢያመልጡ ይሻላል የሚለው ሀሳብ በሂደት እየላቀ መጥቶ መርህ ሆኗል።

አሁን ባለው አፈጻጸም ብዙዎቹ የአማራ ክልል ፍርድ ቤት ዳኞች የወንጀል የጥፋተኝነት መመዘኛ ስርዓት "ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ" እንደሆነ የሚያምኑ ናቸው። ምንም እንኳን እምነታቸው ይህ ይሁን እንጅ የተሰሩት መዛግብት ግን "ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ" ጥፋተኝነትን የማስረዳት መመዘኛ አመላካች አይደሉም።[60] ከዚህም ባሻገር ምን ዓይነት መመዘኛ ፍርድ ቤቱ እንደተጠቀመ ከውሳኔዎቹ መረዳትም አይቻልም።

አሁን ባለው አሰራር ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡላቸውን የወንጀል ጉዳዮች ከመረመሩ እና አሉ የተባሉ ማስረጃዎችን ከሰሙ በኋላ ተከሳሽ እንደ ክሱ የተመሰከረበት ስለሆነ እና በመከላከያ ማስረጃ ያላስተባበለ በመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 149(1) መሰረት ጥፋተኛ ብለናል፣ ተከሳሽ እንደ ክሱ ያልተመሰከረበት ስለሆነ መከላከል ሚያስፈልገው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 141 መሰረት ከክሱ በነጻ ተሰናብቷል እንዲሁም ተከሳሽ እንደ ክሱ የተመሰከረበት ቢሆንም ባቀረባቸው የመከላከያ ማስረጃዎች ያስተባበለ በመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 149(2) መሰረት ከክሱ በነጻ እንዲሰናበት ወስነናል በማለት ተቀራራቢ በሚባል አገላለጽ የሚወሰኑ ውሳኔዎች በቁጥር ቀላል አይደሉም።[61] በእርግጥ የሚቀርቡ ማስረጃዎች ማስረጃ ተብለው በፍርድ ቤት ለመመዘን ዝቅተኛውን የማስረጃነት መመዘኛ ማሟላታቸው እና ለክርክር ምክንያት የሆነው ፍሬ-ነገር መኖሩ ወይም አለመኖሩ

[59] Jon O. Newman ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9፣ ገጽ 3

[60] -በጎንደር ከተማ ወረዳ ዐቃቤ ህግ እና ሽመክት አገኘሁ መካከል የተደረገ ክርክር፣ የጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት፣ 2011 ዓ.ም፣ የፍርድ ቤት ወንጀል መዝገብ ቁጥር 0218619፣ ገጽ 9 እና 10
-በጎንደር ከተማ ወረዳ ዐቃቤ ህግ እና ፈይር (ታደሰ) ካሳው መካከል የተደረገ ክርክር፣ የጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት፣ 2011 ዓ.ም፣ የፍርድ ቤት ወንጀል መዝገብ ቁጥር 0219000፣ ገጽ 12
-በጎንደር ከተማ ወረዳ ዐቃቤ ህግ እና አህመድ ሰይድ መካከል የተደረገ ክርክር፣ የጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት፣ 2011 ዓ.ም፣ የፍርድ ቤት ወንጀል መዝገብ ቁጥር 0218219፣ ገጽ 19
-በጎንደር ከተማ ወረዳ ዐቃቤ ህግ እና አለልኝ ምህረት መካከል የተደረገ ክርክር፣ የጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት፣ 2011 ዓ.ም፣ የፍርድ ቤት ወንጀል መዝገብ ቁጥር 0219125፣ ገጽ 8
-በጎንደር ከተማ ወረዳ ዐቃቤ ህግ እና እነ ሚኪያስ ዳኘው (ሁለት ሰዎች) መካከል የተደረገ ክርክር፣ የጎንደር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት፣ 2011 ዓ.ም፣ የፍርድ ቤት ወንጀል መዝገብ ቁጥር 0218941፣ ገጽ 7

[61] ዝኒ ከማሁ

ሲረጋገጥ ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ እንደሚያስተላልፉ ይታወቃል። ነገር ግን ዋናዉ ጥያቄ በምን ያህል ደረጃ ጉዳዩ መኖሩ ወይም አለመኖሩ ተረጋገጠ የሚለዉ ነዉ።

ስለሆነም ፍርድ ቤቶቻችን በቃላቸዉ የሚነግሩን ጥፋተኝነትን ለማስረዳት የሚጠቀሙት መመዘኛ እና ህጋችንም ላይ ሆነ በተግባር መዛግብት ላይ በዉሳኔ የሚገለጸዉ የጥፋተኝነት መመዘኛ የተደበላለቀ እና ወጥነት የሌለዉ መሆኑን መረዳት ይቻላል።[62] በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ መሰረት ወጥ የሆነ ጥፋተኝነትን የምንመዝንበት ስርዓት ማስቀመጥ ካልቻልን ፍትሀዊነትን ልናሰፍን አንችልም። ፍትሀዊነት የሌለበት የፍትህ ስርዓት ዉስጥ ደግሞ በምንም መለኪያ በህግ የበላይነት የሚያምን ማህበረሰብ መፍጠር አይቻልም። በህግ የበላይነት የሚያምን ዜጋ መፍጠር ደግሞ የአንድ የዘመናዊ ህግ የመጨረሻ ግብ ጭምር ነዉ።

በአገራችን ከቴክኒክ ይልቅ ታክቲክ ማስረጃ ላይ የተጣበቅን መሆናችን፣ የማህበረሰባችን ማህበራዊ ግንኙነት እየላላ መምጣት፣ የወንጀል መርማሪዎች የዕዉቀት እና ክህሎት ማነስ፣ የተደራጀ የማስረጃ ህግ አለመኖር፣ የአጥፊዎች የወንጀል አፈጻጸም እየረቀቀ መምጣት፣ ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት መብዛት እና የመሳሰሉ ምክንያቶች ማስረጃዎችን የማስረዳት አቅም የሚፈታተኑ መሆናቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህን ሁሉ ችግር አልፈዉ የሚመጡ ማስረጃዎችም በአግባቡ እየተመዘኑ አይደሉም።[63]

ዳኞች ሊረጋገጥ የተፈለገዉን ጉዳይ ለማስረዳት የቀረቡትን ማስረጃዎች አግባብነት፣ ተቀባይነት እና ተአማኒነት በመመዘን ተከሳሽን ጥፋተኛ ነዉ አይደለም በሚል ይወስናሉ።[64] በእርግጥ እነዚህ መመዘኛዎች አንድ ማስረጃ እንደ ማስረጃ ተይዞ ይመዘን ወይስ ይዉደቅ የሚለዉን የምንወስንባቸዉ መለኪያዎች ናቸዉ። ነገር ግን እነዚህን መመዘኛዎች ተሟልተዉ ማስረጃዎቹን እንደ ማስረጃ ከተቀበልን በኋላ ለክርክር የቀረበዉን ፍሬ-ነገር በምን ያህል ደረጃ ማስረጃዉ አስረዳ የሚለዉ መሰረታዊዉ ጉዳይ ነዉ።

ስለሆነም የቀረበዉ ማስረጃ ለክርክር የቀረበዉን ፍሬ-ነገር ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ አስረድቷልን? ወይም ግልጽ እና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ተረጋግጧልን? ወይስ በተሻለ ሁኔታ በማሳመን ነዉ ያስረዳዉ የሚለዉን ለመወሰን ፍርድ ቤቱ እንደ ማስረጃ የተቀበላቸዉ

[62] ዝኒ ከማሁ
[63] ዝኒ ከማሁ
[64] የኢፌድሪ የማስረጃ ህግ (ሁለተኛ ረቂቅ) ማብራሪያ፣ ከላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5፣ ገጽ 15

ማስረጃዎች ከጉዳዩ ጋር ምን ያህል ትስስር አላቸዉ የሚለዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ምን ያህል የነጠሩ ማስረጃዎች ናቸዉ የሚለዉ የፍርድ ቤቶቻችን ትኩረት ሊሆን ይገባል፡፡

በመጨረሻም ከላይ ያየናቸዉ ጠቅላላ ነጥቦች ሲጨመቁ የኢትዮጵያ የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ግልጽ እና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ጥፋተኝነትን ማስረዳት መሆኑን እንረዳለን፡፡[65]

[65] Hanna Arayaselassie Zemichael, The Standard of Proof in Criminal Proceedings: the Threshold to Prove Guilt under Ethiopian Law, MIZAN LAW REVIEW, Vol. 8, No.1 September 2014, pp.91-102, http://dx.doi.org/10.4314/mlr.v8i1.3
ሀና አረዓያስላሴ በተቃራኒዉ ነጻ ሆኖ የመገመት መብት ላይ የሰብዓዊ መብት ኮሚቴ የሰጠዉን ትንታኔ (General comment 32)፣ የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 141 የተወሰደዉ ከማለያን ህግ (section 180) በቀጥታ በመሆኑ እና ነጻ ሆኖ የመገመት ህገ መንግስታዊ መብት የወንጀል ጥፋተኝነትን ለማስረዳት የምንጠቀምበት ደረጃ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ መሆኑን የምናረጋግጥባቸዉ ምክንያቶች መሆናቸዉን ትገልጻለች፡፡

ማጠቃለያ

የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ እንደየአገሩ የህግ ስርዓት እና እንደየጉዳዩ አይነት ይለያያል። የአንግሎ አሜሪካን (Common Law) የህግ ስርዓት ተከታይ አገሮች ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃን (Beyond reasonable doubt standard) ተግባራዊ ሲያደርጉ የኮንትኔታል (Civil Law) የህግ ስርዓት ተከታይ አገሮች ግልጽ እና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ (Clear and convincing evidence standard of proof) በመመዘኛነት ይጠቀማሉ።

በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ስርዓት ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ በግልጽ ተደንግጎ አይገኝም። የ1987ቱ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 20(3) ስለ ነጻ ሆኖ የመገመት ወይም የመታሰብ መብት ማዉራቱ ጥፋተኝነትን የማስረዳት መመዘኛችን ነጻ ሆኖ የመገመት መብትን እንዳይሸራርፍ ጠቋሚ እንጅ የትኛዉ የጥፋተኝነት ማስረጃ ለወንጀል ጉዳዮች ተገቢ ነዉ የሚለዉን አመላካች አይደለም።

የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 141 ዐቃቤ ህግ ጉዳዩን ለማስረዳት ያቀረበዉ ማስረጃ በቂ ሆኖ ባልተገኘ ጊዜ ተከሳሹ ከክሱ በነጻ እንዲሰናበት ፍርድ ቤቱ እንደሚያዝ ይገልጻል። የዚህ ድንጋጌ ሙሉ ሀሳብም የተከሳሽን መከላከያ ማስረጃ መጠበቅ ሳያስፈልግ የከሳሽ ወይም የዐቃቤ ህግ ማስረጃዎች ጥፋተኝነትን ለማስረዳት በተቀመጠዉ ደረጃ ልክ አላስረዱም ማለት እንጅ የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 141 በዉስጠ ታዋቂነት ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ የማስረዳት ደረጃን አካቷል ሊያስብል የሚችል ህጋዊ መሰረት የለንም።

የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 141 የተወሰደዉ ከማላያን የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ (section) 180 ሲሆን ይኸዉም ከየትኛዉም ምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ማስረዳት እስካልተቻለ ድረስ በወንጀል የተጠረጠረ ሰዉ ጥፋተኛ ነዉ ለማለት አይቻልም ሲል ይገልጸዋል። ይህ የሚያሳየዉ አንድ ተጠርጥሮ የተከሰሰ ሰዉ ጥፋተኛ ለመባል "ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ" ብቻ ሳይሆን "ከየትኛዉም ምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ" ማስረዳትን የሚጠይቅ መሆኑን ነዉ። ስለሆነም የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 141 ስር የተካተተዉ ጥፋተኝነትን የማስረዳት መመዘኛ አሁን ባለዉ ይዘት "ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ" ምዘናን ለማሳየት የተቀረጸ ነዉ ለማለት የሚያስችል አይደለም።

የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 141 “ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ” የማስረዳት ደረጃን ማካተት ቢፈልግ ኖሮ እንደ ማላያን ህግ በግልጽ ማስቀመጥ በተቻለ ነበር፡፡

የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ኮሚቴ እንደ ንጹህ የመቆጠር መብት ላይ ጠቅላላ ትንታኔ 32 (General Comment 32) የተሰጠ ሲሆን ይኸውም በአጭር አገላለጽ ማንኛውም በወንጀል ጥፋት የተከሰሰ ሰዉ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ እስካልተረጋገጠበት ድረስ ነጻ ሆኖ ይቆጠራል ሲል ህጋዊ አስተያየት ሰጥቷል፡፡ በተባበሩት መንግስታት ሰብአዊ መብት ኮሚቴ ትንታኔ መሰረትም ነጻ ሆኖ የመገመት መብትን ይበልጥ ጥበቃ ለመስጠት የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ መሆን እንዳለበት በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ነገር ግን የተባበሩት መንግስታት ሰብአዊ መብት ኮሚቴ ነጻ ሆኖ የመገመት መብት ላይ የሰጡት ትንታኔ አስገዳጅ ሳይሆን የህግ ሙህራን አስተያየት ነዉ፡፡ ስለሆነም ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃን እንደ መመዘኛ ለመዉሰድ ከአስተያየት የዘለለ በቂ የህግ ድጋፍ ሊኖረን ይገባል፡፡

የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግን ለማሻሻል በረቂቅ ላይ ያለዉ የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 428 የወንጀል ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ግልጽ እና አሳማኝ ማስረጃ (Clear and convincing evidence) መሆን እንዳለበት በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ምንም እንኳን ረቂቁ ስነ-ስርዓት ህግ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ዉይይት ያልተደረገበት እና የህግ አዉጪዉን ሀሳብ የማያሳይ ቢሆንም ረቂቁ በተደጋጋሚ ጊዜ በተለያዩ የህግ ሙህራን (ባለሙያዎች) ዉይይት ተደርጎበት አሁን ያለዉን ቅርጽ ይዞ ሊጸድቅ መሆኑ ሲታሰብ በእርግጥም የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀጽ 141 ስር ያለዉ “በቂ ማስረጃ” ግልጽ እና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ ወካይ እንደነበረ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ለማጠቃለል ያህልም በአገራችን ከቴክኒክ ይልቅ ታክቲክ ማስረጃ ላይ የተጣበቅን መሆናችን፣ የማህበረሰባችን ማህበራዊ ግንኙነት እየላላ መምጣት፣ የወንጀል መርማሪዎች የዕዉቀት እና ክህሎት ማነስ፣ የተደራጀ የማስረጃ ህግ አለመኖር፣ የአጥፊዎች የወንጀል አፈጻጸም እየረቀቀ መምጣት፣ ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት መብዛት እና የመሳሰሉ ምክንያቶችን ከላይ ከተገለጹት ነጥቦች ጋር አጣምረን ስናይ ኢትዮጵያ ግልጽ እና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ ጥፋተኝነትን የማስረዳት ደረጃ በላይ መመዘኛ ይኖራታል ብሎ ማደማደም የሚቻል አይደለም፡፡

ሀሠተኛ ምስክርነት በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ

በይበልጣል ይመር*

አህፅሮተ ይዘት

በአብዛኛዉ የእምነት አስተምህሮቶች ሀሰት መናገር ወይም በሀሠት መመስከር የተወገዘና የተከለከል ተግባር ነዉ። በሀሰት መመስከር በሰዎች መካከል የሚኖረዉን ሰላማዊ መስተጋብር የሚያበላሽ ድርጊት ከመሆኑም ባሻገር ጥፋተኛ በጥፋቱ እንዲይጠየቅ ወይም ንፁሃን ያለጥፋታቸዉ እንዲቀጡ የሚዳርግ አደገኛ በህዝብና በመንግስት ላይ የሚፈፀም ወንጀል ነዉ። የዳኝነት ሂደትን እና የመጨረሻ ግቡን በማሳት ረገድ እንደሀሰተኛ ምስክርነት ወይም ማስረጃ የሚያሰፈራ ጉዳይ የለም። በመሆኑም አገራት ሀሰተኛ ምስክርነትን ወይም ሀሰተኛ ማስረጃ መስጠትን ወይም ማቅረብን የሚከለክል ህግ አላቸዉ። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግም ከአንቀጽ 452-456 ሀሠተኛ ቃል ወይም ምስክርነትን የሚሰጡ ሰዎችን ለመቅጣት ያለሙ ድንጋጌዎች ተካተዋል። ይሁንና እነዚህ ድንጋጌዎች ከዳኝነትና ከዳኝነት ነክነት አካላት ዉጭ የሚሰጡ የሀሰት ቃልን ወይም ምስክርነትን ለመቅጣት አያስችሉም። በመሆኑም የእነዚህን ድንጋጌዎች ይዘት ከሌሎች አገራት ተመሳሳይ ድንጋጌዎች ጋር በማነፃፀር ክፍተቶችን ለመለየትና የተሟላ ይዘት ባላቸዉ ድንጋጌዎች እንዲሻሻሉ የሚያስችል ምክረ ሀሳብ ለማቅርብ ይህ ፅሁፍ ተዘጋጅቷል። ፅሁፉ የተጠቀመዉ የጥናት አይነት ዶክትሪናል (Doctrinal) ነዉ።

---

*(LLB, LLM, በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና ህግ ምርምር ኢንስቲትዩት ተመራማሪ e mail yibeeyimer@yahoo.com)

1. መግቢያ

መፅሃፍ ቅዱስና[1] ቅዱስ ቁርዓን[2] ሀሠት መናገር ወይም በሀሠት መመስከር የተወገዙና የተከለከሉ ተግባራት እንደሆኑ በግልፅ ደንግገዉ ይገኛሉ፡፡ በአብዛኛዉ ማህበረሰቡ ዉስጥ ዉሸት ግብረ ገብነት የጎደለዉ እና ተቀባይነት የሌለዉ ድርጊት ነዉ[3]፡፡ ከዚህ ከፍ ሲል የህግ ተጠያቂነት ያስከትላል፡፡ በኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ጉዳይ ተከራካሪ የሆነ ወገን እዉነቱን ይዞ እንዲከራከር ሲጠበቅበት በወንጀል ጉዳይ ደግሞ ሰዉን በሀሰት መወንጀል ወይም መክሰስ የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላል[4]፡፡ እንደ አሜሪካ ባሉ አገራት በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰ ሰዉ ጭምር በተከሰሰበት ጉዳይ ሀሰት ቢናገር የተከሰሰበትን ጉዳይ መካዱ ነዉ ወይስ ሀሰተኛ ቃል መስጠቱ ነዉ የሚለዉ ነጥብ ለክርክር የተጋለጠ ነዉ፡፡ ይህም በአንድ በኩል በወንጀል የተከሰሰ ወይም የተጠረጠረ ሰዉ እዉነት ብቻ እንዲናገር ወይም በሀሰት እንዳይከራከር ገደብ የለበትም የሚል ክርክር ነበር፡፡[5] ለዚህ ክርክር መነሻዉ ሀሰት በመናገርና በመካድ መካከል ያለዉን ልዩነት በተግባር ለመለየት አስቸጋሪ በመሆኑ ነዉ፡፡ የወንጀል ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ ለሚቀርብለት ምርመራ ወይም ጥያቄ እዉነቱን ክዶ መከራከር እንደ መብት ሊታይ ይገባል የሚለዉን ሃሳብ የሚደግፉት የመካድን ጉዳይ ከመፅሃፍ ቅዱስ ታሪክ ጋር ያገናኙታል፡፡

---

[1] መፅሀፍ ቅዱስ (80 አሃዱ)፣ እሌአ 1962፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ ለምሳሌ ያህል በመፅሃፍ ቅዱስ ኦሪት ዘፀዓት ምዕራፍ 20÷16 ላይ በባልንጀራህ ላይ በሀሠት አትመስክር፣ ኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 19÷18-19"... ፈራጆቹም አጥብቀው ይመረምራሉ:: ያም ምስክር በወንድሙ ላይ በሃሠት ተናግሮ ቢገኝ በወንድሙ ላይ ያደርገው ዘንድ ያሠበውን በእርሡ ላይ ትመልሱበታላችሁ በሚል ሃሠተኛ ምስክር ላይ ቅጣት እንደሚያስፈልግና የቅጣቱም መጠን ይነግረናል፡፡ ኦሪት ዘሌላውያን 19÷11 አትስረቁ፣ አትካዱም፣ ከእናንተም እርስ በርሣችሁ በሃሠት አትነጋገሩ፡፡

[2] ቅዱስ ቁርዓን፣ የአማርኛ ትርጉም (ተርጓሚ ሸህ ሰዒድ መሃመድ ሳድቅ እና ሃጂ መሃመድ ሀቢብ/ ከህዳግ ማስታዎሻ ጋር የተተረጎመ) 2003፣ 1ኛ እትም፣ ነጃሺ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ፣ ሡረቱ አል አህዛብ 33÷70 ላይ እናንተ ያመናችሁ ሆይ፣ አላህን ፍሩ፣ ትክክለኛንም ንግግር ተናገሩ፡፡ ሡርቱ አል ተውባህ 9÷119 ላይ እናንተ ያመናችሁ ሆይ አላህን ፍሩ ከእውነተኞቹም ጋር ሁኑ፡፡ ሡረቱ አልኒሣ 4÷135 ላይ እናንተ ያመናችሁ ሆይ በትክክል (ፍትህ) ቀዋሚዎች በነፍሶቻችሁ ወይም በወላጆችና በቅርብ ዘመዶች ላይ ቢሆንም እንኳ ለአላህ መስካሪዎች ሁኑ፡፡ ሀብታም ወይም ድሃ ቢሆን አላህ በእነርሡ (ከእናንተ) ይበልጥ ተገቢ ነው፡፡ እንዳታዳሉም ዝንባሌን አትከተሉ ብታጣምሙም ወይም መመስከርን ብትተው አላህ በምትሠሩት ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነው፡፡

[3] Stuart P. Green, Lying, Misleading and Falsely Denying: How Moral Concepts Inform the Law of Perjury, Fraud, and False Statements,2001, Hastings Law Journal,page,163 http://respository.uchasting.edu/cgi/veiwcontent/cgi?article=3462&content...law...

[4] የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ 1958፣ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 3፣ ድንጋጌ ቁጥር 52 በብርሃንና ሰላም በቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አንቀፅ 92 አቤቱታ አቅራቢዉ የሚያቀርበዉ አቤቱታ እዉነት መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ-ሥርዓት 1954፣ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 1፣ በተለየ ቁጥር 1 በብርሃንና ሰላም በቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አንቀፅ 18 በተመሳሳይ የሀሰት ክስ ወይም ሀሰት የክስ አቤቱታ ያቀረበ ሰዉ በወንጀል ሊከሰስ እንደሚገባ ያሳያል፡፡ ይህም አንድን ሰዉ በሀሰት መወንጀል ወይም መክሰስ የወንጀል ቅጣት ሊያስከትል እንደሚችል ያስገነዝበናል፡፡

[5] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 3 ገፅ 198

በመካድ ራስን መከላከል የተጀመረው በጥንት ጊዜ ነዉ። መፅሃፍ ቅዱስ እንደሚነግረን "እግዚአብሔርም ቃየንን አለው፦ ወንድምህ አቤል ወዴት ነውን እርሱም አላውቅም የወንድሜ ጠባቂው እኔ ነኝን አለው።[6] በዚህ ታሪክ ላይ እግዚአብሔር በሚያደርገው ምርመራ ቃየንን ራሱን እየተከላከለ ነው። ይህ የመጀመሪያው የክህደት መከላከያ (Exculpatory no defense) ነዉ። አለበለዚያ ራስን በወንጀል ተጠያቂ ማድረግ ይሆናል የሚል ጠንከር ያለ ክርክር እየተደረገበት ይገኛል።[7] በተከሻሽ ወይም በተጠርጣሪ ላይ ክስ ከነማስረጃዉ አቅርቦ የማስረዳት ግዴታ የከሳሽ ነዉ። በመሆኑም ተከሻሽ ወይም ተጠርጣሪ ራሱን በወንጀል ተጠያቂ ያለማድረግ መብቱ ሊከበር ይገባል የሚል ነዉ።[8]

በሌላ በኩል በወንጀል ጉዳይ ላይ ተከሳሽም ይሁን ተጠርጣሪ ሃሰት መናገር አይገባዉም። በአሁኑ ሠዓት በመካድ ራስን መከላከል መርህ (Exculpatory no doctrine)[9] እንደ መብት አይቆጠርም። ምክንያቱም መርሁ የዳበረበት አገር (አሜሪካ) ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሳይቀር በዉሳኔ ዋጋ አሳጥቶታል።[10] በመሰረቱ ራስን በወንጀል ተጠያቂ ያለማድረግ መብት (Right against self incrimination) ወሰኑ ለሚቀርብለት ጥያቄ መልስ አለመስጠት ነዉ። ከዚህ ቢበዛ በደፈናዉ አላዉቅም (non responsive no[11]) ብቻ እንደመብት ሊታይ ይገባል። በደፈናዉ አላዉቅም ማለት መልስ ሰጪ ለሚቀርቡለት ጥያቄዎች አወ/አይደለም፤ አይቻለሁ/አላየሁም ሰርቻለሁ/አልሰራሁም ከሚሉ ጠቅላላ አነጋገሮች መልስ መስጠት ማለት ነው። ነገር ግን የክርክር ወይም የምርመራ ሂደቱን በሚያበላሽና በሚያሳስት መልኩ በዝርዝር መካድና መዋሸት እዉነታዉ እንዳይታወቅ የሚያደርግ ዉጤት ስላለዉ በህግ ሊያስጠይቅ ይገባል የሚል ክርክር ይቀርባል።[12] ሀሰተኛ ምስክርነትን ለመከላከል ሲባል ጠበቃ እየተከራከረበት ባለዉ ጉዳይ ወይም

---

[6] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 1፣ ዘፍጥረት 4÷9
[7] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 3 ገፅ 199
[8] ዝኒ ከማሁ ገፅ 199
[9] Exculpatory no doctrine is developed by United States of America Federal Criminal Law. The principle that a person can not be charged with making a false statement for falsely denying guilt in response to an investigator's question. This doctrine is based on the 5th Amendment right against self-incrimination. But the U.S. Supreme Court has overruled this doctrine. On the other side, some argue that Exculpatory no Doctrine will exempted from prosecution if there are two requirements (1) it had to convey false information in a situation in which a truthful reply would have incriminated the interrogee. (2) It had to be limited to simple words of denial (such as 'no, I did not, none, or never) rather than more elaborate fabrication.
[10] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 3 ገፅ 199
[11] ዝኒ ከማሁ ገፅ 198 [Non-Responsive no had to be limited to simple words of denial (such as 'no, I did not, none, or never) rather than more elaborate fabrication.]
[12] ዝኒ ከማሁ ገፅ 200

በያዘዉ ጉዳይ ምስክሩ እዉነት እየመሰከረ እንዳልሆነ ሲያዉቅ ሀሰተኛ ምስክርነት እየተሰጠ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ የመግለፅ ወይም የማሳወቅ ግዴታ በጠበቃዉ ላይ የሚጥሉ ህግጋት አሉ።[13] ዉሳኔዉም በሀሰተኛ ምስክርነት የተሰጠ ከሆነ ተከሳሽ ወይም ፍርደኛዉ የህግ አግባብ ጥበቃ (Due Process Protection)[14] አግኝተዉ በነፃ ሊሰናበቱ ይገባል የሚል የፍርድ ቤት ዉሳኔ ህግ በአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳብሯል።[15]

በኢትዮጵያ የወንጀል ህግ አንድ ተከራካሪ ወገን እዉነቱን እንዲናገር በፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ነክነት ስልጣን ባለዉ አካል ሲጠየቅ የሀሰት ቃል ከተናገረ በወንጀል እንደሚጠየቅ

---

[13] Nathan M. Crystal, False Testimony by Criminal Defendants Still unanswered Ethical and Constitutional Questions,2003 University of Illinois Law Review, page 1530, available at https://illiinoislawreview.org/wp-content/articles/2003/5/Crystal.pdf {On February 5, 2002, the American Bar Association (ABA's) House of Delegates adopted a revised version of the Model Rules based on the recommendations of its Ethics 2000 Commission. Revised Rule 3.3 provides as follows:
(a) A lawyer shall not knowingly:
(1) make a false statement of fact or law to a tribunal or fail to correct a false statement of material fact or law previously made to the tribunal by the lawyer;
(2) fail to disclose to the tribunal legal authority in the controlling jurisdiction known to the lawyer to be directly adverse to the position of the client and not disclosed by opposing counsel; or
(3) offer evidence that the lawyer knows to be false. If a lawyer, the lawyer's client, or a witness called by the lawyer, has offered material evidence and the lawyer comes to know of its falsity, the lawyer shall take reasonable remedial measures, including, if necessary, disclosure to the tribunal. A lawyer may refuse to offer evidence, other than the testimony of a defendant in a criminal matter that the lawyer reasonably believes is false.
(b) A lawyer who represents a client in an adjudicative proceeding and who knows that a person intends to engage is engaging or has engaged in criminal or fraudulent conduct related to the proceeding shall take reasonable remedial measures, including, if necessary, disclosure to the tribunal.
(c) The duties stated in paragraphs (a) and (b) continue to the conclusion of the proceeding, and apply even if compliance requires disclosure of information otherwise protected by Rule 1.6.
(d) In an ex parte proceeding, a lawyer shall inform the tribunal of all material facts known to the lawyer that will enable the tribunal to make an informed decision, whether or not the facts are adverse}

[14]Anne Bowen Poulin, Convictions Based on Lies: Defining Due Process Protection, 2011, Penn State law review, page 336, available at www.pennstatelawreniew.org/.../116%20penn%20St.%20L.%20Rev.%203. (Two cases form the foundation in the line of precedent relating to both false testimony and non-disclosure of exculpatory evidence. This line starts in 1935 with *Mooney v. Holohan*, a false testimony case.)

[15] ዝኒ ከማሁ ገፅ 334፣ (Due process protection from the use of false testimony developed parallel to and in conjunction with the due process principles, flowing from *Brady v. Maryland*,that require the prosecution to disclose exculpatory evidence to the defense.)

ተደንግጓል።[16] ይሁንና ይህ ተከራካሪ ወገን የሀሰት ቃል የተናገረዉ ጥቅሙን ለማስከበር በሚያቀርበዉ ትክክለኛ ያልሆነ ክርክር ጊዜ የወንጀል ሃላፊነት አይኖርበትም።[17]

1.1 የሀሰተኛ ምስክር ምንነትና ታሪካዊ ዳራ

የሀሰተኛ ምስክርነትን ምንነት በግልፅ ለመረዳት ያስችግራል። በመሆኑም ትክክለኛ ተግባር ካልሆኑት ድርጊቶች እንደ መዋሸት (Lying) ማሳሳት (Misleading) እና በሀሠት መካድ (Falsely Denying) ከህገ-ወጥ ድርጊቶች እንደ በእውነተኛነት ተግባር ላይ የሚፈፀም ወንጀል[18](perjury)፣ ማታለል (fraud) እና ሀሠተኛ ምስክርነት (false statements) ጋር ያላቸውን ተመሣሣይነትና ልዩነት በትክክል ማወቅ ጠቃሚ ነው። በዚህ ፅሁፍ በእውነተኛነት ተግባር ላይ የሚፈፀም ወንጀል ከሚለዉ ይልቅ ፐርጉሪ የሚለዉ የተሻለና የተለመደ በመሆኑ እንጠቀመዋለን። False statements እና false Testimony የሚሉትን ሀሳቦች ሀሠተኛ ምስክርነት በሚል ተጠቅመንበታል። ብላክስ ሎዉ መዝገበ ቃላት ሀሠተኛ ምስክርነት (False Statement) is knowingly made with the intent to mislead[19]ይለዋል። ይህም ሀሠተኛ አነጋገር (ቃል) ማለት ለማሣሣት ታስቦ በዕውቀት የሚሠራ ነው እንደማለት ነው።

በሀሠተኛ ምስክርነት፣ በዉሸትና በማሳሳት መካከል ልዩነቶች እንዳሉ በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች ያሳያሉ[20]። የዉሸት ንግግርን መጠንና ድግግሞሽ በአሃዝ ማስቀመጥ ቢያስቸግርም አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ስለስራ ችሎታ ከሶስት ተቀጣሪዎች ዉስጥ አንዱ፤ ከአስር የኮሌጅ ተማሪዎች ዉስጥ ዘጠኙ ለፍቅር ጓደኞቻቸዉ ይዋሻሉ።[21] መዋሸት ማለት ሌላኛው ሠው ሀሠት የሆነ እምነት እንዲይዝ ማድረግ ነው። ነገር ግን ያመንክበትን መናገር ውሸት አይደለም፣ ውሸት ለመባል እውነት እንዳልሆነ እያመንክ እውነት ነው ብሎ መናገር እንጅ።[22]

---

[16] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ፣ 1996፣ አዋጅ ቁጥር 414፣ አንቀፅ 452 (1)
[17] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 452 (3)
[18] በእውነተኛነት ተግባር ላይ የሚፈፀም ወንጀል ወይም የእንግለዝኛዉ ቃል perjury (ፐርጉሪ) ለማለት ነዉ።
[19] Blacks law Dictionery, 2009, 9th ed, West a Thomson Reuters, USA, page 1536
[20] በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 3፣ ከገፅ 162-167
[21] Lisa Kern Griffin, Criminal Lying, Prosecutional Power, and Social Meaning, 2009, Californian Law Review, Vol, 97, page 4 available at scholarship.law.berkeley.edu/cgi/viewconent.cgi?article=1109&context…
[22] Don Fallis, Lying and Deception, 2010, university of Arizona, page 1 available at http://quod.lib.umich.edu/cgi/p/pod/.../lying-and-deception.pdf?c...pdf
{Lying involves asserting what one believe is literally false. When A lies B, A gets B to place his faith in him, and then breaches that faith.}

በአንፃሩ ማሳሳት[23] አንድ ሠው ሌላኛውን ሠው ሀሠት የሆነ ነገር እንዲያምን እውነተኛነት ባህርይ ያለውን ወይም የሌለውን ፍሬ ነገር መናገር ነው። በመሆኑም አንድ ሰው ሌላኛው ሠው በተናገረው ነገር ተነሣስቶ ልክ ያልሆነ እምነት እንዲይዝ ሚደረግ አሣሣተው ይባላል። መዋሸትና ማሳሳትን የሚያመሣስላቸው ነገር የተናጋሪው ሀሣብና ፍላጐት ሌላኛውን ሠው ማታለል መሆኑ ነው።

እውነተኛ ያልሆነ ንግግር ሁሉ ሌላኛውን ሠው የማታለል ዓላማ ላይኖረው ይችላል። ተናጋሪው የሚናገረውን ነገር በትክክል ካለማወቅ የመነጨ እውነተኛ ያልሆነ ንግግር ሊኖር ይችላል። ነገር ግን ይህ ሀሰት እንጂ ማሳሳት አይሆንም። ሀሰት ዋነኛ ዓላማው ሠውን ማታለል ሆኖ የተረጋገጠ እውነትን ቃል በቃል ሀሠት አድርጐ ማቅረብ ነው። የተረጋገጠ እውነት ማለትም ንግግሩ በተደረገበት ጊዜ እውነት ወይም ሀሠት የመሆን ዕድል የሌለው እውነታ ብቻ ለማለት ነው። ግልፅ ሀሠት (literary false)[24] ማለት ደግሞ ተናጋሪው ለመናገር የፈለገው እንደዚህ ነው ሳይባል ንግግሩ በታወቀ እና በማያሻማ ሁኔታ ሀሰት ሲሆን ነው። በመሆኑም ሀሰተኛ ምስክርነት ሀሰትንና ማታለልን የያዘ የተከራካሪ ቃል ወይም የምስክር መግለጫ (ምስክርነት) ወይም የልዩ አዋቂ አስተያየት ወይም የአስተርጓሚ መግለጫ ወይም ሰነድ ነዉ። ሀሰተኛ ምስክርነት ከፐርጉሪ ጋር ያለዉን ልዩነትና ተመሳሳይነት የሌሎች አገራትን ህግጋት በሚከተለዉ ክፍል ለማብራራት ተሞክሯል።

ሀሰተኛ ምስክርነት እና ፐርጉሪ ቆየት ያለ ታሪክ አለዉ። ከሃይማኖታዊ ህግጋት በተጨማሪ ሀሰተኛ ምስክርነት እና ፐርጉሪን የሚከለክሉ ጥንታዊ ህጎች እንደነበሩ ሰነዶች ያሳያሉ። ለምሳሌ የሃሙራቢ ህግ፣ የጥንቱ የሮማሙያን ህግ፣ የመካከለኛዉ ዘመን የፈረንሳይ ህግ ወዘተ መጥቀስ ይቻላል። ምስክሩም ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ቅጣቱ ሞት ነበር።[25]

በኢትዮጵያ ደረጃ ፍትሐ ነገስት የተባለዉን መንፈሳዊና ዓለማዊ ህግጋትን አንድ ላይ የያዘዉን ህግ በቀዳሚነት መጥቀስ ይቻላል። በዚህ ህግ ክፍል ሁለት (ሥለ ዓለማዉያን ስራና አስተዳደር) በሚለዉ ክፍል ስለ ዳኛና እርሱን ስለመሰለዉ በሚል ርዕስ በአንቀፅ 43 በሀሠት የመሠከረ ወይም በማናቸውም ነገር ቢሆን ዳኛው ለማወቅ ስለሚፈልገው ነገር ተጠርቶ

[23] When A merely misleads B, A invites B to believe something that is false by saying something that is either true or has no truth value.
[24] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 3 ገፅ 200; (A statement that is literary false is false on its face, without reference to the Speaker's meaning (ምንም እንኳ Statement is either true or false proposition ቢሆንም በዚህ ጊዜ እውነት ብቻ የሆነውን ለማለት ነው።)
[25] ዝኒ ከማሁ ገፅ 174

በተጠየቀ ጊዜ የሀሠት ቃል የተናገረው ሠው በሀሠት መመስከሩ የገንዘብና የእስራት ቅጣት እንደሚያስጥልበት ተመልክቷል።[26] በ1923 ዓ.ም በወጣዉ የወንጀለኞች መቅጫ ደንብ ስድስተኛ ምዕራፍ በሀሠት ምስክርነት ስለሚሠራ ወንጀል በሚል ርዕስ ከፍትሐ ነገስቱ ድንጋጌዎች ጋር በተመሳሰለ መልኩ ተካቶ እናገኘዋለን።

በዚህ ህግ አንቀፅ 364፣ በሀሠት የመሠከረ ወይም በማናቸውም ነገር ቢሆን ዳኛው ለማወቅ ስለሚፈልገው ነገር ተጣርቶ በተጠየቀ ጊዜ የሀሠት ቃል የተናገረው ሠው በሀሠት መመስከሩ ነውና ከሶስት ወር እስከ አንድ ዓመት ታስሮ ከሃያ እስከ ሁለት መቶ ብር መቀጮ ይከፍላል ይላል። ምስክርነቱ በሰዉ መግደል ወንጀሎች በሆነ ጊዜ ቅጣቱ ከፍ እንደሚል በአንቀፅ 365 ላይ የተቀመጠ ሲሆን በዚህ መሰረት በነፍሠ ግዳይ ነገር በሀሠት የመሠከረ ከስድስት ወር እስከ ሁለት ዓመት ታስሮ ከ50 ብር እስከ 500 ብር መቀጫ ይከፍላል ይላል። በተለይም በሀሰት ምስክርነቱ የተነሳ የሞት ፍርድ በተፈረደና በተፈፀመ ጊዜ በሀሠት የተመሠከረበት ነፍሠ ገዳይ ይሙት በቃ ተፈርዶበት የተገደለ እንደሆነ በሀሠት መስክሮ ያስገደለው የሞት ፍርድ ይፈረድበታል ሲል አንቀፅ 366 ይደነግጋል። ሌሎችም ዝርዝር ጥፋቶች ከነቅጣታቸዉ በዚህ ህግ ተቀምጠዋል[27]። በቀደሞው ወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀፅ 447 ሀሠተኛ ምስክርነትን እንደሚከተለዉ ደንግጓል፡- (1) ምስክር ሆኖ የቀረበ ሠው የአስተዳደር፣ የፍትሃብሔር፤ የወንጀል ወይም የሽምግልና ወይም የዳኝነት ነክነት ያለው ሥነ-ሥርዓት በሚፈፀምበት ጊዜ ለክርክሩ ግልፅ በሆኑ ምክንያቶች ላይ ሆነ ብሎ ሀሰተኛ የምስክርነት ቃል የሠጠ እንደሆነና ይህ የሀሰት ተግባሩ አንዱን ወገን ተከራካሪ ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ተሠርቶ እንደሆነ ያቀደው ዕቅዱ እግቡ ባይደርስም እንኳ በእስራት ቅጣት ወይም ጥፉቱ በከፍተኛነት የሚገመት ጉዳት ለማድረስ የሚችል የሆነ እንደሆነ እስከ አምስት (5) አመት የሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል[28] ይላል። ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳዉ ሀሰተኛ ምስክርነት ተሠጠ ለማለት የአስተዳደር፣ የፍትሐብሔርና የወንጀል ወይም የሽምግልና ዳኝነት ወይም የዳኝነትነክነት ሥነ-ሥርዓት ላይ

[26] ፍትሐ ነገስት ንባቡና ትርጓሜዉ፣ 1990፣ ትንሳኤ የመፅሃፍት ማሳተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ

[27] የወንጀለኞች መቅጫ ደንብ፣ 1923፣ ክፍል ሁለት ስድስተኛ ምዕራፍ (አንቀፅ 367 ዳኛዉ ለማወቅ ስለፈለገዉ ነገር ወደ ችሎት እንዲጠራ አዉቆ ማናቸዉም የሚቀርብ ምስክር ከ3 ወር እስከ 1 አመት ታስሮ ከ20 እስከ 200 ብር መቀጮ ይከፍላል። አንቀፅ 368 በሀሰት ከመሰከረ በኋላ ዳኛዉ የምስክሩን ቃል ተጠራጥሮ በመረመረዉ ጊዜ ለዳኛዉ እዉነቱን አዉጥቶ የተናገረ እንደሆነ ቅጣቱ እኩሌታ ይሆንለታል።
አንቀፅ 369 በሀሰት ከመሰከረ በኃላ ፍርዱ ባይፈረድ በቶሎ እውነቱን ተናግሮ ቃሉን የለወጠ ሠው ከፊተኛው ቃሉ የኃለኛው ቃሉ እውነት መሆኑን ካስረዳ በኋላ ቅጣት የለበትም።
አንቀፅ-370 በሀሠት የመሠረከ በሀሠት የመሠከረው ገንዘብ ተቀብሎ የሆነ እንደሆነ የእስራቱም የገንዘቡም ቅጣት እጥፍ ይሆናል። የተቀበለውም ገንዘብ ይመለሣል በሚልተደንግጓል።)

[28] የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ህግ 1949፣ ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 1፣ ቁጥር 158፣ በብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ሃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አንቀፅ 447

በተደረገ ክርክር ጊዜ እንደሆነ ነዉ። ሀሰት ለማለት ምስክርነት የተሰጠባቸዉ ፍሬ ነገሮች ግልፅ የሆኑ ሊሆኑ ይገባል። ሀሰት መስካሪዉ ምስክርነት የሰጠዉ ሆነ ብሎ አንዱን ተከራካሪ ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት መሆን ይኖርበታል።

ሲጠቃለል ሀሰተኛ ምስክርነትንና ፐርጉሪ በሃይማኖት ህግጋት አስተምሮት የተወገዙ ናቸዉ። ከዚህ ባሻገር እነዚህን ድርጊቶች የሚቀጣ ረዥም ዘመን ያስቆጠረ ህግ የነበረና ያለ ቢሆንም እንዲሁም ለእነዚህ ድርጊቶች እስከ ሞት ፍርድ የሚደርስ ቅጣት የነበረና ያለ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ወንጀሉ አልቀረም። አንድ ፀሃፊ የዳኝነት ሂደትን እና የመጨረሻ ግቡን በማሳት ረገድ እንደሀሰተኛ ማስረጃ የሚያሰፈራ የለም[29] ይላል::

በዚህ ፅሁፍ በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሀሰተኛ ምስክርነትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ምን ምን ዓይነት ፍሬ ነገሮችን አካተዋል? እንዲሁም ሀሰተኛ የምስክርነት ቃል ወይም አስተያየት በየትኞቹ ተቋማት በተሰጠ ጊዜ ነዉ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትለው የሚሉትን ጉዳዮችና ሌሎች ተያያዥ ነጥቦች የቆየና የዳበረ ልምድ ካላቸዉ አገራት ህግ ጋር በማገናዘብ ምላሽ ለማቅረብ ተሞክሯል።

2. የሀሠተኛ ምስክርነት የህግ ማዕቀፍ የዳበረ ልምድ ባላቸዉ አገራት

በሀሰተኛ ምስክርነት ዙሪያ የዳበረ ህግና ልምድ ያላቸዉ አገራት ሲመረጡ እነዚህ አገራት በምን መስፈርት ተመረጡ? የተመረጡት አገራት ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተቀራራቢ ናቸዉ ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ። አገራቱን ከመረጥኩባቸዉ ምክንያቶች ዉስጥ ቀዳሚዉ ጉዳይ በሀሰተኛ ምስክርነት እና በፐርጉሪ ዙሪያ በተሻለ መጠን ፅሁፍና ማብራሪያ ያገኘሁባቸዉ አገራት በመሆናቸዉ ነዉ። ከዚህ በተጨማሪም የተመረጡት አገራት ዝርዝርና ግልፅ የሀሰተኛ ምስክርነት እና የፐርጉሪ ድንጋጌዎች ያሏቸዉ ሆነዉ አግኝቻለሁ። በሌላ በኩል በሀሰተኛ ምስክርነት እና በፐርጉሪ የህግ ማዕቀፍ ረገድ የረዥም ጊዜ ልምድ መኖርን እንደ ተጨማሪ መመዘኛ ተጠቅሜአለሁ።

[29] George W. Aycock, Nothing but the truth; A Solution to the current inadequacies of the federal perjur statutes, 1993, Valparaiso University of law review, Volume 28 No, 1 page 247 available at scholar.valpo.edu/cgi/viewcontent.cgi?article=1936&context=vulr

ሌላዉ ጉዳይ በሀሰተኛ ምስክርነት ዙሪያ ዝርዝርና ክፍተቶችን የሚሞላ ህግ መፈለግ ቁልፍ ጉዳይ ነዉ። ዝርዝርና ክፍተቶችን የሚሞላ ህግ የተሻለ የማስፈፀም አቅም ካላቸዉ አገራት ስለተገኘ ብቻ ከኢትዮጵያ የማስፈፀም አቅም ጋር አብሮ አይሔድም ሊባል አይችልም። በሀሰተኛ ምስክርነት ዙሪያ የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች ለአሰራር ምቹ አድርጎ ማሻሻል የተለየ የማስፈጸም አቅም የሚጠይቅ ሆኖ አልተሰማኝም። በመሆኑም የኢትዮጵያን የእድገት ደረጃ የዳበረ ልምድ ካላቸዉ አገራት ጋር ማነፃፀር ብዙም ጠቃሚ መስሎ አልታየኝም። በአብዛኛዉ ስራ ላይ ያሉት የኢትዮጵያ ህግጋት አመጣጥም የዳበረ ልምድ ካላቸዉ አገራት መሆኑ ይታወቃል። ይህም ከዚህ የተለየ አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ በርካታ ተዕዕኖ የሚፈጥሩ የፍርድ ቤት ዉሳኔዎችን በተመለከተም የተመረጡት አገራት በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። በዚህ መሰረት የእንግሊዝንና የአሜሪካን አገራት የህግ ማዕቀፍ መፈተሽ መርጫለሁ።

2.1 የእንግሊዝ የህግ ማዕቀፍ

ዩናይትድ ኪንግደም የፐርጉሪ ህግጋትን አስመልክቶ ቀዳሚ አገር ነች ማለት ይቻላል። ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ህግ ነበራት። በተለይም በ1911 (እ.ኤ.አ) የወጣው የፐርጉሪ ህግ ዋነኛው ነው። በዚህ ህግ ምዕራፍ 6(1) ላይ

Perjury

(1) if any person lawfully sworn as a witness or as an interpreter in a judicial proceeding willfully makes a statement material in the proceeding, which he knows to be false or does not believe to be true, he shall be guilty of perjury, and shall, on conviction thereof on indictment be liable to penal servitude for a term not exceeding seven years, or to imprisonment (with or with out hard labour) for a term not exceeding two years, or to a fine or to both such penal servitude[30], or imprisonment and fine. (With or without hard labor)[31]

(2) The expression "judicial proceeding" includes a proceeding before any court, tribunals, or person having by law power to hear, receive and examine evidence on oath.

እነዚህን ድንጋጌዎች ወደ አማረኛ ስንመልሳቸው

[30] Penal servitude in the former English Criminal Law is the imprisonment of an offender and his subjection to hard labour

[31] Perjury Act 1911, article 6(1) available at moj.gov.jm/sites/default/files/laws/perjury%20Act.pdf

(1) ማንኛውም ሠው የዳኝነት ሥነ-ሥርዓት በሚካሔድበት ጊዜ በህግ መሠረት መሃላ ፈፅሞ ምስክር ወይም አስተርጓሚ ሆኖ ሲቀርብ ለክርክሩ አወሣሠን ጠቃሚ በሆነ ጉዳይ ላይ ሀሠት እንደሆነ እያወቀ ወይም እውነት እንዳልሆነ እያመነ በፈቃዱ በሠጠው የሀሰት ምስክርነት ወይም ቃል በፐርገሪ ጥፋተኛ ይባላል። ክስ ቀርቦበት የጥፋተኝነት ውሣኔ ከተሰጠበት በወንጀል አገልጋይነት ከሰባት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ይቀጣል ወይም በጉልበት ስራ ከሁለት አመት ላልበለጠ ጊዜ በእስራት ወይም በገንዘብ ቅጣት ወይንም ሁለቱን ማለትም የወንጀል አገልጋይነት ወይም እስራት ከመቀጮ ጋር ይቀጣል።

(የጉልበት ሥራ ወይም ያለጉልበት ስራ የሚለው አገላለፅ ቀሪ እንደሆነ ልብ ይሏል[32]።)

(2) የዳኝነት ሂደት የሚለው አገላለፅ በማናቸውም ፍርድ ቤት፣ የአስተዳደር ፍርድ ቤት እንዲሁም ቃለ መሃላ አስፈፅሞ ማስረጃ ለመስማት፣ ለመቀበል እና ለመመርመር በህግ ስልጣን በተሠጠው ሠው ፊት የሚደረግ ሂደትን ያካትታል።

ከእነዚህ ድንጋጌዎች የምንገነዘባቸው ነጥቦች ፐርገሪ ለመባል የሚከተሉት ቅደመ-ሁኔታዎች በአንድ ላይ ተሟልተዉ ሊገኙ ይገባል።

- ማንኛውም ምስክር ወይም አስተርጓሚ በህግ መሰረት መማል ወይም እዉነቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል።
- መሃላዉ ወይም እዉነቱ የሚረጋገጠው የዳኝነት ተግባር በሚፈፀምበት ተቋም ነዉ።
- ምስክሩ ወይም አስተርጓሚዉ የሚሰጠዉ ቃል ወይም መግለጫ በራሱ ነፃ ፈቃድ ሲሆን
- የሚሰጠዉ ቃል ወይም መግለጫ ለዉሳኔ አሰጣጥ ተፅዕኖ የመፍጠር አቅም ያለዉ
- የሚሰጠዉ ቃል ወይም መግለጫ ሀሰት እንደሆነ ምስክሩ ወይም አስተርጓሚዉ ማወቅ አለበት የሚሉት ናቸው።

የዳኝነት ሂደት ሲባልም ማናቸውንም ከታችኛው እስከ ላይኛው ደረጃ ያሉ ፍርድ ቤቶችን ያካትታል። እንዲሁም በሁሉም የአስተዳደር መስሪያ ቤቶች የሚገኙትን የተለያዩ የአስተዳደር አካላትንና ፍርድ ቤቶችን ይጨምራል። ከዚህም ባሻገር ሰፋ ባለ መልኩ ቃለ መሃላ የፈፀሙ ሠዎችን ማስረጃ የመቀበል፣ የመስማትና የመመርመር ሥልጣን በህግ የተፈቀደላቸውን

[32] Criminal Justice Act, 1948, Abolition of penal Servitude, hard labour, prison divisions and Sentence os whipping, Chapter 58, Section 1

ሠዎችን ሁሉ ያካትታል። በመሆኑም ማንኛውም ሠው ማስረጃ ለመስማት ለመቀበልና ለመመርመር ህግ ከፈቀደለት ይህ ሂደት የዳኝነት ሂደት እንደሚባል ያሳያል።

በሌላ መልኩ ሀሠተኛ ምስክርነትን የሚመለከተው የህጉ ክፍል አንቀፅ 6(2) ነው። ይህም

(1) If any person being required or authorized by law to make any statement an oath for any purpose, and being lawfully sworn (otherwise than in judicial proceeding) willfully makes a statement which is material for that purpose and which he knows to be false or does not believe to be true, or

(2) Willfully uses any false affidavit for the purpose of the Bills of sale Act, 1878, as amended by any subsequent enactment, he shall be guilty of misdemeanor,[33] and a conviction thereof on indictment, shall be liable to penal servitude for a term not exceeding seven years or imprisonment, with or without hard labor, for a term not exceeding two years, or to a fine or to both such penal servitude or imprisonment and fine[34] ተብሎ ተቀምጧል።

ይህም በግርድፉ የሚሰጠዉ ትርጉም "ማንኛውም ሠው ከዳኝነት ሥርዓት ዉጭ ለማንኛውም ዓላማ ሲባል ቃለ መሃላ ፈፅሞ ምስክርነት እንዲሠጥ በህግ ሲጠየቅ ወይም ሲታዘዝ ለሚፈለገዉ ዓላማ ጠቃሚና ተፅዕኖ በሚፈጥሩ ጉዳዮች ላይ ሀሠት እንደሆነ እያወቀ ወይም እውነት እንዳልሆነ እያመነ የሚሠጠው ቃል ሀሰት በሆነ ጊዜ ወይም በፈቃዱ በ1878 (እ.ኤ.አ) በወጣው የሽያጭ ህግ መሠረት የራስ ቃለ መሃላ (affidavit) ፈፅሞ ከህጉ አላማ ጋር የማይስማማ ሀሠት በተናገረ ጊዜ በተራ ወንጀል ጥፋተኛ ነው።

ክስ ቀርቦበት የጥፋተኝነት ውሣኔ ሲተላለፍበት የጉልበት ሥራ ያለበት ከሁለት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የማረሚያ ቤት እስራት ወይም ቅጣት ወይም ሁለቱንም ይቀጣል" ይላል። (የጉልበት ስራ ቅጣት በ1948 በወጣው የወንጀል ፍትህ ህግ ቀሪ መደረጉን ግንዛቤ ይወሠድበት)። የሁለቱ ድንጋጌዎች መሰረታዊ ልዩነት ፐርጉሪ የዳኝነት ተግባር በሚፈፀምበት ተቋም ጊዜ የሚሰራ ሲሆን ሐሰተኛ ምስክርነት ደግሞ የዳኝነት ተግባር ከሚፈፀምባቸዉ ተቋማት ውጭ መሆኑ ነዉ። ሌላዉ ሐሰተኛ ምስክርነት በተራ ወንጀል ጥፋተኛ የሚያስብል

[33] A misdemeanor is generally a crime that is punishable for a year or less in prison, or only in a county or local jail.
[34] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 30፣ article 6(2)

መሆኑ ነዉ። ከዚህ በላይ ካየናቸው ድንጋጌዎች በተጨማሪ proceeding in other jurisdiction Act 1975 የሚባለዉ ህግ ያለ ቃለ መሃላ ሀሠተኛ ምስክርነት በተሰጠ ጊዜ ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑ ተቀምጧል። ይህም If any person, in giving any testimony (either orally or in writing) otherwise than an oath, where required to do so by an order under section 2 of the Evidence (proceedings in other Jurisdiction) Act 1975, makes a statement

(a) Which he knows to be false in a material particular, or
(b) Which is false in a material particular and which he does not believe to be true, he shall be quilt of an offence and shall be liable an conviction on indictment to imprisonment for a term not exceeding two years or a fine or both"[35] በሚል ይገለፃል።

በመሆኑም ማንኛውም ሠው ቃለ መሃላ ሳይፈፅምም በቃልም ሆነ በፅሁፍ ምስክርነት በሚሠጥበት ጊዜ፡-

(1ኛ) ለልዩ ጉዳይ ሀሠት እንደሆነ እያወቀ
(2ኛ) ለልዩ ጉዳይ ሀሠት ሆኖ እንዲሁም እውነት መሆኑን ሳያምንበት ከሆነ ክስ ቀርቦበት ሲፈረድበት ተጠያቂ ይሆናል። ከሁለት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ በማረሚያ ቤት እስራት ወይም የገንዘብ ቅጣት ወይም ሁለቱንም ይቀጣል። የሚል ሀሳብ ይሰጣል። በዚህ የማስረጃ ህግ መሠረት ምስክርነት እንዲሠጥ የታዘዘ ሠው ቃለ መሃላ ባይፈፅም ሀሠት መሆኑን እያወቀ ወይም እውነት እንዳልሆነ እያመነ ሀሠተኛ የፅሁፍ ቃል ወይም ምስክርነት መስጠት በህግ ያስቀጣል ማለት ነው። በመሆኑም መንግስት ምስክሩ ሀሠት መሆኑን እያወቀ የመሠከረ መሆኑን እና ምስክርነት በሚሠጥበት ልዩ ጉዳይ ውሣኔ አሠጣጥ ተፅዕኖ የሚሠጥ ቃል መሆኑን ካስረዳ ግለሠቡ የህግ ተጠያቂነት አለበት።

2.2 የአሜሪካ ህግጋት

በመሠረቱ ሀሰተኛ ምስክርነት ሀሰትን እና ማሳሳትን አንድ ላይ የያዘ ተግባር ነው። ፐርጉሪ እና ሀሠተኛ ምስክርነት በአብዛኛው ተቀላቅለው ሲገለፁ ይስተዋላል። ለምሳሌ በአሜሪካ የፐርጉሪ ህግ የሚባሉት በምዕራፍ 79 (Chapter 79) ርዕስ 18 (Title 18) ቁጥር (Section)

[35] Evidence (Proceeding in other jurisdiction Act), 1975, London, Majesty's Stationary Office, section 2

1001፣ 1621፣ 1622 እና 1623 ላይ በወንጀልና ወንጀል ሥነ-ሥርዓት ህጉ በዝርዝር ተቀምጠዋል። ድንጋጌዎቹ በኮንግረሱ የወጡ የፌደራል መንግስቱ ህግ አካል ናቸው።[36]

2.2.1 ሀሰተኛ ምስክርነት

በአሜሪካ የፌደራል መንግስት ሀሰተኛ ምስክርነት ህግ በቁጥር 1001 ውስጥ እንደሚከተለው ሰፍሮ እናገኘዋለን።

(a) Except as otherwise provided in this section, whoever, in any matter within the jurisdiction of the executive, legislative, or judicial branches of the government of the United States, knowingly and willfully

(1) Falsifies, conceals or covers up by trick, scheme, or device a material fact:
(2) Makes any materially false, fictitious, or fraudulent statement or representation; or
(3) Makes or uses any false writing or document knowing the same to contain any materially false, fictitious or fraudulent statement or entry: shall be fined this title, imprisoned not more than 5 years, if the offense involves international or domestic terrorism, imprisoned not more than 8 years, or both. If the matter relates to an offense under chapter 109 A (sexual abuse) 109 B (sex offender registration), 110 (sexual exploitation), or 117 (transportation for illicit sexual purpose), or section 1591, (sex trafficking), then term of imprisonment in posed under this section shall be not more than 8 years.[37]

የዚህ ድንጋጌ አቻ የአማርኛ ትርጉም በግርድፉ በሌላ ክፍል ከተደነገገዉ ዉጭ ማንም ሰዉ በአሜሪካ መንግስት የህግ አዉጭ፣ አስፈፃሚና የዳኝነት አካል ስልጣን ስር በሆኑ ጉዳዮች እያወቀና ፈልጎ፦

(1) ግዙፋዊ ነገሮችን በማታለል፣ በማስመሰል ወይም በማናቸዉም መሳሪያ የዋሸ፣ የሸሸገ፣ የደበቀ፣ (2) ማንኛዉም ግዙፋዊ ነገሮችን በሐሰት፣ በፈጠራ፣ በማጭበርበር የሰራ ወይም ዉክልናዎችን ያዘጋጀ፣ (3) ግዙፋዊ ነገሮች ሐሰት፣ ፈጠራዊ (እዉነተኛ ያልሆኑ)፣ የተጭበረበሩ እንደሆኑ የሚታወቁ ማናቸዉንም ሀሰተኛ ፅሁፎች ወይም ሰነዶች ያዘጋጀ ወይም የተጠቀመ እንደሆነ ከአምስት አመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል። ሆኖም ወንጀሎቹ የአገር

[36] Charles Doyle, False statement and perjury: An overview of federal criminal law, 2018, congressional research service, page, 1 available at http://fas.org/sgp/crs/misc/98-808.pdf
[37] United States Crime and Criminal procedure Code (USC) Title 18, Section 1001, page 275

ዉስጥ ወይም አለም አቀፍ ሽብርተኝነት እና ፆታን መሰረት ያደረጉ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ከሆኑ እስከ ስምንት አመት ሊደርስ የሚችል እስራት ወይም ሁለቱም ሊሆን ይችላል። ጉዳዩ ፆታዊ ጥቃትን፣ የጾታዊ ጥቃት ፈጻሚዎች ምዝገባ፣ ጾታዊ ብዝበዛን፣ ህገ-ወጥ ለሆነ ለወሲብ አላማ ማጓጓዝ፣ ለወሲብ ማዘዋወር ወንጀሎችን በተመለከተ ከስምንት አመት ባልበለጠ የሚያስቀጡ መሆኑን ይደነግጋል።

በዚህ ድንጋጌ ላይ የተካተቱት ፍሬ ጉዳዮችን ስንመለከት የመጀመሪያው **ማንኛውም አካል** የሚለዉ ሲሆን ይህም የተፈጥሮና የህግ ሠዎችን የሚያካትት ነው። እንደማህበራት፣ ድርጅቶች፣ ካምፓኒዎች ወ.ዘ.ተ በዚህ ህግ ሊቀጡ ይችላሉ። ሁለተኛው ፍሬ ጉዳይ **ስልጣኑን** የሚደነግገዉ ይዘት ነው። በአሜሪካ መንግስት ህግ አዉጪ፣ አስፈፃሚና ተረጓሚ አካላት ስልጣን ስር በሚገኙ ጉዳዮችን ሁሉ እንደሚይዝ ያሳያል። ይሁንና በህግ አውጭው ሥር ካሉት በተወሠኑት ብቻ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚገባ የ1001 (C) ድንጋጌ ያስገነዝበናል።

ሶስተኛው ፍሬ ጉዳይ **የሀሳብ ክፍል** ነው። በዚሁ መሠረት ድርጊት ፈፃሚው ጉዳዩን አውቆና አቅዶ የፈፀመ መሆን አለበት። ተከሣሹ ሀሠተኛ ምስክርነቱን በሙሉ እውቀቱና ፍላጐቱ የሠጠው ቃል ወይም መግለጫ ወይም ሰነድ ወይም መስጠት ሲገባው ያልሰጠው ቃል ወይም መግለጫ ወይም ሠነድ በጊዜው ሀሠት እንደሆነ ማወቁን መንግስት የማስረዳት ግዴታ አለበት።

አራተኛው ፍሬ ነገር **ግዙፋዊነት (Materiality)** ነው። ግዙፋዊነት ሲባል ሀሠተኛ ምስክርነቱ በውሣኔ ሠጭዎቹ ላይ ተፅእኖ የሚፈጥር ተፈጥሯዊ ባህርይ ወይም ችሎት ያለው መሆን ነዉ።[38] ነገር ግን መንግስት (ከሳሽ ዐ/ህግ) በእርግጥም ውሣኔ ሠጭው ተፅዕኖ ላይ የወደቀ መሆኑን ማሳየት አይጠበቅበትም። ግዙፋዊ ፍሬ ጉዳይ በ1962 በወጣዉ የአሜሪካ የሞዴል ወንጀል ህግ አንቀፅ 241.1 (2) ላይ እንደሚከተለዉ የበለጠ ተብራርቷል። Materiality, Falsification is material, regardless of the admissibility of the statement under rules of evidence, if it could have affected the course or outcome of the proceeding. It is no defense that the declarant mistakenly believed the falsification to be immaterial. Whether a falsification is

[38] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 35 ገፅ 4 {Prosecution for violation of Section 1001 requires proof of materiality, as does conviction for perjury, and the standard is the same: the statement must have a natural tendency to influence, or be capable of influencing the decisionmaking body to which it is addressed.}

material in a given factual situation is a question of law.[39] **የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል። ይህም ሀሰተኛነቱ ግዙፋዊ ነዉ የሚባለዉ የማስረጃዉ ተቀባይነት የማስረጃ ህግ መርህን ከግምት ዉስጥ ሳያስገባ የክርክሩን ዉጤት ወይም ሂደት የማዛባት አቅም ካለዉ ነዉ። ምስክሩ ሀሰትነቱ ግዙፋዊ አይደለም ብየ በስህተት ተረድቸዉ ነዉ የሚል መከላከያ ሊያቀርብ አይችልም። ሀሰትነቱ ግዙፋዊ ይሁንም አይሁንም ይህ ሁኔታ የህግ ጭብጥ ነዉ የሚል ተቀራራቢ ትርጉም ይሰጣል።**

የመጨረሻዉ ፍሬ ነገር ሀሠተኛ ምስክርነት የሚገለፅባቸዉ ክንዉኖች ናቸዉ። በድንጋጌው ላይ እንደሚታየው ሀሠተኛ ምስክርነት የሚገለፅባቸዉ ሶስት አማራጮች ናቸዉ። እነዚህም እውነትን በመደበቅ፣[40] ሀሠትን በመናገርና በመፃፍ[41] መልኩ ሊሆኑ ይችላሉ።

ሌላዉ የድንጋጌዉ ክፍል በቁጥር 1001 (b) **የሰፈረዉ ሀሳብ በዳኝነት ሂደት ወይም ክርክር ዉስጥ ባሉ ተከራካሪዎች ወይም ጠበቆቻቸዉ በሚሰጡት ወይም በሚያቀርቡት ቃል፣ ጽሁፍ ወይም ሰነድ ላይ ተግባራዊ አይሆንም**[42] **የሚለዉ ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ የቁጥር** 1001 (a) **በህግ አዉጭዉ ክፍል ተግባራዊ የሚሆነዉ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ እንደሆነ እንደሚከተለዉ ተመልክቷል።** "(c) With respect to any matter within the jurisdiction of the legislative branch subsection (a) shall apply only to

(1) Administrative matters including a claim for payment, a matter related to the procurement of property or services, personnel or employment practices, or support services, or document required by law, rule or regulation to be submitted to the congress or any office or officer within the legislative branch or

(2) Any investigation or review, conducted pursuant to the authority of any committee, subcommittee, commission, or office of the congress, consistent with applicable rules of the House of senate."[43] **እነዚህም** (1ኛ) **አስተዳደራዊ ጉዳዮች ሆነዉ ከክፍያ ጥያቄ፣ ከመንግስት**

---

[39] American Model Criminal Code, 1962, Washington D.C. American law institute,Article 241.1(2)

[40] **እውነትን መደበቅ ሲባል፡- እውነትን ባለመናገር፣ በመሸፈን፣ ግዙፋዊ ነገሮችን በመሸወድ ሊሆን ይችላል።**

[41] **ሀሠትን በመናገር ሲባል፣ ግዙፉዊ ሀሰት በመናገር፣ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም አሣሣች ነገርን በመግለፅ ወይም በማቅረብ ሊገለፅ ይችላል። እንዲሁም በመፃፍ ሲባል ሀሰተኛ ሰነድን ወይም ምስክርነትን በመፃፍ ወይም በመጠቀም ሊሆን ይችላል።**

[42] Subsection (a) does not apply to a party to a judicial proceeding or that party's councel, for statements, representations, writings or documents submitted by such party or counsel to a judge or magistrate in that proceeding"

[43] **በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር** 36፣ 1001(c), page 275

ንብረት ወይም አገልግሎት፣ ከሰዉ ሃይል ወይም ስራ ልምምድ፣ ከእርዳታ አገልግሎት፣ በህግ በታዘዘ ሰነድ፣ ለህግ አዉጪዉ ክፍል ወይም ሃላፊ ወይም ለምክር ቤቱ በሚቀርቡ ደንቦችና አሰራሮች ጋር በሚገናኙት (2) ከላይኛዉ ምክር ቤት ጋር በተጣጣመ መልኩ ማንኛዉም የታችኛዉ ምክር ቤት ኮሚቴ፣ ንዑስ ኮሚቴ፣ ኮሚሽን ወይም ሃላፊ በሚያደርገዉ ማንኛዉም ምርመራ ወይም ግምገማ ጋር በተያያዙት ጉዳዮች ብቻ ተፈፃሚ ይሆናል።

ከዚህ የምንረዳዉ ሀሰተኛ ምስክር በዋነኝነት የሚያተኩረዉ የወንጀል ተጠርጣሪዎችና ምስክሮች በሁሉም የመንግስት አካላት (ህግ አዉጪ፣ ተርጓሚና አስፈፃሚ) ላይ በሚፈፀሙት የማሳሳትና ያለመታመን ተግባራት ነዉ።

2.2.2 ፐርዠሪ

በአሜሪካ የፌደራል መንግስት የፐርዠሪ ህግ የሚባሉት በአሜሪካ የተባበሩትት መንግስታት የወንጀልና የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ህግ ርዕስ 18 ምዕራፍ 79 በቁጥር 1621፣ 1622 እና 1623 በሶስት አንቀፆች ተዘርዝሯል።[44] ቀዳሚዉ ጠቅላላ ፐርዠሪ የሚባለዉ ቁጥር 1621 ነዉ። ይህ ድንጋጌ ከ1790 ጀምሮ በማገልገል ላይ ያለ ሲሆን በ1988 ተሻሽሏል። ድንጋጌዉ Common Law Perjury Statue በመባል ይታወቃል።[45]

ሀ/ ጠቅላላ ፐርዠሪ (ቁጥር 1621)

Whoever (1) having taken an oath before competent tribunal, officer, or person in any case in which a law of United States authorizes an oath to be administered, that he will testify, declare, depose or certify to such oath states or subscribes any material mater which he does not believe to be true: or

2 In any declaration, certificate, verification, or statement under penalty of perjury as permitted under section 1746 of title 28. United States Code, willfully subscribes as true any material matter which he doesn't believe to be true is guilty perjury and shall, except as otherwise expressly provided by law be fined under this tittle or imprisoned not more

[44] ዝኒ ከማሁ፣ Section 1621, 1622, 1623,
[45] በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 29 ገፅ 248

than five years or both, this section is applicable whether the statement or subscription is made within or without the United States.[46]

ይህ ድንጋጌ በግርድፉ ሲተረጎም፡- “1) ማንም ሰዉ የአሜሪካ አገራት ህግ ቃለ-መሃላ እንዲደረግ በሚፈቅድባቸዉ ጉዳዮች ስልጣን ባለዉ አስተዳደር፣ ሀላፊ ወይም ሰዉ ፊት ምሎ ሲመሰክር፣ ሲያስረዳ ወይም ሲያረጋግጥ በቃለ መሃላዉ መሰረት ካልሆነ ወይም እዉነት እንዳልሆነ እያመነ ማንኛዉንም ግዙፋዊ ጉዳይ ሲያሳዉቅ ወይም

2) የአሜሪካ አገራት ህግ ቁጥር 1746 ርዕስ 28 የፐርዝሪ ቅጣትን ባስቀመጠዉ መሰረት በማናቸዉም መግለጫ፣ የምስክር ወረቀት ወይም ሰነድ፣ ማረጋገጫ ወይም አባባል በራሱ ነፃ ፈቃድ እዉነት ያልሆነ ነገርን እዉነት እንዳልሆነ እያመነ እዉነት አስመስሎ ያቀረበ እንደሆነ በፐርዝሪ ጥፋተኛ ነዉ፡፡ በሌላ ህግ በግልፅ እስካልተመለከተ ድረስ በገንዘብ መቀጮ ወይም እስከ አምስት አመት በሚደርስ እስራት ወይም ሁለቱንም ይቀጣል፡፡ ይህ ድንጋጌ በአሜሪካ ወይም ከአሜሪካ ዉጭ በተሰጠ መግለጫ ወይም አባባል ላይ ተፈፃሚ ይሆናል” ይላል፡፡

ከዚህ ድንጋጌ ላይ ልብ ከምንላቸው ፍሬ ጉዳዬች ውስጥ አንዱ **ማንም ሰው** የሚለው ነው፡፡ እንደ ሀሠተኛ ምስክርነት ድንጋጌ ሁሉ ማንም ሰው የሚለው አገላለፅ የተፈጥሮ እና የህግ ሠዎችን ይይዛል፡፡ የተፈጥሮ ሠው የሚለው ግልፅ ቢሆንም የህግ ሠውነት ያላቸው ድርጅቶች ስንል ግን በሠራተኞቻቸው ወይም በሃላፊዎቻቸው ወይም በወኪሎቻቸው አማካኝነት ለሚፈፀም ጥፋት እና ጥፋቱ ለድርጅቱ ጥቅም ተብሎ የተፈፀመ እስከ ሆነ ድረስ ተጠያቂ ይሆናሉ ለማለት ነው፡፡[47]

2ኛው ነጥብ የሀሳብ ክፍሉ ነዉ፡፡ ይህም ተከሣሹ የሠጠው ምስክርነት ሀሰት መሆኑን ማወቅ ብቻ ሳይሆን ይህንኑ ሀሠተኛ ምስክርነቱን **በፍላጎቱ** የሰጠው መሆኑ ነው፡፡ ይህ ሲባል የሀሳብ ክፍሉ መለኪያ ከመፈለግ በተጨማሪ ማወቅንም ይይዛል ማለት ነዉ፡፡

3ኛው ፍሬ ነገር **የመሃላ ቃል** (oath) መፈፀሙ ነው፡፡ 4ኛዉ ጉዳይ **ምስክርነቱ ሀሠት** መሆን ይኖርበታል፡፡ ሀሠት ነው ለማለት በማያሻሙ ፍሬ ነገሮች ላይ ግልፅ ሀሰት (litrarily false) መሆን ይኖርበታል፡፡

[46] United States Crimes and Criminal Procedure Code (USC) Title 18, Chapter 79, Section 1621, page 386

[47] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 35 ገፅ 7

በ5ኛ ደረጃ የሚጠቀሠው ነጥብ በዚህ ድንጋጌ የተካተተው **የሁለት ምስክሮች ደንብ** ነው። የሁለት ምስክሮች ደንብ (Two Witness Rule) ማለት አንድን ተከሣሽ ከዚህ በላይ ባለው ድንጋጌ ጥፋተኛ ለማድረግ የተከሣሹ ምስክርነት ወይም መልስ ሀሠት መሆኑን ሌሎች ሁለት ምስክሮች ቃለ-መሃላ ፈፅመው በሠጡት ቃል መሰረት የተመሰከረበትን ፍሬ ነገር ተከሳሹ ምስክር በሀሠት ያስረዳ ወይም የመሰከረ ሲሆን ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ አንድ ቃለ-መሃላ ፈፅሞ ከተሰጠ ምስክርነት ቃልና ከደጋፊ ሠነድ ማስረጃ ጋር ሲተያይ የተከሳሹ ምስክር ምስክርነት ሀሠት መሆን ይኖርበታል። የሁለት ምስክሮች ደንብ መርህ በልዩ ሁኔታም ሁለት ምስክሮች ሳይኖሩ ጥፋተኛ ማድረግ የሚቻልባቸው አጋጣሚዎች[48] አሉ።

6ኛው ፍሬ ጉዳይ አንድን ተከሣሽ ከዚህ በላይ ባለው ድንጋጌ ተጠያቂ ለማድረግ የሀሠት ምስክርነቱ ግዙፋዊ (material)[49] መሆን ይኖርበታል። በሌላ አገላለፅ የሀሠት ምስክርነቱ ውሣኔ ሠጭውን በተፅዕኖ ስር የሚጥል ባህሪይ ያለው ሲሆን ነው።

ሌላዉ በቁጥር 1621(2) ላይ የተደነገገው ሀሠተኛ ፅሁፍ በፐርጉሪ ውስጥ የሚካተት መሆኑን ያሳያል ነው። የዚህ ድንጋጌ ፍሬ ነገሮችም ማንም ሠው በማንኛውም መልኩ በሚሠጠው መግለጫ፣ የምስክር ወረቀት (ሠነድ) እና ማረጋገጫ እውነት እንደሆነ አስመስሎ በፈቃድ ከሠጠ እና ይህ ሁኔታም ግዙፋዊ ባህርይ ያለው ከሆነ እውነት እንዳልሆነ እያወቀ ከሠጠ ከአምስት አመት ያልበለጠ እስራት ወይም (እና) የገንዘብ ቅጣት እንደሚያስቀጣ በቁጥር 1746 ላይ ተደንግጓል።[50]

ለ/ በፍርድ ቤቶችና በጁሪዎች ላይ የሚፈፀም ፐርጉሪ (ቁጥር 1623)

ሌላው ድንጋጌ ቁጥር 1623 (Perjury in Judicial Context) የሚባለዉ ነው። ይህም በዳኝነት አካሎች ማለትም በመደበኛ ፍርድ ቤቶችና በጁሪዎች ላይ የሚፈፀሙ የፐርጉሪ ወንጀሎችን የሚመለከት ነው።

---

[48] Lester B. Orfield, Proof of Perjury and the Two WitnessesRequirement in Federal Criminal Cases Southwestern Law Journal, 1963, page 228 available at scholar.smu.edu/cgi/viewcontent.cgi?article=4179smulr ላይ ልዩ ሁኔታዎች የሚባሉት 1ኛ የተከሠሠበት የሀሠት ምስክርነት (መልስ) ጉዳይ ከራሡ ደብዳቤዎች ወይም ሰነዶች ጋር ከተጋጨ (ከተለያየ) (Document Exception) የደጋፊ ሠነድ ማስረጃ ደንብ መርህ ልዩ ሁኔታዎች ደገሞ (1ኛ) የተረጋገጠ ቀረፃ (Authenticated record) በተገኘ ጊዜ (2ኛ) የቀደመው ቃሉ (ምስክርነቱ) ሀሠት መሆኑን ራሡ ባመነ ጊዜ

[49] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 35 ገፅ 9፣ {To be guilty of perjury under section 1621(1), a defendat's false statements must be material. {A fales statement is material in a criminal prospection for perjury (a) if it is material to any proper matter of the Decision maker's inquiry, that is, if it is capable of influencing the tribunal on the issue before it.}

[50] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 45፣ ገፅ 386

ይዘቱ የሚከተለዉ ነዉ፡፡ (A) Whoever under oath or in any, declaration, certificate, verification, or statement under penalty of perjury as permitted under [Section] 1746 of title 28, United States Code, in any proceeding before or ancillary to any court or, grand jury of the United States knowingly makes any false material declaration or makes or uses any other information, including any book, paper, document, record, recording, or other material, knowing the same to contain any false material declaration, shall be fined under this title or imprisoned not more than five years, or both.[51]

የዚህ ድንጋጌ አቻ የአማርኛ ትርጉም በግርድፉ "የአሜሪካ አገራት ህግ ቁጥር 1746 ርዕስ 28 የፐርገሪ ቅጣትን ባስቀመጠዉ መሰረት ማንም ሰዉ ቃለ-መሃላ ፈፅሞ ወይም በማናቸዉም መግለጫ፣ የምስክር ወረቀት ወይም ሰነድ፣ ማረጋገጫ ወይም አባባል በአሜሪካ ፍርድ ቤቶች እና ከፍተኛ ጁሪዎች ፊት በየትኛዉም የክርክር ደረጃ በሚገኙ ጉዳዮች እያወቀ በማንኛዉም ዓይነት መረጃ ማለትም በመፅሀፍ፣ በወረቀት፣ በሰነድ፣ በቀረፃ ወይም በማንኛዉም መሳሪያ ተጠቅሞ ማንኛዉንም ሀሰተኛ ግዙፋዊ መግለጫ ከሰጠ ወይም ከሰራ ወይም ከተጠቀመ ወይም እዉነት ያልሆነ መግለጫ እንደያዘ እያወቀ ከተጠቀመ በዚህ ህግ መሰረት በመቀጮ ወይም ከአምስት አመት ባልበለጠ እስራት ወይም ሁለቱንም ይቀጣል" የሚል ይሆናል፡፡

በዚህ ህግ መሰረት መንግስት በተከሣሹ ላይ ማስረዳት ያለበት ፍሬ ነገሮች አጠር ባለ መልኩ ሲገለጹ፡-

- 1ኛ ተከሣሹ ወንጀሉን የሰራው እያወቀ መሆኑን፣
- 2ኛ የሰጠዉ ቃል ወይም የተጠቀመው ሰነድ ሀሰት ወይም የሚጣረስ መሆኑን፣
- 3ኛ ግዙፋዊ መግለጫ መሆኑን፣
- 4ኛ ቃለ-መሃላ የፈፀመ መሆኑን፣
- 5ኛ በአሜሪካ ግዛት ባሉ ፍርድ ቤቶች ወይም የጁሪ ሥርዓት መሆኑን ነው፡፡

የመጀመሪያዉ ነጥብ ይህን ድንጋጌ ከቁጥር 1621 የሚለየዉ የሀሳብ ክፍሉ ሆነ ብሎ ሳይሆን እያወቀ የሚል ነዉ፡፡ በመሆኑም ለማስረዳት ዉስብስብ አይሆንም፡፡ ሁለተኛዉ ጉዳይ የሰጠዉ

[51] ዝኒ ከማሁ፣ section 1623, (B) This section is applicable whether the conduct occurred within or without the United States. (C) An indictment or information for violation of this section alleging that, in any proceeding before or ancillary to any proceeding before or ancillary to any count or grand jury of the United States. The defendant under oath has knowingly made two or more declaration which are inconsistent to the degree that one of them is necessarily false, need not spicily which declaration is false if (1) each declaration was material to the point in question, and (2) each declaration was made with in the period of the statute of limitation for the offers charged under this section

ቃል ወይም የተጠቀመው ሰነድ የሚያረጋግጠዉ ፍሬ ነገር ሀሰት መሆን አለበት ይላል። ይህም ተከሳሹ የሰጠዉ ቃል የሚያሳስት ሆኖ ነገር ግን ግልፅ እዉነት ቢሆን እንደሀሰት አይቆጠርም።[52] በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጉዳዩ ሀሠት መሆኑን እያወቀ ሲባል ሀሠትነቱ የመነጨው ግራ ከመጋባት፣ ከስህተት ወይም ትውስታን ከማጣት በሆነ ጊዜ ሀሠት አይባልም፤ በመሆኑም የሀሠት መለኪያው ጉዳዩን ሀሠት እንደሆነ ማወቁ ነው ማለት ነዉ። በቁጥር 1621 ላይ እንደተመለከተዉ በተመሳሳይ ለምስክሩ ወይም ለተጠርጣሪዉ የቀረበለት ጥያቄ አሻሚ በመሆኑ የተነሳ የሀሰት ቃል ወይም መግለጫ ቢሰጥ ጥፋተኛ ለማለት አያስችልም። በመሆኑም የሀሰት ቃሉ ወይም መግለጫዉ መታየት ያለበት ከምስክሩ ሀሳብ ጋር በማገናዘብ ነዉ።[53] ከዚህ በተጨማሪ በቁጥር 1623 (c) ስር እንደተመለከተዉ አንድ ምስክር በአንድ ፍሬ ነገር ላይ ሁለት የተለያየና የሚጣረስ ማረጋገጫ ወይም ምስክርነት በሰጠ ጊዜ ከሁለቱ አንዱ ሀሠት ነዉ ማለት ነዉ። ይህንንም ለመለየት ተጨማሪ ማስረጃ ሳያስፈልግ ጥፋተኛ ለማስባል ያስችላል።[54] በሌላ አነጋገር የሁለት ምስክር ደንብ አይጠቀምም። ይህም ቁጥር 1623 (በፍርድ ቤትና በጁሪ ፊት የሚሰራ ፐርጉሪ ህግ) ከቁጥር 1621 (ጠቅላላ ፐርጉሪ) የሚለየዉ ዋናዉ ቁም ነገር ነዉ።

ሶስተኛዉ ፍሬ ነገር ግዙፋዊ ሀሰት ነዉ። ተከሣሽን ተጠያቂ ለማድረግ የሀሠት ምስክርነቱ ግዙፋዊ (material) ሊሆን ይገባል። ይህ ሲባል ዉሳኔ ሰጪዉ አካል (ፍርድ ቤቱ ወይም ጁሪዉ) ይህ ፍሬ ነገር በሀሰት ባይነገራቸዉ ኑሮ ይህን ዉሳኔ አይሰጡም ነበር የሚያስብል መሆን ይኖርበታል።

አራተኛዉ ነጥብ ቃለ-መሃላ የፈፀመ መሆኑ ነዉ። ፐርጉሪን ከሐሰተኛ ምስክርነት የሚለየዉ ምስክሩ በፍርድ ቤት ወይም በጁሪ ፊት እዉነቱን ለመናገር ወይም ለማቅረብ ቃለ-መሃላ የፈፀመ መሆኑ ነዉ። በመሆኑም እዉነቱን ለመመስከር ወይም ለማቅረብ ቃለ-መሃላ ፈፅሞ ወይም ማረጋገጫ ሰጥቶ ከፈፀመዉ ቃለ-መሃላ ወይም ከሰጠዉ ማረጋገጫ በተቃራኒ ከመሰከረ ጥፋተኛ ነዉ። በሁለቱ ቦታ የተሰጡ ምስክርነቶች ወይም መግለጫዎች በሆኑ ጊዜ በሁለቱም

---

[52] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 35 ገፅ 13፤

[53] ለምሳሌ ያህል (United States V. Strohm, 10th cir, 2011) ጉዳይ ችሎቱ ምስክር ለቀረበለት አሻሚ ጥያቄ የሰጠዉ መልስ ሐሰት እንደሆነ ካላወቀ ወይም ካላመነ በስተቀር በፐርጉሪ ጥፋተኛ ማድረግ አይቻልም በማለት ወስኗል።

[54] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 45፣ ገፅ 386፣ Subsection of 1623 (c) "The defendant under oath has knowingly made two or more declaration which are inconsistent to the degree that one of them is necessarily false, need not specify which declaration is false if **(1)** each declaration was material to the point in question, and **(2)** each declaration was made with in the period of the statute of limitation for the offers charged under this section."

ቦታ ቃለ-መሃላ የፈፀመ መሆን ይኖርበታል። ለምሳሌ በግራንድ ጁሪ ፊት ቃለ-መሃላ (oath) ሳይፈፅም በመደበኛ ፍርድ ቤት ጊዜ ቢፈፅምና ከሁለቱ አንዱ እርስ በእርሡ የሚጣረስ በሆነ ጊዜ በፐርጉሪ ጥፋተኛ ለማስባል በቂ አይሆንም[55]።

ሌላው በቁጥር 1623 እና በቁጥር 1621 መካከል ያለዉ ልዩነት ቃልን በማቃናትና በመለወጥ ረገድ ነዉ። በቁጥር 1623 ሀሠት መስካሪው እዛው በችሎቱ ፊት ቃሉን ለማረምና እውነቱን ለመመስከር ዕድል የሚሠጥ መሆኑ ነው። አንድ ፀሃፊ የቁጥር 1621 እና 1623 ዋናው ልዩነት ቃልን የማቃናት ዕድል ላይ ነው[56] ይላል። በመሆኑም ሀሠቱን ትቶ እውነቱን መናገር በቁጥር 1623 መሠረት ከመከሠስ ያድናል። በቁጥር 1621 ጊዜ ግን መከሠስ አይቀሬ ነው። ይህም ከፐርጉሪ ድንጋጌዎች ዋና ዓላማ ጋር ይጣጣማል። የድንጋጌው ዓላማ ምስክርነት እንደማያስከትል የሞዴል የወንጀል ህጋቸው አንቀፅ 241.1 (4) "Retraction, no reason shall be quality of an offense under this section it he retracted the falsification in the course of proceeding in which it was… made before it become manifest that the ratification was or would be exposed and before the falsification substantially affected the proceeding.[57] ስለዚህ አንድ ሠው የሀሠት ቃሉን ትቶ ወይም አስተካክሎ እውነቱን ከመሠከረ በቁጥር 1623 መሠረት ክሱ ከመቀበል ይታገዳል። በዚህ ጊዜም የፐርጉሪ ድንጋጌዎች ዋነኛ ዓላማ የሆነው እውነተኛ ምስክርነት ይገኛል ተብሎ ይታሠባል። ከዚህ አልፎ በክስ ጊዜም ቃሌን አስተካክዬ እውነቱን ስለአሣወኩ ክሱ ሊቋረጥልኝ ይገባል የሚል መከላከያ በተከሣሹ በኩል ሊቀርብ ይችላል። ተቀባይነትም ይኖረዋል። ነገር ግን ተከሣሹ ሀሠት መናገሩን ያመነው ወይም ሀሠቱን ትቶ እውነትን የተናገረው በፍርዱ ሂደት ላይ ከፍ ያለ ጉዳት ካላደረሠ እና ሀሠት መሆኑ በሌላ ማስረጃ ባልተደረሠበት ጊዜ ነው። ሀሠት ተናግሮ እንደነበረ መናዘዘ ያለበት በዚያው ችሎት ወይም የጁሪ ክስ መስማት ሂደት መሆን ይኖርበታል በግልፅ ማመኑን ማሣየት ይኖርበታል።[58]

---

[55] United States V. Jaramillo case at 9 circuit, 1995, (Circuit court - የሚባሉት የፌደራሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ናቸው። በኢትዮጵያ አደረጃጀት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች) ደረጃ ያላቸውን እንደሆነ ልብ ይላል።

[56] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 28፣ ገፅ 248፤ The most significant difference between these statutes is that a retraction bores section 1623 prosecution but not section 1671 prosecution.

[57] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 38፣ Article 241.1

[58] United States V. Wiggan, (9th Cir. 2012), in this case the court states that "recantation requires a defendant to renounce and withdraw the prior statement. And the defendant must unequivocally repudiate his prior testimony. It is not enough if the defendant merely attempted to explain his inconsistent Statements, but never really admitted to the facts in question."

3. ሀሰተኛ ምስክርነት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ.ፌ.ዲ.ሪ) የወንጀል ህግ አራተኛ መፅሃፍ አራተኛ ርዕስ ምዕራፍ ሁለት በፍትህ ሥራ ላይ ሊደረግ በሚገባው በእውነተኛነትና በታማኝነት ተግባር ላይ የሚፈፀም ወንጀል (የእንግሊዝኛው ቅጅ Perjury and Cognate[59] Crimes) በማለት ከአንቀፅ 452-458 ያሉትን ድንጋጌዎች አስፍሯል። ከአንቀፅ 452-455 ያሉት ድንጋጌዎች በአጠቃላይ ሲታዩ በፍትህ ሥራ እውነተኛነት ላይ የሚፈፀም ወንጀል (perjury) የሚባሉት የትኞቹ እንደሆኑ እንዲሁም ሀሰተኛ ምስክርነት ማለት ከፐርጉሪ በምን እንደሚለይ በግልፅ ለማወቅ ያስችግራል። ፐርጉሪ በሚለዉ ርዕስ ስር በተከራካሪ ወገን የሚሠጥ ሀሠተኛ ቃል (አንቀፅ 452)፣ በምስክር፣ በልዩ አዋቂ አስተያየት ሰጪ፣ በአስተርጓሚ የሚሠጥ ሀሠተኛ ምስክርነት (አንቀፅ 453) እና ሐሰተኛ ምስክርነት እንዲሰጥ መገፋፋትና ማግባባት (አንቀፅ 455) ተግባራትን እንደሆነ ተቀምጧል። በሌላ አነጋገር በዚህ ህግ አቀራረጽ ፐርጉሪ ሀሠተኛ ምስክርነትን የሚያካትት ይመስላል። ይሁንና ፐርጉሪና ሀሠተኛ ምስክርነት የተለያዩ ጽንሰ ሀሳቦች እንደሆኑ ከዚህ በፊት በቀረቡት የሌሎች አገራት የህግ ማዕቀፍ ልብ ይሏል።

በፐርጉሪ ስር የተካተቱት ድንጋጌዎች በዝርዝር ሲታዩ በተካራካሪ ወገን የሚሠጥ ሀሠተኛ ቃል የሚባለዉ ማንኛዉም ተከራካሪ ወገን በፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ባለዉ አካል ዘንድ ቀርቦ እዉነት እንዲናገር ታዞ በፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ባለዉ አካል በሚወስነዉ ጭብጥ ላይ አግባብነት ያላቸዉን ፍሬ ነገሮች በሚመለከት እያወቀ የሚሰጠዉ ሐሰተኛ ቃል ነዉ።[60] ቅጣቱም የሀሰት ቃል የሰጠዉ ሰዉ የፈለገዉ ዉጤት ሳይገኝ ቢቀርም ከአንድ አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ሐሰተኛዉን ቃል የሰጠዉ የወንጀል ክስ ሂደት ላይ ሆኖ ኢ-ፍትሐዊ ዉሳኔ ሊያስከትል የሚችል እንደሆነ ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት[61] እንደሆነ ተቀምጧል። ከዚህ ባለፈ ተከራካሪዉ ወገን እዉነቱን ለመናገር ምሎ ወይም ማረጋገጫ ሰጥቶ እንደሆነ በተለይም የተፈለገዉ ዉጤት በከፊል ወይም በሙሉ ተገኝቶ እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እስራት ይሆናል[62] በሚል የቅጣት ማክበጃ ሁኔታዎች ተቀምጠዋል። ነገር ግን ተከራካሪዉ ወገን ጥቅሙን ለማስከበር

[59] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 19 `cognate offences' are, a lesser offence that is related to the greater offense because it shares several of the elements of the greater offense and is of the same class or category.
[60] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 16 አንቀፅ 452(1)
[61] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 452 (1)
[62] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 452 (2)

ሲል ለሚያቀርበዉ ትክክለኛ ያልሆነ ክርክር የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የማይሆኑበት መሆኑ ተደንግጓል[63]።

የዚህ ድንጋጌ የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች፡-

- የሀሳብ ክፍሉ ማወቅ ነዉ።
- በፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን እዉነት እንዲናገር መታዘዝ።
- ሐሰተኛ ቃል የተሰጠባቸዉ ጉዳዮች ለሚወሰነዉ ነገር ወይም ለጭብጡ አግባብነት ያላቸዉ ወይም ለዉሳኔ አሰጣጥ ጠቃሚ የሆኑ ፍሬ ነገሮች መሆናቸዉ።
- ሐሰተኛ ቃል የተሰጠዉ በዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ባለዉ አካል ፊት መሆን የሚሉት ናቸዉ።

ሌላዉ በዚህ ህግ አንቀፅ 453 ሀሠተኛ ምስክርነት፣ አስተያየት ወይም ትርጉም በሚል ርዕስ የሰፈረዉ ድንጋጌ ነዉ። ሙሉ ይዘቱ 453(1) ሀሠተኛ ምስክርነት፣ አስተያየት ወይም ትርጉም "የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለው ሥርዓት በሚካሄድበት ጊዜ ምስክር ሆኖ የቀረበ ማንም ሠው ማንኛውንም ተከራካሪ ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት አስቦ ሐሠተኛ ምስክርነት ወይም የልዩ አዋቂነት አስተያየት የሠጠ እንደሆነ ወይም እውነቱን የደበቀ እንደሆነ ያቀደው ሀሳቡ ከግቡ ባይደርስለትም እንኳ በቀላል እስራት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ ከአምስት አመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል[64]ይላል። ንዑስ ቁጥር (2) ምስክሩ እውነቱን ለመናገር ምሎ ወይም ማረጋገጫ ሠጥቶ እንደሆነ በተለይም የተፈለገዉ ዉጤት በከፊል ወይም በሙሉ ተገኝቶ እንደሆነ ቅጣቱ ከአስር ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እስራት ነዉ። ሆኖም በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ በመስካሪዉ ድርጊት ምክንያት የጥፋተኝነት ዉሳኔ ተላልፎበት እንደሆነ ወይም ከአስር ዓመት ፅኑ እስራት በላይ ተፈርዶበት እንደሆነ የተመሰከረበት ሰዉ በስህተት በተወሰነበት ቅጣት ልክ ሐሰተኛ መስካሪዉ ሊወሰንበት ይችላል በሚል ተደንግጓል። (3) በዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ሥልጣን ባለዉ አካል በሚወሰን ጭብጥ አግባብነት ባለዉ ፍሬ ነገር ሀሰተኛ ትርጉም የሚሰጥ ማንኛዉም ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ እንደአግባቡ ከዚህ በላይ በንኡስ ቁጥር (1) እና (2) የተመለከተዉ ቅጣት ይወሰንበታል። (4) ሀሰተኛ ምስክርነቱ ወይም ልዩ አስተያየቱ፣ በሀሰት መተርጎሙ ወይም ማስተርጎሙ ተደርሶበት ፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት

[63] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 452 (3)
[64] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 453(1)

ነክ ስልጣን ያለው አካል በሚሰጠዉ ፍርድ ላይ ተፅዕኖ ሊያደርግ የማይችል እንደሆነ ቅጣቱ ከሁለት ዓመት የማይበልጥ ቀላል እስራት ነዉ።[65]

በመሰረቱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ሃተታ ዘምክንያት ላይ "አንቀፅ 453 የቀድሞውን ህግ አንቀፅ 447 የተካ ነው። የድንጋጌው ስያሜ ከይዘቱ ጋር የሚጣጣም ስለማይመስል ሀሠተኛ ምስክርነት አስተያየት ወይም ትርጉም በሚል እንዲሻሻል ተደርጓል። የቁጥር 447(1) መግቢያ ምስክር ሆኖ የቀረበ ሠው የአስተዳደር፣ የፍትሃብሔር፣ የወንጀል ወይም የሽምግልና ወይም የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለው ሥርዓት በሚፈፀምበት ጊዜ የሚለው ሃረግ የተንዛዛ በመሆኑ አጠር ባለ ሁኔታ የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለው ሥርዓት በሚካሄድበት ጊዜ በሚል በአጠቃላይ ሃረግ እንዲተካ ተደርጐ ተሻሽሏል"[66] በሚል ተመልክቷል።

በምስክር የሚሠጥ ሀሠተኛ ምስክርነትን በተመለከተ ድንጋጌዉ ከሚይዛቸዉ ፍሬ ነገሮች ዉስጥ የመጀመሪያዉ የሀሳብ ክፍሉ ነዉ። በድንጋጌዉ ላይ የተመለከተዉ የሀሳብ ክፍል ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ሀሳብ የሚለዉ ግልፅ አይደለም። ምክንያቱም የአማርኛዉ ምንባብ "...ምስክር ሆኖ የቀረበ ማንም ሠው ማንኛውንም ተከራካሪ ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት አስቦ ሀሠተኛ ምስክርነት ወይም የልዩ አዋቂነት አስተያየት የሠጠ እንደሆነ ወይም እውነቱን የደበቀ እንደሆነ ያቀደው አሣቡ ከግቡ ባይደርስለትም..." ይላል። ይህም ሆነ ብሎ ወይም አቅዶና አስቦ (purposely[67]) ተከራካሪ ወገኖችን ለመጉዳት ወይም ለመጥቀም ያደረገዉ መሆኑን ያሳያል። ነገር ግን የእንግሊዝኛዉ ቅጂ "...knowingly makes or gives a false statement or expert opinion, or hides the truth whether to the advantage or the prejudice of any party there to, is punishable, even where the result sought..." ይላል። የእንግሊዝኛዉ የሚመስለዉ እያወቀ (knowingly) ነዉ። ስለዚህ በዚህ ድንጋጌ ዉስጥ ያለዉ የሀሳብ ክፍል እያወቀ ወይስ ሆነ ብሎ ነዉ የሚለዉ ሊታይ ያስፈልጋል።

በወንጀል ህጉ አንቀፅ 58[68] ላይ እንደተመለከተዉ ዉጤትን ለማግኘት ብሎ ህገ-ወጥና የሚያስቀጣ ድርጊትን እያወቀ በራሱ ፍላጎት ማድረግ አንደኛዉ ቀጥተኛ ሀሳብ (እዉቀት

---

[65] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 453(2፣ 3፣ 4)

[66] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የተሻሻለዉ የወንጀል ህግ ሀተታ ዘምክንያት ገፅ 214 ያልታተመ

[67] ሆነ ብሎ የሚባለዉ የሀሳብ ክፍል እያወቀ ብቻ ሳይሆን የተለየ ፍላጎት ኖሮት ማድረግ ወይም አለማድረግ ነዉ።

[68] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 16 አንቀፅ 58 "ማንም ሰዉ አስቦ ወንጀል አደረገ የሚባለዉ (1) አንድ የተወሰነ ዉጤት ለማግኘት ብሎ ህገ-ወጥና የሚያስቀጣ ድርጊትን እያወቀ በራሱ ፍላጎት ያደረገ እንደሆነ ወይም (2) ድርጊቱ ህገ-ወጥና የሚያስቀጣ ዉጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ የሆነዉ ይሁን ብሎ ዉጤቱን በመቀበል ድርጊቱን ያደረገ እንደሆነ ነዉ።"

ሲደመር ፍላጎት) የሚባለዉ የሀሳብ ክፍል ነዉ። ድርጊቱ ህገ-ወጥና የሚያስቀጣ ዉጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ የሆነዉ ይሁን ብሎ ዉጤቱን በመቀበል ድርጊቱን ማድረግ ሁለተኛዉ ቀጥተኛ ያልሆነ ሀሳብ (እያወቀ) የሚባለዉ የሀሳብ ክፍል ነዉ። የሁለቱ ልዩነታቸዉ ዉጤቱን በመፈለግ ረገድ ነዉ። ዉጤቱን ለማሳካት ተብሎ በእዉቀትና በራስ ፍላጎት የሚፈፀም ወንጀል ሆነ ብሎ ሊባል ይችላል። ነገር ግን ዉጤቱን ሳይፈልግ ወይም ዉጤቱ ሳያስጨንቀዉ በእዉቀት የሚፈፀም ወንጀል ከሆነ እያወቀ ሊባል እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል። በዚህ መሰረት በአንቀፅ 453 ላይ የሚታየዉ የሀሳብ ክፍል እዉቀትና ዉጤቱን መፈለግ (ዕቅድ) ናቸዉ። ምክንያቱም ከድንጋጌዉ ላይ ...ያቀደዉ አሳቡ ከግብ ባይደርስለትም... የሚለዉ አገላለፅ ድርጊቱን የፈጸመዉ ዉጤቱን በመፈለግ ነዉ። ይህ ከሆነ ደግሞ በፀሃፊዉ እምነት የሀሳብ ክፍሉ እዉቀትና ፍላጎት ነዉ።

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ዉስጥ ተገልፀዉ የሚገኙት ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች አስቦ ወይም በቸልተኝነት የሚሉ ናቸዉ። ከዚህ ባለፈ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ አሳብ በሚል የተቀመጠ አላገኘሁም። በዚህ ጊዜ አስቦ ወንጀል ማድረግን ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ብሎ መከፋፈሉ በተግባር የማይሰራበት ንድፈ-ሃሳባዊ ጉዳይ ነዉ የሚል ነገር ሊነሳ ይችላል። ይሁንና የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 88/2/ እንደሚነግረን ቅጣት ሊወሰን የሚገባዉ፣ የወንጀል አድራጊዉን ግላዊ የአደገኛነት መጠን፣ ያለፈ የህይዎት ታሪኩን፣ ወንጀል ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያቶችና የአሳቡን ዓላማ፣ የግል ኑሮዉን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን ነዉ ይላል።[69]

በፀሃፊዉ እምነት ክስ ሲመሰረት አስቦ ወይም በቸልተኝነት የሚለዉ የወንጀሉ ማቋቋሚያ ሞራላዊ ፍሬ ነገር ተለይቶ ይቀርባል። ፍርድ ቤቱም አስቦ ወይም በቸልተኝነት የሚለዉ የወንጀሉ ማቋቋሚያ ሞራላዊ ፍሬ ነገር ለይቶ በተገቢዉ ድንጋጌ መሰረት ጥፋተኛ ይላል። ከዚህ በኋላ ቅጣት ሲያሳርፍ ወንጀል ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያቶችና የሀሳቡን ዓላማ በመመርመር ቀጥተኛ የሀሳብ ክፍል ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ሀሳብ መሆኑን ወይም የታወቀ ቸልተኝነት ወይም ያልታወቀ ቸልተኝነት የሚሉት ጉዳዮች ከግምት ዉስጥ ሊገቡ ይገባል። ይህንን ሀሳብ የሚያጠናክረዉ በተሻሻለዉ የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ዓ.ም አንቀፅ 19(5) የቅጣት ደረጃን ለመወሰን የወንጀሉን አፈፃፀም ሁኔታ፣ የደረሰዉ ጉዳት ዓይነትና መጠን፣ የተገኘዉ ጥቅም መጠን ወንጀሉ ታስቦ የተሰራ መሆን አለመሆኑ፣ ወንጀሉ በቸልተኝነት ሲሰራ የሚያስቀጣ ከሆነ ቸልተኝነቱ የታወቀ ወይም ያልታወቀ ቸልተኝነት መሆኑ

[69] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀፅ 88(2)

ከግምት ውስጥ ይገባል[70] በሚል የተገለጸው ድንጋጌ ነው። እነዚህ ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ ስናስገባቸው ወንጀለኛው ወንጀሉን ሲፈፅም ውጤቱን በመቀበል ነው ወይስ ውጤቱ የሆነው ይሁን ብሎ ነው የሚለው ነጥብ ይታወቃል። በዚህ ጊዜ አስቦ ወንጀል ማድረግን ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ብሎ መከፋፈሉ በተግባር ይዉላል ማለት ነው። ከዚህ ድንጋጌ የሀሳብ ክፍል ጋር ሊነሳ የሚገባው ነጥብ ከሳሽን ወይም ተከሳሽን የማይጠቅም ወይም የማይጎዳ ሀሰተኛ ምስክርነት ወይም የልዩ አዋቂ አስተያየት ወይም ትርጉም በዚህ ድንጋጌ የማያስቀጣ መሆኑ ነው። በመሆኑም ይህንን የሀሳብ ክፍል የማስረዳት ግዴታ የከሳሽ ነው።

ሁለተኛው ፍሬ ነገር ማንም ሰዉ የሚለዉ ነው። በንኡስ ቁጥር 1 ላይ እንደተመለከተዉ ***"...ምስክር ሆኖ የቀረበ ማንም ሰዉ ...ሐሰተኛ ምስክር ወይም የልዩ አዋቂነት አስተያየት የሰጠ ወይም እዉነቱን የደበቀ እንደሆነ..."*** የሚለዉ አገላለፅ የተፈጥሮ ሰዉን ብቻ የሚመለከት ነዉ ወይስ የህግ ሰዉነት ያለዉን ሰዉ ይጨምራል የሚለዉ ግልፅ አይደለም። በሀተታ ዘምክንያቱ ላይም የተባለ ነገር የለም። በእርግጥ ከተፈጥሮ ሰዎች ዉጭ ያለ አካል የምስክርነት ቃል ወይም የልዩ አዋቂነት አስተያየት ይሰጣል ወይ የሚለው አጠያያቂ ሊሆን ይችላል። በፀሃፊዉ እምነት ከተፈጥሮ ሰዎች ዉጭ ያሉ አካላት የምስክርነት ቃል ወይም የልዩ አዋቂነት አስተያየት ወይም የትርጉም ስራን በሚመለከት የሀሰት ቃል ወይም አስተያየት ወይም ትርጉም የሚሰጡበት አጋጣሚ ቢኖር በዚህ ህግ ለመጠየቅ ይቻላል።

ሶስተኛው ፍሬ ነገር የምስክሩን መማል ወይም ማረጋገጫ መስጠት የሚመለከተዉ ነዉ። በዚህ ድንጋጌ ንኡስ ቁጥር 2 ላይ እንደሰፈረዉ የምስክሩ መማል ወይም እዉነቱን ለመናገር ማረጋገጫ መስጠት ቅጣት የሚያስከትሉ ሁኔታዎች እንጂ ወንጀሉን ለማቋቋም የሚያስፈልጉ ፍሬ ጉዳዮች አይደሉም።

አራተኛው ፍሬ ነገር ሀሠተኛ ምስክርነት የተሰጠዉ የት ነዉ የሚለዉ ነው። በንዑስ ቁጥር 1 ላይ የሰፈረዉ ***"የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለው ሥርዓት በሚካሄድበት ጊዜ..."*** የሚለዉ አገላለፅ ለትርጉም የተጋለጠ ነዉ። ይህንንም ጉዳይ አስመልክቶ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ

[70] የተሻሻለዉ የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ 2006 ዓ.ም፣ ቁጥር 2፣ አዲስ አበባ፣ አንቀፅ 19(5)

ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 153228 በቀን 24/01/2011 ዓ.ም የሀሠተኛ ምስክርነት ክርክርና ውሳኔ አስተላልፏል፡፡[71]

ጉዳዩ በወረዳ ፖ/ሊስ ጣቢያ ምስክርነት የሰጡ ሠዎች በወረዳዉ ፍርድ ቤት የዐቃቢ ህግ ምስክር ሆነው ሲቀርቡ በፖ/ሊስ ጣቢያ ከሰጡት ቃል በተለየ መሠከሩ፡፡ በዚህ ጊዜ የዞኑ ዐቃቢ ህግ በፖ/ሊስ ጣቢያ የመሠከሩበትን ሠነድና በወረዳዉ ፍርድ ቤት የመሠከሩበትን መዝገብ ማስረጃ በማድረግ ክስ መሠረተባቸው፡፡ የዞኑ ፍርድ ቤትም የሁለቱ ሠነዶች ቃል መለያየቱን አረጋግጦ በወረዳዉ ፍርድ ቤት ላይ ሀሠተኛ ምስክርነት ሠጥተዋል በማለት ቅጣት አስተላለፈባቸው፡፡ ግለሰቦቹ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቀረቡ፡፡ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱም በፖ/ሊስ ጣቢያ የተሠጠ የምስክርነት ቃልን በፍርድ ቤት ከተሠጠ የምስክርነት ቃል ጋር አነፃፅሮ ሀሠተኛ ምስክርነት ነዉ ለማለት አይቻልም፤ የወንጀል ህግ አንቀፅ 453 የሚሸፍነው ዳኝነትን ወይም ዳኝነት ነክነት ሂደት ላይ የሚሠጥን ምስክርነት ነው፤ ፖ/ሊስ ጣቢያ ደግሞ ዳኝነት ወይም ዳኝነት ነክነት አይደለም በማለት የዞኑን ፍርድ ቤት ውሣኔ ሻረው፡፡ የክልሉ ሰበር ሠሚ ችሎትም የጠቅላይ ፍርድ ቤቱን ውሣኔ አፀና፡፡

በዚህ ጊዜ የክልሉ ፍትህ ቢሮ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሠሚ ችሎት አቤቱታውን እንደሚከተለው አቀረበ፡፡ “የፖ/ሊስ ተቋም የዳኝነት ነክነት ተቋም አይደለም ተብሎ በስር ፍርድ ቤት የተሠጠው ትርጉም መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት ይታረምልኝ” አለ፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቱ አቤቱታውን ያስቀርባል በማለቱ ግለሠቦቹ ቀርበው የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ የህግ ስህተት የለበትም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፖ/ሊስ ተቋም የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለው ሥርዓት አይደለም የሚለው አተረጓጎም ስህተተ አለበትን የሚለውን በጭብጥነት ይዞ እንደሚከተለው ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ “ዳኝነት እና ዳኝነት ነክነት ለሚሉት ቃላት ትርጉም መፈለግ ግድ ይላል፡፡ የእነዚህ ቃላት ትርጉም በሀገራችን የህግ ኮዶች ወይም መዝገበ ቃላት ላይ በቀጥታ ማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑ የBlack’s Law Dictionary ትርጉም ማየት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሠረት Judiciary the branch of government with judicial power quasi-Judicial hold hearings weigh evidence and draw conclusions from them, as basis for their official action, and to exercise discretion of judicial nature የሚል ትርጉም አለው፡፡ Judiciary መደበኛው ፍርድ

[71]የአብክመ ፍትህ ቢሮ ከእነ ፈንቱ ንጉስ፤ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፤ 2011፤ በሰበር መዝገብ ቁጥር 153228 ዉሳኔ ያልታተመ

ቤትን የሚመለከት ሲሆን የዳኝነት ነክነት ሥራ የሚካሄድበት ደግሞ በዳኝነት መልክ ወይም መሠል ሁኔታ ክርክር የሚሠማበት የቀረበለት ማስረጃ ተመዝኖ ከድምዳሜ የሚደረስበትና የበኩሉን ውሣኔ የሚሠጥበት ተቋም ነው። በዚህ ረገድ ተጠቃሽ የሆኑት ተቋማት እንደግብር ሠሚ ጉባኤ፣ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ፣ የግልግል ተቋማትና ሌሎችም መሠል ከፊል የዳኝነት ሥልጣን ያላቸውን የሚመለከት ነው... በመሆኑም በወንጀል ምርመራ ወቅት ምስክሩ የሚሰጠው ቃል ልክ እንደመደበኛው የዳኝነት አካል ወይም የዳኝነት ነክነት ወይም መሠል ተቋም ቃለ መሀላ ፈፅሞ ምስክርነት የሚሰጥበት ባለመሆኑ በወንጀል ህግ አንቀፅ 453 ስር አይሸፈንም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሠሚ ችሎትና ሠበር ሠሚ ችሎት የሰጡትን ውሣኔ አፅንቷል።

ይህ ዉሳኔ ሁለት የተለያዩ ሀሳቦችን ሊያስነሳ ይችላል። ይኸዉም በአንድ በኩል የዳኝነት (ነክነት) ሥርዓት በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር የሚጀምረዉ በተከሳሽ ላይ ምርመራ በማካሄድ ነዉ። በዚህ የምርመራ ሂደት ላይ ምስክር ሆነዉ የሚቀርቡ ሰዎች እዉነቱን መናገር ይጠበቅባቸዋል። ትክክለኛ ፍትህ ለማረጋገጥ ትክክለኛና እዉነተኛ የፖሊስ ምርመራ እንዲሁም የዐቃቤ ህግ ክስ ወሳኝና የማይታለፍ መስመር ነዉ። እንደዚህ ከታሰበ ደግሞ በምርመራ ወቅት ሀሰተኛ ምስክርነት የሰጠ ሰዉ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን ግድ ይላል። ስለሆነም የዳኝነት (ነክነት) ሥርዓት የፖሊስ ምርመራን ይጨምራል ተብሎ መተርጎም ዉጤታም የአተረጓጎም ዘዴ ነዉ። አለበለዚያ በፖሊስ ምርመራ ወቅት ሀሰተኛ ምስክርነት የሰጡ ሰዎች የሚጠየቁበት ሌላ ድንጋጌ የለም የሚል ነዉ።

በሌላ በኩል ሀሠተኛ ምስክርነት፣ አስተያየት ወይም ትርጉም የተሠጠዉ ወይም እዉነቱ የደበቀዉ የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለው ሥርዓት በሚካሄድበት ጊዜ የሚለዉ አገላለፅ የሚያሳየዉ የዳኝነት ሥርዓት የሚካሄድበትን መደበኛ ፍርድ ቤቶች እና የዳኝነት ነክነት ሥርዓት የሚካሔድባቸዉን መሰል ፍርድ ቤቶች ነዉ። መሰል ፍርድ ቤቶች የሚባሉት ዉሳኔ የሚሰጡ፤ የተሰጠዉ ዉሳኔም ሊፈፀም የሚችል ነዉ። በፖሊስ ምርመራ የማከናወን ተግባሩ መሰል ፍርድ ቤት አያስብለዉም የሚል ሀሳብ ይነሳል። የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አተረጓጎምም በዚህ አስተሳሰብ የተመሰረተ ነዉ።

በፀሃፊዉ እምነት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አተረጓጎም ትክክል ነዉ። ምክንያቱም የወንጀል ህጉ የአንቀፅ 452 እና 453 አቀራረፅ ሲታዩ 452 “ማንኛዉም ተከራካሪ

ወገን በፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ነክ ሥልጣን ባለዉ አካል ዘንድ ቀርቦ እዉነት እንዲናገር ታዞ…" የእንግሊዝኛዉ ቅጂ "Any party to proceedings before a judicial or quasi-judicial tribunal who being required to speak the truth,…" ይላል፡፡ ፍርድ ቤት የሚለዉን ቃል በእንግሊዝኛዉ judicial በሚል ሲጠቀም የዳኝነት ነክ ለሚለዉ ደግሞ quasi-judicial ይላል፡፡ ፍርድ ቤትን judicial በሚል መግለፁ ጉዳዮን ግልፅ ያደርገዋል፡፡ quasi-judicial የሚለውን ደግሞ ፍርድ ቤት መሰል ማለት ይቻላል፡፡ quasi[72] የሚለዉ ቃል ስረ-መሰረቱ የላቲን ቃል ሲሆን ትርጉሙም የሚመሳሰል እንደማለት ነዉ፡፡ ይህ ቃል ከሌሎች ቃላት ጋር በመጣመር ተመሳሳይ ባህርይ ነገር ግን በተወሰነ መልኩ የሚለይ ትርጉም ቃላቶቹ እንዲኖራቸዉ ያደርጋል፡፡[73] በመሆኑም ዳኝነት ነክ ማለት የፖሊስ የወንጀል ምርመራ ስራን ያካትታል ለማለት አያስደፍርም፡፡ የአንቀፅ 453 ድንጋጌ አማርኛ ምንባብ የሚነግረን "የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ያለው ሥርዓት በሚካሄድበት ጊዜ… የሚል ሲሆን እንግሊዝኛዉ "…in judicial or quasi-judicial proceedings…" የሚል ነዉ፡፡ አንቀፅ 452 በግልፅ ፍርድ ቤት ሲል በዚህኛዉ ድንጋጌ ደግሞ ዳኝነት ይላል፡፡ ነገር ግን የእንግሊዝኛዉ ቅጂ ሁለቱንም judicial ይላል፡፡ ስለዚህ ዳኝነት ማለቱ ፍርድ ቤት ማለቱ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ዳኝነት ነክነት ማለቱም ከአንቀፅ 452 ጋር በተመሳሳይ መሰል ዳኝነት ማለቱ ነዉ፡፡ በተጨማሪም የወንጀል ህጉ ሀተታ ዘምክንያት እንደሚነግረን አንቀፅ 453 የ1949 ዓ.ም የወንጀል ህግ አንቀፅ 447ን የተካ ነዉ፡፡[74] ይህም በሁለቱ ድንጋጌዎች መካከል የአቀራረብ እንጂ የጎላ የፅንሰ-ሀሳብ ልዩነት አለ ለማለት አያስችልም፡፡ በዚህ መልኩ ከተረዳነዉ በቀድሞዉ ህግ ላይ የአስተዳደር፣ የፍትሃብሔር፣ የወንጀል ወይም የሽምግልና ወይም ዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት በሚል አመላካች በሆነ ሁኔታ መቀረፁን ስናይ መሰል ፍርድ ቤት የሚባሉት የአስተዳደር ፍርድ ቤት፣ የሽምግልና ዳኝነት ወዘተ እነደሆኑ ያሳያል፡፡ በመሆኑም የሰበሩ አተረጓጎም ያሳምናል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አተረጓጎም በአንቀፅ 453 ላይ ያለዉ ተፅዕኖ ምንድን ነዉ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ከዉሳኔዉ ይዘት እንደምንረዳዉ ፖሊስ ጣቢያ ላይ የሐሰተኛ ምስክርነት መስጠት በአንቀፅ 453 መሰረት ክስ ለማቅረብና ለማስቀጣት አያስችልም፡፡ ይሁንና ምስክሩ በመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በሌሎች መሰል ፍርድ ቤቶች ቀርቦ ማንኛውንም

---

[72] Etymologically is comes from Latin, it means as if, or analogous. But in legal sense the term denotes that one subject has certain characterstics in common with another subject, but that intrinsic and material differences exit between them.

[73]Quasi-a combining form meaning "resembling," "having some, but not all of the features of": quasi-definition; quasi-scientific, quasi contract…

[74] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 65 ገፅ 214

ተከራካሪ ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት አስቦ የሰጠዉ ሀሰተኛ ምስክርነት ወይም የደበቀዉ እዉነት ካለ ይህንን በማስረዳት ተጠያቂ ማድረግ ይቻላል፡፡ በሌላ አነጋገር በመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በሌሎች መሰል ፍርድ ቤቶች ምስክሩ በሀሰት የሰጠዉ ቃል ወይም የደበቀዉ እዉነት አለ ብሎ ክስ ለመመስረትና ለማስቀጣት የሚያቀርበዉ ማስረጃ ፖሊስ ጣቢያ ላይ የሰጠዉ የምስክሩ ቃል ብቻ መሆን የለበትም፡፡ ይልቁንም ሌሎች የሰዉና የሰነድ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይጠበቅበታል ማለት ነዉ፡፡ የክሱ መነሻ ፍርድ ቤት ላይ የተሰጠዉ ቃል ሀሰት ነዉ ወይም በፍርድ ቤት ላይ በተሰጠዉ ቃል የተደበቀ እዉነት አለ የሚል መሆን አለበት፡፡ ሲጠቃለል የሰበሩ ዉሳኔ አንቀፅ 453ን የሻረ ሳይሆን የማስረጃ አቀራረቡን ሌላ መልክ ያስያዘ ነዉ፡፡ በፖሊስ ላይ የተሰጠዉ የምስክሩ ቃል ግን እንደ ተጨማሪ ማስረጃ ሆኖ መቅረብን የሚከለክል ህግ እንደሌለ ልብ ይሏል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ ሀተታ ዘምክንያት ላይ አንቀፅ 453 በቀደሞው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀፅ 447 የተተካ መሆኑ ቢገለፅም ጠቃሚ የነበሩ የቀድሞው ድንጋጌ ይዘቶች በትክክል በአዲሱ የወንጀል ህግ ላይ አልተካተቱም፡፡ በተለይም በቀድሞው ህግ ላይ ***"... ለክርክሩ ግልፅ በሆኑ ምክንያቶች ላይ ሆነ ብሎ ሀሠተኛ ምስክርነት ቃል የሠጠ እንደሆነ..."*** የሚለው አገላለፅ በአዲሱ ህግ ላይ የለም፡፡ ይህም ለአሻሚ ጥያቄ በተሰጠ ምላሽ ላይ ምስክርን ወይም ተጠርጣሪን በፐርጉሪ ወይም በሀሰተኛ ምስክርነት ጥፋተኛ ማስባል አይቻልም ከሚለዉ ጠቅላላ አስተሳሰብ ጋር አብሮ አይሄድም፡፡ አንድ ፀሃፊ The literal falsity rule is the principle that ambiguous questions cannot produce perjuries answers. That is, when there is more than one way of understanding the meaning of a question, and the witness has answered truthfully as to his understanding, he cannot be held liable for perjury[75] **በሚል አስቀምጧል፡፡ ይህም ወደ አማርኛ ስንመልሠው የቃል በቃል ሀሰት መርህ ማለት አሻሚ ጥያቄዎች በቀረቡ ጊዜ የሚሠጡ ምላሾች የፐርጉሪ ወይም የሀሰተኛ ምስክርነት ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር አያሟሉም፡፡**[76]

---

[75] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 3 ገፅ 180

[76] ዝኒ ከማሁ ገፅ 205፤ {ለምሳሌ የቀድሞዉ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ክሊንተን ከወ/ሪት ሞኒካ ለዎንስኪ ጋር በነበራቸዉ የፆታዊ ጥቃት (ትንኮሳ) ጉዳይ ከሳሽ ለፕሬዝዳንት ክሊንተን ከሞኒካ ለዎንስኪ ጋር ፆታዊ ግንኙነት ኖሮዎት አያዉቅምን ሲል ጠይቋቸዉ እርሳቸዉም ከሞኒካ ለዎንስኪ ጋር ፆታዊ ግንኙነት በፍፁም ኖሮኝ አያዉቅም አሉ፡፡ ይህ መልሳቸዉ አሳሳች ነበር፡፡ ምክንያቱም ፆታዊ ግንኙነት የሚለዉ ትርጉም እርሳቸዉ የታመበትን ጉዳይ አያካትትም ነበር፡፡ ነገሩን ግልፅ ለማድረግ የጽሁፉን ሙሉ ሀሳብ እንዳለ በሚከተለዉ መልኩ አስቀምጨዋለሁ፡፡ ምናልባት ቃላቶቹ ፀያፍ ከሆነ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡ During the deposition, Clinton was asked "Have you ever had sexual relations with Monica Lewinsky, as that term is defined in Deposition Exhibit 1?" The judge ordered that Clinton be given an opportunity to review the agreed definition. Afterwards, based on the definition created by the Independent Counsel's Office, Clinton answered, "I have never had sexual relations with Monica Lewinsky." Clinton later

የቀረቡትን ጥያቄዎች ከአንድ በላይ መልዕክት (ግንዛቤ) የሚሰጡ በሆኑ ጊዜ ምስክሩ እሡ በገባው ልክ እውነት ነው ያለውን ከመለሠ ፐርገሪ ወይም የሀሰተኛ ምስክርነት አይሆንም እንደማለት ነው። በመሆኑም የጠያቂው ግዴታ ግልፅ ጥያቄ ማቅረብ እንደሆነ የቀድሞው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቢያስቀምጥም አንቀፅ 453 ይህንን ፍሬ ጉዳይ አለማካተቱ ተገቢ አይደለም። ሌላዉ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ የሀሳብ ክፍሉ በግልፅ ሆነ ብሎ በሚል አስቀምጧል። አንቀፅ 453 ከላይ እንደተመለከትነዉ ግልፅነት ይጎለዋል። የወንጀለኛ መቅጫ ህጉ የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት እነማን ናቸዉ የሚለዉንም የአስተዳደር፣ የፍትሃብሔር፣ የወንጀል የሽምግልና ዳኝነት የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት በማለት ዘርዝሯል። ይህም ከተዘረዘሩት የዳኝነት ወይም የዳኝነት ነክነት ማለቱ የአስተዳደር፣ የፍትሃብሔር፣ የወንጀል የሽምግልና ዳኝነት ሲሆኑ ሌሎች ግን የዳኝነት ነክነት እንዲሆኑ ያሳያል።

---

stated, "I thought the definition included any activity by [me], where [I] was the actor and came in contact with those parts of the bodies" which had been explicitly listed (and "with an intent to gratify or arouse the sexual desire of any person"). In other words, Clinton denied that *he* had ever contacted *Lewinsky's* "genitalia, anus, groin, breast, inner thigh, or buttocks", and effectively claimed that the agreed-upon definition of "sexual relations" included *giving* oral sex but excluded *receiving* oral sex. ለዚህ ውዝግብ መነሻዉ ፆታዊ ግንኙነት የሚለዉ ትርጉም ነዉ። ፆታዊ ግንኙነት ትርጉም "A person engages in "sexual relations" when the person knowingly engages or causes- (1) Contact with the genitalia, anus, groin, breast, inner thigh, or buttocks of any person with anintent to arouse or gratify the sexual desire of any person". የሚል ነዉ። በመሆኑም በሀሰተኛ ምስክርነት ክስ ጊዜ የሚቀርቡ ጥያቄዎች አሻሚ መሆን የለባቸዉም።

ማጠቃለያና ምክረ-ሃሳብ

ሀሰተኛ ምስክርነት በእንግሊዝ የህግ ማዕቀፍ ዉስጥ ማንኛውም ሠው ከዳኝነት ሥርዓት ዉጭ ለማንኛውም ዓላማ ሲባል ቃለ-መሃላ ፈፅሞ ወይም ያለ ቃለ-መሃላ ምስክርነት እንዲሠጥ በህግ ሲጠየቅ ወይም ሲታዘዝ ለሚፈለገዉ ዓላማ ጠቃሚና ተፅዕኖ በሚፈጥሩ ጉዳዮች ላይ ሀሠት እንደሆነ እያወቀ ወይም እውነት እንዳልሆነ እያመነ የሚሠጠው ቃል ነዉ። በአሜሪካ ህግ ሀሰተኛ ምስክርነት ማንም ሰዉ በሁሉም መንግስት አካላት ስልጣን ስር በሆኑ ጉዳዮች እያወቀና በፈቃዱ ግዙፋዊ ነገሮች በማታለል፣ በማስመሰል ወይም በማናቸዉም መሳሪያ የዋሸ፣ የሸሸገ፣ የደበቀ ወይም ማንኛዉም ግዙፋዊ ነገሮችን በሀሰት፣ በፈጠራ፣ በማጭበርበር የሰራ ወይም ዉክልናዎችን ያዘጋጀ ወይም ግዙፋዊ ነገሮች ሐሰት፣ ፈጠራዊ፣ የተጭበረበሩ እንደሆኑ የሚታወቁ ማናቸዉንም ሀሰተኛ ዕሁፎች ወይም ሰነዶች ያዘጋጀ ወይም የተጠቀመ እንደሆነ ተደንግጓል።

ፐርገሪ በአገረ እንግሊዝ ህግ ማንኛውም ሠው የዳኝነት ሥነ-ሥርዓት በሚካሔድበት ጊዜ በህግ መሠረት መሃላ ፈፅሞ ምስክር ወይም አስተርጓሚ ሆኖ ሲቀርብ ለክርክሩ አወሣሠን ጠቃሚ በሆነ ጉዳይ ላይ ሀሠት እንደሆነ እያወቀ ወይም እውነት እንዳልሆነ እያመነ በፈቃዱ የሠጠው የሀሰት ምስክርነት ነዉ። በአሜሪካ ህግ ፐርገሪ ጠቅላላና በፍርድ ቤቶች የሚፈጸም ተብሎ ይለያያል። ጠቅላላ ፐርገሪ የሚባለዉ ማንም ሰዉ የአሜሪካ አገራት ህግ ቃለ-መሃላ እንዲደረግ በሚፈቅድባቸዉ ጉዳዮች ስልጣን ባለዉ አስተዳደር፣ ሀላፊ ወይም ሰዉ ፊት ምሎ ሲመሰክር፣ ሲያስረዳ ወይም ሲያረጋግጥ በቃለ-መሃላዉ መሰረት ካልሆነ ወይም እዉነት እንዳልሆነ እያመነ ማንኛዉንም ግዙፋዊ ጉዳይ ሲያሳዉቅ ነዉ። በፍርድ ቤቶች የሚፈፀመዉ ፐርገሪ ደግሞ ማንም ሰዉ ቃለ-መሃላ ፈፅሞ ወይም በማናቸዉም መግለጫ፣ የምስክር ወረቀት ወይም ሰነድ፣ ማረጋገጫ ወይም አባባል በአሜሪካ ፍርድ ቤቶች ወይም ከፍተኛ ጁሪዎች ፊት በየትኛዉም የክርክር ደረጃ በሚገኙ ጉዳዮች እያወቀ በማንኛዉም ዓይነት መረጃ ማለትም በመፅሀፍ፣ በወረቀት፣ በሰነድ፣ በቀረፃ ወይም በማንኛዉም መሳሪያ ተጠቅሞ ማንኛዉንም ሀሰተኛ ግዙፋዊ መግለጫ ከሰጠ ወይም ከሰራ ወይም ከተጠቀመ ወይም እዉነት ያልሆነ መግለጫ እንደያዘ እያወቀ ከተጠቀመ ነዉ።

ከእነዚህ አገራት ህግ የምንረዳዉ ሀሰተኛ ምስክርነት ከዳኝነት አካል ዉጭ በህግ ማስረጃ ለመቀበል ወይም ለማጣራት ስልጣን በተሰጣቸዉ ኃላፊዎች ወይም መስሪያ ቤቶች የሚሰጥን

የሀሰት ቃል ወይም ሰነድ የሚመለከት ነዉ። በአንፃሩ በዳኝነት አካል ፊት የሚሰጥ የሀሰት ቃል ወይም ሰነድ ፐርጉሪ እንደሆነ ነዉ። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ህግ አቀራረፅ ደግሞ ሀሰተኛ ምስክርነት ወይም ቃል ወይም የልዩ አዋቂ አስተያየት ወይም ትርጉም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክነት አካል ፊት የተሰጠ የሀሰት ቃል ወይም የተደበቀ እዉነት ነዉ ከዚህ አንፃር ፐርጉሪ ይመስላል። በሌላ በኩል ቃለ-መሃላ መፈፀም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ህግ የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር ባለመሆኑ ሀሰተኛ ምስክርነት ይመስላል። ሲጠቃለል በዚህ ህግ ላይ የሰፈሩት ድንጋጌዎች የግድ እንደ ሌሎች አገራት መሆን አለባቸዉ ባይባልም በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ ሀሰተኛ ምስክርነትን እና ፐርጉሪን የቀላቀሉ ናቸዉ። በመሆኑም የሚከተሉትን ምክረ ሃሳቦች አቀርባለሁ።

- ከዳኝነት ወይም ከዳኝነት ነክነት አካላት ዉጭ በሌሎች በህግ ማስረጃ እንዲቀበሉና እንዲመረምሩ ስልጣን በተሰጣቸዉ መስሪያ ቤቶች ወይም ኃላፊዎች ፊት እያወቁ ሀሰተኛ ምስክርነትን ወይም ሰነድን የሚሰጡ ወይም እዉነቱን የሚደብቁ ሰዎች ሊቀጡበት በሚያስችል መልኩ የወንጀል ህጉ ቢሻሻል።
- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ህግ አንቀጽ 453 ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ ድንጋጌዉን የሻረ ሳይሆን የማስረጃ አቀራረብ ልምዱ ትክክል እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው። በመሆኑም የጋራ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ስልጠና ለዳኞች፣ ለዐቃቢ ህጎችና ለመርማሪ ፖሊሶች የአብክመ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እና የህግ ምርምር ኢንስቲትዩት ቢሰጥ።
- በፖሊስ ወንጀል ምርመራ ጊዜ ሀሰተኛ ቃል ወይም ሀሰተኛ ማስረጃ የሚያቀርብ ሰዉ የሚቀጣበት ህግ ሊኖር ይገባል የሚለዉ አስተያየት እንደተጠበቀ ሆኖ በአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታ ሁሉም ፖሊስ የወንጀል ምርመራ አሰራር ህጉን የተከተለ ነዉ ለማለት ያስቸግራል። በተለይም ፖሊስ ያልመሰከርኩትን ዓፈብኝ፤ እንደዚህ ብለህ መስክር ብሎ አስፈራራኝ ወዘተ የመሳሰሉ እሮሮዎች በመርማሪ ፖሊሶች ላይ እንደሚነሱ ከስራ ልምዴ አዉቃለሁ። በመሆኑም አቅም በፈቀደ ልክ በወንጀል ምርመራ ቦታዎች ዉስጥ መቅረፀ ምስልና ድምፅ መሳሪያ ያስፈልጋል። ሌሎች አገሮች No video, No Testimony የሚል መርህ አላቸዉ። ለጉዳዩ ትኩረት ከተሰጠዉ ይህንን አሰራር በቴክኖሎጅ ተግባራዊ ማድረግ ከባድ አይመስለኝም። ስለዚህ የፖሊስ ወንጀል ምርመራ በመቅረፀ ምስልና ድምፅ መሳሪያ አማካኝነት ቢተገበር።

የፍትሐብሄር እና የወንጀል ክርክር የነገር ጭብጥ አመሰራረትና የማስረጃ አግባብነት ግንኙነት፤ የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች ተሞክሮ

ዮሐንስ ቢሻው*

1. አጽርኦተ ጽሁፍ

በጭብጥ አመሰራረት ዙሪያ የህግ ማዕቀፉ እንደተጠበቀ ሆኖ ባሉት ህግጋት እና በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች አተገባበር መካከል ያሉትን ክፍተቶች የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዳኝነት ሙያ ልምድ ካገኘሁት ግንዛቤ በመነሳት የህጉን ይዘት ከአተገባበሩ ጋር በማገናዘብ ጥናታዊ ጽሁፉን እንዳዘጋጅ አድርጎኛል። በተጨማሪም በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የተጻፉ ጥናቶች በብዛት ባለመኖራቸዉ ጥናቱ በመስኩ ለተሰማሩ ባለሙያዎችም ሆነ ለሌሎች አንባቢያን የመነሻ ግንዛቤ የመፍጠር እና ተጨማሪ ጥናቶችን የማነሳሳት ሚና ይኖረዋል በሚል ሀሳብ የተዘጋጀ ነዉ። ጥናቱ በህጉ እና በአተገባበሩ መካከል ያሉ ክፍተቶችን መሰረት አድርጎ የተከናወነ በመሆኑ ጥቅም ላይ የዋለው የምርምር ዘዴ ዶክትሪናል የምርምር ዘዴ ነዉ።

ክርክርን በመምራት ሂደት ዉስጥ ጭብጥ መመስረት የፍርድ ቤቶች ዋና ስራ ነዉ። ዳኛው የክርክሩን የነገር ጭብጥ ሲመሰርት የክርክሩን ሙሉ ታሪክ መገንዘቡን የሚያመላክት ሲሆን ይህን ተከትሎም ለጉዳዩ ዕልባት ለመስጠት የሚያስችሉትን የህግና የፍሬ ነገር አማራጮችንም ለይቶ የሚፈልግበት ወሳኝ ክርክር ምዕራፍ ነው። በፍትሐብሄርም ሆን በወንጀል የክርክር ሂደት ውስጥ ትክክለኛውን የነገር ጭብጥ መሰረት አድርጎ ያልተመራ ጉዳይ መዳረሻው የተሳሳተ ውሳኔ ይሆናል። በመሆኑም የስነ-ስርዓት ህግጋትን ተከትሎ ትክክለኛ ጭብጥ የመመስረት ጉዳይ ትክክለኛ ፍርድ ላይ ለመድረስ የሚያስችል ዋስትና ነው ለማለት ያስችላል።

በዚህ ጽሁፍ ለመመልከት እንደተቻለው በክልላችን ፍርድ ቤቶች ከሚሰጡ ውሳኔዎች ውስጥ በጭብጥ አመሰራረት ችግር ምክንያት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተሽረው ጭብጥ ተመስርቶላቸዉ የሚመለሱ ጉዳዮች በርካታ ናቸዉ። የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሚሰጧቸው ውሳኔዎች በትክክለኛዉ የጭብጥ አመሰራረት ሂደት ቢያልፉ ትክክለኛ ፍርድ የመስጠት እድልን እንደሚጨምሩ በመገንዘብ በዚህም የፍርድ ቤቶችን ስራ ጫና እና የተከራካሪ ወገኖችን ወጭ መቀነስን እዉን ለማድረግ ይረዳ ዘንድ ታስቦ የተዘጋጀ ጽሁፍ ነው።

* ዮሐንስ ቢሻው፤ LLB, LLM፤ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት ባለሙያ

2. መግቢያ

የነገር ጭብጥ አመሰራረት ምናልባትም የክርክር መሰረታዊ ክፍል የሚባል ነው። ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠትም ይሁን ክርክሩን በትክክለኛው አቅጣጫ ለመምራት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ተግባር ነው። ትክክኛ የነገር ጭብጥ ከተመሰረተ ትክክለኛ ውሳኔ ላይ ይደረሳል። የፍርድ ቤትም ይሁን የተከራካሪዎች ወጭ፣ ጊዜና ጉልበት ይቀንሳል። በተቃራኒው ደግሞ በአግባቡ የነገር ጭብጥ ካልተለየ ለአላስፈላጊ ወጭ፣ ጊዜና ጉልበት መባከን በመጨረሻም ለሚሰጠው የተሳሳተ ውሳኔ ያደርሰናል። ይህን የክርክር ክፍል በአግባቡ ለመምራት ትልቅ ትኩረት የሚያሻው መሆኑን ያስገነዝበናል።

2.1 የነገር ጭብጥ አመሰራረት

የነገር ጭብጥ ምንድን ነው? የመዝገበ ቃላት ቀጥተኛ ትርጉም ሲታይ ጭብጥ ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተከራካሪ ወገኖች የሚከራከሩበት ነጥብ ነው። በክርክር ሂደቱ ውስጥ አከራካሪ የሆነው ነገር በተለይም በመካከላቸው የሚለያዩበት ነጥብ ማለት ነው። በአንደኛዉ ወገን የታመነ በሌላኛዉ ወገን የተካደ እንደሆነ የነገር ጭብጥ ይሆናል።[1]

አከራካሪ ፍሬ ነገር /ጭብጥ/ አጠያያቂ የሆነ ህጋዊ መብትን ወይም {legal right} ወይም የአንድን ግዴታ ተጠያቂነት ወይም /liberty/ ያዘለና ውሳኔ ማግኘት ያለበት ፍሬ ነገር ነው።[2] ይህ አከራካሪ የሆነው ነጥብ ወይም የነገር ጭብጥ እራሱን የቻለ የህግና የፍሬ ነገር ወይም ሁለቱን በአንድ ላይ የያዘ ጥያቄ ሲሆን በክርክር ሂደት ውስጥ መልስ ወይም ውሳኔ ማግኘት ያለበት ነው። የኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ስነ-ስርዓት ህግ የነገር ጭብጥን አስመልክቶ የተለየ ትርጓሜ ቢያስቀምጥም በአንቀጽ 246 ላይ የነገር ጭብጥን አስመልክቶ "... ባለጉዳዮችን የሚያከራክረው፣ የተለያዩበት የህግ ወይም የፍሬ ነገር አግባብ ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ ለጉዳዩ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችለውን ጭብጥ በመያዝ ነው" በማለት አስቀምጧል። ይህን የስነ-ስርዓት ህግ ስናይ ከላይ የተጠቀሰውን ስለ ነገር ጭብጥ የተመለከተውን የመዝገበ ቃላት ፍች ትርጓሜ መሰረት ያደረገ እና ተመሳሳይ ይዘት አለው።

---

[1] የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ፣ 1958፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ በተለይ የወጣ፣ አዋጅ ቁጥር 3፣ ዓመት 1958 (ከዚህ ቀጥሎ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ እየተባለ ይጠራል)፣ አንቀጽ 247(1)

[2] ብርጋዴል ጀኔራል ታጠቅ ታደሰ፣ የማስረጃ ህግ መሰረተ ሀሳቦች

የነገር ጭብጥ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች የሚያከራክረው ነጥብ ወይም የሚለያዩበት መልስ ወይም ውሳኔ የሚያስፈልገው ጉዳይ ጭብጥ እንደሆነ ድንጋጌው አስቀምጧል። ይህ የጭብጥ ዓይነት ወይም የፍሬ ነገር ሊሆን ይችላል። ጭብጥ ህግ የሚፈልገውንና በተጨባጭ ያለውን ፍሬ ነገር በማዛመድ የሚቀየስና መልስ ወይም ውሳኔ እንዲሰጥበት የሚያስፈልግ ነጥብ ነው[3]። በአንድ ወገን የቀረበ የህግ ወይም የፍሬ ነገር የክርክር ሃሳብ በሌላ ወገን የተካደ ነጥብ ነው። ስለሆነም እያንዳንዱ የተካካዱበት የክርክር ሃሰብ እራሱን የቻለና የተለየ ጭብጥ በመሆን መያዝ አለበት። ይህ ጭብጥ ግን ከቀረበው የክርክር ሃሳብ አንጻር ብቻ ሊወሰን ይገባል።

የህግ ጭብጥ የቀረበበት ማስረጃዎች ላይ ልዩነት ሳይኖራቸው ነገር ግን በውጤት ደረጃ በፍርድ ቤት የህግ ትርጉም የሚያስፈልገው ነው። ስለዚህ የህግ ጭብጥ በህግ አተረጓጎም መልስ የሚሰጠው የዳኛው ተግባር ነው። አንዳንድ ጸሃፊዎችም ህጋዊ ጭብጥ በማለት ይገልጹታል።

የፍሬ ነገር ጭብጥ በአንዱ ተከራካሪ ወገን የቀረበ ማስረጃ በሌላኛው ወገን የክርክር ሃሳብ የቀረበበት ፍሬ ነገር ነው። የሚቀርበው የክርክር ሃሳብ የፍሬ ነገሮችን መኖር ወይም መከሰትን አስመልክቶ የሚቀርበው የክርክር ሃሳብ ነው።

ስለሆነም ሰዎች የሚካካዱበት ወይም የሚከራከሩበት በተግባር በዓይን በታየው፣ በጆሮ በተሰማው የፍሬ ነገር መኖር ወይም መከሰት ወይም አለመከሰት አስመልክቶ ነው። እነዚህ ፍሬ ነገሮች መኖራቸው ወይም አለመኖራቸው፣ የመከሰት፣ አለመከሰታቸው በሰዎች መካከል የለየለት ወይም መካካድና ክርክር ሊቀርብባቸው ይችላል። እነዚህ ፍሬ ነገሮች ላይ ሰዎች ልዩነት ካላቸው እራሱን በቻለ የማስረጃ ህግ ወይም መርህን ተከትሎ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚያሳርፍባቸው ነጥቦች ናቸው። እነዚህ ፍሬ ነገሮች ወይም ኩነቶች በህግ አተረጓጎም መሰረት በመሆናቸው በፍሬ ነገሮች ላይ ያለውን መካካድ በነጥብ ወይም በጭብጥነት በመያዝ ማከራከርና ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። ስለሆነም በገሃዱ ዓለም ስላለው እውነታ ወይም የነገሮች መኖር ወይም አለመኖር፣ መከሰት ወይም አለመከሰት የሁለት ሰዎች አለመግባባት መከራከሪያ ስለመሆኑ በእርግጥ በማረጋገጥ ጭብጥ ሊመሰረት ይገባል።

[3] Indian evidence act sect-3

2.2 የነገር ጭብጥ መመስረት አስፈላጊነት

ጭብጥ የክርክር ማጠንጠኛ ጥያቄ ነው። ጭብጥ የክርክር ወሰን በማበጀት ክርክርን ይመራል። ጭብጥ አመሰራረት ብቃት ወይም ችሎታ ሳይንስ ሳይሆን ጥበብ /Art/ እንደሆነ ጸሃፍት ይገልጻሉ። የህግ ክርክር ማጠንጠኛ ማዕከል ለመመስረት /ለመለየት/ ያለን ብቃት ወይም ጥበብ አጠቃላይ የክርክር ሂደት መረዳትን ቅድመ-ሁኔታ ነው። ዳኛ ጭብጥ ከመያዙ በፊት ስለጉዳዩ በቂ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል።[4] ስለሆነም ስለጉዳዩ በቂ ግንዛቤና እውቀት በመያዝ የተመሰረተ የነገር ጭብጥ ለአንባቢያን ወይም ተደራሲያኑ ጥሩ መልዕክት ያስተላልፋል። በሌላ በኩል ጥሩ ያልሆነ ጭብጥ የመሰረተ የህግ ባለሙያ የሚያስተላልፈው መልዕክት ጥሩ አይሆንም።

በተጨማሪም የነገር ጭብጥ ፋይዳ ከፍርድ ቤት ውጭ ጊዜ እና ጉልበት ጋር የሚያያዝ እንዲሁም የተከራካሪዎችን መጉላላት የሚያስከትል ቁልፍ የክርክር ክፍል ነው። በተለይም የሚመሰረተው ጭብጥ የፍሬ ነገር ጭብጥ ከሆነ መቅረብ ያለባቸውን ማስረጃዎች በመለየት በተያዘው የክርክር ነጥብ ላይ የማስረዳት ሸክም ያለበትን ወገን /burden of proof/ ምን እንደሆነ ለማወቅ ይረዳል።[5] ስለሆነም ፍርድ ቤቱ ጭብጥን ከተከራካሪ ወገኖች የጽሁፍና የቃል ክርክር በማንጠር በግልጽ ማውጣትና መመዘን ይገባዋል። ስለ ጭብጥ አመሰራረት ተግባራዊ ችግሮች መንበረ ጸሃይ ታደሰ እንደሚከተለው አስቀምጠውታል።

በብዙ አገሮች ትክክለኛውን ጭብጥ በመለየት ሙግትን በአግባቡ መምራት የሙያ ብቃት የሚመዘንበት ትልቅ ችሎታም ነው።

> ጭብጥን በአግባቡና በተገቢው መንገድ መመስረት አንዱ የግልጸኝነት መርህ መገለጫ ነው። የፍርድ ቤት ተግባር ከሚመራባቸው መርሆች ውስጥ ሚዛናዊ ገለልተኛ መሆንን ይጠይቃሉ። ለገለልተኝነቱ መገለጫ ደግሞ ግልጽ ችሎት ማስቻልና በገለልተኝነት የክርክር ነጥብን መለየትን ይመለከታል። በአጠቃላይ የክርክር ነገር ጭብጥን በአግባቡ መመስረት የግልጸኝነት አሰራር መገለጫ መንገድ ነው። በአሰራር ባለፈው ተከራካሪ ወገኖች የሚያከራክራቸው ነጥብ ላይ ግልጽነትና እውቅና መያዛቸው በሚያቀርቡት ሙግት ማስረጃ አቀራረብ ላይ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ተከራካሪ ወገኖች ምስክር

[4] ዮሐንስ ሀሩይ፡ በታጠቅ ታደሰ መቅድም ላይ ስለ ፍሬ ነገር ሲገለጽ የማስረጃ ህግ ማለት የኩነት ወይም የፍሬ ነገር /fact/ ህግ ነው ይሉታል። ፍሬ ነገር /fact/ የሚለው ቃል ፍችን አስመልክቶ የተለያየ ስያሜ እንዳለው ያስቀምጣሉ።

[5] Alen Sedler, The Ethiopian Civil Procedure Code Commentary, 1960

ማሰማትም ይሁን ሌላ ማስረጃ ማቅረብ የሚጠበቅባቸው በተያዘው ጭብጥ ላይ ብቻ ነው።[6]

ሌላውና መሰረታዊ የጭብጥ ምስረታ ትልቅ ፋይዳ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት መሰረት ነው። በመጀመሪያ ትክክለኛውን የነገር ጭብጥ ለመያዝ ዳኛው ስለ ጉዳዩ በቂ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል። በቂ ግንዛቤ ለመያዝ የቀረቡ የክስና የመልስ አቤቱታዎች በአግባቡ መመርመር የጽሁፍ ማስረጃ ከቀረበም ይህንኑ መመልከትና በቃል ክርክር ወቅት እንደ አግባብነቱ ከግራ ቀኙ ወገኖች በማጣራትና በመጠየቅ ዳኛው ስለክርክሩ ግልጽ ግንዛቤ መያዙን ይመለከታል። ይህን በተመለከተ የኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ስነ-ስርዓት ህግ ትኩረት የሰጠው መሆኑን ለማሳየት ፍርድ ቤቱ ጭብጡን ከመያዙ በፊት ስለጉዳዩ በቂ እውቀት አለው የሚለውን ሰው ጠርቶ ሊጠይቀውና በእጁ ሰነድ አለ የተባለውን ሰው ሰነዱን እንደዲያቀርብ መጥሪያ ሊልክለት ይችላል በማለት ያስቀምጣል፡[7] ከዚህ ድንጋጌ የምንገነዘበው ትልቅ ነገር ፍርድ ቤቱ የነገር ጭብጥን ከመያዙ ምን ያህል ግልጽ እና በቂ ግንዛቤ መያዝ እንዳለበትና ለዚህ ተግባር ሲባልም አስፈላጊ ከሆነ ቀነ ቀጠሮ ጭምር ሊይዝ እንደሚችል ነው። በዚህ ሂደት ዳኛው ስለጉዳዩ ግልጽ ይሆናል፤ ትክክለኛ ውሳኔም ለመወሰን ይችላል።[8]

በዚህ ክፍል ለጭብጥ መመሰረት ከሚቀርቡ እና በፍርድ ቤቱ ስለሚሰሙ የማስረጃ ዓይነቶች፣ ከማስረጃ ሸክም አወሳሰን ረገድ የጭብጥን ወሳኝነት እንመለከታለን። ተከራካሪ ወገን የሚያስረዱላቸውን የማስረጃ ዓይነት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 223 እና 224 መሰረት በመዘርዘር ያቀርባሉ። በዚህ መሰረት የቀረቡት ማስረጃዎች ሁሉ ግን ለክርክሩ አስፈላጊ ላይሆኑ ወይም ተቀባይነት ላያገኙ ይችላሉ። የማስረጃዎች አግባብነት በፍርድ ቤቱ ከተያዘው ጭብጥ በመነሳት መገምገም አለባቸው። ረቂቁ የኢፌድሪ የማስረጃ ህግ ማስረጃ የሚያካትታቸውን ነገሮች በትርጉም ክፍሉ እንደሚከተለው አስቀምጧል።

> ማስረጃ ማለት እውነትነቱ እንዲመረመር የቀረበ ማንኛውም የታወቀ ነው የተባለ ነገር የሚረጋገጥበት ወይም ውድቅ የሚሆንበት ማንኛውም ዘዴ ሲሆን ይሄውም የምስክሮችን ቃል፣ በተከራካሪዎች የሚሰጥ የእምነት ቃል፣ ሰነድ፣ የፍርድ ቤት

[6] የግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 2፣ አንቀጽ 263(1)
[7] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 249
[8] አንዳንዶች ስለጭብጥ አስፈላጊነት እንዲህ ይላሉ issues are the very foundation of the case and if they are not framed with accrued and skill it leads to defect in the entire trial leading to an incorrect judgment

መዝገብ ማስታወቂያ በህግ የተወሰደ የህሊና ግምት /legal presumption/ የአንድን ነገር አፈጣጠር እና ሂደት ማሳያ /demonstration/ እንዲሁም ፍርድ ቤቱ በዓይነቱ እንዲመለከታቸው የሚቀርቡ ነገሮችን ያካትታል /የተጨመረ/።

ከላይ በማስረጃ ትርጉም ስር ከተመለከቱት ማስረጃዎች ውስጥ ተከራካሪዎች ጉዳያቸውን የሚያስረዱበትን ማስረጃ ሁሉ ስነ-ስርዓቱ በሚፈቅደው መንገድ ያቀርባሉ። ማስረጃዎች ከቀረቡ በኋላ የዳኛው ስራ የሚሆነው አግባብ የሆነውን ማስረጃ መለየትና ተቀባይነቱን ማረጋገጥ ይሆናል። የማስረጃውን አግባብነት ለመወሰን በመነሻነት የሚታየው የተመሰረተው ጭብጥ ነው። ምክንያቱም ማስረጃ ሊሰጥባቸው የሚችለው በጭብጥ የተያዘውን ነገር እና ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ነገር እንደተባለው መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማስረዳት ብቻ ነው። ከላይ የጭብጥ ትርጉም እንዳየነው ጭብጥ ተከራካሪዎች በፍሬ ነገር ወይም በህግ የሚለያዩበት ነጥብ ነው። ስለሆነም ይህ የፍሬ ነገር ወይም ማስረጃ የሚረጋገጥበትን ነገር አግባብነት መወሰን ያስፈልጋል። አግባብነት ያለው ፍሬ ነገር /እውቅ ነገር/ /relevant fact/ ማለት በጭብጥ የተያዘውን ለማረጋገጥ ወይም ውድቅ ለማድረግ በቀጥታ ወይም ከጉዳዩ በሚገኘው ትርጉም አስፈላጊ ወደሆኑት መደምደሚያ አስተያየቶች የሚያደርስ ነገር ነው።

የማስረጃ አግባብነትን ለመወሰን መነሻ የሚሆነው የተያዘው ጭብጥ መሆኑን በስፋት ተቀምጧል። ስለሆነም በተከራካሪዎች የቀረቡትን ማስረጃዎች አግባብነት ከመወሰናችን በፊት ጭብጥ መመስረት አስፈላጊ ይሆናል። ጭብጥ ከመመስረታችን በፊት የማስረጃ አግባብነትም ሆነ ተቀባይነት ላይ ውሳኔ ወይም ብይን መስጠት ትክክለኛ አካሄድ አይደለም። በተግባር በክልላችን የሚታዩ የማስረጃ አግባብነት ወይም ተቀባይነት ውሳኔ ጭብጥ ከመመስረቱ በፊት የሚሰጥ ውሳኔ ነው። ክርክሩ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ሊሆን ይችላል። ስለሆነም ከወዲሁ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስመልክቶ ተቀባይነት ያለው የማስረጃ ዓይነት የሰነድ /የባለቤትነት ማረጋገጫ ነው ከሚል መነሻ የሚቀርበውን አቤቱታ ሁሉ ውድቅ የማድረግ ዝንባሌ ይስተዋላል። የመሬት ክርክርን አስመልክቶ ሁልጊዜ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ማቅረብን የሚጠይቅ ነው በማለት የክርክሩ ጭብጥ ሳይመሰረት አስቀድሞ የማስረጃው ተቀባይነት አግባብነት ላይ ውሳኔ ይሰጣል። ይህ ደግሞ ለተሳሳተ ውሳኔ የሚዳርግ አሰራር ነው። የማስረጃ ህግ ካስቀመጠው መርህ ውጭ ነው። ስለሆነም የማስረጃ አግባብነት ወይም ተቀባይነት ላይ ውሳኔ መስጠት ያለብን ተከራካሪዎች የሚለያዩበትን ነጥብ ከለየን በኋላ መሆን አለበት። ሁለቱን ተከራካሪዎች የሚያከራክራቸው ነገር ከተለየ የሚቀርበው የማስረጃ ዓይነት ይወሰናል።

ይህ አካሄድ አጠቃላይ በውሳኔ አሰጣጣችን ላይ ከፍተኛ እንድምታ እንዳለው የፍርድ ቤት ውሳኔዎች በምንዳስሳቸው ክፍል እናየዋለን፡፡

የክርክር ውጤታማነት የሚለካው የክርክር አመራሩ በሚኖረው ስነ-ስርዓታዊነት ነው፡፡ የስነ-ስርዓት ህጐች ክርክሩን አስጀምረው፣ አስኪደው የመጨረሻ ውሣኔ ላይ አድርሰው የውሣኔውን አፈፃፀም እውን ለማድረግ ፍርድ ቤቱን በመምራት የማይተካ ሚና አላቸው፡፡ እያንዳንዱ የሥነ-ሥርዓት ህግ ድንጋጌ የክርክሩን መዳረሻ ህጋዊ፣ ፍትሀዊ እና የተሟላ እንዲሆን በማድረግ በኩል የሚኖራቸው ሚና ወሣኝ በመሆኑ ሥነ-ሥርዓት ህጐችን ማዕከል ያላደረገ የክርክር አመራር የህጋዊነትም ሆነ የፍትሀዊነት ጥያቄ የማስነሣት እድሉ የሰፋ ነው፡፡

በክልላችን ፍርድ ቤቶች የህግ አተረጓጐም ሂደቶች የአገሪቱን የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት እና የፍትሐብሄር ሥነ-ሥርዓት ህጎችን መሠረት ያደረገ ሲሆን የህግ ማዕቀፉ የራሱ ክፍተቶች እንደተጠበቁ ሆነው በሥራ ላይ ያሉትን ህጐች ተግባራዊ በማድረግ ረገድ በተግባር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ማንሣት እና ህጋዊ መፍትሄ መጠቆም የዚህ ጽሁፍ ዋና ግቦች ናቸው፡፡

3. በወንጀል ክርክር አመራር የጭብጥ አመሰራረት እና የሚያጋጥሙ ችግሮች

በወንጀል ክስ ሂደት የክርክር ጭብጥ የሚያስመዘግቡት ወይም የሚመሠርቱት ተከራካሪ ወገኖች ራሣቸው ማለትም ዐቃቢ ህግ እና ተከሣሹ ናቸው፡፡[9] የዐቃቢ ህግ ጭብጥ አመሠራረት የሚወሠነው በተከሣሹ የዕምነት ክህደት ቃል ላይ ሲሆን በመካከላቸው ለጭብጥ መመስረት ምክንያት የሚሆነው ልዩነት የሚፈጠረው ደግሞ ተከሣሹ የቀረበበትን ክስ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክዶ የተከራከረ እንደሆነ ነው፡፡[10] በአመዛኙ የዐቃቢ ህግ የክርክር ጭብጥ በክሱ ላይ ከተመለከተው ፍሬ ነገር ጋር የሚመሣሠል ሲሆን ማስረጃ ማሰማት በሚጀመርበት ጊዜ ከክሱ የተለዩ ጭብጥ ለፍርድ ቤቱ ሊያሥመዘግብ የሚችልባቸው አጋጣሚዎች ይኖራሉ፡፡ ይኸውም የመጀመሪያው ተከሣሽ በእምነት ክህደት ቃሉ ድርጊቱን በማመን መብቱን ጠብቆ ጥፋተኛ አይደለሁም ሲል ዐ/ህግ በዚሁ አግባብ ጭብጡን አስተካክሎ ለፍርድ ቤቱ ያስመዘግባል፡፡[11] ሌላው በክሱ ዝርዝር ላይ ያቀረባቸውን ፍሬ ነገሮች በተለያዩ ማስረጃዎች የሚያስረዳ ሆኖ

[9] የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ-ሥርዓት፣ 1954፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ በተለይ የወጣ፣ አዋጅ ቁጥር 1 ዓመት 1954 (ከዚህ ቀጥሎ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ-ሥርዓት ተብሎ ይጠቀሣል)፣ አንቀጽ 136(1) እና 142(2)
[10] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 133
[11] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 133(2)

በተገኘ ጊዜ የትኛው ማስረጃ የትኛውን የክስ ፍሬ ነገር እንደሚያስረዳ በመለዬት ጭብጡን ማስመዝገብ ይጠበቅበታል፡፡

በክልላችን የወንጀል ክስ ሂደት የክርክር ጭብጥን አስመልክቶ ከህጉ ጋር የፍትህ ተቋማትን አተገባበር ስንመለከት ተገቢውን ሥነ-ሥርዓታዊ አካሄድ ባለመከተል የተነሣ የፍትህ መጓደል በተለያዬ መልክ ሲከሠት ይስተዋላል፡፡ የወጀል ክስ የክርክር ሂደት ከፍርድ ቤት በተጨማሪ የዐቃቢ ህግ ተቋምም የፍርድ ሂደቱን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ዋና ባለድርሻ አካል ነው፡፡

ዐቃቢ ህጉ የክሱን ጭብጥ መስራች ሲሆን የጭብጡ ትክክለኛነት የክርክሩን ቀጣይ ዕጣ ፈንታ የሚወስነው ዋናው ጉዳይ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ በሌላ በኩል ጭብጡን ማዕከል ያደረገ የማስረጃ አቀባበል ሂደት እንዲኖር የሚያደርገው ተሳተፎ ለፍትሃዊ ውሣኔ መዳረሻ ወሣኝነት አለው፡፡[12] በመቀጠል በክልላችን የወንጀል ክርክር ከጭብጥ አመሠራረት ጋር በተገናኘ በተግባር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከባለድርሻ አካላት ተሣትፎ እና ከህግ ጋር እያገናዘብን እንመለከታን፡፡

3.1 የዐቃቤ ህግ ክስ አመሠራረት ችግር

ዐቃቢ ህግ በተከሣሹ ላይ የሚያቀርበው የክስ ይዘት በክርክሩ ሂደት የሚሻሻሉ ነገሮች ካላጋጠሙ በስተቀር የከሣሽ የክስ ጭብጥ መሆናቸውን ተመልክተና፡፡ [13] አቃቤ ህጉ የሚያቀርበው ክስ የተከሣሹን ስም፣ ተከሣሹ የተከሠሠበትን ወንጀል እንዲሁም የወንጀሉን መሠረታዊ ነገር እና ሁኔታዎች፣ ወንጀሉ የተፈፀመበትን ጊዜ እና ስፍራ ተገቢ በሆነ ጊዜም የተበደለውን ሠው ስም ወይም ወንጀሉ የተፈፀመበትን ንብረት፣ በወንጀል ድርጊቱ የተጣሰውን የወንጀል ህግ ድንጋጌ መግለጽ አለበት፡፡[14] የተዘረዘሩትን ፍሬ ነገሮች አሟልቶ ያልያዘ ክስ ቀጣዩን የክርክር ሂደት ለመምራት አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ሲሆን በክልሉ የወንጀል ክስ የክርክር ሂደት ከዐ/ህግ ጭብጥ /ክስ/ አመሠራረት ጋር በተያያዘ በብዛት የሚስተዋሉ ችግሮችን ቀጥለን እናነሣለን፡፡

የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመበት ጊዜ እና ቦታ የወንጀል ፈፃሚው ተከሣሹ መሆኑን ለመለዬት በማስረጃ መረጋገጥ ከሚገባቸው ቀዳሚ የጭብጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡ በዐቃቢ ህግ ክስ በብዛት

[12] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 136(3)
[13] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 136(1)
[14] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 111

ከሚስተዋሉት ግድፈቶች መካከል ወንጀል የተፈፀመበትን ጊዜ በክስ ላይ አለመግለጽ ወይም የተሳሳተ ጊዜን ማመልከት አንዱ ነው፡፡

በክሱ ላይ ወንጀል የተፈፀመበት ጊዜ አለመመልከቱ የዐቃቤ ህግን ቀዳሚ የማሥረዳት ሸክም ወይም ኃላፊነት ከባድ የሚያደርግበት ሲሆን የማሥረጃ አቀባበሉን ሂደትም ለመምራት ፍርድ ቤቶች ጭምር እንዲቸገሩ የሚያደርግ ነው፡፡ ከምንም በላይ ጊዜው ያልተጠቀሠ የወንጀል ክስ የተከሣሹን የመከላከል መብት የሚያጣብብ እና በዐ/ህግ ማስረጃ ላይ ጥርጣሬ ለመፍጠር እድል የሚሰጠውን መስቀለኛ ጥያቄ እንዳይጠይቅ የሚያደናቅፍ መሆኑ መሠረታዊ የጭብጥ አመሠራረት ግድፈት ያደርገዋል፡፡[15]

በተግባር ጊዜ ያልተመለከተባቸው የወንጀል ክሦች የሚያጋጠሙ ቢሆንም በሚፈጥሩት የክርክር አመራር ጫና እና በተከሣሽ ላይ ሊያሣድሩት በሚችሉት የመብት መጣበብ ምክንየት ክርክሮች ከመቀጠላቸው በፊት የወንጀል ክሱ ተስተካክሎ የወንጀል ድርጊት መፈፀሚያ ጊዜው ተመልክቶ ክሱ ተሻሽሎ እንዲቅርብ ከሚደረግ በቀር ክርክሩ ቀጥሎ ጊዜው ባልተመለከተ የወንጀል ክስ መነሻነት የተሰጡ ውሣኔዎች በክልሉ በተግባር አያጋጥሙም፡፡ ይህም በፍ/ቤቱ አነሳሽነት፣ በተከሣሹ ተቃውሞ ወይም በዐ/ህግ አመልካችነት ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ በሚሠጥ ትዕዛዝ ችግሩ ሊስተካከል ይችላል፡፡[16]

ሌላው የዐ/ህግ ክስ /ጭብጥ/ መሠረታዊ ችግር በክሱ ውስጥ የተመለከተው የወንጀል ድርጊት መፈፀሚያ ጊዜ ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የተሣሣተ ጊዜ የተመለከተ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህኛው ስህተት ምክንያት የቀረበ ክስ አስቀድሞ የመስተካከል ዕድሉ ጊዜው ካልተመለከተው ክስ አነስተኛ በመሆኑ የተነሣ የስህተቱ ውጤት የሚታየው በሚሠጠው ፍርድ ላይ ነው፡፡ በተግባር በሚስተዋሉ የወንጀል ጉዳዮች ላይ በብዛት የሚታዬው በጭብጡ ላይ የተመለከተው ጊዜ እና በዐቃቤ ህግ ማሥረጃዎች የሚነገረው የወንጀል ድርጊቱ መፈፀሚያ ጊዜ ፈጽሞ የተለያዬ በሆነ ጊዜ ተከሣሹ ከቀረበበት ክስ በነፃ እንዲሰናበት ብይን መስጠት ነው፡፡ ምንም እንኳ የወንጀል ህግ መርሁ ንፁሃን ከሚቀጡ የወንጀለኞችን ማምለጥ ወይም በነፃ መሠናበት የሚያበረታታ ቢሆንም በዐ/ህግ የክስ /ጭብጥ/ አመሠራረት ችግር ምክንያት ተጠያቂ መሆን የሚገባቸው ወንጀል አድራጊዎች በነፃ መሠናበት ግን የመርሁ ልዩ ሀኔታ በመሆኑ ሊበረታታ አይችልም፡፡

[15] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 112
[16] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 119(1)

> “በዞን ዐ/ህግ ከሣሽነት ክስ የቀረበበት አቶ ቢሰነብት ፈንታሁን በቀረበበት ክስ የወንጀል ህግ አንቀጽ 540 ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ ሠኔ 12 ቀን 2009 ዓ.ም በተጠቀሠው ቦታ የግል ተበዳይ ሚች ካሳሁን ሙሉቀንን በዱላ ደብድቦ ገድሏል በሚል በቀረበበት የወንጀል ክስ መነሻነት ከዐ/ህግ ጋር ሲከራከር ቆይቶ ተከሣሹ በቀረበው ክስ ሠኔ 12/2009 ዓ.ም ወንጀሉን እንደፈፀመ የተመለከተ ቢሆንም በዐ/ህግ ምስክሮች ቃል የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመው ነሀሴ 12 ቀን 2009 ዓ.ም በመሆኑ ዐ/ህግ በአስመዘገበው ጭብጥ መሰረት አላስረዳም ሲል ፍርድ ቤቱ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 141 መሰረት በነፃ አሠናብቶታል።”[17]

በዚህ ጉዳይ በዐ/ህግ የክስ አመሠራረት ችግር ምክንያት በሌሎች የክሱ ፍሬ ነገሮች ላይ ወንጀል ፈፃሚነቱ ቢረጋገጥበትም እንኳ ተከሣሹ ክርክሩ ሳይጠናቀቅ በነፃ ተሠናብቷል። ዐቃቢ ህግ በሚመሠርተው ክስ ላይ የወንጀል መፈፀሚያ ጊዜውን ትክክለኛነት ጨምሮ ሌሎች የክሱን ፍሬ ነገሮች በጥንቃቄ ካላቀረበ የክርክሩ አቅጣጫ የሚመሠረተውን የክስ ጭብጥ የሚከተል በመሆኑ የክርክሩ መዳረሻ ፍትሃዊነት የጎደለው እና ስህተት የሚገለጥበትን ውጤት የሚያስከትል መሆኑ አይቀርም።

ይህም የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ ንፁሃን ያለአግባብ የሚቀጡበት ወንጀለኞች የማይቀጡበት ችግሮች የሚፈጠሩበት ሥርዓት ያደርገዋል።

3.2 የዐቃቢ ህግ የክስ ፍሬ ነገር ጭብጦች መሳሳት

በወንጀል የማሥረጃ ህግ መርህ ዐቃቢ ህጉ ያቀረበውን የወንጀል ክስ ከተከሣሹ ቀድሞ የማሥረዳት ኃላፊነት ያለበት ሲሆን በኢትዮጵያ ወንጀል ህግ የዐቃቤ ህግ የማሥረዳት ሸክም ደግሞ ግልጽ እና በቂ (clear and sufficient) ማሥረጃ እስከማቅረብ ድረስ የሚደርስ ነው።[18] ዐ/ህግ ከተከሣሹ ይልቅ የከበደ የማሥረዳት ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ እና ተከሣሽ ራሱን በመከላከል ሂደት በዐቃቤ ህግ ክስ እና ማሥረጃ ላይ ምክንያታዊ ጥርጣሬ (Reasnable doubt) መፍጠር በነፃ የሚያሠናብተው በመሆኑ እያንዳንዱ የዐቃቤ ህግ ክስ ፍሬ ነገር በትክክል መመልከት እና በማስረጃም እንደ ክስ አቀራረቡ መረጋገጡ ሀላፊነቱን በተሻለ ብቃት እንዲወጣ የሚያግዘው ይሆናል።

---

[17] የክልል ዐቃቤ ህግ እና ቢሰነብት ፈንታሁን፣ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ 2010 ዓ.ም፣ የሰው መግደል ወንጀል፣ መዝገብ ቁጥር 17920

[18] የወንጀል ህግ ስነ-ስርዓት፣ ቁጥር 142(1)

ከአንድ በላይ ተከሣሾች በተሣተፉበት የወንጀል ክስ የዐቃቤ ህግ የክስ አቀራረብ የእያንዳንዱን ተከሣሾች የወንጀል ተሣትፎ ለይቶ የሚያመለክት እና ማሥረጃዎችም በክሱ በተመለከተው የተሣትፎ ሁኔታ ለይተው እንዲያረጋግጡ የሚያስችል ካልሆነ በስተቀር ከፍ ብለን በተመለከትነው የዐቃቤ ህግ ከተከሣሽ የከበደ የማስረዳት ኃላፊነት የተነሣ እንዲሁም ከጥርጣሬ በፀዳ ሁኔታ የማስረዳት የወንጀል ህግ የማስረጃ መርህ አኳያ ክሱ ውድቅ የመደረግ እድሉ የሰፋ ነው፡፡

> “የዞኑ ዐቃቢ ህግ የወንጀል ህግ አንቀጽ 670ን ጠቅሦ በ3 ተከሣሾች ላይ ባቀረበው የውንብድና ወንጀል ክስ በክሱ ዝርዝር ይዘት የተከሳሾችን የወንጀል ተሳትፎ ሲገልጽ፡- የግል ተበዳዩን 1ኛ ተከሣሽ በሽመል ራሱን፣ 2ኛ ተከሣሽ በጠብመንጃ ሠደፍ ጐኑን፣ 3ኛ ተከሣሽ በድንጋይ እግሩን መተውት ከወደቀ በኋላ ኪሡን ሦሥቱም ፈትሸው 2ኛው ተከሣሽ ከደረት ኪሡ ላይ ያገኘውን ብር 3,000 /ሦስት ሽህ ብር/ አውጥቶ ይዘው የሄዱ በመሆናቸው በከባድ ውንብድና ወንጀል ተጠያቂ ናቸው ሲል ክስ አቅርቧል፡፡[19]

ከላይ በተመለከተው የዐ/ህግ የክስ ጭብጥ መሠረት እንዲያስረዱ የቀረቡት ሁለት የዐ/ህግ ምስክሮች በሠጡት ቃል ሁለቱም ተከሳሾች በክሱ ላይ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት ሲፈጽሙ አይተናል ካሉ በኋላ በዝርዝር ሥለተሣትፏቸው ሲጠየቁ፡- 1ኛው ምስክር 1ኛ ተከሣሽ በሠደፍ ጐኑን፣ 2ኛ ተከሣሽ በሽመል ራሱን፣ 3ኛ ተከሣሽ በድንጋይ ራሱን መትተውት ሲወድቅ 1ኛ ተከሣሽ ከኪሡ ብር አውጥቶ ይዘው ሄዱ በማለት አስረዱ፡፡ 2ኛ የዐ/ህግ ምስክር በበኩሉ 1ኛ ተከሣሽ በድንጋይ ራሡን፣ 2ኛ ተከሣሽ በሠደፍ ጐኑን፣ 3ኛ ተከሣሽ በሽመል ሆዱን መተውት ከወደቀ በኋላ 3ኛ ተከሣሽ ከደረት ኪሡ ብር አውጥቶ ይዘው ሄዱ በማለት አስረዱ፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዐ/ህግን ክስና ማሥረጃ በማገናዘብ መርምሮ ዐቃቤ ህግ ባቀረበው የክስ ጭብጥ መሠረት አላሥረዳም ሲል ተከሣሾችን በነፃ አሠናብቷል፡፡

በዚህ ጉዳይ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ተከሣሾች የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈፀማቸው በአንድ ድምጽ ቢናገሩም አፈፃፀማቸውን እና የወንጀል ተሣትፏቸውን በተመለከተ ግን በጭብጡ ላይ

[19] አበበ ማረው እና የክልል ዐቃቤ ህግ፣ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ የውንብድና ወንጀል፣ 2010 ዓ.ም፣ መዝገብ ቁጥር 62170

ከተመለከተው በተለዬ መልኩ በመግለፃቸው ክሱ ውድቅ እንዲሆን አድርገውታል። ተከሣሾች የወንጀል ድርጊቱን መፈፀማቸው እውነት ሊሆን ቢችልም እንኳ ዐቃቤ ህግ ክሱን ወይም ጭብጡን ከጥርጣሬ በፀዳ ሁኔታ ወይም በቂ እና ግልጽ በሆነ አግባብ ባለማረጋገጡ ምክንያት ወንጀል ፈፃሚዎችን ተጠያቂዎች ማድረግ አልተቻለም።

የወንጀል ክስ ጭብጥን የማስረዳት ጉዳይ በዚህ ደረጃ ግልጽነትን ወይም ትክክለኛነትን የሚጠይቅ በመሆኑ የዐቃቤ ህግ ክስ አመሠራረት ሁልጊዜም ጥንቃቄን እና የሙያ ትጋትን የሚጠይቅ መሆኑን ከዚህ መዝገብ ታሪክ ለመገንዘብ ይቻላል።

3.3 የፍርድ ቤቶች ክትትል ማነስ

በወንጀል ክስ ክርክር ጭብጥ የሚያስመዘግቡት ዐቃቤ ህግ እና ተከሣሹ ቢሆኑም ግራ ቀኙም ያሥመዘገቡትን ጭብጥ በማሥረጃ በማያረጋግጡበት ጊዜ ለፍትሃዊ ውሣኔ አሠጣጥ በሚረዳ መልኩ ፍርድ ቤቱ ጣልቃ በመግባት በዬትኛውም ጊዜ ማንኛውንም አይነት ጥያቄ ምስክሮችን ለመጠዬቅ ይችላል።[20] ከዚህም በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ ለትክክለኛ ፍርድ አሠጣጥ አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነበት ከማንኛውም የክርክር ጭብጥ አኳያ ማጣሪያ ማሥረጃዎችን አስቀርቦ የመመርመር ስልጣን አለው።[21]

ማስረጃዎች ጭብጦችን ተከትለው የሚፈሡ ፍሬ ነገሮች እንደመሆናቸው መጠን ፍርድ ቤቱ በማሥረጃ አቀባበል ረገድ ጣልቃ እንዲገባ ስልጣን ካገኘበት ምክንያት አንዱ ወይም ፍርድ ቤቱ ጣልቃ በመግባቱ ምክንያት ከሚጫወታቸው ሚናዎች አንዱ ማሥረጃዎች በተያዘው ጭብጥ ዙሪያ እንዲጠየቁ እና መልስ እንዲሠጡ ማድረግን ነው። ፍርድ ቤቱ የተከራካሪ ወገኖችን ጭብጥ በትክክል ከመቀበል አንስቶ የማሥረጃዎችን አቀራረብ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ በአግባቡ መከታተሉ የክርክሩን ሂደት ግልፅ፣ ቀልጣፋ እና ፍትሃዊ ያደርገዋል።

በዚህ ረገድ በወንጀል ክስ ሂደት ዐቃቤ ህግ እና ፍርድ ቤት ትክክለኛ ፍትህን ለማረጋገጥ እንደባለድርሻ በጋራ መስራት የሚችሉበት አጋጣሚ ተደርጐ ሊወሠድ የሚችል በመሆኑ ዐቃቤ ህጉ ማስረጃ የማስደመጥ ተግባሩን ከጭብጥ ሳይወጣ እንዲመራ ወይም በጭብጡ መሠረት የማሥረዳት ኃላፊነቱን እንዲወጣ፣ ይህን ማድረግ ባልቻለ ጊዜ ሁሉ ፍርድ ቤቱ ፍትሃዊ

[20] የወንጀል ህግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 136(4)
[21] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 143

ዳኝነትን በጠበቀ መንገድ ከግድፈቶቹ ሊያስተካክለው የሚችልበት የክርክር አመራር ማዕቀፍ እንዳለን ለመገንዘብ እንችላለን፡፡

የክርክር ጭብጥ እና ማስረጃዎች ተጣጥመው ያልተመሩበት የወንጀል ክስ መዝገብ ብዙ ጊዜ ሠፋፊ ይዘት ይኖራቸውና የምስክሮች ቃል ይዘት ከጭብጥ ጋር ሲገናዘብ የማይገናኝ ወይም ከጭብጥ ውጭ ሆኖ የሚገኝበት፣ ከምስክሩ ቃል ውስጥ ጭብጡን የሚመለከት የማሥረጃነት ቃል ቢኖርም ምስክሩ በደካማ የክርክር አመራር ከጭብጥ ውጭ በሚነሡ ጥያቄዎች መነሻነት የተናገረ በመሆኑ ለጭብጡ አግባብነት ያለውን ቃሉን በምስክርነቱ የተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው የሚገኙበት፣ ይህም የፍርድ ቤቱን የምርመራ ስራ አድካሚ እና ጊዜውንም አባካኝ የሚያደርግበት እንደሆነ በተግባር ከሚያጋጥሙ ጉዳዮች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ብዙ የወንጀል ጉዳዮች በዚህ ጭብጥ እና ማስረጃን አገናዝቦ የማቅረብ እና የመቀበል ችግር ምክንያት በአጭር ጊዜ የሚገባቸውን ፍትህ ሳያገኙ ሲቀሩ እና ብሎም በዳኞች መሠላቸት እና በጊዜ ማነስ ምክንያት ለተሣሣተ ፍርድ ሠለባ ሲሆኑ ይስተዋላል፡፡

ፍርድ ቤቶች በህግ የተሰጣቸውን ስልጣን እና ኃላፊነት በአግባቡ ከመወጣት አኳያ የዐቃቤ ህግንም ሆነ የተከሣሹን ጭብጥ በሚገባ ተቀብለው እና ተገንዝበው የሚቀርበው ማሥረጃም ከተያዘው ጭብጥ አኳያ አግባብነት /Relevant/ እና ተቀባይነት /admissible/ ያለው መሆኑን እየተከታተሉ የወንጀል ክርክሩን መምራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

4. በፍትሐብሔር የክርክር ሂደት የጭብጥ አመሰራረት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች

ከወንጀል ክስ ጭብጥ አመሠራረት በተለየ በፍትሐብሔር ክርክር ጭብጥ የሚመሠረተው በፍርድ ቤቱ በራሱ ነው፡፡ የተከራካሪ ወገኖችን የጽሁፍ እና የቃል ክርክር አካቶ ከተቀበለ በኋላ ከክሱ፣ ከመልሱ፣ ከቃል ክርክሩ እና ከቀረቡ የሠነድ ማሥረጃዎች ይዘት በሚውጣጡ ፍሬ ነገሮች መሠረት ፍርድ ቤቱ ጭብጡን ይመሠርታል፡፡[22] ተከራካሪ ወገኖች የተካካዱባቸው የህግ እና የፍሬ ነገር ነጥቦች ጭብጥ ሆነው የሚያዙ ሲሆን ግራ ቀኙ በየመከራከሪያቸው በተያዘው ጭብጥ ላይ አንዱ የሌላውን ማስረጃ በማስተባበል በማስረጃ እንዲከራከሩ ይደረጋል፡፡[23]

[22] የፍትሐብሄር ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 248
[23] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 247(1)

በፍትሐብሔር ጉዳይ በፍርድ ቤቱ የሚያዘው ጭብጥ ፍርድ ቤቱ የተከራካሪ ወገኖችን የህግ እና የፍሬ ነገር ክርክር መርምሮ ልዩነታቸውን በአግባቡ ሲገነዘብ መሆን ይገባዋል። የተከራካሪ ወገኖችን ልዩነት በግልጽ መገንዘብ ባልቻለ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ጭብጥ ከመመስረቱ አስቀድሞ ጭብጥ ለመመስረት ያስችሉኛል ወይም ክርክሩን የበለጠ ግልጽ ያደርጉልኛል ብሎ ያመነባቸውን ሠዎች እና የሠነድ ማሥረጃዎች አስቀርቦ መመርመር ይችላል።[24]

ፍርድ ቤቱ የሚይዘው የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ጭብጥ ትክክለኛነት ከሚሰጠው ውሣኔ ትክክለኛነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ጭብጥ በሚይዙበት ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።[25] ጭብጥ አመሠራረት ላይ ስህተት የተፈፀመበት ክርክር ትክክለኛ የማሥረጃ አቀባበል ሂደትን የማያስተናግድ በመሆኑ በትክክለኛ ውሣኔ የመቋጨት እድል የለውም።

በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች የውሣኔዎች ስህተት በአመዛኙ ከክርክር አመራር ችግር የሚመነጭ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከጭብጥ አመሠራረት ጋር የሚያያዙት በርካታ ናቸው። በዚህ ረገድ ከጭብጥ አመሠራረት ጋር በተገናኘ በክልሉ ፍርድ ቤቶች በተግባር የሚስተዋሉት ችግሮች ዋና ዋናዎቹ የተሳሳተ የክርክር ጭብጥ መያዝ፣ በተገቢው የክርክር ምዕራፍ ጭብጥ አለመያዝ እና ጭብጥ ሣይመሠርቱ ውሣኔ ላይ መድረስ ናቸው። እያንዳንዱን ችግሮች በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጡ ውሣኔዎችን በማሣያነት እያነሣን በዝርዝር እንመለከታቸዋለን።

4.1 የተሳሳተ ጭብጥ መያዝ

ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ተቀብሎ ከመረመረ በኋላ የሚይዘው ጭብጥ ትክክለኛነት የሚሰጠውን ፍርድ ትክክለኛነት የሚያመላክት ከመሆኑም ባሻገር ዳኛውም ክርክሩን በደንብ ተገንዝቦ የመራው መሆኑን ማሣያ ነው። ክርክሮች ትክክለኛውን ጭብጥ በሣተ መንገድ ሲቋጩ ተከራካሪዎችን ላልተገባ የጉልበት፣ የጊዜ እና የገንዘብ ኪሣራ የሚዳርጉ ሲሆን ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶችም ውሣኔዎችን ከፍሬ ነገር ህግ /Substantive law/ ግድፈቶች አኳያ ከማረም ይልቅ ሥነ-ሥርዓታዊ ግድፈቶችን ብቻ በማረም ሥራ ይጠመዳሉ።

[24] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 249
[25] ዝኒ ከማሁ ቁጥር 246(1)

የጭብጥ አመሠራረት ችግር በተለይ ለሰበር በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ በብዛት የሚስተዋል ሲሆን ሰበር ችሎቱ የፍሬ ነገር ጭብጦችን የማጣራት ስልጣን የሌለው በመሆኑ ምክንያት በጭብጥ አመሠራረት ላይ የሚያገኛቸውን ግድፈቶች የሚያርመው ተገቢ ነው የሚለውን ጭብጥ መስርቶ በዚሁ መሠረት አጣርቶ እንዲወስን ሥህተቱን ለፈፀመው የሥር ፍርድ ቤት በመመለስ ነው። ይህ ደግሞ ተከራካሪ ወገኖች እስከ መጨረሻው የፍርድ ቤቱ መዋቅር ያደረጉትን ክርክር እንዲደግሙት የሚያደርግ በመሆኑ በአጠቃላይ በፍትህ ሥርዓቱ እና በፍትህ ተገልጋዩ ላይ የሚያስከትለው የጊዜ፣ የጉልበት እና የገንዘብ ብክነት ከፍተኛ ነው።

> በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠ ፍርድ ክርክሩ በተጀመረበት የሰሜን አቸፈር ወረዳ ፍርድ ቤት የሰበር አመልካቹ በተጠሪዎች ላይ በጉልበት ያዙብኝ ያለውን የእርሻ መሬት እንዲለቁለት ክስ አቀረበ። የሰበር ተጠሪዎች በተከሣሽነት ቀርበው መሬቱን የያዙት መሆናቸውን አምነው ሆኖም የያዙት በጉልበት ሣይሆን ከአመልካች ጋር በመሬት ተለዋውጠው መሆኑን ገልጠው መልስ ሰጡ። የወረዳው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ሲጨርስ ተጠሪዎች መሬቱን በለውጥ እንደያዙት ያስረዱ ሲሆን አመልካች በጉልበት የተነጠቀ መሆኑን ማሥረዳት አልቻለም ሲል ክሱን ውድቅ በማድረግ ወስኗል። የባህር ዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ የወረዳውን ውሣኔ በማጽናት ትዕዛዝ ሠጥቷል።
>
> የክልሉ ሰበር አጣሪ ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የለውጥ ውሉ በህግ አግባብ የተፈፀመ መሆኑ ሣይጣራ በለውጥ ውል መነሻነት የያዙት ነው የተባለበት አግባብ ይጣራ ዘንድ ግራ ቀኙ በሰበር እንዲከራከሩ ትዕዛዝ ሠጥቶ በሠበር ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመጨረሻ የሰበር አጣሪ ችሎቱ የያዘው ጭብጥ ከክርክር ውጭ ነው ሲል የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ በማጽናት ፍርድ ሰጥቷል።[26]

በዚህ ጉዳይ የተሳሳተ ጭብጥ በመያዝ ተከራካሪ ወገኖችን ለወጭና ኪሣራ የዳረገው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት ነው። ለሰበር የሚቀርቡ ጉዳዮች ያለአግባብ በአጣሪው ችሎት ሊሠረዙ የሚችሉ መዝገቦች የመኖራቸውን ያክል ያለአግባብ ወይም የተሳሳተ ጭብጥ ተይዞም

[26] በቃሉ አቤ እና እነ ተዋቸው አናጌ፣ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰ/ሰ/ችሎት፣ የገጠር መሬት ክርክር፣ 2011 ዓ.ም መዝገብ ቁጥር 03-75196

ግራ ቀኙ በሠበር ለአመታት ሲመላለሡ ቆይተው በመጨረሻ የማጽናት ፍርድ የሚሰጥባቸው ጉዳዮች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።

የሰበር አጣሪ ችሎቱ የያዘው "የውሉ ህጋዊነት ሣይጣራ" የሚለው ጭብጥ በአመልካችም ሆነ በተጠሪ የውል ይፍረስልኝ ወይም ውል ይፈፀምልኝ የዳኝነት ጥያቄ ባልቀረበበት ሁኔታ ከግራ ቀኙ የክርክር ይዘት ውጭ በአጣሪ ችሎቱ በራሱ አነሣሽነት የተመሠረተ ጭብጥ ነው።

በሌላ የሰበር መዝገብ በተሠጠ ፍርድ በደቡብ አቸፈር ወረዳ ፍርድ ቤት የሰበር አመልካች ከሣሽ በመሆን በሰበር ተጠሪ ላይ ባቃረበው ክስ ተጠሪ በመኖሪያ አካባቢያችን የእህል ወፍጮ ለመትከል ዝግጅቱን አጠናቋል። የእህል ወፍጮው ቢተከል በአካባቢው ነዋሪዎች ላይ የድምጽ እና የአየር ብክለት የሚያስከትል በመሆኑ በጤናችን ላይ ጉዳት ከሚያደርስብን ድርጊት እንዲቆጠብ ሲሉ የሁከት ይወገድ የዳኝነት ጥያቄ አቀረቡ።

ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርቦ በሠጠው መልስ የምተክለው የእህል ወፍጮ በጤና ላይ ጉዳት አያደርስም፣ የምተክለውም በህጋዊ መንገድ በተሰጠኝ የድርጅት ቦታ ላይ በመሆኑ ከሣሽ እንዲቆም የመጠየቅ መብት የለውም ሲል ተከራክሯል።

የወረዳው ፍርድ ቤት ወፍጮው በነዋሪዎች ላይ የጤና ችግር ያስከትላል ወይስ አያስከትልም የሚል ጭበጥ ይዞ ከአከራከረ በኋላ የጤና ችግር እንደሚያስከትል በባለሙያ ተረጋግጧል ሲል ሁከት እንዲወገድ ወሰነ። ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ከፍተኛው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን በይግባኝ ሲያከራክር ቆይቶ በመጨረሻም ቦታው በይግባኝ ባይ በህጋዊ መንገድ ወፍጮ እንዲተክልበት የተሰጠው በመሆኑ ሁከት አልፈጠረም ሲል የወረዳ ፍርድ ቤቱን ውሣኔ ሻረው። በዚህ ፍርድ ላይ የይግባኝ ቅሬታ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ አፀናው።

የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰ/ሰ/ችሎት ጉዳዩን በሰበር ተመልክቶ ሲያከራክር ከቆዬ በኋላ በመጨረሻ የክርክሩ ትክክለኛ ጭብጥ ወፍጮው በጤና ላይ ጉዳት ያስከትላል የሚለው መሆኑን በመለዬት የወረዳ ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሲያፀና የከፍተኛ እና ጠ/ፍ/ቤት መደበኛ ችሎቶች የሰጡትን ውሣኔ ሽሯል።[27]

[27] ጸጋሁን ሁነኛው እና መኮንን ስሜ፣ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰ/ሰሚ ችሎት፣ የፍትሐብሄር ሁከት ይወገድ ክርክር፣ 2011 ዓ.ም መዝገብ ቁጥር 03-76409

በዚህ ክርክር የጭብጥ አያያዝ ስህተት የፈፀመው ከፍተኛው ፍርድ ቤት ሲሆን የጭብጥ አመሠራረቱ የተጠየቀውን ዳኝነት እና ለክሱም የተሰጠውን ምላሽ መሠረት አድርጐ በተካካዱበት ፍሬ ነገር ላይ ማጠንጠን እየተገባው ከዚህ በመውጣት በተከሣሹ መከራከሪያ ውስጥ ቦታውን በህጋዊ መንገድ አግኝቶታል የሚል በአመልካች ያልተነሳ ወይም ያልተካደ ፍሬ ነገር ይዞ መወሠኑ የጭብጥ አመሠራረት ድንጋጌዎችን ያልተከተለ የክርክር አመራር ማድረጉን ያሳያል።

የተጠየቀው ዳኝነት የጤና ችግር የሚያስከትለው የወፍጮ ሥራ ይቁም ሲሆን በዚህ ላይ የተሰጠው ምላሽ የጤና ችግር አያስከትልም የሚለው የመካድ ክርክር በመሆኑ የተለያዩበት ፍሬ ነገር ወፍጮው የጤና ችግር ያስከትላል ወይስ አያስከተልም የሚለው ነው። የከፍተኛው ፍርድ ቤት ግን በጭብጥነት የያዘው ነጥብ ግራ ቀኙ የተካካዱበትን ሣይሆን በአንድ ወገን ብቻ የተነሣን የክርክር ፍሬ ነገር ነው። የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ የተሳሳተ ጭብጥ ለተሳሳተ ውሣኔ አሠጣጥ ቀጥተኛ ምክንያት መሆኑን ግልጽ ማሣያ ነው።

4.2 ጭብጥን በተገቢው የክርክር ምዕራፍ ላይ አለመመስረት ወይም ምንም ጭብጥ ሳይዙ ውሣኔ ላይ መድረስ

ይህ በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች በስፋት የሚስተዋል ችግር መሆኑን የሰበር መዛግብት ያሣያሉ። የፍትሐብሄር የክርክር ጭብጥ የሚያዘው የግራ ቀኙ በጽሁፍ እና በቃል የሚያደርጉት ክርክር እንደተጠናቀቀ ነው።[28] ሆኖም ክርክሮችን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን የሚመሩት አብዛኛው የክልሉ ወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 241 መሠረት የተከራካሪ ወገኖችን ክርክር በቃል ከተቀበሉ በኋላ መዝገቡን ወይም ጠቅላላ ክርክሩን መርምሮ ጭብጥ ከመያዝ ይልቅ በቀጥታ የግራ ቀኙን ማስረጃ ለመቀበል የመጥሪያ ትዕዛዝ ይሰጣሉ።

ይሄኛው የክርክር አመራር ክርክሩ መነሻውም ሆነ መድረሻው ሳይታወቅ ፍርድ ቤቱም በአግባቡ ሣይገነዘበው ውሣኔ ላይ እንዲደርስ የሚያደርግ ነው። ፍርድ ቤቱ ውሣኔ መስጠት የሚገባው ክርክሩ ውስጥ እልባት የሚሹትን ጭብጦች አስቀድሞ ተገንዝቦ በመለዬት እልባቱንም በተገቢው ማሥረጃ አፈላልጐ ሆኖ እያለ የክርክሩን ችግር ሣያውቅ፣ ማስረጃ የሚቀበለውም ለምን አላማ መሆኑን በውል ሣይረዳ በግምት ክርክሩን መርቶ የሚሰጠው ውሣኔ ውጤቱን አስቀድሞ በፍርድ ቤቱ የማይታወቅ እና ግምታዊ ያደርገዋል።

[28] የፍትሐብሄር ስነ-ስርዓት ህግ፣ ቁጥር 248

ፍርድ ቤቶች ጭብጥ ሣይዙ ክርክሩን መርተው ካጠናቃቁ በኋላ ውሣኔ ሲሰጡ ጭብጥ መስርተው ሲመረምሩ ይስተዋላል። ምንም እንኳ ፍርድ ቤቱ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት አስቀድሞ የተያዙ ጭብጦችን ማሻሻል ወይም አዲስ ጭብጥ መመስረት የሚችል ቢሆንም፣[29] አስቀድሞ የያዘው ምንም ጭብጥ በሌለበት ሁኔታ ፍርድ ሲሠጥ የሚይዘው ጭብጥ ግን ጭብጡን ከተቀበለው የግራ ቀኝ ማሥረጃ ጋር አገናዝቦ የማሥረጃውን አግባብነት ለመለየት የሚያደርገውን ምርመራ አስቸጋሪ ከማድረጉም ባለፈ ጭብጡ ከማስረጃ በኋላ የተመሠረተ በመሆኑ የተሰበሰበው ማስረጃ በጭብጡ የተነሣውን ጥያቄ ለመመለስ የማይጠቅም ሆኖ ሊገኝ ይችላል።

የዚህ ሥነ-ሥርዓታዊ ግድፈት ሠለባ የሆኑ የፍትሐብሄር ክርክሮች እጣፈንታቸው በይግባኝ እና በሠበር እየተሻሩ በአዲስ መልክ ክርክሩ ይቀጥል ዘንድ ጭብጥ በሠበር ሰሚው ወይም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት እየተመሠረተ ግድፈቱን ለፈፀመው ችሎት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 343 መሠረት መመለስ /remand/ ነው።

በወረዳ ፍርድ ቤት በተጀመረ ክርክር ከሣሽ በውርስ ከአባቱ ያገኘውን መሬት ለተከሣሽ ቢያከራዬው እንደቀማው በመግለጽ መሬቱን እንዲመልስለት እንዲወሠንለት ዳኝነት ጠይቋል። ተከሣሽ በመልሱ መሬቱን ከ10 ዓመት በላይ እንደያዘው በመግለጽ ክሱ በይርጋ እንዲቋረጥ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል። የወረዳው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ጭብጥ ሣይመሠርት በይርጋው ላይ በሚል ብቻ የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሠማ በኋላ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ሲል ብይን ሰጠ። ብይኑን ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በይግባኝ ተመልክቶ አፀናው።

ጉዳዩን በሰበር የተመለከተው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰ/ሰ/ችሎት የሥር ውሣኔዎችን ሽሮ "ተከሣሽ መሬቱን የያዘው ከከሣሽ ተከራይቶ ነው ወይስ አይደለም?" የሚለውን ከአጣራ በኋላ በይርጋ መቃወሚያው ላይ የመሠለውን ብይን እንዲሠጥ መዝገቡን ለወረዳው ፍርድ ቤት መልሦታል።[30]

[29] ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 251

[30] ደመላሽ ደመቀ እና ተክሉ ደመቀ፣ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰ/ሰ/ችሎት፣ 2010 ዓ.ም፣ የመሬት ክርክር፣ መዝገብ ቁጥር 60221

በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ላይ ግራ ቀኙ ያደረጉት ክርክር ተከሣሹ ከ10 ዓመት በላይ መሬቱን ስለያዝኩት ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል ሲሆን ከሣሽ ደግሞ መሬቱን አከራይቶት በውል ምክንያት የያዘው መሆኑን ገልፆ ክሱ በይርጋ እንደማይታገድ ተከራክሯል፡፡

የክርክራቸው መለያያ ነጥብ መሬቱን ተከሣሹ የያዘው ያለምንም የውል ግንኙነት ነው ወይስ ከሣሽ እንደሚለው ተከሣሽ ተከራይቶት ነው? የሚለው ነው፡፡ ምክንያቱም በውል ምክንያት መሬቱ ከተያዘ የይዞታ ዘመኑ አስር ዓመት ቢሞላም የይርጋ ዘመኑ ስለማይቆጥርበት ነው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ክርክሩን በአግባቡ በመረዳት ይህን የፍሬ ነገር እና የህግ ጭብጥ ይዞ የግራ ቀኙን ማሥረጃ ከዚሁ ጭብጥ አኳያ በማዳመጥ ብይን መስጠት ሲገባው ጭብጥ ሣይዝ በይርጋው ላይ በሚል ብቻ ማስረጃ ሰምቶ ክሱ በይርጋ ይቋረጣል ሲል መበየኑ መዳረሻውን የተሳሳተ አድርጐታል፡፡ ብይኑ ጭብጥን መሰረት ባደረገ ክርክር መነሻነት ያልተሰጠ መሆኑ ውሳኔው የተሣሣተ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱም በውል ሣይገነዘብ የሰጠው ብይን መሆኑ እንዲታወቅ እና ክርክሩ ወጪና ኪሣራ የበዛበት እንዲሆን አድርጎታል፡፡

በሌላ ክርክር የቀበሌው አስተዳደር ጽ/ቤት ከሣሽ በመሆን በግለሰብ ተከሣሹ ላይ በቀረበው ክስ 1 (አንድ) ቃዳ የወል መሬት ገፍቶ የሰራውን ቤት አፍርሦ መሬቱን እንዲለቅ ይወሠንልኝ ሲል የዳኝነት ጥያቄውን ለወረዳው ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ ግለሰቡ በተከሣሽነት ቀርቦ ቤት የሠራው ህጋዊ ይዞታው በሆነው ግማሽ ቃዳ መሬት ላይ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ ሆኖ በነፃ እንዲሠናበት በማመልከት መልስ ሠጥቷል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን የቃል እና የጽሁፍ ክርክር ከተቀበለ በኋላ ጭብጥ ሣይዝ ማስረጃም ሣይሠማ በተከሣሹ ደብተር ላይ የተከሣሽ ህጋዊ ይዞታ ¼ ቃዳ መሆኑን የተመለከተ በመሆኑ ¼ኛ ቃዳውን ለቆ ለከሣሽ ያሥረክብ ሲል ወስኗል፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በይግባኝ ተመልክቶ የወረዳ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር ተመልክቶ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ በመሻር ተከሣሹ የወል መሬት ገፍቷል ወይስ አልገፋም? ከገፋ ምን ያክል ገፍቷል የሚለውን አጣርቶ እንዲወስን መዝገቡን ለወረዳው ፍርድ ቤት መልሦለታል፡፡[31]

[31] ጌቱ መስፍን እና የአትክና ቀበሌ አስ/ጽ/ቤት፣ የአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰ/ሰ/ችሎት፣ የወል መሬት ክርክር፣ 2010፣ መዝገብ ቁጥር 60187

በዚህ ጉዳይ የወረዳው ፍርድ ቤት የፈፀመው ሥነ-ሥርዓታዊ ግድፈት ጭብጥ አለመያዝ ብቻ ሣይሆን የግራ ቀኙን ማስረጃ ሣይቀበል ያለማስረጃ ውሣኔ መስጠትም ነው፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር ሲመረመር ሙሉ በሙሉ ተካክደው የሚከራከሩ መሆኑን መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ውሣኔው ግን ተከሣሹ ¼ኛ ቃዳ የወል መሬት መያዙን እንዳመነ ወይም በማሥረጃ እንደተረጋገጠበት ተቆጥሮ የተሰጠ ነው፡፡

4.3 ጭብጥን መሠረት ያላደረገ የማሥረጃ አሰባሰብ /አቀባበል/

ትክክለኛ ውሣኔ ለመስጠት ትክክለኛ የክርክር ጭብጥ ከመያዝ ቀጥሎ ወሣኙ ሥነ-ሥርዓታዊ ተግባር በጭብጡ ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች መቀበል ነው፡፡[32] የክርክር ጭብጥ የሚያዘው ትክክለኛ ውሣኔ ለመስጠት የሚያስችሉ ለክርክሩ አግባብነት እና ተቀባይነት ያላቸውን ማሥረጃዎች ለመሰብሠብ እንዲያመች ሲሆን የማስረጃዎች አግባብነትም የሚለካው በተያዘው ጭብጥ መሠረት በመሆኑ አንዱን ከሌላው ነጥሎ ማዬት አይቻልም፡፡

ፍርድ ቤቱ የሚቀበለውን ማንኛውንም ማሥረጃ ተቀባይነት እና አግባብነት ያለው መሆኑን የሚወስነው ከያዘው ጭብጥ ጋር በማገናዘብ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአንድ የክርክር ሂደት የተለያዩ አይነት ማሥረጃዎች በቀረቡ ጊዜ የትኛው አይነት ማሥረጃ ለየትኛው የፍሬ ነገረ ጭብጥ አግባብነት (Relevance) እንዳለው የሚለየውም የተያዘውን ጭብጥ መነሻ በማድረግ ሲሆን በሌላ መንገድ ፍርድ ቤቱ እንዲቀርቡለት ትዕዛዝ የሚሠጥባቸውን ማሥረጃዎች አይነት የሚለዬው ወይም የሚወስነው ከያዘው ጭብጥ በመነሳት ነው፡፡

ከዚህ አኳያ ከጅምሩ ጭብጥ ሣይያዝባቸው የሚመሩ የፍትሐብሄር ክርክሮች ማሥረጃ የሚሠማባቸው ወይም የሚቀርብባቸው ቢሆኑ የሚቀርበው የማሥረጃ ዓይነት ለተያዘው ክርክር እልባት ለመስጠት የሚያግዝ መሆን አለመሆኑ ማሥረጃው በሚቀርብበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ አይገነዘበውም፡፡ ከቀረበው ወይም ከተሠበሠበው ማስረጃ ውስጥ ለክርክሩ አግባብነት ያለው የሚለየው ፍርድ ቤቱ ውሣኔ በሚሰጥበት ጊዜ በሚይዘው ጭብጥ መነሻነት በሚደረግ የምርመራ ሥራ ይሆናል፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ ማስረጃዎች አስቀድመው ሲሠበሠቡ ጭብጥን መነሻ ያላደረጉ በመሆናቸው በውሣኔ አሰጣጥ ጊዜ ከተያዘው ጭብጥ ጋር በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ አግባብነት እና ጥቅም የሌላቸው ሆነው የሚገኙበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡ በዚህ አግባብ

[32] የፍትሐብሄር ስነ-ስርዓት ህግ፣ ቁጥር 257

የተሰበሰበ ማሥረጃ የክርክር ግብን ያላማከለ በመሆኑ የተነሣ ለተሣሣተ ውሣኔ ምክንያት ከመሆኑም ባሻገር የፍርድ ቤቶችን እና የተከራካሪ ወገኖችን ጊዜ እና ጉልበት ያለአግባብ የሚያባክን ይሆናል።

በሌላ በኩል ፍርድ ቤቶች ጭብጥ ከያዙ በኋላ የማሥረጃ አቀባበላቸው የመሠረቱትን ጭብጥ ያላገናዘበ ሆኖ የሚገኝባቸው አጋጣሚዎች ይገኛሉ። ጭብጥ እና ማሥረጃ አንዱ በሌላው ላይ የተመሠረተ እና የማይነጣጠሉ እንደመሆናቸው መጠን ፍርድ ቤቱ የሚቀበለውን ማንኛውንም አይነት ማሥረጃ ከያዘው ጭብጥ ጋር እያገናዘበ መቀበል እና አቀባበሉንም ከዚሁ አኳያ መምራት ይጠበቅበታል። ጭብጡን መሰረት ባደረገ መልኩ ያልተሰበሠበ ማሥረጃ የፍርድ ቤቱን ጊዜ እና ጉልበት ብክነት ብሎም የተከራካሪ ወገኖችን ወጪና ኪሣራ ከሚጨምር በቀር ለትክክለኛ ፍርድ መዳረሻ የመሆን እድሉ አነስተኛ ነው።

ጉዳዩን በምሣሌ ለማሣየት ከሣሽ በ1989 ዓ.ም በሽግሽግ የተመራሁትን መሬት ቀማኝ ብሎ ከሦ ተከሣሹ መሬቱን ቀምቸው ሣይሆን በመሬት ተለዋውጠን የያዝኩት ነው ብሎ መልስ ሠጠ። ቀጥሎ ፍርድ ቤቱ አከራካሪውን መሬት ተከሣሽ የያዘው በለውጥ ነው ወይስ ከከሣሽ ቀምቶ ነው የሚል ጭብጥ ያዘ። በመቀጠል ጭብጡን በማሥረጃ ለማጣራት የግራ ቀኙን ምስክሮች ቃል ተቀብሎ ሲጨርስ ጉዳዩን በባለሙያ ለማጣራት ለክፍሉ ወረዳ አካ/ጥ/መ/አስ/አጠ/ጽ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ አከራካሪው መሬት በ1989 ዓ.ም ለማን እንደተሰጠ ተጣርቶ እንዲቀርብለት አዘዘ። ውጤቱም በ1989 ዓ.ም ለከሣሽ የተሰጠ መሬት መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ መሬቱ የከሣሽ መሆኑ ስለተረጋገጠ ለከሣሽ እንዲመልስ ሲል ፍርድ ሰጠ።

በዚህ የክርክር አመራር ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የያዘው የነገር ጭብጥ ትክክለኛ ቢሆንም ለውሣኔው መሠረት ያደረገውን ማጣሪያ ማሥረጃ ያስቀረበው ግን ከጭብጥ ውጭ በሆነ ነጥብ ላይ በመሆኑ ለያዘው ጭብጥ ምላሽ ሊሆን የሚችል ማስረጃ አልቀረበለትም። በዚህ ምክንያት የሰጠው ውሣኔም ለጭብጡ አግባብነት የሌለውን ማስረጃ መሠረት ያደረገ እና ትክክለኛነትም የጐደለው ሊሆን ችሏል።

5. ማጠቃለያ

በወንጀልም ሆነ በፍትሐብሔር ጉዳዮች ክርክሮች የሚመሩት በስነ-ስርዓት ህግ ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ የስነ-ስርዓት ህጐች የክርክሩን ዱካ በማሣዬት ዳኛውን ወደ ትክክለኛ ውሣኔ አሰጣጥ የሚመሩ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ የክርክር አመራር ከሥነ-ሥርዓት ህጉ ድንጋጌዎች ጋር በቅርበት በተከናወነ ቁጥር ፍትሀዊነቱ የላቀ ትክክለኛ ውሣኔ የመወሠን እድሉ የሰፋ የመሆኑን ያክል ከህግ ውጭ በግምት የተመራ ክርክር ደግሞ በኢ-ፍትሃዊ ፍርድ የመደምደም እድሉ የዚያኑ ያክል የሰፋ ነው፡፡

ተከራካሪዎችን ወደ ፍርድ ቤት የሚወስዳቸው አብይ ምክንያት አለመግባባት ወይም መካካድ ሲሆን የሥነ-ሥርዓት ህጐቻችን ለዚህ የክርክር ሂደት ክፍል ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ፍርድ ቤቶች የግራ ቀኙን ክርክር በጽሁፍ እና በቃል ከተቀበሉ በኋላ ተከራካሪ ወገኖች የተለያዩበትን ወይም የተካካዱበትን ፍሬ ነገር ጭብጥ ብሎ በመተርጐም በአመሠራረቱ እና በአጠቃቀሙ ላይ በቂ ድንጋጌዎችን ያስቀምጣል፡፡ በተለይ የፍትሐብሔር ክርክሮች ጭብጥ አመሠራረት፣ የሚመሠረትበት የክርክር ምዕራፍ እና የጭብጡ ትክክለኛነት ከሚሰጠው ውሣኔ ትክክለኛነት ጋር ያለው ግንኙነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህጋችን በቂ ማዕቀፍ ያገኘ ሲሆን በዚህ ጽሁፍም እያንዳንዱን የጭብጥ አመሠራረት ድንጋጌዎች በተግባር ከሚያጋጥሙ ጉዳዮች ጋር በማገናዘብ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጡ ውሣኔዎችን ለአብነት በማንሣት እና በመተንተን በህጉ እና ተግባሩ መካከል ያሉ ክፍተቶችን ለማሣዬት ጥረት ተደርጓል፡፡

በወንጀል እና በፍትሐብሔር ክርክሮች መሃል ያለውን የጭብጥ አያያዝ ልዩነት የተመለከትን ሲሆን በዋናነት በወንጀል ክስ ክርክር ጭብጥ የሚያስይዙት ዐቃቤ ህጉ እና ተከሣሹ በየራሣቸው የዐቃቢ ህጉ በቅድሚያ የተከሣሹ ደግሞ ከዐቃቢ ህግ ክስና ማስረጃ በኋላ የሚመዘገብ ሲሆን በፍትሐብሔር ክርክር ደግሞ ጭብጥ የሚያዘው በፍርድ ቤቱ በራሱ ከግራ ቀኙ ክርክር በመነሣት ነው፡፡ ሆኖም በፍትሐብሔር ክርክር ተከራካሪ ወገኖች በራሣቸው ጭብጥ ማስመዝገብ የሚችሉበት መብትም በህጉ ተጠብቆላቸዋል፡፡[33]

ትክክለኛ የክርክር ጭብጥ መያዝ ትክክለኛ ውሣኔ ለመስጠት የሚያስፈልግ በመሆኑ የክርክር ጭብጥ አያያዝ ላይ ስህተት የተፈፀመበት ጉዳይ መዳረሻው የተሳሳተ ውሣኔ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ትክክለኛ ጭብጥ መያዝ ለውሣኔያቸው ትክክለኛነት ወሣኝ መሆኑን እና የማሥረጃ

[33] የፍትሐብሄር ስነ-ስርዓት ህግ፣ ቁጥር 252

አቀባበል ትክክለኛነትም ከጭብጡ ትክክለኛነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው መሆኑን ተመልክተው የሚመሩትን ክርክር በተገቢው የክርክር ምዕራፍ ላይ ትክክለኛ ጭብጥ በመያዘ እና ክርክሩን በመምራት ፍትሃዊ እና ትክክለኛ ውሣኔ አሠጣጥን ማጠናቀር ይጠበቅባቸዋል።

6. ምክረ ሀሳብ

- በጭብጥ አያያዝ ችግር ምክንያት በክልሉ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ውሣኔዎች ከወረዳ ፍርድ ቤት ጀምረው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከደረሱ በኋላ ተሽረው ለወረዳ ወይም ለከፍተኛ ወይም ለጠቅላይ ፍ/ቤት ለድጋሚ ክርክር ሲመለሱ በተከራካሪ ወገኖች ላይ የሚደርሠውን እንግልት፣ ወጭና ኪሣራ ለመቀነስ እንዲቻል የክልሉን ዳኞች በቂ እና ተከታታይ የሙያ ስልጠና በመስጠት ወጥ የሆነ የሥነ-ሥርዓት ህግ ግንዛቤ እና አተረጓጎም እንዲኖር መስራት ያስፈልጋል።
- በጭብጥ አመሠራረት ረገድ የሚፈፀሙ ሥነ-ሥርዓታዊ ግድፈቶችን በይግባኝ የሚያርሙ ይግባኝ ሠሚ ፍርድ ቤቶች እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስህተቱን የፈፀሙት ዳኞች ከግድፈታቸው እንዲታረሙ፣ እንዲማሩ እና ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጋር ተመሣሣይ የህግ አተረጓጎም እንዲከተሉ ለማስቻል ስህተቱ የታረመበት ፍርድ ግልባጭ ለፍርድ ቤቱ ብሎም ለወሠነው ዳኛ እንዲደርስ በይግባኝ ሰሚው ችሎት የመታዘዝ ልምድ እንዲዳብር መስራት ያስፈልጋል።
- ዳኞች ክርክሮችን አንብበው፣ መርምረው እና ተገንዝበው ትክክለኛ ጭብጥ ለመመስረት የሚያስችል ምክንያታዊ ጊዜ እንዲኖራቸው እና የተከራካሪዎችን የጽሁፍ እና የቃል ክርክር እንደተቀበሉ ክርክሩን በውል ሣይገነዘቡ በአጣዳፊ ሁኔታ የተሳሳተ ጭብጥ እንዳይመሠርቱ የግራ ቀኙን ክርክር መቀበል እንደተጠናቀቀ መዝገቦች ለምርመራ በቂ ጊዜ ተሰጥቷቸው እንዲቀጠሩ የሚያደርግ የቀጠሮ ፖሊሲ በሁሉም የክልሉ ፍርድ ቤቶች እንዲዳብር መስራት ያስፈልጋል።
- ዐቃቢያን ህግ ከፖሊስ የተረከቡትን መዝገብ መርምረው፣ የመሰረቱትን ክስ ጭብጥ አድርገው፣ ፍርድ ቤት ማስረጃ አቅርበው ከማሰማታቸው በፊት በተሳሳተ ጭብጥ መነሻነት ማስረጃ የማስደመጥ ግድፈትን ለማስቀረት ክሳቸውን ከማስረጃው ጋር የማገናዘብ ስራን የሃላፊነታቸው አካል ማድረግ ያስፈልጋል።

የመንግስት የግንባታ ውሎች እና አጠቃላይ የዉል ሁኔታዎች ከግንባታ አፈጻጸም ጋር ያላቸዉ ግንኙነት ምልከታ

ጋሻዬ ቢያድግ*

አህጽሮተ ይዘት

ይህ ጥናት ዓላማ አድርጎ የተሰራዉ በመንግስት የሚከናወኑ የግንባታ አሰራሮችን ለማሻሻል በማሰብ ነዉ። የግንባታ አፈጻጸም የሚለካዉ በጊዜ፣ በጥራትና በዋጋ ላይ መሰረት አድርጎ ነዉ። የግንባታ አፈጻጸምን ከሚወስኑ አሰራሮች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ ደግሞ የግንባታዉ የዉል ዓይነት ነዉ። የግንባታዉ የዉል ዓይነት በራሱ የግንባታዉን አስተዳደር፣ በግንባታ ወቅት የሚያጋጥሙ አደጋዎችን በተመለከተ በምን ሁኔታ እንደሚተዳደሩ መልስ ከመስጠቱ በላይ የግንባታዉን ፕላን የሚሰራዉና በሂደትም የፕላን ለዉጥ ካለ በሀላፊነት የሚሰራዉን አካል የሚወስንልን አሰራር የግንባታዉ ዉል ዓይነት ነዉ። የግንባታ ዉሎች የተለያየ ቅርፅ (ዓይነት) ያላቸዉ ሲሆኑ ከእነዚህ የግንባታ ዉል ዓይነት መካከል ለመምረጥ የተለያዩ መስፈርቶች እና ከግምት ዉስጥ የሚገቡ ምክንያቶች አሉ። በተጨማሪም የዉሉን ዓይነት ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ አሰራሮች ጋር የሚታዩት የዉል ሁኔታዎች ናቸዉ። የዉል ሁኔታዎች የዉሉን ዓይነት የመወሰን አቅም ባይኖራቸዉም የዉል ሁኔታዎች ሲዘጋጁ የተለያዩ አማራጮችን የዉል ዓይነቶችን ከግምት ዉስጥ ባስገባ መልኩ ሊሆን ይገባል። ይህ ጥናት በሀገራችን የመንግስት ግንባታ ዉሎችን ለማዘጋጀት የሚያስችሉ የዉል ሁኔታዎችን ይመረምራል። ጥናቱ ንድፈ-ሀሳባዊ ስለሆነ ሰነዶችን እና ህጎችን በመመርመር የተከናወነ ዓይነታዊ የጥናት ዘዴን የተከተለ ነዉ። በዚህ መሰረትም የመንግስትን የግንባታ ዉሎች ለማዘጋጀት በስራ ላይ ያሉ አሰራሮች ዉስንነት፣ የተለያዩ የዉል አማራጮን በመከተል ለማዘጋጀት የሚያስችሉ አሰራሮች ላይ ማሻሻያዎች እንደሚያስፈልጉ ይህ ጥናት ይጠቁማል።

ቁልፍ ቃላት:- የግንባታ ዉል፣ የግንባታ ዉል ዓይነት፣ የግንባታ ውል ሁኔታዎች፣ ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች፣ ልዩ የዉል ሁኔታዎች

* በአብክመ የፍትህ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የህግ ምርምር ኢንስቲትዩት በአስልጣኝነትና በተመራማሪነት፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት በዳኝነት ያገለገለ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ በመምህርነት እንዲሁም በየትኛውም ፍ/ቤት ጠበቃና የህግ አማካሪ በመሆን እያገለገለ ይገኛል። ማንኛዉንም አስተያየት በgashayebiadge@gmail.com ልታደርሱኝ ትችላላችሁ።

መግቢያ

የማንኛውም የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ባለድርሻ አካላት መሰረታዊ ግባቸው ፕሮጀክቱ በተገመተው ጊዜ፣ በተተመነው ዋጋና በሚፈለገው የጥራት ደረጃ እንዲጠናቀቅ ማድረግ ነዉ።[1] አንድ የግንባታ ፕሮጀክት በወቅቱ እንዳይጠናቀቅ የሚያደርጉ ምክንያቶች በሰፊዉ በጥናት ተለይተዋል። ከእነዚህ መካከልም የግንባታ ፕላን ለዉጥ (changes in drawings) የተግባቦት ጉድለት፣ የመረጃ ክፍተት፣ የዉሳኔ ሰጭነት ችግር እና የፕሮጀክት አስተዳደር ጉድለት በዋናነት ይጠቀሳሉ።[2] አንድ ግንባታ በተያዘለት ዋጋ፣ ጊዜ እና ጥራት እንዲከናወን የማድረግ ሁኔታ የሚወሰነዉ በሰዉ ሀይል ሀብት፣ የግንባታ ልምድ እና አቅም ነዉ። ስለሆነም በግንባታ ዉጤታማነት ላይ የሰዉ ሀብት አስተዋጽዖ ስላለዉ መንግስት የሰዉ ሀብት አቅም ግንባታ ላይ ትኩረት የመስጠትና አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል ይገባዋል። የመንግስት ግንባታ ፕሮጀክት የተቀናጀ አሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑን ጥናቶች ይጠቁማሉ።[3]

አንደኛዉ አሰራርን የምናሻሽልበት መንገድ ተስማሚ የዉል ዓይነት ማዘጋጀት ነዉ። የግንባታ ዉል፣ በዉሉ ላይ የተቀመጡ እና ስምምነት የተደረሰባቸዉን ጉዳዮች ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ከዚህ ያለፉ እና የዉሉን አስተዳደር የሚመለከት ሥርዓት ጭምር የሚዘረጋ ነዉ። ይህ ሥርዓት የግንባታ ባለድርሻ አካላት በግንባታ አፈጻጸሙ ላይ የሚኖራቸዉን ሚና የሚወስን፣ አደጋዎችን በአግባቡ ማስተዳደር ያለበትን አካል የሚለይ እና አጠቃላይ የግንባታ አፈጻጸሙ ላይ የራሱ የሆነ የማይተካ አስተዋጽዖ ያለዉ ስርዓት መዘርጋትን ይመለከታል።[4]

የመንግስት የግንባታ ፕሮጀክት በወቅቱ፣ በተያዘለት ዋጋ፣ በጥራት እንዳይፈጸም ከሚያደርጉ ችግሮች መካከል የተግባቦት ክፍተት መኖር ብዙ ጊዜ ለክርክርና ለፕሮጀክቱ ዉድቀት አሉታዊ አስተዋጽዖ አላቸዉ። እንዲሁም የፕሮጀክት ስራን በእቅድ አለመምራት በመንግስት የግንባታ ዉል ላይ የሚከሰት እና የተለመደ ችግር ነዉ።

የስራ አድማስ ለዉጥ መኖር በግንባታ አፈጻጸም ላይ ጉድለት እንደሚያስከትል ጥናቶች ያመለክታሉ። የስራ አድማስ ለዉጥ መኖር የግንባታ አፈጻጸም ጊዜን ስለሚያራዝም ለፕሮጀክት

---

[1] Sidwall, A. (1984). Time Performance of Construction Projects Adelaide: South Australian Institute of Technology

[2] World Bank (2004) the Construction Industry: Issues and Strategies in Developing Countries. Washington, DC

[3] ዝኒ ከማሁ

[4] ዝኒ ከማሁ

ውድቅት የሚዳርግ ነዉ። በተለይም በማደግ ላይ ባሉ አገራት የስራ አድማስን በአግባቡ አለማስቀመጥ እና የፕላን እንዲሁም የአስተዳደር ችግር የሚስተዋልበት ዘርፍ ነዉ።[5] ስለሆነም እነዚህና መሰል ችግሮችን ለመቅረፍ እና የግንባታ አፈጻጸምን ለማሻሻል ከሚጠቅሙ መንገዶች አንዱ ተስማሚ የዉል ዓይነት ማዘጋጀት ነዉ።

1. **የግንባታ ዉል ዓይነት**

ውል የተዋዋይ ወገኖችን መብትና ግዴታ እንዲሁም ውሉ የሚተዳደርበትን ደንብና ስርዓት ይይዛል። የግንባታ ውል ትርጉም በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለዉ ትርጉም ማስቀመጥ አስቸጋሪ ቢሆንም ከዉሉ ተፈጥሯዊ ባህሪ በመነሳት ጸሀፍት ተርጉመዉት እናገኛለን። ሁድሰን[6] የተባለ ጸሀፊ ይህን አስመልክቶ የግንባታ ዉል ማለት ስምምነት ሆኖ በተለምዶ ተቋራጭ ወይም ገንቢ በክፍያ ላይ በተመሰረተ ግንባታ ለመስራት ከግንባታዉ ባለቤት ወይም አሰሪ ከሚባለዉ ጋር የሚያደርገዉ ስምምነት ነዉ በማለት አስቀምጦታል። በተመሳሳይ ኬቲንግ[7] የግንባታ ዉል አንደኛዉ ተወዋይ ወገን በክፍያ ላይ የተመሰረተ ግዴታ የሚገባበት በምትኩም ግንባታ ወይም አጠቃላይ የምህንድስና ስራ ለመስራት የሚደረግ ስምምነት ነው በማለት አብዛኛዉን ጊዜ ተቀባይነት ያለው ትርጉም ያስቀምጣል።

እንደ (FIDIC 1987) የግንባታ ውል ማለት ወጥ የሆነ የውል ሁኔታዎች፣ የሥራ መዘርዝሮች፣ የልኬት ዘዴዎች፣ የስራ ንድፎች፣ የዋጋ ልኬቶች፣ የክፍያ እና የልኬት መጠን መርሃ ግብሮች፣ የውል መቀበያ ማስታወቂያ፣ የውል ስምምነቱ እና ሌሎች ሰነዶችን የያዘ ነው።

በኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ህግ ከአንቀጽ 2610-2631 እና ከአንቀጽ 3019-3040 ባሉት ድንጋጌዎች ዉስጥ የግንባታ ዉሎችን አመሰራረት ያስቀምጣል። ከዚህም የግንባታ ዉል ምንነትና አንድምታ የድንጋጌዎችን አጠቃላይ ይዘት በመገንዘብ መረዳት ይቻላል። የግንባታ ዉል ተቋራጭ በክፍያ ላይ በተመሰረተ ግዴታ የሚገባበት ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ የግንባታ ስራ በመስራት ለአሰሪዉ የሚያስረክብበትን ሁኔታ የሚመለከት ነዉ። ይህም ከላይ በጸሀፍት ከተገለጸዉ ትር□ሜ ጋር አብሮ የሚሄድና ተግባር ላይ የሚዉል ትርጉም ነዉ።

[5] የግርጌ መስታወሻ ቁጥር 2

[6] I.N Duncan Wallace, Hudson "Building and Engineering Contracts", 10th ed., (Sweet and Maxwell: London, 1970)

[7] Keating “constraction contract", 8th ed (Sweet and Maxwell: London, 2000)

የዉል አመሰራረት ስርዓት የሚያሳየዉ የግንባታ ሂደቱን እና ግንባታዉ የሚጠናቀቅበትን አጠቃላይ ማዕቀፍ ነዉ። ይ□ዉም የግንባታ ዉሎች ሀላፊነትን፣ የተሳታፊዎችን ግንኙነት ይወስናሉ። ከዚህ በመነሳት ጸሀፍት የግንባታ ዉል አመሰራረት ስርዓት የግንባታዉ ዉጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መኖሩን ያስቀምጣሉ።[8] ይህ ስርዓት የተወዋይ ወገኖችን ስምምነት፣ የተመረጠዉን ዲዛይን፣ ጊዜ፣ ዋጋና ሌሎችን ሁኔታዎች የሚመለከት ስለሆነ የግንባታዉ አፈጻጸም ወሳኝ ምዕራፍ ነዉ።

የግንባታዉን ዉጤታማነት ከሚወስኑት ጉዳዮች መካከል አንደኛዉ የግንባታ <u>ውል ዓይነት</u> ነዉ።[9] "የዉል ዓይነት" የሚለዉ ቃል የተለያየ መልዕክት አለዉ።[10] ስለሆነም የግንባታ ዉል ዓይነት የሚለዉ ቃል እንደአግባብነቱ ጥቅም ላይ የሚዉል ቃል መሆኑን ለመጠቆም እፈልጋለሁ። በዚህ ጽሁፍ የዉል ዓይነት የሚለዉ ቃል የግንባታ ስራዉ የሚከናወንበትን ሂደት (project delivery system) የሚመለከት ነዉ።

የግንባታዉ ዉል ዓይነት የግንባታዉ የስራ አድማስ ወይም ወሰን፣ የተወዋይ ወገኖችን ተነጻጻሪ መብትና ግዴታዎችን ጭምር ስለሚወስን በአጠቃላይ የግንባታዉ አፈጻጸም ላይ ያለዉን ከፍተኛ ሚና መገንዘብ ይገባል። በተጨማሪም በግንባታዉ ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎችን (Risks) በመለየት ሀላፊነት ሊወስድ የሚችለዉን አካል አስቀድሞ ያስቀምጣል። የግንባታ ዉሉ የሚተዳደርበትን መንገድ እና ሁኔታ ስለሚያመለክት በዉል አስተዳደሩ ላይም የራሱ የሆነ ሚና ይጫወታል።[11]

የዓለምአቀፍ የመሀንዲሶች ፌደሬሽን (FIDIC 1992፣ 1999፣ 2006) ሰነድ እንደሚያስቀምጠዉ የግንባታ ዉል ስራዉ የሚፈጸምበትን ዋጋ፣ የሚጠናቀቅበትን ጊዜ፣ ግንባታዉ የሚከናወንበትን መንገድ፣ የግንባታዉን መጠን፣ የጥራት ሁኔታ እና ክፍያ የሚፈጸምበትን ስርዓት የሚይዝ ስለሆነ እነዚህንና ሌሎችንም የዉል ሁኔታዎች በተመለከተ አስቀድመዉ በተዘጋጁ የዉል

---

[8] PETER MARSH Contracting for engineering and construction projects1P.D.V. Marsh - 5th ed. p. cm. ISBN 0-566-08282-9 ገጽ 11 ላይ ይመልከቱ።

[9] Franagan R. & Norman, G. (1993) Risk management and construction Blackwell Scientific Publications

[10] አንደኛዉ የዉል ዓይነት ዋጋን መሰረት አድርገን የዉሉን ዓይነት የምንመድብበት ትርጉም ሲሆን፣ እነዚህም፡- Cost plus Percentage of Cost Contract, Cost plus Fixed Fee Contact, Cost plus, Lump sum and scheduled contract, Unit Price or Bill of Quantity Lump Sum Contract ወዘተ ይመለከታል። ጥቅል ውል (Lump sum contract)፣ እንደገና የሚለካ ውል (Re-measurement Contract)፣ ወጪ የሚሸፈንበት ውል (Cost-reimbursement contact) በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት በዉል ዓይነት የሚጠቃለሉ ናቸዉ።

[11] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9

ሁኔታዎች (standared conditions of contract) በመጠቀም የግንባታ ዉልን ማዘጋጀት የተወዋይ ወገኖችን መብትና ሀላፊነት በግልጽ ለመለየት ስለሚረዳ የግንባታዉ አጠቃላይ አፈጻጸም ላይ ከፍተኛ አወንታዊ አስተዋጽዖ እንደሚኖረዉ በሰነዱ መግቢያ ላይ ተመላክቷል።[12] ለዚህ ደግሞ በዋና ምክንያትነት የሚጠቀሰዉ እነዚህ የዉል ሁኔታዎች የረጅም ጊዜ የባለሙያዎችን ልምድ በመጠቀም የተዘጋጁ በመሆናቸዉ አዲስ ከሚዘጋጁ ዉሎች ጋር ተያይዞ ከሚፈጠሩ ዉዥንብሮች ይታደጋሉ።

በግንባታ ስራ ወቅት አደጋዎች የማይቀሩ ክስተቶች መሆናቸዉ ላይ ብዙዎች ይስማማሉ።[13] “The sum of the risks and responsibilities involved in the execution of the planned project do not change because of the method of contracting which is adopted. They are a function of the nature of the project itself and its location related to the technology to be employed and the physical and political conditions under which the work is to be executed. What the particular method of contracting chosen will do is to allocate the risks as between the parties involved and in so doing affect the likely outcome of the project in terms of cost, time and performance.”

ከዚህ ዓረፍተ ነገር መረዳት እንደሚቻለዉ አንድን የግንባታ ስራ በተፈለገዉ ደረጃ ለማከናወን ሲታሰብ የሚያጋጥሙ አደጋዎች (Risks) ወይም ሀላፊነቶች በተጠቀምንበት የግንባታ ዉል ዓይነት ሊለወጡ ወይም ሊቀየሩ አይችሉም። ይልቁንም የዉል ዓይነቶች የሚወስኑት በግንባታ ዉል ተሳታፊ በሆኑ ወገኖች ላይ ያለዉን የሀላፊነት ዘዉግ ይሆናል። ይህ የሀላፊነት ዘዉግ በግንባታዉ አጠቃላይ አፈጻጸም ላይ በተለይም ከዋጋ፣ ከጊዜ እና ግንባታዉ የሚጠናቀቅበትን ሁኔታ ስለሚወስን ስራዉ ችግር ሊገጥመዉ ወይም የገንዘብ ግሽበት በመከሰቱ የስራዉ ጥራት ላይ ቀጥታ ተጽዕኖ የሚያሳርፉ አደጋዎችን በማስተዳደር ረገድ **የግንባታዉ ዉል ዓይነት ጥሩ** መሆን ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለዉ።[14] ይህም አደጋዎችን በአግባቡ ማስተዳደር እንጅ ማስቀረት አይቻልም ከሚለዉ መርህ ጋር አብሮ የሚታይ ነዉ።[15] ስለዚህ የሚመረጠዉ የግንባታ ዉል

[12] FIDIC (2006) Conditions of Contract for Construction: For Building and Engineering Works designed by the Employer, Multilateral Development Bank Harmonized Edition. Fédération Internationale des Ingénieurs-Conseil

[13] Bunni, Nael G. (2003). Risk and Insurance in construction, 2nd ed. Spon Press, London

[14] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8 ላይ ከገጽ 7 ጀምሮ ይመልከቱ።

[15] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9 ላይ ከገጽ 33 ጀምሮ ይመልከቱ።

ዓይነት የሚከሰቱ አደጋዎችን በማስተዳደር ረገድ የራሱ ሚና እንዳለዉ በመገንዘብ ተስማሚ የግንባታ ዉሎችን በማዘጋጀት የግንባታ አጠቃላይ አፈጻጸምን ማሳደግ ይገባል።[16]

ከውል ዓይነት ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ተብለዉ የሚታወቁት ችግሮች፣ ግልጽ ያልሆነ የስራ ወሰን (unclear scope of work) ግልጽ ያልሆነ የስራ ዝርዝር ወደ ግጭት እና የዉል አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳርፋል። ሌላዉ የጊዜ ሰሌዳ በአግባቡ ያላስቀመጠ የዉል ዓይነት በወቅቱ አለመፈጸም ችግርና በተለያየ ምክንያት የግንባታ አፈጻጸም መዘግየት ሊያስከትል ይችላል። የውል ሁኔታዎች መለወጥ እና የስራ አድማስ መለወጥ ወይም ተጨማሪ ስራዎች፣ ወጭ እና ጊዜን ይጠይቃሉ። አለመግባባቶች የሚፈቱበት ሁኔታ በተለያዩ ምክንያቶች አለመግባባቶች ስለሚከሰቱና በአግባቡ ካልተመሩ በዉል አፈጻጸሙ ላይ ተጽዕኖ ያሳርፋሉ።[17]

የውል አፈጻጸም አደጋ (Risks) ተወዋይ ወገኖች በስራ አፈጻጸሙ ላይ የሚከሰቱ አደጋዎችን አስመልክቶ በአግባቡ ካልተስማሙ የዉል አፈጻጸሙ ላይ ተጽዕኖ ያሳርፋል።[18] ይህም የግንባታ ስራ አፈጻጸም በሚጠበቀዉ ደረጃ ሳይፈጸም ሊቀር ይችላል። በስራ አፈጻጸሙ ላይ የሚደርሱ ተፈጥሯዊ አደጋዎች በተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰዉ ሰራሽ ምክንያቶች የዉል አፈጻጸሙን ሊያስተጓጉሉት ይችላሉ። በተመሳሳይም ምጣኔ ሀብታዊ በሆኑ ምክንያቶች የዉል አፈጻጸሙ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳርፍ ይችላል። ስለሆነም የሚዘጋጀዉ የዉል ዓይነት እነዚህን ከዉል ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ችግሮችን የሚቀርፍ ሊሆን ይገባል።

በአሁኑ ሰዓት ተቀባይነት ያገኙ ሶስት ዓይነት የግንባታ ዉል አመሰራረት ወይም የግንባታ ዉል አይነቶች አሉ።[19] እነሱም፡- 1/ ባህላዊ ዉል (traditional type of contract)፣ 2/ የተቀናጀ ዉል (integrated or single type of contract) እና 3/ የግንባታ አስተዳደር ዉል (Construction Management Contract) ሲሆኑ የግንባታ ውሎች ሲዘጋጁ እንደፕሮጀክቱ ባህርይና ተስማሚነት እየታዩ የሚመረጡ ይሆናል። በሚቀጥለዉ ክፍል እያንዳንዱን የዉል ዓይነት ባህሪ፣ ጠንካራና ደካማ ጎን እንመለከታለን።

[16] በመሀንዲሶች ፌደሬሽን ሰነድ መሰረት (FIDIC (2006, 1999, 1992), የሚከተለዉን ዓረፍተነገር እናገኛለን "the contract to be used is one of the first questions to address when documenting a project" ይህም የግንባታ ዉል ከመፈጸሙ በፊት የዉል ዓይነት መምረጥ አስፈላጊነትን ያሳያል።
[17] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8
[18] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9
[19] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8 ላይ ከገጽ 7 ጀምሮ ይመልከቱ።

2.1 ባህላዊ የግንባታ ዉል ዓይነት (design - bid - build)፡- የዚህ ዉል ልዩ ባህሪ የግንባታዉ ዲዛይን እና አጠቃላይ የግንባታዉን ስራ በተመለከተ ያለዉ ሀላፊነት መለያየት ነዉ፡፡ በአሰሪዉ ወይም በአማካሪው እና በተቋራጩ መካከል የተለያየ ሀላፊነት የሚያስቀምጥ የውል ዓይነት ነው፡፡ የዚህ ዓይነት የግንባታ ዉል የሚያስፈልገዉ ፕሮጀክቱን በቶሎ ለማጠናቀቅ ሲፈለግ እና በዝቅተኛ ዋጋ በዉድድር ለማሰራት ሲፈለግ፣ የፕላን ለዉጥ ሊኖር ይችላል ተብሎ ሲታሰብ፣ የፕሮጀክት ስራዉ በአሰሪዉ ቁጥጥር ስር መሆን የሚያስፈልግ ሲሆን ለምሳሌ ቅርስ እና የታሪክ ግንባታዎችን በተመለከተ ሲሆን የዚህ ዓይነት የዉል ዓይነት ተመራጭ ይሆናል፡፡[20]

ሌላዉ የዚህ ዓይነት ግንባታ ዉል ፕላኑን በሚያዘጋጀዉና በተቋራጩ መካከል የተቃርኖ ሁኔታን ስለሚያሳድር ለግጭት ይዳርጋል፡፡ በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ጸሀፍት እንደሚገልጹት የባህላዊ የግንባታ ዉል ዓይነት ላለፉት ሶስት አስርት ዓመታት ተቀባይነቱ እየቀነሰ መጥቷል፡፡[21]

2.1.1 ጠንካራ ጎን

ይህ የዉል ዓይነት ለአሰሪዉ የፕላን ስራዉን በብቸኝነት በባለሙያ ለማሰራት እድል ይሰጠዋል፡፡ ይህም ስራዉን ለመቆጣጠርና ዉሳኔዎችን በፍጥነት ለመወሰን ይረዳል፡፡ የግንባታዉ አጠቃላይ አስተዳደር በአሰሪዉ ስለሚከናወን በንጽጽር ከዋጋ አንጻር ዝቅተኛ ነዉ፡፡

2.1.2 ደካማ ጎን

አጠቃላይ አስተዳደር ስራዉ በአሰሪዉ ስለሚከናወን በአስተዳደር ረገድ የሚከሰት ጉድለት ወይም (Risk) በአሰሪዉ ላይ ይወድቃል፡፡ የዚህ ዓይነት የግንባታ ዉል በስፋት የሚነሳበት ችግር ሂደቱ ረጅምና የተለያዩ የዉል ሰነዶችን የሚይዝ ስለሆነ ብዙ ጊዜ ግልጸኝነት ስለሚጎድለዉ ለክርክር ይዳርጋል፡፡ በተጨማሪም የፕላን ይሁን የዉል አስተዳደር አደጋዎችን የሚሸከመዉ አሰሪዉ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል በጀት በማቀድ ረገድ በንጽጽር ተቋራጩ የተሻለ እዉቀት ሲኖረዉ አሰሪዉ ግን አጠቃላይ በጀት ማቀድ ላይ የሚስተዋል ክፍተት እንዳለበት መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡[22] ስለሆነም ይህ የግንባታ የዉል ዓይነት አደጋዎች ክፍፍል ላይ ሚዛናዊ አይደለም፡፡

---

[20] Seely, I. H. Quantity surveying practice London (1997)
[21] ዝኒ ከማሁ
[22] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 4ን ይመልከቱ፡፡

2.2 የተቀናጀ የግንባታ ዉል ዓይነት (design - build)፦ ይህ የግንባታ ዉል ዓይነት ደግሞ የዲዛይን ስራዉ እና አጠቃላይ የግንባታ ስራዉ የሚከናወነዉ በተቋራጩ ነዉ።[23] የዚህ ዉል ዓይነት ዋና ዓላማ አብዛኞችን የአደጋ (Risks) አይነቶችን ከአሰሪዉ ወደ ተቋራጭ ማስተላለፍ ነዉ። አደጋዎች ሲባል ለምሳሌ ዲዛይን ላይ ለሚከሰት አደጋ፣ በግንባታ ሂደት ለሚከሰት አደጋ እና ሌሎች ምጣኔ ሀብታዊ አደጋዎች ሊሆኑ ይችላል። ስለሆነም የውሉ ዓይነት የተቀናጀ ከሆነ እነዚህን አደጋዎች በሀላፊነት የሚሸከመዉ ተቋራጩ ይሆናል። ይህ የግንባታ ዉል ዓይነት ከሌሎች የግንባታ ዉል አይነት ጋር ሲነጻጸር በተቋራጭ ላይ የበለጠ ጫና አለዉ።[24] በዚህ የዉል ዓይነት መሰረት የአሰሪዉ ሀላፊነቶች የተወሰኑ ሲሆኑ የግንባታ ስራዉ የሚሰራበትን ሁኔታ መግለጽ፣ የግንባታ ቦታዉን ማስረከብ፣ የግንባታ ስራዉ የደረሰበትን ሁኔታ መከታተል፣ ክፍያ መፈጸምና የግንባታ ስራዉ በተፈለገዉ ደረጃ ከተከናወነ ርክክብ መፈጸም ብቻ ይሆናሉ። ከዚህ በላይ ከተገለጹት ዉጭ ያሉ ተግባሮች በሙሉ የተቋራጩ ሀላፊነት ይሆናሉ ማለት ነዉ። ይህን የግንባታ የዉል ዓይነት በተመለከተ ዓለም ዓቀፍ አጠቃላይ የዉል ሁኔታዎች ከሚያስቀምጧቸዉ ግዴታዎች መካከል ዋና ዋናዎቹን ስንመለከት፦

- ግንባታዉ የሚከናወንበትን ፕላን (Design) የማዘጋጀትንና ከፕላን ስራዎች ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ አደጋዎችን ይሸከማል።
- ለጊዜ ማራዘሚያነት የሚያገለግሉ ምክንያቶች በዚህ የግንባታ ዉል ዓይነት በአብዛኛዉ አገልግሎት ላይ አይዉሉም።
- የግንባታ ስራዉ ተጠናቆ ርክክብ የሚፈጸመዉ ሁሉም የዋስትና ዓይነቶች ከተፈተሹ እና የአፈጻጸም ጉድለት ካለ በዉሉ የተመለከተዉ ካሳ ከተከፈለ በኋላ ይሆናል።
- የተራዘመ የሀላፊነት ዋስትና ጊዜ በዚህ የዉል ዓይነት ጊዜ የተለመደ ነዉ።[25]

የተቀናጀ የግንባታ ዉል ዓይነት ለማዘጋጀት በምሳሌነት የሚጠቀሰዉ የ(FIDIC Conditions of Contract for Design and Build-Turnk) በመባል የሚጠራዉ ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎችን የሚገልጸዉ ክፍል ነዉ።[26] ነገር ግን ይህ የ(FIDIC) የዉል ሁኔታ የስራ ጥራት ሁኔታን

---

[23] ገዙ ከማሁ

[24] Hendrickson, C. (2000). Project Management for construction, Second edition በሚከተለዉ አድራሻ ማግኘት ይቻላል online - http://www.ce.cmu.edu/pmbook/

[25] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 20

[26] Turner, W. (In Fenn, P. and Gameson, R. (eds), (1992). Construction Management integration: Ananalysis of the degree of integration between construction professional and Project performance

አስመልክቶ የሚሰጠዉ የዋስትና ጊዜ ርዝማኔ 12 ወር ብቻ በመሆኑ በአንዳንድ ጸሀፍት ይተቻል።[27] ይሁን እንጅ የዚህ ዓይነት የግንባታ ዉል ፕላንና የግንባታ ስራ በአንድ ተቋም የሚከናወን በመሆኑ ፕላኑን በሚያዘጋጀው እና በተቋራጩ መካከል የሚኖረዉን ግጭት ያስቀራል። ፕላኑ በተቋራጩ በየጊዜዉ እየተገመገመ ግንባታዉ በተያዘለት ዓላማ የሚከናወን ስለመሆን አለመሆኑ ስለሚታይና ስለሚፈተሽ ከወጭ አንጻርም በዚህ ረገድ የተሻለ ነዉ።[28]

1.2.1 ጠንካራ ጎን

ይህ የግንባታ ዉል ዓይነት አጠቃላይ የስራ ሀላፊነት ለአንድ ተቋም ስለሚሰጥ በአሰሪዉ በኩል ለግንባታ አስተዳደር የሚወጣዉን ወጭ ይቆጥባል። ግንባታዉን ለማጠናቀቅ በአንጻራዊ ሁኔታ ያነሰ ጊዜ ያስፈልገዋል። የፕላን ስራዉ ለዉድድር ለጫራታ ስለሚቀርብ ፈጠራን ያበረታታል፤ በሂደትም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አለዉ።

በግንባታ ሂደት ዉስጥ ፕላን የማዘጋጀት ምዕራፍ ሊቀጥል የሚችልበት አጋጣሚ ስለሚኖር ይህንንም የማሻሻል ተግባር በተሻለ ሁኔታ የሚከናወነዉ መጀመሪያ ፕላን ባዘጋጀዉ አካል ቢሆን ጥሩ እንደሆነ ይታመናል።[29] ይህም የግንባታዉን ጥራትና ጊዜ እና ወጭ በመቀነስ የግንባታ ሂደቱን ያፋጥናል። የግንባታዉን የፕላን ስራ፣ የግንባታ ስራ፣ የግዥ ስራዉ ደግሞ ከሌላ ተቋም ጋር የሚደረገዉን የዉል እና የጫራታ ሰንሰለት በማስቀረት የግንባታ መዘግየትን ይቀርፋል።

1.2.2 ደካማ ጎን

አንድ ጊዜ የተቀናጀ የግንባታ የዉል ዓይነት ከተመሰረተ አሰሪዉ ለተለያዩ አነስተኛ ስራዎች ሌሎች በምጣኔ ሀብታዊ ምክንያት ዝቅተኛ ተቋራጮችን የማሰራት እድልን ያጣብባል። አነስተኛ ስራዎችን በአነስተኛ ዋጋ ለማሰራት ያለዉን እድል አሰሪዉ ይቸገራል። የግንባታ ስራዉ አጠቃላይ ዋጋ ከግንባታዉ ጋር ካሉ አደጋዎች (Risks) ግምት ዉስጥ በማስገባት ዋጋዉ በአንጻራዊነት ከፍተኛ ነዉ። በዚህ የግንባታ የዉል ዓይነት አብዛኛዉ የግንባታ አደጋዎችን

[27] ዝኒ ከማሁ
[28] ዝኒ ከማኑ
[29] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 16

የሚሸከመዉ ተቋራጩ በመሆኑ በአግባቡ ማስተዳደር ካልተቻለ ተቋራጩን ለኪሳራ ሊዳርግ ይችላል።[30]

1.3 የግንባታ አስተዳደር ዉል (Construction management contract)

ይህ የግንባታ ዉል ዓይነት በቅርብ ጊዜ የተጀመረና በመንግስት አማካኝነት የሚቋቋም የባለሙያዎችን ስብስብ የያዘ ሲሆን እነዚህ ባለሙያዎች የሚሰጣቸዉ ሀላፊነት የግንባታዉን ፕላን ማዘጋጀትና የግንባታዉን ሂደት እንዲሁም የግንባታዉን ዋጋ ማስተዳደርን ያጠቃልላል። እነዚህ ባለሙያዎች የፕላን መስፈርቱን መሰረት በማድረግ የግንባታ ስራዉ ከተያዘዉ በጀት አንጻር የሚከናወን መሆን አለመሆኑን ይገመግማሉ። ይህ ዓይነት የግንባታ ዉል ዓይነት በአሁኑ ሰዓት በአጠቃላይ የዉል ሁኔታዎች አማካኝነት የተደገፈና የዳበረ አሰራር አይደለም። ነገር ግን ይህ አሰራር እንደ አንድ አማራጭ ተደርጎ በተለያዩ ሀገራት ተግበራዊ እየተደረገ ይገኛል።[31] የዚህ የዉል ዓይነት ጠንካራና ደካማ ጎን ከመንግስት መዋቅራዊ ሁኔታ ጋር የሚገናኝ ነዉ።

ከላይ የተጠቀሱት የዉል ዓይነቶች የራሳቸዉ የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አላቸዉ። ስለሆነም ተስማሚ የዉል ዓይነቶችን ለመምረጥ እነዚህን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመመርመር ሊሆን ይገባል። የዉል ዓይነቶችን ለመምረጥ ከግምት ዉስጥ የምናስገባቸዉ መስፈርቶች የሚከተሉት ሲሆኑ እነዚህን ነጥቦች በመመርመር የዉሉን ዓይነት መወሰን ይገባል።[32]

- **ጊዜን ከግምት ዉስጥ ማስገባት፡-** ግንባታዉን በአጭር ጊዜ ማጠናቀቅ ከወጭና ከአደጋዎች ሊታደግ ይችላል። የግንባታ ውል አፈፃፀም ረዥም ጊዜ የሚወስድ እና በግንባታው ላይ ግድፈቶች ዘግይተው ሊታዩ መቻላቸው አንደኛዉ ባህሪዉ ቢሆንም ተግባራዊ የምናደርገዉ የዉል ዓይነት የጊዜ አጠቃቀማችን ላይ ያለዉን ክፍተት በማስተካከል የግንባታ አጠቃላይ አፈጻጸማችን ላይ የራሱ አስተዋጽዖ አለዉ። በተለይ ደግሞ መንግስት የሚያከናዉናቸዉን ግንባታዎች በተመለከተ እና ከመንግስት ግንባታዎች መዘግየት ጋር ተያይዞ ያለዉን ችግር በመረዳት በዚህ ረገድ ተግባራዊ የምናደርገዉ የዉል ዓይነት ምን ያህል አስፈላጊ ቅድመ-ሁኔታ እንደሆነ መረዳት አያዳግትም።

---

[30] ዝኒ ከማሁ

[31] ዝኒ ከማሁ

[32] ከላይ በመስፈርትነት የተመለከቱት ነጥቦች በዝርዝር ለማግኘት፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 24 Hendrickson (1998) online - http://www.ce.cmu.edu/pmbook/ ላይ ይመልከቱ።

- **ለተጨማሪ ስራ የማይዳርግ፡-** የዉል ዓይነቱ ለተጫማሪ ስራና ወጭ የሚዳርግ መሆን አለመሆኑን መገምገም ይገባል፡፡ የሥራ መለዋወጥ የሚጠበቅና የማይቀር ስለመሆኑ (variations to the works are almost inevitable) ብዙ ጊዜ ይታመናል፡፡ በግንባታው ውቅት በሚታዩ ጉድለቶች ምክንያት ወይም ከዲዛይን ጉድለት ምክንያት ጋር በተያያዘ ብዙ ጊዜ ለተጨማሪ ስራዎች የሚዳረግበት አጋጣሚ አንዱ የግንባታ ዉል ልዩ ባህሪ እስኪመስል ድረስ ይስተዋላል፡፡ በተለይ ደግሞ በግንባታዉ ሂደት ወቅት የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት ብዙ ከመሆናቸዉ ጋር ተያይዞ ግንባታዉ በመጀመሪያዉ ፕላን መሰረት የማይፈጸምበት ዕድል ይሰፋል፡፡ ስለሆነም ይህንን ችግር የሚቀርፍ የዉል ዓይነት አስቀድሞ በማዘጋጀት የግንባታዉን አፈጻጸም ማሳደግና ከተጨማሪ ስራና ተጨማሪ ወጭ መዳን ያስፈልጋል፡፡
- **አደጋዎችን የሚያከፋፍልበት ሁኔታ፡-** በግንባታዎች ሂደት ዉስጥ ማስቀረት የማይቻልን ነገር በአግባቡ በማስተዳደር ተጽዕኖዉን መቀነስ የሚቻለዉ አደጋዎችን ለግንባታ ተዋንያን በአግባቡ ማከፋፈልን አንድ ዉል ሲዘጋጅ ግምት ውስጥ ማስገባት ይገባል፡፡ የግንባታዉ ዘርፍ ከፍተኛ በሆኑ አደጋዎች (risks) እና ኃላፊነት (liabilities) የተሞላ ስለሆነ እነዚህን አደጋዎች በአግባቡ ማስተዳደር ለሚችለዉ ወገን አስቀድሞ ማከፋፈል አጠቃላይ የግንባታ አፈጻጸሙ ላይ የሚኖረዉ አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነዉ፡፡ ስለዚህ የሚዘጋጀዉ የዉል ዓይነት በዚህ ረገድ የታሰበበትና ችግር የሚፈታ መሆን አለበት፡፡
- **የፕሮጀክቱ ዓይነትና ዉስብስብነት፡-** የዉሉን ዓይነት ለመምረጥ አንደኛዉ ከግምት ዉስጥ ማስገባት ያለብን የፕሮጀክቱን ዓይነት መሰረት አድርገን ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት የራሱ ልዩ ባህርይ ያለው በመሆኑ (Prototypical Nature of the Works) የሚዘጋጀዉ የዉል ዓይነትም ለዚሁ ስራ የሚስማማ መሆኑ ተመርምሮ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡[33]

2. **ጠቅላላ የውል ሁኔታዎች አስፈላጊነት** (Standard condition of contract)[34]

የዉል ሁኔታዎች ሁለት ዓይነት ይዘት ሲኖራቸዉ፣ ጠቅላላ የዉል ሁኔታ እና ልዩ የዉል ሁኔታ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች ለረጅም ጊዜ ጥቅም ላይ የዋሉ እና

[33] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 26 ይመልከቱ፤ የFIDIC ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች የተዘጋጁት በተለያዩ ዘርፎች ሆኖ አጠቃቀማቸዉም እንደ ግንባታዉ ባህሪ እንደሆነ የሰነዱ አጠቃቀም መመሪያ ያስረዳል፡፡

[34] የሲቪል መሀንዲስ ኢንስቲትዩት (ICE) (ACE) የአማካሪ ማሕንዲስ ማህበር)፣ የመሀንዲሶች ፌደሬሽን (FIDIC) አዲስ የምህንድስና ዉል (NEC) የሚሉት ዓለም አቀፍ የጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች ተጠቃሾች ናቸዉ፡፡

ተቀባይነት ያላቸዉ ሁኔታዎች ሲሆኑ ልዩ የዉል ሁኔታዎች ደግሞ ዝርዝር ድንጋጌዎች በባለ ድርሻ አካላት ፍላጎት የሚጨመሩ ናቸዉ፡፡

ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አስፈላጊነት የግንባታ ዉሉ በሚዘጋጅበት ወቅት የሚፈጠሩ ጉድለቶችን ወይም ግድፈቶችን ለማስቀረትና በተቋራጩና በአሰሪዉ መካከል መልካም ግንኙነት ለመፍጠር በማሰብ ነዉ፡፡[35] ይህም የተወዋይ ወገኖችን ወጭና ጊዜ ይቆጥባል፡፡ ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች የረጅም ጊዜ ልምድ ባለቸዉ ባለሙያዎችና ተቋማት የተዘጋጁ ስለሆኑ ዉጤታማ የሆነ ዉል ለማዘጋጀት ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸዉ፡፡[36] በአብዛኛዉ ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ የተዋዋይ ወገኖችን ጥቅም ያስከብራሉ፡፡ ጠቅላላ የውል ሁኔታዎች የተዋዋይ ወገኖችን ሀላፊነትና የስራ ድርሻ አስቀድመዉ ስለሚያስቀምጡ በግንባታዉ የሚሳተፉ ወገኖችን በማስተዳደር ግንባታዉ በአግባቡ እንዲከናወን ይረዳሉ፡፡

ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች ተዋዋይ ወገኖች በተወሰኑ የዉል ሁኔታዎች ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ይረዳሉ፡፡ እነዚህ የዉል ሁኔታዎች በዘርፉ አቅም ባለቸዉ ባለሙያዎች እና ተቋማት ስለሚዘጋጁ ግልጽነት የተሞላበት ዉል ለማዘጋጀት ጠቃሚ ቢሆኑም ጊዜዉን የዋጀ የዉል ሁኔታዎች ለማዘጋጀት እና እንደ ፕሮጀክት ዓይነቱ ተስማሚ የዉል ሁኔታዎችን ወይም የአሰሪዉን ልዩ ፍላጎት መሰረት በማድረግ የዉል ሁኔታዎችን ለማዘጋጀት ግን አስቸጋሪ የሚሆንበት አጋጣሚ አለ፡፡[37] በአሁኑ ሰዓት ጥቅም ላይ የዋሉ የተለያዩ ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አሉን፡፡ እነዚህ የዉል ሁኔታዎች የግንባታ ስራዉ የሚከናወንበትን ደረጃ፣ ጊዜ፣ መጠንና የግዥ ሂደቱን አስመልክተዉ ዝርዝር ነጥቦችን ስለሚያስቀምጡ በዉል ሁኔታዎች መሰረት የዉል አስተዳደሩ ይከናወናል፡፡

ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች ዓለም አቀፍና ሀገራዊ ወይም የሀገር ዉስጥ ብለን መክፈል እንችላለን፡፡ እንደ FIDIC (2006, 1999, 1992)[38] በመጀመሪያ መታየት የሚገባዉ የዉሉ

[35] Chrisna Du Plessis (2007). A strategic framework for sustainable construction in developing countries Construction Economics and Management, 25:1

[36] … construction could not function efficiently without the use of standardized construction contracts

[37] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 23

[38] FIDIC (1987) Conditions of Contract for Works of Civil Engineering Construction, 4th ed Fédération Internationale des Ingénieurs-Conseils
FIDIC (1999) Conditions of Contract for Construction: For Building and Engineering Works designed by the Employer, 1st ed. Fédération Internationale des Ingénieurs-Conseils

ዓይነት ሲሆን ይህም የሚወሰነው በፕሮጀክቱ ዓይነት እና የፕሮጀክቱን ፕላን የሚያዘጋጀው አካል ማን ነዉ የሚሉትን ነጥቦች መሰረት በማድረግ ይሆናል። በዚህም መሰረት፡-

- ፕሮጀክቱ ቀላልና የማያስቸግር ከሆነ - የFIDIC አጭር ኮፒ ተግባራዊ ይደረጋል።
- አሰሪዉ ፕላን የማዘጋጀት ሀላፊነቱ የእርሱ ከሆነ - The "Red Book" for Building and Civil Engineering Works designed by the Employer Conditions of Contract
- የፕላን ስራን በተመለከተ ተቋራጩ የሚያዘጋጅ ከሆነ - The "Silver Book" EPC (Turnkey) Contract Conditions
- የዓለም ዓቀፍ አበዳሪዎች የገንዘብ ምንጭ በሆኑበት ፕሮጀክት - FIDIC (2006) 4th Edition ተግባራዊ ይሆናል።
- ተቋራጩ ፕላን የማዘጋጀትና ስራዉ ኤሌክትሪካል መካኒካል ስራ ከሆነ "Yellow Book" - Plan and Design-Build Contract Conditions.

ከላይ በምሳሌነት ያየነዉ የFIDIC ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አጠቃቀም የሚያስገነዝበን ቁም ነገር አለ። ይኸዉም ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አንድ ወጥ ብቻ ሳይሆኑ እንደ ፕሮጀክት ዓይነቶች የሚለያዩ፣ የፕላን ዝግጅት ሀላፊነት በተለያየ ሁኔታ ለአሰሪዉ ወይም ለተቋራጩ ሀላፊነት የሚሰጡ ናቸዉ። ስለሆነም የዉል ሁኔታዎች በአማራጭነት የተዘጋጁና አስቀድመዉ ፕሮጀክቱንና የዉሉን ዓይነት ጠንካራና ደካማ ጎን በመመዘን በተዋዋይ ወገኖች የሚመረጡ ይሆናል። እንደ (FIDIC, 1999) ጥሩ የዉል ዓይነት የሚከተሉትን የሚያካትት ነዉ። 1/ አንድ ዉል በታለመለት ደረጃ ግቡን የሚመታ ሲሆን 2/ ዉሉ ውጤታማ (efficient) ማለትም በግንባታ ሂደቱ የተጠቀምንባቸዉ ግብአቶችና የምናገኘዉ ውጤት ሚዛናዊ መሆን አለበት። ስለሆነም አንድን ግንባታ ለማከናወን ከመጀመራችን አስቀድመን የዉሉን ዓይነትና ዉሉ ለስራዉ ያለዉን ተስማሚነት በተገቢዉ መመርመር የሚያስፈልግ መሆኑን ያስገነዝባል።

2.1 *ሀገራዊ ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች*

በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች የተዘጋጀዉ በ1951 ዓ.ም ሲሆን የተዘጋጀዉም በከተማና ቤቶች ልማት ሚኒስቴር ነበር። በመቀጠል ከአስር ዓመት በኋላ 1969

FIDIC (2006) Conditions of Contract for Construction: For Building and Engineering Works designed by the Employer, Multilateral Development Bank Harmonized Edition. Fédération Internationale des Ingénieurs-Conseils

በድሮው የህንፃና ትራንስፖርት ኮንስትራክሽን ዲዛይን ባለስልጣን የወጣ ሲሆን በ1987 እንደገና ተሻሻለ፡፡[39]

በ1984 ዓ.ም የሲቪል የግንባታ ስራዎች ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች በተሚላ ሁኔታ ከጫራታ ሰነድ ጋር የሚዘጋጅ የዉል ሁኔታ ተዘጋጅቷል፡፡ በ2006 ዓ.ም የጫራታ ሁኔታን የሚያስተዳድር ሰነድ በገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር (SBD) ተዘጋጅቷል፡፡[40] በዚህ መሰረት አሁን በስራ ላይ የዋሉ እነዚህ ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች ያሉ ሲሆን በሚቀጥለዉ ክፍል የጠቅላላ የዉል ሁኔታዎችን ከዉል ዓይነቶች ጋር በማያያዝ እና አጠቃላይ በግንባታ አፈጻጸም ላይ ያለዉን ተጽዕኖ በማየት አስፈላጊ ማስተካከያ የሚያስፈልግበትን ነጥብ መጠቆም አላማ የዚህ ጽሁፍ ግብ ነዉ፡፡ በተለይ ደግሞ የመንግስት የግንባታ ዉል የሚከናወነዉ በገንዘብና ኢኮኖሚ በተዘጋጀዉ ጠቅላላ የዉል ሁኔታ (SBD) ስለሆነ የዚህን የዉል ሁኔታ ከግንባታ አፈጻጸም ዉጤታማነት አንጻር በሚከተለዉ ክፍል ይዳሰሳል፡፡

3. የመንግስት የግንባታ ዉል እና አጠቃላይ የዉል ሁኔታዎች ተስማሚነት

በኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ህግ ከቁጥር 2610-2631 እና ከቁጥር 3019-3040 ባሉት ድንጋጌዎች ዉስጥ የግንባታ ዉሎችን አመሰራረት ያስቀምጣል፡፡ በዚህ ክፍል የጠቅላላ የዉል ሁኔታዎችን አስፈላጊነት አስመልክቶ ደግሞ በፍትሐብሔር ህግ በቁጥር 1686 እና 3135 ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ጠቅላላ የሆኑ የሥራ አፈጻጸም ሁኔታዎች አስፈላጊነታቸዉም አስቀድሞ በህግ ማዕቀፎቻችን ተመልክቷል፡፡

ለአስተዳደር መሥሪያ ቤት ውሎች ተፈፃሚ የሚሆኑ ጠቅላላ ሁኔታዎች (ግዴታዎች) የውሎች አጻጻፍ በሚል አርዕስት ስር የሚከተለዉ ዓረፍተ ነገር ተቀምጧል፡-

"ሥራዎች የሚፈጸሙባቸውን አኳኋን የሚያመለክቱ ለአይነት የሆኑ ደብተሮችን (ከዩደሻርዝቲፕ) ጠቅላላ ውለታዎችንና ደንቦችን የሚመለክቱ ደብተሮችን አጠቃላይ የሆኑ ውሳኔዎች ያሉባቸውን ደብተሮች ሥራው የሆነው ኤያንዳንዱ የአስተዳደር መሥሪያ ቤት

[39] በአማርኛ ምህጻረ-ቃል ባትኮዳ ሲባል በእንግለዘኛዉ ማሳጠሪያ BaTCoDA ይባልል፡፡
[40] የኢትዮጵያ የፌዴራል መንግስት ስለግንባታ የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 430/1997 ዓ.ም እና of the Federal Public Procurement Proclamation No. 430/2005 which is repealed by Proclamation No. 649/2009, Yohannes Eneyew Ayalew, Risk Allocation Norms of Civil Construction Contracts in Ethiopia.

ሊያዘጋጃቸውና በሚኒስቴሩ ትዕዛዝ ሥራዎቹ የሚፈጸሙት በእነዚህ መሠረት ነው ተብሎ ሊወሰን ይችላል።[41]

ከዚህ ድንጋጌ የምንገነዘባቸዉ ሁለት ቁም ነገሮች አሉ። 1/ በመንግስት መስሪያ ቤት የሚደረጉ የግንባታ ዉሎች የዉሎች ጠቅላላ ሁኔታን አስፈላጊነት ይመለከታል። 2/ እያንዳንዱ የአስተዳደር መስሪያ ቤት የሚያዘጋጃቸዉ የዉል ሁኔታዎች እንደሚኖሩ ህጉ ታሳቢ ያደርጋል። ስለሆነም የዉል ሁኔታዎች ብዛት ያላቸዉና ለእያንዳንዱ ግንባታ ተስማሚ የሆነ የዉል ዓይነት ለማዘጋጀት በሚቻልበት አግባብ ሊዘጋጁ ይገባል የሚለዉን ሀሳብ ያመለክታል።

ነገር ግን አሁን በተግባር እየተሰራበት የሚገኘዉ አጠቃላይ የዉል ሁኔታ የሚያሳየዉ አንድ ዓይነትና በገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር የተዘጋጀዉ (SBD) ሰነድ ነዉ።[42] ይህ የጫራታ ሰነድ ከአዓለም ባንክ አጭር የዉል ሁኔታ የተቀዳ ስለሆነ ለትላልቅና ዉስብስብ ግንባታ አያገለግልም። ይህ ጠቅላላ የዉል ሁኔታ የሚያገለግለዉ ለግንባታ ስራ ብቻ ሳይሆን ለማማከር አገልግሎት ጭምር ነዉ። ይህ ሰነድ የሚያሳየዉ በአሰሪዉ መስሪያ ቤት አማካኝነት በሚዘጋጅና በማህንዲስ በማጸደቅ <u>የግንባታዉ ንድፍ</u> ከተዘጋጀ በኋላ በጫራታ ሂደት በፋይናንስና በቴክኒክ ብቃት አሸናፊ ከሆነ ተቋራጭ ጋር የዉል ስምምነት በማድረግ የግንባታ ሂደቱ የሚከናወን መሆኑን ነዉ። ይህ ደግሞ ባህላዊ የዉል ዓይነት (Design - bid - build) የሆነ ዓይነት ዉል እንድናዘጋጅ እንገደዳለን ወይም ሌላ አማራጭ እንዳይኖረንና የባህላዊ የዉል ዓይነት ደካማ ጎኖችን ማስቀረት እንዳንችል ይሆናል። በተጨማሪም ይህ የገንዘብና ኢኮኖሚ የጫራታ ሰነድ በራሱ የአጠቃቀም መመሪያ ላይ ለሚከተሉት የግንባታ ፕሮጀክቶች እንደማያገለግል ማብራሪያ አስቀምጧል። እነዚህም፡-

1. ዉስብስብ ለሆነ ግንባታ ማለትም ከ10 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ
2. ዲዛይናቸዉ በተቋራጮች ለሚዘጋጁ (turnkey contracts) ስራዎች ይህ የጫራታ የዉል ሁኔታ ተግባራዊ እንደማይሆን ይገልጻል።

[41] የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት የፍትሐብሔር ሕግ፣ 1952 ዓ.ም ቁጥር 3135

[42] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ለግንባታ ሥራዎች ግዥ የሚዉል መደበኛ የጨረታ ሰነድ፣ ብሔራዊ ግልጽ ጨረታ፣ የግንባታ ሥራዎች ግዥ-በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የተዘጋጀ 2006 ዓ.ም ይህ ሰነድ በአብዛኛዉ በእንግሊዘኛ ማሳጠሪያ ቃል (SBD) በሚል የሚታወቅ ስለሆነ ይህን ስያሜ በዚህ ጽሁፍ ይዞ ይቀጥላል።

በሌላ በኩል ደግሞ በፌደራል መንግስት በጀት የሚከናወኑ ግንባታዎች ይህን የጫራታ ሰነድ ተከትሎ የዉል ዓይነቱ በአስገዳጅ ሁኔታ ሊዘጋጅ እንደሚገባ በሚቀጥለዉ ዓይነት ተመላክቷል፡፡[43]

> *በጨረታው ዝርዝር መረጃ ሰንጠረዥ (ጨ.ዝ.መ.ሰ) የተጠቀሰው የመንግሥት አካል ግዥውን የሚፈጽመው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የግዥ አፈፃፀም ሕጎችና መመሪያዎች መሠረት ይሆናል፡፡ ይህ መንግሥታዊ አካል የግንባታ ሥራዎች ግዥ የመፈጸም ሥልጣንና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ በመሆኑም ይህ ግዥ የሚፈፀመው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅና የአፈፃፀም መመሪያ እንዲሁም በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሰነድ ላይ በተጠቀሰው የግዥ ዘዴ መሠረት ይሆናል፡፡[44]*

ስለሆነም የሰነዱ ይዘት ሲመረመር ባህላዊ የሆነ የዉል ዓይነት ብቻ ለማዘጋጀትና ዉስብስብ ለሆኑ ፕሮጀክቶች ዉል ለማዘጋጀት የማያገለግል ስለሆነ አጠቃላይ የመንግስት የግንባታ አፈጻጸም ላይ የሚያደርሰዉን አሉታዊ ተጽዕኖ መገመት ይቻላል፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የግንባታ መዘግየት ዋነኛ መንስኤ የሆነዉ ባህላዊ የዉል ዓይነት ነው፡፡ ለዚህም በምክንያትነት የተመላከተዉ የአሰሪዎች በግንባታ ሂደቱ ጣልቃ መግባት፣ ተገቢ ያልሆነ እቅድ መኖር፣ የገንዘብ አቅርቦት የመሳሰሉት የዉል ዝርዝር ነጥቦች ላይ አስቀድመዉ ባስቀመጡት የዉል ዓይነት የሚመራ በመሆኑ እና የባህላዊ የዉል ዓይነት ደግሞ በግንባታ ሂደቱ የሚሳተፉ የተለያዩ አካላት ሰንሰለት የያዘ በመሆኑ የእነዚህ አካላት መስተጋብር እና ዉሳኔ በግንባታዉ አፈጻጸም ላይ የራሱ የሆነ ከፍተኛ አስተዋጽዖ በመኖሩ ነዉ፡፡[45] በመሆኑም ይህን ችግር ለማስቀረት ይህ የጫራታ ሰነድ በአማራጮች ለሁሉም የፕሮጀክት ዓይነት በሚሆን መንገድ የተዘጋጀ፣ የዲዛይን ስራ ለተቋራጭ በማሰራት የግንባታ ስራን ለማሰራት የሚያስችል ሰነድ ሊሆን ይገባል፡፡

---

[43] እንዲሁም በአማራ ብሔራዊ ክልል አዋጅ ቁጥር 179 መሰረት በመንግስት ለሚሰሩ ግንባታዎች የሚያገለግሉ የዉል ሁኔታዎች ናቸዉ፡፡ ስለሆነም በክልሉ በጀት የሚከናወኑ የመንግስት ግንባታዎች ይህ ሰነድ ተፈጻሚ ነዉ፡፡

[44] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 41 ላይ የሰነዱ መግቢያ ላይ የተወሰደ ነዉ፡፡

[45] Werku Koshe, K. N. Jha. Investigating Causes of Construction Delay in Ethiopian Construction Industries Journal of Civil, Construction and Environmental Engineering Vol. 1, No. 1, 2016, pp.18-29. doi: 10.11648/j. jccee.20160101.13

በኢትዮጵያ በግንባታዉ ዘርፍ ችግሮች ላይ ጥናት ያደረጉ ባለሙያዎች የሚያረጋግጡት አብዛኛዉን ጊዜ የግንባታ ፕሮጀክቶች መጀመሪያ በተያዘላቸዉ ፕላን መሰረት አይፈጸሙም።[46] በተለይም የግንባታ መዘግየት፣ የዋጋ መጨመር፣ የጥራት ችግር በከፍተኛ ሁኔታ ይስተዋላል። ይህ ችግር በመንግስት የሚከናወኑ የግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ በእጥፍ ይጨምራል። ይህ ደግሞ የግንባታ ዉል አስተዳደር ችግር እንደሆነ ይገለጻል።[47] የግንባታ ዉል አስተዳደር ችግር ደግሞ ተስማሚ የዉል ዓይነት በማዘጋጀት ሊቀረፍ የሚችል ችግር ነዉ። ስለሆነም የግንባታ ዉል ለማዘጋጀትና ተስማሚዉን የዉል ዓይነት ለመምረጥ የሚያስችል አጠቃላይ የዉል ሁኔታ ሊዘጋጅ ይገባል። በተለይ ደግሞ ይህ የዉል ሁኔታ የተለዩ አማራጮች ያሉትን እንደየ ፕሮጀክቱ ዓይነትና ባህሪ ተጠንቶ የተዘጋጀ ሊሆን ይገባል። ለአብነትም የFIDIC የዉል ሁኔታዎችን ስናይ በተደጋጋሚ ጊዜ እየተፈተሹ የተሻሻሉ እና በተለያዩ አማራጮች የተዘጋጁ ጊዜዉን የዋጀ የግንባታ ዉል ለማዘጋጀት የሚያስችሉ ናቸዉ።[48]

የኢትዮጵያ የግንባታ ኢንዱስትሪ መገለጫ በመሆን የሚጠቀሰዉ የፕላን እና የግንባታ ስራዎች በተለያዩ ደረጃዎች (fragmentedly) የሚፈጸሙ መሆኑ ነዉ። በሌላ አገላለጽ በኢትዮጵያ የግንባታ ኢንዱስትሪ የተለመደዉ የዉል ዓይነት ባህላዊ የሆነዉ ፕላን-ጫራታ-ግንባታ (Design-Bid-build) ወይም በእንግሊዘኛዉ ማሳጠሪያ ቃል DBB ሲሆን ይህም በአጠቃላይ የፕሮጀክት አፈጻጸሙ ላይ ለተለያዩ ክርክሮች የሚዳርግ እና በዉጤትም ደረጃ በዋጋ፣ በጊዜ እና ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር ነዉ።[49] በተለይ ደግሞ በመንግስት የሚፈጸሙት የግንባታ ስራዎች በመንግስት የግዥ መመሪያ የሚከናወን ከመሆኑ አኳያ ሲታይ በግንባታ ሂደት ላይ የሚያጋጥሙ አደጋዎች በአግባቡ ለግንባታ ተዋንያን ለማከፋፈል አመች አይደለም። የዋጋ ግሽበትን፣ የተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰዉ ሰራሽ የሆኑ ሊገመቱ የማይችሉ አደጋዎች በማስተዳደር በግንባታ ሂደቱ ላይ ተጽዕኖ እንዳያደርስ በሚያደርግ መልኩ የዉል ዓይነት ለማዘጋጀት አመች አይደለም።[50]

---

[46] ዝኒ ከማሁ

[47] ዝኒ ከማሁ

[48] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 26

[49] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 13

[50] Wubishet Jekale (2005). Development of Construction Industry in Ethiopia EACE Journal, Vol. 4, No. 1, Addis Ababa

በመንግስት የሚከናወን ግንባታ ላይ የሚሳተፉ አካላት ብዛት ያላቸዉ የመንግስት ተቀጣሪዎች እና ተቋራጭን ጨምሮ በተለያዩ ሀላፊነት የሚወከሉ የባለድርሻ አካላት ሰንሰለት የያዘ የዉል ዓይነት ነዉ። በተለይ ደግሞ በመንግስት በኩል የሚወከሉት የአሰሪ መስሪያ ቤት ሀላፊዎች በአብዛኛዉ የፖለቲካ ተሿሚ ስለሆኑ የሚያስተላልፉት ዉሳኔ ከግንባታ ስራ ጋር ተዛምዶ ላይኖረዉ ይችላል። በግንባታ ሙያ መሰረት ተግባብቶ ለመስራት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም የባህላዊ የዉል ዓይነት በባህሪዉ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ሰንሰለት የሚሳተፉበት እና ለክርክር ክፍት የሆነ (adversarial in its performance) ስለሆነ የግንባታ አፈጻጸሙ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ አይቀርም። ለአብነት የሚከተለዉ የግንባታ ዉል አስተዳደር ሂደት ጠቃሚ ነዉ።

"የማኔጅመንት ስብሰባዎች፦ መሐንዲሱ ወይም የሥራ ተቋራጩ ከሁለቱ አንዳቸው በውሉ ውስጥ የተከናወኑ የግንባታ ሥራዎችን አስመልክቶ የግዥ ፈጻሚ አካልን የእርካታ ደረጃ በመወያየት፣ የቀሪ ሥራዎች ዕቅዶችን በመገምገም እና ቅሬታ ያለባቸውን ነጥቦች ለመፍታት የሚያስችል እርምጃዎች ላይ በመስማማት መደበኛ የማኔጅመንት ስብሰባ ላይ እንዲገኝ ሊደረግ ይችላል። የሥራ ተቋራጩ እንደእነዚህ አይነት አስፈላጊ እርምጃዎችን ሊያደናቅፍ ወይም ስምምነቱን ሊያዘገይ ወይም ሊነፍግ አይችልም። እንደእነዚህ አይነት ስብሰባዎች በሁለቱም ማለትም በግዥ ፈፃሚ አካልና በሥራ ተቋራጩ በኩል ሕጋዊ ሥልጣን ያላቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሠራተኞች እና ሌሎች አስፈላጊ ተሳታፊዎች መገኘት አለባቸው። እንደዚህ አይነት ግምገማዎች ተዋዋይ ወገኖች በቋሚ አጀንዳ መስማማት አለባቸው። መሐንዲሱ የማኔጅመንት ስብሰባ ነጥቦች መመዝገብና የመዘገበውን ግልባጭ ለተሳታፊዎች እና ግዥ ፈፃሚ አካል መስጠት ይኖርበታል። በሚወሰዱ እርምጃዎች ላይ የተዋዋይ ወገኖች ያለባቸውን ኃላፊነት መሐንዲሱ በማኔጅመንት ስብሰባው ጊዜ ወይም ከስብሰባው በኋላ መወሰን ይገባዋል። ውሳኔውንም ለስብሰባው ተሳታፊዎች በሙሉ በጽሑፍ ይገልጻል።"[51]

ከላይ በSBD ሰነድ በምዕራፍ 3 ክፍል 7 አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ የተቀመጠዉ የዉል አስተዳደር ሲታይ የግንባታዉን አጠቃላይ እንቅስቃሴ በመንግስት መስሪያ ቤት የማኔጅመንት ሂደት እንዲያልፍ የሚያደርግ ነዉ። ይህ ደግሞ ከመንግስት መስሪያ ቤት ባህሪ ጋር ተደምሮ የግንባታ ዉል አስተዳደር ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ የሆነ አስተዋጽዖ አለዉ። ይህን ክፍተት መሸፈን የሚቻለዉ ደግሞ ተስማሚ የሆነ የዉል ዓይነት አስቀድሞ በማዘጋጀት ነዉ። ነገር ግን ይህን የዉል ዓይነት ለማዘጋጀት የሚያስችሉ ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች በአማራጭ አለመቅረባቸዉና ክፍተት መኖሩ በግንባታ አፈጻጸም ላይ እንዲሁም በዋጋ፣ በጊዜ እና በጥራት ላይ ራሱን የቻለ አስተዋጽዖ ያሳድራል።

[51] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 41 በምዕራፍ 3 ክፍል 7 አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ላይ ይመልከቱ።

ማጠቃለያ

አንድን ግንባታ በተያዘለት ዋጋ፣ ጊዜ እና ጥራት ማከናወን ዉጤታማ የግንባታ አፈጻጸም መኖሩን ለመለካት የሚያስችሉ አመልካች መስፈርቶች (Indicators) ናቸዉ። ስለሆነም ማንኛዉንም ግንባታ የሚያከናዉኑ አካላት የመጨረሻ ግብ በእነዚህ መስፈርቶች መሰረት ግንባታዉን ማከናወን ነዉ። ይህን ለማሳካት ደግሞ አስቀድሞ በእቅድ፣ በሰዉ ሀብት፣ በበጀት እና የመሳሰሉት አቅሞች ላይ መደራጀት ይጠይቃል። ይህ ደግሞ ከግንባታ ዉል አስተዳደር ጀምሮ ተስማሚ የዉል ዓይነትን መምረጥን ያካትታል። ተስማሚ የዉል ዓይነት በግንባታ አፈጻጸም ላይ የሚኖረዉን አሉታዊ ተጽዕኖ ለማየት አጠቃላይ የዉል አመሰራረት ስርዓት ይኸዉም ሀላፊነትን፣ የተሳታፊዎችን ግንኙነት አጠቃላይ የግንባታዉን ይዘትና ተፈጥሮ ያሳያል። ከዚህ በመነሳት የግንባታ ባለሙያዎች እንደሚገልጹት የግንባታ ዉል አመሰራረት ስርዓት የግንባታዉ ዉጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መኖሩን ነዉ። ይህ ስርዓት የተዋዋይ ወገኖችን ስምምነት፣ የተመረጠዉን ዲዛይን፣ ጊዜ፣ ዋጋና ሌሎችን ሁኔታዎች የሚመለከት ስለሆነ የግንባታዉ አፈጻጸም ወሳኝ ምዕራፍ ነዉ። የግንባታዉን ዉጤታማነት ከሚወስኑት ጉዳዮች መካከል አንደኛዉ የግንባታ ውል ዓይነት ነዉ።

ዉሉ የግንባታ አስተዳደር አካል ተደርጎ የሚወሰድ እና አስተዳደሩን ስለሚወስን በግንባታ አፈጻጸሙ ላይ ያለዉን ሚና መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም ተስማሚ የዉል ዓይነት በተገቢዉ ሁኔታ በመመዘን ማዘጋጀት በግንባታ አፈጻጸሙ ሙጤታማነት ላይ ቁልፍ ጉዳይ ነዉ። የዉል ዓይነት የሚለዉ ቃል እንደአግባብነቱ ስራ ላይ የሚዉል ቃል ስለሆነ በዚህ ጽሁፍ የዉል ዓይነት የሚመለከተዉ ፕሮጀክቱ የሚከናወንበትን ሂደት (project delivery system) የሚመለከት ነዉ። በዚህ መሰረት አሁን በስራ ላይ ሶስት ዓይነት የዉል ዓይነቶች አሉን። እነዚህም ባህላዊ የዉል ዓይነት (Design-bid-bulid)፣ የተቀናጀ የዉል ዓይነት (design-bulid) እና የግንባታ አስተዳደር ዉል (Construction management contract) ናቸዉ። እነዚህ የዉል ዓይነቶች የራሳቸዉ ጥንካሬ እንዲሁም ደካማ ጎን አላቸዉ። ስለሆነም ከእነዚህ የዉል ዓይነቶች መካከል ለመምረጥ መመዘኛ መስፈርቶች አሉን። ተስማሚ የዉል ዓይነት ለመምረጥ ከግምት ዉስጥ የሚገቡ መስፈርቶች፡- ጊዜ፣ ለተጨማሪ ስራ የማይዳርግ፣ አደጋዎች የሚከፋፈሉበት ሁኔታን፣ የስራዉን ዉስብስብነት ከግምት ዉስጥ በማስገባት ነዉ። ስለሆነም ተስማሚ የዉል ዓይነት በግንባታ አፈጻጸሙ ላይ ያለዉን ሚና በመገንዘብ በእነዚህ መስፈርቶች መሰረት የተሻለዉን የዉል ዓይነት መምርጥ አስፈላጊ ይሆናል።

የግንባታ ዉሉን ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች (Standared condition of contract) አስፈላጊ ናቸዉ። የዉል ሁኔታዎች አለም አቀፍና ሀገራዊ የዉል ሁኔታዎች በመባል ሊመደቡ ይችላሉ። እነዚህ የዉል ሁኔታዎች የረጅም ጊዜ ልምድ ባላቸዉ ባለሙያዎች የተዘጋጁ ስለሆነ የዉሉን ይዘት ግልጽ በማድረግ የዉል ባለድርሻ አካላት ሀላፊነትን እና በግንባታ ወቅት የሚከሰቱ አደጋዎችን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ በማከፋፈል አስፈላጊነታቸዉ ይጎላል። እነዚህ የዉል ሁኔታዎች አስቀድመዉ ሲዘጋጁ እንደግንባታዉ ባህሪ የተለያየ ቅርጽ (Format) ሊኖራቸዉ ይገባል። ይህም ከግንባታ አፈጻጸም ሂደት (Project delivery system) ጋር የተጣጣሙ በአማራጭ የቀረቡ ሊሆኑ ይገባል። ለአብነት የFIDIC የዉል ሁኔታዎችን መመልከት ጠቃሚ ነዉ።

ወደ ኢትዮጵያ አጠቃላይ የዉል ሁኔታዎች ስንመጣ በግለሰቦች መካከል ለሚዘጋጁ የግንባታ ዉሎች የሚያገለግሉ አጠቃላይ ሁኔታዎች በቀድሞዉ ስራና ከተማ ልማት የተዘጋጀ ሰነድ ሲኖር ለመንግስት የግንባታ ዉሎች ደግሞ በገንዘብና ኢኮኖሚ የተዘጋጀ የዉል ዓይነት አለ። የዚህ ጽሁፍም ዓላማ የመንግስት የግንባት ሂደትና አጠቃላይ የዉል ሁኔታን ተስማሚነት መገምገም ነዉ። በዚህ መሰረትም በገንዘብና ኢከኖሚ ተዘጋጅቶ በስራ ላይ ያለዉ የግንባታ የጫራታ ሰነድ ይዘት ሲታይ የመንግስትን የግንባታ ሂደት (Project delivery system) አማራጭ ያሳጣና ባህላዊ የዉል ዓይነት ብቻ ለማዘጋጀት የሚያስችል ነዉ። ይህ ደግሞ በግንባታ አፈጻጸም ላይ በባህሪዉ ለክርክር የሚዳርግ እንዲሁም ብዙ ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ስለሆነ በዉል አስተዳደሩ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም የገንዘብና ኢኮኖሚ የጫራታ ሰነድ በአማራጮች የተዘጋጀ እና እንደየ ፕሮጀክት ዓይነትና ባህሪ የተለያዩ ሊሆኑ እንደሚገባ በ1960 ዓ.ም የወጣዉ የፍትሐብሄር ህግ ያስገነዝባል። ነገር ግን የሀገራችን የመንግስት የግንባታ ሂደት (Project delivery system) ባህላዊ የሆነ እንዲሁም ከመንግስት መስሪያ ቤት ተፈጥሯዊ ባህሪ ጋር ተደምሮ ለግንባታ አፈጻጸም ጉድለት የሚዳርግ አሰራር ነዉ።

ስለሆነም የመንግስት የግንባታ ፕሮጀክት አሰራርን ለማሻሻል አስፈላጊ ከሆነ የግንባታ ሂደቱን (Project delivery system) በአማራጮች የተዘጋጀና እንደየ ፕሮጀክት ባህሪዉ ተስማሚ ዉል ለማዘጋጀት የሚያስችል አሰራር መዘርጋት ያስፈልጋል። ይህን ለማድረግ ደግሞ በቀድሞዉ ገንዘብና ኢኮኖሚ የተዘጋጀዉ የግንባታ የጫራታ ሰነድ (PPA) በአግባቡ ተፈትሾ ጠቅላላ የዉል ሁኔታዎችም በዚሁ አግባብ በአማራጭ ሊዘጋጁ ይገባል።